ተስፋ ዐቃብያን ክርስትና ማኅበር

የሚከተሉትን መጻሕፍት ገዝተው እንዲያነቡ ያበረታታል

1. የይሖዋ ምስክሮችና አስተምህሮአቸው በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን—ከተስፋዬ ርበሌ
2. የሥነ ምግባር መርሖ—ከተስፋዬ ርበሌ
3. ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር—ርእሰ ጉዳዮችና ተግዳሮቶች —ከምኒልክ አስፋው
4. ዐበይት መናፍቃን—ከተስፋዬ ርበሌ
5. ሰባልዮሳውያን:—"የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" የሥላሴ አስተምህሮ በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን (ቅጽ 1)—ከተስፋዬ ርበሌ
6. ውሃውና ስሙ:—"የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" የድነት አስተምህሮ በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን (ቅጽ 2)—ከተስፋዬ ርበሌ
7. ቅድስት ሥላሴ:—የአስተምህሮተ ሥላሴ መጽሐፍ ቅዱሳዊ፣ ታሪካዊና ሥነ አመክንዮአዊ ትንታኔ —ከአማረ መስፍንና ከተስፋዬ ርበሌ
8. የዳ ቪንቺ ኮድ:—ድርሳነ ጠቢብ ወይስ ድርሳነ ባልቴት? —ከተስፋዬ ርበሌ
9. በውኑ እግዚአብሔር አለን? ፍልስፍናዊ ጥናት —ከሪቻርድ ስዊንበርን (ፕሮፌሰር)
10. ይድረስ ለሐያስያን—ብውኑ መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በርሱ ይቃረናልን?—ከተስፋዬ ርበሌና ከአማረ መስፍን
11. የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያንና ትምህርተ ሥላሴ—ከተስፋዬ ርበሌ
12. በቅዱሳት መጻሕፍት ዘገባ በርግጥ ኢየሱስ ክርስቶስ ማነው? —ከተስፋዬ ርበሌ
13. የአስተምህሮተ ሥላሴ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት—ከተስፋዬ ርበሌ
14. በእምነት መኖር—ከተስፋዬ ርበሌ
15. እግዚአብሔርን በተመለከተ ልጆች የሚጠይቋቸው 101 ጥያቄዎች—ከተስፋዬ ርበሌ
16. መጽሐፍ ቅዱስን በተመለከተ ልጆች የሚጠይቋቸው 102 ጥያቄዎች—ከተስፋዬ ርበሌ
17. ትክክልና ስሕተትን በተመለከተ ልጆች የሚጠይቋቸው 103 ጥያቄዎች—ከተስፋዬ ርበሌ

የሺህ ዓመት ጐረቤታሞች

ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች

ዴቪድ ደብሊው ሼንክ

የሺህ ዓመት ጐረቤታሞች

ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች

ዴቪድ ደብሊው ሼንክ

ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር
የመልእክት ሣጥን ቁጥር 23045፣ ኮድ 1000
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

የሺህ ዓመት ጉረቤታሞች—ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች
—ዴቪድ ደብሊው ሼንክ
ተርጓሚና አሳታሚ—ተስፋ ወንጌልያን ክርስትና ማኅበር
መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው © 2000 ዓ.ም

ያለ አሳታሚው ፈቃድ አባዝቶ ማሳተምም ሆነ የተወሰነን ክፍል በተለያዩ መንገዶች ማሪባት/ማባዛት በጥብቅ የተከለከለ ነው። በማንኛውም መልኩ መረጃ ለመውሰድ ከተፈለገ፣ በትክክል ሥርዐቱን ጠብቆ ሲጠቀስ፣ በግርጌ ማስታወሻ ሲመሳከት ይገባዋል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት የኢትዮጵያ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በኹሊያን የዘመን አቈጣጠር በ1954 ዓ.ም ካሳተመው መጽሐፍ ቅዱስ ትርጒም እንዲሁም የኢንተርናሽናል የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በኹሊያን የዘመን አቈጣጠር በ1993 ዓ.ም ካሳተመው የአዲሱ መደበኛ ትርጒም ነው። የቁርአን ጥቅሶች የተወሰዱት፣ ሸኽ ሰይድ ሙሐመድ ሳዲቅና ሐጂ ሙሐመድ ሳኒ ሐቢብ ወደ አማርኛ ተርጒመውት ነጃሺ አሳታሚ ድርጅት በኹሊያን የዘመን አቈጣጠር 1961 ዓ.ም እንዲሁም ወርኀ ሚያዝያ 1997 ዓ.ም ካሳተመው የቁርአን ቅጅ ነው።

በእንግሊዝኛው ቅጅ ላይ የሴሱ አንዳንድ አስፈላጊ መረጃዎችን በግርጌ ማስታወሻ ላይ አቅርበናል። ዕዩ መግለጫ ካልቀረበ በስተቀር፣ የተከተልነው የጉርጉሮሳውያኑን የዘመን አቈጣጠር ነው።

መጽሐፉን ማግኘት የሚፈልጉ ከሆነ ወይም በርእሰ ጒዳዩ ላይ ጥያቄ፣ አስተያየትም ሆነ ሒስ ካልዎ በሚከተለው አድራሻ ይጻፉ:—

ተስፋ ወንጌልያን ክርስትና ማኅበር
የመልእክት ሣጥን ቍጥር 23045፣ ኮድ 1000
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

Journeys of the Muslim Nation and the Christian Church: Exploring the Mission of Two Communities

Author—David W. Shenk
Translator and Publisher —TESFA Evangelical Society For Apologetics
Copyright © 2007—TESFA Evangelical Society For Apologetics

All rights reserved. No part of this publication may be reproduced, stored in a retrieval system, or transmitted in any form or by any means-electronic, mechanical, photocopying, or other wise-without the prior written permission of the publisher and copyright owner.

If you need the book write us in our address. Comments, questions, corrections, and criticisms of this book are welcome. Please address all correspondence to the publisher on the following address:

The Evangelical Society For Apologetics (TESFA)
Post Office Box 23045, Code 1000
Addis Ababa, Ethiopia.
E-mails: <apologetics@ethionet.et>, <tesfa_apologetics@yahoo.com>

Dedication

In loving memory of our beloved brother and co-labourer,

Rev. Luke Paul Wilson

Who is away from the body
and at home with the Lord
(Corinthians 5:8)

Acknowledgments

THERE ARE MANY WHO HAVE GIVEN BOTH THEIR encouragement and support to this work. We would especially like to thank the following persons and institutions, all of whom contributed to making this book not only possible but actual.

We wish to earnestly express our gratitude for to our friend and fellow worker the late Rev. Luke P. Wilson. He supported the idea to translate this material into the Amharic language and approached Dr. David Shenk and led him to our office. We would like to give thanks to the staff and board of the Institute for Religious Research, the organization which Rev. Wilson directed for their constant encouragement and generosity. We are grateful beyond words.

We would like to give special thanks to Dr. David W. Shenk, Tobias Messner and Waldemar Pritzkau for helping us in so many ways.

We are grateful to Professor Eleonore Stump, Mr. Paul Carden, and Dr. Brian Holt for sharing our passion for this ministry. We are also grateful to the translators, editors, pagemakers, and cover designers. We thank our members who critically read the book manuscript prior to publication.

It is our sincerest hope that this book will glorify God, and, instruct and edify the people of God. May God be pleased to use this book to those ends, and may He richly bless you as you read the fruits of our labour.

ማውጫ

መቅድም 1

1. ምዕራፍ አንድ—የተለያዩ ጉዞዎች 15
2. ምዕራፍ ሁለት—ወረባዊ ጅማሬ 41
3. ምዕራፍ ሦስት—በኤድን ገነት 57
4. ምዕራፍ አራት—የአብርሃም ልጆች—እስማኤልና ይስሐቅ 74
5. ምዕራፍ አምስት—መሪዎች—የነቢያት መደምደሚያና መሲሑ 91
6. ምዕራፍ ስድስት—ቅዱሳት መጻሕፍት—ቀርአንና መጽሐፍ ቅዱስ 115
7. ምዕራፍ ሰባት—መገለጥ—ታንዚልና ተሰገሞ 141
8. ምዕራፍ ስምንት—ጎይል—ሒድራና መስቀል 163
9. ምዕራፍ ዘጠኝ—ቅድስቲቱ ከተማ—መዲናና ኢየሩሳሌም 181
10. ምዕራፍ ዐሥር—አሐዱ አምላክ—ተውሂድና ሥላሴ 203
11. ምዕራፍ ዐሥር አንድ—ሃይማኖታዊ ጉዞ—ሃጂና የገታ ሬት 223
12. ምዕራፍ ዐሥራ ሁለት—ሁለት መንገዶች—ጽሪአና መንፈስ ቅዱስ 241
13. ምዕራፍ ዐሥራ ሦስት—ጸሎት—ሰላት—ጎበረት 263
14. ምዕራፍ ዐሥራ አራት—ምድራዊ ተልእኮ—አማና በተ ኮርስተያን 281
15. ምዕራፍ ዐሥራ አምስት—ማጠቃለያ ሐሳብ—303
16. ሙጻዋ ቃላት—305

ዋቢ መጻሕፍት—ከአጫጭር ማብራሪያዎች ጋር 317

መቅድም

ከሙስሊሙ ማኅበረሰብ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ የተዋወቅሁት ሶማሊያ በኖርሁባቸው ዓመታት ነው። አብዛኛው ሕዝቧ ግመል እያረባ በሚኖርባት በዚህች ሙስሊም አገር፣ ከጉርጉሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር 1963 ዓ.ም ጀምሮ ለዐሥር ተከታታይ ዓመት ኖሬያለሁ። ወደዚህች አገር የላከንም፣ ምሥራች ሚኖናይት ሚስዮን ነበር። ወደ ሶማሊያ ከመሄዴ በፊት ዕድገቴ በታንጋኒካ (በታንዛኒያ) ሲሆን፣ ከዚያ በኋላ በአሜሪካን አገር ዐሥር ዓመት ተቀምጫለሁ።

ከባለቤቴ ግሬስና ከሁለቱ ሴት ልጆቼ (ከሁለት ዓመቷ ካረንና ከሁለት ወር ጨቅላ ሕፃኗ ዶሪስ) ጋር በመሆን፣ ሞቃዲሾ አውሮፕላን ማረፊያ ስንደርስ የሰማሁት ጩኸት፣ ከዚህ በፊት ከማውቀው ፍጹም የተለየ ነበር። ከዚያ በፊት በዚህ መልኩ የእግዚአብሔርን ስም የሚገልጹ ንግግሮች የሚሰሙት በአብዛኛው በአምልኮ ቦታዎች እንዲሁም ዐልፎ ዐልፎ፣ ጸያፍ በሆኑ ንግግሮች ውስጥ ነው።

ምንም እንኳ ሥራችንን የምንሠራው በሶማሊያ ሜኖናይት ሚስዮን የትምህርት ፕሮግራም ውስጥ ቢሆንም፣ በዐሥር ዓመት ቆይታችን ያስተዋልነው ነገር ቢኖር፣ የሶማሊያ ማኅበረሰብ የእግዚአብሔር ጉዳይ እጅግ ገድ እንደሚለው ነው። የሶማሊያውያኑ ሕይወት የተሞላው፣ ስለእግዚአብሔር መናገርና እግዚአብሔርን ማወቅ በሚሉት ርእሰ ጉዳዮች ነው። እስልምና በሶማሊያውያን ሕይወትና ባህል ውስጥ ትልቅ ቦታ አለው።

የእምነትን ጉዳይ በተመለከተ ከሶማሊያውያን ጓደኞቼ ጋር በየሻይ መጠጫ ስፍራም ሆነ በየቤታችን ውስጥ፣ በርፍልና በኢል የተቀመመውን ሻያችንን ፉት እያልን ለረጅም ሰዓት እንወያያለን።

እንደ ጉርጉሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር 1973 ዓ.ም የግርክሰዊው አብዮት ከአገር ሲያስወጣን፣ መቀመጫችንን ያደረግነው፣ የሶማሊያ ደቡባዊ ጉረቤት አገር በሆነችው በኬንያ ነበር። በዚህ ጊዜ ከሙስሊሙ ማኅበረሰብ ርቀን መኖር ስላልፈለግን ነበር፣ መኖሪያችንን በናይሮቢ ምሥራቃዊ ክፍል ያደረግነው። ከምንኖርበት ቤት ፊት ለፊት ካለው መንገድ ባሻገር ቃድርያ ሱፊ የሚባል መስጊድ ነበር። በቤታችን ውስጥም ከሙስሊሞችና ቍልፍ ከሚባሉ የሃይማኖቱ

መሪዎች ጋር ውይይት እናካሂድ ነበር። በእንዲህ ዐይነቱ ውይይት ጊዜም፣ የቤታችንን ወንበሮች ሁሉ አውጥተን ምንጣፍ በማንጠፍ፣ ክብ ሠርተን ምንጣፉ ላይ በመቀመጥ ሻያችንን እየጠጣን ስለአምላክ፣ ስለእምነት፣ ስለእውነት፣ ስለቁርአን፣ ስለመሐመድ፣ ስለክርስቶስ እንዲሁም ስለድነት እንወያያለን።

በኬንያ ቆይታዬ፣ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ሲገናኙ ለውይይት የሚያነሡአቸው የነገረ መለኮት ርእሰ ጉዳዮች፣ ለነገረ መለኮት ያለኝን ፍላጎት አሳድጎታል። በሙስሊሙ ማኅበረሰብ መካከል በመኖር የምሰጠውን የፍቅር አገልግሎትና ምስክርነት በክርስቲያኖችና በሙስሊሞች መካከል ያለውን ልዩነት በመጠኑም ቢሆን ሊቀንሰው እንዲሁም ያለመተማመኑንም ሊያረግብ አልቻለም። "የሙስሊም ክርስቲያን ግንኙነት በአፍሪካ ኘሮጀክት" (Program for Christian-Muslim Relation in Africa [Procmura]) በመባል የሚታወቀው ድርጅት፣ በሙስሊሞች መካከል ከሌሎች መሰል ክርስቲያኖች ጋር በታማኝነትና በጥምረት እንድንሠራ መልካም የሆነን አጋጣሚ ፈጥሮልኛል። እኔም ከኘሮክሙራ (Procmura) ቡድን ጋር በመሆን ለሙስሊሞች ወንጌል ለሚመሠክሩና ውይይት ለሚያደርጉ አገልጋዮችና መሪዎች ሥልጠና እሰጣለሁ፤ በዐውደ ጥናቶችም ላይ አስተምራለሁ።

ከእኔ ጋር የሚሠራውም ቡድን እስላማዊ በሆነው ንጽርአተ ዓለም ውስጥ ሙስሊሞች ክርስቲያኖችን አስመልክቶ ያላቸውን የተሳሳተ ግንዛቤና ተቃውሞ ሊያስወግድ የሚችል፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶችን እናዘጋጃለን። የሚዘጋጀው የትምህርት ርእስ፣ "የእግዚአብሔር ሕዝብ" የሚባል ሲሆን፣ አርባ በሚሆኑ ቋንቋዎችም ይተረጐማሉ፤ በየዓመቱም በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች በዚህ ተከታታይ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ውስጥ ይካፈላሉ።

በድሩ ዲ. ቀትራጋ ከተባለው ሙስሊም ጓደኛዬ ጋር ለረጅም ጊዜያት ያካሄድነው ውይይት፣ ከሙስሊሞች ጋር የሚደረገውን ውይይት በተመለከተ ትልቅ ለውጥ አምጥቶአል። እኔና በድሩ በዩኒቨርስቲ ኦፍ ናይሮቢ እንዲሁም በኬንያታ ኮሌጅ ስለ ዓለም ሃይማኖቶች እናስተምር ነበር። ትምህርቱን በጎበረት በምናስተምርበትም ወቅት፣ በተማሪዎቹ ፊት ሃይማኖትን በተመለከተ እንወያይና እንከራከር ነበር። ተማሪዎቻችንም በእንዲህ ዐይነቱ ውይይት ደስተኞች ከመሆናቸውም በላይ፣ ውይይቶቹ የሕይወታቸውን ጥያቄዎች የሚዳስሱ ነበሩ።

በትምህርቱ ክፍለ ጊዜ እናካሂዳቸው የነበሩ ውይይቶች በእኔና በበድሩ መካከል መተማመንን ስለፈጠሩ፣ ውይይቱ በመጽሐፍ መልክ እንዲዘጋጅ ተስማማን። ይህም፣ "የሙስሊሞችና የክርስቲያኖች ውይይት" (A Muslim and a Christian in Dialogue) የተሰኘውን መጽሐፍ እንድንጽፍና ብዙዎችን እንድንደርስ ረድቶናል። እኔና በድሩ ባልንጀሮች ነን። ስለ እግዚአብሔር ያለን መረዳት የተመሠረተው በየራሳችን የእምነት አስተምህሮ ላይ ቢሆንም፣ የእኔም ሆነ የባልንጀራዬ የእምነት መሠረት እግዚአብሔር ነው።

እንደ ጉርጉሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር በ1979 ዓ.ም እኔና ቤተሰቤ ወደ አሜሪካን አገር ብንመለስም፣ ከሙስሊሞች ጋር የነበረኝ ውይይት አልተቋረጠም። በዓመት ውስጥ ለብዙ ተደጋጋሚ ጊዜያት በየምሽቱ እኔና ክርስቲያን ባልንጀሮቼ መስጊድ ሄደን፣ በተነጠፈው ምንጣፍ ላይ በመቀመጥ ወደ ስፍራው እንድንመጣ የጋበዙንን ሙስሊሞች እናደምጣለን። ሁኔታው አመቺ ሆኖ ሲገኝ፣ የመሲሑ ደቀ መዛሙርት እንደ መሆናችን መጠን፣ በመሲሑ ላይ ያለንን እምነት እናካፍላቸዋለን።

ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ፣ ከሙስሊሞች ጋር ያደረግኋቸው አንዳንድ ውይይቶች፣ በሕይወቴ ውስጥ ትልቅ ቦታ ያላቸው ናቸው። ቶሮንቶ የሚገኘው የሙስሊም መረጃ ማዕከል ዳይሬክተር ከሆነው ከሻቢር ዓሊ ጋር በእንግሊዝ አገር ያደረግናቸው ስድስት ተከታታይ ውይይቶች፣ ከእነዚህ ከሥተቶች መካከል አንዱ ነው። ይህንን ውይይት በገንዘብ የረዳው መቀመጫውን እንግሊዝ አገር ያደረገውና "በእንግሊዝ አገር የሙስሊም ተማሪዎች ጎብረት" በመባል የሚታወቀው ማኅበር ሲሆን፣ ውይይቶቹ የተካሄዱት እንደ ጉርጉሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር በወርኀ መስከረም 2000 ዓ.ም ነው። እነዚህ ውይይቶች የተካሄዱት በአምስት ዩኒቨርስቲዎችና በማዕከላዊ ለንደን መስጊድ ውስጥ ነበር።

ይህ የሦስት ሰዓት የውይይት ጊዜ ትኵረት ያደረገው፣ መሠረታዊ በሚባሉት የሙስሊሞችና የክርስቲያኖች አስተምህሮ ላይ ነው፤ ይኸውም መገለጥ፣

መሲሕ፣ በግሪክ ክርስቶስ ለሚለው ሴማዊ ቃል አቻ ትርጕም ነው። መሲሕ የሚለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል ትርጕሙ፣ "የተቀባ ማለት ነው"። ቁርአን ኢየሱስ የተቀባ መሲሕ መሆኑን ስለሚቀበል፣ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ መሲሕ የሚለውን ሴማዊ ስያሜ ተጠቅመናል።

እግዚአብሔር፣ ድነት፣ ኢየሱስ፣ መስቀል፣ ትንሣኤ፣ አብርሃም እንዲሁም ሙስሊሞች በክርስቲያኖች ላይ ባላቸው አመለካከት፣ በእንጻሩም ክርስቲያኖች በሙስሊሞች ላይ ያላቸውን በተመለከተ ነበር:: ከሙስሊሞቹ በኩል በስፋት የተንጸባረቀው የሱኒ ሙስሊሞች አስተምህሮ ነበር::

2002 ዓ.ም በበልግ ወራት ጀርመን አገር በ(Theologische Studientage Der AMG) ጋባዥነት በተካሄደው ዐውደ ጥናት የሚስ ሐሚደህ ሞሐገጊ የውይይት አጋር በመሆን መመረጤ አስደንቆኛል:: ከሙስሊሞች ወገን ደግሞ የእስልምናን አስተምህሮ ዘመናዊ ለማድረግ ፍላጎት የነበረው ኢራናዊ ሺአ ነበር:: አራት ቀናት የፈጀው የአናባፕቲስቶች—ሜኖናይት ዐውደ ጥናት ጥልቅ የሆኑ የነገረ መለኮት ርእሰ ጉዳዮች የተነሡበትና መከባበር የሰፈነበት በመሆኑ በተለምዶ በሙስሊሞችና በክርስቲያኖች መካከል ከሚደረጉ ግንኙነቶች ያልተለመደ ገጽታ ነበረው::

የዚህ ውይይት አቻ የሆነውን በጀርመን በሺአ ሙስሊም አስተምህሮና በሜኖናይት ክርስቲያን መካከል የተደረገው ውይይት አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ሁሉ ዕገዛ ያደረጉት፣ በኢራን "ቆም" በምትባል ከተማ የሚገኘው "የኢማም ሆሜይኒ የትምህርትና የምርምር ተቋም" እንዲሁም ካናዳ ቶሮንቶ ያለው "የቶሮንቶ ሜኖናይት የነገረ መለኮት ማዕከል" "ከሜኖናይት ማዕከላዊ ኮሚቴ" ጋር በመተባበር ነበር:: ይህ ውይይት የጐለበተው እነዚህ ሦስት ድርጅቶች በቆምና በቶሮንቶ ለብዙ ዓመታት ካካሄዱት ውይይት ነው:: የውይይቱ ርእስ ዘመናዊነት የሚል ነበር:: የኢራን ሙስሊሞችንም ሆነ የሰሜን አሜሪካ ሜኖናይቶችን የዘመናዊነት ተግዳሮቶች ክፉኛ እየተፈታተኗቸው ነው:: ኢራናውያን፣ "የእስልምናን ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ፋይዳዎች ዘመናዊ በሆነው ሥርዐት ውስጥ እንዴት ጠብቆ መቆየት ይቻላል?" የሚለው ጉዳይ ያሳስባቸዋል:: እነዚህ አከራካሪ ጉዳዮች ኢራን ውስጥ በዲሞክራሲ አራማጅ የተማሪ እንቅስቃሴዎችና በነገረ መለኮት ሰዎች መካከል ያለማቋረጥ ለሚካሄዱት የፖለቲካ ክርክሮች ማዕከል ናቸው:: በቶሮንቶ ኮንፈረንስ የተዳሰሱት የነገረ መለኮት ርእሰ ጉዳዮች ቀላል ግምት የሚሰጣቸው አይደሉም::

ይህ መጽሐፍ ለአራት ዐሥርተ ዓመታት ከሙስሊሞች ጋር ያደረግኋቸው ውይይቶችን እንዲሁም በጣም ከማከብራቸው ጓደኞቼ ጋር የነበረኝን ቆይታ የሚዳስስ ነው:: አንዳንዴ በአጋጣሚ እየተገናኘን በሌላ ጊዜ ደግሞ ጊዜ

ቈርጠን በመሰብሰብ እውነተኛና ጥልቅ የነገረ መለኮት ውይይቶችንና ሙግቶችን እናካሂድ ነበር::

ተሳታፊ በነበርሁበት በመካከለኛው ምሥራቅ ኮንፈረንስ ላይ፣ ታዋቂው የእስልምና የነገረ መለኮት ሊቅ የሆነው ጳጳስ ኪኔት ክራግ፣ "ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ሲገናኙ የሚለያዩባቸው ርእሰ ጉዳዮች እንዳሉ ሁሉ፣ አንድ የሚያደርጋቸውም ርእሰ ጉዳዮች አሉ" ብለው ነበር::

አንዳንድ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች በእስልምናና በወንጌል መካከል ያለውን አንድነት በማጉላት ልዩነቶችን ችላ ብለዋቸዋል:: ሌሎች ደግሞ በልዩነቶቹ ላይ ትኩረት በመስጠት፣ የሌላኛው እምነት ፈጽሞ ሐሰት ነው ባዮች ናቸው:: ይህ መጽሐፍ ለሚያስማሙን ነጥቦች አክብሮት በመስጠት፣ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች የአብርሃምን አምላክ የማምለካቸውን ጉዳይ ትኩረት ይሰጥበታል:: እኔም የእስልምናና የወንጌል ጥሪ በዕለታዊ ኑሮአችን ምን እንደሚመስል፣ የሙስሊሙን ማኅበረሰብ እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን የሚስዮናዊነት ሥራ ባሕርያትና አካሄድ የሚዳስስ ነው::

በድሩ ቀትራጋ እና እኔ በጻፍነው መጽሐፍ ማጠቃለያ ላይ፣ የሁለታችንንም ምልከታ የሚገልጽ አስተያየት ሰጥተናል:: በአንድነት በሚገኘው ደስታና በልዩነታችን መኻል የሚፈጠረውን የልዩነት ስሜት ተጋርተናል:: ይህንም ጉዳይ እንዲህ ገልጸነዋል:—

> አንድ የሚያደርጉንን መሠረተ እምነቶች በጽናት ብናወድሳቸውም፣ ዐቢይ በሆኑ አስተምህሮዎችም ላይ ልዩነት እንዳለን ከሙሉ ልብ የምንቀበለው ጉዳይ ነው::
>
> በእስልምና የአላህ ምሕረት በከፍተኛ ደረጃ የተገለጸው ፍጹም በሆነው ሕግ በኩል ነው:: በክርስትና እምነት ደግሞ የእግዚአብሔር ፍቅር የተገለጸው በመሲሑ በክርስቶስ መከራ፣ በመስቀል ላይ ሞቱ፣ በትንሣኤውና በሕይወቱ በተገለጠው የማዳን ፍቅሩ ነው:: እነዚህ ቀላል የሚባሉ ልዩነቶች አይደሉም:: ምክንያቱም ስለሰው ሕይወት መሠረታዊ ጥያቄዎች በጥልቅ የሚነኩ ጉዳዮች ናቸውና:: ክርስቲያንም ሆነ ሙስሊም የሆነ ማንኛውም ሰው፣ እነዚህ ልዩነቶች

አላስፈላጊ ወይም ዐቢይ ጉዳዮች አይደሉም ብሎ መናገርም ሆነ ማመን አይችልም[2]::

ይህ ውይይት ጨዋነት የተላበሰ፣ ቀጥተኛ እንዲሁም በመከባበር ላይ የተመሠረተ ነበር:: መጽሐፉም በክርስቲያኖችም ሆነ በሙስሊሞች ዘንድ ጥሩ ተቀባይነት ያገኘ መጽሐፍ ነው:: ነገር ግን ከበድሩ ጋር ውይይቱን ከጻፍን በኋላ፣ የዚህ ተከታይ ክፍል በእስልምናና በክርስትና እምነት መካከል ያለውን የግንኙነት ባሕርይ ጠለቅ ባለ መልኩ በተለይም ደግሞ ከራሴ ተሞክሮ በመነሣት ለመጻፍ ፈልጌ ነበር:: በማንኛውም ጊዜ ሙስሊሞችን በመስጊድ አግኝቼ ስለ ወንጌል ያላቸውን አተያይ ስሰማ ስለ ወንጌል ያለኝን መረዳት የበለጠ ግልጽ ያደርግልኛል፣ ምክንያቱም መረዳታቸው ከቃለ እግዚአብሔር ጋር የሚጋጭ እንዲሁም እርስ በርሱ የተምታታ ነው:: ብዙ ጊዜ እስልምና የክርስትና አቻ ተፎካካሪ ሃይማኖት እንደ ሆነ አድርጎ ራሱን ያቀርባል:: ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ዐይነቱ ተግዳሮት በሚገጥማት ጊዜ በወዲያ ወገን ያለውን ገለጻ መስማት ብቻ ሳይሆን፣ ስለ ወንጌል ትምህርት የጠራ መረዳት ታገኛለች::

በዚህ መጽሐፍ የውይይት መንፈስ ባዘለ መልኩ በእስላማዊ የአስተሳሰብ ዐውድ ውስጥ፣ መሲሑ ምን እንደሚመስል ለማስረዳት ጥረት አድርጌያለሁ:: ክርስቶስን በሙስሊም ዐውድ መመልከትና ትንተና መስጠት ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ሁሌ የሚዘነጉትን የወንጌል ክፍል በጠለለ መልኩ እንዲረዱት ያደርጋቸዋል::ስለዚህ የዚህ መጽሐፍ ቀዳማይ ተደራሲያን ክርስቲያኖች ናቸው:: ሙስሊሞችን ግራ የሚያጋባቸው፣ ክርስቲያኖች መሲሑን እንደሚያምኑ ነገር ግን የመጽሐፍ ቅዱሱን ኢየሱስ በዕለት ተዕለት ኑሮአቸው የመካዳቸው ጉዳይ ነው (የዕለት ተዕለት ሕይወታቸው መሲሑን ያለመምሰሉ ጉዳይ ነው):: ፍጥረተ ዓለም ሁሉ ለአላህ ፈቃድ መገዛት አለበት የሚለውን የሙስሊሞች አስተሳሰብ፣ ክርስቲያኖች ሁሉ ትልቅ ስፍራ እንደሚሰጡት እሙን ነው::

ወንጌልን በተመለከተ ከመስሊሞች በኩል የሚሰነዘረው ሒስ ክርስቲያኖች ጠንቃቃ የነገረ መለኮት ሰዎች እንዲሆኑ የሚጠይቅ ነው:: ክርስቲያኖች ለምስክርነትና ለውይይት ሲገናኙ፣ ተገቢውን ዝግጅት ያላደረጉበትን የነገረ

[2] Badru D. Kateregga and David W. Shenk, *A Muslim and a Christian in Dialogue* (Scottdale: Herald Press, 1977), 205-6.

መለኮት ርእሰ ጉዳይ ለውይይት ይዘው ቢቀርቡ የሚያዋጣቸው አይሆንም:: ስለዚህ ይህ መጽሐፍ መሲሑን የተዛባው ባህላቸው ውጤት አድርገው የተረዱትን ክርስቲያኖች ለንስሓ በመጋበዝ ክርስቶስን ያሳያቸዋል የሚል ጽኑ እምነት አለኝ:: ስለወንጌል የሚቀርበው እስላማዊ ሒስና አማራጭ አስተምህሮ ክርስቲያኖች ወደ አዲስ ኪዳን የነገረ መለኮት ትምህርት እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱሱ ኢየሱስ እንዲመለሱ ያበረታታቸዋል የሚል ተስፋ አለኝ::

ሙስሊሞችም የዚህ መጽሐፍ ተደራሲያን ናቸው:: ቁርአንና ሙስሊሞች መሲሕ ነው ብለው ስለሚመሰክሩለት ኢሳ (ኢየሱስ) ምሉዕ ማንነትና የጠራ ግንዛቤ እንደሚያገኙ ተስፋ አደርጋለሁ:: መሲሑን በተመለከተ ሙስሊሞች ከአይሁዶች ይልቅ ለክርስቲያኖች ቅርብ ናቸው::

ቁርአን በሱራ 5+82 እንዲህ ይላል:—

> ይሁዶችን እነዚያን ያጋሩትን ለነዚያ ለአመኑት በጠላትነት ከሰዎች ሁሉ ይበልጥ የበረቱ ሆነው በእርግጥ ታገኛለህ፤ እነዚያንም እኛ ክርስቲያኖች ነን ያሉትን ለእነዚያ ለአመኑት በወዳጅነት በእርግጥ ይበልጥ የቀረቧቸው ሆነው ታገኛለህ፣ ይህ ከእነርሱ ውስጥ ቀሳውስትና መነኮሳት በመኖራቸውና እነርሱ የማይኰሩ በመሆናቸው ነው::

ሙስሊሞች ኢየሱስ ከድንግል የተወለደ መሲሕና የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ፍጻሜ እንደ ሆነ ይመሰክራሉ:: የአይሁድ እምነት ግን ስለ ኢየሱስ እንዲህ አያስተምርም:: ምንም እንኳ ሙስሊሞች የኢየሱስን መሲሕነት ቢቀበሉም፣ በእስልምና እምነት ውስጥ ኢየሱስን ግልጽ በሆነ መንገድ መረዳት አዳጋች ነው:: ሙስሊሞች ስለክርስቶስ መሲሐዊ አገልግሎት ያላቸው መረዳት ከመጽሐፍ ቅዱሱ ኢየሱስ ወይም ከቤተ ክርስቲያን ምስክርነት መሠረታዊ ልዩነት አለው:: ሙስሊሞች ይህንን መጽሐፍ ሲያነቡ፣ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ መሲሑ የተናገራቸውን ነገሮች በውል እንዲገነዘቡ ዕገዛ ያደርግላቸዋል የሚል ተስፋ አለኝ::

በተጨማሪም ስለሙስሊሙ ማኅበረሰብና እምነቶች ትክክለኛ ዘገባ ለማቅረብ እሞክራለሁ:: ከሙስሊሞች ጋር ባደረግኋቸው ብዙ ውይይቶች ሙስሊሞች እስልምናን እንዲቀበሉ ያደረጋቸውን ውስጣዊ ስበት (ምክንያት) ለማየት በመቻሌ፣ አንባቢዎቼ ይህንኑ ጉዳይ በግልጽ እንዲረዱት ለማድረግ ሞክሬያለሁ:: ነገር ግን እኔ ሙስሊም አይደለሁም፤ ክርስቶስ እግዚአብሔር

የቀባውና የዓለም ሁሉ መድኀኒት እንደ ሆነ አምናለሁ። እንዳንድ ሙስሊሞችም፣ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ካሰፈርኋቸው የተወሰኑ ሐሳቦች ጋር ላይስማሙ ይችላሉ። ይህ ዐይነቱን ጉዳይ ማስወገድ አይቻልም። ሆኖም እስልምናን በተሳሳተ መንገድ እንዳላቀረብሁት ተስፋ አደርጋለሁ። ይህ መጽሐፍ ከመታተሙ በፊት፣ ሙስሊሞች በጥንት ቅጆች ላይ ያላቸውን ሒስ በጥንቃቄና በትልቅ ትኩረት የመረመርሁበትም ዐቢይ ምክንያት ይኸው ነው።

አንዳንድ ክርስቲያኖች፣ የሙስሊሞችን መንፈሳዊ ትጋት እያዳነቅሁ የጻፍሁ መስሉ ሊሰማቸው ይችል ይሆናል። ስለሙስሊሞችም ስጽፍ የሙስሊሞችን እምነትና ተልእኮ ከሙስሊሞች የመረዳት አንጻር ሆኜ ነው ለመናገር የሞከርሁት። እስልምናን የገለጽሁት በሙስሊሞች ስፍራ በመሆን ነው። ይህንንም የማደርገው ሆን ብዬ ነው፤ ምክንያቱም ክርስቲያኖች፣ ሙስሊሞች እምነታቸውን በሚረዱበት መንገድ የእስልምናን እምነት መረዳታቸው ወሳኝ ነው ብዬ አምናለሁ።

ወታደራዊ እንዲያውም ጦረኛ የሆነው እስልምና የገጠማቸው ክርስቲያኖች፣ እኔ የምገልጸው ዐይነት እስልምና "እኛ የምናውቀው እስልምና አይደለም" ወደሚል ድምዳሜ ሊያደርሳቸው ይችላል። ይህ እውነት ነው። እኔም እንደዚህ ዐይነት ሙስሊሞች ገጥመውኛል። ነገር ግን ከዚህ ዐይነቱ እስልምና ጋር የነበረኝ ግጥጥሞሽ ዘውትራዊ አልነበረም። የእነዚህን ሰዎች ጦረኛ መንፈስ በሚያነሣሡ ዐበይት ቁርአናዊ ትምህርቶች ላይ አስተያየት ሰጥቻለሁ። ይሁንና አብዛኛውን ጊዜ የኖርሁት ልማዳዊ ከሆኑና ብዙኃኑን ከሚወክሉት ሙስሊሞች ጋር እንጂ፣ ከጦረኛ ሙስሊሞች ጋር አልነበረም።

አንዳንድ ሙስሊሞች እኔ ስለ ኢየሱስና ቤተ ክርስቲያን የገለጽሁት ነገር እነርሱ ከሚያውቁት ኢየሱስና ቤተ ክርስቲያን ወደ ተለየ ድምዳሜ ሊያመጣቸው የሚችል ሲሆን፣ ብዙ ሙስሊሞች ደግሞ የክርስትናን እምነት የሚመለከቱት የሙስሊሙን ሕዝብ በወጉት ጎይለኛ የመስቀል ጦርነት ተዋጊዎች የምልከታ መነጽር ነው። የቅርብ ጊዜ ታሪኮችን እንኳ ብንመለከት፣ በቦስኒያ፣ በቼቺንያ፣ በኮሶቮና በኢራቅ ልብን የሚሰብሩ ሁኔታዎችን አስተውለናል። ሙስሊሞች ብዙ ጊዜ እነዚህን ግጭቶች በእስልምናና የሙስሊሞች ላይ የተፈጸሙ ግጭቶች አድርገው ይመለከቷቸዋል፤ የጦርነቱ ቀስቃሾች ሙስሊሞች ክርስቲያን እንደ ሆኑ የሚገምቷቸው አገሮች ናቸውና።

በመስቀል ጦረኞች ለጦርነታቸው መሠረት አድርገው በሚያቀርቧቸው የብሉይ ኪዳን ክፍሎች ላይ የምለው ይኖረኛል። ነገር ግን ስለእስልምናና ወንጌል በማቀርበው ጽሑፍ የትኩረት አትጣጫዬ የሆነው ለሙስሊም አገሮችና ለቤተ ክርስቲያን መሠረታዊ ናቸው በሚባሉ ርእሰ ጉዳዮች ላይ ነው። ከዚህም የተነሣ ለቁርአንና ለመሲሑ አጽንኦት ሰጥቻለሁ። የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ቁርአን መልካሙንና ክፉን መለያ መሣሪያ ነው የሚል እምነት አለው፤ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ ክርስቶስ መሲሕና የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ነው ብላ ትመሠክራለች።

የሙስሊሙ ማኅበረሰብና ቤተ ክርስቲያን፣ በውስጣቸው የተለያዩ ቡድኖችን ዐቅፈው ይዘዋል። ይህ አጭር ነገረ መለኮታዊ ትንተና የተለያዩ የሙስሊምና የክርስቲያን ወገኖችን የተለያየ አተያይ በበቂ ሁኔታ መግለጥ አይችልም። ከዚህም የተነሣ ስለ ሙስሊሞች የቀረበው ዘገባ በዋነኝነት ያተኮረው ልማዳዊ በሆነው የሱኒ ሙስሊም ማኅበረሰብ አተያይ ላይ ነው።

በክርስቲያኖች መካከል ያለው ልዩነት ከሙስሊሞቹም ይሰፋል። ነገር ግን እኔ መሠረት የማደርገው በሜኖናይት የእምነት መግለጫ ላይ ሲሆን፣ "የአናባፕቲስት አስተምህሮን"[3] ("የመሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን" አስተምህሮ) የሚያንጸባርቅ ነው። የሜኖናይት ማለትም የመሠረተ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ከ16ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በአውሮፓ የነበረና በዳግም መጥምቃውያን (በአናባፕቲስቶች) እንቅስቃሴ ከተመሠረቱ ቤተ እምነቶች አንዱ ነው። ዳግም መጥምቃውያን፣ እያንዳንዱ የሕይወት ክፍል ለክርስቶስ ሥልጣንና መንግሥት መገዛት አለበት ብለው ያምናሉ። መላውን ሕይወታቸውን ለእላህ ፈቃድ ለማስገዛት ራሳቸውን የሰጡ ሙስሊሞች፣ ይህ ዐይነቱ መገዛት ምን እንደ ሆነ በቀላሉ ሊረዱት ይችላሉ። በእርግጥ የእግዚአብሔር መንግሥት ባሕርይን በተመለከተ፣ በመጽሐፍ ቅዱሳዊውና በቁርአናዊው እምነት መረዳት መካከል ልዩነት አለ። የሆኖ ሆኖ ዳግም መጥምቃውያንና (በአናባፕቲስት) ሙስሊሞች የአንድን ሰው ሕይወት ዓለማዊና መንፈሳዊ ብሎ መከፋፈልን ይቃወማሉ፤ ይልቁንም ሁሉም የሕይወት ክፍል ለአምላክ ሕግ መገዛት እንዳለበት አበክረው ያስተምራሉ። ለዚህ ራእይ

[3] *Confession of Faith in A Mennonite Perspective* (Scottdale: Herald Press, 1995). ይህ የሃይማኖት መግለጫ የሰሜን አሜሪካ ዳግም መጥምቃውያን ሜኖናይት (መሠረተ ክርስቶስ) ቤተ ክርስቲያን የሃይማኖትና የምግባር አቋም ነው።

ራሳቸውን የሰጡ ክርስቲያኖች በሙሉ፣ ከሙስሊሞች ጋር ለሚያደርጉት ውይይት የጋራ የሆነ መግባባት ያገኛሉ።

ዳግም መጥምቃውያን (በአናባፕቲስቶች) በመጀመሪያዎቹ የፕሮቴስታንት ተሐድሶ ዓመታት ብቅ ያሉ የነጻ ቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴዎች ነበሩ። ዳግም መጥምቃውያን በአዲስ ኪዳኗ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ፣ ታማኝ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ለመሆን የሚጓጉ ነበሩ። ጥቂት ጽንፈኞችና ሁከት ፈጣሪዎች በእንቅስቃሴው ውስጥ ቢኖሩም፣ አብዛኞቹ ዳግም መጥምቃውያን የአዲስ ኪዳኑን ኢየሱስ በሙላት ለመከተል ራሳቸውን የሰጡ ነበሩ። ጥምቀት ለዚህ መሰጠት በጉባኤ ፊት የሚቀርብ ምስክርነት እንደ ሆነ ያምኑ ስለነበር፣ ሰዎች ክርስቶስን ከተቀበሉ በኋላ የሚያጠምቁት ዐዋቂዎችን ብቻ ነበር። መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን መለያየት እንዳለባቸው አበክረው ያምናሉ። በአውሮፓ በሙስሊም ቱርኮች ላይ የታወጀውን ጦርነት ጨምሮ በማንኛውም ጦርነቶች ውስጥ መሳተፍን ተቃውመዋል። የመሲሑ ኢየሱስ፣ ታማኝ ደቀ መዛሙርት ሆነው ለመገኘት ይጥሩ ነበር። ትጉኅ የወንጌል ሰባኪዎችም ነበሩ። የመንግሥትንና የቤተ ክርስቲያንን የጥምረት አስተሳሰብ ስለተቃወሙ በባለሥልጣናት እየተገደሉ ሰማዕት ሆነዋል።

ከሙስሊሞች ጋር የነበረኝ ቆይታ የዳግም መጥምቃውያን ማንነቴ አሻራ ያረፈበት ነው። ይህም መጽሐፍ ይህንን እውነታ ያንፀባርቃል። እኔ የመሲሑ ኢየሱስ ተከታይ ነኝ። እግዚአብሔር በመሲሑ ኢየሱስ ሰውን እንዳዳነ እንዲሁም በክርስቶስ ይቅርታንና ከእግዚአብሔር ጋር ዕርቅን እንዳገኘሁ አምናለሁ። ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር ላይ ለመኖሩ ምልክት እንድትሆን እግዚአብሔር ጠርቶአታል ብዬ አምናለሁ። ይህም መንግሥት በመሲሑ የተጀመረ ሲሆን፣ በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ለዘላለም ፍጻሜን ያገኛል። በዚህ መጽሐፍ ገጾች ውስጥ፣ መሲሑን ኢየሱስ ከፍ አድርጌ ለማቅረብ የፈለግሁትም በዚሁ ምክንያት ነው።

ይህ መጽሐፍ ከሙስሊም ጓደኞቼ ጋር የነበሩኝን ውይይቶች እንጂ፣ ሰፊ ነገረ መለኮታዊ ዘገባዎችን አያንጸባርቅም። ትረካዊ ነገረ መለኮት እንዲሁም አሜሪካ የግል ገጠመኝ ታሪኮችን ይሏል። እስከማስታውሰው ድረስ፣ ሁሉም የግል ገጠመኞችና የውይይት ሐሳቦች እውነተኛ ናቸው። ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ የሰዎችን ስም ከመጥቀስ ይልቅ ሌላ ስም ተጠቅሜያለሁ።

የሕይወቴ መመሪያ በ1ጴጥሮስ 3+15 ላይ የሚገኝ ሲሆን እንዲህ ይላል፦

> ዳሩ ግን ጌታን እርሱም ክርስቶስ በልባችሁ ቀድሱት። በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያት ለሚጠይቃችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ፣ ነገር ግን በየዋሕነትና በፍርሓት ይሁን።

ከሻቢር ዓሊ ጋር ለስድስት ቀናት ለነበረኝ ውይይት በጥቅምት ወር 2000 ዓ.ም ለንደን ደረስሁ። ጥሪ ላቀረቡልኝ ሙስሊም ተማሪዎች ማኅበር ካቀረብሁላቸው ጥያቄዎች መካከል አንዱ፣ "ለምን ወደዚህ ጋበዛችሁኝ" የሚል ነበር። እነርሱም "ምክንያቱም መጽሐፍህ ለወንጌል ራሱን የሰጠና አንተም ለሙስሊሞች ትልቅ አክብሮት እንዳለህ ስላስገነዘበን ነው" የሚል መልስ ነበር ይሰጡኝ።

ይህን መጽሐፍ የጻፍሁት እንዲህ ዐይነት አስተዋጽኦ ሊኖረው እንደሚችል ተስፋ በማድረግ ነው። በእርግጥ ይህን ዕትዴን ከዳር አድርሼዋለሁ የሚለውን ጉዳይ፣ መጨረሻ ላይ እናንተ እንደ አንባቢ የምትወስኑት ጉዳይ ነው የሚሆነው።

<u>የመጽሐፉ አጠቃቀም</u>

ይህ መጽሐፍ በእስልምናና በወንጌል እንዲሁም በሙስሊሙና በክርስቲያኑ ማኅበረሰብ መካከል ያለውን ባሕርይ ንጽጽራዊ በሆነ መልኩ የሚያቀርብ ነው። የተጻፈውም በዐላማ ለሚያነቡ አንባቢያን እንደዚሁም ልዩ ትኩረት ሰጥተው ለሚወያዩ ቡድኖች ወይም በርእሰ ጉዳዩ ላይ መደበኛ ትምህርት ለሚሰጥባቸው ክፍሎች እንዲሆን ታስቦ ነው። ለእስልምናና የዓለም እምነቶች ለተሰኙ ክፍለ ትምህርቶች (ኮርሶች) አጋዥ መጽሐፍ ሆኖ ጥቅም ላይ ሊውልም ይችላል።

"የተለያዩ ጉዞዎች" የሚል ርእስ የተሰጠው የመጀመሪያው ምዕራፍ፣ ሁለት ክፍሎችን ይዟል፤ እነዚህም የሙስሊሙ ማኅበረሰብና የቤተ ክርስቲያን ባሕርይ ገለጻዎችና ታሪካዊ ዳሰሳ ናቸው። የሙስሊሙ ማኅበረሰብና የቤተ ክርስቲያን ታሪካዊ ጉዞዎች ምን ይመስላሉ? ይህም በሙስሊሙና በክርስቲያኑ ማኅበረሰብ መካከል ስላለው ነገረ መለኮታዊ ልዩነት ዐውዳዊ ግንዛቤ ይሰጠናል።

የዚህ መጽሐፍ ነገረ መለኮታዊ ትንተናዎች የተጠቃለሉት በዐሥራ ሦስት ምዕራፎች ውስጥ ነው። ይህም ስለ ሙስሊሙና ስለ ክርስቲያኑ ማኅበረሰብ እምነትና ተልእኮ ለሦስት ወራት ሳምንታዊ የሆነ ንጽጽራዊ ጥናት ለማድረግ ይረዳል። መጽሐፉ በአብዛኛው መሠረት ያደረገው የቁርአንንና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን ሲሆን፣ ለቀጣይ ንባብና ጥናት የሚረዱ ክፍሉችንም ይሰጣል። በየምዕራፉ መጨረሻ ላይ የሚገኙት ጥያቄዎች ለውይይት ጥሩ መደላድል ያደርጋሉ የሚል እምነት አለኝ።

ተማሪዎችና አጥኚ ቡድኖች መጽሐፍ ቅዱስና ቁርአን በእጃቸው ሊኖራቸው ይገባል፤ ምክንያቱም ብዙዎቹ ጥያቄዎች የተወሰዱት ከእነዚህ ሁለቱ የእምነት መጽሐፎች ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት የኢንተርናሽናል የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በጆሊያን (በኢትዮጵያውያን) የዘመን አቈጣጠር በ1993 ዓ.ም ካሳተመው የአዲሱ መደበኛ ትርጒም እንዲሁም የኢትዮጵያ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር በ1954 ዓ.ም ካሳተመው መጽሐፍ ቅዱስ ሲሆን፣ የቁርአን ጥቅሶች የተወሰዱት ደግሞ፣ ሸኽ ሰይድ ሙሐመድ ሳዲቅና ሐጂ ሙሐመድ ሳኒ ሐቢብ ወደ አማርኛ ተርጒመውት ነጃሺ አሳታሚ ድርጅት 1961 ዓ.ም እንዲሁም ወርኀ ሚያዝያ 1997 ዓ.ም ካሳተመው የቁርአን ቅጅ ነው። በቀላሉ እንዲነበብ ዐረብኛ ላልሆኑ ፊደላት የዐረብኛ አናባቢ ፊደላትን አስቀርተናል። ነገር ግን አይን (ayn) እና ሐምዛ (Hamza) ጨምረናል።

እንደ ተጨማሪ ምንጭ ሆኖ እንዲያገለግል በመጽሐፉ የመጨረሻ ክፍሎች ላይ የአርእስታዊና የገላጭ ዋቢ መጻሕፍት ዝርዝር ተካቶአል። የዋቢ መጻሕፍቱ ዝርዝር የተዘጋጀው በዶክተር ጆን ሁቨር ሲሆን፣ እኚህ ምሁር ዳር ኮምቦኒ በሚሰኘው የእስልምና ጥናት ፕሮግራም ካይሮ ለሚገኘው የዐረብኛ ጥናት ረዳት ሱፐርቫይዘር ናቸው። እኚህ ሰው ለዚህ መጽሐፍ ላበረከቱት ታላቅ አስተዋጽኦ፣ ላቅ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ።

ምስጋና

መጽሐፉን በማዘጋጀት ሂደት ውስጥ የተወሰኑ ባልንጀሮቼ በማደርገው ጥረት ውስጥ አብረውኝ ተጉዘዋል። ብዙዎቹ መጽሐፉን በማንበብ አስተያየታቸውን

ሰጥተውኛል። በተለይም በጣም ጠቃሚ ምክር በመስጠት የረዱኝን ሁለት ጓደኞቼን ማመስገን እፈልጋለሁ። የመጀመሪያው በፈላደልፊያ የቀዶ ጥገና ሐኪም የሆነው የረጅም ጊዜ ጓደኛዬ ዶክተር አ. አር. ሳፊ ሲሆን በጣም ወሳኝ የሆኑትን ምዕራፎች በማንበብ ገንቢ ትችቶችን ሰጥቶኛል። እንዲሁም ቶሮንቶ የሚገኘውን እስላማዊ የመረጃ ማዕከልን ከሚመሩት ከኢማም ሻቢር ዓሊ ጋር በመሆን ጥልቅ የሆነ ትምህርት ያላቸውን ቅጆችን መርምሬአለሁ። እነዚህ ወዳጆቼ እኔ እስልምናን በተመለከተ ለተከተልሁትና ላጸበርሁት አቀራረብ አስላማዊ አስተውሎቶችን አበርክተዋል።

ብዙ የሙስሊም ምሁራን ሥራዬን በተመለከተ ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ ሒሳዊ ግምገማ ሰጥተውኛል። ሳሙኤል ሰክሉርፍ ትክክለኛነቱንና ነገረ መለኮታዊ እውነተኛነቱ በተመለከተ አስተያየት ሰጥቶኛል። እንዲሁም ሮልፍ ኩትሲ እና አንቶን ዌሴልስ የተባሉ ሁለት የደች የእስልምና ምሁራን ደግሞ፣ ተመሳሳይ አስተያየት ሰጥተውኛል። ጆን ሑቨር የመጽሐፉን አካዳሚያዊ ጥራት በተመለከተ አግባብነት ያለው አስተያየት የሰጠ ሲሆን ጉርደን ኒኬል፣ ካልቪን ሼንክ እና ሮይ ሐንጅ ደግሞ ተመሳሳይ ሐሳብ አበርክተዋል። የመጽሐፉን ግልጽነት፣ ጠቃሚነት፣ ነገረ መለኮታዊ ይዘት እንዲሁም ቅያሜ ፈጣሪ አለመሆኑን በተመለከተ ሪይ ሬትዝ፣ ዴቪድ ዊትመር፣ ሊአን ሚለር፣ ሐሮልድ ሪድ፣ ዳሪን ስካውን፣ ባርባራ ዊትመር፣ አርበኔ ፒቼይ እና ጄፍል ቨዋልተር ምክር ሰጥተውኛል። አቶ ጥላሁን በየነ ደግሞ ከዓለም ዐቀፋዊ እይታ አንጻር ጠቃሚ ምክር ሰጥተውኛል። ጃኔት ክሪይደር እና እኅቷ ኤልሳቤጥ ጽሑፉ ከተገመገመ በኋላ መልሶ በማዘጋጀቱ ሥራ ብዙ ደክመዋል። ይሁንና በመጽሐፉ ለተንፀባረቁ ሐሳቦች በሙሉ፣ ሙሉ ኀላፊነቱን የምወስደው እኔው ጸሓፊው ነኝ።

ይህ ጥረት በእኔ ውስጥ ለረጅም ዓመታት ተፀንሶ ለፍሬ እየተቃረበ ያለ ነገር ነበር። በሊቱንያ ክርስቲያን ኮሌጅ የአራት ዓመት ቆይታዬ፣ ኮሌጁ በአውሮፓውያን ዐውድ ከሙስሊም አገላለጾች ጋር መስተጋብር እንድፈጥር ዕድሉን ሰጠኝ። "ኢስተርን ሜኖናይት ሚሽን" ደግሞ ይህንን ጥረት በማበረታታት በገንዘብ ደገፈኝ። እኔ አባል የነበርሁበት "ማውንት ቪሲ ሜኖናይት ቤተ ክርስቲያን" ደግሞ፣ ይህንን ጽሑፌን እስከጨርስ ድረስ ያበረታቱኝና ይጸልዩልኝ ነበር።

በተለይ ለእግዚአብሔር መገዛትን ጨምሮ ብዙ ትምህርት ለቀሰምሁባቸው ብዙ ሙስሊም ወዳጆቼ በተለየ ሁኔታ ባለዕዳ ነኝ። ከብዙ ዓመታት በፊት "ኤ ሙስሊም ኤንድ ኤ ክርስቲያን ኢን ዲያሎግ" የሚል መጽሐፍ በጋራ አብረኤትው ጽፈ ለነበሩት ለበድሩ ዲ. ቀትራጋ ልዩ ምስጋና አቀርባለሁ። ከእኚሁ ሰው ጋር አብሬ በመጻፈ ይህንን መጽሐፍ ለመጻፍ ራእይ አግኝቻለሁ። በዚህ ጥናት ውስጥ ቀድሞ ሙስሊም የነበሩ አሁን ግን በመሲሑ ጌጻና እየተጓዙ የሚገኙ ወዳጆቼ ልዩ ሚና ነበራቸው። ባለቤቴ ግሬስም ይህንን ሥራ በባርኮት ተቀብላዋለች። ጽሑፈን በምጽፍበት የጥናት ክፍሌ ውስጥ እኔን ለማበረታታት የምጠጣውን ሻይ በተደጋጋሚ አቅርባልኛለች። ያለ እርሷ አጋዥነት መጽሐፉ በእጅጉ ውስጥ የሚቀር ሐሳብ ብቻ ይሆን ነበር፣ አመሰግናታለሁ።

ምዕራፍ አንድ

የተለያዩ ጉዞዎች

በነበርንበት ሬስቶራንት፣ "ሁለቱ መንትያ ሕንፃዎች" የሚል የድንጋጤ ድምፅ እንግዳ ተቀባይዋ በተንቀሳቃሽ ስልኳ ስትናገር ሰማን። በዚያን ጊዜ እኔና ባለቤቴ ግሬስ፣ በኡዝቤኪስታን ታሽከንት በሚባል ስፍራ ነበርን። በመስከረም 11 ቀን 2001 ዓ.ም. ምሽት በኒውዮርክ፣ በዋሽንግተን ዲሲ እና በፔንሲልቬንያ የተፈጸመውን አሠቃቂ ድርጊት ዜና የሰማነው፣ በመሻል ከተማ ባለው ሬስቶራንት (ምግብ ቤት) ውስጥ ከባልንጀሮቻችን ጋር ራት እየበላን ነበር።

ይህ "ከኢየሩሳሌም" ጋር የተገናኘ እንደ ሆነ ስለገመትን በሐዘን ተዋጥን። በዚህ አደጋ የእምነት፣ የታሪክ፣ የትውፊትና የብሔርተኝነት ርእሰ ጉዳዮች ተጠላልፈውበት ነበር።

በሚገርም መልኩ ኢየሩሳሌም የሰላም ከተማ ተብላ ትታወቅ ነበር። ከየትኛውም ከተማ ይልቅ ለእስራኤል "የሻሎም" (shalom) ለእስልምናና ለመንጌል "የሰላም" ስፍራ ነበረች። እነዚህ ምስቱ ግለትም የአይሁድ፣ የእስልምናና የክርስትና እንትስቃሴዎች መሠረታቸውን የጣሉት በዘፍጥረት 12÷3 ላይ በምድር ያሉ ሕዝቦች ሁሉ በእርሱ በኩል ለመባረክ እግዚአብሔር ጠርቶት በነበረው አብርሃም ላይ ነው። የጽዮናውያን ተስፋ፣ የቤተ ክርስቲያንና የሙስሊሞች ራእይ "ሰላም ለሰው ልጆች ሁሉ" የሚል ነው። ኢየሩሳሌም ውስጥ በጉርብትና የሚኖሩት ሙስሊሞች፣ ክርስቲያኖችና አይሁዶች በመካከላቸው በመቻቻል ላይ መሠረት ያደረገ ሰላም አለ። ይሁንና በመካከላቸው ከፍተኛ ጥፋት የሚያስከትሉ፣ የማያቋርጡና አደገኛ የሆኑ ነገረ መለኮታዊ፣ ብሔራዊና ባህላዊ ችግሮች ይታያሉ። ለእነዚህ ችግሮች መፈጠር ምክንያቱ ምን ይሆን?

ሰላምን መፍጠር

በመስከረም 11 ጥፋት ማግሥት፣ በታሽከንት ከተማ በነበረን ወዲደ ጥናት ላይ የተነጋገርንበት ርእስ፣ "የሰላም ጌጻና" የሚል ነበር። ጓደኞቻችን የወዳደቁ ቁርቁሮች ያሉበትና ለመንቀሳቀስ አስቸጋሪ ወደ ሆነው የምድር ቤት ክፍል

ይዘውን ወረዱ። ይህም ክፍል አንድ ቀን የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መስጫ ተቋም ይሆናል ተብሎ የሚታሰበው ሕንፃ ሥራ የተጀመረበት ነው። በዚያ ክፍል ውስጥ ሰባ የኡዝቤክ ወይንም የራሽያ መጋቢዎችና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ነበሩ። በግምት ሁሉም የቅርብ ጊዜ አማኞች ሲሆኑ፣ የመጡትም ከእስልምና ወይም እግዚአብሔር የለም ብሎ ከሚያምነው የሶሻሊስት ርዕዮተ ዓለም ነበር። የተለያዩ መረጃዎች እንዳሉን እንዲሁም በመሲሑ ሰላምና በእስልምና ሰላም ውስጥ ለተገለጠው ተልእኮ ያለውን መሰጠት የተገነዘብንበት ልዩ ቀን ሆነልን። በዚያን ቀን አብዛኛውን ጊዜያችንን ያጠፋነው በመስቀል ላይ በመሞት ሰላምን በፈጠረው የሰላም አለቃ (የክርስቶስ) አምባሳደር መሆን ማለት ምን ማለት ነው? የሚለውን ርእሰ ጉዳይ በመመርመር ነበር። የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት ገደማ መሲሑ በአህያ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ "ለሰላምሽ የሚሆነው...ከወይንሽ ተሰውሮአል" ብሎ ለኢየሩሳሌም ያለቀሰው ትዝ አለን (ሉቃስ 19+42)።

በታሸኬንት በተካሄደው ዐውደ ጥናት፣ ሰላምን ለመፍጠር/ለማምጣት የምንጠቀምበት መንገድ መሠረት ያደረገው፣ ነገረ መለኮታዊ አስተምህሮአችንን እንደ ሆነ መለየት ቻልን። ለምሳሌ ከ23 ዓመት በፊት (1978 ዓ.ም) ክርስቲያን የነበሩት የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ጂሚ ካርተር፣ ሙስሊም የነበሩትን የግብፅ ፕሬዝዳንት አንዋር ሳዳትንና የአይሁድ እምነት ተከታይ የነበሩትን የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ሜናኬም ቤጊንን ወደ አሜሪካ ጋብዘዋቸው ነበር። በሜሪላንድ ግዛት በካምፕ ዴቪድ ተገናኝተው፣ ለዐሥራ ሦስት ቀናት ያህል ሰላም ሊመጣ በሚችልበት መንገድ ላይ ትኩረት ሰጥተው ተነጋግረዋል። በመጀመሪያ ያደረጉት ነገር የየእምነት ተከታዮቻቸው ለየእምነታቸው ስለ ሰላም እንዲጸልዩ ጥሪ ማቅረብ ነበር። በሰላም ድርድሩ ወቅት ካርተር መጽሐፍ ቅዱስ ይዘው ነበረና እርሳቸውና ቤጊን በጋራ የሚያምኑትን ከየብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ክፍሎች ከፍተው አነበቡ። አንዋር ሳዳትም አንድ ቀን ሙስሊሞች፣ ክርስቲያኖችና አይሁዶች ዘላቂ የሆነ ሰላም ለማምጣት በሲና ተራራ ይገናኛሉ የሚለውን ተስፋቸውን አበሰሩ። በእምነት ረገድ የየራሳቸውን ሕዝብ የወከሉት እነዚህ ሦስት መሪዎች በዚህ ሁኔታ መገናኘታቸው፣ የሰላም ሂደቱ ቀጣይ ሊሆን እንደሚችል ያመለከተ ነበር ።

[1] Jimmy Carter, *Keeping Faith: Memoirs of a President* (New York: Bantam Books, 1982), 273-403. Karl-Josef Kuschel, *Abraham: Sign of Hope for Jews, Christians, and Muslims* (New York: Continuum, 1995).

የሰላሙ ጉዞና ተልእኮ እንደ ታሰበው ሊሄድ አልቻለም። ከሦስት ዓመት በኋላ አንዋር ሳዳት ተገደሉ። ቀጥሎም ስለ ሰላም ይታገሉ የነበሩት የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ይስሐቅ ራቢን በ1995 ዓ.ም ተገደሉ። ሰላምን ለመፍጠር መከራ መቀበል አስፈላጊ ነውን? ይህ መጽሐፍ ለዚህ ጥያቄ የሙስሊሞችንና የክርስቲያኖችን ምላሽ እንዲሁም የእስልምናንና የክርስትናን የነገረ መለኮት መሠረቶች ይዳስሳል።

የአብርሃም ቅርስ

በየሳምንቱ ሙስሊሞች በመስጊዳቸው፣ ክርስቲያኖችና አይሁዶች በየቤተ ክርስቲያኖቻቸውና በምኩራቦቻቸው የአብርሃምን አምላክ ለማምለክ ይሰበሰባሉ። እነዚህ የጎበረተሰብ ክፍሎች የአብርሃምን እምነት የሚገልጡ እንዲሁም የአብርሃም ልጆች እንደ ሆኑ ያምናሉ። እያንዳንዱ የእምነት ቡድን፣ አምልኮና ታማኝነት ፈጣሪ ለሆነው አምላክ ብቻ እንደሚቀርብ ከሙሉ ልብ ይቀበላል። ነገር ግን እነዚህ የእምነት ክፍሎች ስለ ፈጣሪ ባላቸው መረዳት እንዲሁም ራሱን በገለጠበት መንገድ ላይ ልዩነት አላቸው። ሦስቱም እምነቶች እግዚአብሔር ለሰው ልጆች እውነትን እንደ ገለጠ ያምናሉ። እነዚህ አማንያን ስለፈጣሪና ስለ እርሱ ፈቃድ በተረዱት እውነት ታማኝ ሆነው መኖር ይፈልጋሉ። ይህም ማለት አይሁዶች ለቶራ፣ ክርስቲያኖች ለወንጌል፣ ሙስሊሞች ደግሞ ለቁርአን እውነት ይገዛሉ። እነዚህ የእምነት ማዕከሎች የተለያዩ የእምነት ቡድኖችን (ማኅበረሰብን) ይሸውም እስራኤልን፣ ቤተ ክርስቲያንንና ኡማን ፈጥረዋል። በዚህ ክፍል ስለ ኡማ እና ስለ ቤተ ክርስቲያን መናገር እፈልጋለሁ።

የሙስሊሙ ማኅበረሰብ (ኡማ)

ኡማ ማለት ሕዝብ ወይንም ማኅበረሰብ ማለት ነው። የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ለእስልምና እምነት (ለአላህ ፈቃድ) ራሳቸውን ያስገዙና በዓለም ዙሪያ ያሉ አማኞች ጎብረት (ኡማ) ነው። እስላም ማለት ለአላህ ፈቃድ መገዛት (ሰላም) ማለት ነው። ማንኛውም ሙስሊም ዜጋ ከሆነበት ከራሱ አገር ይልቅ ለዓለም ዐቀፉ የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ታማኝ መሆን ይጠበቅበታል። የጎብረቱ ዋና ተልእኮ እስልምናን መጠበቅና ሙስሊሞች ወደ ተሳሳተ መንገድ እንዳይሄዱ

መከላከል ነው። እስልምና የሙስሊሙን ማኅበረሰብ መሥርቶአል፤ የሙስሊሙ ኅብረተሰብ ደግሞ እስልምና እንዳይጠፋ ይጠብቃል።

በእስልምና እምነት መሠረት የሰው ዘር ለሁለት ተከፍሎአል። ለእስልምና ሕግ የሚገዙ ሰዎች ሁሉ በሙስሊሙ ማኅበረሰብ ውስጥ ሲሆኑ፣ ያልተገዙት ግን ከዚህ ማኅበረሰብ ውጪ ናቸው። የሙስሊሙ ማኅበረሰብ (ኡማ) የሚከተለውን ምስክርነት ይሰጣል፦ "ላ ኢላሃ ኢለላህ ሙሐመደን ረሱሉ ለላህ"። ይህም፣ "ከአንድ አምላክ (አላህ) በቀር ሌላ አምላክ የለም፣ መሐመድ የአላህ መልእክተኛ ነው" ማለት ነው። ይህንን ምስክርነት የሚሰጡ በሙስሊሙ ማኅበረሰብ (ኡማ) ውስጥ የሚገኙ ሲሆን፣ ይህን ምስክርነት ያልሰጡ ደግሞ ከኡማው ውጪ ናቸው።

በመጂና፣ በመሐመድ አስተዳደር ሥር የነበሩ ሙስሊሞች፣ መተዳደሪያ ደንብ ወይም ሕገ መንግሥት አርቅቀዋል። ሕገ መንግሥቱ "ሙስሊሞች ከሌላው ሕዝብ የተለዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍል ናቸው"[2] ሲል ያብራራል።

የእስልምና ኡማ ሁሉንም የኅይልና የሥልጣን እርከኖች እስኪቆጣጠር ድረስ ምሉዕ እንደ ሆነ አይታሰብም። ይህም ሥልጣን አገራዊ ክልል አይገድበውም። በሙስሊም አስተዳደር ሥር ባልሆኑ አካባቢዎች የሚኖሩ የብዙ ሙስሊሞች የልብ ናፍቆት፣ ሙስሊሞች የፖለቲካ የበላይነት አግኝተው የሚመሠርቱትን የሙስሊሙ ማኅበረሰብ (ኡማ) ባሉበት አካባቢ ተፈጽሞ ማየትን ነው። በካሽሚር፣ በሚንዳናኦ፣ በመቄዶኒያ በቼችኒያ የተካሄዱት ዐመፆች የዚህ ናፍቆት ውጤት ናቸው። ይሁንና እንዲህ ዐይነት የፖለቲካ አጀንዳ የሌላቸው ሙስሊሞች ያሉ ሲሆን፣ ሙስሊም ባልሆነው ማኅበረሰብ ውስጥ እምነታቸውን ጠብቀው መኖር የመረጡና ባሉበት ሁኔታ ረክተው መኖር የሚፈልጉ ናቸው።

ሙስሊሞች፣ ኡማ "መካከለኛ የኅብረተሰብ ክፍል ነው" ብለው ያምናሉ። ይህም ከዐረቢያ የተገኘ ኅብረተሰብ እንዲሁም በሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል ያለ ክልል ነው። እንዲሁም እስልምና ፍጹም ሚዛናዊ እንደ ሆነ ይታሰባል። ወደ መናኝነት ወይም ደግሞ ዓለማዊነት የተሳበ ጽንፈኝነት የለበትም። ሙስሊሞች፣ የአይሁድ እምነት በዚህ ዓለም ጉዳዮች ላይ

[2] W. Montgomery Watt, *Muhammad Prophet and Statesman* (New York: Oxford University Press, 1961), 94.

ሲያተኩር፣ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ በመጪው/በመንፈሳዊው ዓለም ጉዳይ ላይ ታተኩራለች ብለው ያስባሉ። የሙስሊሙ መካከለኛ ማኅበረሰብ ግን ይህንን ዓለምና ከሞት በኋላ ያለውን ዓለም ሚዛናዊ በሆነ መንገድ እንደሚያጣምር ይታሰባል። ኡማ፣ "ከአምላክ ወገን"[3] የሆኑ ሰዎች "ኅብረት/ጉባኤ" ነው። ይህም ወገን ምርጥ ሕዝብና በዓለም ላሉ ሕዝቦች በሙሉ የመመስከር ተልእኮ ያለው ነው። ቁርአን እንዲህ ይላል፦—

> በእናንተ ላይ መስካሪ ይሆን ዘንድ ምርጥ ሕዝቦች አደረግናችሁ።
>
> (ሱራ 2÷143)[4]

ቤተ ክርስቲያን

ቤተ ክርስቲያን ማለት "ጉባኤ" ማለት ነው። በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት፣ ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል በግሪክ ቋንቋ "ኤክሌሲያ" ተብሎ ይጠራል። ይህም ለአንድ ዐይነት ዐላማ በአንድ ቦታ ተሰብስበው የተበተኑ የሰዎችን ኅብረት ያመለክታል። ቤተ ክርስቲያን ሁለት ሺህ ዓመት ገደማ የክርስቶስ የመጀመሪያ ደቀ መዝሙር የነበረው ጴጥሮስ፣ "አንተ ክርስቶስ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ ነህ" ሲል እንደ መሰከረው የሚመሰክሩ ሰዎች ስብስብ ናት (ማቴ 16÷16)። ምስክርነቱም የቤተ ክርስቲያን መሠረት ነው። በዓለም ዙሪያ ያሉ ቤተ ክርስቲያናት በሙሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታና አዳኝ እንደ ሆነ ይመሰክራሉ።

ሐዋርያው ጴጥሮስ ቤተ ክርስቲያንን፣ "ቅዱስ ሕዝብ" 1ጴጥሮስ 2÷9 ሲል ገልጾአታል። ዳሩ ግን በአዲስ ኪዳን፣ ልክ እንደ ሙስሊሙ ማኅበረሰብ ከፖለቲካ ወይም ከግዛታዊ ሥልጣን ጋር የተያያዘ አይደለም። ቤተ ክርስቲያን እንደ ቅዱስ ሕዝብ ከሌሎች ሕዝቦች መካከል ለድነት የተጠሩ ሰዎች ኅብረት ናት። ቤተ ክርስቲያን የሚለው ቃል ክርስቶስን ጌታና አዳኝ አድርገው የተቀበሉ ሰዎችን ሁሉ የሚጠቀልል ስም ሲሆን፣ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚቀላቀሉትም በኅጢአታቸው ንስሓ በመግባትና በመጠመቅ ነው። ትክክለኛ አማኝ መሆናቸውም ሆነ ከክርስቶስ አካል ጋር መቀላቀላቸው የሚታወቀውም በሕይወታቸው ከሚታዩት መንፈሳዊ ፍሬዎች ነው። የግዛትና የፖለቲካ

[3] ዝኒ ከማሁ፤ 213።

[4] የእንግሊዝኛው ቅጅ እንዲህ ይላል "Thus We have appointed you a middle nation, That ye may be witnesses against mankind" (Baqara [The Cow] 2:143).

የበላይነት አመለካከት፣ ከአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ባሕርይ ጋር የሚቃረን ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ቤተ ክርስቲያን በዓለም ሁሉ የእርሱ ምስክር እንድትሆን ተልእኮ ሰጥቶአታል። ወደ ሰማይ ከማረጉ ቀደም ብሉም የሚከተለውን ትእዛዝ አስተላልፎአል፦—

> እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠ መቃችኋቸው፣ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ (ማቴ 28÷19-20)።

ክርስቲያኖች ይህንን ትእዛዝ፣ "ታላቁ ተልእኮ" በማለት ይጠሩታል። ለሁለት ሺህ ዓመት ይህ መልእክት ቤተ ክርስቲያን ለዓለም ዐቀፍ የወንጌል ተልእኮ እንድትነሣሣ ወቢይ ምክንያት ሆኖአል።

ወንጌል መስካሪዎች ፖለቲካውን ወይም የሌሎችን ግዛት በመቈጣጠር አልመሰከሩም። ምስክርነቱም ሰዎችን በማስገደድ ላይ የተመሠረተ ሳይሆን፣ ምስክርነቱን የሰሙ ሰዎች በሚሰጡት አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ ውጤት ላይ መሠረት ያደረገ ነው። የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስን የድነት መልእክት በመቀበል በመሲሑ ያመኑ ሰዎች ኅብረት ናት።

ሕዝብና መንግሥት

ሕዝብና መንግሥት ዓለም ዐቀፋዊ ማኅበረሰብ አይደሉም። መንግሥታት የእግዚአብሔርን ሥልጣንና ልዕልና ሊቀበሉም ሆነ ላይቀበሉ ይችላሉ።

ይህ አባባል ለቤተ ክርስቲያን ወይም ለሙስሊም ኡማ አይሠራም። ሁለቱም የኅብረተሰብ ክፍሎች ለአምላክ የበላይነት ወይም ሥልጣን ይገዛሉ። በአሜሪካን የነጻነት በዓል ቀን ስለ ሃይማኖት ድርጅቶችና መንግሥት ግንኙነት የተመለከቱ ሁለት ትምህርቶች ሰምቻለሁ። አንደኛውን ትምህርት የሰማሁት ከሱኒ ሙስሊሞች መስጊድ ሲሆን፣ ሁለተኛውን ደግሞ ከጻግም መጥምቃውያን (ከሜኖናይት) ክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያን ነበር።

የሙስሊሞቹ ኢማም (መሪ) እንዲህ ሲል ተናገረ፣ "የአገር ፍቅር ጥሩ ነው፤ ነገር ግን ገደብ ሊኖረው ይገባል። ታማኝነታችንን ማሳየት ያለብን በመጀመሪያ ለሙስሊሙ ማኅበረሰብ ነው። ይህም ዓለም ዐቀፋዊ ኅብረት ሲሆን፣ ከአገራዊ ክልል ደግሞ ያልፋል"።

ክርስቲያኑ መጋቢም እንዲህ አለ፤ "የአገር ፍቅር የራሱ ስፍራ አለው፤ ነገር ግን ጥንቃቄ ያስፈልገዋል። ታማኝነታችን በመጀመሪያ ለክርስቶስና ለቤተ ክርስቲያን ነው። ቤተ ክርስቲያን በዓለም ዙሪያ ካሉ ሕዝቦችና ኅብረተሰቦች ውስጥ የተጠሩ ሰዎች ኅብረት ስትሆን ዓለም ዐቀፋዊም ናት"።

ስለቤተ ክርስቲያንና ስለሙስሊም ኡማ ታሪካዊ ጉዞ ከዚህ የበለጠ አስተያየት መስጠት ያስፈልጋል። ስለ ታሪካዊ ጉዞው ማጥናት የሙስሊሙና የክርስቲያኑን ማኅበረሰብ ነገረ መለኮታዊ አስተምህሮና ተልእኮ ለመረዳትና በዓለም ማኅበረሰብ ውስጥ ሁለቱም ቡድኖች እንዴት አብረው እንደሚኖሩ ለማወቅ ይረዳል።

ቤተ ክርስቲያን በሕዝቦች መካከል

በመጀመሪያ ስለቤተ ክርስቲያን ታሪክ በአጭሩ እንቃኝ። ቤተ ክርስቲያን "ወደ ዓለም ሂዱ፤ ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ" የሚለውን የክርስቶስን ትእዛዝ መሠረት በማድረግ፣ በዓለም ዙሪያ ሰፍታለች። በሐዋርያት ዘመንም ከስፔን እስከ ሕንድ፣ ከሰሜን አፍሪካ እስከ ማዕከላዊ አውሮፓ ባሉት ኅብረተሰቦች ውስጥ እጅግ ከፍተኛ ተቀባይነት በማግኘት መሠረቱን ጥሎ ነበር። ቤተ ክርስቲያን ፈጣን ዕድገት ያሳየችውም በመከራ ውስጥ ነበር።

አንዳንዴም የነገሥታት ቊጣ በቤተ ክርስቲያን ላይ ቦኅይል ይነድ ስለነበር፣ የተወሰኑ ሐዋርያት ተገድለዋል። ይህ ተቃውሞ የመጣው ለምን ይሆን? የተቃውሞው ምክንያት ክርስቲያኖች፣ "ክርስቶስ የሁሉ የበላይ ባለሥልጣን ነው" ብለው በመመስከራቸው ነው። የተለያዩ ግዛቶችና ሕዝቦች ለሚያመልኳቸው አማልክትና ለሚሰግዱላቸው ሮማውያን ነገሥታት፣ ክርስቲያኖች ለመስገድም ሆነ አምልኮ ለማቅረብ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው እንደ ከሐዲ ተቈጠሩ። ከዚህ የተነሣ ተሰደዱ። በሮማ ግዛተ ዐፄም ለዘጠኝ ዓመት (ከ303-312 ዓ.ም) በጣም ዘግናኝ የሆነ ስደትና እንግልት ደርሶባቸዋል።

የቁስጠንጢኖስ አሻራ በምዕራቡ ቤተ ክርስቲያን

ከዚያ በኋላ ስደቱ አበቃ። የሮማ ንጉሠ ነገሥት የነበረው ቁስጠንጢኖስ ከቤተ ክርስቲያን ጋር ሰላምን በመፍጠር በ313 ዓ.ም. የመቻቻል ዐዋጅ አወጣ። በዚህ መልኩ በወቅቱ የነበረው የክርስቲያኖች ስደት ፍጻሜ አገኘ። ቁስጠንጢኖስ ከዚህ ያለፈም ሥራ ሠርቶአል። የግዛቲቱ መሪዎች ወዲያውኑ ክርስቲያኖችን መደገፍ ጀመሩ፣ ንጉሡም በቤተ ክርስቲያን ጉዳዮች በመሳተፉ፣ በክርስቶስ ማንነት ላይ የነበሩ አንዳንድ ያልጠሩ ምልከታዎችን ለማጥራት የጳጳሳት ጉባኤ በ325 ዓ.ም ላይ በኒቂያ ሰበሰበ።

ስደት በዳርቻዎች አካባቢ

በምሥራቅ እስያ አካባቢ የነበረው ስደት ብዙ ክርስቲያኖችን ያወከ ነበር። ይህ ያለመረጋጋት ውሉ አድሮ ከእስልምና መስፋፋት ጋር ግንኙነት ነበረው። ይህ ምን ማለት እንደ ሆነ በተለይም በሮም ግዛቶች ድንበር አካባቢ ለነበሩ ክርስቲያኖች መረዳቱ ትልቅ ጠቀሜታ አለው። ከኒቂያ ጉባኤ በኋላ የሮም መንግሥትና የምዕራቢ ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳት፣ በቤተ ክርስቲያንና በመንግሥት መካከል ተገቢ ያልሆነ ግንኙነት እንዲመሠረት አደረጉ። ብዙም ሳይቆይ ጳጳሳቱ፣ ሰዎች የቤተ ክርስቲያንን አስተምህሮ እንዲቀበሉ የመንግሥትን ኀይል በመጠቀም ማስገደድ ጀመሩ።

በሰሜን አፍሪካ፣ በግብፅና በምሥራቃዊ እስያ ያሉት ቤተ ክርስቲያናት ለዚህ ችግር የተጋለጡ ነበሩ። ለምሳሌ በሰሜን አፍሪካ በበርበር ሕዝቦች ውስጥ ዶናቲዝም የሚባለው ቡድን ከማንም ነጻ በሆነ መንገድ ከቤተ ክርስቲያን ውጭ በራሱ እንቅስቃሴ የሚያደርግ ታዋቂ ቡድን ነበር። ይህች አገር በቀል የሰሜን አፍሪካ ቤተ ክርስቲያን፣ በሮም መንግሥትና በቤተ ክርስቲያን ጥምረት ስደት እንዲሁም መገለል ደርሶባታል። ሁኔታውን ለዚህ ያደረሱት ጉዳዮች ውስብስብ ነበሩ። የሐሰት አስተምህሮዎች የችግሮቹ አካል ነበሩ። የሆነ ሆኖ የግጭቱ ዋነኛ ምክንያት የሮም መንግሥትም ሆነ ቤተ ክርስቲያን፣ በሮም ግዛት ሥር ባሉ አካባቢዎች ከእነርሱ ትእዛዝ ውጪ ቤተ ክርስቲያን እንዲኖር አለመፈለጋቸው ነው[5]። በ7ኛው ክፍለ ዘመን የሙስሊሙ ጦር ወደ ሰሜን

[5] W. H. C. Frend, *The Early Church* (London: Hodder & Stoughton, 1971), 93, 164.

አፍሪካ ሲዘምት የገጠመው፣ የተጻከሙች ቤተ ክርስቲያን ነበር። ለቤተ ክርስቲያኒቱ መድከም ምክንያት የነበረው፣ ሁለት ምዕተ ዓመታት ቀደም ብሎ ክርስቲያን መንግሥት የነበረው የሮም መንግሥት፣ አገር በቀልና ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳድሩ ቤተ ክርስቲያናት እንዳይፈጠሩ በመከልከሉ ነው።

መሪር ስደት በፐርሽያ

የሮም መንግሥትና የምዕራብ አውሮፓ ጳጳሳት ጎብረት መፍጠራቸው፣ በምሥራቅ እስያ ባሉ ቤተ ክርስቲያናት ላይ ጉጂ ውጤት አስከትሏል። ከክርስቶስ ልደት በኋላ ባሉት ሦስት መቶ ዓመታት ስደት የነበረባቸው በሮም ግዛት ሥር የነበሩ ቤተ ክርስቲያናት ነበሩ። ነገር ግን የቁስጠንጢኖስ ክርስትናን መቀበልና የመንግሥትና የጳጳስ ጎብረት በምዕራብ በመፈጠሩ ምክንያት በምሥራቅ እስያ የነበሩት አብያተ ክርስቲያናት የአሳዳጆች ቀጣ ያርፍባቸው ጀመር። በቁስጠንጢኖስ ሥር ባለው በምዕራቡ ክፍል ክርስትና የመንግሥት ሃይማኖት በመሆኑ፣ ለምዕራቢ ቤተ ክርስቲያን የሰላም ዘመን ሆነ። የኢዶሳው ጳጳስ ማር ያዕቆብ ሲጽፍ እንዲህ ብሏል፣ "ቁስጠንጢኖስ የአሸናፊዎች መሪ ነገሠ፣ አሁን ደግሞ የንጉሡ መስቀል በዘውዱ ላይ ከፍ አለ"[6]።

በፐርሽያ ግን እንዲህ ዐይነት ደስታ አልነበረም፣ ምክንያቱም የፐርሽያ ቤተ ክርስቲያን በሁለት ግዛቶች በተፈጠረ ግጭት ተወጥራ ነበርና። ለሦስት ምዕተ ዓመት የፐርሽያና ዐልፎ ዐልፎ እርስ በርሳቸው የሮም ገዢዎች ይዋጉ ነበር። ቆይቶም ሌላ የጦርነት አደጋ ሲያንዣብብ። ቁስጠንጢኖስ ለፐርሽያው ንጉሥ ጻግማዊ ሻፑር፣ እንዲህ ሲል ጻፈለት፣ "ጥቂት በማይባሉ የፐርሽያ ክፍሎች ውስጥ ክርስቲያኖች እንዳሉ ሰሙ ደስ ብሎኛል...አንተ ጠንካራ ሃይማኖተኛ ስለሆንህ እንድትንከባከባቸው አሳልፌ ሰጠሁህ፤ በእንተም ጥበቃ ሥር ይሁኑ"[7]። ይህ ለፐርሽያ ንጉሥ ላሳሃ የላከው መልእክት አንድ ነው። ይኸውም፣ የዞሮአስትሪያን እምነት የምትከተለውን ፐርሽያን በስውር ለማፍረስ የተጉነጉኑ ሤራ እንዲሁም ክርስቲያኖች የሮም ዐላማ አስፈጻሚዎች ናቸው ማለት ነው።

[6] Samuel Hugh Moffett, *A History of Christianity in Asia: Beginnings to 1500*, vol 1 (Maryknoll, N. Y.: Orbis, 1998), 138.

[7] Theodoret, *Ecclesiastical History* 1, quoted in Moffett, 144.

ከሃያ ዓመት በኋላ ቈስጠንጢኖስ ከጳጳሳት ጋር በመሆን በፐርሹያ ላይ ጦሩን አዘመተ። በጊዜው የቤተ ክርስቲያን የታሪክ ጸሓፊ የነበረው አውሳብዮስ ጳጳሳት ቈስጠንጢኖስን ያጀቡት፣ "እግዚአብሔር ድል እንዲሰጠው በጸሎት ለመርዳት ነው" ሲል ጽፎአል[8]።

ከዚህ የተነሣ የፐርሹያውያን ቍጣ በክርስቲያኖች ላይ ያለ ልክ ነደደ። ከሃያ ዓመታት በላይ በፐርሹያ ግዛት ያሉት ክርስቲያኖች በረቀቀ ዘዴ ታደኑ፣ ተገረፉ፣ ተገደሉ። በዚህ ታላቅ ስደት የፐርሹያ ቤተ ክርስቲያን ወደ መጥፋት ደረሰች። ከዚያ በኋላም ስደቱ ካስከተለው ጥፋት ማገገም አልተቻለም።

በምሥራቅ አስያ የነበሩት ቤተ ክርስቲያናት

ይህ ዐይነቱ የነገሮች አካሄድ በምሥራቅ እስያ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን ወዲያውኑ ከምዕራብ ቤተ ክርስቲያን ራስዋን ማራቅ እንዳለባት ግልጽ አደረገላት። ቈስጠንጢኖስና እርሱን ተከትለው የተነሡ መሪዎች፣ ኋላም ቅዱስ የሮም ግዛት የምሥራቋ ቤተ ክርስቲያን የምዕራቢ ቤተ ክርስቲያን አካል ስለመሆኗ አቋሟን እንድትገልጽ ግፊት ተደርጉባታል። ምንም እንኳ ከምዕራባውያን ክርስቲያኖች ጋር አንድነቷን ብትገልጽም ንስጥሮሳውያን ክርስቲያኖች እንደ መናፍቃን ተቈጥረው ነበር[9]።

ጳሉ ግን አረንድ ቲኦዶር ቫን ሊወን የተባለው የደች የሃይማኖት ታሪክ ጸሓፊ፣ በቤተ ክርቲያን መካከል የነበረው ክፍፍል ለእስልምና መስፋፋት በር እንደ ከፈተ ይናገራል። እንዲህ ሲልም ጽፎአል፣ "እስላማዊ ጎይሎች...ከየትኛውም የክርስቲያን የመናፍቅ አስተምህሮ ቡድኖች በጣም በላቀ መልኩ ፀረ-ቢዛንታይን አስተምህሮ አሠራጭተዋል"[10]።

ሆኖም በምዕራቢ ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት ላይ ከነበረው የተቃውሞ መግለጫ የተነሣ፣ ሁሉም ክርስቲያኖች ወደ እስልምና አልተለወጡም።

[8] Eusebius, *Life of Constantine*, 4:56, quoted in Moffett, 138.

[9] Arend Theodoor van Leeuwen, *Christianity in World History, The Meeting of Faiths East and West*, translated from Dutch by H. H. Hoskins (New York: Charles Scribner's Sons, 1964), 210.

[10] ዝኒ ከግሁ፣ 211።

አንዳንድ ጊዜም የምሥራቅ እስያ ቤተ ክርቲያናት፣ ወንጌልን በማሠራጨት የራሳቸውን እምነት ተገቢነት ይገልጡ ነበር። ለአንድ ሺህ ዓመታት ያህል ሚስዮናውያንን ወደ ማዕከላዊው የእስያ ክፍል በመላክ የምሥራቹን ቃል አሠራጭተዋል። እነዚህ ጥቂት ቤተ ክርስቲያናት የመንግሥት እጀንዳ ያልያዘ የወንጌል ተልእኮ ፈጽመዋል። ከቈስጠንጢኖስ በኋላ ለመስፋፋት ሲባል ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት አብረው ከሚያዘጋጁት ሚስዮናዊ አገልግሎት ጋር ሲነጻጸር ከፍ ያለ ልዩነት ነበረው።

የምሥራቅ ቤተ ክርስቲያናት ሁሌም በቀኖር አነስተኛ፣ አብዛኛውን ጊዜ የሚሰደዱና አንዳንዴም እስከ መጥፋት የሚደርሱ ናቸው። ይሁንና ከእነዚህ ውስጥ የተወሰኑት ለአንድ ሺህ ዓመታት ያልተቋረጠ የወንጌል ሥርጭት እስከ ቻይና ድረስ በሚዘልቅ አገልግሎት ይሰጡ ነበር። እጅግ ትኩረት የሚስብ ታሪክ ነው። የፐርሹያ ቤተ ክርስቲያናት በሙስሊሞች ቀኖቶር ሥር ከወደቁም በኋላ፣ ለአምስት መቶ ዓመታት ለዓለም ሁሉ ወንጌልን ማሠራጨታቸውን ቀጥለዋል።

ከፍፍል በምዕራቡ ቤተ ክርስቲያን

ውሉ አድሮ ስለተፈጠሩት ክሥተቶች አጭር ዳሰሳ እናድርግ። በ1054 ዓ.ም የሮም ግዛት ምዕራቡ ክፍል ሮምና የምሥራቁ ክፍል ቢዛንታይን በመባል ለሁለት በመከፈሉ በቤተ ክርስቲያንም ክፍፍል ተፈጠረ። የምዕራቡ ቤተ ክርስቲያን መከፈል፣ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንና የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መፈጠር ምክንያት ሆኖአል።

ይሁን እንጂ እነዚህ የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት፣ የመንግሥትና የቤተ ክርስቲያን አንድነትን ለመጠበቅ ሞክረዋል። ስለዚህ የምዕራቢ ቤተ ክርስቲያን ሁል ጊዜ ራሷን እንደ መንግሥት ትቈጥራለች። ይህም ማለት ከቈስጠንጢኖስ በኋላ አብያተ ክርስቲያናት ካቶሊክ፣ ኦርቶዶክስ ወይም ኘሮቴስታንት በሚል ጐራ ቢከፈሉም መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን የተቈራኙ ተቋማት ነበሩ።

በዘመናችን የተከሠቱ ሦስት ኩነቶችን እንደ ምሳሌ ልጥቀስ፣ አንደኛ፣ የራሺያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳት ራሺያ በቼችኒያ ዐማፅያን ላይ ድል እንድታገኝ ጸልየዋል። ሁለተኛው፣ ክርስቲያን ሰርቦች ባልካንን ከሙስሊሞች ለማስወገድ ተዋግተዋል። ሦስተኛው፣ የአሜሪካ የወንጌላውያን አብያተ

ክርስቲያናት መሪዎች፣ በኢራቅ ላይ የተደረገው ጦርነት ፍትሐዊ በመሆኑ ክርስቲያኖች ድጋፍ ሊሰጡ ይገባል ሲሉ ተከራክረዋል።

በዘመናችንም እንኳ የምሥራቋ ቤተ ክርስቲያን ከምዕራቢ ቤተ ክርስቲያን ያላትን ግንኙነት በተመለከተ አቋሟን እንድትለይ የግድ ይሆንባታል። በትርቡ አሜሪካ የፀረ-ሽብርተኝነትን ዘመቻ እየመራች ትገኛለች። በዘመቻው የተሳተፉ እንደ አንዳንድ ክርስቲያኖች አነጋገር ከሆነ፣ የምሥራቋ ቤተ ክርስቲያን ከምዕራቢ ቤተ ክርስቲያን የተለየች መሆኗን ግልጽ እንድታደርግ የሚያደርጓት ናቸው። በዋሽንግተን ዲ. ሲ. የተቃጣው አደጋ አንዳንድ ጊዜ በምሥራቅ በሚገኙት ክርስቲያኖች ላይ ሲፈጸም የነበረ ነው። የቄስጠንጢኖስ ወይም የ11ኛው ክፍለ ዘመን የመስቀል ተዋጊዎች፣ የመስቀል ምልክት ይዘው ወደ ምሥራቅ ያደረጉት ወረራ ዛሬም ይታያል። የዘመኑ ቄስጠንጢኖሶች ወይም የመስቀል ጦርነት ተዋጊዎች፣ የምሥራቅ ቤተ ክርቲያናትን ለአደጋ እያጋለጡ ናቸው[11]። በሚሊዮን የሚቆጠሩ እስያውያን በምዕራባውያን አካሄድ ግራ ስለተጋቡ እስልምናን እንደ አማራጭ ለመቀበል እያሰቡ ናቸው።

አማራጭ መንገዶች

በምዕራቢ ቤተ ክርስቲያን ውስጥም በቄስጠንጢኖስ የተጀመረውን የቤተ ክርስቲያንና የመንግሥት ጎብረት የማይቀበሉ ክርስቲያኖች አሉ። ይህንን አማራጭ የሚቃወሙ ክርስቲያን ቡድኖች፣ ለምሳሌ የሰሜን አሜሪካ መጥምቃውያን ቤተ ክርስቲያናት በአሜሪካ ሕገ መንግሥት፣ መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን እንዲለያዩ የማይናቅ ሚና ተጫውተዋል።

በ16ኛው ክፍለ ዘመን በጎርቴስታንት ተሐድሶ የተፈጠሩ ጸጋም መጥምቃውያን (አናባፕቲስቶች) የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ለመሆን በጽናት ታግለዋል። እነዚህ ጎብረቶች በሕይወታቸው ሁሉ የክርስቶስ ደቀ መዝሙር የመሆን ራእይ ሰንቀው ነበር። የኢየሱስ እምነትንና ሥነ ምግባርን እንዲሁም ሰላምን የመፍጠር ጥሪን ጨምሮ ተግባራዊ ለማድረግ ሞክረዋል። እርግጥ ነው፣ ይህ ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት መለያየት አለባቸው ማለት ነው።

[11] Alex Awad, "Learning to Live with Muslims," *The Mennonite* (19 November 2002): 8-10.

ኡማውና ሕዝቦቹ

ከዚህ በመቀጠል የእስልምናን ታሪካዊ ጉዞ በአጭሩ እንመለከታለን። ከ610 ዓ.ም ጀምሮ ለዐሥራ ሁለት ዓመት መሐመድ በመካ እስልምናን ሰብከዋል። ከፍተኛ የሆነ ስደትም ገጥሞአቸዋል። በ622 ዓ.ም 250 ማይል በስተ ሰሜን ወደምትገኘው መዲና ከተማ መሐመድና ተከታዮቻቸው በድብቅ ተሰደዋል። ይህም ስደት (ሒጅራ) የሙስሊሞች አዲስ ምዕራፍ መጀመር ምልክት ሆኖአል።

ሒጅራ በጣም ጉልሕ ሚና ያለው ለምንድን ነው? ሒጅራ በጣም ወሳኝ ምዕራፍ የሆነበት ምክንያት፣ መሐመድ በመዲና ጠንካራ የሙስሊም ማኅበረሰብ በመመሥረት የነቢይነት አገልግሎታቸው እንዲቀጥል ስላደረጉ ነው። የሙስሎሙን ግዛት ለመመሥረት፣ ከጥቃት ለመከላከልና ወደ ተለያየ አትጣጫ ለመስፋፋት የሚያስችሉ ፖለቲካዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊና ወታደራዊ ተቋማትን አቋቁመዋል። በመዲና የነበረው መሠረት በጣም ውጤታማ ነበር። በዐሥር ዓመታት ውስጥ መካን ጨምሮ አብዛኛው የዐረቢያ ክፍል በሙስሊሞች ቁጥጥር ሥር ወድቋል።

መሐመድ ከመሞታቸው (632 ዓ.ም) በፊት ወደ ጉረቤት አገሮች ግለትም ወደ አቢሲኒያ፣ ፐርሺያና ቢዛንታይን መልእክተኞችን ልከዋል። መልእክተኞች የላከበትም ዐላማ፣ የእስልምና ግዛትን ከዐረቢያ ዐልፎ ወደ ጉረቤት አገሮች ለማስፋፋት ነበር። በተወሰኑ ዓመታት ውስጥ የሙስሊም ሰራዊት የዐረብያን ጠረፍ አካባቢዎች ተቆጣጠረ። የዘመናችን ሙስሊም ዐቃቤ እምነቶች (apologists) እነዚህ አካባቢዎች የተያዙት ራስን ለመከላከል ነው ይላሉ[12]፤ ልክ በቁርአን አንቀጾች እንደ ተገለጸው ማለት ነው፦—

> እነዚያንም የሚጋደሉዋችሁን (ክሓዲዎች) በአላህ መንገድ ተጋደሉ፤ ወሰንንም አትለፉ፤ አላህ ወሰን አላፊዎችን አይወድምና። ባገኛችኋቸውም ስፍራ ሁሉ ግደሉዋቸው፤ ከአወጧችሁም ስፍራ አውጧቸው፤ መከራም ከመገደል ይበልጥ የበረታች ናት፤ በተከበረው መስጊድም ዘንድ በርሱ ውስጥ እስከሚጋደሏችሁ ድረስ አትጋደሉዋቸው፤ ቢጋደሉዋችሁም ግደሉዋቸው፤ የከሓዲዎች ትጣት እንደዚህ ነው። ቢክዱለሉም አላህ መሓሪ አዛኝ ነው። አውከት እስከማይገኝና

[12] Badru D. Kateregga and David W. Shenk, *A Muslim and a Christian in Dialogue*, (Scottdale, Pa.: Herald Press, 1997), 108-9.

ሃይማኖት ለአላህ ብቻ እስከሚሸን ድረስ ተጋደሉዋቸው፣ ቢከለከሉም ወሰንን ማለፍ፣ በበጻዮች ላይ እንጂ የለም (ወሰን አትለፉባቸው) (ሱራ 2÷190-193 በትንፍ ያለውን ይጨምራል)።

ሆኖም ግን ከመሐመድ ሞት በኋላ የአስተዳዳር መዋቅሩን ለማጥራትና ለማጠ ናከር ሙስሊሞች ጥረት እያደረጉ በነበሩበት ወቅት፣ በሙስሊሞች መካከል የነበረውን ውጥረት በወታደራዊ ድሎች መሸፈን አልተቻለም። በመጀመሪያዎቹ ዘመናት ሙስሊሞችን እንደ ሙስሊም ማኅበረሰብ ማደራጀት በራሱ ትልቅ ፈተና ነበር። ከመሐመድ ሞት በኋላ በነበሩት 29 ዓመታት ምሪትን በትክክል ባገኙ መሪዎች (ካሊፎች) ሙስሊሞች ተመርተዋል። በእነዚህ ዘመናት የሙስሊሙ ማኅበረሰብ አስቸጋሪ የሆኑ ፈተናዎች ገጥመውት ነበር። የመጨረሻዎቹ ሁለት ከሊፋዎች ግለትም ኡስማንና ዓሊ ተገድለዋል።

ከዚያ በኋላ እስካሁን ድረስ ፈውስ ያላገኘው የሱኒና የሺአ ሙስሊሞች ክፍፍልና የእርስ በርስ ጦርነት ተከሠተ። ሺአ ሙስሊሞች የሙስሊሙን ማኅበረሰብ ሊመሩ የተገባቸው የመሐመድ ዘሮች ናቸው የሚል ጠንካራ አቋም ሲኖራቸው፣ በአንጻሩ ሱኒዎች ደግሞ መሪዎች መመረጥ ያለባቸው በሙስሊሞች ነው የሚል እምነት አላቸው። የሆኖ ሆኖ ምንም እንኳ በአስተዳደሩ ውስጥ ጠብ ቢኖርም እስከ ዓሊ ዘመን (661 ዓ.ም) የመካከለኛው ምሥራቅ በአጠቃላይ ማለትም ከግብፅ እስከ ፕርሻያ በሙስሊሞች እጅ ወድቋል።

ከመሐመድ ሞት በኋላ ባሉት ስድስት ዓመታት (638 ዓ.ም) ብቻ የሙስሊም ሰራዊት ኢየሩሳሌምን ተቆጣጥሮአል። ሙስሊሞች የሙስሊም ኡማ በዓለም ላሉ ሕዝቦች በሙሉ ምስክር ሊሆን ይገባል ብለው ያምናሉ። የሙስሊሙ ግዛት ለክርስቲያኖችና ለአይሁዶች ጉልሕ ሚና ወዳላት ከተማ (ኢየሩሳሌም) መዝለቁ ከሙስሊም ተልእኮ ጋር የሚስማማ ነው።

ከብ ጣሪያ ያለው መስጊድ (ሸል-ሸቅሳ)

ካሊፍ አብድ አል-ማሊክ በተልእኳቸው ውስጥ በራስ የመተማመን መንፈስ ስለነበራቸው በ691 ዓ.ም አንደኛውና ሁለተኛው የአይሁድ ቤተ መቅደስ በተሠራበት ቦታ ላይ ከብ ጣራ ያለው የድንጋይ መስጊድ አነጹ። መስጊዱ የተሠራውም ሃይማኖታዊ ጉዞ የሚደረግበት ቦታ እንዲሆን ታስቦ ነው። የሕንፃው ዲዛይን የሶሪያ ቤተ ክርስቲያንን ይመስላል። እስካሁን ድረስ ያለ

አስደናቂ ሕንፃ ነው። መስጊዱም በኢየሩሳሌም ከሚገኙ ቤተ ክርስቲያናት እንዲሁም ሕንፃዎች ከፍ ተደርጉ ተሠርቶአል። ሕንፃው በጥሩ ሁኔታ የተሠራ ሲሆን፣ በአሁን ጊዜ ከሚገኙ ሕንፃዎች ጥንታዊ የሆነ የሙስሊም ሕንፃ (መስጊድ) ነው።

ይህ መስጊድ የተሠራው ያለምንም ጥርጥር እስልምና ከአይሁድና ከክርስትና እምነት በላይ የላቀና የሚበልጥ መሆኑን ለማሳየት ነው። ይህም መስጊድ የተሠራው አል-አቅሳ (በጣም ሩቅ በሆነ ስፍራ) ሲሆን፣ መሐመድ በተአምራዊ ሁኔታ በአንድ ሌሊት ከመካ ወደ ኢየሩሳሌም ባደረጉት ጉዞ (ሚዕራጅ) ያረፉበት ቦታ ነው ተብሎ ይታመናል። ሙስሊሞች መስጊዱ ከተሠራበት ቦታ ቀጥታ ወደ ሰማይ በማረግ የነቢያዊ ተልእኮአቸውን እንዲቀጥሉና እንዲሰብኩ ከአላህ ዘንድ አበረታች መልእክትን ተቀብለዋል ብለው ያምናሉ። በመስጊዱ ውስጥ ተቀርጸው የሚገኙት ጽሑፎች እስልምና የአይሁድና የክርስትና እምነትን ይበልጣል እንዲሁም ይተካል የሚለውን የሙስሊሞችን እምነት ያሳያል[13]።

እስልምናና መሐመድን የሚያሞጋግሱ፣ ብዙ ጽሑፎች በመስጊዱ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ተጽፈው ይገኛሉ። ከጉልላቱ ሥር ከሱረቱ አል-ኒሳእ የተጠቀሰው እንዲህ ይላል:—

> "እናንተ የመጽሐፉ ሰዎች ሆይ! በሃይማኖታችሁ ወሰንን አትለፉ፣ በአላህም ላይ እውነት እንጂ አትናገሩ፣ የመርየም ልጅ አልመሲሕ ዒሳ የአላህ መልእክተኛ ወደ መርየም የጣለው (የኹን) ቃሉም ከእርሱ የሆነ መንፈስም ብቻ ነው፣ በአላህና በመልእክተኞቹም እመኑ፣ (አማልክት) ሦስት ናቸው አትበሉም፣ ተከልከሉ፣ ለእናንተ የተሻለ ይኾናልና፣ አላህ አንድ አምላክ ብቻ ነው። ለእርሱ ልጅ ያለው ከመሆን የጠራ ነው። በሰማያትና በምድር ያሉ ሁሉ የእርሱ ነው። መመኪያም በአላህ በቃ" (ሱራ 4÷171 በትንፍ ያለውን ይጨምራል)።

ክርስቲያኖች በሙስሊም አስተዳደር ሥር

የሙስሊም ገዢዎች ኢየሩሳሌምን መያዛቸው፣ በሙስሊም ሰራዊት ከተገኙት በርካታ አስደናቂ ድሎች መኻል አንዱ ነበር። ከሒጅራ አንድ መቶ ዓመታት

[13] Andrew Rippin, *Muslims: Their Religious Beliefs and Practices* (London: Routledge, 2002), 63-65.

በኋላ፣ የምድራችን ነዋሪ ከነበረው የክርስቲያን ኅብረተሰብ ውስጥ ግማሹ በእስልምና ቱጥጥር ሥር ውሏል። አሳዛኙ ገጽታ፣ ክርስቲያኖችና አይሁዶች ሙስሊሞን በሆኑ ክልሎች ውስጥ እንዲኖሩ የተደረገው፣ ከሌላው ኅብረተሰብ በተለየ ሁኔታ ጥበቃ እየተደረገላቸው መሆኑ ነው። ይህም አስተዳደራዊ አካሄድ "ዚሚ" ተብሎ ይጠራል። የሚቀጥለው ምዕራፍ በዚህ ጉዳይ ላይ ግብራሪያ ይሰጣል። የሙስሊም ሰራዊት የተቀሩትን አካባቢዎች ለመቈጣጠር፣ ወደ ምሥራቅና ምዕራብ ተንቀሳቅሷል። በአራት የትውልድ ዘመናት ውስጥ እስላማዊው አስተዳዳር፣ ከኢንደስ ወንዝ እስከ መካከለኛው ምሥራቅ እንዲሁም ሰሜን አፍሪካን አቋርጠ እስከ ስፔንና ደቡባዊ ፈረንሳይ ድረስ መሠረቱን ጥሎአል።

የክርስቲያኖች ቊጥር ከፊኛ መመናመን

ሙስሊሞች ለረጅም ጊዜያት በገዙባቸው አካባቢዎች ቤተ ክርስቲያናት ለሙስሊም ኡማ ታማኝነታቸውን እንዲያረጋግጡ በተደረገው እንቅስቃሴ፣ የክርስቲያኖች ቊጥር ከፉኛ ሊመናመን ችሎአል። እንዲያውም በየመን፣ በሰሜን አፍሪካና በሰሜናዊ ሱዳን የሚገኙ ጥንታዊ ቤተ ክርስቲያናት ሙሉ ለሙሉ ጠፍተዋል። የቤተ ክርስቲያናቱ መጥፋት በጥቂት ዓመታት ውስጥ የተፈጸመ ክሥተት ግን አይደለም። ቤተ ክርስቲያናት የሚደርስባቸውን ከፍተኛ ተጽእኖዎች በመቋቋም ለብዙ ዓመታት በክርስትናቸው ጸንተው ቆመዋል። ነገር ግን የማታ ማታ፣ የሰሜን አፍሪካ ቤተ ክርስቲያናትን ጨምሮ፣ ሰማዕት ሆነው የቆዩት እነዚህ ቤተ ክርስቲያናት በእስልምና ተጽእኖ ጠፍተዋል።

በጣም አስገራሚው ጉዳይ፣ እስልምና እነዚህን አካባቢዎች በሚቈጣጠርበት ወቅት፣ በየትኛውም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ በአገሬው (በአካባቢው) ቋንቋ አለመተርጉሙ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በራሳቸው ቋንቋ የነበራቸው ቤተ ክርስቲያናት ግን፣ ፈተናውን በጽናት ዘልቀው ዐልፈዋል። ከእነዚህም ውስጥ ግብፅ፣ ሶሪያና ኢትዮጵያ ይጠቀሳሉ። በተቃራኒው የሰሜን አፍሪካ ቤተ ክርስቲያናት፣ ወደ ላቲን የተተረጐመውን መጽሐፍ ቅዱስ ይጠቀሙ ነበር። የላቲን ቋንቋ የአውሮፓ ቅኝ ገዢዎች ቋንቋ ነው። ላቲን የሰሜን አፍሪካ ቋንቋ ባለመሆኑ ምክንያት፣ ቤተ ክርስቲያን አገር በቀል በሆነ መልኩ በኅብረተሰቡ ዘንድ ዘልቃ እንዳትገባ ማነቈ ከመሆኑም በላይ፣ ወንጌል በሰሜን አፍሪካውያን ባህልና አመለካከት ውስጥ ሰርጾ እንዳይገባ ደንቃራ ፈጥሮአል።

ከሥልጣኔ ጋር የተደረገ ግብግብ

በመጀመሪያዎቹ ዘመናት እስልምና ከወረቢያ ምድር ወደ ሌሎች አካባቢዎች የተስፋፋው ሥርዐትን በጠበቀ መልኩ ነው። የመስፋፋት ዘመቻው የተካሄደው ንብረትና ሕዝብን አውዳሚ በሆነ መልኩ አልነበረም። በተጨማሪም በኡማያድና በአባሲድ ሥርወ መንግሥት ወቅት የነበረው መስፋፋት፣ ሌሎችን የእምነት ቡድኖች ፈጽሞ በማጥፋት ላይ ያነጣጠረ ሳይሆን፣ ሌሎችን የማቀፍ መርሕ የተከተለ ነበር[14]። የአባሲድ ካሊፎች (ሥርወ መንግሥት) ወርቃማው የእስልምና ዘመን ተብሎ የሚጠራውን ከስምንተኛው እስከ ዐሥራ አንደኛው ምዕተ ዓመት ያሉትን ዘመናት መርተዋል። ታላላቅ የትምህርትና የባህል ማዕከሎች ናቸው የሚባሉት የክርስቲያኖች፣ የዕብራውያን፣ የግሪካውያን (የሔለኒዝም)፣ የአርመናውያን፣ የግብፃውያን እንዲሁም የአሲሮ-ባቢሎናውያን አስተምህሮ እስልምና በተስፋፋባቸው አካባቢዎች እንዲካተት ተደርጓል[15]።

የሙስሊሞች የአራት መቶ ዓመታት የበላይነት ዘመን፣ በተለይም በተለያዩ ዘርፎች ያስመዘገቡት የቴክኖሎጂ ዕድገት፣ ከዚያ በኋላ ላለው የእስልምና እንቅስቃሴ አስተዋጽኦ አድርጓል። አውሮፓውያን ወደ "ጨለማው ዘመን" ሲገቡ፣ በተቃራኒው ሙስሊሞች በራሳቸው በተጀመሩና በራሳቸው በሚመሩ የተለያዩ ጥናቶችና ምርምሮች ውስጥ ገብተዋል፤ ይህም የእስልምና ወርቃማ ዘመን ነው።

አስገራሚው ጉዳይ ግን እስልምና ሥር እየሰደደና እየተስፋፋ ሲመጣ፣ የምርምር ሥራውና ዕድገቱ እየጠፋ ሄደ። እንዲያውም በሙስሊሞች ተቀባይነት ሊኖራቸው የማይችሉ የጥናት ዘርፎችም ነበሩ። ከእነዚህም ውስጥ በቀደምትነት የሚጠቀሱት የግሪኮች የፖለቲካ ሥርዐት፣ ምርምርና ምክኒያዊ ፍልስፍና ናቸው። ከጊዜ በኋላ እነዚህ የጥናት ዘርፎች የምዕራባውያን ዕድገት መሠረቶች ሲሆኑ፣ ሙስሊም አገሮች ግን እንደ ተቃወሙት ኖረዋል[16]። ከሙስሊሞች ትምህርት ጋር የማይሄዱ ሌሎችንም የጥናት ዘርፎች አውድመዋል።

---

[14] H. A. R. Gibb, *Muhammedism* (New York: Oxford University Press, 1969), 3-5.
[15] Van Leeuwen, *Christianity in World History*, 254.
[16] Gibb, *Muhammedism*, 8.

ቫን ሊዌን እንዲህ ሲል አስተያየት ሰጥቶአል:—

> እስልምና የራሱን አሻራ እንደጠበቀና በትምህርቱ ይዘቶች ላይ መሠረታዊ ለውጥ ሳያደርግ በገዛቱ ሥር ባሉ ሌሎች ሥልጣኔዎች ላይ ውጫዊ የሆኑ ቅርፆቹን ሳይቀይር መዝለቁ የምስጢራዊ ጎይሉ አካል ነው[17]::

የእስልምና ምሑር የሆነው ኤች. ኤ. አር. ጊብ እንዲህ ሲል ጽፎአል:—

> ሁሉም የምርምር ዘርፎች በሃይማኖት ቁጥጥር ሥር እንዲወድቁ የተደረገው ትግል ለብዙ ምዕተ ዓመታት የዘለቀና ወደ ሌሎችም የሙስሊም ግዛቶች የተዛመተ ጉዳይ ነበር:: የምርምር ዘርፎችን ለማጠናከርና እንዲቀጥሉ ለማድረግ አንዳችም እንቅስቃሴ አልተደረገም:: የእስልምና ባህል የምርምሩን እንቅስቃሴ ሥር እንዳይሰድ ከማድረጉም በላይ፣ በገደብ እንዲንቀሳቀሱ በመፍቀድ ለራሱ መጠቀሚያ አድርጓቸዋል:: ጥቅም ላይ የሚያውላቸውን እንደ ሕክምና ምርምርና ሒሳብ የመሳሰሉ ሂደቶች ዕድገታቸው ተቀጨ፣ ወይም ጠፋ[18]::

ጊብ በመቀጠል:—

> የሳይንሳዊ ምርምሮችን ሰፍራ በአንድ ሆነ በሌላ መንገድ የወሰደው የነገረ መለኮት ጥናት አልነበረም:: ሙስሊሞች የሳይንሶች ሁሉ የበላይ አድርገው የሚመለከቱት የሕግ ትምህርት (የሸሪአ) ነው[19]::

ይህ እስልምና እያደገ ሲመጣ፣ የተለያዩ የሥልጣኔ ዘርፎች ክፉኛ እየተጻከሙ መምጣታቸውን የሚየሳይ ነው:: አንዳንድ ምሁራን በዚህ ጉዳይ ላይ የተለያየ አቋም ይዘው ይከራከራሉ:: ይሁን እንጂ፣ ትምህርትን በተመለከተ ግንኙውም የዕውቀት ዘርፍ በተገለጠው የአላህ ፈቃድ (ቁርአን) መቃኘት አለበት:: ከአላህ ዘንድ የተሰጠውም መመሪያ ግልጽ በሆነ መልኩ ከሸሪአ ሕግ ጋር እንዲስማማ ተደርጎ ተተርጉሞአል::

እስልምናና የምዕራቡ ዓለም

ሙስሊም አገሮችና የምዕራቡ ዓለም በመተማመን ላይ የተመሠረተ ግንኙነት መፍጠር አዳጋች ሆኖባቸዋል:: በቅጡ የሚያግባባ የጋራ መሠረትም ማግኘት ቀላል አልሆነላቸውም:: እነዚህ ቡድኖች በተደጋጋሚ እርስ በርሳቸው ይዋጉ

[17] Van Leeuwen, *Christianity in World History*, 255.

[18] Gibb, *Muhammedism*,9.

[19] ዝኒ ከማሁ::

ነበር:: በመጀመሪያዎቹ የእስልምና ዘመናት ሙስሊሞች ሰሜን አፍሪካን ተቆጣጥረው ቢዛንታይንንና ስፔንን ወግተዋል:: ከመሐመድ ሞት መቶ ዓመት በኋላ አውሮፓውያን ለሙስሊሞቹ አጸፋ በመስጠት በ732 ዓ.ም ደቡባዊ የፈረንሳይ ክፍል በሆነው በቱር ዐውደ ግንባር (Battle of Tours) ከሙስሊሞች ጋር ተዋግተዋል:: ከሦስት ምዕተ ዓመታት በኋላ በመስቀል ጦርነት (ክሩሴድ) "ቅድስቲቱ ምድር" በክርስቲያኖች እጅ ገባች::

በመጀመሪያው የመስቀል ጦርነት (ክሩሴድ) ኢየሩሳሌም በነበሩት ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ላይ የተፈጸመው የጅምላ ጭፍጨፋ ዘግናኝ ነበር:: ያኔ የተፈጸመው የጅምላ ፍጅት መቼም የሚዘነጋ አይደለም:: ስለ ሁኔታው ሊባኖሳዊው ጋዜጠኛ አሚን ማዕሉፍ እንዲህ ሲል ጽፎአል:—

> በሙስሊሙና በክርስቲያኑ ዓለም መካከል ያለው ጥላቻ የተጀመረው በመስቀል ጦርነት ጊዜ እንደ ሆነ ምንም ጥርጥር የለውም፣ እስከ ዛሬ ድረስ ዐረቦች ይህን ድርጊት አስገድዶ ከመድፈር የተለየ ተግባር አይደለም በማለት በቀጭት ያስቡታል[20]::

የመስቀል ጦርነት ከግጭቱ መገለጫዎች ውስጥ አንዱ ነው:: ባለፉት ዐሥራ አራት ምዕተ ዓመታት፣ በየጊዜው በምዕራባውያንና በሙስሊሞች መካከል ጦርነቶች ተካሂደዋል:: ከመስቀል ጦርነቶች በኋላ ሙስሊሞች በበቀል ስሜት ተነሣሥተው በመዋጋታቸው ጦርነቱ ወደ ምሥራቃዊ የአውሮፓ ክፍል ተዛምቶአል:: በ16ኛው ክፍለ ዘመን ቪየና ከተማ በሙስሊሞች ተከባ ነበር:: አብዛኛው አውሮፓም ለጦርነት ተንቀሳቅሶ ነበር:: አውሮፓ በዚህ ዐይነት ሁኔታ በነበረበት ጊዜ ነው የኘሮቴስታንት የተሐድሶ እንቅስቃሴ የተጀመረው:: አንዳንድ የተሐድሶ አራማጆች ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጋር በመተባበር አውሮፓን ከጥቃት ለመከላከል ወታደራዊ ድጋፍ ሰጥተዋል:: ማርቲን ሉተር ግን በነገሩ ላይ ያመነታ ነበር:: ክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያንን ወክለው መዋጋት አይችሉም፣ እንደ አገር ዜጋ ግን በጦርነቱ መሳተፍ ይችላሉ ብሏል[21]::

[20] Paul Crawford, "A Deadly Give and Take," *Christian History* 21, no. 2 (August 2002): 24.

[21] Gregory Miller, "From crusades to Homeland Defense" *Christian History* 21, no. 2 (August 2002): 31-34.

የዳግም መጥምቃውያን ምላሽ

የማርቲን ሉተር አቋም የመነጨው ክርስቲያኖች በሁለት መንግሥታት (በእግዚአብሔርና በምድራዊ መንግሥት) ውስጥ የሚኖሩ ናቸው ከሚለው አስተምህሮው ነው። ይሁንና ሁሉም ክርስቲያኖች የእርሱን እምነት አይጋሩም። ዳግም መጥምቃውያን ሁሉ፣ ሁለት መንግሥታት አሉ በሚለው ጉዳይ ላይ ቢስማሙም፣ ክርስቲያኖች ቅድሚያ መስጠት ያለባቸው ለእግዚአብሔር መንግሥት ነው ይላሉ። ክርስቶስ ከበቀል ይልቅ ፍቅርን ለጠላቶቹ ገልጦአል። ክርስቲያኖችም እንደዚሁ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል[22]።

ስለዚህ በአውሮፓ የፍርሓትና የጭንቀት ዘመን፣ ዳግም መጥምቃውያን ከቱርኮች ጋር በሚደረገው ጦርነት ለመሳተፍ ፈቃደኛ አልነበሩም፤ ምክንያቱም ለእነርሱም ክርስቶስ ሞቶላቸዋል የሚለው አቋማቸው ከሙስሊሞቹ ጋር እንዳይዋጉ አድርጓቸዋል። የዳግም መጥምቃውያን መሪ የነበረው ሚካኤል ሳትለር ከመገደሉ በፊት በዚህ ረገድ ያለውን አቋም ገልጾአል[23]። ክርስቲያኖች ቱርኮችን ሊወዱዋቸውና ወንጌልን ሊሰብኩላቸው እንጂ ሰይፍ ሊመዙባቸው በጭራሽ አይገባም ባይ ነው። ዳግም መጥምቃውያን ከጦርነት ይልቅ ሰላም ለመፍጠር በነበራቸው ጽኑ አቋም ምክንያት እንደ ከሐዲ ስለተቆጠሩ፣ በሰማዕትነት ማለፍ ግድ ሆኖባቸዋል። መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን የተቀላቀሉበትን የክርስቲያን ግዛት ተቃውመዋልና። መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን የተጸበሉበት ግዛት፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ግለት አይደለም ሲሉም ተከራክረዋል።

የምሰራባውያን ጣልቃ ገብነት

በሙስሊሞችና በምዕራባውያን መካከል የነበረው ፖለቲካና ወታደራዊ ሁኔታ ለተወሰነ ጊዜ ሚዛኑን ስቶ ነበር። ኋላ በ1683 ዓ.ም ቪየናን ለመያዝ በተደረገው የመጨረሻ ጦርነት፣ የሙስሊም ወታደሮች ወደ ኋላ አፈግፍገዋል። ከአንድ ምዕተ ዓመት በኋላ በ1798 ዓ.ም ናፖሊዮን ጦሩን በግብፅ አስፍሮአል። ይህ ክሥተት ከዚያ በኋላ ለሆኑ ዘመናዊ ክሥተቶች ሁሉ ወሳኝ ተግባር ነው።

[22] Cornelius J. Dyck, *An Introduction to Mennonite History* (Scottdale: Herald Press, 1993), 39, 57-59.

[23] Myron S. Augsburger, *Pilgrim Aflame* (Scottdale: Herald Press, 1967), 252-68.

በምሥራቅ አውሮፓ የሚደረጉ ጦርነቶች ከግዕከላዊው የእስልምና ግዛቶች በጣም የራቁ ነበሩ፣ ነገር ግን ግብፅ በጣም ቅርብ ነበረች። የምዕራባውያን ወደ መካከለኛው የእስልምና ግዛት መገሥገሥ ከሁለት መቶ ዓመት በፊት ናፖሊዮን ጀብደኛ ዘመቻ እስከ ፈጸመበት ጊዜ ድረስ ቆይቶአል።

የምዕራባውያን ምጣኔ ሀብትና ባህል መስህብና ጎይል የግግኙቱ ምክንያት ምን እንደ ሆነ ለሙስሊም አገሮች እንቈቅልሽ ነው። የሙስሊም ኡማ ተልእኮ በዓለም ላይ ምስክር መሆን ነው። ላለፉት በርካታ ዓመታት ግን ይህ ሲሆን አልታየም[24]። በዚህ ረገድ አንድ ምሳሌ ልጥቀስ፡— በምዕራባውያን ዩኒቨርስቲዎች ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ተማሪዎች፣ ራሳቸውን ዕድለኛ አድርገው ይቈጥራሉ። በተቃራኒው በሙስሊም ማኅበረሰብ ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ግን፣ ትምህርታቸውን በሙስሊም ዩኒቨርስቲዎች ለመከታተል ደስተኛ አይደሉም። የዚህ ችግር መንሥኤው ምንድን ነው?

ባህላዊ ጥያቄዎች በቀላሉ መልስ የሚያገኙ አይመስሉም። ፖለቲካዊና ወታደራዊ አካሄዶች የበለጠ አዋኪዎች ናቸው። ከናፖሊዮን ጊዜ ጀምሮ የሙስሊሙ ማኅበረሰብ በምዕራባውያን ተፅዕኖና ዛቻ ሥር ቆይቶአል። ሙስሊሞች ስለምዕራቡ ዓለም የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲኖራቸውና ራሳቸውን እንዲያገሉ የሚያደርግ ክሥተት በሌላ የታሪክ ዘመን በሙስሊም ክልል እምብርት ላይ ተፈጠረ[25]።

በ1917 ዓ.ም የአይሁዶችን የፍልስጥኤም ምድር የይገባኛል ጥያቄ የሚደግፍ የባልፎር መግለጫ በእንግሊዝ መንግሥት ታወጀ። ፍልስጥኤማውያንን በጉዳዩ ላይ ያማከራቸው ወገን አልነበረም። የኦቶማን ግዛት አንደኛው የዓለም ጦርነትን ተከትሎ በሽርሳይልስ (1919 ዓ.ም) ስምምነት ከአባልነት ተሰረዘ። ቀጥሎም አውሮፓውያን መካከለኛው ምሥራቅን ተቈጣጥረዋል።

በከማል አታቱርክ ወታደራዊ አመራር (1924 ዓ.ም)፣ ቱርክ የሱኒ ከሊፋትን በማስወገድ ዓለማዊ ሪፐብሊክ ሆነች።

[24] Bernard Lewis, *What went Wrong? Western Impact and Middle Eastern Response* (New York: Oxford University Press, 2002).

[25] ዝኒ ክግሁ፣ 1-63።

የእስራኤል መንግሥት በ1948 ዓ.ም ተመሠረተ። ይህ በመሆኑ ምክንያት፣ በተባበሩት መንግሥታት ዕርቅ አፈላላጊ ኮሚሽን ሪፖርት መሠረት፣ 750,000 ፍልስጥኤማውያን ከመኖሪያቸው ተፈናቅለዋል። ከዚያ በኋላ በ1967 ዓ.ም እስራኤል የኢየሩሳሌም፣ የዌስት ባንክ፣ የጋዛንና የጐላንን ተራሮች ተቈጣጠረች። ለብዙ ዓመታት እስራኤል የሲናን ባሕረ ሰላጤ ይዛ ቆይታለች። ከዚያም ደቡባዊ ሊባኖስንም ተቈጣጠረች፣ በመቀጠልም እስራኤል በፍልስጥኤማውያን ግዛቶች የሰፈራ ኘሮግራሞችን ማካሄድ ጀመረች። በ2002 ዓ.ም በተያዙት ግዛቶች ውስጥ፣ በመቶ አርባ የሰፈራ መንደሮች ውስጥ ለሁለት መቶ ሺህ እስራኤላውያን የመኖሪያ ቤቶች ተገንብተዋል።

በ1991 ዓ.ም በአሜሪካ የሚመራው የጎብረ ብሔሩ ጦር ለኩዌይት ነጻነት ወደ ኢራቅ ዘመተ። የአሜሪካ ጦር፣ የእስልምና እምብርት በሆነችው ሳውዲ ዐረቢያ ከዐሥር ዓመታት በላይ ቆይቶአል። እነዚህ ክሥተቶች በምዕራቡና በሙስሊሙ ዓለም መካከል ለተፈጠረው ቅራኔ የራሳቸው የሆነ አስተዋጽኦ አላቸው።

<u>አል-አቅሳ መስጊድ</u>

ነገር ግን ሙስሊሞች አል-አቅሳ ብለው የሚጠሩት በኢየሩሳሌም የሚገኘው መስጊድ፣ ከምንም በላይ ቅሬታውን አባብሶአል። በመግቢያው ላይ ስለ መስጊዱ አመሠራረት የተወሰነ ማብራሪያ ተሰጥቶአል። መስጊዱ የተሠራው በ7ኛው ክፍለ ዘመን ሲሆን፣ ለአንድ ሺህ ሦስት መቶ ዓመታት ሳይፈርስ በተራራው ላይ ቆይቶአል። ይሁንና ከ1967 ዓ.ም ጀምሮ ተራራው በእስራኤል ቊጥጥር ሥር ይገኛል።

መስጊዱን ማን ይቈጣጠረው የሚለው ጥያቄ መልስ እስካላገኘ ድረስ፣ በእስራኤልና በፍልስጥኤም መካከል ሰላም ማስገኘት አይቻልም። በሐምሌ 2000 ዓ.ም የአሜሪካው ኘሬዝዳንት ቢል ክሊንተን፣ ከፍልስጥኤም መሪ ያሲር አራፋትና ከእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ኢሁድ ባራክ ጋር ስብሰባ አድርገው ነበር። በሁለት ሳምንታት የካምፕ ዴቪድ ስብሰባቸው ስለ ኢየሩሳሌም የተነጋገሩ ሲሆን፣ ትልቅ ትኵረት የሰጡበት ጉዳይ የአል-አቅሳ መስጊድ ጉዳይ ነበር። ተሳታፊዎቹ ይህ ጉዳይ መፍትሔ ካገኘ ሌሎቹን ችግሮች መፍታት ቀላል ነው የሚል እምነት ነበራቸው።

በኢየሩሳሌም ያሉት አብያተ ክርስቲያናት በጉዳዩ ለመሳተፍ ቢጠይቁም በስብሰባው አልተጋበዙም። ክርስቲያኖቹ እንደ ሙስሊሞችና አይሁዶች መስጊዱ የቆመበት ስፍራ ቅዱስ ነው የሚል አቋም ስለሌላቸው ጉዳዩ ችግር የሚያስከትል ሆኖ አልተገኘም። ኢየሩሳሌም በክርስቲያኖች ዘንድ ትልቅ ስፍራ አላት። ነገር ግን ለሙስሊሞችና ለአይሁዶች የሆነችውን ያህል አይደለም። ምንም እንኳ ሦስቱም ተሳታፊዎች ሃይማኖታዊ ሕዝቦች ቢሆኑም፣ ይህን ስፍራ በተመለከተ አንዱ የሌላውን መንፈሳዊነት ለመስማት ዐቅም የለውም[26]። ከዚህ አስቸጋሪ ጉዳይ የተነሣ ድርድሩ ተደናቀፈ።

ከሁለት ወር በኋላ በመስከረም 28 ቀን ኤሪየል ሻሮን የቤተ መቅደሱን ስፍራ አንድ ሺህ በሚጠጉ የእስራኤል ወታደሮች ታጅበው ከጉበኙ በኋላ፣ በተቀደሰችው ተራራ ላይ ሉዓላዊነታችንን ማረጋገጥ እንፈልጋለን፣ "ለእኛ ቅዱስ ስፍራችን ናትና"[27]። በማለት መናገራቸው የፍልስጥኤማውያንን ኢንቲፋዳ (ዐመፅ) የሚያቀጣጥል ከብሪት ሆኖአል።

ከዓመት በኋላ መስከረም 11 ቀን 2001 ዓ.ም ሙስሊም ታጣቂዎች አውሮፕላኖችን በመጥለፍ በፔንታጉን፣ በዋሺንግተን ዲ. ሲ እንዲሁም በዓለም የገበያ ማዕከል ላይ ጥቃት አድርሰዋል። የአሜሪካ አስተዳደር ከጥቃቱ በኋላ በአሸባሪነት ላይ ጦርነት ዐውጇአል። የጥቃቱ ጠንሳሽና ፈጻሚ በአፍጋኒስታን የነበረው የታሊባን አስተዳደርና መቀመጫውን አፍጋኒስታን ያደረገው የአል-ቃይዳ ድርጅት እንደ ሆነ ተገመተ። በዓለም ዙሪያ ያሉ ሙስሊሞች ራሳቸውን መከላከል እንዳለባቸው ተሰማቸው። አንዳንድ ሙስሊሞች አሜሪካ ዘመናዊ የመስቀል ጦርነት እያካሄደች እንዳለች አመኑ።

ከመጋቢት 19 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ አሜሪካ በኢራቅ ላይ ጦርነት ዐወጀች። በመላው የመካከለኛው ምሥራቅ ክልል ቊጣ ተቀሰቀሰ። በአሜሪካ የሚመራውን ጦር የደገፉት የመካከለኛው ምሥራቅ ዐረብ መንግሥታት በተጠንቀቅ መቆም እንዳለባቸው አሰቡ። ብዙ ሙስሊሞች ጦርነቱን ምዕራባውያን፣ በእስልምናና በሙስሊም አገሮች ላይ የከፈቱት ጥቃት አድርገው ወሰደውታል።

---

[26] Charles M. Sennott, *The Body and the Blood, the Holy Land's Christians, and the turn of a new Millennium* (New York: Public Affairs, 2001), 323-26.

[27] ዝኒ ከማሁ፣ 334-35።

የመካከለኛው ምሥራቅ ክርስቲያኖች

በአሁኑ ዘመን የመካከለኛው ምሥራቅ ቤተ ክርስቲያናት ከምዕራቡ ቤተ ክርስቲያናት የተለየ አቋም እንዳላቸው በግልጽ እንዲያስታውቁ እየተገደዱ ነው። በቅርቡ በአሜሪካ መሪነት በሽብርተኝነት ላይ የሚደረገው ጦርነት እንዲሁም አንዳንድ ክርስቲያናት ጦርነቱን የመቀላቀላቸው ጉዳይ ጥያቄውን እያጉላው መጥቶአል። በዋሽንግተን ላይ ያነጣጠረው ጥላቻ በመካከለኛው ምሥራቅ በሚገኙ ክርስቲያናዊ ማኅበረሰቦች ላይ እየተንጸባረቀ መጥቶአል። ቄስጠንጢኖስም ሆነ የ11ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የመስቀል ጦርነት ተዋጊዎች፣ ወደ ምሥራቅ የዘመቱት የመስቀል ምልክት አንግበው ነበር። የዘመኑ ምዕራባውያን/ቄስጠንጢኖሶች ወይም የመስቀል ጦርነት ተዋጊዎች፣ የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናትን ለጥቃት አጋልጠዋቸዋል የሚል አስተሳሰብ አለ[28]።

በ20ኛው ክፍለ ዘመን፣ በመካከለኛው ምሥራቅ የተፈጠሩ ነውጦች ለክርስቲያኖች ቁጥር መመናመን አስተዋጽኦ አድርገዋል። በ1914 ዓ.ም በኦቶማን ግዛት የክርስቲያኖች ቁጥር ሃያ አራት ከመቶ (24%) ነበር። ይህ ግዛት የሚያጠቃልለው ቱርክን፣ ሶሪያን፣ ኢራቅን፣ ሊባኖስን፣ ፍልስጥኤምን/እስራኤልን፣ ዮርዳኖስንና ግብፅን ነበር። በ21ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ በእነዚህ አገሮች ያለው የክርስቲያኖች ቁጥር ወደ አራት በመቶ (4%) አሽቆልቁሉአል[29]።

ለክርስቲያኖች ቁጥር መመናመን ዋነኛው ምክንያት፣ በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ የኦቶማን ግዛት መፈረካከሱ ነው። የግዛቱ መውደቅ፣ አውዳሚ በሆነ ሁኔታ የእርስ በርስ ብጥብጥን አስከተለ። በአርሜንያ ክርስቲያኖች ላይ የተፈጸመው የጅምላ ጭፍጨፋ፣ እጅግ በርካታ ቁጥር ያለው የክርስቲያኖች ማኅበረሰብ እንዲጠፋ ምክንያት ሆኖአል። እነዚህም ክርስቲያኖች አውቃቂ በሆነ ሁኔታ ተገድለዋል፣ እንዲሁም ወደ ግሪክና ወደ ሌሎች የአርሜንያ ግዛቶች ተሰደዋል። ይህ የዘር ማጥፋት ወንጀል የተፈጸመው፣ የመካከለኛው ምሥራቅ ፖለቲካ በሙስሊሞች ኀይል ሥር በወደቀበት ጊዜ ነው። የኦቶማን ሙስሊም መንግሥት ሥልጣን ላይ በነበረ ጊዜ፣ ይህ ዐይነቱ ድርጊት ታይቶ አይታወቅም።

[28] Awad, "Learning to Live with Muslims," 8-10.

[29] Sennott, *The Body and the Blood*, 22.

ለክርስቲያኖች ቁጥር መመናመን ሌላኛው ምክንያት ክርስቲያኖች እስልምናን ለመቀበል የወሰዱት ምርጫ ነበር። ነገር ግን ኩቱርክ ጭፍጨፋ በስተቀር በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ክርስቲያኖች ከመካከለኛው ምሥራቅ ወደ ሌሎች አገሮች መፍለሳቸው እንደ ዋና ምክንያት ይጠቀሳል።

ፍልሰት በመካከለኛው ምሥራቅ ያለውን የክርስቲያኖች ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ እንዲቀንስ አድርጉአል። በተለይም በእስራኤል/በፍልስጥኤም ቁጥራቸው ክፉኛ ተመናምኖአል። በ1947 ዓ.ም በእስራኤል/ፍልስጥኤም የነበረው የዐረብ ክርስቲያን ቁጥር፣ በቤተ ክርስቲያን ቄጠራ ሃያ በመቶ (20%) ሲሆን፣ በእንግሊዝ መንግሥት ቄጠራ ደግሞ ዐሥራ ሦስት በመቶ (13%) ነበር። ከሃምሳ ዓመት በኋላ ማለትም በምዕተ ዓመቱ መጨረሻ ላይ የክርስቲያኖች ቁጥር ሁለት ከመቶ (2%) በታች ሆኖአል[30]። ዛሬ በእስራኤል/ፍልስጥኤም ካሉት የዐረብ ክርስቲያኖች ቁጥር ይልቅ፣ በሲድኒና በአውስትራሊያ የሚኖሩ የዐረብ ክርስቲያኖች ቁጥር የበለጠ ነው[31]።

የዮርዳኖሱ ንጉሥ ሀሰን፣ ከአንድ ክርስቲያን ጋዜጠኛ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ እንዲህ በማለት ተናግረዋል:— "ፍልሰቱ የሚያሳዝነኝ ብቻ ሳይሆን የሚያሳስበኝም ጉዳይ ነው። በዚህ ዓለም ውስጥ ክርስቲያኖች ሳይኖሩ የእምነት ብዝኃነት ይኖራል ብሎ ማሰብ እንዴት ይቻላል? ለእኛ እጅግ እውናዊ የሆነ አንገብጋቢ ጥያቄ ነው"[32]።

በአካባቢው የክርስቲያኖች ቁጥር እየቀነሰ መምጣቱ፣ የተለያዩ ሃይማኖቶች በአካባቢው የመኖራቸውን ጉዳይ አጣብቂኝ ውስጥ የሚያስገባ ነው። እነዚህ አካባቢዎች አንድ ዐይነት አመለካከት የሆነውን እስልምናን ወይም በእስራኤል አንዳንድ ግዛቶች ደግሞ የይሁዲ እምነትን እያንፀባረቀው ነው። የክርስቲያኖች ቁጥር መቀነስ፣ በአካባቢው የሚኖሩ ሌሎች ሰዎች ወንጌል የመስማታቸው ዕድል እየጠበበ መምጣቱን አመላካች ነው።

የክርስቲያኖች ቁጥር ክፉኛ ይመናመን እንጂ፣ ክርስቲያኖች በመካከለኛው ምሥራቅ ያላቸው ተጽእኖ እጅግ ከፍተኛ ነው። አገር በቀል የሆኑ

[30] ዝኒ ከማሁ፣ 22-23።

[31] ዝኒ ከማሁ፣ 252።

[32] ዝኒ ከማሁ።

የመካከለኛው ምሥራቅ ቤተ ክርስቲያናት፣ ለአካባቢው በመጸለይ እንዲሁም በሙስሊሞች መካከል እየኖሩ ወንጌልን የመመስከር ባህልን አዳብረዋል። አንዳንዶቹም በእስራኤልና በፍልስጥኤም መካከል እየተካሄደ ባለው የሰላም ሂደት ውስጥ እውናዊ ተሳትፎ እያደረጉ ነው። አንዳንዴም በአካባቢው በሚገኙ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናትና ምዕራባውያን በሆኑ ሚስዮናውያን እርስ በርስ በመተባበር አድናቆት የሚቸራቸው ዐይነት አገልግሎቶችን ይሰጣሉ። በእስራኤል የሚገኘው የናዝሬት ሆስፒታል የክርስቲያኖችን እውናዊ ተሳትፎ ከሚያመለክቱ በርካታ ናሙናዎች ወስጥ አንዱ ነው። በዚህ ሆስፒታል ክርስቲያኖች ለበርካታ ዘመናት ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ የክልሉን ጎብረተሰብ አገልግለዋል። በክልሉ፣ ከፍተኛ የሆነ የማስተማር ጥራት አላቸው የሚባሉ ትምህርት ቤቶችም የክርስቲያኖች የመሆናቸው ጉዳይ፣ ክርስቲያኖች በክልሉ ያላቸው ተጽእኖ በቀላል የሚገመት እንዳልሆነ የሚያሳይ ነው።

በቅርቡ እኔ ተሳታፊ በነበርሁበት የመስጊድ ውስጥ ውይይት፣ ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር ላይ የስድብን ቃል የሚናገሩ ሰዎች ናቸው የሚል ክስ በአንዳንድ ወገኖች ተሰንዝሮ ነበር። ይህ ክስ የውይይቱን መንፈስ ክፉኛ በረዘው። በመግባባት ላይ ተመሥርቶ የነበረውን ውይይት ያበላሸውን መንፈስ አንድ ፓኪስታናዊ መሐንዲስ እንዲህ በማለት ጭጋጉን ገፈፈው፣ "እኔ ባደግሁባት ፓኪስታን በጣም ጥሩ የሚባሉ ትምህርት ቤቶች የክርስቲያኖች ነበሩ። እነዚያ ክርስቲያን አስተማሪዎች በእነዚያ የክርስቲያን ትምህርት ቤቶች ባይኖሩ ኖሮ፣ እኔ መሐንዲስ ባልሆንሁ ነበር። እኔ ስለ ቤተ ክርስቲያንም ሆነ ስለክርስቲያኖች እምነት መቼም ቢሆን አንቋሸሼ የመናገር ዐቅም የለኝም"።

ክርስቲያኖች፣ ፓኪስታናዊው ሙስሊም እንደ ተናገረው ይህንን መልካም ምሳሌ አጥብቀው ሊከተሉ ይገባል። መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ሕይወትን የሚወድ፣ መልካም ቀኖችን ሊያይ የሚፈልግ፣ ምላሱን ከክፉ፣ ከንፈሮቹንም ተንኰል ከመናገር ይከልክል። ከክፉ ይራቅ፣ መልካምንም ያድርግ፣ ሰላምን ይፈልግ፣ ይከተላትም" (1ጴጥሮስ 3÷10-11) ሲል ያስተምራል።

ምዕራፍ ሁለት

ዐረባዊ ጅማሬ

እስልምና በዐረብ ምድር መስፋፋት በጀመረበት ወቅት፣ ክርስቲያኖች በተለያዩ የነገረ መለኮት ርእሰ ጉዳዮች ዙሪያ፣ እርስ በርስ ይወዛገቡ ነበር። ክርስቲያኖች የነገረ መለኮት እሰጣገባ ከሚፈጥሩባቸው ርእሰ ጉዳዮች መኻል፣ የሚከተሉት ቀዳሚውን ስፍራ ይወስዳሉ፦—

- "ድንግል ማርያም የአምላክ እናት ናት"
- "ይህ በፍጹም ሊሆን አይችልም! ሴት አምላክን እንዴት ትወልዳለች? ቅድስት ድንግል ማርያም የክርስቶስ እናት ነች!"

- "የእግዚአብሔር ልጅ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሞተ"
- "አምላክን መግደል በፍጹም አይቻልም! ስለዚህ በመስቀል ላይ የሞተው ሰው የሆነው ክርስቶስ ነው፣ መለኮታዊው ልጅ ኢየሱስ ግን አልሞተም፣ እግዚአብሔር ከሞት አስመልጦ ወደ ራሱ ወስዶታል"።

- "ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ *ሆኖአል*"
- "እንደዚያ ሳይሆን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ልጅ ስለሆነ፣ ከጊዜ በኋላ የእግዚአብሔር ልጅ *ለልሆነም*"

- "ክርስቶስ አምላክ ነው!"
- "ይህ በፍጹም ሊሆን አይችልም! አምላክ ክርስቶስ ነው!"

መሐመድ የተወለዱት፣ ክርስቲያኖች በተለያዩ የነገረ መለኮት ርእሰ ጉዳዮች በተለይ ደግሞ መሲሑን ኢየሱስ በተመለከተ የተለያየ አመለካከት ወግነው ይወዛገቡ ባነበሩበት፣ በ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ ነው። ክርስቲያኖች በእንዲህ ዐይነቱ ክርክር ውስጥ በነበሩበት ወቅት መሐመድ መወለዳቸው፣ እምነታቸውን በተመለከተ ግራ ለተጋቡ ክርስቲያኖች ትክክለኛውን መንገድ ለማሳየት እንደ ሆነ ሙስሊሞች ያምናሉ። ይህንኑ የሙስሊሞች እምነት ቁርአን እንዲህ ሲል ይገልጸዋል፦—

> ከነዚያም እኛ ክርስቲያኖች ነን ካሉት የጠበቀ ቃል ኪዳናቸውን ያዝን። በርሱም ከታዘዙበት ነገር ፈንታውን ተዉ፣ ስለዚህ እስከ ትንሣኤ ቀን ድረስ በመካከላቸው ጠብንና ጥላቻን ጣልንባቸው፣ አላህም ይሠሩት የነበሩትን ሁሉ

በእርግጥ ይነግራቸዋል። ...እናንተ የመጽሐፉ ሰዎች ሆይ! አብሳሪና አስፈራሪ አልመጣልንም እንዳትሉ፣ ከመልእክተኞች በመቋረጥ ጊዜ ላይ ሲሆን (ሕጋችንን) የሚያብራራ ኾኖ መልእክተኞችን በእርግጥ መጣላችሁ። አብሳሪና አስፈራሪም በእርግጥ መጣላችሁ (ሱራ 5÷14:19)።

የሙስሊሙ ማኅበረሰብ የጀመረው፣ ቤተ ክርስቲያን ከተቈረቈረች ከስድስት መቶ ዓመታት በኋላ ነው። በዚህ ምዕራፍ፣ እስልምና ሲጀመር የዐረብ ኅብረሰ ሁኔታ ምን ይመስል ነበር? በሙስሊሙ ማኅበረሰብ (ኡማ) እና በክርስቲያኖች ወይም በአይሁዶች መካከል የነበረው ግንኙነት ምን መልክ ነበረው? ነገረ መለኮትን በተመለከተ ሙስሊሞች ለክርስቲያኖች ማብራሪያ የመስጠት ኀላፊነት እንዳለባቸው የሚያምኑት ለምንድን ነው? የሚሉትን ርእሰ ጉዳዮች እንመለከታለን።

ለሙስሊሞች እንቅስቃሴና ለቀሩአን ተጽእኖ ያደረጉት ሃይማኖታዊ፣ ነገረ መለኮታዊና ባህላዊ ተጽእኖዎች የትኞቹ ናቸው? ይህ ለክርስቲያኖች ዋነኛ ርእሰ ጉዳይ ነው፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር ለቅዱሳን ሰዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊውን መገለጥ ሲሰጥ፣ ያሉበትን ታሪካዊ ዐውድ ባገናዘበ መልኩ ነው የሚለው መሠረታዊ እምነት በክርስቲያኖች ዘንድ ስላለ ነው። ነገር ግን በዚያን ጊዜ የነበረው ታሪካዊ ዐውድ፣ በእስልምና አስተምህሮና በቁርአን መልእክት ላይ ተጽእኖ አለው የሚለው አባባል በሙስሊሞች ዘንድ ተቀባይነት የለውም። ለዚህ ዐቢይ ምክንያቱ፣ የቁርአን መልእክት ከሰማይ በቀጥታ የወረደና ከማናቸውም ዐይነት ታሪካዊ ተጽእኖዎች በላይ ነው የሚል እምነት ስለለ ነው። ቁርአን በዚያን ጊዜ ለነበሩት ችግሮች የተሰጠ ወቅታዊ መፍትሔ አይደለም፣ "ከታሪካዊ ሁኔታ ጋር አንጻችም ግንኙነት የሌለው መገለጥ ነው"[1] (በምዕራፍ አምስትና ስድስት ላይ ይህን ጉዳይ በስፋት እንመለከተዋለን)። በቀጣይ አንቀጾች ግን ይህን የሙስሊሞችን አመለካከትና ስሜት ሳንዘነጋ በመሐመድ ዘመን የነበረውን የዐረብ ታሪካዊ ዐውድ እንዲሁም ይህ ሁኔታ በእስልምና ላይ ያለውን ተጽእኖ እንዳስሳለን።

በመሐመድ ዘመን የዐረብያ ሁኔታ

መሐመድ የተወለዱት እንደ ጉርጉሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር በ570 ዓ.ም በመካ ሲሆን፣ ዘመኑም የገዘሆን ዓመት ተብሎ ይጠራል። ዘመኑ፣ የገዘሆን

[1] Andrew Rippin, *Muslims: Their Religious Beliefs and Practices* (New York: Routledge, 2001), 236-38.

ዓመት ተብሎ የተጠራበት ምክንያት፣ ክርስቲያን የሆነው የኢትዮጵያ ጦር ዝሆኖችን እንደ ጦር ታንክ በመጠቀም፣ መካን ያጠቃበት/የወረረበት ዓመት ስለ ነበር ነው። ጦርነቱም በ6ኛው ክፍለ ዘመን፣ የዐረብን ምድር ከበው የነበሩ የክርስቲያኖችን የበላይነት ያረጋገጠ ሲሆን፣ በተቃራኒው ደግሞ የዐረብ ምድር ከዓለም ኅብረተሰብ የተገለለና ጓላ ቀር አካባቢ እንደ ሆነ ያመላከተ ነበር። ከዐረብያ በመለስ ያለው የዓለም ክፍል የነበረበትን የዕድገት ሁኔታ ጠንቅቀው ያወቁት ጥቂት የዐረብ መሪዎች፣ ዐረቦች ካደጉ ሕዝቦችና መንግሥታት ጋር እኩል የሚሆኑበትን ቀን በተስፋ ይጠባበቁ ነበር። በዝሆን ዓመት የሚወለድ ነቢይ ይህን ተስፋ እውን ያደርጋል የሚል እምነትም ነበራቸው። ይህ የዐረቦች ተስፋ በሚፈጸምበት ወቅት የዐረብያ ታሪካዊ ሁኔታ ምን ይመስል ነበር?

በዚያን ዘመን አራት ዐይነት የእምነት ቡድኖች በዐረቦች ምድር ነበሩ። እነርሱም፦— (1) የመድብለ አማልክት አምላኪዎች (2) የክርስቲያኖች (3) የአይሁድ እምነት ተከታዮች (4) በአንድ አምላክ የሚያምኑ ዐረቦች ናቸው።

ጃሂሊያ

"ጃሂሊያ" ከመሐመድ በፊት የነበረውን ዘመን የሚያመላክት ሲሆን፣ በእስልምናና በቁርአን ውስጥ ላሉ ትምህርቶች በምንጭነት ይጠቀሳል። ጃሂሊያ "የጨለማው ዘመን" የሚል ትርጓሜም አለው። ዘመኑም የአላህን መንገድ የሚያሳዩ ነቢያት የተላኩበት ዘመን እንደ ሆነ ቁርአን እንዲህ ሲል ይገልጸዋል፦— "ከእንተ በፊት ምንም አስፈራሪ ያልመጣላቸውን ሕዝቦች ታስፈራራ ዘንድ ከጌታህ በኾነ ችሮታ (ላክንህ)" (ሱራ 28÷46) በእነዚህ ዘመናት በዐረብ ምድር የመድብለ አማልክት አምላኪዎች በከፍተኛ ሁኔታ ተስፋፍተው ነበር። በጃሂሊያ ዘመን የጣዖት አምልኮ ማዕከል የነበረውም የመካ ከተማ ነው። አምልኮው በሚፈጸምበት በካዕባ ቤተ መቅደስ ውስጥ፣ "የተቀደሰው ድንጋይ" እየተባለ የሚጠራው ጥቁር ድንጋይ፣ በዚያ ስፍራ ተቀምጦ ነበር። ካዕባንና ዙሪያው "ሐራም" አካባቢ ተብሎ ይጠራል። "ሐራም" ማለት የተከለከለ ማለት ነው። ሐራም ተብሎ በተከለለው አካባቢ ሰላምን ሊያደፈርስ የሚችል ግንኙውም ዐይነት ተግባር መፈጸም በፍጹም የተከለከለ ነበር።

እርስ በርሳቸው ይዋጉ የነበሩ የዐረብ ጐሣዎችም፣ የሰላም ስምምነት ሲያደርጉ ስምምነቱን የሚፈጽሙት ወደ አማልክቶቻቸው ወደ ካዕባ በመምጣት ነበር። በዚህ ዐይነት መንገድ ሰላም ይመጣ ነበር፣ ምክንያቱም የሁለቱ ጐሣዎች አማልክት አብረው በካዕባ ውስጥ በሰላም ይኖራሉ ብለው ስለሚያምኑ ነው።

ቅዱስ ቤተ መቅደስ (ካዕባ) እና በዙሪያው ያሉ አካባቢዎች ሐራም ክልል ተብለው ስለሚጠሩ፣ ለብዙ ዓመታት የሰላም ቀጣና በመሆን ኖሮአል። የዐረብ ጐሣዎች ከሌሎች ጐሣዎች የሰላም ስምምነታቸውን ዳግም ለማደስ፣ ዓመታዊ የጸሎት ጉዞ ወደ ካዕባ ያደርጋሉ። አንዳንድ መረጃዎች፣ እያንዳንዱን ጐሣ የሚወክሉ አንዳንድ ጣዖታት በአጠቃላይ፣ 360 ጣዖታት በካዕባ ውስጥ እንደ ነበሩ ያስረዳሉ[2]።

መሐመድና ተከታዮቹ፣ ካዕባ የአምልኮ ስፍራቸው እንድትሆን ሲወስኑ፣ የሰላም ቀጠና እንደ ሆነች ከሙሉ ልባቸው አልተቀበሉም ነበር፤ ምክንያቱም ካዕባ በጣዖታት ተበክላለች የሚል አመለካከት ስለነበራቸው ነው። ይሁንና መካ በነቢዩ መሐመድ ቀጥጥር ሥር ስትወድቅ፣ በካዕባ የነበሩትን ጣዖታት በማጥፋት ካዕባን ከጣዖት አምልኮ ነጻ አድርገዋል። ኋላም ካዕባ ለአላህ አምልኮ የሚቀርብባት ቅዱስ ስፍራ እንድትሆን ለዩአት። ስለዚህም በመድብለ አማልክት አምላክያን የአምልኮና የሰላም ቀጣና ተብሎ ይጠራ የነበረው ስፍራ ማለትም ካዕባ፣ የአንድ አምላክ ማለትም የአላህ የሰላም ስፍራ ተብሎ ተጠራ። ይህም ማለት የመስጊዱ ሰላምና ዐረባዊ የሆነው የባህላዊው ሃይማኖት ሰላም ተቀላቀሉ ማለት ነው[3]።

የክርስቲያኖች መገኘት

በእስልምና አስተምህሮም ሆነ በቁርአን ውስጥ ላሉ መሠረተ እምነቶች በምንጭነት ከሚጠቀሱት ውስጥ፣ ክርስትና ሁለተኛውን ስፍራ ይይዛል። እንደማንኛውም የዐረብ ሕዝብ መሐመድ ስለክርስቲያኑ ማኅበረሰብ፣ በዐረብያ ዙሪያ ስላሉ ክርስቲያን ነገሥታትና ስለ ክርስትና እምነት ያውቁ ነበር። የክርስቲያኖችና የአይሁዶች የአስተሳሰብ፣ የአኗኗርና የእምነት ዘይቤዎች በዐረቦች የዕለት ተዕለት ኑሮ ውስጥ ይንጸባረቁ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ እንኳ ባይሆንም፣ ስለክርስትና እምነት በቃል ብቻ ሰምተው የክርስትናን እምነት ከተቀበሉ ክርስቲያኖች ጋር መሐመድ የቅርብ ግንኙነት ነበራቸው። በሙስሊሞችና በክርስቲያኖች መካከል ይህ ዐይነቱ ግንኙነት እንደ ነበረ ቁርአን የተወሰኑ ፍንጮችን ይሰጣል። ግንኙነቱ አንዳንዴ በመከባበር ላይ

[2] Badru D. Katerrega and David W. Shenk, *A Muslim and a Christian in Dialogue* (Scottdale, Pa.: Herald Press, 1997), 69.

[3] Kenneth Cragg, *Muhammad and the Christian: A Question of Responses* (Maryknoll, N.Y.: Orbis, 1984), 36.

የተመሠረተ ሲሆን፣ በሌላ ጊዜ ደግሞ አንደኛው ወገን ሌላኛውን ወገን በመንቀፍ ላይ ያተኩረ ነበር።

ሙስሊሞች የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት በተመለከተ፣ በክርስቲያኖች ዘንድ አለመግባባቶችና ውዝግቦች እንደ ነበሩ ያውቁ ነበር። ከላይ ለማየት እንደ ሞከርነው የእስልምና አንደኛው ተልእኮና ግብ ይህንን ግርታ በማጥራት ለክርስቲያኖች ስለክርስቶስ ማንነት ትክክለኛ የሆነውን ትምህርት መስጠት እንደ ሆነ፣ ሙስሊሞች ጠንካራ አቋም ነበራቸው።

በዚህ ዘመን ያለችውን የአፍሪካ ቤተ ክርስቲያን ስንመለከት፣ በሺህ የሚቆጠሩ ቤተ እምነቶችን እናገኛለን። ቤተ ክርስቲያናቱ ከሚሰጡአቸው ትምህርቶች ውስጥ የተወሰኑት፣ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ወጣ ያሉ ሲሆን፣ በአንጻሩ ደግሞ ሁሉም በሚስዮናውያን የተተከሉ ቤተ ክርስቲያናትን የሚያሒሱ/የሚተቹ ናቸው። ምናልባት የመጀመሪያው የሙስሊም ማኅበረሰብ በተወሰነ መልኩም ቢሆን የቀናው ክርስቲያናዊ እንቅስቃሴ ሒስ አቅራቢ እንደ ሆነ ማሰቡ በጣም የራቀ ይሆንን? ክርስቲያኖች፣ መሐመድን ከነቢያቶቻቸው እንደ አንዱ አድርገው አለመቀበላቸው ሙስሊሞችን የሚያስገርም ብሎም የሚያሳዝን ነገር ነበር።

የአይሁዶች መገኘት

ለሙስሊም ማኅበረሰብ (ኡማ) መፈጠር አስተዋጽኦ ካደረጉ አካላት መካከል በሦስተኛ ደረጃ የሚገኘው፣ የአይሁድ እምነት/ሕዝብ ነው። በእስልምና ሃይማኖትና በአይሁድ እምነት መካከል ጉልሕ መመሳሰሎች አሉ። ከመመሳሰሎቹ ውስጥ ጥቂቶቹ፣ እግዚአብሔር የፍጥረተ ዓለሙ ፈጣሪ ነው፣ እግዚአብሔር ቅዱሳት መጻሕፍትን ለነቢያቱ ሰጥቶአል፣ ነቢያትን ልኮአል፣ ለእግዚአብሔር/ለአላህ ሕግ መገዛት ይገባል የሚሉት ትምህርቶች ይገኙበታል። ይሁን እንጂ መሐመድ በተለይ በመዲና ከነበሩት አይሁድ የሚበዙቱ እንደ እግዚአብሔር ነቢይ አድርገው ስላልተቀበሏቸው ግዘናቸው አልቀረም። በመዲና፣ በሙስሊሞችና በአይሁዶች መካከል የነበረው ግንኙነት አንዱ ሌላውን በመንቀፍ ላይ ያተኩረ ሲሆን፣ ኋላም ግጭትን አስከትሎአል። የግጭቱ መንሥኤም አይሁዶች የሙስሊሞችን እንቅስቃሴ ለማዳከም እያሤሩ ናቸው የሚል ጥርጣሬ በሙስሊሞች ዘንድ ስለነበር ነው።

በተለይ በሙስሊሙ ማኅበረሰብ ጅማሬ ወቅት አይሁዶች የጉላ ሚና ቢኖራቸውም፣ ግንኙነታቸው ባመዛኙ ፍጥጫ የነገሠበት ነበር። በቁርአን ውስጥ

የሚገኙት ማኅበረሰባዊ ሕጎችና ማኅበራዊ ግንኙነቶችን በተመለከተ የይሁዲ እምነት ያለው አስተምህሮ የመመሳሰሉ ጉዳይ የሚያስደንቅ ነው።

በቱለር የነገረ መለኮት ትምህርት ቤት የእስልምና ሃይማኖት ምሁር የሆነው ዱድሌይ ውድቤሪ ስለ እስልምና እንትስቃሴ ሲናገር፣ እስልምና "የአይሁድ እምነት በድኅረ ክርስቶስ ዘመን ያለውን እምነት የሚመስል ሃይማኖት ነው" ይላል።

መሐመድ ከአይሁዶች ጋር ዕርቅ ለመመሥረት ያደርጉ የነበረውን ፍላጎትና ጥረት እርግፍ አድርገው የተውት፣ ነገሮች በዚህ መልክ እየተካረሩ በመሄዳቸው ነበር። ነገር ግን በሙስሊሞችና በአይሁዶች መካከል የነበረው ቅራኔ መፈታት ስላልተቻለ፣ መሐመድ የሃይማኖት ሥርዐቶች ለውጥ አደረጉ። በዚህም መሠረት ቀድሞ ወደ ኢየሩሳሌም አቅጣጫ ይሰገድ የነበረው ሶላት ወደ መካ እንዲዞር እንዲሁም በአይሁድ የሰንበት ቀን ወይም በክርስቲያኖች የአምልኮ ቀን (እሑድ) የነበረው የሙስሊሞች የአምልኮ ቀን፣ ወደ ዐርብ እንዲዞር ተደረገ። በሙስሊሞችና በአይሁዶች መካከል የነበረው ቅራኔ እየተባባሰ ሲሄድ፣ በአይሁድ የሥርየት ቀን የነበረው የሙስሊሞች ጾም፣ በወር ተራዝሞ ወደ ረመዳን ወር እንዲሸጋገር ተደረገ። ከእነዚህ ለውጦች በኋላ፣ ሙስሊሞች እምነታቸውን ከአይሁዶችና ከክርስቲያኖች እምነት በተለየ መልኩ እንዲደራጅና እንዲቀጥል ጥረት የማድረግ እንትስቃሴ ጀመሩ።

የአብርሃም አምነት

"ሐኒፍ" የተሰኘው የእምነት ቡድን፣ በዐረብ ምድር ከሚገኙት እምነቶች አንዱ ሲሆን፣ በእስልምና ውስጥ ትቶት ባለፈው አሻራ በአራተኝነት ይፈረጃል። የሐኒፍ እምነት አስተምህሮ ያተኩረው በፈጣሪ አንድነት ላይ ነው። አንዳንድ የሐኒፍ እምነት ተከታዮች፣ ስለአብርሃም በቂ ግንዛቤ የነበራቸው ሲሆን፣ የአብርሃምን አምላክ እንደሚያመልኩ ይገልጻሉ።

የመሐመድ የእምነት ጉዞ ከሐኒፍ እምነት ተከታዮች ጋር በእያሌው የተጣጣመ ነበር። የአብርሃምን አምላክ እናመልካለን የሚለው የሐኒፎች እምነትና አስተምህሮ በሙስሊሙ ማኅበረሰብ ውስጥ በስፋት ሲንጸባረቅ ይታያል። የሙስሊሙ ማኅበረሰብም እያደገ ሲመጣ፣ እስልምና ከአይሁድ እምነትና ከክርስትና የተለየ እንደ ሆነ፣ ነገር ግን እስልምና የአብርሃም እምነት ነው የሚል አስተምህሮ ማራመድ ጀመረ። በካዕባ የሚደረጉት ሃይማኖታዊ ሥርዐቶች፣ አብርሃም ወደ አላህ ቤት ያደረገውን ጉዞ ለማስታወስ እንደ ሆነ

ይነገራል። ታሪክ እንደሚያሳየን ዐረቦች የእስማኤል ዘሮች ናቸው። መሐመድም ከዚሁ የዘር ሐረግ የተገኘ ነው። ስለዚህ እስልምና ደብዝዞ የነበረውን የአብርሃም እምነት ዳግም ተመልሶ እንዲታደስ አደረገ። አብርሃም አላህ ልጁን መሥዋዕት እንዲያደርግ ባዘዘው ጊዜ በፍጹም ልቡ እንደታዘዘ ሁሉ፣ ሙስሊም የሚለውም ቃል የሚገልጸው፣ እንደ አብርሃም በፍጹም ልባቸው ለአላህ የሚታዘዙ ሰዎችን ነው።

ለእስልምና እንትስቃሴ አብርሃምና እስማኤል መንፈሳዊ አባቶች ተደርገው ከተወሰዱ በኋላ፣ እስልምናና አይሁድ የተለያዩ እምነቶች ሆነው ጉዞ ጀመሩ። በሙስሊሙ ማኅበረሰብ ዘንድ እስራኤል፣ "ለዓለም ሕዝቦች ብርሃን ናት" የሚል ስያሜ ተሰጥቶአታል[4]።

ከመሐመድ በፊት በነበሩት ዘመናት ስለአብርሃምና ስለእስማኤል ያለው ታሪክና አስተምህሮ፣ በዐረቦች መካከል በስፋት ተሠራጭቶ ይገኝ ነበር። ስለአብርሃምና ስለእስማኤል ለነበረው አስተምህሮ መስፋፋት አስተዋጽኦ ያደረጉት ደግሞ፣ የሐኒፍ እምነት ተከታዮች ናቸው። ይህ ለመሆኑ ከሚቀርበው ማስረጃ መኻል አንዱ፣ ሐኒፎች ስለአብርሃምና ስለእስማኤል ያስተምሩ ስለነበር እንዲሁም እምነታቸው የአብርሃም እምነት እንደ ሆነ አጠንክረው የሚናገሩ መሆናቸው ነው። በዚያን ጊዜ በዐረብ ምድር ዐረቦች የሚያመልኳቸው በርካታ አማልክት ቢኖሩም፣ ሐኒፎች ግን የሁሉ ፈጣሪ የሆነውን አምላክ (አላህን) ብቻ እናመልካለን ይሉ ነበር። መሐመድ አንድ አምላክ (አላህን) ከሚያመልኩ ሰዎች መካከል አንዱ ነበር። መሐመድ መጺና ይኖሩ የነበሩት አይሁዶች ነቢይነቱን አንቀበልም ሲሉ፣ እስልምና የአብርሃም እምነት ነው የሚለውን አመለካከት አጠናክሮ ቀጠለ[5]።

ቀደም ብለን እንደ ተመለከትነው የቫሂሊያ፣ የክርስትና፣ የአይሁድና የሐኒፍ እምነቶች ለሙስሊም ማኅበረሰብ (ኡማ) መፈጠርና መስፋፋት የየራሳቸው አስተዋጽኦ አድርገዋል። ስለዐረብ ምድርና ስለሙስሊም እንትስቃሴ በጥልቀት ማጥናት የሚፈልጉ ሰዎች፣ የፍሊኘ ሒይቲን [Philip K. Hitti, *History of the Arabs*, rev., 10th ed. (New York: Macmillan, 2002)] መጽሐፍ ቢያነቡ፣ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን ያገኛሉ[6]።

---

[4] W. Montgomery Watt, *Muhammad Prophet and Statesman* (New York: Oxford University Press, 1969), 117-118.

[5] Cragg, *Muhammad and the Christian*, 90.

[6] Philip K. Hitti, *History of the Arabs*, rev., 10th ed. (New York: Macmillan, 2002).

የጥናታችን ትልቁ ትኩረት የሙስሊም ማኅበረሰብና የቤተ ክርስቲያን ነገረ መለኮታዊ መሠረት ምን እንደ ሆነ መረዳት ስለሆነ፣ በመሐመድ ዘመን የነበረው የቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴ ምን እንደሚመስል መዳሰሱ ተገቢ ይሆናል።

የቤተ ክርስቲያን ሁኔታ

በሰባተኛው ክፍለ ዘመን በዐረብያ የጠረፍ አካባቢዎች ክርስትና መስፋፋት ጀምሮ ነበር። የደቡባዊ የመን ግዛት ነዋሪዎች፣ ክርስቲያኖች እንደ ነበሩ ይገመታል። ኢትዮጵያና ግብፅ የክርስቲያን አገሮች ሲሆኑ፣ መጽሐፍ ቅዱስ በራሳቸው ቋንቋ እንዲተረጉም አድርገዋል። በግብፅ መጽሐፍ ቅዱስ በሦስት የግብፅ ቋንቋዎች ተተርጉሞ ነበር። የፍልስጥኤም፣ የሶሪያና የመስጴጦምያ አብዛኛው ነዋሪ ክርስቲያን ነበር። በመስጴጦምያ የኢዶሳ መንግሥት ተከታታይነት ያለው የወንጌል ሥርጭት ወደ ፐርሺያና ወደ ቻይና ያደርግ ነበር። በዚህ መጽሐፍ ምዕራፍ አንድ ላይ በፐርሺያ ስላለችው ቤተ ክርስቲያን እንዲሁም በ4ኛው ክፍለ ዘመን በዚያ ስለነበረው ስደት ተመልክተን ነበር። ነገር ግን በዚያ ስፍራ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን፣ ዘገምተኛ ማኅበራዊ ግሳየት ጀምራለች። በኢዶሳ እንዳለችው ቤተ ክርስቲያን በፐርሺያ የምትገኘውም ቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያንን ወደ ሌሎች አካባቢዎች የምትልክ ቤተ ክርስቲያን ነበረች። በሚያደርጉትም የወንጌል ሥርጭት መካከለኛው እስያንና ቻይናን በወንጌል ለመድረስ ችለዋል።

ከዚህ በተጨማሪ በዐረብያ ምድር የክርስቲያኑ ማኅበረሰብ እንዲሁም ተበታትነው ይኖሩ የነበሩ ክርስቲያኖች ይገኙ ነበር። ዳሩ ግን በዐረብያ ክርስቲያኖች ይኑሩ እንጂ፣ በዐረብኛ ቋንቋ የተዘጋጀ መጽሐፍ ቅዱስ አልነበራቸውም[7]። ዐረቦች በዚህ ዐይነት ሁኔታ ውስጥ እንዳሉ ነበር መሐመድ የቁርአን መልእክት ከአላህ ዘንድ ተቀብያለሁ ያሉት (ሱራ 13+30-31: 36-39)። ይህ ከሥተት ለዐረቦች አስደናቂ ተአምርና ከዓለም ሥልጣኔ ወደ ኋላ ለቀረችው የዐረብ ምድር ታላቅ የምሥራች ነበር።

በሌላ አንጻር ደግሞ የክርስቲያኑ ማኅበረሰብ በነገረ መለኮታዊ ጉዳዮች በተለይም ደግሞ የክርስቶስ ባሕርያትን በተመለከተ ከፍተኛ ውዝግብ ውስጥ ነበር። ቤተ ክርስቲያናት ከመንግሥት ጋር ሊኖራቸው የሚገባው ግንኙነት ምን መልክ ይኑረው የሚለውን ጥያቄ ለመመለስም ጭንቅ ውስጥ ነበሩ።

[7] John P. Kealy and David W. Shenk, *The Early Church and Africa* (Nairobi: Oxford University Press, 1975), 168-88.

እነዚህ ሁለቱ ጉዳዮች ግለትም የክርስቶስ ባሕርያትና የቤተ ክርስቲያንና የመንግሥት ግንኙነት፣ የቤተ ክርስቲያን ቀዳሚ አጀንዳዎች ነበሩ። ከእነዚህ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ በክርስቲያኖች መካከል የነበሩት ችግሮች፣ በ7ኛው ክፍለ ዘመን በነበረው የሙስሊሞችና የክርስቲያኖች ማኅበረሰብ ላይ ተፅዕኖ ነበረው። ከዚህ በመነሣት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበሩ ችግሮች ለሙስሊም ማኅበረሰብ መፈጠር ያደረጉትን አስተዋጽኦና የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ከቤተ ክርስቲያን ጋር የነበረውን ግንኙነት ለመዳሰስ እንሞክራለን።

ኢየሱስ ማን ነው?

ከክርስቶስ ልደት በኋላ ባሉት ሦስት መቶ ዓመታት ውስጥ፣ የቤተ ክርስቲያን ዕድገት ተስፋ ሰጪ ቢሆንም፣ አመርቂ የሚባል ግን አልነበረም። አንዳንዴ ክርስቲያን ካልሆኑ ሰዎች የሚነሣው ስደት፣ የቤተ ክርስቲያንን ዕድገት ሲፈታተን ቆይቶአል። ነገር ግን እንደ ጉርጉሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር ከ313 ዓ.ም ጀምሮ በሮማ ግዛት የነበረውን ስደት የሚሽር ወሳጅ በመውጣቱ ምክንያት የስደቱ ዘመን ሊያበቃ ችሎአል። ብዙም ሳይቆይ የሮማ ባለሥልጣናት በግዛቲቱ የሚኖሩ ሰዎች ክርስትናን እንዲቀበሉ መስበክ ጀመሩ። በመሆኑም በብዙ ሚሊዮን የሚቈጠሩ ሰዎች ከጣዖት አምልኮ ወደ ክርስትና መጥተዋል። በዚህ ሂደት ውስጥ ቤተ ክርስቲያን በሚሊዮን ለሚቈጠሩ አዲስ አማኞች የሥላሴን አስተምህሮ የምታስተምረው እንዴት ነው? የሚለው ጥያቄ መልስ ማግኘት ያለበት ጉዳይ ነበር። ይህ እንዳለ ሆኖ የመጀመሪያዎቹ ቤተ ክርስቲያን ብዙ የክርስትና ቡድኖች ያሉባት ብትሆንም፣ የእምነት አቋሞችዋን በትክክል ማስቀመጥ እንዳለባት አሳስተዋለችም ነበር። ነገር ግን በ4ኛው ክፍለ ዘመን በሮማ መንግሥት ሥር የነበሩ አካባቢዎች የክርስትናን እምነት ሲቀበሉ፣ አንዳንድ ሰዎች ግን የሥላሴ አስተምህሮን በተመለከተ የነበራቸው አስተሳሰብ፣ የሥላሴ አስተምህሮ መድብለ አማልክትን (ጣዖታትን) ከማምለክ የሚለይ አይደለም የሚል ነበር። ከዚህ ችግር የተነሣ ክርስቶስ ማን ነው? የሚለው ጥያቄ በብዙዎች ዘንድ ለውይይት የሚቀርብ ርእሰ ጉዳይ ነበር።

ግብፅ ላይ በተካሄደው የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ላይ አርዮስ የተባለ ሰው የቤተ ክርስቲያን መጋቢዎችን፣ "ማመን ያለብን አንድን አምላክ ነው፣ ክርስቶስ መለኮታዊ የእግዚአብሔር ልጅ አይደለም" በማለት ስለተከራከራቸው መጋቢያኑ ክፉኛ መደናገጥ ጀመሩ። የአሪዮስ አስተምህሮ በክርስቲያኖች መካከል ስለክርስቶስ ግንኙነት ክርክር እንዲነሣ አደረገ። ክርክሩ በአጠቃላይ

በግብፅ ሕዝብ ይኸውም በገበሬዎች፣ ሽቀጥ በመንገድ ዳር በሚቸረችሩ ሰዎች፣ ዕቃ በግመል ጭነው ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በሚያጓጉዙ ሰዎች እንዲሁም በሌሎች ሰዎች ዘንድ የውይይት ርእስ ሆነ። በዛኛው ክፍለ ዘመን የአርዮስ ትምህርት ግብፅን ዐልፎ እንደ ሰደድ እሳት ወደ ሌሎች አካባቢዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ተዛመተ። ከጣዖት አምልኮ ወደ ክርስትና ለመጡ ክርስቲያኖች የአርዮስ ትምህርት የሥላሴን አስተምህሮ ለመረዳት የተሻለ አማራጭ ሆኖ ስላገኙት የአርዮስን ትምህርት መርጠዋል።

የሮማ ንጉሠ ነገሥት የነበረው ቈስጠንጢኖስ እንኳ ሳይቀር፣ በክርክሩ ተሳትፎአል። የሮም ንጉሥ የሁሉም አብያተ ክርስቲያናት ጳጳሳት በኒቂያ ተሰብስበው በክርስቶስ ማንነት ላይ እንዲነጋገሩና ውሳኔ እንዲያሳልፉ ሲያደርግ፣ ክርስቲያኖች በሙሉ ሊደነቁ እንደሚችሉ ማሰብ እንችላለን። የመደነቃቸውም ምክንያት ከጥቂት ዓመታት በፊት ማለትም እንደ ጉርጉሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር ከ303-312 ዓ.ም ላይ ቤተ ክርስቲያን በሮም መንግሥት ከፍተኛ ስደት ሲደርስባት ስለ ነበር ነው። እንደ ጉርጉሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር በ325 ዓ.ም ይኸውም ስደቱ ካበቃ ከ13 ዓመት በኋላ፣ ቈስጠንጢኖስ ሕጋዊ የሆነ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ በኒቂያ እንዲዘጋጅ አደረገ። በዚህ ጉባኤ ወደ ሦስት መቶ የሚደርሱ ጳጳሳት ተካፋዮች ነበሩ። ስብሰባው ለሦስት ወራት ያህል የተካሄደ ነበር። የቤተ ክርስቲያን ጉባኤው በክርስቶስ ማንነት ላይ በጥልቀት ከተወያየ በኋላ፣ ስለ ክርስቶስ ማንነት የሚከተለውን መግለጫ አውጥቶአል። "ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ከአምላክም አምላክ፣ ከብርሃንም ብርሃን፣ ከእውነተኛ እግዚአብሔር እውነተኛ እግዚአብሔር፣ የተወለደ ነገር ግን ያልተፈጠረ፣ ከአብ ጋር አንድ ዐይነት ባሕርይ ያለው ነው"[8]። ይህ የሃይማኖት መግለጫ የኒቂያ የሃይማኖት መግለጫ በመባል ይታወቃል።

አስልምናና የአርዮሳውያን አምነት

እየዋለ እያደር የአርዮሳውያን እንቅስቃሴ እየተጸከመ ሄደ። ቤተ ክርስቲያን በጉባኤ ኒቂያ መሠረተ እምነቷን ይፋ እንዳደረገችው ሁሉ፣ ቤተ ክርስቲያናት የአሪዮሳውያንን አስተምህሮ ሊቀበሉ አልቻሉም። በጣም የሚያሳዝነው ግን ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት አሪዮሳውያንን ለማጥፋት ጎይልን የመጠቀማቸው

[8] J. W. C. Wand, *A History of the Early Church to A.D. 500* (New3 York: Methuen & Co., 1965), 157.

ጉዳይ ነው። ይህ እንዳለ ሆኖ አሪዮሳውያን ስለ ክርስቶስ ማንነት ያላቸው አስተምህሮ፣ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ከሚያስተምሩት መሠረታዊ አስተምህሮ ጋር የሚጣጣም አልነበረም። ይህ ለአሪዮሳውያን እምነት መጸከም እንደ ዋነኛ ምክንያት የሚጠቀስ ጉዳይ ነው። ለጊዜው ብዙ ሰዎች ወደዚህ እምነት ቢሳቡም እንኳ፣ አስተምህሮው የወንጌልን እውነት ስለማይገልጥ የኋላ ኋላ እየከሠመ ሊሄድ ችሎአል።

አስገራሚው ጉዳይ ግን አርዮሳውያን ከተነሡ ከሦስት መቶ ዓመታት በኋላ የእስልምና እምነት ሊቈረቈር፣ ቁርአን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት የሚያስተምረው ትምህርት ከአርዮስ አስተምህሮ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሆኖ መገኘቱ ነው። በእስልምና ሃይማኖት ኢየሱስ ክርስቶስ (ኢሳ) የተከበረ ነው ቢባልም እንኳ፣ ኢየሱስ የእግዚአብሔር መገለጥ ነው የሚለው የክርስቲያኖች እምነት በሙስሊሞቹ ዘንድ ተቀባይነት የለውም። ሙስሊሞች የኢየሱስን መሲሕነት ቢቀበሉም፣ የእግዚአብሔር ልጅ ነው የሚለውን ጉዳይ አጥብቀው ይቃወማሉ። ስለዚህ የአርዮስ አስተምህሮ ከቤተ ክርስቲያን ቢወገድም፣ የእስልምና እምነት ከአርዮስ ትምህርት ጋር ተመሳሳይ የመሆኑ ጉዳይ፣ የአርዮስ አስተምህሮ መልኩን ቀይሮ ተገለጠ ማለት ይቻላል።

ኢየሱስ ክርስቶስና ፈሳስፎች

የአርዮስ አስተምህሮ በተነሣበት ዘመን፣ ቤተ ክርስቲያንን የሚያውክ ሌላ የነገረ መለኮት ውዝግብ ተነሥቶ ነበር። ቀደም ብለን እንደ ተመለከትነው የአርዮስ ትምህርት ክርስቲያኖች የመድብለ አማልክት አምላክያን ናቸው ለሚለው ትምህርት ምላሽ ነበር። ነገር ግን ከዚህ እንቅስቃሴ በኋላ በግሪክ የተነሣው አዲሱ አፍላጦናዊነት፣ መንፈስ ሠናይ (ጥሩ) ሲሆን ሥጋ (ቀሊስ አካል) ግን እኩይ (ክፉ) ነው የሚል ነበር። ምንም እንኳ ይህ ትምህርት በስፋት የተሠራጨ ቢሆንም፣ አንዳችም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት አልነበረውም።

እነዚህ ፈሳስፎችም ስለ ክርስቶስ እንዲህ ሲሉ ይጠይቁ ነበር፣ "ሠናይ እንዲሁም መንፈስ የሆነው እግዚአብሔር፣ ሰው ከሆነው ከናዝሬቱ ኢየሱስ ጋር እንዴት አንድ ሊሆን ይችላል? ዘላለማዊ መንፈስ የሆነ አምላክ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ እንዴት ሊሞት ይችላል?"። ከእነዚህ ክርክሮች የተነሣ እንደ ጉርጉሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር በ451 ዓ.ም በኬልቄዶን የተካሄደው ጉባኤ እንዲሁም ሌሎች መሰል ጉባኤዎች በዚህና ይህን መሰል በሆኑ ርእስ ጉዳዮች

ላይ ትኩረት ያደረጉ ነበሩ። ይህ ወቅት ለቤተ ክርስቲያን ፈታኝ ወቅት ነበር።
ቤተ ክርስቲያን በእነዚህ ችግሮች ውስጥ እንዳለች፣ በእስያ ያሉት የምሥራቅ ቤተ ክርስቲያን አማኒያን በመንግሥት ከምትደገፈው ከምዕራቢ ቤተ ክርስቲያን ራሳቸውን ለማግለል ወሰኑ። ከዚያ በኋላ የንስጥሮሳውያን አስተምህሮ በምሥራቋ ቤተ ክርስቲያን ሥር እየሰደደና እየተጠናከረ መጣ። ይህም በምዕራብ ለሚገኘው የክርስትና አስተምህሮ አማራጭ ትምህርት ሆኖ ቀረበ።

ጳጳስ ንስጥሮስ ድንግል ማርያም የክርስቶስ እናት እንጂ፣ የአምላክ እናት መባል የለባትም የሚል ሐሳብ አቀረበ። ይህም ሐሳብ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ረጅም ክርክር እንዲነሣ አደረገ። በምሥራቅ የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት፣ ጳጳሳትና መንግሥት በአንድነት ከሚሠሩባት ከምዕራቢ ቤተ ክርስቲያን ጋር ልዩነት እንዳላቸው አስታወቁ። ልዩነቱ አስተምህሮአዊና፣ አስተምህሮአዊ ባልሆኑ ርእሰ ጉዳዮችም ላይ እንደ ሆነ ይፋ አደረጉ። ከእነዚህም ውስጥ አንዳንድ የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት የንስጥሮስን አስተምህሮ ተቀብለዋል[9]።

በሰባተኛው ክፍለ ዘመን ሙስሊሞች የምሥራቁንና የምዕራቡን ክርስቲያን ግዛቶች ሲቈጣጠሩ፣ በክርስትና ውስጥ ያሉትንና ያወዛግቡ የነበሩትን የነገረ መለኮት ርእሰ ጉዳዮች ለማብራራትና ሰላምን ለማውረድ ተልእኮ እንዳላቸው ይገልጹ ነበር። እነዚህ ሙስሊሞችም የሥላሴ አስተምህሮ ስሕተት መሆኑን፣ ክርስቶስ፣ ሰው እንጂ አምላክ እንዳልሆነ፣ በመስቀል ላይ ተሰቅሎም እንዳልሞተ፣ ሊሞትም እንደማይችል ይገልጹና ይከራከሩ ጀመር።

ቀስ በቀስ ብዙ ክርስቲያኖች ይህ የሙስሊሞች አስተምህሮ ትክክል እንደ ሆነ ተቀበሉ። በሰሜን አፍሪካና በመካከለኛው ምሥራቅ የሚኖሩ አብዛኞቹ ሙስሊሞች የዘር ሐረጋቸውን ስንቈጥር እንዝላቶቻቸውና እንጅላቶቻቸው በአንድ ዘመን ክርስቲያኖች የነበሩ ናቸው። ክርስቲያኖች ወደ እስልምና እንዲቀየሩ ያደረጋቸው፣ የእስልምና እምነት አስተምህሮዎች ክርስቲያኖችን የሚስቡ ስለሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ በሙስሊም ግዛቶች ውስጥ የሚኖሩ ክርስቲያኖች የእስልምናን ሃይማኖት እንዲቀበሉ ጫና ይደረግባቸው ስለ ነበር ነው።

[9] Ibid., 223.

በሰው በይን የማይሞላ እምነት

የክርስትና እምነት እንቅስቃሴ የጀመረው፣ ዝቅተኛ ኑሮ ከሚኖሩ ሰዎች መካከል ነው። በናዝሬት ከተማ የምትኖር ድንግል፣ በግርግም የተኛ ሕፃን፣ መንጒቻቸውን በኩረብቶች አካባቢ የሚያሠማሩ እረኞች፣ ከምሥራቅ የመጡ የከዋክብት ተመራማሪዎች፣ ወደ ግብፅ የተሰደደ ቤተሰብ፣ ከኢየሩሳሌም ውጪ በኩረብታ ላይ ያለ መስቀል፣ ዓሣ ያጠምዱ የነበሩትን ደቀ መዛሙርት በሐይቅ ዳር ያገኘ የትንሣኤ ጌታ። እነዚህ ሁሉ ከሥተቶች የተፈጸሙት በሰው ዐይን እዚህ ግቡ በማይባሉ ሰዎች እንደ ሆነ ሁሉ፣ ቤተ ክርስቲያንም እንደዚህ ዐይነቱን የጎብረተሰብ ክፍል በወንጌል በመድረስ ወንጌል በሰው ሕይወት ውስጥ የሚያስከትለውን መለኮታዊ ኀይል በማሳየት ታላቅ ተሐድሶን አምጥታለች። ነገር ግን በንጉሥ ቈስጠንጢኖስ አማካይነት የተከሠደው ለውጥ፣ በምዕራቢ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙ ጳጳሳት በማኅበረሰቡ ውስጥ እጅግ ትልቅ ሥልጣን እንዲኖራቸው አድርጉአል። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ቤተ ክርስቲያን ዝቅተኛ ከሚባለው የማኅበረሰብ ክፍል ተነሥታ፣ የሥልጣን ማዕከል ወደ መሆን እንዲሁም የነገሥታትን ሥልጣን ጠባቂ ወደ መሆን ተሸጋግራለች።

በተመሳሳይ ሁኔታ እስልምናም ያቈጠቈጠው ዝቅተኛ ከሆነ የማኅበረሰብ ክፍል ነው። የዐረቡ ዓለም የነይል የበላይነት ያልነበረውና በሠለጠኑት የጒረቤት መንግሥታት ክፉኛ የሚናቅ አካባቢ ነበር። ከእስልምና በፊት ዐረቦች ትኩረት የተሰጣቸው ሕዝቦች አልነበሩም። የሙስሊሙ ኅብረተሰብ ጠንክሮ ለዓለም ሕዝቦች ሁሉ ምስክር እንዲሆን ያደረገው የአላህ ቸርነት እንደ ሆነ ሙስሊሞች ያምናሉ።

ሙስሊሞች፣ ከአነስተኛና ከተናቀ የዐረብ ጐሣ የተነሣው የሙስሊሙ ማኅበረሰብ (ኡማ) በተከፋፈሉት ክርስቲያኖችና አይሁዶች መካከል ሰላምን የማምጣት ተልእኮ ከፈጣሪ ዘንድ እንደ ተሰጠው ጠንካራ እምነት ነበራቸው። ኡማው፣ በወቅቱ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ክርስቶስን አስመልክቶ ይካሄዱ የነበሩትን እሰጣገባዎች የመፍታት ተልእኮ አለው የሚል እምነት በሙስሊሞች ዘንድ አለ። ሙስሊሞች የዓለም ማኅበረሰብን በተመለከተ ትልቅ ራእይ እንዳላቸው ያምናሉ። ሙስሊሞች፣ የነቢያት መደምደሚያ በሆኑ፣ ፊደል ባልቈጠረውና ያለወላጅ ባደገው መሐመድ አማካይነት የተጀመረው ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴ፣ ለዓለም ሕዝቦች ሁሉ የቁርአንን እውነት የመመስከር ኀላፊነት ከአላህ ዘንድ እንደ ተሰጠው ይናገራሉ። በሌሎች ሕዝቦች ዘንድ ተንቆ የነበረውም የዐረብኛ ቋንቋ፣ አላህ የመጨረሻውን መገለጥ ያስተዋወቀበት ቋንቋ እንደ ሆነ ሙስሊሞች ያምናሉ። በሙስሊሞች

አመለካከት በሌሎች ሕዝቦች የተረሱት ዐረቦች፣ አላህ ለዓለም ሁሉ ሕዝብ የሚሆን መልእክት በእነርሱ በኩል ልኳል የሚል ጽኑ እምነት አላቸው።

ለሁሉ ቦታ የሚሆን እምነት

ሙስሊሞች የእስልምና ሃይማኖት በዓለም ላሉ ሕዝቦች ሁሉ የሚሆን እምነት እንደ ሆነ ያምናሉ። ከዚህ የተነሣም ሙስሊሞች፣ ሰዎች የእስልምናን ሃይማኖት እንዲቀላቀሉ ጥሪ ከማቅረብ ባለፈ፣ እስልምናን የተቀበሉ በአላህ አገዛዝ ሥር መኖር እንደሚጀምሩ ይናገራሉ። በእስልምና ሃይማኖት የምስክርነት አገልግሎትና የግዛት ጥያቄ አብረው የሚታዩ ጉዳዮች ናቸው። በሙስሊሞች አመለካከት የአላህ መገለጥ (ቁርአን) የአላህን ፍጹም ፈቃድ የሚያስታውቅ ስለሆነ፣ እስልምና አንድን አካባቢ ሲቈጣጠር በአካባቢው ያሉ ሕዝቦች ሁሉ በአላህ መንግሥት ቀጥተኛ ሥር እንደ ሆኑ ይታሰባል። የእስልምና ቀዳማይ ተልእኮ ፍጽምናን በማጎበረሰብ ውስጥ ማስረጽ ነው። ይኸውም እስልምና—ፍጹም ሃይማኖት፣ ቁርአን—ፍጹም የሆነ የአላህ መገለጥ፣ መሐመድ—ፍጹም ሰው፣ የሸሪአ ሕግ—ፍጹም የሆነ መሪ እንዲሁም የሙስሊም ኡማ—ሚዛናዊና ምርጥ ማኅበረሰብ የሚሉት ናቸው።

ከላይ የተጠቀሱት እነዚህ መሠረታዊ ነጥቦች ሊሆን ያለውን ፍጹም ነገር የሚያመለክቱ በመሆናቸው፣ በእነርሱ ላይ ምንም ዐይነት ትችት መሰንዘር በጥብቅ የተከለከለ ነው። ስለዚህ የሙስሊሙ ማኅበረሰብ የሚያደርገው ነገር በሙሉ ትክክል ነው። ፍጹም ለሆነው የእስልምና እምነት መገዛት ደግሞ በራስ የመተማመንን መንፈስ እንደሚሰጥ ይገለጻል።

ሙስሊሞች በተቈጣጠሯቸው አካባቢዎች ከክርስቲያኖች ጋር እንዴት አብረው መኖር እንዳለባቸው ነቢዩ መሐመድ መመሪያ ሰጥተው ነበር። በዚህም መሠረት ሙስሊሞች ለክርስቲያኖች የደኅንነት ዋስትና ይሰጣሉ። ክርስቲያኖች ደግሞ የደኅንነት ከለላውን የሚያገኙ ሕዝቦች (ዚሚ) ተብለው ይጠራሉ። እስልምና ወደ ተለያዩ ቦታዎች ሲስፋፋ፣ ክርስቲያኖች በሙስሊም ግዛቶች ስለሚያገኙአቸው ከለላዎች የተጠናከረ መመሪያ ወጥቶ ነበር። ለጊዜው ይህንን ጉዳይ በስፋት የምንመለከተው አይሆንም። በደኅንነት ከለላው መሠረት ክርስቲያኖች የማምለክ ነጻነት ነበራቸው። ነገር ግን ሌሎችን ወደ ክርስትና ማምጣት በፍጹም የተከለከለ ነው። በእስልምና ቀዳጥር ሥር በወደቁ አካባቢዎች፣ ከእስልምና ውጪ ሌሎች ሃይማኖቶች እንዲስፋፉ በጭራሽ አይፈለግም። ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎችን የተመለከቱ ሕጉች ይጠ

የነበረው ከዚህ ዐላማ አንጻር ብቻ ነው። የጋብቻ ሕግጋት፣ የቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ግንባታ፣ ወደ ሌላ እምነት የመቀየርና የቀረጥ ሕጉች በሙሉ፣ የእስልምናን እንቅስቃሴ በሚያበረታታ መልኩ ይዘጋጁ ነበር። በሙስሊም ግዛት ውስጥ የሚኖሩ ክርስቲያኖች ዐልፎ ዐልፎ መብታቸው ተጠብቆ ቢኖሩም እንኳ አብዛኛውን ጊዜ ግን የሚጣሉባቸው እጅግ በርካታ ገደቦች አለመጠን ጥብቅ ነበሩ። አንዳንዴም ጭቆናና ስደት ይደርስባቸው ነበር። ለምሳሌ እንደ ጉርጉሮሳውያኑ አቈጣጠር በ807 ዓ.ም ካሊፍ ሐሩን አል-ራሺድ አዳዲስ ቤተ ክርስቲያናት በሙሉ እንዲፈርሱ አድርጓል[10]።

በዚህ ዐይነቱ አካሄድ ከዝቅተኛ የኅብረተሰብ ክፍል የተነሣው የእስልምና ሃይማኖት፣ ወደ ተለያዩ ቦታዎች በፍጥነት ተስፋፋ። በተቃራኒው ደግሞ በሙስሊም ግዛቶች ውስጥ ያሉ ቤተ ክርስቲያናት ያላቸው ተቀባይነትና ዐቅም እየቀነሰ መጣ። ክርስቲያኖች ለዚህ ችግር ምላሽ መስጠት ያለባቸው በምን መልክ ነበር?

ዝቅተኛውን የማኅበረሰብ ክፍል መሠረት ያደረገ ምስክርነት

ልክ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ዝቅ በማድረግ ወንጌልን ለዝቅተኛው የኅብረተሰብ ክፍል እንደ ሰበከ ሁሉ፣ ለዝቅተኛው የማኅበረሰብ ክፍል ወንጌልን መስበክ የቤተ ክርስቲያን የተልእኮ አካሄድ መሆን አለበት። በሙስሊም ግዛቶች ውስጥ ያሉ ቤተ ክርስቲያናት የተገፉና በመከራ ውስጥ የሚያልፉ በመሆናቸው፣ እንደ ምዕራቢ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖትና መንግሥት ስላልተጋቡ ቈስጠንጢኖስ ክርስትናን ከመቀበሉ በፊት በክርስቲያኖች ላይ የሚደርሰው መከራ ስለሚደርስባቸው በምስክርነታቸው የወንጌል እውነት ይጸናል። ይሁንና ክርስቲያኖች እግዚአብሔር የሁሉ ነገር ፈጣሪ ሆኖ ሳለ፣ ራሱን ለዓለም የገለጠው በክርስቶስ በኩል በበረት ውስጥ እንዲሁም መኝታውን ግርግም በማድረግ እንደ ሆነ ያምናሉ። ልክ እንደዚሁ የወንጌሉም ሥራ ከትንሽ ወደ ትልቅ ነው።

---

10 "Three Phases of Christian-Muslim Interaction," *Christian History* 21, no.2 (August 2002): 26.

የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ

ዮሐንስ ወንጌል 1÷1-18: 29-34

የቁርአን ምንባብ

ሱራ 2÷135-147

<u>የአስተውሎትና የሙይይት ጥያቄዎች</u>

1. ስለ እስልምና ካወቁት/ከተረዱት ነገር ሁሉ፣ ያስደነቅዎት ነገር ምንድን ነው? በሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን በተመለከተ ያስገረሞት ነገር ምንድን ነው?
2. ሙስሊሞች ከተሰጣቸው ኀላፊነቶች መካል አንዱ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት ለክርስቲያኖች ማብራሪያ መስጠት እንደ ሆነ ያምናሉ የሚለውን ሐሳብ ሲያነቡ ምን ዐይነት ስሜት ተሰማዎ? ለዚህ ዐይነቱ ምልከታ ክርስቲያኖች ምላሽ መስጠት ያለባቸው እንዴት ነው?
3. የክርስትናም ሆነ የእስልምና ሃይማኖት እንቅስቃሴዎች የተጀመሩት እዚህ ግባ ከማይባል ዝቅተኛ ስፍራ ነው:: እነዚህ እንቅስቃሴዎች ራሳቸውን የዐቅመ ቢሶች አጋር አድርገው መቀሩጠር ቀጥለዋል? ለሚሰጡት ምላሽ አጥጋቢ ምክንያት ይስጡ::
4. በሰባተኛው ክፍለ ዘመን፣ በዐረብያ የሚገኘው የሙስሊም ኡማ እንዴት እንደ ተጀመረ ግብራሪያ ይስጡ::
5. በሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የሙስሊም ኡማ ሲጀመር አስተዋጽኦ ስላደጉት ስለ አራቱ የእምነት ክፍሎች አስተያየት ይስጡ:: ከአራቱ ውስጥ ለሙስሊም ኡማ መፈጠር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው የትኛው ነው?
6. የዐረብኛው ቁርአን ለዐረቦች በጣም አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?
7. በእስያ ምሥራቅ ያሉ ቤተ ክርስቲያናት ከምዕራቢ ቤተ ክርስቲያን የተለዩ መሆናቸውን ማሳወቅ ያስፈለገባቸውን ምክንያቶች ይዘርዝሩ::
8. እርስዎ በሙስሊም ግዛት ውስጥ ከሚኖሩ ክርስቲያኖች (ዚሚ) ውስጥ አንዱ ቢሆኑ እምነትዎን የሚገልጹትና ወንጌልን የሚመሰክሩት እንዴት ባለ መንገድ ይሆናል? በነጻነት የሚኖሩ ክርስቲያኖች በሙስሊም ማኅበረሰብ ውስጥ ከሚኖሩ እንዲሁም የተለያዩ ዐይነት ገደቦች ከሚጣልባቸው ክርስቲያኖች ምን ሊማሩ ይችላሉ?

ምዕራፍ ሦስት

በኤድን ገነት

አብዱላሂና እኔ በሶማሊያ አገር ጀሀር በተባለው ስፍራ ወደ አንድ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ለመግባት ቀጠሮ ይሰጠን ዘንድ እየተጠባበቅን ነበር:: እንደ ወትሮው ሁሉ የእኔና የአብዱላሂ ውይይት ያተኰረው በእግዚአብሔርና በተፈጥሮ ውስጥ የእግዚአብሔር ተአምራቶች (ምልክቶች) ላይ ነበር:: አብዱላሂ እንዲህ አለኝ፣ "የእግዚአብሔር ተአምራቶችን ተመልከት፣ ነፋስን፣ ዛፎችን፣ አሀዮችንና የራስህን አካል:: እነዚህ ነገሮች ሁሉ የእግዚአብሔር ተአምራቶች ናቸው፣ የእግዚአብሔር ተአምራቶች (አያት) በየትኛውም ስፍራ አሉ:: እነዚህ ተአምራቶች (ምልክቶች) የእግዚአብሔርን ታላቅነት ይገልጣሉ"::

ፍጥረት

ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን እንደ ፈጠረ ያምናሉ:: እንዲሁም ሁለቱም ወገኖች፣ አዳምና ሔዋን (ሐዋ) እግዚአብሔር ባዘጋጀው በኤድን ገነት ውስጥ የመጀመሪያ ነዋሪዎች እንደ ሆኑ ይስማማሉ:: እስልምናም ክርስትናም ፍጥረት መልካም እንደ ሆነና እግዚአብሔር ግን ከፍጥረቱ የተለየና ምጡቅ[1] አምላክ እንደ ሆነ ያምናሉ:: እግዚአብሔር በፍጥረቱ ውስጥ ራሱን እንደ ገለጠም ይስማማሉ::

መጽሐፍ ቅዱስ በሮሜ 1÷20 ላይ እንዲህ ይላል:— "ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የማይታየው የእግዚአብሔር ባሕርይ ይኸውም ዘላለማዊ ኀይሉና መለኮትነቱ፣ ከፍጥረቱ በግልጽ ይታያል፤ ስለዚህ ሰዎች ማመካኛ የላቸውም"::

ቁርአን በሱረቱ አል-ጋሺያህ 88÷17-21 ላይ ሰዎች ሁሉ በተፈጥሮ ውስጥ የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ተአምራቶች (ምልክቶች) በማየት፣ እግዚአብሔርን እንደ አምላክነቱ መጠን እንዲያከብሩት እንዲህ ሲል ጥሪ ያቀርባል:—

(ከሓዲዎች) አይመለከቱምን?
ወደ ግመል እንዴት እንደ ተፈጠረች!
ወደ ሰማይም እንዴት ከፍ እንደ ተደረገች!

---

[1] transcendent

ወደ ተራራዎችም እንዴት እንደ ተሞከሉ!
ወደ ምድርም እንዴት እንደ ተዘረጋች (አይመለከቱምን?)
አስታውስም፣ እንተ አስታዋሽ ብዎ ነህና።

መጽሐፍ ቅዱስና ቁርአን ሰማይና ምድር የእግዚአብሔር ፍጥረታት፣ የልዑል አምላክ የእጅ ሥራዎች እንደ ሆኑ ያስተምራሉ። እግዚአብሔርም ይሁኑ አለ፣ ተፈጠሩም! (ዘፍጥረት 1÷3-31፣ ሱራ 2÷117፣ 16÷40)። ፍጥረታት የእግዚአብሔርን ታላቅነት የሚገልጡ ናቸው። እኛም ለእነዚህ ምልክቶች አስፈላጊውን አክብሮት እንድንሰጥና ክብርን ሁሉ ለእግዚአብሔር እንድናቀርብ ታዘናል። እንዲሁም እያንዳንዱ ፍጥረት የተፈጠረው ለዐላማ ነው።

ቁርአን በሱራ 21÷16 እንዲህ ይላል:— "ሰማይንና ምድርን በመካከላቸው ያለውንም ሁሉ ቀላጆች ሽነን አልፈጠርንም"። ስለዚህ ፍጥረትን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስተካክሉ ወይም ፍጥረትን መለኮት ነው የሚሉ ሰዎች ጠንካራ ቅጣት እንደሚጠብቃቸው በሱራ 21÷18 እንዲህ ተጽፎአል:—

> በእርግጥ እውነትን በውሸት ላይ እንጥላለን፣ አንጉሉን ያፈርሰዋልም፣ ወዲያውም እርሱ ጠፊ ነው፣ ለናንተም ከዚያ (ሚስትንና ልጅ አለው በማለት) ከምትመጥኑት ነገር ብርቱ ቅጣት አላችሁ፣ (ወጥላችሁ)።

እግዚአብሔር ፍጥረትን የፈጠረበት ዐላማ ምን እንደ ሆነ በእስልምና መረዳት ምን ይመስላል? በእስልምና አስተምህሮ ምድር የሰው ልጆች እንዲጠቀሙባት፣ እንዲጠብቋትና እንዲደሰቱባት የተሰጠች የአምላክ ስጦታ ነች። ይህንን ሐሳብ በተመለከተ ቁርአን እንዲህ ይላል:—

> ግመልን ከብትን ፍየልንም በርሷ (ብርድ መከላከያ) ሙቀት ጥቅሞችም ያሉባት ስትሽን ለእናንተ ፈጠረላችሁ፣ ከእርሷም ትበላላችሁ። ለእናንተም በርሷ ወደ ማረፍያዋ በምትመልሷት ጊዜ በምታሰማርዋትም ጊዜ ውበት አላችሁ። ጉዛዞችሁንም በነፍሶች ችግር እንጂ ወደማትደርሱበት አገር ትሸከማለህ፣ ጌታችሁ በእርግጥ ሩኅሩኅ አዛኝ ነውና። ፈረሶችንም፣ በቅሎዎችንም፣ አህዮችንም፣ ልትቀመጡዋቸውና ልታጌጡባቸው (ፈጠረላችሁ)፣ የማታውቁትንም ድንቅ ነገር ይፈጥራል (ሱራ 16÷5-8 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)።

እስልምና ሰዎች እግዚአብሔር በተፈጥሮ ውስጥ የገለጣቸውን ምልክቶች እንዲያከብሩ ያዛል። ዛፎች ለማገዶ ተፈልገው ካልሆነ መቁረጥ የለባቸውም ይላል። እኔ በሥራቅ አፍሪካ ሙስሊም ተማሪዎችን እያስተማርሁ እያለሁ፣ ከእኔ ጋር ያገለግል የነበረ አሜሪካዊ ዓደኛዬ፣ ዕብድ ውሻ ተኩሶ ገደለ።

ተማሪዎቼ ተናደው "ያለምንም ምክንያት ውሻን መግደል አትችልም!" አሉት። ነገር ግን ዓደኛዬ "እኔ ውሻዪቱን መግደሌ ምሕረት እንዳደረግሁላት ይቁጠራል፣ ምክንያቱም ስለታመመች መሞቷ አይቀርምና" አላቸው። በዚያን ጊዜ ተማሪዎቹ በመልሱ ረኩ፣ ደስም አላቸው።

በእስልምና እምነት ውሃ እንኳ መባከን የለበትም የሚል አቋም አለ። አንድ ሰው ገላውን ሲታጠብ ውሃን በቀጥታ መጠቀም አለበት። ምግብም ሲበላ የሚባክን ምግብ መኖር የለበትም[2]። ለተፈጥሮ ክብካቤ ማድረግ ተገቢ ነው፣ ያለአንዳች ጥቅም የሚቀር ማናቸውም ዐይነት የአላህ ፍጥረት እንደሌለ የእስልምና ሃይማኖት ያስተምራል።

ተፈጥሮ በራሱ ፍጥረታት ሁሉ እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ ያነሣሣቸዋል። ስለዚህ ጉዳይ ቁርአን እንዲህ ይላል:—

> ወደዚያ ከማንኛውም ነገር አላህ ወደ ፈጠረው ጥላዎቹ እነርሱ የተዋረዱ ሲኾኑ ለአላህ ሰጋጆች ኾነው ከቀኝና ከግራዎች ወደሚዛወሩት አላዩምን? ለአላህም በሰማያት ያለው ከተንቀሳቃሽም በምድር ያለው ሁሉ መላእክትም ይሰግዳሉ፣ እነርሱም አይኩሩም። ጌታቸውን ከበላያቸው ሲኾን ይፈሩታል፣ የታዘዙትንም ሁሉ ይሠራሉ (ሱራ 16÷48-50)።

በአንድ ዩኒቨርሰቲ ውስጥ ከሙስሊም ባልንጀራዬ ጋር በነበረን ውይይት ዓደኛዬ እንዲህ ሲል ተናግሮ ነበር:— "የቁርአን ምንባባት የአላህ ምልክት (ተአምር) እንደ ሆኑ ሁሉ፣ ፍጥረት የእግዚአብሔር ምልክት (ተአምር) ነው። ቅዱሳት መጻሕፍት እንኳ ባይኖሩ፣ የእግዚአብሔርን እውነት ከተፈጥሮ መገንዘብ እንችላለን"።

መጽሐፍ ቅዱስ ፍጥረት የእግዚአብሔር የእጁ ሥራ እንደ ሆነ ይገልጻል። እኛም በመልካሚቱ ምድር ውስጥ እንድንደሰት ተጋብዘናል። መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች ከፈጣሪ ይልቅ ተፈጥሮን ወደ ማምለክ እንዳያዘነብሉ ያስጠነቅቃል (ሮሜ 1÷25)። በእርግጥም በተለያዩ ሃይማኖቶች ውስጥ፣ ሰዎች ከፈጣሪ ይልቅ ፍጥረታትን ሲያመልኩ ይስተዋላል። በዚህ ዘመንም እግዚአብሔር የለም የሚሉ ወገኖች እግዚአብሔርን ወደ ጐን በመተው፣ የሁሉ ነገር ባለሥልጣን ሳይንስና ተፈጥሮ ነው ይላሉ።

---

[2] Badru D. Kateregga and David W. Shenk, *A Muslim and a Christian in Di* (Scottdale, Pa.: Herald Press, 1997), 40.

ቁርአንም ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ፣ እግዚአብሔርን ትቶ ተፈጥሮን የማምለክ ዝንባሌን አጥብቀው ይቃወማሉ። እግዚአብሔር ከፍጥረቱ የተለየ ምጡቅ የሆነ አምላክ ነው። ፍጥረቱን በሙሉ በተፈጥሮ ሕግ እንዲንቀሳቀስና እንዲኖር የሚያደርግ ጌታ ነው። ነገር ግን አምላክና ፍጥረት አንድ አይደሉም። በማንኛውም መልኩ ፍጥረትን የሚያመልኩ ሰዎች ሐሰተኛ አማልክትን ያመልካሉ። አምልኮና ስግደት የሚገባው፣ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

አዳምና ሔዋን

ስለ ተፈጥሮ ያለው ግንዛቤ፣ በኤድን ገነት አዳምና ሔዋንን በተመለከተ በቁርአንና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኛቸው ገለጻዎች ናቸው። በእያንዳንዱ ባህልና እምነት ውስጥ ስለምድርና ሰለሰው አፈጣጠር ያለው አስተምህሮ፣ ሰዎች ስለ ሰው ማንነትና ሁኔታ ባላቸው አመለካከት መሠረት ነው። በተለያየ ማኅበረሰብ ውስጥ ስለ ሰው አፈጣጠር ያሉ ታሪኮች እኛ ግን እንደሆንና ወዴት እየሄድን እንዳለን እንዲሁም ምን ዐይነት እምነት ሊኖረን እንደሚገባ ስለሚነግሩን በዚህ ረገድ ጉልሕ ሚና አላቸው።

በሚከተሉት እንቀጾች ቁርአንና መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ የሚያስተምሩትን ትምህርት በዳሰሳ መልክ እንቃኛለን። ምንም እንኳ ከዚህ በታች የምዘረዝራቸው ሐሳቦች በአንባብያን ዘንድ የታወቁ ቢሆኑም፣ የሁለቱን ሃይማኖቶች አመለካከት ለማነጻጸር የተወሰኑ ሐሳቦችን ለማቅረብ እሞክራለሁ። የምዕራፉ ማጠቃለያ የክርስቲያንና የሙስሊም ገለጻዎች ምን ዐይነት እንድምታ እንዳላቸው በንጽጽር ያቀርባል።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ

መጽሐፍ ቅዱስ በመጀመሪያዎቹ ሦስት ምዕራፎች ውስጥ፣ የሰዎች ሁሉ አባትና እናት ስለሆኑት ስለአዳምና ስለሔዋን ይናገራል። እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን የፈጠረው በስድስተኛው ቀን፣ ሌሎች አጥቢ እንስሳትን በተፈጠረበት ጊዜ ነበር። እግዚአብሔር ሰውን በመልኩ ፈጠረ። እነርሱም ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን ያላቸው ፍጡሮች ሲሆኑ፣ ሰብአዊነታቸውም የተገለጠው ከእግዚአብሔር ጋር በነበራቸው ትክክለኛና አስደሳች ኅብረት ነው። እግዚአብሔር ለመጀመሪያ ጊዜ ከእነርሱ ጋር ያደረገው ቃል ኪዳን የተመሠረተው፣ እንዲፈጽሙት በሰጣቸው ሕግጋት ላይ ነበር። ሕግጋቱም ብዙ ተባዙ፣ ምድርን ግዙአት፣ ምድርንና ዛፎችን ጠብቁ፣ ምድርን ዕረሱ፣ እንስሳትን ጠብቁ፣ ለእንስሳትም ስም አውጡ የሚሉ ነበሩ።

እግዚአብሔርም አዳምንና ሔዋንን ወስዶ በኤድን ገነት አስቀመጣቸው። በኤድን ገነት ውስጥም፣ ሁለት ዐቢይ ትርጉም ያዘሉ ዛፎች ነበሩ። አንደኛው መልካሙንና ክፉውን የሚያስታውቀው ዛፍ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የሕይወት ዛፍ ነው። እግዚአብሔር፣ ለአዳምና ለሔዋን መልካሙንና ክፉውን ከሚያስታውቀው ዛፍ እንዳይበሉ አዞአቸው ነበር።

እግዚአብሔር አዳምን ከምድር ዐፈር አበጀው። ከአዳምም ጐን ዐጥንት ወስዶ ሔዋንን ሠራ፣ ምክንያቱም ከእንስሳት ውስጥ ለአዳም ረዳት የሚሆነው ፍጥረት ስላልተገኘ ነው። አዳምም በደስታ እንዲህ ብሎ ተናገረ :—

> ይህች ዐጥንት ከዐጥንቴ ናት፣ ሥጋም ከሥጋዬ ናት፣ እርስዋ ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል" (ዘፍጥረት 2÷23)።

ከዚህ በመቀጠልም እንዲህ የሚል ሐሳብ እናነባለን :—

> ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፣ በሚስቱም ይጣበቃል፣ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። አዳምና ሚስቱ ሁለቱም ዕራቁታቸውን ነበሩ፣ አይተፋፈሩም ነበር (ዘፍጥረት 2÷24-25)።

በዚህ ክፍል በአዳምና በሔዋን መካከል የተደረገውን ጋብቻ እንመለከታለን። ይህም ሐሳብ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፣ ስለ ጋብቻ ለተጻፉት ትምህርቶች መሠረት ነው። አዲስ ኪዳንም ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደወደደ ባል ሚስቱን ይውደዳት በማለት፣ በጋብቻ ውስጥ ያለውን ቃል ኪዳን በሰፊው ያብራራል (ኤፌ 5÷25)። እንዲሁም ሚስት ባልዋን እንድታከብርና በቤት ውስጥ እንድትታዘዘው ተጽፎአል (ኤፌ 5÷22-24:33)። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ የሚጀምረው፣ "እያንዳንዳችሁ በክርስቶስ ፍርሓት የተገዛችሁ ሁኑ" (ኤፌ 5÷21) በሚለው ዐቢይ ትእዛዝ ነው። ትዳር ከእግዚአብሔር መልካም ስጠታዎች መኻል አንዱ ነው። በርግጥም እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለው ዐላማ አስደናቂ ነው።

ዳሩ ግን ብዙም ሳይቆይ አሳዛኝ አደጋ ተፈጠረ። ሔዋን መልካሙንና ክፉውን ከሚያስታውቀው ዛፍ እንድትበላ እባብ አሳሳታት። አዳምም ከእርሷ ጋር በመተባበር ከዛፉ ወስዶ በላ። ይህ የተከለከለው ዛፍ የተለያየ ዐይነት ትርጉም አለው። ዛፉ በኤድን ገነት ውስጥ ያለ ሲሆን፣ ሰዎች ከእግዚአብሔር ሥልጣን ይልቅ ወደ ተፈጥሮ በልባቸው ማዘንበላቸውን የሚያሳይ የፈተና ምልክት ነው። በዚህም መሠረት አዳምና ሔዋን እግዚአብሔርን ከመታዘዝ ይልቅ ልባቸውን ወደ ተፈጥሮ አዘነበሉ።

እግዚአብሔርን ከመታዘዝ በተመለሱ ጊዜ፣ የዋህነታቸውን ጣሉ። ዕራቁታቸውን በመሆናቸውም ተፋፈሩ፣ ሐፍረተ ሥጋቸውንም ለመሸፈን የበለስን ቅጠሎች ሰፍተው አገለደሙ። የእግዚአብሔርን ድምፅ በሰሙ ጊዜም በገነት ዛፎች ሥር ተሸሸጉ።

እግዚአብሔርም እንዲህ ሲል ጠራቸው :— "አዳምና ሔዋን ወዴት ናችሁ?" እግዚአብሔር አምላክም በገነት ዛፎች ውስጥ ተሸሽገው አገኛቸው። እግዚአብሔር በሠሩት ሥራ ከፋኛ አዘነ። እርሱን ባለመታዘዛቸውም ምክንያት የሚደርስባቸውን አበሣና ሥቃይ ነገራቸው። እንዲህም አላቸው:— በምትወልጂበት ጊዜ ጭንቅሽ ይበዛል፣ በወንድና በሴት መካከል መከፋፈል ይሆናል፣ ወንዱ ገዢሽ ይሆናል፣ ሥራ አድካሚ ተግባር ይሆንባችኋል፣ እንደ ቀድሞው ተፈጥሮ ዘወትር አስደሳች ብቻ ሳትሆን አስቸጋሪ ትሆንባችኋለች፣ ሰው ምድርን ከመከባከብ ይልቅ አግባብነት በሌለው መንገድ መጠቀም ይጀመራል፣ የሰው ልጆች ምድርን ከመጠበቅና የተሻለ ከማድረግ ይልቅ በምድር ላይ ያሉትን ነገሮች ያበላሻሉ። በመጨረሻም ከሕይወት ዛፍ በልተው ለዘላለም እንዳይኖሩ እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ከኤድን ገነት አስወጣቸው። አዳምና ሔዋን ብቻ ሳይሆኑ እግዚአብሔርን ካለመታዘዝን የተነሣ የእነርሱ ዝርያዎች የሆንን ሁሉ በኀጢአት ወደቅን። ሞትም ወደ ሁላችን መጣ። ጥቂት ቆይቶም በአዳም ቤተሰብ ውስጥ ሞት በመግባቱ ምክን አቤልን ገደለ።

ከዚህ አሳዛኝ ታሪክ በኋላም ቢሆን፣ እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን እንዲሁም የሰውን ዘር አልተወም። እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን ኀጢአት በሠሩ ጊዜ በኤድን ገነት እንደፈለጋቸው፣ እኛም የትም ብንኖር ምንም ዐይነት ኀጢአት ቢኖርብን እግዚአብሔር ይፈልገናል። ፈጣሪ አምላክ የክፉ መገለጫ ለሆነውና ሰዎችን ወደ ፈተና ለጣለው እባብ እንዲህ ሲል ተናግሮታል:— "በአንተና በሴቲቱ መካከል፣ በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ፤ እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፤ አንተም ሰኩናውን ትቀጠቅጣለህ" (ዘፍ 3÷15)። ይህ ተስፋ ምን ማለት ነው? ብዙ ክርስቲያኖች በመጽሐፍ ቅዱስ ስለመሲሑ የተነገረ ተስፋ ነው ብለው ያምናሉ[3]። የክርስቶስ አገልግሎት ከሞት ፍርድ ነጻ ሊያወጣን፣ ኀጢአተኛ ከሆነው ማንነታችን ሊያድነንና ከእግዚአብሔር ጋር ሊያስታርቀን ነው። ለዚህም አገልግሎት እርሱ ለኀጢአተኞችና ለዐመፀኞች ታልፎ በመሰጠት በመስቀል ላይ ሞተ። "ሰኩናውም ቁሰለ"። ይሁንና የሞትን

[3] C. K. Leaman, *Biblical Theology: Old Testament*, vol. 1 (Scottdale, Pa.: Herald Press, 1971), 65.

ጣር አሸንፎ ከሞት ተነሣ፣ በመስቀል ላይ ሞቱና በትንሣኤው የክፉን ራስ ሲቀጠቅጥ፣ ኀጢአተኝነትና ሞት ድል ተነሣ።

እንደዚህ ዐይነት አመለካከት ያላቸው ክርስቲያኖች ዘፍ 3÷15 ላይ ያለው ቃል በዮሐንስ 3÷16 "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና" በሚለው ቃል ተፈጽሞአል ይላሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ ከእንስሳት ቁዳ ልብስ ሠርቶ ለአዳምና ሔዋን አለበሳቸው ይላል። ይህም ልብስ እነርሱ ከበለስ ቅጠል ሰፍተው ካገለደሙት ግልድም በእጅጉ የተሻለ ነው። እግዚአብሔር ያለበሳቸውን ልብስ ለማግኘት እንስሳትን ማረድ (መሥዋዕት ማድረግ) የሚጠይቅ ነው። በባህላዊ እምነቶች ውስጥ ለኀጢአት ይቅርታ ሲባል እንስሳቶችን መሥዋዕት ማድረግ ከዚህ ታሪካዊ ሁኔታ የተቀዳ ይሆንን?[4] ከዚህ ጋር በተያያዘ እንዲህ የሚል ሌላ ጥያቄ ማሰብ ተገቢ ነው:— እግዚአብሔር ለአዳምና ሔዋን ልብስ ሊያለብሳቸው በመፈለጉ ምክንያት እንዲሠዋ ያደረገው እንስሳ ወደ ፊት ለዓለም ሁሉ ኀጢአት መሥዋዕት ስለሆነው መሲሕ ምሳሌ አይደለምን? እንዴታ! ይሆናል እንጂ! በዮሐንስ 1÷29 ከመሲሑ ስሞች ውስጥ "የዓለምን ሁሉ ኀጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ" የሚለው ስም ይህንኑ እውነት የሚያመላክት ነው።

ቁርአናዊ አስተምህሮ

ከዚህ በመቀጠል ቁርአን ከላይ ባየነው ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ የሚያስተምረውን ትምህርት ደግሞ እንመልከት። ቁርአን እግዚአብሔር አዳምን በገነት (ጀና) ውስጥ እንደ ፈጠረው ይናገራል። እግዚአብሔር አዳምን ከሸክላ አበጀው፣ መናፍስትን (ጂኒዎችን) ደግሞ ከእሳት። እግዚአብሔር መንፈሱን በአዳም ውስጥ ዕፍ አለበት። ፈጣሪ አምላክ ለአዳም ከጂኒዎች፣ ከመላእክትና ከእንስሳት የላቀ የአስተሳሰብ ብቃትን ሰጠው። አዳም ከመላእክት እንደሚበልጥ በቁርአን በሱራ 15÷29 እንዲህ ተጽፎአል:—

> ፍጥረቱን ባስተካከልኩትና በውስጡ ከመንፈሴ በነፋሁበትም ጊዜ ለእርሱ ሲጋጆች ኹናችሁ ውደቁ።

[4] Rene Girard, *I See Satan Fall Like Lightning*, translated by James G. Williams (Maryknoll, N. Y.: Orbis, 2002) and Girard, *Violence and the Sacred*, translated by Patrick Gregory (Baltimore: Johns Hopkins University Press, 1981).

ከርሷም ሰይጣን እንዳለጣቸው፣ በውስጡም ከነበሩበት (ድሎት) አወጣቸው፣ ከፍላችሁም ለከፊሉ ጠላት ሲኾን ውረዱ፣ ለናንተም በምድር ላይ እስከ ጊዜ (ሞታችሁ) ድረስ መርጊያና መጠቀሚያ አላችሁ አልናቸው። አዳምም ከጌታው ቃላትን ተቀበለ፣ በርሱ ላይም (ጌታው ጸጸትን በመቀበል) ተመለሰለት፣ እነሆ እርሱ ጸጸትን ተቀባይ አዛኝ ነውና"። (ሱራ 2÷36-37 በትንፍ ያለውን ይጨምራል)።

እግዚአብሔር ለአዳምና ሔዋን ያደረገው ምሕረት የተገለጠው እርሱ በሰጣቸው ምሪት ነው፣ ምሪቱም እስልምና ነው። ምሪቱም (እስልምና) እግዚአብሔር ለአዳምና ሔዋን ለሐፍረታቸው መሸፈኛ እንዲሆን የሰጣቸው ልብስ እንደ ሆነ ተገልጿል። ይህንን አስደናቂ ምሕረት ቁርአን እንዲህ ይገልጸዋል፦

> የአዳም ልጆች ሆይ! ሐፍረተ ገላችሁን የሚሸፍን ልብስ ጌጥንም በእርግጥ በናንተ ላይ አወረድን፣ አላህን የመፍራትም ልብስ ይህ የተሻለ ነው፣ ይህ ከአላህ ታምራቶች ነው፣ ይገሡ ዘንድ (አወረደላቸው)። (ሱራ 7÷26 በትንፍ ያለውን ይጨምራል)።

እንደ ቁርአን ትምህርት፣ አዳም እግዚአብሔር የእስልምናን እምነት የገለጠለት የመጀመሪያው ነቢይ ነው። የአዳምና የሔዋን መኖሪያቸው በመካ አካባቢ በሚገኘው አራፋት በተባለው ሜዳ ላይ እንደ ነብረ ሙስሊሞች ያምናሉ። አዳም የመጀመሪያ ነቢይ ሲሆን፣ እርሱና ሔዋን ደግሞ የመጀመሪያዎቹ ሙስሊሞች ናቸው። በአሁኑ ጊዜ ሙስሊሞች በመካ ወደሚገኘው ካዕባ እንደሚሰግዱ አዳምና ሔዋን እንደሙስሊሞች በካዕባ እግዚአብሔርን ያመልኩ ነበር። ካዕባ ተብሎ የሚጠራው በመካ መካከለኛው ስፍራ ላይ የሚገኘው ጥቁር ድንጋይ ነው። እንደ ሙስሊሞቹ እምነት ከሆነ በዚህ ስፍራ አዳም የመጀመሪያውን የአላህ ቤት (የአምልኮ ስፍራ) ገንብቶ ነበር። በዚሁ ስፍራ አብርሃምና ልጁ እስማኤል፣ የእግዚአብሔር ቤት እንደ ገና አንጸው ነበር።

እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን እንዲሁም ዘሮቻቸው በምድር ላይ እንዲኖሩ ያደረጋቸው ለጎጢአታቸው መቀጣጫ አይደለም። እነርሱም ሆኑ የሰው ዘር በሙሉ የሚወለደው የውርስ ጎጢአት ኖሮበት አይደለም። አዳምና ሔዋን ሲፈጠሩ በመልካም አብነት (ፍትራህ) ነው፣ የሰው ልጅም እንደዚሁ ነው። ማንኛውም ሰው የሚወለደው ጥሩ ሙስሊም ሆኖ ነው። ሰዎች ቢያውቁም ባያውቁም፣ እግዚአብሔር የፈጠራቸው ከወሰነው መልካም ነገር አኳያ ነው።

> ወደ እውነት ተዘንባይ ሆነህም፣ ፊትህን ለሃይማኖት ቀጥ አድርግ፣ የአላህን ፍጥረት ያችን አላህ ሰዎችን በርስዋ ላይ የፈጠረባትን (ሃይማኖት ያዙዋት)፣

ለዚህም ይመስላል መላእክት እግዚአብሔር ስለአዳም በነበረው ዕቅድ እምብዛም ያልተደሰቱትና ያላወቁት። እግዚአብሔር በምድር ላይ ሰውን እንደሚያስቀምጥ ሲናገራቸው መላእክት እንዲህ በማለት ተቃውመው ነበር፦—

> (መሐመድ ሆይ) ጌታህ ለመላእክት፦— እኔ በምድር ላይ ምትክን አድራጊ ነኝ፣ ባለ ጊዜ (የኾነውን አስታውስ፣ እነርሱም) እኛ ከማመሰገን ጋር የምናጠራህ ላንተም የምንቀድስ ስንኾን በርሷ ውስጥ የሚያጠፋንና ደሞችንም የሚያፈስን ታደርጋለህን? አሉ፣ (አላህ) እኔ የማታውቁትን ነገር ዐውቃለሁ አላቸው። (ሱራ 2÷30 በትንፍ ያለውን ይጨምራል)።

የአዳም የማሰብና የማስተዋል ችሎታው መላእክትን ጨምሮ ከሁሉም ፍጥረት የላቀ ነበር። እርሱም እግዚአብሔር እንዳስተማረው የእንስሳት ስምና ሌሎች የፍጥረት ሁኔታዎች በሙሉ በአእምሮው ለማወቅ ችሎ ነበር። እንደ ቁርአን ትምህርት፣ መላእክት እንኳ ይህንን ተግባር ሊፈጽሙት አይችሉም። ሰይጣንም በአዳም የአእምሮ ብቃት ስለቀና፣ እግዚአብሔር መላእክትን በሙሉ ለአዳም እንዲሰግዱ ባዘዛቸው ጊዜ ሰይጣን (ኢብሊስ) አልሰግድም ብሎ ዐመፀ። አዳምን የፈጠርኸው ከሸክላ ነው፣ እኔን ግን የፈጠርኸኝ ከእሳት ነው በማለት ስግደቱን ተቃወመ። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር ሰይጣንን ከገነት አስወጣው።

ነገር ግን ሰይጣን የማታለል ሥራውን ከመሥራት አልቦዘነም። እግዚአብሔር ለአዳም ሚስት እንድትሆን ሔዋንን ከፈጠራት በኋላ፣ እግዚአብሔር በገነት ውስጥ ካሉት ዛፎች ነገር ግን አላህ እንዳይበሉ ከከለከላቸው ዛፍ በሰይጣን አሳሳችነት በሉ። ስለዚህ አላህ አዳምንና ሔዋንን ከገነት አስወጣቸው፣ እነርሱና ዘራቸው ወደሚኖሩባት ምድር አመጣቸው። ለተወሰኑ ዘመናት በምድር ላይ ለፈተና አስቀመጣቸው። ፈተናው ምንድን ነው? ፈተናውም ለአላህ ምሪት መገዛታቸው ወይም አለመገዛታቸው ነው፣ የአላህም ምሪት እስልምና ነው። ከሌሎች እንስሳት ለየት ያለ ጎላፊነት ተሰጥቶአቸው ነበር። እርሱም የምድር ጠባቂዎች (ኻሊፋ) እንዲሆኑ ነው።

ቁርአን አዳምና ሔዋን ከአላህ ዘንድ ለጎጢአታቸው ይቅርታ እንደ ጠየቁ ያስተምራል፦—

> ጌታችን ሆይ! ነፍሶቻችንን በደልን፣ ለእኛ ባትምር ባታዝንልንም በእርግጥ ከከሳሪዎቹ እንኾናለን አሉ (ሱራ 7÷23)።

እግዚአብሔር ለአዳምና ለሔዋን ምሕረት አድርጉላቸዋል። ይህንን ሐሳብ ቁርአን እንዲህ ያብራራዋል፦—

የአላህን ፍጥረት መለወጥ የለም፣ ይህ ቀጥተኛ ሃይማኖት ነው፣ ግን አብዛኛዎቹ ሰዎች አያውቁም (ሱራ 30÷30 በትንሹ ያለውን ይጨምራል)።

በሙስሊሞች አመለካከት ሕፃናት ሁሉ ጥሩ ሙስሊሞች ሆነው ይወለዳሉ። ነገር ግን ባለማወቅ ወይም በተሳሳተ ትምህርት ምክንያት ከእውነተኛው መንገድ ይወጣሉ። እነዚህ ጎጢአት የሌለባቸው ሕፃናት፣ እንዴት መኖር እንዳለባቸው የሚያሳይ ምሪት ያስፈልጋቸዋል፣ ምሪቱም የእስልምና እምነት ነው። የእስልምና አስተምህሮ (ምሪቱ) አዳምንና ሔዋንን እንዲሁም ሰዎችን በሙሉ ምድርን ጎላፊነት በተሞላበት ሁኔታ እንዲጠብቁአትና እንዲንከባከቧት ረድቶአቸዋል።

ሆኖም እግዚአብሔር ለአዳምና ለሰው ዘር ሁሉ የሰጠውን ይህንን ታላቅ ጎላፊነት ከዳር ማደረስ በሰው ዐቅም የሚቻል አይመስልም። እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው የእርሱ ወኪል (ሽሊፋ) እንዲሆን ነው። እግዚአብሔር ለአዳም የፍጡራንን ስም ሁሉ ያስተማረው፣ በፍጥረት ላይ ሥልጣን እንዲኖረው ነበር።

እግዚአብሔር ለአዳም ይህንን ሥልጣን የሰጠው፣ የፍጡራንን ስም በሙሉ ባስተማረው ጊዜ ነበር፣ እንዲሁም ሥልጣኑ በአዳም ላይ እንዲኖር የተደረገው እግዚአብሔር አዳምን በፈጠረበት ጊዜ ነው። በዚያ ጊዜ እግዚአብሔር በአዳም ላይ መንፈሱን ዕፍ ብሎበታል። ሙስሊም የነገረ መለኮት ምሁራን፣ እግዚአብሔር መንፈሱን በሰው ላይ አደረገ በሚለው ሐሳብ ዙሪያ የተለያየ አመለካከት አላቸው። አንዳንዶች ይህ ስጦታ ሰው በፍጥረት ላይ ሥልጣን እንዲኖረው የሚያደርገው ነው ይላሉ። ወኪል (ሽሊፋ) የሚለው ሐሳብ የእግዚአብሔር መንፈስ በሰው ላይ ሆነ የሚለውን ሐሳብ ለማብራራት ይረዳል። ቀትራጋ የተባለው ሙስሊም ምሁር ይህን መንፈስ ልዩ ስጦታ ነው ይላል፡—

(ሀ) እውነትን ከሐሰት፣ እኩይን ከሠናይ፣ እውነታን ከትዝታ ለመለየት የሚረዳ ዕውቀት ነው።

(ለ) መልካሙን ከክፉ፣ እውነትን ከሐሰት፣ ሠናይን ከእኩይ በነጻነት ለመምረጥ የሚያስችል ፈቃድ ነው።

(ሐ) ሰው በዙሪያው ያሉትን ነገሮች የመላመዱና የመጠቀሙ ሥልጣን ነው።

(መ) የመናገር ጎይል ነው። ይህም ፈጣሪውን ለማምለክ መቻሉ ነው[5]።

[5] Kateregga and Shenk, *A Muslim and a Christian in Dialogue*, 42-43.

ከላይ የተመለከትናቸው የቁርአንና የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮዎች፣ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ፍጥረትን በተመለከተ ያላቸውን የተለያየ አመለካከት እንድናውቅ ይረዱናል። በቁርአንና በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች መካል የተወሰኑ ምስስሎች ቢኖሩም፣ መሠረታዊ በሆነ ደረጃ ግን አማንያኑን የሚመሩት በተለያየ አትጣጫ መሆኑን ልብ ማለት አለብን።

የተለያዩ ጌዳናዎች

ከፓኪስታን ወደ ናይሮቢ የመጣ ሙስሊም ሚስዮናዊ፣ እርሱ እስልምናን የሚሰብከው ክርስቲያኖች ወንጌልን ከሚሰብኩበት መንገድ በተለየ መሆኑን ነገረኝ። ብዙ ጊዜ ከቤታችን ትንሽ ራቅ ብሎ ባለው አስፋልት ላይ እስልምናን ይሰብካል። ከብዙ ጊዜ በኋላ ስለ እስልምና ሃይማኖት ሊነግረን እቤታችን መጣ። በውይይታችንም ወቅት ስለ አዳምና ሔዋን መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚያስተምር ነገርሁት። እኔም ከአንድ ሳምንት በኋላ የእርሱን ምላሽ ለመስማት ወደ ቤቱ ሄድሁ። ስለታሪኩ እንዲህ አለኝ፣ "ይህ ታሪክ ትክክለኛ ያልሆነ እጅግ መጥፎ ታሪክ ነው። በጣም ቅር አሰኝቶኛል፣ በእውነት በጣም ነው ያስቀየመኝ"።

ይህንን ፓኪስታናዊ ሙስሊም ሚስዮናዊ ቅር ያሰኘው ጉዳይ፣ በዚህ ጥያቄ ዙሪያ የሚያጠነጥን ነበር፡— "ሰው መሆን ማለት ምን ማለት ነው?"። ግለሰቡ ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥሮአል የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ለመቀበል በእጅጉ ተቸግሮአል። እንዲሁም ሰው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ባለመጠበቁ የተነሣ በጎጢአት ወድቆአል፣ አዳኝም ያስፈልገዋል፣ የሚለው አስተምህሮ በአያሌው ረብሾታል። ሰው በጎጢአት ስላልወደቀ ለድነት ወደ ትክክለኛው መንገድ የሚመራው ምሪት እንጂ፣ አዳኝ አያስፈልገውም ሲል ይህ ኢማም[6] አጥብቆ ተከራከረ።

ከተወሰኑ ዓመታት በኋላ፣ በመካከለኛው ለንደን በሚገኝ መስጊድ ውስጥ በነበረን የግል ውይይት እንዲህ ስል ተናገርሁ :— "መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰው ተፈጥሮ የሚያስተምረው ትምህርት ለእውነታ የቀረበ ነው። ጎጢአተኛ መሆናችንን በግልጽ ያስተምራል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በስም የተጠቀሱት ነቢያት እንኳ እንከን አለባቸው። የእምነት ሰው የነበረው አብርሃም እንኳ፣ ሚስቱን እህቴ ናት በማለት ውሸት በመናገሩ ጎጢአት ሠርቶአል"።

[6] "ኢማም" በመስጊድ ውስጥ ጸሎት ለሚያደርሱ ሰዎች መሪ ነው ወይም ታዋቂ የሆነ የሙስሊሙ ማኅበረሰብ መሪ ነው። በሺአይት ሙስሊሞች ዘንድ ደግሞ የዘር ሐረጉ ከመሐመድ ወገን የሆነ የሃይማኖቱ መሪ ነው።

ይህ ቃል ከአፌ እንደ ወጣ፣ በመስጊዱ ውስጥ የነበሩ አምስት መቶ የሚሆኑ ሙስሊሞች በአንድነት፣ "ይህ በፍጹም አይሆንም!" ሲሉ ልቋቋመው በማልችለው ዐይነት ድምፅ ተቃወሙኝ። አብሮኝ የነበረው ሙስሊም ጓደኛዬ እንዲህ ሲል መለሰልኝ፦ "አብርሃም ነቢይ ስለሆነ ኀጢአት አልሠራም። የአብርሃም ውሸት ምክንያታዊ ነበር። ኀጢአት ሊባል አይገባውም። ነቢያት ሁሉ ጻድቃን ናቸው፣ ኀጢአትም አይሠሩም"።

እነዚህ ውይይቶች ስለ ሰው ማንነት በቁርአንና በመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮዎች ላይ ልዩነቶች እንዳሉ ያመላክታሉ። በዚህ ርእስ ዙሪያ በሁለቱ መጻሕፍት ውስጥ ያሉትን አስተምህሮዎች በአጭሩ እንመልከት፦

1. ሙስሊሞችም ሆኑ ክርስቲያኖች ሕያዋንና ግዑዛን፣ የሚታዩና የማይታዩ፣ ምድርና በውስጥዋ ያሉት ነገሮች ሁሉ በእግዚአብሔር እንደ ተፈጠሩ ያምናሉ። ተፈጥሮንም በቀጣይነት እንዲኖር የሚያደርገው እግዚአብሔር እንደ ሆነ ይስማማሉ። ተፈጥሮ የእግዚአብሔርን ኀያል ከንድ የሚገልጽ ምልክት ነው።
2. ሙስሊሞችም ሆኑ ክርስቲያኖች፣ አዳምና ሔዋን (ሐዋ) የመጀመሪያዎቹ የሰው ልጆች እንደ ሆኑ ያምናሉ። የሰው ዘር ሁሉ የመጣው ከእነርሱ ነው። ስለዚህ ሰው ሁሉ አንድ ነው።
3. ሁለቱም፣ ሰው ከእንስሳት እንዲሁም ከቀሳዊው ዓለም ጋር የሚጋራው ነገር እንዳለና የተፈጠረውም ከዐፈር እንደ ሆነ ያምናሉ።
4. መጽሐፍ ቅዱስ አዳምና ሔዋን በእግዚአብሔር አምሳል እንደ ተፈጠሩ ይገልጻል። ይህ ፅንሰ ሐሳብ የተለያዩ የትርጉም አቅጣጫዎች ያሉት ነው። ዋነኛው እውነታ ግን ሰዎች የተፈጠሩት ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ለማድረግ ነው የሚለው ነው። እግዚአብሔር እኛ ለእርሱ የቃል ኪዳን ሕዝቦቹ እንድንሆን ይፈልጋል። ቁርአን ደግሞ አዳም የእግዚአብሔርን መንፈስ እንደ ተቀበለ ይናገራል። የሙስሊም ነገረ መለኮት አስተማሪዎች በዚህ ጉዳይ ላይ እየተከራከሩ ይገኛሉ። ነገር ግን ብዙዎቹ የሚያምኑት፣ ሰዎች የእግዚአብሔር ወኪል (ኸሊፋ) እንዲሆኑ ሥልጣን የሚሰጥ መንፈስ ነው ወደሚለው ሐሳብ ነው።
5. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ትዳር የሚያስተምረው ትምህርት የሚገኘው ስለኤድን ገነት በተጻፈው ታሪክ ውስጥ ነው። ነገር ግን ብዙም ሳይቆይ ሰዎች ስለ ትዳር ያለውን ሕግ መጠበቅ እንዳልቻሉ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። ይሁንና ስለ ጋብቻ ያለው አስተምህሮ መሠረት የተጣለው በአዳምና ሔዋን የትዳር ግንኙነት ውስጥ ነው። ከመሠረተ ሐሳቦቹ ውስጥ፦ አንድ ሥጋ

መሆናቸው፣ አንድ ወንድ ለአንድ ሴት፣ በእግዚአብሔር የተመሠረተና ሊፈርስ የማይችል ጥምረት እንዳላቸው የሚያሳይ ነው። ልጆች ስጦታ ናቸው ግዴታ ግን አይደሉም። ባል ራሱን እንደሚወድ ሚስቱን እንዲወድና እንዲከባከብ የሚለው ሕግ ግልጽ የሆነ ኀብረትና መተማመን እንዲሰፍን የሚያደርግ ነው። እንዲሁም ያለ ትዳር መኖር ተቀባይነት ያለው ሲሆን፣ የሰዎች ደስታ ፍጹም የሚሆነው ግን ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ኀብረት እንጂ በጋብቻ አይደለም። ጋብቻ አስፈላጊ ነገር ቢሆንም ሳያገቡ መኖርም ተፈቅዶአል።

ቁርአን የጋብቻን ትርጉም ከመጀመሪያዎቹ ጣምራዎች (አዳምና ሔዋን) ሕይወት ጋር በማያያዝ ያስተምራል (ሱራ 4፡1)። ነገር ግን ቁርአን ስለ ጋብቻና ስለሴቶች ዘርዘር ያለ ሐሳብ ይሰጣል። ሙስሊም ላልሆነ ሰው፣ ስለ እስልምና አስተምህሮ የሙስሊሞችን አመለካከት በትክክል በሚወክል መልክ ማቅረብ እጅግ አስቸጋሪ ስለሆነ፣ ጋብቻና ሴቶችን በተመለከተ ከእስልምና ምንጮች የተወሰዱ ሐሳቦችን ያለምንም ማብራሪያ ለማቅረብ እሞክራለሁ።

መሐመድ በአንድ ወቅት፣ "ከእናንተ በጣም የተሻለ የሚባለው ሰው ለሚስቱ በጣም ጥሩ የሆነላት ሰው ነው"[7] ብለው ነበር

> ወንዶች በሴቶች ላይ ቋሚዎች (አሳዳሪዎች) ናቸው፣ አላህ ከፊላቸውን በከፊሉ ላይ በማብለጡና (ወንዶች) ከገንዘቦቻቸው (ለሴቶች) በመስጠታቸው ነው። መልካሞቹም ሴቶች (ለባሎቻቸው) ታዛዦች አላህ ባስጠበቀው ነገር ሩቅን ጠባቂዎች[8] ናቸው። እነዚያንም ማመጣቸውን የምትፈሩትን ገሥጹዋቸው፣ በመኝታዎችም ተለዩዋቸው (ሳካ ሳታደርሱ) ምቱዋቸውም። ቢታዘዙዋችሁም (ለመጨቆን) በነርሱ ላይ መንገድን አትፈልጉ፣ አላህ የበላይ ታላቅ ነውና (ሱራ 4፡34 በትንሹ ያለውን ይጨምራል)።
>
> ሴቶቻችሁ ለናንተ እርሻ ናቸው፣ እርሻችሁንም በፈለጋችሁት ሁኔታ እረሱ፣ ለነፍሶቻችሁም (መልካም ሥራን) አስቀድሙ፣ አላህንም ፍሩ፣ እናንተም

[7] Muhammad Hamidullah, *Introduction to Islam* (Paris: Centre Culturel Islamique, 1969), 134.

[8] "ሩቅን ጠባቂዎች" የሚለውን ሐሳብ ቁርአን በግርጌ ማስታወሻው ላይ እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል፣ "ባሎቻቸው በራቁ ጊዜ መብታቸው እንዳይደፈርና ገንዘባቸውን ጠባቂዎች"።

ተገናኝዎቹ መሆናችሁን ዕወቁ፣ ምዕመናንንም (በነነት) አብሥር (ሱራ 2÷223 በትንፍ ያለውን ይጨምራል)።

ነቢዩ መሐመድ ወደ መካ ለመጓዝ ሲዘጋጁ ለተከታዮቻቸው እንዲህ ብለዋቸው ነበር፦—

ሴቶችን እንድትንከባከቡ እነግራችኋለሁ፣ ምክንያቱም እነርሱ በቤታችሁ ውስጥ እንዳለ አስረኛ ናቸውና፣ የራሳቸው የሆነ ንብረትም የላቸውምና፣ ለእናንተም ከአላህ ዘንድ የተሰጡ ስጦታዎች ናቸው። እንዲሁም በሴቶቻችሁ ሰውነት እንድትደሰቱ የአላህ ቃል ያዛል። ሴቶችን በተመለከተ አላህን ፍሩ፣ ሴቶችንም እንድትንከባከቡ አዛችኋለሁ። ልብ በሉ ! እኔ ተናገርሁ? ኦ አላህ ምስክር ነው[9]

ከዐሥር ዓመት በፊት ባልቲሞር በሚባል ስፍራ በሚገኝ መስጊድ በአንድ ምሽት ውስጥ ብዙ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች ለውይይት ተሰብስበው ነበር። የሙስሊሞቹ መሪ (ኢማም) ሴቶችንና ጋብቻን በተመለከተ የሙስሊሞች አመለካከት ምን እንደሚመስል ትምህርት ሰጠ። እኔም በዚህ ጉዳይ ላይ መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚያስተምር ተናገርሁ።

የሙስሊሞቹ መሪ (ኢማም) እንዲህ ሲል ተናገረ፦— "እስልምና ነባራዊ ሁኔታዎችን ያገናዘበና ትክክለኛ ነው። እናንተ ክርስቲያኖች የምታስተምሩት ነባራዊ ሁኔታዎችን ያላገናዘበና ተግባራዊ ሊሆን የማይችል ነገር ነው"።

ከእኛ መካከል አንድ ሰው እንዲህ ሲል መለሰ፦— "አንተ የምትለው ነገር ትክክል ሊሆን ይችላል። ነገር ግን የእግዚአብሔር መንፈስ ሰዎችን አዲስ ፍጥረት በማድረግ በመጽሐፍ ቅዱሳዊው ጋብቻ እንዲኖሩ ወይም በብቸኝነት ኑሮ ውስጥ በቅድስና እንዲመላለሱ ኀይልን ይሰጣቸዋል"።

6. መጽሐፍ ቅዱስ ኤድን ገነት በምድር ላይ እንደ ነበረች ያስተምራል። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊው ትምህርት በዚያ አያበቃም። በመጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻው ክፍል በጣም ስለተዋበችውና እግዚአብሔር በዘመኑ መጨረሻ ላይ ለቅዱሳን ሁሉ ስላዘጋጀላቸው ስለ ቅድስቲቱ ከተማ ይገልጻል። እግዚአብሔር በኤድን ገነት የጀመረውን ታሪክ፣ የነገሮች ሁሉ ፍጻሜ ወደ

[9] Hamidullah, (cf. Ibn Hisham), 135.

ሆነችው ወደ ታሳቂቱና ቅድስቲቱ ከተማ እንዲመጡ ጥሪ በማቅረብ ታሪክን ይቋጫል።

በቁርአን የአዳምና የሔዋን የመጀመሪያ መኖሪያቸው መንግሥተ ሰማያት ነበር። እግዚአብሔር በፈተናቸው ጊዜ ወደ ምድር ተጥለዋል። ሰው በምድራዊ ኑሮው በሁለት ጉዳናዎች መካከል ይገኛል። እርሱም ከገነት በመባረሩ ምክንያት ዕድሉን ማጣቱ አንዱ ሲሆን፣ በመጨረሻው ዘመን የምትገለጠዋ መንግሥተ ሰማይ፣ ለእግዚአብሔር ታማኝ የሆኑ ሰዎች ብቻ የሚያገኟት ናት የሚለው ደግሞ ሁለተኛው ነው።

7. በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር አዳም ለእንስሳት ሁሉ ስም እንዲያወጣ ሥልጣን ሰጥቶታል። በቁርአን ግን እግዚአብሔር ለአዳም የእንስሳትንና የፍጥረትን ሁሉ ስም አስተምሮታል።

በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ለሰዎች አስገራሚ ፈቃድንና ተጠያቂነትን ሰጥቶአል። ይህ በጣም ትልቅ ኀላፊነት ነው። ሰው በእግዚአብሔር ፍጥረት ላይ ጥሩ ያልሆነ ነገር ሠርቶአል። ሰው በጣም ጥሩ የሆኑ በእንጻሩ ደግሞ እጅግ ጥሩ ያልሆኑ ነገሮችን አድርጎአል። ለምሳሌ ናይትሮጅን የተባለውን ንጥረ ነገር በመጠቀም የመሬት ማዳበሪያ እንደ ሠራ ሁሉ፣ ይህንኑ ንጥረ ነገር ለኬሚካል ጦር መሣሪያነት ተጠቅሞበታል።

በቁርአን አስተምህሮ መሠረት ለማንኛውም ሥራ እግዚአብሔር ተጠያቂ ነው። ግና ከጅምሩ ለእንስሳት ስም የማውጣቱ ሥራ ሰው ከእግዚአብሔር የመጣውን ትእዛዝ መቀበሉን እንጂ፣ በራሱ ስም አላወጣም። ሰው የእግዚአብሔር ወኪል ስለሆነ ምድርን የመጠበቅና የመከባከብ ኀላፊነት ከእግዚአብሔር በሚሰጠው ትእዛዝ መሠረት መፈጸም አለበት።

ስለዚህ እነዚህ የተለያዩ አመለካከቶች አንድን ማኅበረሰብ ለምጣኔ ሀብት፣ ለልማትና ለሳይንስ ባለው ምልከታ ላይ ምን ዐይነት ተጽእኖ ይኖራቸዋል? እኔ ሁል ጊዜ ይህ ጥያቄ ያሳስበኛል። ለዚህም ጥያቄ ሁለት ምሳሌዎችን እንመልከት።

ሶማሊያ በነበርንበት ጊዜ አብዲ መሐመድ ከተባለ ወጣት ተማሪ ጋር አንድ ምሽት በቤታችን ሻይ እየጠጣን (አብዲ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ ነው)፣ አብዲ እንዲህ ሲል ጠየቀኝ፣ "ዓለማዊ ሰው መሆን እፈልጋለሁ፣ ነገር ግን እግዚአብሔርን መካድ አልፈልግም። ክርስትና ለዓለማዊ ሰው የሚሆን እምነት ነውን?"።

እንዲህ ስል ጠየቅሁት:— "ይህ ዐይነቱን ጥያቄ ለምን ጠየቅኸኝ" አብዲ እንደዚህ ሲል መለሰልኝ፣ ""በአገሬ ክርስቲያን የሆኑ ሚስዮናውያን፣ የልማትን ሥራ በመሥራቱ ረገድ ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ናቸው። በቤተ ክርስቲያን የተሠሩ የልማት ሥራዎች፣ የቀለም ትምህርት ቤቶች፣ የሕክምና አገልግሎት መስጫ ተቋማት፣ የመሠረተ ትምህርት አገልግሎት፣ ግብርና፣ የኢኮኖሚ ልማት፣ የንግድ ሥራዎችና የሴት ትምህርት ቤቶች በርካታ ናቸው።..

ከናይሮቢ መስጊድ ፊት ለፊት ባለው ቤቴ ውስጥ በኖርሁባቸው ዘመናት ሁሉ የአብዲን ጥያቄ ሁል ጊዜ አስላስለው ነበር። በዚያ ስፍራ የሚኖሩት ሙስሊሞች፣ ሁል ጊዜ ምሽት ሦስት ሰዓትና ዐሥር ሰዓት ገደማ ላይ ወደ መስጊድ ለጸሎት ሲሄዱ እሰማ ነበር። እነርሱ ወደ መስጊድ በሚሄዱበት ወቅት እኔ መኝታ ላይ ነኝ። በዚያን ጊዜ እኛ የተለያየ አገልግሎት እንድትሰጥ በማሰብ ባቋቋምናት ትንሽ የክርስትና ማዕከል ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ለጥናት የሚሆኑ ማንበቢያ ክፍሎችን እያደራጀን ነበር። ለድኻ ልጆችም የትምህርት ቤት ክፍያ እንከፍልላቸዋለን። የሙስሊሞቹ መሪ (ኢማም) ሴት ልጆች እንኳ ለትምህርት ቤት የሚሆን ክፍያ ገንዘብ የማያስጨንቃቸው ከእኛ ነበር። ነገር ግን ሙስሊሞች ከዐረብ አገሮች የሚገኘውን የገንዘብ ዕርዳታ ለዐረብኛና ለቁርአን ትምህርት ቤቶች ማስፋፊያነት ይጠቀሙበታል። ክርስቲያኖች በልማት ዘርፍ ሲሠማሩ ሙስሊሞች ግን ሃይማኖታዊ ሥራዎችን ይሠራሉ።

በዚህች ምድር የሚኖር ክርስቲያን እንደ መሆኔ መጠን፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት የልማት ሥራ እንዲስፋፋ እንዴት እንዳደረገ የሚገልጹ ሁለት መጻሕፍት አንብቤ ነበር[10]። የእነዚህ መጻሕፍት ጸሓፍያን፣ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊውን እምነት አንግበው በማኅበረሰቡ ባህል ውስጥ በመግኘት፣ የሰዎችን አመለካከት በመለወጥ ለልማት ሥራዎች እንዲነሣሡ ታላቅ ዕገዛ አድርገዋል ሲሉ ጽፈዋል። የጸሓፍቱ አባባል ትክክል ነውን? ለዚህ ጥያቄ የአብዲ አባባል በጣም ጥልቅ መልእክት አለው። ስለ ሰው ተጠያቂነት፣ ነጻነትና ስለ ታሪክ አስፈላጊነት ያለን መረዳት በልማት ሥራዎች እንድንሳተፍ ምን ያህል ተጽእኖ አድርጉብን ይሆን?

[10] እነዚህ ሁለት መጻሕፍት የሚከተሉት ናቸው Lesslie Newbigin, *Honest Religion for Secular Man* (London: SCM 1966) and Arend Theodoor van Leewen, *Christianity in World History*, translated by H. H. Hoskins (New York: Charles H. Scribner, 1964), 324-33.

8. መጽሐፍ ቅዱስ አዳምና ሔዋን ከእግዚአብሔር ፈቃድ መውጣታቸው እንዲሁም ከጎጢአት የተነሣ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር፣ ሰው ከሰው ጋር፣ ሰው ከሥራ ጋር እንዲሁም ሰው ከፍጥረት ጋር የነበረውን ጎብረት ምን ያህል እንዳበላሸው ያስተምራል። በሰዎች ሕይወት ውስጥ ዘወትር እንደሚታየው አዳምና ሔዋን እግዚአብሔርን የሕይወታቸው መሠረት አላደረጉም። በሰው ሁሉ ውስጥ ያለው፣ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠርንበት ምልክት በሚያሳዝን ሁኔታ ተበላሽቶአል።

ቁርአን፣ የአዳምና የሔዋን አለመታዘዝ በእግዚአብሔር ይቅርታ ያገኘ ስሕተት ነው የሚል አቋም አለው። በአዳምና በሔዋን የተገለጠው ሰብአዊነት፣ ጎጢአት ባስከተለው ጥፋት አንዳችም ችግር አልደረሰበትም፣ ሰው ሁሉ ሲወለድ ጎጢአት የሌለበት ንጹሕ ፍጡር ነው።

9. መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረው እግዚአብሔር ወደ ኤድን ገነት በመምጣት አዳምና ሔዋን ተደብቀው ባሉበት አግኛቸው። ከዚያም ከገነት አስወጣቸው። ነገር ግን የቄዳ ልብስን አለበሳቸው። ወደ ፊት ከሴቲቱ የሚወለደው ልጅ የእባቡን ሰኩና ይቀጠቅጣል፣ ነገር ግን ልጁ የክፉን ራስ በመቀጥቀጥ ድልን እንደሚነሣ እግዚአብሔር ተስፋ ሰጥቶአቸዋል።

ቁርአን ደግሞ እግዚአብሔር አዳምን የመጀመሪያ ነቢይ በማድረግ ለሕይወቱ መመሪያ የሚሆን መልእክት ሰጥቶታል ይላል። ከአንድ ሙስሊም የነገረ መለኮት ምሁር ጋር የጎብረት ውይይት ካደረግን በኋላ እንዲህ አለኝ:— "እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ለመፈለግ ወደ ኤድን ገነት መጣ የሚለው አመለካከት ያበሳጨናል"።

እኔም እንዲህ ስል መለስሁለት:— "ይህ ጉዳይ ሊያበሳጭ እንደሚችል እገምታለሁ። ይሁንጂ ይህ የወንጌል ታላቅ ምሥራች ነው። እግዚአብሔር ፈቃዱን ብቻ ከሰማይ አልላከልንም። ይልቁንም በሰዎች ታሪክ ውስጥ እውናዊ ተሳትፎ በማድረግና ታሪካችንን በመጋራት ከገባንበት አረንቋ አወጣን። እኛ ከእግዚአብሔር ብንደበቅም እርሱ ግን ያለንበት ድረስ በመምጣት ታሪካችንን ታሪኩ በማድረግ ፈለገን። እግዚአብሔር በሉዓላዊነቱ ፈለገን፣ በመሲሑ ሥቃይ፣ መሲሑ ባፈሰሰው ደምና በቄረሰው ሥጋ በኩል አዳነን"[11]። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ታሪኮች ለሰዎች አለኝታና ተስፋ የሚሰጡት በዚህ መልክ ነው።

[11] Miroslav Volf, *Exclusion and Embrace* (Nashville: Abingdon, 1996), 35-166.

የውይይት ጥያቄዎች

1. ቁርአን እኛ በምድር ላይ የእግዚአብሔር ወኪሎች እንደ ሆንን ሲያስተምር፣ መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ በእግዚአብሔር አምሳል እንደ ተፈጠርን ያስተምራል (ሱራ 2+30፤ ዘፍጥረት 1+27)። በእነዚህ አመለካከቶች ላይ ያልዎትን መረዳት ይግለጹ።
2. "ለእንስሳት ስም ማውጣት" የሚለው ሐሳብ ላይ ከቁርአንና ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ አኳያ የእርስዎን አስተያየት ይስጡ (ሱራ 2+30-32፤ ዘፍጥረት 2+19-20)። እነዚህ የተለያዩ መረዳቶች ምን ዐይነት ትርጉም ያዘሉ ይመስልዎታል?
3. "መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት ለዓለማዊ ሰው ትክክለኛ እምነት ነውን?" ለሚለው ለአብዲ ጥያቄ የእርስዎ መልስ ምንድን ነው?
4. ስለ ኀጢአት እንዲሁም ኀጢአት ስላስከተለው ጥፋት መጽሐፍ ቅዱሳዊና ቁርአናዊ አስተምህሮዎችን ያነጻጽሩ (ሱራ 2+36-37፤ 7+14-23፤ ዘፍጥረት 3+1-4:9)።
5. በአሁኑ ጊዜ እስልምና ስለ ሰው ተፈጥሮና ኀጢአት ያለው አስተምህሮ ክርስትና ስለ ሰው ውድቀት ካለው አስተምህሮ ይልቅ በሰዎች ዘንድ ተቀባይነት አለው ወይ? ለመልስዎ ማስረጃዎችን ይስጡ። ከሰው ልጆች የዕለት ተዕለት ኑሮ አንጻር የትኛው አመለካከት ለእውነታው የቀረበ ይመስልዎታል?

6. እግዚአብሔር መመሪያን ላከልን በሚለውና እግዚአብሔር አዳነን በሚሉት አስተምህሮዎች መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው (ሱራ 2+37-38፤ ዘፍጥረት 3+15)?
7. "ታማኝ የሙስሊም ኡማ የጥንቱን አዳም ያመለክታል፤ ታማኝ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ የአሁኑንና የወደፊቱን ክርስቶስ ታመለክታለች" (ሱራ 30+30፤ ዘፍጥረት 3+15፤ ዮሐንስ 3+16፤ ራእይ 1+7፤ 22+20) ስለሚለው ሐሳብ የእርስዎን አስተያየት ይስጡ።
8. ቁርአን በሱራ 4+34 እንዲሁም 2+223፣ ስለ ሴትና ስለ ትዳር ለእውነት የቀረበ ትምህርት ያስተምራል። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በዘፍጥረት 1+27 እና 2+20-25 ላይ ስለ ሴትና ትዳር የሚያስተምረው ትምህርት ተፈጥሮን የሚቃረንና እውነታን ያገናዘበ አይደለም፣ ለሚሉ አመለካከቶች የእርስዎን አስተያየት ይስጡ።

ምዕራፍ አራት

የአብርሃም ልጆች
አስማኤል—ይስሐቅ

በአሜሪካን አገር ፔንሲልቬኒያ በሚባለው ክፍለ አገር ዴቨን በሚባል ቦታ በሚገኝ አንድ መስጊድ ውስጥ፣ ሰባ አምስት የምንሆን ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች የግታ የውይይት ጊዜ ነበረን። በውይይቱ ጊዜ የሙስሊሞቹ ኢማም (መሪ)፣ "እስልምና ለማንኛውም ሰው የሚሆን ሃይማኖት ነው። ያልተዛባ ሥነ አመክንዮም ሆነ ፍልስፍና ሰዎችን ወደ እስልምና ሃይማኖት ይመራቸዋል" ሲል ቁፍጠን ብሎ ተናገረ።

እኔም ለሙስሊሞቹ መሪ እንዲህ ስል መለስሁለት፣ "በዚህ ጉዳይ ወንጌል ከእስልምና ይለያል። የሰው ፍልስፍናም ሆነ ሰብአዊ የሆነ ሃይማኖት የወንጌልን የምሥራች በእውኑ ይቅርና በህልሙ እንኳ ሊያስበው አይችልም። ወንጌል ማለት እግዚአብሔር በመሲሑ አማካይነት በሰዎች መካከል እንዴት እንደ ገባና ፍቅሩን እንዴት እንደ ገለጠ የሚያስረዳ ታላቅ የምሥራች ነው። እግዚአብሔር በመሲሑ በኩል በእኛ ምክንያት እንዲሁም ለእኛ ሲል ተሠቃየ። ከመሲሑ አገልግሎት የምንረዳው፣ እግዚአብሔር ኀጢአተኞችን እንደሚወድና ኀጢአተኞችንም ለማዳን እንደሚፈልግ ነው። ይህን እውነት ፍልስፍና ውስጥ ማግኘት አይቻልም። እግዚአብሔር ለሰዎች ኀጢአት ሲል በመሲሑ በኩል የገለጠውን ጸጋ ወይም የእግዚአብሔርን ምሕረት ማወቅና መቀበል የምንችለው በእምነት አማካይነት ብቻ ነው"። ለእኔ ምላሽ፣ የሙስሊሞቹ መሪ ፊቱን ቅጭም አድርጎ እንዲህ ሲል በአጭንአት ተናገረ፣ "በመሠረቱ እግዚአብሔር ይህን ያህል ሰዎችን ሊወድ አይችልም"።

የእምነት ጉዞ

ፔንሲልቬኒያ በነበረን የውይይት ጊዜ የሙስሊሞቹ መሪ፣ "እስልምና ተፈጥሮአዊና ለሰዎች ልምምድ የቀረበ ነው"። በማለት የተናገረው ነገር የተጋነነ ይመስላል። አብዛኛው ሙስሊም የቁርአን መገለጥ ተአምራዊ ነው የሚል እምነት አለውና። ይሁንና በዴቨን መስጊድ ውስጥ በነበረን ውይይት ወቅት እንነጋገርበት የነበረው ርእሰ ጉዳይ፣ "ለማንኛውም ሰው የሚገባ

(ሰብአዊ/ተፈጥሮአዊ) ሃይማኖት ወይስ ሰዎችን በሚያስደንቅ ጸጋ የሚነካ እምነት?" የሚለውን ትኩረት ያደረገ ነበር። ከአራት ሺህ ዓመት በፊት በአብርሃም ቤት ውስጥ የነበረው ግራ መጋባት፣ ከዚህ ርእሰ ጉዳይ ጋር ተመሳሳይነት አለው። በአብርሃም ሕይወትና ቤት ውስጥ ይስተዋል የነበረው ግራ መጋባት፣ በአሁኑ ዘመን ባለው የሙስሊም ማኅበረሰብ (ኡማ) እንዲሁም በተወሰነ ደረጃ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይስተዋላል። በአብርሃም ሕይወት ጥያቄ እንደ ነበረ ሁሉ እኛም፣ "ቀላልና ተፈጥሮአዊ በሆነ ሁኔታ መኖር ወይስ እግዚአብሔር ለሰዎች የማይገባቸውን ምሕረት በገለጠበት ጸጋ ውስጥ መመላለስ?" በሚሉት ሁለት አማራጮች መካከል እንዋዥቃለን።

አብርሃም እግዚአብሔር የሰጠኝ ተስፋ የሚፈጸመው እንዴት ነው? የሚለውን ጉዳይ ዘወትር ያወጣና ያወርድ ነበር። እግዚአብሔር ለአብርሃም ልጅ እንደሚሰጠው ቃል የገባለት ቢሆንም እንኳ፣ ሚስቱ ሣራ መካን ነበረች። አብርሃም ልጅ ለመውለድ ከባሪያዪቱ ከአጋር ጋር መተኛት ነበረበት ወይስ ተስፋ አስቈራጭ ቢመስልም እንኳ፣ ሣራ ልጅ ትወልዳለች ብሎ እግዚአብሔርን መታመን? አብርሃም መኖር ያለበት እንደ ማንኛውም ሰው ተፈጥሮአዊ የሆነውን ኑሮ ወይስ እግዚአብሔር የሰጠኝን ተስፋ ይፈጽምልኛል በሚለው ልዕለ ተፈጥሮአዊ (መለኮታዊ) እምነት? ሣራ በሴቶች የሚታየው ወግ ከእርስዋ ከቀረ በኋላ፣ ልጅ እወልዳለሁ የሚለውን ጉዳይ እርሷም ሆነች አብርሃም በአያሌው ተጠራጥረውታል። ስለዚህ አብርሃምና ሣራ ሰብአዊ በሆነ አካሄድ ልጅ ለማግኘት ፈለጉ። አብርሃም ከአገልጋዩ ከአጋር ጋር በመተኛቱም አስማኤል ተወለደ (ዘፍጥረት 16)።

አስማኤል ከተወለደ በኋላ፣ እግዚአብሔር ወደ አብርሃም በመምጣት በዘፍጥረት 17÷15-16 እንዲህ ሲል ኪዳኑን አደሰ፦ "እግዚአብሔርም አብርሃምን አለው፦ የሚስትህን የሦራን ስም ሦራ ብለህ አትጥራ፤ ስምዋ ሣራ ይሆናል እንጂ። እባርካታለሁ፣ ደግሞም ከእርስዋ ልጅ እሰጥሃለሁ፣ እባርካትማለሁ፣ የአሕዛብ እናት ትሆናለች፣ የአሕዛብ ነገሥታት ከእርስዋ ይወጣሉ"።

አብርሃም፣ እግዚአብሔር የሰጠው ተስፋ አይፈጸምም ብሎ ስላሰበ ከእግዚአብሔር ጋር ለመከራከር ፈለገ። አብርሃምም ለእግዚአብሔር፦ "እስማኤል በፊትህ ቢኖር በወደድሁ ነበር አለው" (ዘፍጥረት 17÷18)። በሣራ ልጅ የመውለድ ጉዳይ ፈጽሞ ተስፋ ቈርጦአልና።

እግዚአብሔር ለአብርሃም እንዲህ ሲል መለሰለት፦—

> በእውነት ሚስትህ ሣራ ወንድ ልጅን ትወልድልሃለች፣ ስሙንም ይስሐቅ ብለህ ትጠራዋለህ፣ ከእርሱ በኋላ ለዘሩ የዘላለም ቃል ኪዳን እንዲሆን ቃል ኪዳኔን ከእርሱ ጋር አቆማለሁ። ስለ እስማኤልም ሰምቼሃለሁ፣ እነሆ ባርኬዋለሁ፣ ፍሬያማም አደርገዋለሁ፣ እጅግም አበዛዋለሁ፣ ዐሥራ ሁለት አለቆችንም ይወልዳል፣ ታላቅ ሕዝብም እንዲሆን አደርገዋለሁ (ዘፍጥረት 17÷19-20)።

የእግዚአብሔር መልአክ የዘጠና ዓመት ዕድሜ ያላት ሣራና የመቶ ዓመት ዕድሜ ያለውን አብርሃምን ልጅ ትወልዳላችሁ ሲላቸው፣ ቀልድ መስሏቸው ነበር። እየተነጋገሩ ሳለም ሣራ በድንኳን ውስጥ ሆና ስትሥቅ የእግዚአብሔር መልአክ ሰማት። አብርሃምም በሣቅ ተሞልቶ ነበር።

የአብርሃም ሁለተኛ ልጅ የይስሐቅ መወለድ ለሰዎች ሁሉ አስደናቂ ክሥተት ነበር። ነገር ግን በእስማኤል መወለድ ማንም ሰው አልተደነቀም፣ ተፈጥሮአዊ ሕግን የተከተለ ነውና።

በእርግጥ ከስሙ መረዳት እንደሚቻለው ይስሐቅ ማለት "ሣቅ" ማለት ነው። የይስሐቅ መወለድ ብዙ ደስታንና መገረምን አምጥቶአል። ሣራ የዘጠና ዓመት ሴት ሆና ይስሐቅን መውለድዋ፣ በየትኛውም ዘመን የሚኖሩ ሰዎችን ይህ ጉዳይ እንደሚያሥቃቸው ተናግራ ነበር። ልጅዋ ይስሐቅ በእርግጥም የኪዳኑ ልጅ እንዲሁም የእግዚአብሔር አስደናቂ ስጦታ ነው።

ዳሩ ግን እስማኤልም በእምነት የተወለደ ልጅ ነው። እስማኤል የሚለው ስም ትርጕሙ፣ "እግዚአብሔር ይሰማል" ማለት ነው። እግዚአብሔር ለአብርሃም ዘር እንደሚኖረው ተስፋ ሰጥቶት ነበርና።

አብርሃምና ሣራ እግዚአብሔር ተስፋውን ለመፈጸም እንዳይከብደው እርሱን ለማርዳት/ለማገዝ ወሰኑ። ከዚህም ውሳኔ የተነሣ አብርሃም ከአጋር ጋር ተኛ። አብርሃምና ሣራ እምነታቸውን ሥነ አመክንዮአዊ እንዲሁም ሰውኛ በሆነ አስተሳሰብ ገለጹት።

ወደ ጽድቅ የሚደረግ ጕዞ

የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪኮች እውነትነት የሚያስደንቅ ነው። አብርሃም የአማኞች ሁሉ አባት ነው። አንዳንዴ ግን አብርሃም የሚሠራውን ሥራ ለማመን መቸገሩንና ግራ መጋባቱን የሚያሳዩ ናቸው። አብርሃም፣ ሣራን

ይፈልግ የነበረው ንጉሥ እንዳይገድለው በመፍራት ሚስቱን ሁለት ጊዜ እህቴ ናት በማለት ዋሽቶአል። ይህ ዐይነቱ ድርጊት፣ ለአብርሃም ሙሉ ጥንቃቄ ለማድረግ ሙሉ ችሎታ ያለውን አምላክ መታመኑን ያመለክታልን?

በአብርሃም ቤተሰብ ውስጥ የነበረው ቤተሰባዊ ሥርዐት እየተበላሸ መጣ። እስማኤል ከተወለደ በኋላ ሣራ አገልጋይዋ የሆነችውን አጋር ምርር ብሏት ከቤት እስክትጠፋ ድረስ በነገር ትነዘንዛት ነበር። ይስሐቅ ከተወለደ በኋላ ግን ሣራ፣ ሥራተኛዪቱ አጋርንና ልጅዋን እስማኤልን፣ አብርሃም ከቤት እንዲያባርራቸው ግፊት ታደርግ ነበር። ይህን ያደረገችበት ዐቢይ ምክንያት፣ የሠራተኛዪቱ ልጅ እስማኤል ከልጇ ይስሐቅ ጋር በሰላም አብረው መኖር አይችሉም በሚል አስተሳሰብ ነው (ዘፍጥረት 16፤ 21+8-14)።

የአብርሃም የወንድም ልጅ የነበረው ሎጥ፣ ወይን ጠጅ ጠጥቶ በስካር ራሱን በሳተ ጊዜ፣ ከሁለት ሴት ልጆቹ ጋር የዝሙት ኀጢአት ፈጸመ። ከዚያ በኋላ ርብቃ ይስሐቅን በማታለል፣ በሁለቱ ልጆቻቸው በያዕቆብና በኤሳው መካከል የመረረ ጠብ እንዲፈጠር አደረገች።

<u>እምነትን መሠረት ያደረገ ጽድቅ</u>

ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ጸጋ ምሕረትና ታማኝነት ሕይወታቸው ኩነኒአት ባልጸዳ በእነዚህ ሰዎች ላይ ሰፈነ። ምንም እንኳ አብርሃምና ሣራ እግዚአብሔር ለሣራ በስተ እርጅናዋ ልጅ እንደሚሰጣት የተናገራትን አስደናቂ ኪዳን ለማመን ቢቸገሩም፣ ሣራ የዘጠና ዓመት ሴት ሆና ሳለ እግዚአብሔር ይስሐቅን በመስጠት ባርኮአቸዋል።

አብርሃም በእግዚአብሔር ላይ ያለውን እምነት ሰብአዊ በሆነ አካሄድ ቢገልጽም፣ እግዚአብሔር ግን በጸጋው ባርኮቱን አበዛለት። የአብርሃም ሕይወትና የቤተሰቡ ሥርዐት ከስሕተት የጸዳ ባይሆንም፣ እግዚአብሔር ለአብርሃም እምነት ዕውቅና ሰጥቶአል። መጽሐፍ ቅዱስ በዘፍጥረት 15+6 ላይ፣ "አብርሃምም በእግዚአብሔር አመነ፤ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት" ይላል።

አብርሃም እግዚአብሔርን መታመን ቀላል ጒዳይ ሆኖ ባያገኘውም ታማኝ ሆኖ ለመገኘት ሲጸክርና ሲውተረተር እናገኘዋለን። አንዳንዴም በሁለት ሐሳብ ያነክስ ነበር። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ጥሪ በመከተልና የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል በማመን ሕይወቱን በትጋት ኖሮአል። አብርሃም ላሳየው የእምነት ትጋት፣ በእግዚአብሔር አምላክ "ጻድቅ ሰው" ተብሎ ተጠራ። ማናችንም

ብንሆን ለእግዚአብሔር ጸጋ የተገባን ሰዎች አይደለንም። ነገር ግን ለእግዚአብሔር በእምነት ምላሽ ስንሰጥ እግዚአብሔር የጽድቅንና የድነትን ልብስ ያጐናጽፈናል (ኢሳይያስ 61+10)።

ከሁለት ሺህ ዓመታት በኋላ፣ "ጽድቅ በእምነት ይገኛል" የሚለው ሐሳብ ግልጽ በሆነ ሁኔታ ለሰዎች ተገለጠ። ይህም የተገለጠው በመሲሑ አገልግሎት ውስጥ ነው። በመሲሑ አገልግሎት ውስጥ በእርግጥም እግዚአብሔር ኀጢአተኞችን እንደሚወድ መገንዘብ ችለናል።

መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ልዩነት የለምና፤ ሁሉ ኀጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጕድሉአቸዋል" ይላል (ሮሜ 3+23)። እንዲሁም በሮሜ 5+8 ላይ፣ "ነገር ግን ገና ኀጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአል፤ እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል" ይላል።

ይህንን የእግዚአብሔርን የጸጋ ስጦታ ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ መልክ ይገልጸዋል፦ "ጻድቅ በእምነት ይኖራል" ሮሜ 1+17። በወንጌል እንደ ተጻፈው የእግዚአብሔር ጽድቅ ተገለጠአል። ይህም ጽድቅ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በእምነት የሚሆን ጽድቅ ነው። እንዲሁም ሐዋርያው ጳውሎስ በኤፌሶን 2+8-9 ላይ፣ "ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና፤ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ግንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም" ይላል።

የወንጌል አንኳር መልእክት፣ ድነት በጸጋ አማካይነት በእምነት ይገኛል የሚለው ትምህርት ነው። የወንጌል ዘር የተዘራው፣ "አብርሃም አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት" በሚለው ታሪክ ውስጥ ነው። አብርሃም ጻድቅ የተባለው የሠራው ሥራ ሁሉ ትክክል ሆኖ ስለተገኘ አይደለም። የጽድቁ ፍሬ የተፈጸመውና ግልጽ ሆኖ የታየው፣ በመሲሑ አገልግሎትና ተልእኮ ውስጥ ነው።

እስልምና የእግዚአብሔር ርኅራኄና ምሕረት ለጻድቅ ሰዎች ብቻ እንደሚገለጥ ያስተምራል። ቁርአን በሱራ 19+96 እንዲህ ይላል፦ "እነዚያ ያመኑና በጐ ሥራዎችን የሠሩ አልራሕማን ለእነሱ ውዴታን ይሰጣቸዋል"።

አንድ ቀን በአንድ ዩኒቨርሲቲ በተካሄደ ረዘም ያለ የአደባባይ ውይይት ሙስሊም ጓደኛዬ ስለ አብርሃም እንዲህ ሲል ተናገረ፦ "አብርሃም በፊቱ ተደፍቶ ለእግዚአብሔር ሰገደ። በዱት ተደፍቶ ለእግዚአብሔር መሰገድ

ትክክለኛው የስግደት ዐይነት ነው። ስለዚህ የእግዚአብሔርን ምሕረት ለመቀበል እንደ አብርሃም በፊታችሁ ተደፍታችሁ እንድትሰግዱ ጥሪ አቀርብላችኋለሁ"።

እግዚአብሔር ለአብርሃም ጸጋን የሰጠው ለምንድን ነው? አብርሃም ሃይማኖታዊ ጸሎትንና ስግደትን በሥርዐትና በታማኝነት በመፈጸሙ ነውን? ወይስ የእግዚአብሔር ጸጋ ያገኘው የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል በማመኑ ነው?

በዚህ ምዕራፍ የእግዚአብሔርን ምሕረትና ጸጋ በስፋት ለመመልከት እንሞክራለን። የእስማኤልና የይስሐቅ ታሪክ የእግዚአብሔርን ጸጋና ምሕረት በጥልቀት እንድንመለከት ይረዳናል።

አብርሃምና እስማኤል

እግዚአብሔር ልጁን መሥዋዕት እንዲያደርግ አብርሃምን ያዘዘው ትእዛዝ፣ ለአብርሃም ፈታኝ ነበር። ቁርአን አብርሃም ልጁን መሥዋዕት አድርጎ ለማቅረብ አዘጋጅቶ እንደ ነበር ይነግረናል። አብርሃምና ልጁ ለአላህ ፈቃድ በመታዘዝ መሥዋዕቱ ወደሚካሄድበት ስፍራ ሄዱ (ሱራ 37+99-113)። ነገር ግን በሚያስደንቅ ሁኔታ እግዚአብሔር ጣልቃ ገብቶ በልጁ ፈንታ የመሥዋዕቱን በግ አዘጋጀ። ቁርአን በሱራ 37+107 እንዲህ ይላል:— "በታላቅ ዕርድም (መሥዋዕት) ተቤዠነው"።

መጽሐፍ ቅዱስ አብርሃም ልጁ ይስሐቅን መሥዋዕት ለማድረግ ተዘጋጅቶ እንደ ነበር፣ ነገር ግን እግዚአብሔር በኪነ ጥበቡ የመሥዋዕቱን በግ እንዳዘጋጀ ያስተምራል (ዘፍ 22)። ቁርአን ለመሥዋዕት የቀረበው ልጅ ማን እንደ ሆነ አይናገርም። ነገር ግን ሙስሊም ምሁራን ለመሥዋዕት የቀረበው ልጅ እስማኤል ነው ይላሉ[1]።

በየዓመቱ በሚደረገው የሐጅ ጉዞ ወቅት፣ ከዓለም ዙሪያ የሚመጡት ሙስሊሞች፣ እግዚአብሔር ጣልቃ በመግባት እስማኤልን ከሞት ያዳነበትን ዕለት ለመዘከር፣ እንስሳትን በማረድ እንዲሁም ያረዱትን እንስሳ በመብላት ቀኑን ያከብራሉ። ለሐጅ ጉዞ ወደ መካ የተጓዙ ምዕመናን ደግሞ ሚንስ

[1] Abdullah Yusuf Ali, *The Holy Qur'an: Text, Translation, and Commentary* (Beirut: Dar Al Arabia, 1958), Commentary and Notes, no. 4101, p. 1205.

በተሰኘው ኩረብታ አጠገብ መሥዋዕት ያቀርባሉ። መሥዋዕት የማቅረቡ ሥርዐት የሚፈጸመው አብርሃም እስማኤልን ለመሠዋት በቀረበ ጊዜ እግዚአብሔር የመሥዋዕቱን በግ ማዘጋጀቱን ለማስታወስ ነው።

መሐመድና እስማኤል

የአብርሃምና የእስማኤል ታሪክ ሙስሊሞች ለራሳቸው ባላቸው ግንዛቤ ላይ ጉልሕ የሆነ አሻራ አሳርፎአል። በመሐመድ ዘመን ከመሐመድ ዘመዶች ውስጥ የሐኒፍ እምነት ተከታዮች ነበሩ። የሐኒፍ እምነት ተከታዮች በዐረብያ ውስጥ የሚኖሩ ሲሆን፣ አንድ አምላክ ብቻ የሚያመልኩ ነበሩ። ከእነርሱ ውስጥ አንዳንዶቹ፣ እምነታቸው ከአብርሃም ዘመን ጀምሮ እንደ ነበር ያምናሉ። እነርሱ የሚያመልኩት አላህ የተሰኘው ፈጣሪ አምላክ ሲሆን፣ ኋላም ሙስሊሞች ይህን ስም ለፈጣሪ አምላክ መጠቀም ጀምረዋል። የሐኒፎች አምላክና የሙስሊሞች አምላክ አንድ እንደ ሆነ ሙስሊሞች ያምናሉ። አላህ የሚለው ስም በዐረብኛ እግዚአብሔር ማለት ሲሆን፣ አብርሃም የጠራው እግዚአብሔር "ኤል" ወይም "ኤሎሂም" ከሚለው ስም ጋር ተመሳሳይ ነው። እግዚአብሔር ለአብርሃም ከመገለጡ በፊት ኤሎሂም በተራራ ላይ ሰፍሮ የሚኖር አምላክ እንደ ሆነ ይቈጠር ነበር። ከመሐመድ ዘመን በፊት ለዐረቦች አላህ ማለት ፈጣሪ አምላክ ማለት ነው። በእርግጥ በዐረብያ ከፈጣሪ አምላክ (አላህ) ባሻገር ሌሎችም አማልክት ይመለኩ ነበር። ባህላዊ እምነት ከሚያምኑ ዐረቦች ውስጥ አላህ ሦስት ሴት ልጆች አሉት ብለው ያምኑ ነበር። እነርሱም አል-ላት፣ አል-ኡዛ እና አል-መናት (ዕጣ ፈንታ፣ ጨረቃ እና ቬነስ) ይባላሉ። አይሁዶችና ክርስቲያኖች እንዲህ ዐይነቱን የጣዖት አምልኮ እንደሚቃወሙ ሁሉ፣ መሐመድም በዐረብያ የነበረውን የጣዖት አምልኮ ተቃውሞአል። መሐመድ አላህ ሴት ልጆች ቀርቶ እርሱን የሚመስለው የለም ሲሉ ሰብከዋል። አስልምና የጣዖት አምልኮን በማስቀረት፣ አላህ ብቻውን ፈጣሪ አምላክ ነው የሚል እምነት እንዲመሠረት አድርጉአል።

በሙስሊሞቹ አላህና በአብርሃም አምላክ (ኤሎሂም) መካከል መመሳሰሉች አሉ። ሙስሊሞች የአብርሃም አምላክ የመሐመድም አምላክ እንደ ሆነ ሙሉ እምነት አላቸው። አላህ የአብርሃም አምላክ ነው ይላሉ። ከመሐመድና ከሙስሊም ኡማ ምሥረታ በፊት ሐኒፎች ለብዙ ዓመት አላህን የማምለክ ሥርዐት በዐረብያ እንዲቆይ አድርገዋል። ሐኒፎች አንድ ፈጣሪን ብቻ የሚያመልኩና የዐረቦችን የጣዖት አምልኮ ለዘመናት የተቃወሙ ናቸው።

ለመሐመድ በተለይ በመዲና ቆይታቸው ከአብርሃምና ከእስማኤል አምላክ ጋር መገናኘት ወሳኝ ቢሆንም ከአይሁድ ማኅበረሰብ ግን የከፋ ተቃውሞ ደርሶባቸዋል[2]። አይሁዶች ለመሐመድ፣ "ነቢያት በሙሉ አይሁዶችና የአብርሃም ልጆች ናቸው። ዐረብ ነቢይ መሆን አይችልም" ሲሉ ተቃወሙአቸው።

ከዚህም የተነሣ ሙስሊሞች በአይሁዶች ላይ ያላቸው ጥላቻ እየከረረ ሄደ። ሙስሊሞቹ "መሐመድ ሐኒፍ ነው፣ የሐኒፎች መነሻ አብርሃምና እስማኤል ናቸው" ሲሉ የአይሁዶችን ተቃውሞ መከላከል ጀመሩ።

የመሐመድ የዘር ሐረግ

በእርግጥ ሙስሊሞች እንደሚሉት የመሐመድ የዘር ሐረግ እስከ እስማኤል ይደርሳል። መሐመድ የሐኒፍ እምነት ተከታይ ብቻ ሳይሆኑ፣ ቤተሰባቸው የእስማኤል ዘር የሆነው የቁረይሽ ጐሣ አባል ናቸው። የአብርሃምና የእስማኤል ደም በመሐመድ ውስጥ ነበር።

የዐረብን የዘር ሐረግ በተመለከተ ግጥም የሚገጥሙ አንዳንድ ሙስሊሞች የመሐመድ የዘር ሐረግ ከአብርሃም ዐልፎ እስከ አዳም ድረስ ይዘልቃል በማለት ዝርዝር ያቀርባሉ። በምድር ላይ ያለ ሰው በሙሉ የአዳምና የሔዋን ዘር መሆኑ እሙን ነው። ይሁንና በዚህ የዘር ሐረግ ቀመር መሐመድ የአብርሃም ዘር ብቻ ሳይሆኑ፣ የአዳምም ዘር እንደ ሆኑ ግልጽ ነው። ሙስሊሞች እንደሚያስረዱት፣ በመሐመድ የዘር ሐረግ ስሌት፣ መሐመድ በመካከለኛው ዘመን ከተነሡ የእስልምና ነቢያት አንዱ እንዲሁም ከአብርሃምና የነቢያት መጀመሪያ ከሆነው ከአዳም ዘር የተገኙ ናቸው።

በመዲና ለነበሩ ሙስሊሞች የዘር ሐረግ መቀኛጠር አስፈላጊ እንደ ነበረ ሁሉ፣ ከዚያ በኋላ ለመጡ ሙስሊሞችም ጒልሕ ስፍራ አለው። ከነቢዩ መሐመድ ሞት በኋላ የሺአ ሙስሊሞች ከሱኒ ሙስሊሞች ጋር የመለየታቸው ዋነኛ ምክንያት የዘር ሐረግ ጒዳይ ነው። ሺአ ሙስሊሞች፣ "የሙስሊሙን ማኅበረሰብ የሚመራው ኢማም (የሃይማኖቱ መሪ) የመሐመድ ዘር" መሆን አለበት ሲሉ ይከራከራሉ። በተቃራኒው ሱኒ ሙስሊሞች ደግሞ፣ "ኻሊፋ (ፖለቲካዊና መንፈሳዊ መሪ የሚሆነው ሰው) በሙስሊሙ ኅብረተሰብ

[2] "Ibrahim," *Encyclopedia of Islam*, vol. 3, new ed. (Leiden: Brill, 1960), 980-81.

ስምምነት መመረጥ አለበት እንጂ፣ የዘር ሐረግን በመቀኛጠር መሆን የለበትም" ሲሉ ተቃውሞውን ይከላከላሉ።

ሺአ ሙስሊሞች የመሐመድ የወጉት ልጅና የፋጡማ ባል የነበረው፣ ዓሊ ቢኒ አቡ ጣሊብ የሙስሊሙ ማኅበረሰብ መንፈሳዊ መሪ ሆኖ ማገልገል አለበት የሚል እምነት ዐደረባቸው። እርሱ ከሞተ በኋላም ሁሴን የተሰኘው የዓሊ ልጅ በአመራሩ ቦታ እንዲተካ ፈልገው ነበር። በዚህ አሰጣገባ ውስጥ፣ በሱኒና በሺአ ሙስሊሞች መካከል ግጭት ተፈጥሮ ሁሴን ተገደለ። ከዚህ በኋላ ሱኒዎችና የሺአ ሙስሊሞች እንደ ተለያዩ ቀሩ።

ይሁንና የዘር ሐረግ በሺአ ሙስሊሞች ብቻ ሳይሆን በሱኒ ሙስሊሞችም ዘንድ ትልቅ ዋጋ አለው። በዘመናችን የሚገኙ በብዙ ሚሊዮን የሚቈጠሩ የሱኒና የሺአ ሙስሊሞች፣ የራሳቸውንና የመሪዎቻቸውን የዘር ሐረግ እስከ መሐመድ ድረስ ይቈጥራሉ። እንዲሁም የሱፊ መንፈሳዊ መሪዎች የዘር ሐረጋቸው እስከ መሐመድ ድረስ እስኪደርስ ይዘረዝራሉ።

የዘር ሐረጋቸውን በመቀኛጠር አንጻር፣ የሶማሌ ሕዝብ በቀደምትነት ተጠቃሽ ነው። ሶማሌዎች ሁሉ የመሐመድ ዘሮች እንደ ሆኑ ይናገራሉ። ለአንድ የሶማሌ እረኛ ልጅ ዘርህ ምንድን ነው? ስል ጠየቅሁት። በጣም ደስታ በተሞላበት ፊት እንዲህ ሲል ነገረኝ፣ "ስሜ መሐመድ የኡመር ልጅ፣ የአህመድ ልጅ፣ የፍዶው ልጅ፣ የሮብሌህ ልጅ፣ የአቡበክር ልጅ፣ የአዶዋ ልጅ፣ የጉኤልድ ልጅ፣ የሐለኔ ልጅ፣ የሳማተር ልጅ፣ የዩሱፍ ልጅ፣ የጉኡድ-አዴህ ልጅ፣ የጉሬይ ልጅ፣ የባስ-ጋብ ልጅ፣ የሁሴይን ልጅ፣ የመሐመድ ልጅ፣ የአብደላህ ልጅ፣ የሳሞ-ታሊስ ልጅ፣ የሐዋድሌ ልጅ፣ የመሐመድ ልጅ-የእኔ ጐሣ አባት ነው"። የጐሣው አባት የሆነውን የዘር ሐረግ ቈጠራ የጨረሰው፣ የነቢዩ መሐመድ ልጅ የሆነችው ፋጡማ ላይ በመድረስ ነው[3]። ይህ ፊደል ያልቈጠረ እረኛ ልጅ፣ የነቢዩ መሐመድ ዘር በመሆኑ እንዲሁም እስልምና በደም ሥሮቹ ውስጥ እንዳለ በማሰብ በደስታ ተፍነከነከ።

ዳሩ ግን በዚህ የዘር ሐረግ ቈጠራ አብዝቶ የመደሰቱ ጒዳይ በጥንቃቄ መታየት አለበት። ቁርአን ትክክለኛ የአብርሃም ዘሮች የሚባሉት እግዚአብሔርን ያመኑ ሰዎች እንደ ሆኑ በሱራ 3÷68 ላይ በትክክል አስፍሮአል፦—

[3] David W. Shenk, *Global Gods* (Scottdale, Pa.: Herald Press, 1999), 48.

ከሰው ሁሉ በኢብራሂም ተገቢዎቹ እነዚያ የተከተሉትና ይህ ነቢይ እነዚያም ያመኑት ናቸው፤ አላህም የምእመናን ረዳት ነው።

የበኩር ልጅ

እስማኤል የአብርሃም የመጀመሪያ ልጅ ነው። በሴማውያን ባህል መሠረት የቤተሰብን ጎላፊነት የሚሸከመው የመጀመሪያ ልጅ እንደ ሆነ የሙስሊም ነገረ መለኮት ምሁራን ይናገራሉ። የአብርሃምና የይስሐቅ ታሪክ በጣም አስደናቂ ታሪክ ነው። ነገር ግን ለዓለም ሕዝብ ሁሉ የበረከት ምንጭ የሆነው የጎብረተሰብ ክፍል የሙስሊሙ ማኅበረሰብ እንደ ሆነ፣ ይህም በረከት የመጣው በአብርሃም የመጀመሪያ ልጅ በእስማኤል በኩል ነው ሲሉ እነዚህ ምሁራን ያስረዳሉ። ምሁራኑ እግዚአብሔር እስራኤልን የመረጠው ለተወሰነ ጊዜ ብቻ እንደ ሆነ ከሱራ 2+122 በመጥቀስ ይሞግታሉ። እግዚአብሔር ለአብርሃም አንተንና ዘርህን "ለሕዝብ ሁሉ ኢማም (መሪ)" አደርጋችኋለሁ ሲል የሰጠው ተስፋ፣ በመሐመድ መምጣት ምክንያት በአሁኑ ዘመን በሙስሊሙ ኡማ አማካይነት ተፈጽሞአል ሲሉ እነዚህ ሙስሊም ምሁራን ያስረዳሉ። በእርግጥ አብርሃም አይሁድም ሆነ ክርስቲያን አልነበረም፤ ነገር ግን እንደ አላህ ፈቃድ ለአላህ የሚሰግድና ለአላህ የሚታዘዝ ሰው ነበር። የአላህን ፈቃድ የፈጸመው በእስልምና እምነት ነው (ሱራ 3+67)።

አብደላ ዩሱፍ ዓሊ የተባለው የእስልምና ሃይማኖት ምሁር፣ "እግዚአብሔር ለእስራኤል የጸጋ ስጦታ ሰጥቶአል የሚለው ክርክር ግሩም በሆነ ሁኔታ ተጠናቋል፤ አሁን መዞር ያለብን በአብርሃም በኩል ለዐረቦች የመጣውን መንፈሳዊ ስጦታ ወደሚመለከተው ጉዳይ ነው ብሏል"[4]።

የሙስሊሙ ዓለም በእስማኤል በኩል አገኘሁት በሚለው መንፈሳዊ በረከት ሐሴት ያደርጋል። ሙስሊሞች ይህ ታሪክ ምክንያታዊና አመክንዮአዊ ነው የሚል እምነት አላቸው። የአብርሃም የመጀመሪያ ልጅ የሆነው እስማኤል ከብዙ ዓመታት በኋላ የእምነትና በዐረብያ የሙስሊም ማኅበረሰብ መመሠረት የሚያበሥር ችቦ ይዞ ቢነሣ የሚያስደንቅ አይደለም። የመጨረሻው ነቢይ የእስማኤል ዘር እንደሚሆን ግምት ነበር። ሙስሊሞች፣ እስራኤል ከዓለም ሕዝብ መካከል የተመረጠች የመሆኗ ጉዳይ እየደበዘዘ መምጣቱ፣ እግዚአብሔር የሙስሊሙን ማኅበረሰብ የዓለም ሕዝብ ሁሉ ብርሃን እንዲሆን

[4] Ali, *The Holy Qur'an*, 52.

ለመምረጡ ሁነኛ ማስረጃ ነው የሚል እምነት አላቸው። እግዚአብሔር ለሙስሊሙ ማኅበረሰብ የሰጠው አገልግሎት፣ ውስን ለሆነ ጊዜ እግዚአብሔር ለእስራኤል ከሰጣት አገልግሎቶች እጅግ ከፍ ያለ እንደ ሆነ ይታሰባል። አንድ የሙስሊም ሼክ፣ "በአግባቡ የማገናዘብ ችሎታ ያለው ሰው፣ ውሉ አድሮ የእስልምናን ትክክለኛነት መረዳቱ አይቀርም" ብሎ ሲናገር ሰምቼአለሁ።

አብርሃምና ይስሐቅ

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ይስሐቅ የሚያቀርበው ታሪክ፣ ከእስልምናው እጅ ታሪክ በጣም በተለየ መንገድ እንድንመለከተው ያደርገናል። ቁርአን ስለ አብርሃምና ስለ እስማኤል ያለውን ትምህርት ተመልክተናል፣ አሁን ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አብርሃምና ስለ ይስሐቅ ምን እንደሚያስተምር እንመልከት። ይህ ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ የምናካሂደው ጥናት ይሆናል፤ ምክንያቱም እስልምና ይስሐቅ ተባርኮአል ስለሚል እንዲሁም በተመሳሳይ ሁኔታ መጽሐፍ ቅዱስ እስማኤልም ተባርኮአል ስለሚል ነው። ይህ ለጥናታችን ጠቃሚ የአትኩሮት ቦታ ነው። የእስልምና ነገረ መለኮት ለእስማኤል ቀዳሚውን ስፍራ ይሰጣል፤ ይስሐቅን ያከብራል፤ ይባርከዋልም። መጽሐፍ ቅዱሳዊው ነገረ መለኮት ደግሞ በይስሐቅ በኩል በረከት ለሰዎች ሁሉ እንደ መጣ ሲያስተምር፣ የእስማኤልንም መባረክ ይቀበላል። በእርግጥ በዘፍጥረት 17+20 ላይ ትልቅ ሕዝብ እንዲሁም ዐሥራ ሁለት አለቆች ከአብርሃም የመጀመሪያ ልጅ ከእስማኤል እንደሚወጡ ጌታ እግዚአብሔር ተናግሮ ነበር።

በሁለት ልጆች መካከል ያለ ትግል

በይስሐቅ ሕይወት ውስጥ የተፈጸመው አስደናቂ ነገር በወንጌል ውስጥ ላለው አስደናቂ ነገር ምልክት ነው። ይስሐቅ ለአብርሃምና ለሣራ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጣቸው ነጻ ስጦታ ነው። የወንጌልም ባሕርይ እንደዚሁ ነው። በወንጌል ውስጥ ለሰዎች የተሰጠው የእግዚአብሔር ስጦታ ከሰዎች ፍልስፍና እንዲሁም ሃይማኖታዊ ከሆነ ሥርዐት እጅግ ያለፈ ነው። ማንኛውም ዐይነት ሰብአዊ ሥነ አመክንዮ፣ ፍልስፍና ወይም ሃይማኖት በወንጌል ውስጥ ያለውን እውነት የተከተለ ወይም ግምት ውስጥ ያስገባ አልነበረም። እግዚአብሔር በሰው ታሪክ ውስጥ ሰው ሆኖ በመገኘት ከሰዎች ጋር በመኖር ለሰዎችና በሰዎች ምክንያት መከራ ተቀብሎ ፍቅሩን ለእኛ ይገልጣል ብሎ እንኳን በውኑ በህልሙ ያሰበ እንኳ የለም። ለእኛ የተሰጠን ስጦታ ይህ ውድ የሆነ

የምሥራች ወንጌል ነው። ይህ ስጦታ በእኛ ጥረት ወይም መልካም ሥራ ምክንያት ያገኘነው ሳይሆን፣ በእምነትና በምስጋና የምንቀበለው ነው።

ከአብርሃም ዘመን ሁለት ሺህ ዓመት በኋላ፣ አዲስ ኪዳን በአብርሃም ቤት ውስጥ በሣራና በአጋር እንዲሁም በይስሐቅና በእስማኤል መካከል የነበረው ግጭት ምን ዐይነት የነገረ መለኮት ገጽታ እንዳለው በስፋት ያብራራል (ገላትያ 4÷21-31)። ሐዋርያው ጳውሎስ በአብርሃም ቤት የነበረው ትግል፣ በተራ እምነትና እግዚአብሔር በመሲሑ በኢየሱስ በኩል በገለጠው እምነት መካከል ያለውን ትግል የሚያሳይ ምሳሌ እንደ ሆነ ተናግሯል።

የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት፣ አብርሃም ከአጋር ጋር የነበረው ጥምረትና የእስማኤል መወለድ፣ ሰዎች እግዚአብሔርን ለማስደሰት የሚያደርጉትን ጥረት የሚያሳይ ተምሳሌት እንደ ሆነ ይገልጻሉ። በሌላ በኩል ደግሞ የይስሐቅ መወለድ፣ እግዚአብሔር ያለ ሰው አነሳሽነት በራሱ የጊዜ ሰሌዳ ለአብርሃምና ለሣራ የሰጣቸው ነጻ ስጦታ ነው። ማንኛውም ዐይነት ሃይማኖታዊ ሥርዐት ይስሐቅን አላስገኘም። የሁለቱ ሴቶችና የሁለቱ ልጆች ታሪክ የሚያሳየን፣ የማይገባንን የእግዚአብሔርን ጸጋ በእምነት በመቀበልና የእግዚአብሔርን ተስፋና በረከት የተለያዩ ሃይማኖታዊ ሥርዐቶችን በመፈጸም ከእግዚአብሔር እጅ ለመቀበል የሚደረገውን ሙከራ በንጽጽር የሚያሳይ ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ እነዚህ ሁለት የተለያዩ ጉዞዎች፣ የእግዚአብሔርን ጸጋ በሃይማኖታዊ ሥርዐቶችና በሰብአውያን ጥረት ለማግኘት የሚደረግ ጉዞ እንዲሁም በእግዚአብሔር ጸጋ የሚገኝ ችሮታ ተምሳሌቶች እንደ ሆኑ ጽፎአል። ሃይማኖታዊ ሥርዐቶችና የሰዎች ጥረት የእግዚአብሔርን ጸጋ ሊያመጡ ይችላሉን? እንደዚህ ከሆነ የእግዚአብሔርን ጸጋ ለማግኘት ምን ያህል ሃይማኖታዊ ሥርዐት መፈጸም አለብኝ? አልያ የእግዚአብሔር ጸጋ በእምነት ብቻ የሚገኝ ስጦታ ነው?

አንድ ጊዜ ከሙስሊም ጓደኞዬ ጋር ለአንድ ሳምንት ያህል በነበረን ጉዞ ወቅት እንዲህ ሲል አስተያየቱን ሰጥቶኛል፣ "ወንጌል አንተ እንደምትለው ከሆነ ክርስቲያን ከመሆን ይልቅ ሙስሊምነቴ በጣም ነጻ ያደርገኛል ማለት ነው"። ይህ ሰው ምን ማለቱ ነው? እኔ ምን ማለቱ እንደ ሆነ በእርግጠኝነት መናገር ይቸግረኛል። እኔ ያየሁት ነገር ቢኖር እየተጓዝን በነበርንበት ወቅት ለእስልምና ታማኝ የሆኑ ሙስሊም ጓደኞቼ ዕረፍት በምናደርግበት ጊዜ ሁሉ፣ ሃይማኖታዊ የጸሎት ሥርዐት (ሶላት) ለመፈጸም ሲጨናነቁ ተመልክቼአለሁ።

የተሰያዩ የእምነት ምሳሾች

የእስማኤልና የይስሐቅ ታሪክ ለሙስሊም ኡማና ለቤተ ክርስቲያን ያለው አስተዋጽኦ ምንድን ነው? በሙስሊም ኡማና በቤተ ክርስቲያን መካከል ያለው መሠረታዊ ልዩነት፣ በእስማኤልና በይስሐቅ መካከል የነበረው ልዩነት ቀጣይ ገጽታ ነውን? በሁለቱ የአብርሃም ልጆች መካከል የነበረው ልዩነት ውጤት ነው ማለት አይቻልም። ይልቁንም አብርሃም በውስጡ ለእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ምላሽ ለመስጠት ያደረገውን ትግል ያመለክታል።

አብርሃም የእግዚአብሔርን ፈቃድ በራሱ ጊዜ ለመፈጸም ርምጃ መውሰድ (እስማኤል) ወይስ የእግዚአብሔርን ጥሪ በመከተልና እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን በራሱ መንገድና ጊዜ እንዲፈጽም (ይስሐቅ) መጠበቅ ነበረበት? አብርሃም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ተራ በሆነ መንገድ መፈጸም (እስማኤል) ወይስ እግዚአብሔር ራሱ በተአምራዊና በሚያስደንቅ ሁኔታ እንዲፈጽመው (ይስሐቅ) መጠበቅ ነበረበት። እነዚህ ታሪኮች ስለ እስልምናና ስለ ወንጌል የሚያስተምሩት ትምህርት አላቸውን?

ቀደም ብሎ እንደ ተገለጸው ትግሉ ያለው በሙስሊም ኡማና በቤተ ክርስቲያን መካከል አይደለም። ይልቁንም ትግሉ የሚካሄደው በእኛ ነፍስ ውስጥ ሲሆን፣ ዕለት ተዕለት ለሚገጥሙን ተግዳሮቶች ምላሽ በምንሰጥበት ጊዜ የሚፈጠሩ ትንቅንቆች ናቸው። በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ተካፋዮች የምንሆነው፣ ሃይማኖታዊ ሥርዐቶችን በመፈጸም ነው ወይስ እግዚአብሔር ራሱ መንግሥቱን በሚያስደንቅ ሁኔታ እንዲመሠርት በተስፋ በመጠበቅ? ይህ ነው እንግዲህ ዐቢዩ ጥያቄ።

ዘርዐ ሐረግ

ልማዳዊ የሆነው የሰው አካሄድ በዘር ሐረግ ቁጠራና ግንኙነት የሚመራ ነው። ለምሳሌ እናትህ ማን ናት? አያትህን የማውቀው ይመስለኛል፣ ትልቅ ሰው ነበር። ቅድመ አያቴ ታሳቅ ሰባኪ ነበር። አንተ ሦስተኛው የወንቴ ልጅ ነህ። ከቅድመ አያቶቼ ውስጥ አንዱ፣ በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የአናባፕቲስት ሰማዕት ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ መሐመድና የሙስሊም ኡማ ከቁረይሽ እስከ እስማኤል ላለው የዘር ሐረግ ትልቅ ክብር ይሰጣሉ።

መጽሐፍ ቅዱሳዊው ታሪክ፣ አብርሃምን በእነዚህ የምልክታ ንጽሮቶች እንጻር እንድናየው አያደርጉንም። በመሠረቱ የዘር ሐረጉች የተመሰነ ጠቀሜታ አላቸው። ይሁንና እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። የአብርሃምን ታሪክ ስንመለከት መልክ ጼዴቅ የተባለ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላከ ካህን እናገኛለን። አብርሃም ነገሥታትን ገድሉና ዘርፎ ሲመለስ፣ ይህ ካህን አብርሃምን በመንገድ አግኝቶ ባረከውና ለእርሱ እንዲሁም ከእርሱ ጋር ለነበሩት ዳቦና ወይን ጠጅ ሰጣቸው። አብርሃምም ከሰበሰበው ንዋይ ሁሉ አንድ ዐሥረኛውን ለመልክ ጼዴቅ ሰጠው።

ዕብራውያን 7÷3 መልክ ጼዴቅ፣ "አባትና እናት፣ የትውልድም ቍጥር የሉትም" ይላል። ይሁንና መልክ ጼዴቅ ከአብርሃም ይበልጣል። ከዚህም የተነሣ መልክ ጼዴቅ አብርሃምን ባረከው፣ አብርሃምም ለመልክ ጼዴቅ ዐሥራትን ሰጠ።

የትውልድ ሐረጋችን እኛ የምናስበው ያህል አስፈላጊ እንዳልሆነ ልብ ልናደርግ ይገባናል። ማንነቱ በውል ከማይታወቀው ከመልክ ጼዴቅ ሕይወት ከምንማራቸው ቁም ነገሮች መካከል ይህ አንዱና ዋነኛው ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን የይስሐቅን ታሪክ ብንመለከት የዘር ሐረግ ቄጠራ የምናስበውን ያህል ትልቅ ሚና እንደሌለው እንገነዘባለን። የአብርሃም ሁለተኛው ልጅ ይስሐቅ የቃል ኪዳን ልጅ ተባለ። እስማኤል በእግዚአብሔር ተባርኮአል፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ዓለምን ለመባረክ ቃል ኪዳን የገባው በሁለተኛው ልጅ በይስሐቅ በኩል ነው። በእርግጥ እንዲህ ዐይነቱ ግርንፈጥ (የተገላቢጦሽ) አካሄድ ለበርካታ ባህሎች ባይተዋር ነው።

የአብርሃም ቤተሰብ

ከዓለማችን ነዋሪ ግማሽ የሚሆነው ሕዝብ የክርስትና፣ የእስልምናና የአይሁድ እምነት ተከታይ ስለሆነ፣ እምነቱን ከአብርሃም ጋር ያያይዛል። የእምነት ዘር የተዘራው በአብርሃም ቤት ሲሆን፣ ላለፉት አራት ሺህ ዓመታት ይህ ዘር በዓለም ዙሪያ ሲፈካና ሲያብብ ቆይቶአል። በእነዚህ የእምነት ቡድኖች መካከል የሚታዩት ዐበይት አንድነቶችና ልዩነቶች በአብርሃም ቤት ውስጥ የነበሩ ናቸው። እኛም በአብርሃም እምነት ጥላ ሥር ተገኝተናል። የአብርሃም የሕይወት ጉዞ እስማኤልንና ይስሐቅን አስገኝቶአል።

የአብርሃም የሕይወት ጉዞ ለአይሁዶች፣ ለክርስቲያኖችና ለሙስሊሞች መሠረት ነው። የሙሴ መጻሕፍት (ቶራ) ብቻ ሳይሆኑ፣ አዲስ ኪዳንና ቁርአን ለአብርሃም የእምነት ጉዞ የራሳቸው የሆነ ጉልሕ ምላሽ አላቸው። ከፍ ብለን ያየናቸው እነዚህ እውነታዎች ከሙስሊሞች ጋር ላለን ውይይት እንደመሠረት ሆነው ማገልገል አለባቸው።

የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ
ዘፍጥረት 2÷11-20
የቁርአን ምንባብ
ሱራ 21÷24-29

የአስተውሎትና የውይይት ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር ለአብርሃም ስለ ዘሩ ተስፋ ሰጥቶታል። ሚስቱ ሣራ መካን ነበረች። የእስማኤልና የይስሐቅ ታሪክ አብርሃም በእግዚአብሔርና እርሱ የሰጠውን ተስፋ ለማመን የሚያደርገውን ትግል ይገልጻል። እርስዎ፣ በአብርሃም ሕይወት ውስጥ ያለውን ትግል በምን ዐይነት መንገድ ሊረዱት ይችላሉ?
2. ቀጥሎ ባለው ዐረፍተ ነገር ላይ አስተያየት ስጥበት። በእስማኤልና በይስሐቅ መካከል ያለው ትግል የሚያሳየን እስልምናን ማዕከል ባደረገና መንፈስን ማዕከል ባደረገ እምነት መካከል የሚደረገውን ትግል ነው (ገላ 4÷21-31)።
3. ከፍ ብሎ በነበረን ውይይት እንደተገለጸው ሙስሊም ጓደኛዬ ሲናገር ለእርሱ በሙስሊምነቱ ወንጌል በጣም ነጻ ያደርጋል ብሎ ነበር። የተናገረው እውነት ነውን? ለመልስህ መረጃ ስጥ።
4. የዘር ሐረግ በሙስሊም ኡማ ውስጥ ምን ያህል ጉልህ ሚና እንዳለው ተመልከት። የዘር ሐረግን በተመለከተ የክርስቲያኖች ትኩረት ምን ላይ እንደሆነ ምሳሌዎችን አገናዝብ። የመልክጼዴቅ ታሪክ የትውልድ ቍጥር ላይ ከፍተኛ ትኩረት መስጠትን የሚተቸው እንዴት ነው? (ሱራ 106÷1-4፤ ዘፍጥረት 14÷18-20፣ ዕብራውያን 7÷1-10)
5. አብርሃም ለሙስሊሞች የመካከለኛ ዘመን ነቢይ መሆኑና ለክርስቲያኖች የእምነት አባት መሆኑ ያለውን ትርጉም አዘልነት አነጻጽር። (ሱራ 3÷96-97፣ ሮሜ 4÷12:16)
6. የአብርሃም ውርስ በአይሁዶች፣ በክርስቲያኖችና በሙስሊሞች መካከል ሰላምን ለመፍጠር ምን ያህል አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል?

ምዕራፍ አምስት

መሪዎች

የነቢያት መደምደሚያ—መሲሑ

ኢየሱስ መሲሕ ነው። ኢየሱስ መሲሕ እንደ ሆነ ሙስሊሞችም ሆኑ ክርስቲያኖች በአንድ ይስማማሉ። እንዲሁም ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ነቢያት የእግዚአብሔር ቃል እንዳበሠሩ ከሙሉ ልብ ያምናሉ። ነገር ግን በእስልምናና በክርስትና ስለ መሲሑና ስለ ነቢያት የሚሰጠው ትርጓሜ እጅግ ለየቅል ነው።

ለምሳሌ ሙስሊሞች ሁሉ፣ መሐመድ የነቢያት መደምደሚያ ናቸው እንዲሁም መሐመድ የእግዚአብሔርን የመጨረሻ እንዲሁም የተጣራና የማይለወጥ መልእክት ሰብከዋል ብለው ያምናሉ። ነገር ግን ክርስቲያኖች የመሐመድ መልእክት የመሲሑን መልእክት ተክቶአል የሚለውን የእስልምና ትምህርት ፈጽመው አይቀበሉም። ምክንያቱም ክርስቲያኖች ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታና አዳኝ ነው ብለው ከሙሉ ልብ ስለሚያምኑና ስለሚመሰክሩ ነው። ይህም ምስክርነት ሙስሊሞች ስለ መሲሑ ካላቸው እምነት በእጅጉ የተለየ ነው።

መሲሑን በተመለከተ በክርስቲያኖችና በሙስሊሞች መካከል ያለው ልዩነት በቀላሉ የሚታይ ጉዳይ አይደለም። ይህ ምዕራፍ፣ ይህን ርእሰ ጉዳይ በተመለከተ በሁለቱ ሃይማኖቶች መካከል ያለውን መሠረታዊ ልዩነት መዳሰስ፣ የትኩረት አቅጣጫው ነው። ስለ መሲሑ ሕይወትና አገልግሎት የክርስቲያኖች መሠረተ እምነት ምንድን ነው? በአንጻሩ ሙስሊሞች ስለ መሲሑ ያላቸው መረዳት ምን ይመስላል? የነቢያት መደምደሚያ እንደ ሆኑ ስለሚታመነው ስለ ነቢዩ መሐመድ ሙስሊሞች ያላቸው ግንዛቤ ምንድን ነው? በርእሰ ጉዳዩ ላይ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች የሚስማሙባቸው ነጥቦች የትኞቹ ናቸው? እነዚህ ሁሉ ርእሰ ጉዳዮች የሚያመጡት ለውጥ ምንድን ነው?

መሲሑ በክርስትና እምነት

ምዕራፍ ሦስት ስለ አዳምና ስለ ሔዋን በተለይ ደግሞ መልካሙንና ክፉውን ከሚያስታውቀው ዛፍ ከበሉ በኋላ እግዚአብሔር ለእነርሱ ያደረገውን ክብካቤ/ጥንቃቄ ምን እንደሚመስል ይዳስሳል። በእስልምና ሃይማኖት

የመጀመሪያ ነቢይ ነው ተብሎ የሚታመነው አዳም ሲሆን፣ ቁርአን እግዚአብሔር ለአዳም መመሪያን እንዳወረደለት ይገልጻል። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ከሴቲቱ ዘር የሚወለደው መሲሕ፣ የክፉውን (የእባቡን) ራስ እንደሚቀጠቅጥ በአንጻሩ ደግሞ ክፉው (እባቡ) የመሲሑን ሰኰና እንደሚመታ (ዘፍጥረት 3÷15) ያስተምራል። እግዚአብሔር ይመጣል ብሎ ለሰው ልጆች የሰጠው ተስፋ፣ ሰኰናው የሚቀጠቀጠው ወይም መከራን የሚቀበለው አዳኝ፣ መሲሑ እንደ ሆነ ክርስቲያኖች ያምናሉ[1]። በእስልምና እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ምሪትን ይሰጣቸው ዘንድ ተስፋ እንደ ገባላቸው ሲታመን፣ በክርስትና (በመጽሐፍ ቅዱስ) ግን እግዚአብሔር ሰዎችን ለማዳን ምሪትን ሳይሆን መድኀኒትን እንደ ሰጠ ያስተምራል።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተስፋ—መሲሑ

አዳምና ሔዋን በኤድን ገነት ኀጢአት ከሠሩበት ጊዜ ጀምሮ፣ መሲሑ እስከ መጣበት ጊዜ ድረስ፣ እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ አማካይነት ደግሞ ደጋግሞ ያስረገጠው ተስፋ፣ በሞትና በኀጢአት ላይ ድል የሚነሣውን ቤዛ/አዳኝ እንደሚልክልን ነው። በዚህ አጭር አሰሳዊ ጥናት፣ እግዚአብሔር የሰጠውን ተስፋና ኪዳን የሚገልጹትን መልክቶች በጥልቀትና በዝርዝር እንመለከታቸዋለን። እግዚአብሔር በየዘመናቱ ያስነሣቸው ነቢያት በሙሉ፣ ይህን የተስፋ ልጅ አስመልክቶ ትንቢት ተናግረዋል። ነቢዩ ኢሳይያስ ይህን የተስፋ ቃል አስመልክቶ ከየትኛውም ነቢይ ይልቅ በዚህ መልኩ በግልጽ ተናግሮአል፦ "ሕፃን ተወልዶልናልና ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል፤ ስሙም ድንቅ መካር፣ ኀያል አምላክ፣ የዘላለም አባት፣ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል። ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም ድረስ በፍርድና በጽድቅ ያድነውና ይደግፈው ዘንድ በዳዊት ዙፋንና በመንግሥቱ ላይ አለቅነቱ ይበዛል" (ኢሳይያስ 9÷6-7)።

ኢሳይያስ ከኖረበት ከብዙ ዓመታት በፊት፣ እግዚአብሔር አብርሃምን ሲጠራው ስለዚህ ተስፋ ገልጦለት ነበር። እግዚአብሔር ለአብርሃም በዘሩ ሕዝቦች (አሕዛብ) ሁሉ እንደሚባረኩ በዘፍጥረት 12÷1-3 ላይ እንዲህ ሲል ተናግሮታል፦ "ከአገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ

[1] አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ዘፍጥረት 3÷15 የመሲሑን ቤዛዊ ሥራ የሚገልጽ ተስፋ ነው የሚል እምነት የላቸውም። አብዛኞቹ ሊቃውንት እንዲሁም በርካታ ቤተ ክርስቲያናት፣ ይህ ኪዳን በመሲሑ በኢየሱስ ሕይወትና አገልግሎት ሙሉ ለሙሉ እንደ ተፈጸመ ከሙሉ ልባቸው ያምናሉ።

ወደማሳይህ ምድር ውጣ. . .የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ"። ይህ የተስፋ ቃል፣ የአብርሃምን እምነት የተጋሩትን የእግዚአብሔርን ሰዎች ማመልከቱ እሙን ቢሆንም፣ በሌላ አንጻር ደግሞ ስለ መሲሑ መምጣት የሚያስተምር እንደ ሆነ ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዳሉ (ገላትያ 3÷16)።

እግዚአብሔር በአብርሃም የእምነት መስመር እንዲመላለሱ የእስራኤልን ሕዝብ የቃል ኪዳን ሕዝብ አድርጉ መረጠ[2]። እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝብ የመረጠው ለዚህ ተልእኮ ለዓለም ሁሉ ብርሃን እንዲሆኑ በማሰብ ነበር (ኢሳይያስ 49÷6)። ይህን የቃል ኪዳን ሕዝብ ስናስብ ልንደነቅ እንችላለን። እስራኤላውያን የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ሕዝብ መሆን ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ መረዳት ሲጀምሩ በግብፅ የፈርዖን ባሮች ሆኑ።

እግዚአብሔር "እኔ ነኝ" ሲል ራሱን ገለጠለት

አብርሃም ከኖረበት ከአምስት መቶ ዓመት በኋላ፣ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብፅ ባርነት ነጻ ያወጣቸው ዘንድ ሙሴን ላከላቸው። እግዚአብሔር ሙሴን የተገናኘበትና የጠራበት ሁኔታ እጅግ አስደናቂ ነበር። ይህ የጥሪ ሁኔታም የመሲሑን አገልግሎት ፍንትው አድርጉ የሚያሳይ ነው። እግዚአብሔር ለሙሴ የመገለጡ ጉዳይ ለእስራኤላውያን የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ሕዝብ የሚል ማንነት አጉናጽፎአቸዋል።

እግዚአብሔር ለሙሴ በሚገለጥበት ወቅት፣ ሙሴ በሲና ተራራ አጠገብ በጉቾን ይጠብቅ ነበር። ሙሴም በቀጥቋጦ ውስጥ እሳት ሲነድ አየ፣ ነገር ግን እሳቱ ቀጥቋጦውን አላቃጠለውም። ሙሴ ወደ ቀጥቋጦው እየቀረበ ሲመጣ እግዚአብሔር ሙሴን፣ "ሙሴ"፣ "ሙሴ" ሲል ጠራው። ወደ ግብፅ ሄዶም እስራኤላውያንን ዐርነት እንዲያወጣቸው አዘዘው።

ሙሴም በመደነቅ፣ "ስምህ ማን ነው?" ሲል እግዚአብሔርን ጠየቀ። እግዚአብሔርም "ያለና የሚኖር እኔ ነኝ" አለው (ዘፀአት 3÷1-15)። የነገረ መለኮት ምሁራን ያካሄዷቸው ጥናቶች እንደሚያስረዱት፣ "ያለና የሚኖር" የሚለው ሐረግ ትርጕሙ፣ በተወሰነ መጠንም ቢሆን ያህዌ በሚለው

[2] እስራኤል ማለት፣ እግዚአብሔርን አጥብቆ የሚሻ/የሚፈልግ ማለት ነው። ምንም እንኳ እግዚአብሔር ዘወትር ታማኝ ቢሆንም፣ የኪዳኑ ሕዝብ የሆነው እስራኤል ግን ሁል ጊዜ ለአምላኩ ለእግዚአብሔር ታማኝ አይደለም። የእግዚአብሔር ሕዝብ ታሪክ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገውን ትግል የሚያሳይ ነው።

የእግዚአብሔር ስም ውስጥ እንደሚገኝ ይገልጻሉ። ነገር ግን "ያለና የሚኖር" የሚለው ሐረግ፣ እግዚአብሔር በየትኛውም ዐይነት ስም ሊገለጽ እንደማይችል አመላካች ነው። እርሱ ያለ፣ የነበረና ወደ ፊትም የሚኖር ነው። እርሱ እኛን በየግላችን በማንነታችን የሚገናኘን አምላክ ነው። እግዚአብሔር የግል፣ የኪዳንና የጽድቅ አምላክ ሲሆን፣ ፈቃዱን ብቻ ሳይሆን፣ ራሱንም እንኳ ለሰው ልጆች የገለጠ ጌታ ነው። እኛን ከእስራት ለማውጣት በላከልን መገለጦች አማካይነት ይሠራል። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከፈርዖን የባርነት ቀንበር ነጻ እንዳወጣቸው፣ እርሱን የሚከተሉትን በሙሉ ከክፉ እስራት ነጻ ያወጣቸዋል።

እግዚአብሔር ለሙሴ በቀሩጥጸጠ ውስጥ የተገለጠበት ከሥተት ለመጽሐፍ ቅዱሳዊው ነገረ መለኮት አዲስ ምዕራፍ ከፍቶአል። አብርሃም እግዚአብሔርን የሚያውቀው ኤሎሂም በሚለው ስሙ ነበር። ቀደም ብሎ ባለው ምዕራፍ ውስጥ አላህ የሚለው የዐረቦቹ ስያሜ ኤሎሂም ከሚለው ከብሉይ ኪዳኑ የእግዚአብሔር ስም ጋር ተመሳሳይነት እንዳለው ገልፀን ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ለሙሴ "ያለና የሚኖር" አምላክ በማለት ራሱን ሲገልጥለት፣ እርሱ የቃል ኪዳን አምላክና ሰዎችን በግል የሚገናኝ እንደ ሆነ አስታውቆታል። እኛም ለእግዚአብሔር ጥሪ ምላሽ ስንሰጥና ከእርሱ ጋር ጎብረት ስናደርግ፣ "ያለና የሚኖር አምላክ የእኔና የእናንተ አምላክ ነው" ማለት እንጀምራለን።

ይህ ዐይነቱ ለውጥ እግዚአብሔርን ማወቅ እንደ ሆነ፣ መጽሐፍ ቅዱስ በዘፀአት 6÷2-3 እንዲህ ሲል ይገልጻል:— "እግዚአብሔርም ሙሴን ተናገረው፣ አለውም፣ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፣ ለአብርሃምም፣ ለይስሐቅም፣ ለያዕቆብም ሁሉን እንደሚችል አምላክ ተገለጥሁ፣ ነገር ግን ስሜ እግዚአብሔር አልታወቃቸውም ነበር"።

የመሲሑ ስሞች

የመሲሑ አገልግሎት እግዚአብሔር ራሱን፣ "ያለና የሚኖር" በማለት ካስተዋወቀው መገለጥ ጋር ይስማማል። የእግዚአብሔር ዋና ትኩረት ፈቃዱን እንጂ ከሰው ጋር ያለውን መስተጋብር/ግንኙነት ያላካተተ ቢሆን ኖሮ፣ በወንጌል ውስጥ የተገለጠው የመሲሑ አገልግሎት ትርጉም አልባ ይሆን ነበር። ሆኖም ግን መልአኩ ስለ ኢየሱስ መወለድ ሲያበሥር፣ እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለሙሴ ከሰጠው መገለጥ ጋር የሚስማሙ ሁለት ስሞችን ለመሲሑ ሰጥቶታል።

የመጀመሪያው ስም ኢየሱስ የሚል ነው። መልአኩ፣ "ልጅም ትወልዳለሽ፤ እርሱ ሕዝቡን ከኀጢአታቸው ያድናቸዋልና፣ ስሙን ኢየሱስ ትይዋለሽ" (ማቴዎስ 1÷21) ሲል ለሕፃኑ ስም አወጣለት። ኢየሱስ የሚለው ስም የዕብራይስጥ ስም የተወሰደ ሲሆን ትርጉሙም፣ "ያህዌ ያድናል" ማለት ነው። ነገር ግን የሚያድነን ከምንድን ነው? መልአኩ ሲናገር "ሕዝቡን ከኀጢአታቸው ያድናቸዋል" ብሎአል። ከኀጢአታቸው የሚያድናቸው እንዴት ነው? እግዚአብሔር በመሲሑ በኩል ወደ ሰው ታሪክና ወደ እያንዳንዳችን ሕይወት ፈቃዱን ከማስታወቅ በበለጠ ሁኔታ መጥቶአል። ምንም እንኳ ኀጢአታችን ብዙ ቢሆንም፣ ከኀጢአትና ኀጢአት ካስከተለው ሞት ሊያድነን ወደ እኛ መጥቶአል። እግዚአብሔር በራሱ አነሳሽነት እንዴት ወደ ሰው እንደ መጣ በሚቀጥለው ምዕራፍ በስፋት እንመለከታለን።

የመሲሑ ሁለተኛ ስም አማኑኤል የሚለው ስም ነው። አማኑኤል ማለት "እግዚአብሔር ከእኛ ጋር" ነው ማለት ነው። ኢየሱስ አገልግሎት ሲጀምር ልክ እንደ እግዚአብሔር በሥልጣን ይሠራ ስለነበር፣ ሰዎች ሁሉ ይደነቁበት ነበር። የክርስቶስ ሕይወት በእውነት፣ "እግዚአብሔር ከእኛ ጋር" እንዳለ የሚያሳይ ነበር። ጌታ ኢየሱስ ሲናገር፣ "እኔን ያየ አብን አይቶአል" ብሎአል (ዮሐንስ 14÷9)፤ ምክንያቱም እርሱ የአብ ብቸኛና ፍጹም ወኪል ስለሆነ ነው[3]።

ከሁለቱ ስሞች በተጨማሪ ኢየሱስ፣ "የእግዚአብሔር በግ" የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል። ኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት ከመጀመሩ በፊት በዮርዳኖስ ወንዝ ቢጠመቅ፣ እርሱን ያጠመቀው መጥምቁ ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ እንዲህ ሲል ተናግሮአል:— "እነሆ የዓለምን ኀጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ"።

ወደ ኋላ መለስ ብለን ስንመለከት፣ የአብርሃምን ልጅ ለግዳን እግዚአብሔር የመሥዋዕቱን በግ አዘጋጀ። ክርስቲያኖች ይህ መሥዋዕት እኛ ከእግዚአብሔር ዘንድ ይቅርታ እንድናገኝና እንድንድን በእኛ ፈንታ መሥዋዕት የሆነውን ኢየሱስን ያመለክታል ብለው ያምናሉ። በሚቀጥለው ምዕራፍ ይህን ጉዳይ በስፋት ለመመልከት እንሞክራለን።

---

[3] በኢትዮጵያ "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" በመባል የሚታወቀው የሃይማኖት ድርጅት፣ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር አብ ነው ወይም ኢየሱስና አብ አንድ አካል ናቸው የሚል የተሳሳተ ትምህርት ያስተምራል። የዚህን ሃይማኖት መናፍቃዊ ትምህርት በስፋት መመልከት ከፈለጉ፣ ተስፋዬ ሮበሌ፣ *ሰባልዮሳውያን— "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" የሥላሴ አስተምህሮ በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን፣* (ቅጽ 1) በሚል ርእስ ያዘጋጀውን መጽሐፍ ይመለከቷል።

ይህንን ነገር ሁሉ ማየት ያስፈለገው የመጽሐፍ ቅዱስ ምስክርነት እንደሚነግረን፣ አፍቃሬ አባታችን የሆነው እግዚአብሔር፣ እኛን ለማዳን ቤዛና አዳኝ ሆኖ በመሲሑ በኩል መገለጡን እንድንረዳ ታስቦ ነው። ይህ እውነት የነገረ መለኮት ምሁራን ሆን ብለው የፈጠሩት ታሪክ አይደለም። ይልቁንም የኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት፣ ምስክርነትና አገልግሎት ይህንን እውነት በተጨባጭ የሚያሳየን ታሪክ ነው። ሐሳቡን በደንብ ለመገንዘብ የተወሰኑ ምሳሌዎችን እንመልከት:—

በአንድ አጋጣሚ ኢየሱስ "አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ" ብሎ ለአይሁድ ሲነግራቸው፣ እጅግ ተገርመው ነበር። "እኔ አለሁ" የሚለው ዐረፍተ ነገር እግዚአብሔር ለሙሴ ሲገለጥ፣ "ያለና የሚኖር" በማለት ራሱን ይፋ ካደረገበት ስም ጋር አንድ ነው።

በሌላ አጋጣሚ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ መካከል ከሦስቱ ጋር በተራራ ላይ ነበር። በዚያ ጊዜ ሙሴና ኤልያስ ተገልጠው ከኢየሱስ ጋር ተነጋግረው ነበር። ሙሴና ኤልያስ በብሉይ ኪዳን ታላላቅ ነቢያት (ወበይተ ነቢያት) ከሚባሉት የእግዚአብሔር ነቢያት መካከል ናቸው፣ ምክንያቱም ሙሴ ሕግ ሰጪ ሲሆን፣ ኤልያስ ደግሞ ታላላቅ ተአምራትን ያደረገ ነቢይ ነው። ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ በተራራው ላይ እንዳሉ ሙሴና ኤልያስ ተሰወሩባቸው፣ ደመናም ተራራውን ሸፈነው፣ እግዚአብሔርም በደመና ውስጥ፣ "በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው፣ እርሱን ስሙት" ሲል ተናገረ። ከሞቱና ከትንሣኤው በኋላ ኢየሱስ፣ "ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ" ሲል ተናግሮአል (ማቴ 28+18)።

መሲሑ ኢየሱስ ማን ነው?

ይህ ምን ማለት ነው? እነዚህ አስደናቂ የሆኑ ነገሮች ከመሲሑ ከኢየሱስ ጋር ያላቸውን ግንኙነት፣ አንድ ሰው በነገረ መለኮት ቋንቋ እንዴት ሊገልጻቸው ይችላል?

ከክርስቶስ ሞት፣ ትንሣኤና ዕርገት በኋላ የአዲስ ኪዳን ጸሐፍያን ክርስቶስን እንዲህ ሲሉ ገልጸውታል:—

> እግዚአብሔርም ሙላቱ ሁሉ በእርሱ ይሆን ዘንድ ወዶአልና፣ በመስቀሉ ላይ በፈሰሰው ደሙ ሰላምን በማድረግ በምድርም ሆነ በሰማይ ያለውን ነገር ሁሉ በእርሱ በኩል ከራሱ ጋር አስታረቀ (ቈላ 1+19-20)።
>
> ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዐይነትና በብዙ ጕዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፣ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን፣ እርሱም የክብሩ መንጸባረቅና የባሕሪዩ ምሳሌ ሆኖ ሁሉን በሥልጣኑ ቃል እየደገፈ፣ ኀጢአታችንን በራሱ ካነጻ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ (ዕብራውያን 1+1-3)።

እኔና ቤተሰቦቼ ሶማሊያን በረገጥንበት ወቅት፣ ከመሲሑ ደቀ መዛሙርት ውስጥ አንዱ የሆነውን ሱማሊያዊ በሚኖርበት ሚስዮን ትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ አገኘነው። በወቅቱ ከእግራችን በታች ምግብ ፍለጋ ወዲህ ወዲያ የሚርመሰመሱትን ጕንዳኖች በማመላከት፣ ይህ ግለሰብ እንዲህ አለኝ:— "የእነዚህ ጕንዳኖች ጓደኛ ለመሆን ፈልገህል እንበል። አንተ ወደ እነርሱ ስትጠጋ ፈርተው ከአንተ ይሸሻሉ፣ ወደ ጕድጓዳቸውም ይገባሉ። የጕንዳን ጓደኛ ለመሆን ከፈለግህ፣ ብቸኛው መንገድ ጕንዳን መሆን ነው ያለብህ"።

ንግግሩን በመቀጠል፣ "እግዚአብሔር በመሲሑ በኩል ያደረገው ነገር ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ነው። እኛ በእግዚአብሔር ፊት እንደ ጕንዳኖች ነን። ይሁንና እግዚአብሔር የሰው ወዳጅ መሆን ፈለገ። ከዚህም የተነሣ እግዚአብሔር በመሲሑ በኩል ከእኛ አንደ አንዱ ሆነ"።

መሲሕ የሚለው ስም ምን ማለት ነው? መሲሕ ማለት፣ "የተቀባ" ማለት ነው። ተልእኮውስ ምንድን ነው? ከክርስቶስ ልደት ከአምስት መቶ ዓመታት በፊት ነቢዩ ኢሳይያስ ስለ መሲሑ ተልእኮ እንዲህ ሲል ጽፎአል:—

> የጌታ የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው፣ ለድኾች የምሥራችን እሰብክ ዘንድ እግዚአብሔር ቀብቶኛልና፣ ልባቸው የተሰበረውን እጠግን ዘንድ፣ ለተማረኩትም ነጻነትን፣ ለታሰሩትም መፈታትን እናገር ዘንድ ልኮልኛል። የተወደደችውን የእግዚአብሔርን ዓመት፣ አምላካችንም የሚበቀልበትን ቀን እናገር ዘንድ፣ የሚያለቅሱትንም ሁሉ አጽናና ዘንድ እግዚአብሔር ለክብሩ የተከላቸው የጽድቅ ዛፎች እንዲባሉ ለጽዮን አልቃሾች አደርግላቸው ዘንድ፣ በዐመድ ፈንታ አክሊልን፣ በልቅሶም ፋንታ የደስታን ዘይት፣ በሐዘንም መንፈስ ፋንታ የምስጋናን መጐናጸፊያ አሰጣቸው ዘንድ ልኮኛል" (ኢሳይያስ 61+1-3)።

ኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎቱን በናዝሬት ሲጀምር ኢሳይያስ 61+1-3 ያለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ለአይሁድ ጉባኤ አንብቦ ነበር። መጽሐፉን ካነበበ በኋላ፣ "ዛሬ ይህ መጽሐፍ በጆሮአችሁ ተፈጸመ ይላቸው ጀመር" (ሉቃስ 4+21)። ይህ ዐይነቱ ንግግር በሕዝቡ ላይ ታላቅ መደነቅን የፈጠረ ነበር። ይህ ነው እንግዲህ የኢየሱስ ክርስቶስ ተልእኮ። ሙስሊሞች የነቢያት መደምደሚያ የሚሏቸው የነቢዩ መሐመድ ተልእኮና ግብስ ምን ነበር?

የነቢያት መደምደሚያ በእስልምና ሃይማኖት

መሐመድ የእግዚአብሔር መልእክተኛ (ረሱል) እንደ ሆኑ ሙስሊሞች ያምናሉ። ይህ እርሳቸው ለሰው ልጆች የአላህን መልእክት የሚናገሩ ነቢይ ናቸው ማለት ነው። እስልምና በዓለም ላይ ላሉ ሕዝቦች ሁሉ ነቢያት ተልከውላቸዋል ሲል ያስተምራል። ነገር ግን መልእክተኛ (ረሱል) የሚለውን ቦታ የሚጐናጸፉት እግዚአብሔር መጻሕፍትን እንዲጽፉ መገለጥን የሰጣቸው ሰዎች (ነቢያት) ብቻ ናቸው።

መሐመድ የመጨረሻ መልእክት የሆነውን ቁርአን፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተቀበሉ የመጨረሻው መልእክተኛ ናቸው። መሐመድ የነቢያት ሁሉ ማሳረጊያ/ማክተሚያ ናቸው፣ ይህም ማለት እርሳቸው በመጨረሻው ዘመን የመጡና የነቢያት ሁሉ መደምደሚያ ናቸው ማለት ነው። ስለ ነቢዩ መሐመድ ቁርአን እንዲህ ይላል፦—

> መሐመድ ከወንዶቻችሁ የአንድ ሰው አባት አይደለም፣ ግን የአላህ መልእክተኛና የነቢዮች መደምደሚያ ነው፣ አላህም በነገሩ ሁሉ ዐዋቂ ነው (ሱራ 33+40)።
>
> አንተንም ለሰዎች ሁሉ በማላ አብሳሪና አስፈራሪ አድርገን ቢኾን እንጂ አልላክንህም፣ ግን አብዛኞቹ ሰዎች አያውቁም (ሱራ 34+28)።
>
> እርሱ ያ አጋሪዎቹ ቢጠሉም መልእክተኛውን በመምሪያ (መጽሐፍ)፣ በእውነተኛው ሃይማኖትም (በኢስላም)፣ ከሃይማኖት ሁሉ በላይ ይፋ ሊያደርገው የላከ ነው (ሱራ 61+9 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)።

መሐመድ የመጨረሻ ነቢይ ሲሆኑ፣ የቀድሞ ነቢያቶች ያስተማሩትን ትምህርት ለማጽናትና ለማብራራት የተላኩ የእግዚአብሔር መልእክተኛ

ናቸው። ሙስሊሞች፣ ቀደምት ነቢያት የመጨረሻ ነቢይ ስለሆኑት ስለመሐመድ ተልእኮ እንደ ተነበዩ ጠንካራ እምነት አላቸው። ከዚህም የተነሣ አንዳንድ ሙስሊም ምሁራን፣ ስለ ነቢዩ መሐመድ መምጣት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ትንቢት ተነግሮ እንደ ሆነ በሚል፣ መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት ጀምረዋል።

መጽሐፍ ቅዱስና መሐመድ

ሙስሊሞች ስለ መሐመድ መምጣት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ትንቢት ተነግሮአል የሚለውን ግምታዊ ትምህርት እውን ቢሆን በሚል፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት ነቢያትና ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገሩዋቸውን ንግግሮች በጥንቃቄ እያጠኑ ነው። በብሉይ ኪዳን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የተነገሩ ትንቢቶች ለመሐመድ የተነገሩ ናቸው ሲሉ ይከራከራሉ። ለምሳሌ የሚከተለውን ክፍል እንደ ማስረጃ ያቀርባሉ፦—

> እግዚአብሔርም አለኝ፦— የተናገሩት መልካም ነው፣ ከወንድሞቻቸው መካከል እንደ አንተ ያለ ነቢይ አስነሣላቸዋለሁ፣ ቃሌንም በአፉ አደርጋለሁ፣ ያዘዝሁትንም ቃል ሁሉ ይነግራቸዋል፣ በስሜም የሚናገረውን ቃሌን የማይሰማውን ሰው እኔ እበቀልለታለሁ (ዘዳግም 18+17-19)።

ሙስሊሞች ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፣ ሙሴ ስለ መሐመድ መምጣት የተናገረው ትንቢት ነው ሲሉ በእርግጠኝነት ይገልጻሉ። ሙስሊሞች በተለየ ሁኔታ እንቄቅልሽ የሚሆንባቸው፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ነቢዩ መሐመድ የተናገረው አንዳችም ትንቢት የለም የሚለው ጉዳይ ነው። ይህ ጉዳይ ለሙስሊሞች እንቄቅልሽ የሆነበት ዐቢይ ምክንያት ቁርአን በሱራ 61+6 እንዲህ ስለሚል ነው፦— "የመርየም ልጅ ኢሳም፦— የእስራኤል ልጆች ሆይ እኔ ከተውራት በፊት ያለውን የማረጋግጥና ከእኔ በኋላ በሚመጣው መልእክተኛ ስሙ አሕመድ በሆነው የማበሥር ስሆን፣ ወደናንተ (የተላክሁ) የአላህ መልእክተኛ ነኝ ባለ ጊዜ (አስታውስ)፣ በግልጽ ታምራቶች በመጣቸውም ጊዜ ይህ ግልጽ ድግምት ነው አሉ"።

ቁርአን ስለ ነቢዩ መሐመድ መምጣት ኢየሱስ ትንቢት ተናግሮአል ካለ፣ ትንቢቱ በየትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ ተጽፎ ይገኛል? ሙስሊም ምሁራን በመደነቅ፣ "ስለ መሐመድ ኢየሱስ የተናገረውን ትንቢት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አግኝተነዋል" ይላሉ።

ሐኒስበርግ በሚገኘው የሙስሊም ማዕከል ይሠራ የነበረ አንድ የሙስሊሞች መሪ (ኢማም)፣ ምስጋና በተሞላበት አንደበት፣ "እግዚአብሔር ይመስገን" ብሎ አምላኩን ካመሰገነ በኋላ፣ "ኢየሱስ ክርስቶስ፣ መሐመድ ሲመጣ ሰዎችን ሁሉ ወደ እውነት ይመራል ሲል ትንቢት ተናግሮአል። ነገር ግን እጅግ በሚያሳዝን ሁኔታ መሐመድ የሚለውን ቃል መንፈስ ቅዱስ በሚለው ቃል በመቀየር ኢየሱስ ስለ መሐመድ የተናገረውን ትንቢት ለውጠውታል" ሲል ተናገረኝ።

ይህ የሙስሊሞቹ መሪ (ኢማም) ንግግር፣ በዓለም ዙሪያ በሚገኙ የሙስሊም የነገረ መለኮት ማዕከሎች ሁሉ የሚሰጥ ትምህርት በመሆኑ፣ አስተያየት ልንሰጥበት ይገባል። በግሪክ ወደ ተጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ በመሄድ ሙስሊሞች የሚጠቅሷቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ምን እንደሚሉ መመልከት ያሻል። በዮሐንስ 14÷16:26፤ 16÷7 ኢየሱስ አጽናኙ እንደሚመጣ ተናግሮአል። የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት ደግሞ፣ አጽናኙ መንፈስ ቅዱስ እንደ ሆነ በግልጽ ያስተምራሉ። የግሪኩ መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ፓራክሊቶስ" የሚለው ቃል በአማርኛ ቅጆች ላይ "አጽናኝ" ተብሎ ነው የተተረጐመው። ነገር ግን ሙስሊም ምሁራን፣ ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን ስለበረዙት እንጂ በመጀመሪያ በዚህ ክፍል ላይ የተነገረው ቃል፣ "ፐሪክሉቶስ" ወይም "የተከበረው" የሚለው ቃል ነበር በማለት ይከራከራሉ[4]። በዐረብኛ መሐመድ የሚለው ቃል፣ "የተከበረ" የሚል ትርጉም አለውና። ስለዚህ ሙስሊሞች ኢየሱስ የተናገረው ስለ መንፈስ ቅዱስ ሳይሆን ስለ መሐመድ ነው በዮች ናቸው።

እኔም ለሙስሊሞቹ መሪ (ኢማም) እንዲህ ስል መልስ ሰጠሁት፦— "ሙስሊሞችም ሆንን ክርስቲያኖች እግዚአብሔር ወደ እውነት ሁሉ እንዲመራን እንጸልያለን። የሙስሊሞችም ሆነ የክርስቲያኖች ቅዱሳት መጻሕፍት ሰዎች ቅዱሳት መጻሕፍትን ቅንጣት ታህል እንዳይቀይሩ ወይም እንዳያበላሹ ያስጠነቅቃሉ። ዛሬ አምስት ሺህ የሚሆኑ ጥንታዊ የእጁ ኪዳን መጻሕፍት ቅጆች በእጃችን አሉ። እነዚህ ጥንታዊ ቅጆች ሁሉ "አጽናኙ" ይመጣል እንጂ፣ "የተከበረው" ይመጣል አይሉም። ይልቁንስ አሁን በዐጸደ ሥጋ ያለን እኛ የሃይማኖት ሰዎች፣ መጽሐፉ የማይለውን እያልን መጽሐፉን አንበርዘው"።

[4] Abdullah Yusuf Ali, *The Holy Qur'an: Text, Translation and Commentary* (Beirut: Dar Al Arabia, 1958), 1540, note 54438.

"በእነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች፣ ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስን እንደሚልክ ተስፋ ሰጥቶ ነበር። ስለመንፈስ ቅዱስ የሚናገሩትን ምንባባት፣ ስለ ነቢይ ይናገራሉ ብሎ መከራከር ጥበብ ያለበት አካሄድ አይደለም[5]። እግዚአብሔርንም ሆነ እውነትን ማወቅ የምንችለው፣ በመንፈስ ቅድስ ዕገዛ ብቻ ነውና"።

መሐመድ የሙስሊሞች አብነት

እንደ ቁርአን ትምህርት፣ በእግዚአብሔርና በመልእክተኛው ማመን ከቶውኑ የማይነጣጠሉ ነገሮች ናቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ ግን፣ በእግዚአብሔርና በእግዚአብሔር በመልእክተኛ መካከል እንዲህ ዐይነት ምስስል ፈጽሞ የለም። ለምሳሌ ለእስራኤላውያን የእምነታቸው መሠረት የሆነው ሐሳብ በዘዳግም 6÷4 ላይ እንዲህ ይላል፦— "እስራኤል ሆይ ስማ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው" እንጂ፣ በክፍሉ ነቢያት አልተጠቀሱም። በመጽሐፍ ቅዱስ ነቢያት ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች ናቸው። ሙሴ እንኳ በሰዎች ፊት እግዚአብሔርን ስላሳከበረ ወደ ተስፋዪቱ ምድር እንዳይገባ እግዚአብሔር ቀጥቶታል (ዘኍልቊ 27÷12-17)።

በእስልምና እምነት ውስጥ የሚታየው በእግዚአብሔርና በነቢዩ መሐመድ መካከል ያለው ዐይነት የጠበቀ ጥምረት፣ መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔርና በነቢያቱ መካከል አለ የሚል ትምህርት አያስተምረንም። ሌሎች ልዩነቶችም አሉ። ለምሳሌ መሐመድ ለሙስሊሞች ኑሮ እንከን የሌላቸው ተምሳሌት ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ነቢያት ለአማኞች እንከን የሌላቸው ተምሳሌት ናቸው አይለንም። በመጽሐፍ ቅዱስ የብዙ ነቢያት ዝርዝር ሕይወት በውል የማይታወቅ ሲሆን፣ በተወሰነ መጠንም እንኳ ቢሆን ሕይወታቸውና አኗኗራቸው የሚታወቀው የእግዚአብሔር ሰዎች፣ ሰው ስለሆኑ እንደማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር ድካምም ሆነ ጎጢአት ነበረባቸው።

ለምሳሌ በብሉይ ኪዳን፣ ሙሴ የእግዚአብሔርን ቃል ባለመጠበቁ ወደ ተስፋዪቱ ምድር አልገባም። ነቢዩ ዮናስ ለነነዌ ሰዎች የንስሓን መልእክት

[5] በሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን፣ ማኒ በመባል የሚታወቅ የፋርስ (የኢራን) ተወላጅ፣ ማንቼይዝም በመባል የሚታወቅ መናፍቃዊ እንቅስቃሴ ጀምሮ ነበር። ይህ ሐሰተኛ መምህር፣ "ኢየሱስ ይመጣላችኋል ያለው መንፈስ ቅዱስ እኔ ነኝ" ይል ነበር። ቤተ ክርስቲያን ይህን መናፍቃዊ እንቅስቃሴ በአንድ ድምፅ ኩንናዋለች። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚናገረውን ትንቢት ስለ ነቢይ የሚናገር ነው የሚለው ይህ ዐይነቱ ትምህርት፣ መሐመድ ከኖረበት ከብዙ መቶ ዓመት በኋላ የተጀመረ መናፍቃዊ ንቅናቄ ነው።

እንዲሰብክ በተላከ ጊዜ፣ ላለመታዘዝ ከእግዚአብሔር ፊት ሸሸ። በሐዲስ ኪዳንም በጳውሎስና በባርናባስ መካከል ግጭት ነበር። ኢየሱስ በተያዘ ጊዜ ጴጥሮስም ሆነ ሌሎች ሐዋርያት ወደ ኋላ ሸሽተዋል። ነገር ግን በእስልምና ነቢዩ መሐመድ ለሙስሊሞች እውነተኛ ምሳሌ እንደ ሆኑ ይታመናል።

መሐመድ በእስልምና እምነት የመጀመሪያው ሙስሊም ናቸው። ስለዚህ የእርሳቸው የሕይወት ዘይቤ ለሌሎች ሙስሊሞች ምሳሌ ስለሆነ፣ ሙስሊም ሁሉ ሊከተለው ይገባል። ይህን ጉዳይ በተመለከተ ቁርአን ስለነቢዩ መሐመድ እንዲህ ይላል፦—

> እኔ ጌታዬ ወደ ቀጥተኛው መንገድ ትክክለኛን ሃይማኖት ወደ እውነት አዘንባይ ሲሆን፣ የአብርሃምን መንገድ መራኝ፤ እርሱም ከአጋሪዎቹ አልነበረም በል። ስግደቴ መገዛቴም ሕይወቴም ሞቴም ለዓለማት ጌታ ለአላህ ነው በል። ለርሱ ተጋሪ የለውም፤ በዚህም (በማጥራት)ታዘዝሁ፤ እኔም የሙስሊሞች መጀመሪያ ነኝ (በል) (ሱራ 6+161-163 በትንፍ ያለውን ይጨምራል)።

በተጨማሪም መሐመድ እንዳይሳሳቱ በእግዚአብሔር ይጠበቁ እንደ ነበር ቁርአን በዚህ መልክ ያስተምራል፦—

> ነቢያችሁ (መሐመድ) አልተሳሳተም፤ አልጠመመምም። ከልብ ወለድም አይናገርም። እርሱ (ንግግሩ) የሚወረድ ራእይ እንጅ ሌላ አይደለም። ኀይሎቹ ብርቱው (መልአክ) አስተማረው. . .ከዚያም ቀረበ፤ ወረደም። (ከርሱ) የሁለት ደጋኖች ጫፍ ያህል ወይም (ከዚህ) ይበልጥ የተረበ ሆነም። ወደ ባሪያውም (አላህ) ያወረደውን አወረደ። (ነቢዩም በዐይኑ) ያየውን ልቡ አልዋሸም (ሱራ 53+2-5: 8-11 በትንፍ ያለውን ይጨምራል)።

አስልምና ከተጀመረ ከሁለት መቶ ዓመታት በኋላ፣ ሙስሊም የነገረ መለኮት መምህራን፣ መሐመድ የአላህን መልእክት ከመቀበል ባለፈ በሚሠሯቸው ሥራዎች በፍጹም አልተሳሳቱም ይሉ ነበር። የመሐመድ ሕይወት ለሌሎች ሙስሊሞች የሕይወታቸው መመሪያ ነው[6]። መሐመድ ከኀጢአት ነጻ የሆነ ሕይወት (ኢስማ) ኖረዋል፤ ማንኛውም ሰው እንደ አላህ ፈቃድ እንዲኖር

[6] H. A. R. Gibb, *Mohammedanism* (New York : Oxford University Press, 1969), 92, 98.

የመሐመድ የኑሮ ዘይቤ እውነተኛና ፍጹም ምሳሌ ስለሆነ በዚያ መሠረት መኖር አለበት[7]።

ቀስ በቀስ መሐመድ ምንም ዐይነት ኀጢአት አልሠሩም የሚለው አስተምህሮ በሰፊው መሠራጨት ጀመረ። ሙስሊሞች፣ ቁርአን ፍጹም ተአምር ከሆነ መልእክቱን የተቀበሉት ነቢይ ኀጢአት የሌለባቸው መሆን አለባቸው ይላሉ[8]። ይህ አስተምህሮ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ማርያም ኀጢአት የለባትም ከሚለው አመለካከት ጋር ይመሰሰላል። የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የነገረ መለኮት መምህራን፣ ክርስቶስ ኀጢአት አልባ እስከ ሆነ ድረስ ድንግል ማርያምም ኀጢአት ሊኖርባት በፍጹም አይችልም ሲሉ ይከራከራሉ[9]።

ምንም እንኳ ሙስሊሞች ነቢዩ መሐመድ ኀጢአት ሠርተው አያውቁም የሚል አቋም ቢኖራቸውም፣ ቁርአን ከዚህ አስተሳሰብ ጋር የሚቃረኑ ትምህርቶችን ያስተምራል። ለምሳሌ ሱራ 80+1-10 ባለው ክፍል፣ የሕይወትን መመሪያ በመፈለግ አንድ ዐይነ ስውር ሰው የእርሳቸውን ዕገዛ በመሻት እርሳቸው ዘንድ በመምጣቱ፣ ፊታቸውን አጨፍግገው ከእርሱ ዞር በማለታቸው እግዚአብሔር እንደ ገሠጻቸው ይናገራል። ነቢዩ መሐመድ ለሠሩት ኀጢአት ከእግዚአብሔር ዘንድ ምሕረትን እንዲጠይቁ ቁርአን ሲያዛቸው እንመለከታለን (ሱራ 47+19፤ 48+2)። ይሁንና እስልምና መሐመድን ያለ ልክ ከፍ ከፍ አድርጉአቸዋል። ቁርአን እግዚአብሔር ለመሐመድ "አንተም በታላቅ ጠባይ ላይ ነህ" (ሱራ 68+4) ሲል ተናግሮአቸዋል። በሌላ ስፍራም ቁርአን ስለ ነቢዩ መሐመድ፣ "ለናንተ አላህንና የመጨረሻውን ቀን የሚከጅል ለሆነ ሰው አላህንም በብዙ ለሚያወሣ በአላህ መልእክተኛ መልካም መከተል አላችሁ" (ሱራ 33+21) ይላል። በተጨማሪም ቁርአን መሐመድን መቀበል አላህን እንደመቀበል ነው ይላል[10]።

> እኛ መስካሪ አብሳሪና አስፈራሪም አድርገን በእርግጥ ላክንህ። በአላህ ልታምኑ በመልእክተኛውም (ልታምኑ) ልትረዱትም ልታከብሩትም (አላህን) በሚትና

[7] Andrew Rippin, *Muslims: Their Religious Beliefs and Practices* (New York: Rutledge, 2001), 50.

[8] ዝኒ ከማሁ።

[9] በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙ አንዳንድ ምሁራን፣ ይህ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን ትምህርት ትክክል ነው የሚል አቋም አላቸው።

[10] Abdullah Yusuf Ali, *The Holy Qur'an: Text, Translation and Commentary* (Beirut: Dar Al Arabia, 1958), 1393. note 4877.

ከቀትር በኋላ ልታወድሱትም (ላክነው)። እነዚያ ቃል ኪዳን የሚጋቡህ ቃል ኪዳን የሚጋቡት አላህን ብቻ ነው፣ የአላህ እጅ (ጎይሉ) ከእጆቻቸው በላይ ነው፣ ያፈረሰም ሰው የሚያፈርሰው በነፍሱ ላይ ብቻ ነው፣ በርሱ ላይ አላህን ቃል ኪዳን የተጋባበትን የሞላም ሰው ታላቅ ምንዳን በእርግጥ ይሰጠዋል (ሱራ 48+8-10 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)።

ሙስሊሞች የመሐመድን ደረጃ በጣም ከፍ የሚያደርጉት የመሐመድን የኑሮ ዘይቤ ለመከተል ስለሚፈልጉ ነው። ሱፊ ሙስሊሞች የመሐመድን ደረጃ ከሌሎች ሙስሊሞች ይልቅ ያተልቁታል። ክርስቲያኖች ለመሲሑ የሚሰጡትን የጌትነት ደረጃ፣ ሱፊ ሙስሊሞች ደግሞ ለነቢዩ መሐመድ ይሰጣሉ። እንደ ጉርጉሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር ከ1876 ዓ.ም—1938 ዓ.ም የኖረው መሐመድ ኢቅባል የተባለ ሰው፣ ስለ መሐመድ የጻፈው ውዳሴ በእስልምና ጽሑፎች ውስጥ እንደ ምሳሌ ይጠቀሳል። መሐመድ ኢቅባል ከጻፋቸው ውዳሴዎች ውስጥ ቀጥሎ ያለው ግጥም አንዱ ነው፦—

> በዓለም ውስጥ ያሉ ግሕፀኖች ሁሉ መሐመድን የሚመስል አይፀንሱም፣
> እንደበቴ በመሐመድ የፍቅር ዝማሬ ሞልቶአል።
> መቶ ቃላት ልቤን በጎይል ይደልቃሉ፣
> ኧረ ለመሆኑ፣ ለእርሱ የሚመጥነውን ውዳሴ እንዴት አድርጌ ልገልጽ እችላለሁ?[11]

የሙስሊሙ ማኅበረሰብ የመሐመድን የሕይወት ዘይቤ ለመከተል ካለው ፍላጐት የተነሣ፣ ስለ መሐመድ ማንነት አዎንታዊ የሆነ አመለካከት አዳብሮአል። ነቢዩ መሐመድ ምን ዐይነት ሰው ነበሩ? ምን ዐይነትስ ተከለ ሰውነት ነበራቸው? ከእርሳቸው በኋላ ያለው ትውልድ ስለነቢዩ መሐመድ የሚነገሩ ታሪኮች ጥቃቅን ዝርዝሮችን በመጨመር እያበራከታቸው መጥቶአል። የመሐመድ ተከታዮች፣ መሐመድ እጅግ ዐይነ ግቡ የሆነ ተከለ ሰውነት እንደ ነበራቸው ብቻ ሳይሆን፣ ውበታቸውንና ደም ግባታቸውን ለመግለጽ በተደረገው ሙከራ ላይ፣ አስደናቂ የሆኑና "በርግጥ አስፈላጊ ጒዳይ ናቸውን?" ብለን እስክንጠይቅ ድረስ የሚያደርሱ ጥቃቅን ዘገባዎች ቀርበዋል፤ ለምሳሌ፦—

[11] Kenneth Cragg, *Muhammad and the Christian* (Maryknoll, N.Y.: Orbis Books, 1984), 75.

> የመሐመድ ጠጒር ቀጭን ወይም አጭር ወይም የሱፍ መልክ አልነበረውም። ጠጒራቸው ትከሻቸው ላይ የተንዘላፋ ነው። ጠጒራቸው በአራት ቦታ የተከፈለ ነበር። ጆሮአቸው በሁለቱ ጒንጒኖች መካከል ደምቀው ይታያሉ። በጠጒራቸው መካከል ያሉ ሽበቶች ቀጥራቸው ከወሥራ ሰባት አይበልጥም ነበር። ወይናቸው ዛጐላማ እንዲሁም ጥቁር ነበር፣ አፍንጫቸው ሰልካካ፣ ደረታቸውም ሰፊ ነበር[12]።

ሙስሊሞች ሁሉ መሐመድን ያከብራሉ። ሱፊ ሙስሊሞች ግን ከልክ በላይ የሆነ እንዲሁም ወደ አምልኮ የቀረበ ከበሬታ አላቸው። ከቀድሞዎቹ የሱፊ ሙስሊም ምሁራን ውስጥ ኢብን አል-ዐራቢ የተሰኘው ሰው፣ መሐመድን "ለተከታዮቹ ብርሃን፣ በተፈጥሮው የእግዚአብሔር ፍጹም ምስያ ያለበት፣ መለኮታዊ ዕውቀት የነበረው፣ ፍጥረታት ሁሉ የተፈጠሩበት ቀደምት ብርሃን ነው"[13] ሲል ጽፎአል። የኢብን አል-ዐረቢ አስተምህሮ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል የተባለው ኢየሱስ ሥጋ በመሆን (በምስጢረ ሥጋዌ ወይም ትስብእት በመሆን) ተገለጠ ከሚለው አስተምህሮ ጋር ይቀራረባል። አርቶዶክስ ሙስሊሞች ይህንን አስተምህሮ የሚቃወሙ ቢሆንም፣ የተለያዩ የሱፊ ሙስሊም ቡድኖች ይህንን እምነት በተጠናከረ ሁኔታ ያስተምራሉ።

ሱና

"ሱና" ማለት የመሐመድ የኑሮ ዘይቤ ማለት ነው። የመሐመድ የኑሮ ዘይቤ ምን ይመስል እንደ ነበር መማር የምንችለው፣ ከቁርአን ሳይሆን ከሐዲስ ነው። ሱና ነቢዩ መሐመድ ለተከታዮቻቸው መመሪያ ይሆን ዘንድ ትተውላቸው ያለፉት የሕይወት ዘይቤ ነው።

የነቢዩ የሱና መመሪያ ግራ የሚያጋቡና ትርጒማቸው እምብዛም የማይጨበጥ ትምህርቶችን የያዘ ነው። ለምሳሌ ከነቢዩ መሐመድ ሚስቶች ውስጥ አይሻ ስለመሐመድ እንዲህ ትናገራለች፦— "ማንኛውንም ሥራ ሲሠሩ በቀኝ እጃቸው መጠቀም ይወዱ ነበር፣ ከእነዚህም ውስጥ ጫማቸውን ሲጫሙ፣ ጠጒራቸውን

[12] From Al-Ghazali, *Ihya' 'Ulum al-Din*, Vol. 2 (Cairo: al-Maktabe al-Tijara al-Kubra, 1965), 381, quoted in Kees Wagtendonk, "Images in Islam, Discussion of a Paradox," *in Effigies Dei: Essays on the History of Religion*, edited by Dirk van der Plas (Leiden: E. J. Brill, 1987), 123.

[13] J. S. Trimingham, The Sufi Orders in Islam (Oxford: Clarendon Press, 1971), 161.

ሲያበጥሩ እንዲሁም ከሰላት በፊት በሚካሄደው መተጣጠብ ጊዜ ሁሉ ከቀኝ ይጀምሩ ነበር"[14]። አብዛኛው ሙስሊም ከዚህ ንግግር የተነሣ በቀኝ ጀምሮ በግራ መጨረስ ይወዳል።

የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ባህል፣ በነቢዩ መሐመድ የአኗኗር ዘይቤ የተቃኘ ነው። ማንኛውም ሙስሊም በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ የነቢዩን የኑሮ ዘይቤ ባህሉ አድርጉአል። ይህ የሆነበት ምክንያት፣ ሙስሊሞች የነቢዩ መሐመድን ፈለግ መከተል የሕይወታቸው ቀዳማይ ዐላማ ስለሆነ ነው (ምዕራፍ 12 ላይ ስለ ሱና በሰፊው እንመለከታለን)።

ኢየሱስ በእስልምና እምነት

ኢየሱስ በሙስሊሞች ዘንድ የተከበረና የተወደደ ነቢይ ነው። ከረጅም ዓመት በፊት ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች በመስጊድ ተሰብስበን እየተወያየን ሳለን፣ በውይይታችን መኻል የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ድንገት ሲነሣ፣ የሙስሊሞቹ መሪ ግልቀስ ጀመረ። የሰውየው ሁኔታ ውይይታችንን እንድናቋርጥ የግድ ስላለን፣ የግለሰቡን ገጽ በጉጉት መመልከት ጀመርን። ግለሰቡም አፍንጫውን እያጸዳና ዕንባውን እየጠረገ፣ "የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ሲጠራ፣ ከደስታዬና ለእርሱ ካለኝ አክብሮት የተነሣ ዕንባ ቀደመኝ። ኢየሱስን እጅግ በጣም እወደዋለሁ"፣ በመቀጠልም "ኢየሱስ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነው፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር ልጅ አይደለም" አለ።

ታሪፍ ሐሊዲ የተባለ ጸሓፊ፣ "ዘ ሙዝሊም ጂሰስ" (የሙስሊሙ ኢየሱስ) በሚለው መጽሐፉ ከስምንተኛው እስከ ዐሥራ ስምንተኛው ክፍለ ዘመን ባለው ጊዜ ውስጥ ሙስሊሞች ለኢየሱስ ክርስቶስ የነበራቸውን አክብሮትና ፍቅር ለመዳሰስ ሞክሮአል[15]። ታሪፍ ሐሊዲ ስለ ኢየሱስ የጻፈው ጽሑፍ፣ ቁርአን ስለ ኢየሱስ በሚያስተምረው ትምህርት የተቃኘ ነው። በእርሱ አገላለጽ ኢየሱስ ሙስሊማዊ ነቢይ ነው።

[14] Cragg, *Muhammad and the Christian*, 70

[15] Tarif Khalidi, *The Muslim Jesus* (Cambridge, Mass.: Harvard University Press, 2001).

አንዳንድ የእስልምና ቡድኖች፣ ኢየሱስ በመጨረሻው ዘመን ወደ ምድር ዳግም በመምጣት ሰዎችን ለመጨረሻው ፍርድ ያዘጋጃል ብለው ያምናሉ[16]። የዚህ አመለካከት ምንጩ፣ በሱራ 43፡61 ላይ የመጨረሻው ዘመን ምልክት የኢየሱስ ዳግም ምጽአት ነው የሚለው የቁርአን አስተምህሮ ነው።

ስለኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ምጽአት ያለው ሌላኛው አመለካከት፣ ኢየሱስ ከሌሎች ነቢያት ጋር በመሆን ለእግዚአብሔር ንጹሕ አምልኮን ለማቅረብ እንዲሁም በጽድቅ ለመኖር ይመጣል የሚል ነው። ይህ ኢየሱስ ለሙስሊም መናንያን ጠባቂ ቅዱስ ነው[17]። ኢየሱስ በሱፊ ሙስሊሞች ዘንድ የተከበረና የተመሰገነ ቢሆንም፣ የኢየሱስን የሕይወት ዘይቤ በመከተሉ በኩል ወይም ይሆን ጉዳይ ይተገብሩታል የሚለውን ጥያቄ በእርግጠኝነት መመለስ ያስቸግራል። ኢየሱስን በየበረሃው በሚገኙ ዋሻዎች የሚከተሉት መነኩሳት፣ ከተከተሉት ይበቃል የተባለ ይመስላል።

ምንም እንኳ ሙስሊሞች በየዘመናቱ ኢየሱስን እናከብረዋለን ቢሉም፣ ስለ ኢየሱስ ያላቸው አመለካከት ቤተ ክርስቲያንም ሆነች ወንጌላት ስለ ኢየሱስ የሚያስተምሩት አስተምህሮ ለዘመናት ሳይጣጣሙ ኖረዋል። ታሪፍ ካሊዲ ስለ ሙስሊሙ ኢየሱስ እንዲህ የሚል አስተያየት ሰጥቶአል፦—

> ይህ ኢየሱስ የተራራው ስብከት ወይም ምሳሌያዊ ንግግሮች ወይም ስለ ሕግና ስለመንፈስ ወይም ስለመስቀል አላስተማረም። በዚህ ፈንታ ኢየሱስ ለእናቱ ታማኝና ታዛዥ ነበር፣ የቀድሞዎቹን ነቢያት ትምህርት በሚያጠናክር መልኩ የአላህን እንድነት ሰብኮአል።. . ትክክለኛው ኢየሱስ ይህ ነው። ክርስቶስን ከተዛባው የሐዋርያቱ አመለካከት ነጻ አድርገን ስናየው፣ ይህ ኢየሱስ እንደ ነቢይ ለፈጣሪው ታዛዥ እንደ ነበረ እንረዳለን፣ ትክክለኛው ኢየሱስ በዚህ መልኩ ሊቀርብ ይገባዋል እንጂ፣ ክርስቶስ የእግዚአብሔር መገለጥ ነው፣ ሞቶአል እንዲሁም አዳኝ ነው ማለት አግባብ አይደለም[18]።

የቁርአኑ ኢየሱስ፣ "የራሱን ማንነት በተመለከተ እውነታውን ለመግለጽ ባደረገው ሂደት፣ ቁርአናዊ ውጥረቶች እንዲፈጠሩ ምክንያት ሆኖአል"[19]። ይህ ውጥረት በልደቱ ጊዜ ኢየሱስ በተአምራዊ ሁኔታ በመናገሩ ይጀምራል። በሱራ

[16] ዝኒ ከማሁ፣ 24-26።

[17] ዝኒ ከማሁ፣ 34።

[18] ዝኒ ከማሁ፣ 15።

[19] ዝኒ ከማሁ።

19+30 ላይ ኢየሱስ ስለራሱ እንዲህ ብሏል:— "(ሕፃኑም) አለ:— እኔ የአላህ ባሪያ ነኝ፣ መጽሐፍን ሰጥቶኛል ነቢይም አድርጐኛል"። ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አወላለድ በእስልምና ኢየሱስና በወንጌላት ውስጥ ባለው ኢየሱስ መካከል ላለው ክርክር ቁርአን አስታራቂ የሆነ "እውነት" እንዳለው ይታመናል።

> ይህ የመርየም ልጅ ኢሳ ነው፣ ያ በርሱ የሚጠራጠሩበት እውነተኛ ቃል ነው። ለአላህ ልጅን መያዝ አይገባውም፣ (ከጉድለት ሁሉ) ጠራ፣ ነገርን በሻ ጊዜ ለርሱ የሚለው ኹን ነው ወዲያውም ይሆናል (ሱራ 19+34-35 በትንሹ ያለውን ይጨምራል)።

ቁርአን ሐሰተኞች ስለኢየሱስ የሚያስተምሩትን የሐሰት አስተምህሮ ለማጥራት የተላከ መልእክት እንደ ሆነ ይታመናል። ሙስሊሞችም ቁርአን ስለ ኢየሱስ ትክክለኛውን አስተምህሮ ይሰጣል የሚል እምነት አላቸው (ሱራ 3+55)።

ቁርአን ለኢየሱስ የሰጠው ስም በእስልምናና በወንጌል ውስጥ ዐቢይ ልዩነቶች እንዳሉ ፍንጭ የሚሰጥ ነው። በቁርአን ኢየሱስ "ኢሳ" ተብሎ ይጠራል። በመጽሐፍ ቅዱስ በክርስቶስ ልደት ዋዜማ መልአኩ የሕፃኑ ስም "የሹዋ" ተብሎ ይጠራል ሲል ተናግሮ ነበር። ወደ ዐረብኛ ሲተረጉም "ያሱአ" ሲሆን፣ በግሪኩ ደግሞ "ኢየሱስ" ነው። በዕብራይስጥ ቋንቋ "የሹዋ" ማለት "እግዚአብሔር ያድናል" ማለት ነው። በቁርአን በተጻፈው "ኢሳ" በሚለው የኢየሱስ ስም ውስጥ "እግዚአብሔር ያድናል" የሚለው ትርጉም የለም። ኢየሱስ ነቢይ ብቻ ነውና[20]።

አንዳንድ ሙስሊሞች በቁርአን ውስጥ ስለኢየሱስ ክርስቶስ ተአምራዊና ልዩ ማንነት የተዘረዘሩት አስተምህሮዎች እንቁቅልሽ ይሆኑባቸዋል። ከዚህ ቀጥሎ በቁርአን ውስጥ ስለኢሳ/ኢየሱስ ማንነት እንዲሁም ስለሠራቸው ሥራዎች የተጻፉትን ምንባባት ከቁርአን በአጭር በአጭሩ በመጥቀስ ለማቅረብ ልሞክር።

መሲሕ፣ መልካም የምሥራች ነው (ሱራ 3+45)፣ ወንጌልን አብሣሪ ነው (ሱራ 5+49፣ 19+30)፣ ለማርያም በመልአኩ አማካይነት ስለ ልደቱ ተነግሮለታል (ሱራ 19+16-20)፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆነ ምልክት ነው (ሱራ 19+20)፣ ከድንግል የተወለደ (ሱራ 19+16-35)፣ የእግዚአብሔር ቃል ነው (ሱራ 4+171)፣

[20] Cragg, *Muhammad and the Christian*, 10.

የእግዚአብሔር መንፈስ ነው (ሱራ 4+171)፣ የእግዚአብሔር ልጅ አይደለም (ሱራ 19+34-35፣ 9+30)፣ የእግዚአብሔር ነቢይና መልእክተኛ ብቻ ነው (ሱራ 4+171)፣ ለእግዚአብሔር ታዛዥ (ሱራ 19+30)፣ ተአምር አድራጊ (ገባሬ መንክራት) (ሱራ 3+49)፣ የቀድሞዎቹን ቅዱሳት መጻሕፍት ያጸና (ሱራ 5+49)፣ ለእስራኤል ልጆች ለተወሰነ ጊዜ የተላከ (ሱራ 3+49-50፣ 13+38)፣ በመስቀል ላይ እንዳይሞት እግዚአብሔር ያስመለጠው (ሱራ 4+157)፣ ሳይሞት ወደ ሰማይ ያረገ (ሱራ 3+55-58)፣ በዘመን መጨረሻ ሰዎችን ለመጨረሻው ፍርድ ለማዘጋጀት የሚመጣ (ሱራ 43+61)፣ ስለመሐመድ መምጣት ትንቢት የተናገረ (ሱራ 61+6)፣ ኀጢአት የሌለበት (ሱራ 19+19) ነው።

ከላይ የተመለከትናቸው የቁርአን ጥቅሶች፣ ቁርአን ለኢየሱስ ያለውን ከፍተኛ ግምትና አክብሮት የሚያሳዩ ናቸው። ይሁንና የቁርአኑ ኢየሱስ ለእስራኤል ሕዝብ ለተወሰነ ጊዜ የተላከ እንጂ፣ ለሰው ልጆች ሁሉና ለየትኛውም ዘመን የተላከ አይደለም።

የክርስቶስ ሥነ ምግባር ለሌሎች አርአያ የሚሆን ቢሆን፣ የተወሰኑ የኀብረተሰብ ክፍሎች በዓለም ውስጥ እንዴት መኖር እንዳለባቸው የሚያሳይ ነው። ክርስቶስ አገልግሎቱ ለዓለም ሁሉ አልነበረም። በእንጻሩ መሐመድ ለዓለም ሕዝብ በሙሉ መጥተዋል[21]። መሲሑ ነቢይ እንጂ፣ "የእግዚአብሔር በእኛ መካከል መገኘት" አይደለም። እግዚአብሔር ክርስቶስ በመስቀል ላይ እንዳይሞት አስመልጠታል፣ በእርሱም ፈንታ ሌላ ሰው ተሰቅሎአል። የሙስሊሞች መጽሐፍ በክርስትና ውስጥ ክርስቶስን በተመለከተ የሚታመኑት እምነቶች ለምሳሌ ትሥጉት (ትስብእት)፣ ሥርየት እንዲሁም ክርስቶስ በአካለ ሥጋ ከሙታን ተነሥቶአል የሚሉትን አስተምህሮዎች ይቃወማል። ኢየሱስ ክርስቶስ በሙስሊሞች ዘንድ የተከበረ ቢሆንም እንኳ፣ ቁርአን ስለ ኢየሱስ የሚያቀርበው ዘገባ ከመንጌላት ትምህርት ጋር በእያሌው የሚለያይ አንዳንዴም የሚቃረን ነው።

ክርስቶስን በተመለከተ የሚነሡ ተቃውሞዎች የሚያጠነጥኑት በክርስትና ውስጥ ስለ ሥላሴ የሚሰጠውን ትምህርት፣ ሙስሊሞች በተሳሳተ መንገድ በመረዳት ክርስቲያኖች ሦስት አማልክት ያመልካሉ ብለው ስለሚያስቡ ነው። ለሙስሊሞች የሥላሴ አስተምህሮ እግዚአብሔርን ለሦስት ቦታ የሚከፍል

[21] *Ra'd* (Thunder) 13:38. Ali, *The Holy Qur'an*, footnote 1861.

ይመስላቸዋል። በተጨማሪም ክርስቲያኖች እግዚአብሔር ማርያምን አግብቶ ልጅ ወለደ ብለው ያምናሉ የሚል የተሳሳተ ግንዛቤ አላቸው።

እንዲሁም ክርስቲያኖች መሲሑ እግዚአብሔር ነው የሚል እምነት እንዳላቸው ከሙስሊሞች አስተምህሮ መረዳት ይቻላል። በመጪረሻዎቹ ምዕራፎች ስለክርስትና እምነት በሙስሊሞች ዘንድ ስላለው የተሳሳተ ግንዛቤ እንመለከታለን።

በእስልምናና በክርስትና እምነት መካከል ያለው መሠረታዊ ልዩነት ምንጩ ስለ እግዚአብሔር ማንነትና ስለሰው አጠቃላይ ሁኔታ ያለው አስተምህሮ ነው። እስልምና የእግዚአብሔርን ልዕልናና ታላቅነት የሚነካ ማንኛውንም ዐይነት ትምህርት በአጽንኦት ይቃወማል። በአንጻሩ ደግሞ፣ ሙስሊሞች የክርስቲያኖች ወንጌል የእግዚአብሔርን ልዕልናና ታላቅነት ያሳንሳል የሚል እምነት አላቸው። እግዚአብሔር በመሲሑ ውስጥ በመስቀል ላይ ሆኖ የጠፋውን ሰው ወደ ራሱ በመጥራት ከራሱ ጋር በማስታረቅ በእርሱ የሚያምኑትን ሰዎች ያድናል ለሚለው ትምህርት ሙስሊሞች ሲመልሱ፦ ይህ ዐይነቱ ተግባር ልዑል በሆነው ጎያል አምላክ ላይ እንዴት ሊፈጸም ይችላል? ሲሉ ይጠይቃሉ። ይህም ሙስሊሞች ግራ እንዲጋቡና ወንጌልንም እንዲቃወሙ አርጉአቸዋል።

መሐመድና ክርስቲያኖች

ብዙ ጊዜ ሙስሊሞች፣ ክርስቲያኖች ስለመሐመድ ያላቸው አመለካከት ምን እንደሚመስል ለማወቅ ይፈልጋሉ። ይህ እንደዋዛ መታየት የለበትም። ቁርአን መሐመድ የመጨረሻው ነቢይ እንደ ሆኑ የማያምን ሰው እግዚአብሔርን የሚወድ ሰው አይደለም ይላል (ሱራ 58+20-22)። ይሁንና ክርስቲያኖች ለሙስሊሞች የቀረቡና ወዳጆች እንደ ሆኑ ቁርአን ያስተምራል (ሱራ 5+81-88)።

በናይሮቢ ከተማ ኢስትሌይ በተባለው ቦታ በአንድ ምግብ ቤት ግብኖ ላይ እንዳለን፣ የሙስሊሞች መሪ፣ መሐመድ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ናቸውን? ሲል ጠየቀን። እኔም፣ "እግዚአብሔር ለአዳምና ሔዋን ከኬቲቱ የሚወለደው ልጅ ሰኩናው በጠላት ይቀጠቀጣል፣ ነገር ግን በመጨረሻ በክፉና በሞት ላይ ድል ይነሣል። ይህም የተስፋ ቃል ስለ መሲሑ የተነገረ ነው። ከሁለት ሺህ ዓመት በፊት የተስፋው ቃል ተፈጽሞአል አልሁት"።

ነቢያት ስለዚህ የተስፋ ቃል የተለያየ ገጽታዎች በተደጋጋሚ ሰብከዋል። መሲሑ ሲመጣ ሰዎችን ከኀጢአታቸው እንደሚያድናቸው አስተምረዋል። የመሲሑ ተልእኮ የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር ሁሉ እንዲሰፋ ነው፣ ለዘላለም ይነግሣል። መሲሑ ሰላምና እውነት ለሕዝብ ሁሉ ያውጃል። እርሱ የዓለም ሁሉ መድኀኒት ነው።

ለበርካታ መቶ ዓመታት ነቢያት የተናገሩት የተስፋ ቃል፣ በመሲሑ ሕይወትና አገልግሎት ውስጥ እውን ሆኖአል። ስለ መሲሑ መጽሐፍ ቅዱስ የሚሰጠው ምስክርነት ግልጽ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ መሲሑ በእግዚአብሔር የተቀባ የዓለም ሁሉ መድኀኒት ነው ይላል።

ነቢዩ መሐመድ ከመሲሑ ሕይወት፣ አገልግሎት አስተምህሮና መጽሐፍ ቅዱስ ስለመሲሑ ከሚሰጠው ምስክርነት ጋር ምን ያህል ይስማማሉ? እኔን ሁል ጊዜ የሚያሳስበኝ ይህ ጥያቄ ነው። ምንጊዜም ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መሲሑ የሚሰጠው ምስክርነት ትክክል ነው ብለን እንድናምን ሲያበረታቱን ውስጤ ሐሴት ያደርጋል።

ኢየሱስና መሐመድ

ክርስቲያኖች መሐመድና ኢየሱስን ማነጻጸር የለባቸውም፣ ምክንያቱም መሲሑ ከነቢይ ይበልጣልና። ምንም እንኳ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኛቸው ነቢያት ትምህርታቸው ከመሐመድ በእጅጉ የተለየ ቢሆንም፣ ነቢዩ መሐመድ መነጻጸር ያለባቸው ሕዝባቸውን ከጣዖት አምልኮ መልሰው በጽድቅ እንዲኖሩ ከሰበኩት ነቢያት ለምሳሌ ከአሞጽና ሆሴዕ ጋር ነው።

እስልምና የነቢይንና የመሲሕን ተግባር ክፉኛ ስለሚያደባልቅ ክርስቲያኖች መሐመድንና ኢየሱስን በሚያነጻጽሩበት ጊዜ ሁሉ በእስልምና አስተምህሮ ግራ ይጋባሉ። የትኛውም ነቢይ መሲሕ ተብሎ አልተጠራም። መሲሕ ማለት የተቀባ ማለት ነው። ይህም ከነቢያት ተግባር ፍጹም የተለየ ነው። ቀጥሎ ባሉት ተከታታይ ምዕራፎች የመሲሑን የኢየሱስን ተግባራት በጥልቀት እንመለከታለን።

የኢየሱስ ተግባር ምንድን ነው?

ነቢዩ መሐመድ የመጨረሻ ነቢይ ናቸው ብሎ በሚያምነው በሙስሊም ነገረ መለኮት ውስጥ የመሲሑ ተግባር ምንድን ነው? በእስልምና እምነት አዳም፣ አብርሃምና መሐመድ እንደ ቅደም ተከተላቸው የመጀመሪያ፣ የመካከለኛና የመጨረሻ ነቢያት ናቸው። አዳም የመጀመሪያ ነቢይ ሲሆን፣ ከእግዚአብሔር

ምሪትን በመቀበል የእስልምናን ሃይማኖት መርሖች በካዕባ ተግባራዊ ያደረገ ሰው ነው። መካከለኛው ነቢይ አብርሃም ነው። አብርሃም ከልጁ ከእስማኤል ጋር በመሆን የእስልምናን እምነት በካዕባ መሥርቶአል። የመጨረሻው ነቢይ ደግሞ መሐመድ ናቸው። መሐመድም እንደ አዳምና አብርሃም እውነተኛውን የእስልምና ሃይማኖት በካዕባ መሥርተዋል። ከሙስሊም ነገረ መለኮት ዐላማ አንጻር መሲሑ ወሳኝ ስፍራ የለውም።

መሲሑ በመከራ ውስጥ ጸንተው እግዚአብሔርን እንደ ተከተሉት ነቢያት ለምሳሌ ኖኅ፣ አብርሃም፣ ሙሴና መሐመድ ሁሉ ክብር ይሰጠዋል (ሱራ 42÷13)። ሙስሊሞች የመሲሑን ርኅራኄ ያወድሳሉ። ይሁን እንጂ በዕለት ተዕለት ኑሮአቸው ውስጥ መሲሑ ኢየሱስ አንዳችም ስፍራ የለውም፤ እንዲያውም ክርስቲያኖች የኢየሱስን ተልእኮ ክፉኛ አዛብተዋል የሚል እምነት አላቸው።

ልብ በሉ፣ አንዳንዴም ክርስቲያኖች እንደ ሙስሊሞች ሁሉ ስለ ኢየሱስ ማንነት ለመረዳት አስቸጋሪ ይሆንባቸዋል። በዚህ ዐይነት ግራ በተጋባ መልኩም ያቀርቡታል። የመሲሑ ማንነትና ተልእኮ ሙስሊሞችን ብቻ ሳይሆን፣ ብዙ ክርስቲያኖችንም ግራ የሚያጋባ ጉዳይ ነው። ስለ ኢየሱስ ማንነት ግራ የሚጋቡት ሙስሊሞች ብቻ ሳይሆኑ፣ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ክርስቲያኖችም ጭምር ናቸው። የጦርነት ዜና ዓለምን በሚያስጨንቅበት በዚህ ጊዜ ለክርስቲያኖች የክርስቶስ ሚና ምንድን ነው? ከመቼውም ጊዜ በበለጠ የሀብት ክምችት ባለበት ዓለም ውስጥ፣ በየምሽቱ በቢሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች በረሀብ እየተጠበሱ ባሉበት ጊዜ ለክርስቲያኖች ክርስቶስን ማክበር ማለት ምን ማለት ነው? በመቶ ሚሊዮኖች የሚገመቱ የዓለም ሕዝቦች፣ የወንጌልን እውነት ባልሰሙበት ሁኔታ እንደ ክርስቲያን ክርስቶስን መከተል ማለት ትርጕሙ ምንድን ነው?

በእስልምና ነገረ መለኮት አተያይ መሲሑ የነበረውን ተልእኮ ፈጽሞ ዐልፎአል። መሐመድ ለሰው ዘር በሙሉ እንዲሆን የታቀደውን የመጨረሻ መልእክት ይዘው ተነሥተዋል። መሲሑ ከእርሱ በኋላ፣ ነቢዩ መሐመድ እንደሚመጡና ዓለም ዐቀፋዊ ተልእኮ እንደሚኖራቸው እንደ ተናገረ ይታሰባል።

የኢየሱስ እውነታ ሕያውነት

እንደ እውነቱ ከሆነ ግን ኢየሱስ ስፍራውን ለሌላ ነቢይ አላስረከበም። በጣም በሚያስደንቅና ልታይ ባይነት በሌለበት መንገድ ኢየሱስ ሰዎች እንዲሰሙትና ትኩረት እንዲሰጡት ማድረጉን እንደቀጠለ ነው።

ታሪፍ ካሊዲ የተሰኘው ጸሓፊ ስለመሲሑ እንዲህ ብሎአል፦—

> "የሆነ ይሁን፣ ኢየሱስ ዛሬም ግዙፍና ጉልሕ ሚና አለው። በቀላልና ተራ በሆነ መንገድ በእስልምናና በክርስትና ሃይማኖቶች ውስጥ ከፍ ያለ ቦታ አግኝቶአል። አንደኛው ሃይማኖት ቀዳሚ ሲያደርገው ሌላኛው ተቀብሎታል። . . .ኢየሱስ ከታሪክና ከሃይማኖታዊ ደረጃዎች በላይ የሆነ ባሕርይን አላብሶታል"[22]።

በሳሪዬቮ ከብዙ ዓመታት የዘርና የሃይማኖት ጦርነት በኋላ፣ ክርስቲያን ሰርቢያውያንና ቦስኒያውያን ተማሪዎቼን አስከትዬ በፈረሰችው ከተማ ወደሚገኘው "የሙስሊም ተማሪዎች ኅብረት" በመባል ወደሚጠራው ስፍራ ለመጐብኘት ሄደን። እነዚህ ወጣት ሙስሊም ተማሪዎች ሻይ ጋበዙን። ከዚያ በኋላ የነበረን ውይይት በጣም ጥሩ ነበር። ለአራት ሰዓት ያህል ውይይት ካደረግን በኋላ ከተማሪዎቹ መካከል ብዙዎቹ ውይይቱ ሌላም ጊዜ እንዲቀጥል ተስማሙ።

ከተማሪዎቹ ተለይተን ልንሄድ ስንዘጋጅ፣ በውይይቱ ውስጥ ከነበሩት መካከል አንዱ እንዲህ አለ፦— "ዛሬ በዚህ ከሰዓት በኋላ በመካከላችን እንግዳ አብሮን አለ፣ ተለይቶን መሄድ የሚወድ አይደለም። እንግዳው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱም በመካከላችን መገኘት ብቻ ሳይሆን የውይይታችን ማዕከላዊ ስፍራ ይዞ ነበር"።

በሳሪዬቮ በዚያች ከሰዓት በኋላ እንደ ነበረው፣ ኢየሱስ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ እርሱን እንዲያውቁትና እንዲረዱት ይፈልጋል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ

ሉቃስ 1÷26-38፤ 4÷14-30

የቁርአን ምንባብ

ሱራ 19÷16-36፤ 3321፣ 40፣ 34÷28

---

[22] Khalidi, *The Muslim Jesus*, 45.

የአስተሙሶትና የሙያይት ጥያቄዎች

1. ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ኢየሱስ መሲሕ እንደ ሆነ ይስማማሉ። በሙስሊሞችና በክርስቲያኖች መካከል ስለመሲሑ ማንነት እንዲሁም ሥራ ያለውን ልዩነት ይግለጹ።
2. አንድ ሰው ሙስሊሞች ማንኛውንም ሃይማኖታዊ ተግባር እንዴት እንደሚፈጽሙ መረዳት ይችላል። ነገር ግን የክርስቲያኖችን መረዳት ያዳግተዋል። ልዩነቱ ከምን እንደ መጣ ይግለጹ። (ማቴዎስ 5÷48፣ ሱራ 33÷40)።
3. ሙስሊሞች ነቢዩ መሐመድ የመጨረሻ ነቢይ ናቸው ብለው ማመናቸው ምን ዐይነት ትርጉም እንዳለው ይግለጹ (ሱራ 33÷40)?
4. ክርስቲያኖች ኢየሱስ መሲሕ ነው ብለው ማመናቸው ምን ትርጉም ያለው ይመስሉታል (ሉቃስ 4÷14-40)?
5. ኢየሱስ ክርስቶስ በቁርአን ውስጥ ምስጢራዊ ሰው ነው። ኢየሱስ በሙስሊሙ ማኅበረሰብ (ኡማ) ውስጥ ያለው ስፍራ እጅግ አነስተኛ ነው። ለብዙ መቶ ዓመታት ቤተ ክርስቲያንም ኢየሱስን አስፈላጊ ወዳልሆነና ከእውነተኛ ሕይወት ተሞክሮ ውጪ በሆነ ሁኔታ ምስጢራዊ ሰው ስታደርገው ቆይታለች። ስለ ኢየሱስ እውነታ ከመሆኑ ይለቅ ምስጢር ተደርጎ የቀረበበት ምክንያት ምን እንደ ሆነ ይግለጹ።

ቅዱሳት መጻሕፍት
ቁርአን—መጽሐፍ ቅዱስ

ኢብራሂም መሐመድ፣ "እባክህ መጽሐፍ ቅዱስህን አውሰኝ" ሲል ጠየቀኝ። እኔም መልካሙ የምሥራች (Good News) የሚባለውንና አረንጓዴ እንዲሁም ጠንካራ ያልሆነ ጥራዝ ያለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጅ አንሥቼ ሰጠሁት። ኢብራሂምም ሰዎች የመጽሐፉን ማንነት እንዳያውቁ በሚል በቡናማ ወረቀት ለበደው። መጽሐፉን በአክብሮትና በጥንቃቄ በመያዝ ከቤታችን ሹልክ ብሎ በመውጣት ወደ ቤቱ ሄደ።

በማግሥቱ ማታ ኢብራሂም ያንኑ መጽሐፍ ይዞ ወደ ቤታችን መጣ። በኢብራሂም ገጽ ላይ ከፍተኛ የሆነ የሐዘን ድባብ በግልጽ ይነበብ ስለነበረ፣ በአያሌው እንዳዘነ ማወቅ አዳጋች አልነበረም። ቤት በመግባት ወንበር ላይ ከተቀመጠ በኋላ፣ መጽሐፉን ከቦርሳው ውስጥ በማውጣት ጠረጴዛው ላይ አነጠፈው።

"እኔ መቼም መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መስሎኝ ነበር። ነገር ግን እንደዚያ ሆኖ አላገኘሁትም። ሰዎች የክርስቲያኖችን ቅዱሳት መጻሕፍት አበላሽተዋል። እንዴት ዐይነት አሳዛኝ ጥፋት ነው! መጽሐፍ ቅዱስ የታሪክ መጽሐፍ ከሆነ እንጂ፣ የእግዚአብሔር ቃል ግን አይደለም"።

ኢብራሂም በዚህ ዐይነቱ ታላቅ ሐዘን ውስጥ እያለ፣ ቡናማ መልክ ያለውን ባዶ ቦርሳውን አንከርፍፎ በዚያ ጨለማ ወደ ቤቱ ሄደ። "ተበላሽቶአል" የተባለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጅ ምስቅልቅል ባለው ጠረጴዛዬ ላይ ተዘርሮአል።

ታሪክና መገለጥ

ኢብራሂም ትክክል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የታሪክ መጽሐፍ ነው። እስትንፋሰ እግዚአብሔር ያለበት እንደ እርሱም ያለ የታሪክ መጽሐፍ የለም። በእኔ ግምት ኢብራሂም ንባቡን የጀመረው ከዘፍጥረት መጽሐፍ ሲሆን፣ ንባቡን ከጀመረ ከጥቂት አንቀጾች በኋላ ቃየን ወንድሙ አቤልን የገደለበትን በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያውን የግድያ ታሪክ አንብቦአል። ከጥቂት ምዕራፎች በኋላም፣ የኖኅ ልጆች አባታቸው ሰክሮ እንዲሁም ራቁቱን ሆኖ

ምዕራፍ ፀሥራ ሁለት

ሁለት መንገዶች

ሸሪአ—መንፈስ ቅዱስ

ሙስሊም ባልንጀሮቼ ወደ እንግሊዟ በርሚንግሃም መካከለኛ ስፍራ በመኪና እየወሰዱኝ፣ "ይህ የከተማው አካባቢ የሚተዳደረው በሸሪአ ሕግ ነው፣ ይህ እውን ለመሆኑ ማስረጃዎቹን እያስተዋልህ ነው?" አሉኝ። ብዙ የማስታወቂያ ሰሌዳዎች ጥቀር ተቀብተዋል። ቀድሞ ጥቀር ከተቀባው ሥዕል ጋላ አጭር የለበሰች ሴት አልያም የቢራ ማስታወቂያ እንደ ነበረበት ነገሩኝ። እርግጥ ነው ማስረጃዎቹን ተመልክቻለሁ።

ይህ የሆነው የእንግሊዝ ሙስሊም ተማሪዎች ማኅበር ለስድስት ቀን ባዘጋጀው የውይይት ወቅት ነበር። ለአንድ ሳምንት ከተካሄዱ ሞቅ ደመቅ ካሉ የእደባባይ ክርክሮች ማጠናቀቂያ ላይ፣ በፕሮግራሙ ላይ እንድገኝ የጋበዙኝ እንዲሁም በፕሮግራሙ ላይ አብረውኝ ሲሟገቱ የነበሩ ወዳጆቼ፣ ወደ ሒትሮው አየር ማረፊያ እየወሰዱኝ በነበረበት ወቅት ነው። በጉዞው ላይ ስንሟገት ከነበሩት ሰዎች መኻል አንዱ፣ "ምዕራባውን ሸሪአ ያስፈልጋቸዋል። ምዕራባውያን ከመበስበስ የሚድኑት ይህ ቀን ሲመጣ ብቻ ነው" አለ። "እኔ ከዚህ ሐሳብ ጋር አልስማማም፣ በእኔ እምነት ሸሪአ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሰጣቸውን ጎላፊነቶችና ነጻነቶች ገፎአል። ለምሳሌ በሱዳንና በናይጄሪያ እየሆነ ያለውን ነገር በውል እንደምትረዱት፣ የቤተ ክርስቲያን ነጻነት አስጊ በሆነ ሁኔታ ተገድቧል" አልሁ። አንደኛው ወገን ጮኽ ብሎ፣ "አንተ እንደምትለው በጭራሽ አይደለም። ሸሪአ የግብረገብ ድቀትን ስለሚከላከል እንዲሁም የክርስቲያኖችን ነጻነት ስለሚያስከብር ክርስቲያኖች ራሳቸው የሚደግፉት ጉዳይ ነው" አለ። "እኛ ክርስቲያኖች ሸሪአን የምናውቀው አንተ እየገለጽኸው ባለበት መንገድ አይደለም፣ ይልቁንም እኛ ስለ ሸሪአ ያለን ግንዛቤ፣ ሸሪአ ሁል ጊዜ ክርስቲያኖችንና በቀጥር አናሳ የሆኑ ሃይማኖቶችን እንደ ሁለተኛ ዜጋ እንደሚመለከታቸው ነው" ስል በሐሳቤ ጸናሁ።

በማንሰላሰልና በማስተዋል የተሞላ ዝምታ ነገሠ። ከቡድኑ አባላት መካከል አንዱ፣ "እኔ አሁን ወደ ካናዳ ልሄድ ነው። ወደ ትውልድ አገሬ ወደ ፓኪስታን ለመመለስ በጭራሽ አልፈልግም። ዕድሜ ልኬን በካናዳ ለመኖር ወስኛለሁ። ለዚህ ደግሞ ዋነኛ ምክንያቱ በዚህ መኪና ውስጥ ያለነው ሰዎች

ሁሉ በምንም መልኩ ዳግም በሸሪአ ሕግ ሥር መኖር ስለማንፈልግ ነው" ሲል ተናገረ::

በመካከላችን ይደረግ የነበረው ውይይት በየዓለማቱ በሚገኙት ሙስሊሞችና በሙስሊሙ ማኅበረሰብ መካከል የሚደረገውን ትግል አመልካች ነው:: የሙስሊሙ ማኅበረሰብ፣ የግለሰቦችን ነጻነት የሚገፍና የሰዎችን ስብእና ክፉኛ የሚያጐድፈውን ሕግ፣ የማይለወጥ የእግዚአብሔር ሕግ ነው ብሉ ሊያጸናው እንዴት ይችላል?[1] ሸሪአ የሚለው ቃል ጥሬ/ቁም ትርጉሙ፣ "ወደ ውሃ ጕድጓድ የሚያመራ መንገድ" ማለት ሲሆን፣ የሸሪአ ቀዳማይ ዐላማም ደኅንነትና ሰላም ነው:: ይህ የሰዎችን ደኅንነት አስተማማኝ በሆነ መንገድ የሚያረጋግጠው አቅጣጫ የቱ ነው? ሙስሊማን የሆኑ ባለ ሥልጣናት ይህን አቅጣጫ የሚያብራሩበትና ከጥቃት የሚከላከሉበት መንገድስ ምንድን ነው?

ይህ በወርኀ ጥቅምት 2002 ዓ.ም በኢራናውያን ሙስሊሞችና በሜኖናይት ክርስቲያን የነገረ መለኮት ምሁራን መካከል በቶሮንቶ ካናዳ የተካሄደው ውይይት በዚህ ርእሰ ጕዳይ ላይ ያተኰረ ነበር:: ይህ የሙስሊም ነገረ መለኮት ሊቃውንት ከቆም ኢራን ወደ ቶሮንቶ ካናዳ በመጓዝ፣ ከሜኖናይት የነገረ መለኮት ምሁራን ጋር ለአራት ቀናት ያካሄዱት ውይይት ጭብጥ ነው:: በሙስሊማኑ ጥያቄ መሠረት እምነትና ዘመናዊነት የሚለው ርእሰ ጕዳይ በውይይቱ ተካቶ ነበር:: እነዚህ ሙስሊሞች በሠለጠነው ዓለም ውስጥ እምነታቸውን እንዴት ጠብቀው መኖር እንደሚችሉ ከሜኖናይት የነገረ መለኮት ምሁራን ትምህርት መቅሰም ፈልገው ነበር:: የኢራን ሙስሊሞች አብዮት ውስጥ ውስጡን የሚብላላና እርስ በርሱ የሚታመስ ትግል ነው:: ይኸውም የዲሞክራሲ ግንባታ ጎይሎች ከእግዚአብሔር ሕግ ጋር ሳይጣረሱ ተስማምተው መኖር እንዴት ይችላሉ የሚለው የትርምሱ ማዕከል ነው:: በአጠቃላይ ይህ ማንኛችንንም ቢሆን በእጅጉ የሚያሳስበን ርእሰ ጕዳይ ነው::

"ኢየሱስና የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ያመኑበትና ይኖሩበት የነበረው የአኗኗር ዘይቤ በየትኛውም ማኅበረሰብ በዝቅተኛ ደረጃ ለሚታዩት መሰኩሳት እጅግ ተስማሚ ጕዳይ ነው:: የፖለቲካ ሥልጣንና ጎይል ባለቤት ለሆኑት የሃይማኖት መሪዎች ግን እንደዚያ አይደለም" ይህ ለፈርጀ ብዙ ባህልና እውነት አናባፕቲስቶች ለሰጡት ትንተና አንድ ኢራናዊ የሰብሰባው ታዳሚ የሰጠው አስተያየት ነው::

[1] Andrew Rippin, *Muslims: Their Religious Beliefs and Practices* (New York: Routledge, 2002), 8-9.

ሸሪአ እንዲት ሊጐለብት እንደቻለና ዘመናዊው ዓለም ለሸሪአ ያለውን አተያይ ለመጻሰክ እንሞክራለን:: በመቀጠልም በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ያለውን የሥራ ድርሻ እንቃኛለን:: በእነዚህ ርእሰ ጕዳዮች ላይ የምናጠናው ጥናት በዋነኝነት የሚያጠነጥነው ሸሪአና መንፈስ ቅዱስ ሙስሊሙ ማኅበረሰብና ቤተ ክርስቲያን ፈርጀ ብዙ በሆነው ማኅበረሰብ ውስጥ ያሉባቸውን ተግዳሮቶች እንዴት ማሸነፍ እንደሚችሉ እንደሚረዷቸው ነው::

የሸሪአ ዕድገት

ሙስሊሞች እስልምና ለእምነትና ለምግባር ፍጹም የሆነ መመሪያ እንደ ሆነ ያምናሉ:: ከላይ በተመለከትናቸው ተከታታይ ምዕራፎች ደጋግመን እንደ ተመለከትነው፣ ሙስሊሞች እስልምና እግዚአብሔር በመላእክቶች አማካይነት ለሰው ልጆች ሁሉ ይሆን ዘንድ የላከው እምነት እንደ ሆነ ያስባሉ:: እስልምና በፍጹም ሊቀየር የሚችል ሃይማኖት አይደለም የሚል አቋም አላቸው:: በቀዳሚነት ለነቢዩ አደም (አዳም) የተላከው እስልምና በመካከለኛው ዘመን ነቢይ ለነበረው ለአብርሃም እንዲሁም የመጨረሻው ዘመን ነቢይ ለሆነው ለመሐመድ ከተላከው እስልምና ጋር አንድ ዐይነት ነው:: እስልምና በቁርአን ውስጥ የተገለጠና የተብራራ የመጨረሻውና ፍጹምነትን የተላበሰ መመሪያ እንደ ሆነ ይታሰባል::

ይህ ሙስሊሞች ስለ መመሪያው ያላቸው መረዳት፣ እስራኤላውያን ስለ ሙሴ ሕግ ካላቸው ነገረ መለኮታዊ መረዳት ጋር በተወሰነ መልኩ ይመሳሰላል:: የሙሴ የሕግ መጻሕፍት የአይሁዳውያን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ማዕከልና የብሉያት የመጀመሪያዎቹ አምስት መጻሕፍት ናቸው:: የአይሁድ ሕዝብ የቶራን ሕግ ሙሉ በሙሉ በታማኝነት ለመታዘዝ እጅግ በጣም ይጨነቅ ነበር:: የአይሁድ ቤተ መቅደስ በሰባ ዓ.ም ከተደመሰሰ በኋላ፣ የአይሁድ የሕግ ምሁራን ለ350 ዓመት አይሁድ እንዴት መኖር እንዳለባቸው የሚገልጽ ታልሙድ የሚባል መጽሐፍ አዘጋጁ:: ስድሳ ሦስት ተከታታይ ቅጽ ያላቸው የታልሙድ መጻሕፍት፣ "በሕገ አሪት ዙሪያ የታነጹ ዐጥሮች" ተደርገው ይታያሉ:: እነዚህ መጻሕፍት ለቶራ እንዴት ታማኝ ሆኖ መኖር ይቻላል የሚለውን ጕዳይ የሚተነትኑና ቶራን ከጥቃት የሚከላከሉ ሰነዶች ናቸው::

በተመሳሳይ መንገድ ሙስሊሞች ቁርአንን ከጥቃት ለመጠበቅ ይቻል ዘንድ ሸሪአን አዘጋጅተዋል:: በአይሁዶች ልምምድ ታልሙድ እንዴት ለሕገ አሪት መታዘዝ እንዳለባቸው የሚያብራራ ሲሆን፣ ለሙስሊሞች ደግሞ ሸሪአ እንደ ት

ለቁርአን መታዘዝ እንዳለባቸው ያስተምራል። የአይሁዶችም ሆነ የሙስሊሞች ቀዳማይ ዐላማ፣ ለእግዚአብሔር ሕግ ሙሉ በሙሉ መገዛት (መታዘዝ) ነው። ነገር ግን ለእግዚአብሔር ሕግ ሙሉ ለሙሉ መገዛት ማለት ምን ማለት ነው? ይህን በተመለከተ ቁርአን እንዲህ ይላል:—

> "መልካም ሥራ ፊቶቻችሁን ወደ ምሥራትና ምዕራብ አትጣጫ ማዞር አይደለም፣ ግን መልካም ሥራ በአላህና በመጨረሻው ቀን በመላእክትም በመጻሕፍትም በነቢያትም ያመነ ሰው ገንዘብንም ከመውደዱ ጋር ለዝምድና ባለቤቶችና ለየቲሞች፣ ለምስኪኖችም፣ ለመንገደኞችም፣ ለለማኞችም፣ ለጫንቃዎችም (ማስለቀቅ) የሰጠ ሰውና ሦላትንም ደንብን ጠብቆ የሰገደ፣ ዘካንም የሰጠ ቃል ኪዳንም በገቡ ጊዜ በኪዳናቸው የሞሉ (ሰዎች ሥራ) ነው፣ በችግር በበሽታና በጦር ጊዜም ተጋሾችን (እናወድሳለን)፣ እነዚህ እነዚያ እውነትን የያዙ ናቸው። እነዚያም ተጠንቃቂዎቹ እነርሱ ናቸው" (ሱራ 2+177)።

ሙስሊሞች ይህን ክፍል የእስልምና ሰባቱ ትእዛዛት ሲሉ ይጠሩታል። ሙስሊሞች ሊያምኗቸው የሚገቡ የእስልምና አምስት መሠረተ እምነቶች በዚህ ክፍል ውስጥ ተካተዋል፤ እነርሱም:— (1) እግዚአብሔር፣ (2) የመጨረሻው ፍርድ፣ (3) መላእክት፣ (4) ቅዱሳት መጻሕፍትና (5) ነቢያት ናቸው። ክፍሉ ፍትሕ፣ ጽድቅ፣ ለድኻ መመጽወት መደበኛ የሆነን ጸሎት ያዛል። ልክ እንደዚህ ክፍል ሁሉ መላውም ቁርአን የእምነትና የተግባር መመሪያ መጽሐፍ ነው። ሆኖም አንድ ሙስሊም እነዚህን ትእዛዛት መጠበቁን እንዴት ያውቃል? ለምሳሌ የዘወትር ጸሎትና መደበኛ ልገሳ ምንድን ነው?

ሱና

ሱና መሐመድ ምድራዊ ኑሮአቸውን የኖሩበት የሕይወት ዘይቤ ነው። እርሳቸው የነቢያት መጨረሻ እስከ ሆኑ ድረስ፣ የእግዚአብሔርን ሕግ ሁሉ ትክክለኛ በሆነ መንገድ የታዘዙ ነቢይ ናቸው። መሐመድ የእግዚአብሔርን መገለጥ በሙላት የሚረዱበት፣ የሚተረጕሙበትና የሚተገብሩበት ጥበብ (ሒክማ) አላህ ሰጥቶአቸው ነበር። ስለዚህ አማንያን ሁሉ የነቢያቱ መንገድ የሆነውን ሱናን በሙላት ሊከተሉ ይገባቸዋል። ነገር ግን ይህ የመሐመድ መንገድ (ሱና) ምንድን ነው?

ሐዲስ

በሙስሊሞች የመጀመሪያዎቹ ሁለት ምዕት ዓመታት፣ ይህ ጥያቄ ሐዲስ እንዲዋቀር ምክንያት ሆኖአል። እጅግ ትልቅና ዋነኛ የሚባለው 9,082 ሐዲሶችን ያካተተው የቡካሪ ስብስብ ነው (ድግግሞሹ ሲወገድ የቡካሪ ስብስብ 2,602 ሐዲሶችን የያዘ ነው)[2]። እያንዳንዱ ሐዲስ ስለነቢዩ አኗኗር ዘዬ የሚያስተምረው ትምህርት አለው። ለምሳሌ:—

ዮቅባ ኢብን አሚር እንዲህ ይላል፣ "አንድ ሰው ለነቢዩ የሐር ካባ ላከላቸውና በጸሎት ጊዜ ለበሱት። ከጸሎት በኋላ ልብሱን በቀጣ አወለቁት። እጅግም በመጸየፍ፣ 'ይህ እግዚአብሔርን ለሚፈራ ሰው ተስማሚ (የሚመች) ልብስ አይደለም' አሉ"[3]።

ሌሎች ትውፊቶች ደግሞ የተለየ ፖለቲካዊና ሥነ መለኮታዊ ዐላማ ነበረቸው። ለዚህ ሁነኛ ምሳሌ የሚሆነው:— ሐዲስ፣ የነቢዩን ዐማች እንደ አራተኛ ከሊፋ ንግሥናው በግጭት የተናወጠውን የዓሊን ሥልጣን ተገቢነት ያጸናል። የዚህ ሐዲስ ዐላማ የፈጠራ ሱናን ማቋቋም ነበር። የሥልጣን ሰንሰለቱ የሐዲስን ትክክለኝነት ለማረጋገጥ ይጠቅማል።

> አቡ በክር ኢብን አቢ ሻአይባ እንደ ነገረን ጉሀንዳር በሸባ ሥልጣን እንደ ነበረውና መሐመድ ኢብን አል-ሙታአንና ኢብን ባሻር ሁለቱ እንደ ነገሩት መሐመድ ኢብን ጀአፈር እንደ ነገረው ሹብም ደግሞ እንደ ነገረው በማደንሱር ሥልጣን በራአቢ ኢብን ሂራሽ ሥልጣን የሚከተለውን በሰማው፣ "እግዚአብሔር በእርሱ ይከብር ዘንድ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ብሉ መልእክት ሰጠው ጸሎትና የእግዚአብሔር ሰላም በእርሱ ላይ ይሁን" አለ። "ስለእኔ ውሸትን አትናገር ስለእኔ ውሸትን የሚያሠራጭ በገሐነም እሳት ይገባል"[4]

ከመሐመድ ዘመን በኋላ ብዙ መቶ ሺህ ሐዲሶች ተሠራጭተዋል። የቡካሪ ሥራ የትኞቹ እውነተኞች እንደ ሆኑ መወሰን ነው። ይህም ውሳኔ በምስክሮች

---

[2] Frederick Mathewson Denny, *An Introduction to Islam* (New York: Macmillian, 1994), 161.

[3] H. A. R. Gibb, *Mohammedanism* (New York: Oxford University Press, 1969), 74.

[4] Rippin, *Muslims*, 47.

ሰንሰለት (ኢስናድ) ታማኝነት ላይ የተመረኰዘ ነው። ኻአቺ ሙስሊም የተባለው ሌላው ምሁር እንደ ቡካሪዎች ያለ ጥረት አድርጓል። ትውፊት እንደሚያረጋግጠው ቡካሪ ከመረመራቸው ስድስት መቶ ሺህ ሐዲሶች መካከል 9,082ን መርጧል[5]፤ ሌሎች በመቶ ሺህ ለሚቈጠሩት ምንም ግምት አልሰጣቸውም። የእርሱ ቅጽ 3,450 ምዕራፎች የተከፋፈሉ ሰባት መጻሕፍትን የያዘ ነው[6]።

የሸሪአ አሠራር

ከነቢዩ ሱና የታማኝነት ጉዳይ ባሻገር ሌሎች የነገረ መለኮት ሰዎች ደግሞ የሕግ ሥርዐቶችን (ሸሪአን) ሲያጐለብቱ ነበር። ሐዲስ በዚህ ረገድ ታሳቅ ድርሻ ነበረው። ሸሪአን ያጐለበቱት ከአራት ሥልጣናዊ ምንጮች በመነሣት ነው፤ ይኸውም፦—

የመጀመሪያው ቁርአን ሲሆን
ሁለተኛው ሐዲስ
ሦስተኛው ቂያስ የምስሉሽ ጥበብ
አራተኛ ኢጅማ ስምምነት/ሥልጣን ነው

ከቁርአንና ከሐዲስ ወጥ የሆነ የሕይወት መመሪያ ለማዘጋጀት ትልቅ የሆነ ጥበብና ግስተዋል ይፈልጋል። ከዚህ የተነሣ የነገረ መለኮት ምሁራን ለሙስሊሞች ደንብን ሲጽፉ የምስሉሽን ጥበብ በማጐልበትና የማኅበረሰቡን ስምምነት መሠረት በማድረግ ነው። በሱኒ እስልምና የነገረ መለኮት ሰዎች እርስ በርስ የሚደርሱበት ስምምነት ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ጉዳይ ነው። የትኛው ጽሑፍ በቁርአን ውስጥ ይካተት የሚለው ውሳኔ እንኳ የሚወሰነው፣ በነገረ መለኮት ምሁራን ስምምነት ነው። የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ምሪት መተርጐምና ይህንኑ ምሪት ኅብረተሰቡ በሕይወቱ እንዲተገብረው የማድረግ ኀላፊነት አለባቸው። ይህ ዐይነቱ የአተረጓጐም ሥርዐት ሊቂታሃድ ይባላል። የመተርጐም ኀላፊነቱ የተመሠረተው በእስልምና ሕግ ሳይንስ ላይ ባለ ጥልቅ ዕውቀትና መረዳት ላይ ነው።

በዚህ ስምምነትን መልክ ማስያዝ ሂደት ውስጥ የነገረ መለኮት ምሁራኑ የሕግ ትምህርት ቤቶችን መሥርተዋል። በስምንተኛውና በዘጠነኛው ምዕተ ዓመት

[5] Denny, *An Introduction to Islam*, 161.
[6] Gibb, *Mohammedanism*, 78-79.

የሱኒ ሙስሊሞች አራት የሸሪዓ ትምህርት ቤቶችን መሥርተዋል። እነርሱም ሃናፊ (Hanafi)፣ ማሊኪ (Maliki)፣ ሻፊኢ (Shafi'i)፣ እና ሃንባሊ (Hanbali) ይባላሉ። አተረጓጐማቸው የተለያየ ቢሆንም፣ ዋናው ሐሳብ ግን አንድ ነው። ይህም ዋና ሐሳብ ቁርአንና የመሐመድ የአኗኗር ሥርዐት የሆነው ሱና ለሕይወት ትክክለኛ መንገድ ነው የሚለውን አቋም ይፋ የሚያደርግ ነው። እነዚህ መንገዶች አራቱን የሱኒ ሙስሊም ቤተሰቦችን የሚገልጹ ናቸው። የሺአይት ሙስሊሞችም ደግሞ ሌሎች የሕግ ሥርዐቶችን አቋቁመዋል።

ምንም እንኳ እነዚህ የተለያዩ የአተረጓጐም ትምህርት ቤቶች የተለያየ አካሄድ ቢከተሉም፣ ሁሉም የነቢዩ አኗኗር የሆነውን ሱናን መከተል ይፈልጋሉ። ከዚህም የተነሣ በመሐመድ ላይ የሚሰነዘር ማንኛውም ዐይነት ትችት በሙስሊሞች ሁሉ ላይ እንደ ተቃጣ የማጥቃት ወይም የመግደል መከራ ይቈጠራል።

የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ከለውጥ ፈተና ጋር እየታገለ ነው ያለው። አዲስ ለውጥ/ፈጠራ (ቢዳአህ) ፈጽሞ የተከለከለ ተግባር ነው። ከዐሥረኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ የሱኒ ሙስሊሞች መጽሐፍን የመተርጐም በር ፈጽሞ ስለተዘጋ ሸሪአን የማሻሻል አንዳችም ዕድል የለም የሚል አቋም አላቸው። በአንጻሩ የሺአይት ሙስሊሞች ደግሞ ሸሪአን ለመተንተንና ለማሻሻል በሩ በጭራሽ አልተዘጋም የሚል አቋም አላቸው። ለሺአይት ሙስሊሞች ሸሪአን የመተርጐምና ከእስልምና ሃይማኖት ልምምድ ጋር የማጣጣሙ ሂደት በየትውልዱ ሁሉ የሚቀጥል ተግባር ነው ባዮች ናቸው።

ሸሪአ በሁሉም ሙስሊሞች ተቀባይነት ያላቸውን ምግባራት (ሐላል) እንዲሁም የተከተለከሉት (ሐራም) ሥራዎች ምን እንደ ሆኑ ያብራራል። ለምሳሌ በተገለጸው መልኩ ያልታረደን የእንስሳ ሥጋ መብላት ሐራም ነው። በተገቢው መንገድ የታረደን ሥጋ መብላት ደግሞ ሐላል ነው። ሸሪአ አብዛኛውን የሕይወት አካሄድ ተቀባይነት ያለው ተግባር (ሐላል) ወይም ተቀባይነት የሌለው ተግባር (ሐራም) በማለት በሁለት ዐቢይ ወገን ይከፍለዋል። ሐራም ነገሮችን ማድረግ ትጣት (ሃድ)ያስከትላል።

ሸሪአና ጸርሰላይ

ለሸሪአ ሕይወትን ማስገዛት ማለት ወደ እስልምና የተለወጠን ሕዝብ ከራሳቸው ባህል ወደ እስልምና ባህል የመለወጥ ግዴታ ማለት ነው፤ ይህም "እርሰላይ"

(proselyte) ይባላል። የዚህም ምክንያቱ ሸሪአ ብርቱ የሆነ የእስልምናን ባህል ሊወክል ስለሚችል ነው። ይህ እንግዲህ የሁሉም እስልምና ትምህርት ቤቶች ቀደምት ሚና ነው። በሙስሊሙ ማኅበረሰብ ያሉ ሁሉም የትምህርት ተቋማት ዐላማ የመተርጉምና የሙስሊም ባህልን በሸሪአ እንደ ተገለጸው ማስፋፋት እንዲችሉ ማስታጠቅ (ብቁ ማድረግ) ነው። ይህ ማለት በማናቸውም ጊዜ አንድ ሰው ሙስሊም ሲሆን፣ እምነቱን የመለወጡ ሂደት ጀምሯል ማለት ነው። እምነት መለወጥ ማለት ከአንድ ባህል ወደ ሌላ ባህል መሄድን የሚያመለክት ነው። ይህ ለውጥ የሚጀምረው እምነትን ይፋ በማድረግ ሲሆን፣ ይኸውም፣ "ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ የለም፣ መሐመድም የአላህ መልእክተኛ ነው" የሚለው ነው። ይህ ቀላል የእምነት መግለጫ አንድን ሰው ከሙስሊሙ ባህልና ከሙስሊሙ ማኅበረሰብ ጋር ይቀላቅለዋል። መሐመድ የእግዚአብሔር ነቢይ ስለሆነ፣ በቁርአን እንደ ተገለጠው ማንኛውም አማኝ ለእግዚአብሔር ፈቃድ መገዛት እንዲሁም የመሐመድን መንገድ መከተል አለበት፤ ይኖርበታልም። ይህም ማለት ደግሞ ለሸሪአ መገዛት ማለት ነው። ይህ የዐረብኛ ቋንቋ መማርን የሚጨምር ጉዳይ ነው። በሸሪአ ውስጥ በግልጥ እንደ ተገለጸው እስልምናን መቀበል ከሙስሊማዊው ባህል ጋር መዋሐድ ማለት ነው።

ሸሪአና የፖለቲካ ሥርዐት

የሙስሊሞች እደርስበት (ideal) የወልም ሆነ የተናጠል ሕይወት በሸሪአ እንደ ተገለጠው በሕጉ ሥልጣን ሥር መኖር ነው። ሆኖም ብዙውን ጊዜ የሙስሊሙ ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ሕይወት በጥቂቱ ሁለት የተለያዩ አተረጓጐም እውነታዎችን የያዘ ነው። የዓለማዊው ሙስሊሞች የፖለቲካ ባለ ሥልጣናት የመንግሥትን አስተዳደር ጉዳይ የፖለቲካን እውነታ በሚጠይቀው መንገድ ተግባራዊ ከማድረግ ባሻገር ሸሪአንና የኡለማን (የሙስሊም ሕግ ምሁራንን) ድርሻ ያከብራሉ። ምንም እንኳ መሐመድ ነቢይ እንዲሁም የአስተዳደር ሰው ቢሆኑም፣ ብዙ ጊዜ ከሙስሊሞች ታሪክ እንደምንረዳው፣ ኡለማና የአስተዳደር ሰው የተለያየ ተግባራትን የሚያከናውኑና የተለያዩ ሙያዎች መሆናቸውን ነው። በዘመናችን የእነዚህ ሁለቱ ጉዳዮች እርስ በርስ መቀላቀላቸው፣ በአንዳንድ ሙስሊሞች መካከል የሙስሊሞች ተሐድሶ እንቅስቃሴዎች የማኅበራዊውንና የፖለቲካውን ሥርዐት በኡለማ ሥልጣንና ቀጥጥር ሥር ለማድረግ መፈለጋቸው ታላቅ ውጥረትን ፈጥሮአል።

ዘመናዊቷ ኢራን ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነች። ሽንጉው የእስልምናው አብዮት ደጋፊ ነው። ሁሉም ሕዝባዊም ሆነ ግላዊ ሕይወት በሼካዎች (የሙስሊም ነገረ

መለኮት ዐዋቂዎች) እንደሚተረጐመው በአንድ በእግዚአብሔር ፈቃድ ሥር ማዋል ነው። በሌላ በኩል በሕዝብ የተመረጠው መንግሥት፣ ዐምባ ገነናዊ የነገረ መለኮት ሥልጣን መመሥረትንና በግለሰቦች ነጻነት ላይ የሚጥለውን ገደብ ይቃወማሉ።

በኅዳር 2002 ኢራን ታላቅ ነውጥ ገጥሟት ነበር። በወሩ አጋማሽ ላይ የኮሌጅ መምህር በሆኑት በኘሮፌሰር ሃሺም አጋሃጃሪ ላይ በእስልምናው ፍርድ ቤት የተወሰነውን የሞት ፍርድ በሺዎች የሚቈጠሩ ተማሪዎች በጐዳና ላይ በመውጣት ተቃውሞአቸውን ገልጠው ነበር። እንደ የአሶሼትድ ፕሬስ ጋዜጠኛ ዓሊ አክባር ዳሪኒ የኘሮፌሰሩ ከሳሾች የመከራከሪያ ነጥብ እንዲህ ብሏል በማለት ነው፣ "እያንዳንዱ አዲስ ትውልድ እስልምናን በራሱ መንገድ መተርጐም አለበት"። የቀደሙት ሼኮች የተረጐሙትን እንደማይነካና እንደማይለወጥ መታየቱን ተችቶአል[7]።

ፕሬዚዳንት መሐመድ ሐታሚ የሞቱን ቅጣት እንዲህ በማለት ተችተውታል፣ "ክሱ በፍጹም መመሥረት አልነበረበትም" የመንግሥት ቃል አቀባዩም እንዲህ ነበር ያለው፣ "ከብሔራዊ ጥቅማችን ጋር በሚጋጭ አቅጣጫ የሚጓዝና እንደዚህ ዐይነት ፍርድ በማንም ያልተደገፈ ነው"[8] ይህ በጎይል የተሠነዘረ ተቃውሞ ፍርዱን በእስላም ባለሥልጣናት ደግሞ ለመመልከት ለተወሰነው ውሳኔ አስተዋጽኦ አድርጓል። በሚቀጥሉት ወራት እነዚህ በኢራን ያሉ ባለሥልጣናት ልዩነቶቻቸውን ማስወገድ ስላልቻሉ የኘሮፌሰር አጋሃጃሪም ጉዳይ መፍትሔ ሊያገኝ አልቻለም።

ኢራን በዚህ ዐይነቱ ውዝግብ ውስጥ እያለች አራት ሺህ ማይል ርቀት ላይ የምትገኘው ናይጄሪያ ከዓለም ዐቀፍ ኅብረተሰብ የመገለል አደጋ ውስጥ ገባች። አሚና ላዋል የተባለች ሴት ከጋብቻ ውጪ ፀንሳ የሞት ፍርድ ተፈረደባት። ከዓመት በፊት ሱፊያ ሑሴን በተመሳሳይ ጥፋት የሞት ፍርድ ተፈርዶባት ነበር። የልጇ አባት የቀድሞ ባለቤቷ እንደ ሆነ በመናገሯ ፍርዱ ተሻሽሏል፤ የተሻሻለበት ዋና ምክንያትም የፀነሰችው፣ ሸሪአ በሰሜን ናይጄሪያ ውስጥ ከመተግበሩ በፊት ስለነበረ ነው። ነገር ግን የአሚና ፍርድ ውሳኔ እስካሁን እንደጸና ነው። ፍርዱ ባይቀለበስ (ባይሻር) ኖሮ ሱፊያ ልጇ ጡት መጥባት እንዳቆመ በድንጋይ ተወግራ ልትሞት ነበር። ምንም እንኳ ትላልቅ ወይም

[7] Ali Akbar Dareini, *"Iran President Chides Death Sentence,"* from the Associated Press (13 November 2002), 191-95.

[8] ዝኒ ከማሁ።

በሰውነት ላይ በግርፋት የሚፈጸሙ ቅጣቶች ሃድ ተብለው ለሚታወቁት ታላላቅ ጥፋቶች የሸሪአን ፍርድ የሚጠይቁ ቢሆኑም በአጠቃላይ የዚህ ዐይነት ፍርዶች በእስላማዊ መንግሥታት አይበረታቱም ወይም ችላ ተብለዋል።

በሰሜን ናይጄሪያ በዐሥራ ሁለቱ ግዛቶች የሸሪአ በተግባር ላይ መዋል (መተግበር) በዘመናዊ እስልምና ማኅበረሰቦች ተታውሞ እንዲጥመው አድርጓል። ይህ እንትስታሴ በግንቦት 1999 ዓ.ም በተደረገው ምርጫ ክርስቲያን ኘሬዚዳንት ኦሊሴጎን ኦባሳንጆ እንዲመረጡ አስተዋጽኦ አድርጓል። የሰሜናዊቹ ሙስሊሞች በሙስሊሞች አመራር ሥር መሆንን አጥብቀው ይመርጡ ነበር። የሰሜናዊቹ ሙስሊሞች በሸሪአ ሥልጣን ሥር ለመተዳደር የወሰኑት ከክርስቲያን ሥልጣን አካባቢውን ለመጠበቅ ነበር[9]።

በሰሜኑ ግዛት የሚኖሩ በዛ ያለ ቁጥር ያላቸው አናሳ ክርስቲያኖች በግዛቱ የሸሪአ መደንገግ ነጻነታቸው ይገደባል። በእርግጥ ሁሉን ዐቀፍ በሆነው በፈደራል መንግሥትና በክልል መንግሥት መካከል ውጥረት ነበር። የአሚና ላዋል የሞት ፍርድ ለዚህ የፍርድ መቀልበስ አንድ አስተዋፅኦ አድርጓል። የፈደራል ፍርድ ቤቶች የዚህ ዐይነቱን ፍርድ በፍጹም ሊያጸድቁ አይችሉም። በሰሜን ናይጄሪያ የሸሪአ ፕሮግራም መተግበር በክርስቲያኖችና በሙስሊሞች መካከል ብዙ ሁከት የተሞላ ግጭት በዓለም ዐቀፍ የዜና ማሠራጫ ትኩረት ተሰጥቶበታል። በአገሪቱ ውስጥ ላሉ የጸሎት ስብሰባዎችና ጸም ጸሎቶች በዓለም ዙሪያ ትልቅ ትኩረት ነው የተሰጠው። የክርስቲያኑ ማኅበረሰብ በሙሉ፣ ከሙስሊም ጐረቤቶቻቸው ጋር በሰላም የመኖር ናፍቆታቸውንና ሽሪአ በግዴታ እንደ ተጫነባቸው በቀጥታ ገልጸዋል። ብዙ በናይጄሪያ ያሉ አብያተ ክርስቲያናት ለውይይትና ለጸሎት ዝግጁ ሆነዋል።

ለሺህ ዓመታት ሙስሊሞች "ወደ ውሃ ኩሬ የሚያመራው መንገድ" በሚባ ተብራርቶአል ብለው ሲያምኑ ቆይተዋል። የነገረ መለኮት ዐዋቂዎች እንደሚያምኑትም ሁሉም የተሐድሶ ሰዎች የመንገዱን ዐጥሮች አጠናክረውታል። ጸሩ ግን ዘመናዊነት በተደጋጋሚ እና በአደገኛ ሁኔታ ዐጥሮቹን ክፉኛ እየተፈታተናቸው ነው።

ኢራናውያን ተማሪዎች ለጓደኞቹ እንዲህ ብለው ነገሩት፣ "የኢራናውያን አብዮት ለእስልምና ሃይማኖት አንዳችም ዝንባሌ እንዳይኖረን አድርጓል"።

[9] John Alembillah Azumah, *The Legacy of Arab Islam in Africa* (Oxford: Oneworld Publications, 2001), 191-95.

ሌሎች ኢራናውያን ደግሞ ተገቢ ባልሆነ የምዕራብ ወዳጅነት ምክንያት ለዓመታት ከተደረገብን ተጽእኖ ተላቀው በመጨረሻ እውነተኛ በሆነው የእስልምና መንገድ መመሥረት በጣም ደስተኞች ናቸው። ለእነዚህ ሙስሊሞች ሽሪአ፣ "ጥልቅ የሆነ የመረጋጋትና የደኅንነት ስሜት" ይሰጣቸዋል[10]። በዘመናዊዎቹ እና በአጥባቂዎቹ ጎይላት መካከል ያለው ውጥረት ንድፈ ሐሳባዊ አይደለም። በብዙ ሙስሊም ማኅበረሰብ መካከል ትልቅ ተግዳሮት ያመጣ ነው።

አሁን ከዚህ ፍጹም የተለየውን የመሲሑን መንፈስ እናጠናለን።

መንፈስ ቅዱስ

አንድ ሙስሊም ምሁር በአንድ ምሽት በዩኒቨርሲቲ ትጥር ግቢ ውስጥ በተደረገ ውይይት ላይ፣ "ስለ መንፈስ ቅዱስ የማውቀው አንዳች ነገር የለኝም" ሲል ተናገረ። እኔም እንዲህ ብዬ መለስኩለት፣ "መንፈስ ቅዱስ እጅግ ክቡር ስጦታ ነው። የመጨረሻውንና ፍጹማዊውን እውነት የሚገልጥ፣ ስለ ኀጢአት የሚወቅስና ሰው በወንጌል ማመን የሚችልበትን ዐቅም የሚሰጠው መንፈስ ቅዱስ ብቻ ነው"።

"ታዲያ አንተ፣ ለእኛ ለሙስሊሞች የወንጌልን እውነት ልታስረግጥልን አትችልም ማለት ነው? እስልምና ግን ፍጹም በማስተዋልና በአመክንዮ የተመሠረተ ስለሆነ በዚህ ምሽት የእስልምናን እውነተኛነት ላረጋግጥልህ እችላለሁ። ታዲያ አንተስ የወንጌልን እውነተኛነት ለማረጋገጥ ሙከራ አታደርግም?" በማለት ሙስሊሙ ወዳጄ ጉተጉተኝ። እኔም እንዲህ አልሁት፣ "ወንጌል ከአመክንዮ ጋር የሚጣረስ/የሚጋጭ እውነት የለውም። እንዲያውም ለማኙ የሕይወት ትርጉሙንና የአመክንዮ ማዕከሉን የሚቀዳው ከወንጌል ነው። ያለ መንፈስ ቅዱስ ዕገዛ እንዲያው በተፈጥሮ ከሀሉታችን፣ የተሰቀለው ክርስቶስ የእግዚአብሔር ጎይል ነው ወደሚለው ድምዳሜ በፍጹም ልንደርስ አንችልም"።

ባልንጀራዬም በመደነቅ፣ "በአመክንዮና በተፈጥሮ ከሀሉታችን እውነትን ማግኘት አንችልም ማለትህ ነው?" ሲል ጠየቀኝ። እኔም፣ "እውነት ነው!

[10] Denny, *An Introduction to Islam*, 197.

መንፈስ ቅዱስ ለእውነት ልባችንን ካልከፈተው በስተቀር በፍጹም እውነትን ማመን አንችልም" አልሁት::

"እንግዲያው መንፈስ ቅዱስን እንዴት ማግኘት እንችላለን?"

"ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስን እንዲሰጣችሁ አብን ጠይቁ ብሏል:: እኛ መንፈስ ቅዱስን ለማግኘት እግዚአብሔርን ከጠየቅነው እግዚአብሔር አያሳፍረንም"::

ሙስሊሞች፣ እስልምና ተፈጥሮአዊ ስለሆነ ሰዎች በተፈጥሮአቸው እጅግ መልካሞች ናቸው የሚል አመለካከት አለው:: ከዚህም የተነሣ ሰዎች በአላህ ለማመንም ሆነ መሐመድ የአላህ ነቢይ ነው ብሎ ለመቀበል የመንፈስ ቅዱስ ርዳታ አያስፈልጋቸውም የሚል እምነት አላቸው:: ወደዚህ ድምዳሜ ለመድረስ ሥነ አመክንዮና ምክንያታዊ የሆነ አመለካከት በቂ ነው ባዮች ናቸው:: የሰዎች ፈቃድ ትክክለኛውን ጉዳና አመራምሮ ለማግኘት በቂ ነው:: ለዚህም ነው የሸሪአው የእስልምና አወቃቀር ፈጋ በሚባለው ግለትም በመረጃ ላይ በተመሠረተ ዕውቀት ላይ የሚደገፈው[11]::

መንፈስ ቅዱስ በእስልምና

ምንም እንኳ በእስልምና ነገረ መለኮት መንፈስ ቅዱስ ብዙ ስፍራ ባይኖረውም ቁርአን ስለ መንፈስ ቅዱስ ይናገራል:: በእርግጥ እግዚአብሔር አዳምን በፈጠረበት ጊዜ መንፈሱን እፍ ብሎበታል (ሱራ 15+29):: በተጨማሪም መሲሑ ከእግዚአብሔር የተላከ መንፈስ ነው (ሱራ 41+75):: በሌላ ስፍራ

[11]ይህ ግለት ሙስሊሞች የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነትና የሰዎችን ነጻ ፈቃድ በማስታረቁ ዙሪያ ችግር የለባቸውም ማለት አይደለም:: ይህ ጉዳይ የክርስትና ነገረ መለኮት ምሁራንንም በአያሌው የሚያወዛግብ ጉዳይ ነው:: ነገር ግን በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ መተቸት ይህ መጽሐፍ ዐላማ ካደረገው እንዲሁም ይህ ምዕራፍ ሊዳሰሰው ከሰበው ቀሣ ነገር ወጣ ያለ ነው:: በርእሰ ጉዳዩ ላይ ሰፊ ጥናት ማካሄድ የፈለጉ የሚከተለውን የዶክትሬት ድግሪ ማሟያ ጽሑፍ ይመለከቷል:— John Hoover, *An Islamic Theodicy: Ibn Taymiyya on the Wise Purpose of God, Human Agency, and Problems of Evil and Justice,* Centre for the Study of Islam and Christian-Muslim Relations, University of Birmingham, United Kingdom, 2002. እንዲሁም የሚከተለውን ያልታተመ ይመልከቱ John Hoover, *"A Typology of Responses to the Philosophical Problem of Evil in Islamic and Christian Traditions"* (Unpublished paper Presented at a Mennonite-Shi'I dialogue: Toronto, October 24-26, 2002).

ከእግዚአብሔር የሆነው መንፈስ አማኞችን እንደሚያነቃቃ እናነባለን (ሱራ 17+85-86)::

ጸሩ ግን የሙስሊም ነገረ መለኮት ምሁራን፣ ቁርአን ስለ መንፈስ ቅዱስ የተናገራቸውን ምንባባት ከአዲስ ኪዳን ነገረ መለኮት ጋር በሚጻረር መልኩ ወደ መተርጉሙ ያዘነብላሉ:: የእስልምና ነገረ መለኮት የሥላሴን አስተምህሮ ስለማይቀበል፣ ሙስሊሞች ስለ መንፈስ ቅዱስ ያላቸው አመለካከት ትልቅ ጥንቃቄ የሞላበት ነው:: ሆኖም ግን በሙስሊም ነገረ መለኮት ምሁራን ዘንድ መጽሐፍ ቅዱስን የማንበብ ልማድ የለም:: ዐልፎ ዐልፎ የማንበቡ ልማድ ያላቸውም ሙስሊሞች ቢኖሩ፣ ክርስቲያኖች ብሉይ ኪዳንን በክርስቶስ አንጻር እንደሚተረጉሙት ሁሉ እነርሱ መጽሐፍ ቅዱስን በቁርአን አንጻር ለመተርጉም ትልቅ ጥረት ሲያደርጉ ይስተዋላል:: መንፈስ ቅዱስን በተመለከተ ሙስሊም የነገረ መለኮት ምሁራን የተለያየ ምልከታ አላቸው::

እንደ አንዳንድ የእስልምና የነገረ መለኮት ሰዎች ዕውቀትን የሚያካፍለውና የሚያነሣሣው መንፈስ ቅዱስ፣ ለመሐመድ መገለጥን ያመጣው መልአኩ ገብርኤል ነው ባዮች ናቸው:: በእርግጥም አንዳንድ የነገረ መለኮት ሰዎች ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚናገሩ ምንባባት ሁሉ ስለ መልአኩ ገብርኤል ነው የሚል አቋም ይዘዋል::

አብደላ ዮሴፍ ዓሊ የተባለው የነገረ መለኮት ምሁር፣ እነዚህን ምንባባት በጥንቃቄ ከመረመርን ወደዚህ ድምዳሜ በፍጹም አንደርስም የሚል አቋም አለው:: በርግጥ አንዳንድ ምንባባት ስለ መልአኩ ገብርኤል የሚናገሩ ቢሆንም ሁሉንም ከፍሎች እንደዚያ መተርጉሙ ግን ትክክል አይደለም ባይ ነው:: አንዳንድ ጊዜ ቁርአን መንፈስ ቅዱስን ከመላእክትና ከራእይ መጻሕፍት በተለየ መንገድ እንደ እግዚአብሔር ምሕረት አድርጎ ያቀረበበት ሁኔታ እንዳለ ጽፎአል[12]::

ሌሎች ሙስሊም የነገረ መለኮት ምሁራን ደግሞ፣ ኢየሱስ በዮሐንስ 14፣ 15 እና 16 ላይ ስለ መንፈስ ቅዱስ የሰጠውን ተስፋ ከቁርአን አንጻር ለመተርጉም ጥረት እንደሚያደርጉ ይታያል:: እነዚህ ምሁራን እነዚህ የመጽሐፍ ክፍሎች ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አንዳችም ግንኙነት እንደሌላቸው ነገር ግን ስለሚመጣው ስለ ነቢዩ መሐመድ የተሰጠ የተስፋ ቃል ነው የሚል አስተምህሮ አላቸው::

[12] Abdullah Yusuf Ali, *The Holy Qur'an: Text, Translation and Commentary* (Beirut: Dar Al Arabia, 198) 1605, footnote 5677.

ነገር ግን ኢየሱስ ስለ መንፈስ ቅዱስ፣ "እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል...የምነግራችሁ ገና ብዙ አለኝ ነገር ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም። ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ይመራችኋል" (ዮሐንስ 14+26፣ 16+12) የሚል ተስፋ ሰጥቶአል።

ሙስሊሞች እነዚህን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ሲያነቡ፣ ኢየሱስ ስለ ነቢዩ መሐመድ እንደ ተነበየ እንዲሁም መሐመድ ኢየሱስ የተናገረውን ነገርና ያስተማረውን ትምህርት እንደሚፈጽም የተሰጠ ተስፋ አድርገው ስለሚወስዱት በትልቅ ደስታ ይሞላሉ። አንዳንድ የአስልምና ሃይማኖት ዐቃብያን ከዚህም ርቀው በመሄድ፣ እናት ቋንቋው ስለ አሕመድ (መሐመድ) የሚናገር ነው የሚል ትምህርት እንዳላቸው ምዕራፍ 5 ላይ ለማየት ሞክረናል። ነገር ግን ለዚህ ዐይነቱ ትምህርት/ድምዳሜ አንዳችም ታሪካዊ የሆነ ምንባባዊ መሠረት እንደሌለ ልብ ይሏል።

ነገር ግን ለምንድን ነው ሙስሊሞች አዲስ ኪዳን ስለ መንፈስ ቅዱስ ከሚያስተምረው ትምህርት ራሳቸውን በማግለል አትጫን ለማስቀየር የሚፈልጉት? ለዚህ ሦስት ሁነኛ ምክንያቶች አሉ፣ እነርሱም:—

አንደኛ፣ ሙስሊሞች ማንኛውም ሰው እውነትን የመፈለግና እውነትን የመቀበል ችሎታ እንዳለው ሙሉ የሆነ እምነት አላቸው። ቁርአንና የመሐመድ ሱና ለእውነት ግልጽ ምስክር እስከ ሆኑ ድረስ እንዲሁም እግዚአብሔር ራሱን በፍጥረተ ዓለም ውስጥ እስከ ገለጠ ድረስ መንፈስ ቅዱስ ምን ሊጨምር ይችላል?

ሁለተኛ፣ በአብና በወልድ የተላከው መንፈስ ቅዱስ በቁርአን ውስጥ ከተገለጠው መንፈስ ቅዱስ ይልቅ በሐዋርያቱ ሕይወት ውስጥ ትልቅ ለውጥ አምጥቶአል። በአንድ የቁርአን ክፍል መንፈስ ቅዱስ አማኞችን በማገዝ ገንቱ ይገቡ ዘንድ እንደሚያበረታቸው ተገልጸአል (ሱራ 58+21-22)። ይህ ክፍል ስለ መንፈስ ቅዱስ ተጨማሪ ትምህርትም አለው፣ ይኸውም አማኙ እግዚአብሔርን ወይም መሐመድን (ሐዋርያውን) የሚቃወሙ ሰዎች ዘመዶቻችን ቢሆኑ እንኳ በፍጹም ልንወዳቸው ስለማይገባ እንዳንወዳቸው ጎይል እንደሚሰጠን ተገልጸአል።

አስገራሚው ተቃርኖ በአዲስ ኪዳን የመንፈስ ቅዱስ የመጀመሪያው ምልክት በአማኞች ውስጥ በመኖር ለአማኙ የሚለግሰው ነገር ፍቅር ነው፣ "የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር" (ገላትያ 5+22) ነው።

የመሲሑ ተልእኮ ጎጢአተኞችንና አማኝ ያልሆኑትን ሰዎች መውደድ ነው። ይህ የመንፈስ ቅዱስም ባሕርይ ነው። "በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለ ፈሰሰ ተስፋ አያሳፍርም። ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ጎጢአተኞች ሞቶአልና... እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል" (ሮሜ 5+5-6:8)።

ምስተኛ፣ ሙስሊሞች "ወደ ውሃ ምንጭ የሚመራቸው" ሸሪአ አላቸው። እንግዲያው መንፈስ ቅዱስ ምን ሊጨምር ይችላል? ለእግዚአብሔር ፈቃድ ለመገዛት ምን ማመን እንዲሁም ምን መተግበር እንደሚያስፈልግ ሸሪአ ያስተምራል። በዚህ ሂደት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ አንዳችም አስፈላጊነት አይኖርም። "ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል" (ዮሐንስ 16+13) የተባለለት መንፈስ ቅዱስ አንዳችም ድርሻ ከሌለው እንዲሁም ሸሪአ የእርሱን ቦታ ሙሉ ለሙሉ የሚተካው ከሆነ የመንፈስ ቅዱስ አስፈላጊነት ቦታ አይኖረውም። ሰዎች በፍጥረታቸው ፍጹም መልካም ከሆኑና አንዳችም ክፋት በውስጣቸው የሌለ ከሆነ፣ ለሸሪአ ከመገዛት ውጪ ውስጣዊ ለውጥ ሊያስፈልገን አይችልም። ሸሪአን ግዕዝኛዊ ባደረገ የኑሮ ዘይቤ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ድርሻ እጅግ በጣም አናሳ ነው።

መሲሑና መንፈስ ቅዱስ

ቤተ ክርስቲያን ከመመሥረቷ አስቀድሞ መሲሑ ጎላፊነቱን በብቃት ይወጣ ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ ተቀብቶአል። ከድንግል ማርያም መወለድም የጅለው በመንፈስ ቅዱስ ጎይል ነው። ወደ ማርያም መጥቶ የነበረው መልአክ ያወጀው የምሥራች፣ "መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፣ የልዑልም ጎይል ይጸልልሻል ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱሱ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል" (ሉቃስ 1+35) የሚል ነው።

ከዚያም መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስን ሲያጠምቀው መንፈስ ቅዱስ በአምሳለ ርግብ በኢየሱስ ላይ ወርዷል (ሉቃስ 3+21-22)። ከዚያም ኢየሱስ፣ "መንፈስ ሞላበት" (ሉቃስ 4+1)። የአደባባይ አገልግሎቱን ሲጀምር የመጀመሪያ ስብከቱን የጀመረው መኖሪያ ከተማው በሆነች በናዝሬት ምኩራብ ነው። ያንን የስብከት መልእክት የጀመረው የነቢዩ ኢሳይያስን መጽሐፍ እንዲህ ብሎ የሚጀምረውን ሐረግ በማንበብ ነው፣ "የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው" (ሉቃስ 4+18) የመሲሑ ኢየሱስ ሕይወትና አገልግሎት በመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት የተሞላ ነበር።

ኢየሱስ በአገልግሎት ዘመኑ ስትላቱንና ትንሣኤውን ተከትሎ ስለሚኖረው ስለ መንፈስ ቅዱስ ተግባር ቃል ገብቶአል። ከላይ እንደ ተጠቀሰው የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎቶች ቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ እውን የሆኑት፣ ኢየሱስ ስለመንፈስ ቅዱስ ቃል በገባው መሠረት ነው። አንድ ጊዜ በቤተ መቅደስ የዳስን በዓል እያከበረ ሳለ፣ ስለ መንፈስ ቅዱስ አስደናቂ ቃል ኪዳን በመግባት በዓሉን ለማክበር የተሰበሰቡትን ሁሉ አስደንቋቸዋል።

ኢየሱስ ቆሞ፣ "ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ። በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ የሕይወት ውሃ ወንዝ ከሽዱ ይፈልቃል ብሉ ጮኸ። ይኸን ግን በእርሱ የሚያምኑ ሊቀበሉት ስላላቸው ስለመንፈስ ተናገረ፣ ኢየሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ ገና አልወረደም ነበርና" (ዮሐንስ 7÷37-39)።

ሽሪአ ግለት፣ "ወደ ውሃ ጒድጓድ የሚያመራ መንገድ" ግለት እንደ ሆነ ተገልጸአል። በዚህ ክፍል እንዳየነው ኢየሱስ መንፈስን የገለጸው ከአማኞች ሕይወት የሚፈልቅ የሕይወት ውሃ እንደ ሆነ ነው።

በቤተ ክርስቲያን ተሞክሮ መንፈስ ቅዱስ ከኢየሱስ ተቃራኒ ሳይሆን መሲሑን በሁሉም መንገድ የሚያከብር ነው። ስትለትና ትንሣኤ የመሲሑ አገልግሎት ዋና ክፍል ናቸው። መንፈስ ቅዱስም ይህን ቀኖፍ ሐሳብ ሳይገልጥ (ሳይተረጒም) አያልፍም። በተሰቀለውና ሞትን ድል አድርጎ በተነሣው መሲሕ፣ አማኞች የጸጋን ስጦታ ዮኀኒአት ይቅርታንና አዲስ ሕይወትን ተቀብለዋል። መንፈስ ቅዱስ አማኞች በመሲሑ እንዲያምኑና የድኑትን ስጦታ እንዲቀበሉ ጒልበት ይሰጣቸዋል።

መንፈስ ቅዱስ አማኞች ፍሬያማ ሕይወት እንዲኖሩ ያስችላቸዋል። መጽሐፍ ቅዱስ ሲያብራራ፦—

> የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጐነት፣ እምነት፣ የዋህነት፣ ራስን መግዛት ነው። እንደዚህ ያሉትን የሚከለክል ሕግ የለም። የክርስቶስ ኢየሱስ የሆኑት ሥጋን ከክፉ ምኞቱና መሻቱ ጋር ሰቀሉት። በመንፈስ ብንኖር በመንፈስ ደግሞ እንመላለስ (ገላትያ 5÷22-25)።

መንፈስ ቅዱስ በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ

በክርስትና ታሪክ ውስጥ የቤተ ክርስቲያንን መመሥረት እውን ያደረገው መንፈስ ቅዱስ ነው (ሐዋርያት ሥራ 8)። ከይሁዲነት ወይም ከእስልምና በተቃረነ መልኩ፣ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን በሕግ እንዳትታጠር ዐርነት

ያወጣት መንፈስ ቅዱስ ነው። እንዲያውም መንፈስ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ውስጥ ትልቅ ድርሻ ከያዘ በኋላ ክርስቲያኖች ሕገ አሪት በተለየ መንገድ እንዲያብራሩት አድርጓቸዋል። ጴጥሮስና ጳውሎስ ለዚህ ሁነኛ ተጠቃሾች ናቸው።

መጀመሪያ ጴጥሮስ በኢዮጴ በጣራው ላይ ሆኖ ራቱን እየጠበቀ ሳለ፣ በራእይ በአራት ማዕዘን የተያዘ ታላቅ ሸማ የሚመስል ዕቃ ከሁሉም ዐይነት እንስሳ ተሞልቶአል፦— ዐሣማን ጨምሮ በሕገ አሪት የተከለከሉ እንስሳትን ይዞአል። እንዲህ የሚል አስፈሪ ድምፅ ወደ ጴጥሮስ መጣ፦—

> ጴጥሮስ ሆይ ተነሣና ዐርደህ ብላ የሚልም ድምፅ ወደ እርሱ መጣ። ጴጥሮስ ግን፦— ጌታ ሆይ አይሆንም አንዳች ርኩስ የሚያጸይፍም ከቶ በልቼ አላውቅምና አለ። ደግሞ ሁለተኛ፦— እግዚአብሔር ያነጻውን አንተ አታርክሰው። የሚል ድምፅ ወደ እርሱ መጣ (ሐዋርያት ሥራ 10÷13-15)።

ይህ የሆነው ሦስት ጊዜ ነው። ከዚያ በኋላ ሁለት መልእክተኞች ጴጥሮስን 30 ማይል ርቀት ላይ ወደ ምትገኘውና በቂሣሪያ በሚኖረው መቶ አለቃ ወደ ቆርኔሌዎስ ቤት እንዲመጡ ጋበዙት። ቆርኔሌዎስ ጴጥሮስን እንዲጋብዝ መመሪያ የተቀበለው ከመልአክ ነው።

ጴጥሮስ ቆርኔሌዎስ ቤት ሲደርስ መልእክቱን በመቀበል ከእርሱ ጋር ለመስማት በጒጒት የሚጠባበቁ ሰዎች ተሰብስበው አገኘ። እርሱም ትሕትና በጐደለው አነጋገር፣ "አይሁዳዊ ሰው ከሌላ ወገን ጋር ይተባበር ወይም ይቀራረብ ዘንድ እንዳልተፈቀደ እናንተ ታውቃላችሁ" (ሐዋርያት ሥራ 10÷28) በማለት ተናገረ።

ጴጥሮስ ለቆርኔሌዎስ እና ለቤተሰቦቹ ወንጌልን ሰበከ። ቤተሰቡ ሁሉ ካመነ በኋላ መንፈስ ቅዱስ በጴንጤቈስጤ ቀን በሐዋርያት ላይ እንደ ወረደና ቤተ ክርስቲያን እንድትመሠረት እንዳደረገው ሁሉ መንፈስ ቅዱስ በሁሉም ሰው ላይ ወረደ ጴጥሮስም በዚህ እጅግ ተደነቀ። ከዚህ በኋላ ጴጥሮስ ምን ሊያደርግ ይችላል? አሕዛብ እንዲሁም እንደ ሙሴ ሕግ ያልተገረዙ ሰዎች ቢሆኑም ጴጥሮስ ግን ያመኑትን ሁሉ አጠመቃቸው።

ከጥቂት ቀናት በኋላ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በኢየሩሳሌም ነገሩን እንዲገልጽላቸው ጴጥሮስን ጠሩት። የሃይማኖት ሥርዐት የሆነውን ሕገ አሪትን ያልታዘዙ አሕዛብ፣ በክርስትና ውስጥ እንዴት ሊታቀፉ ይችላሉ የሚለው

ጕዳይ ግልጽ ሊሆንላቸው አልቻለም። ነገር ግን ጴጥሮስ የተከሠተውን ነገር ሁሉ ነገራቸው። እነርሱም አስደናቂ የሆነውን የመንፈስ ቅዱስ ማረጋገጫ ሲሰሙ፣ "እንኪያስ እግዚአብሔር ለአሕዛብ ደግሞ ለሕይወት የሚሆን ንስሓን ሰጣቸው እያሉ እግዚአብሔርን አከበሩ" (ሐዋርያት ሥራ 11÷18)።

አስደናቂ ነጻነት

የሕገ ሙሴና የመንፈስ ቅዱስ ጕዳይ የሚለያይ (የሚነጣጠል) አይደለም። ጳውሎስና ጓደኞቹ የተላኩት በአንጾኪያ ቤተ ክርስቲያን በአሕዛብ መካከል እንዲሰብኩ ነበር። በትንሿ እስያ በተጓዙበት ስፍራ ሁሉ ቤተ ክርስቲያን ተመሥርቶ ነበር። በዚህ ሂደት ውስጥ ከአሕዛብ ወገን የሆኑ ሰዎች ሥርዐተ ግርዘትን እንዲፈጽሙ ሲደረጉ አንመለከትም። ከአይሁድ ወገን የነበሩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ አሕዛብ ከሙሴ ሕግ በራቀ መንገድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የመሆናቸው ጕዳይ እጅግ በጣም አሳስቦአቸው ነበር። ከዚህም የተነሣ በሕገ ሙሴና በመንፈስ ቅዱስ መካከል ያለውን ልዩነት ለመመርመር በኢየሩሳሌም ተሰበሰቡ። የሙሴን ሕግ ከልቡ ያፈቅርና ይገዛ የነበረው ሐዋርያው ጴጥሮስ በስብሰባው መካከል በመቆም እንዲህ ሲል ተናገረ፦—

> እንግዲህ አባቶቻችን እኛ ልንሸከመው ያልቻልነውን ቀንበር በደቀ መዛሙርት ሜንታ ላይ በመጫን፣ እግዚአብሔርን አሁን ስለምን ትፈታተናላችሁ? ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ እንደ እርሱ ደግሞ እንድን ዘንድ እናምናለን (ሐዋርያት ሥራ 15÷10-11)።

የስብሰባው ታዳሚዎች በአንድ ልብ በመስማማት ለአሕዛብ አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ የሚከተለውን ደብዳቤ ጻፉ፦—

> ለጣዖት ከተሠዋ ከደምም ከታነቀም ከዝሙትም ትርቁ ዘንድ ከዚህ ከሚያስፈልገው በቀር ሌላ ሸክም እንዳንጭንባችሁ እኛና መንፈስ ቅዱስ ፈቅደናል። ከዚህም ሁሉ ራሳችሁን ብትጠብቁ በመልካም ትኖራላችሁ። ጤና ይስጣችሁ (15÷28-29)።

ቤተ ክርስቲያንን ከሕግ ሸክም ለማላቀቅ የተወሰነው ውሳኔ እጅግ ከፍተኛ የሆነ ድፍረት የተሞላበትና እጅግ አስደናቂ የሆነ ውሳኔ ነው። ይህ ማለት ቤተ ክርስቲያን የእኔ ነው የምትለውና የራሷም የሆነ ባህልና ሃይማኖታዊ ሥርዐት አልነበራትም ማለት ነው። ቤተ ክርስቲያን የተለያዩ ማኅበረሰቦች ጥርትም

ከመሆን ባሻገር መጽሐፍ ቅዱስን የምትተረጕምበት መንገድ ተቀይሯል። ውሳኔው የእግኙን ማኅበረሰብና መንፈስ ቅዱስን ባካተተ መልኩ፣ "እኛና መንፈስ ቅዱስ ፈቅደናል" ተብሎ ነበር የተገለጸው።

ከዚህ ውጪ፣ የኢየሩሳሌሙ ጉባኤ ውሳኔ የሚያመለክተው፣ ቤተ ክርስቲያን የክርስትናን ባህልና ምግባር የሚገልጽ አንዳችም ነገር እንዳላዘጋጀች ነው። ቤተ ክርስቲያን እንደ አይሁድ ታልሙድን እንደ እስልምና ደግሞ ሸሪአን አልቀረጸችም (ምናልባት ከዚህ የሚቃረነው ነገር በመካከለኛው ዘመን የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ያዘጋጀችው ቀኖና ነው፦— ይህ ለእኔ ከአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ለየት ያለ ነው)።

መንፈስ ቅዱስና ጸርሰሳይ

በኢየሩሳሌሙ ጉባኤ የተወሰነውና ለቤተ ክርስቲያን የተሳሰፈው ሚስዮናዊ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን ሰዎችን ትለውጣለች እንጂ ጸርሰሳይ አታደርግም[13]። ቤተ ክርስቲያን ሰዎች መሲሑ ኢየሱስን ተቀብለው የእርሱን የሕይወት ዘይቤ እንዲከተሉ ማድረግ ቀዳማይ ዐላማዋ ነው። ሆኖም አንድ ክርስቲያን ከራሱ ባህል ወደ ሌላው ባህል መቀየር/መምጣት በጭራሽ አያስፈልገውም። አሕዛብ ክርስቲያኖች በሙሴ ሕግና በታልሙድ ላይ የተመሠረተውን የአይሁድ ባህል የራሳቸው አድርገው መቀበል/መውሰድ በጭራሽ አያስፈልጋቸውም። አሕዛብ እንደ ሆኑ ክርስትናን ተቀብለው መኖር ይችላሉ።

ከኢየሩሳሌም ጉባኤ ቀደም ብሎ የነበሩት ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር የኪዳን ግንኙነት ውስጥ ማደር የሚፈልጉ ሰዎች ወደ ይሁዲነት መቀየር አለባቸው የሚል እምነት ነበራቸው። ከኢየሩሳሌሙ ጉባኤ በኋላ ግን አሕዛብ ወደ ይሁዲ ባህል ሊቀየሩ እንደማይገባቸው ተወሰነ። በተቃራኒው የእግዚአብሔር የኪዳን ሕዝብ ለመሆን ብቸኛው መስፈርት አንድ ብቻ ነው፤ ይኸውም ንስሓ

---

[13] "ጸርሰላይ" (proselyte) እና "መለወጥ" (conversion) የተለያየ ትርጉም የሚወክሉ ቃላት ናቸው። ጸርሰላይ አንድ ሰው አንድን ሃይማኖት ሲቀበል ሃይማኖቱ የበቀለበትን ባህል አብሮ ሲቀበልና የራሱን ባህል ወግድ ሲል የሚከሠት ሲሆን መለወጥ ግን የራሱን ባህል እንደያዘ አንድን ሃይማኖት የሚቀበልበት መንገድ ነው። የይሁዲ እምነትና እስልምና ሰዎች ሃይማኖቱን ሲቀበሉ የራሳቸውን ባህል ዕርግፍ አድርገው በመተው የእይሁዳችን ወይም የዐረቦችን ባህል እንዲቀበሉ የሚያስገድድ ሲሆን ክርስትና ግን ሰዎች የራሳቸውን ባህል እንደያዙ የክርስትናን መሠረተ እምነት መቀበላቸው ነው። በዚህ መልኩ ክርስትና መለወጥን እንጂ ጸርሰላይነትን አይደግፍም፣ አያበረታታምም።

መግባት፣ ኮነጢአት መመለስ፣ ለመሲሑ ለኢየሱስ መገዛትና ከቤተ ክርስቲያን ጋር ኅብረት ማድረግ ነው።

አዲስ ፍጥረት

መጽሐፍ ቅዱስ ሕግ በሰው ልብ ውስጥ እንደ ተጻፈ አበክሮ ይገልጻል። ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች መካከል አንዱ ይህንን የውስጥ ለውጥ ማስገኘት ነው። መንፈስ ቅዱስ ግለሰቡን አዲስ ፍጥረት ያደርገዋል። ከመሲሑ መምጣት አምስት መቶ ዓመታት ቀደም ብሎ እግዚአብሔር በነቢዩ ኤርምያስ አማካይነት የሚከተለውን የተስፋ ቃል ሰጥቶአል፣ "ሕጌን በልቦናቸው እጽፈዋለሁ" (ኤርምያስ 31+33)። ክርስቲያኖች ይህ ትንቢት፣ መንፈስ ቅዱስ በክርስቲያኑ ሕይወት ውስጥ ከሚሠራው ሥራ የተነሣ በአዲስ ኪዳን ፍጻሜ አግኝቶአል የሚል እምነት አላቸው።

ከአንደ ተማሪ ጋር የነበረኝ ውይይት ሽሪአንና መንፈስ ቅዱስን በተመለከተ ያለውን ልዩነት በግልጽ ያሳያል። አብዲ መሐመድ ወደ ቤቴ ጉራ ብሎ የሚያስደስቱ ሃሣቃዎችን ከተጫወትን በኋላ፣ "እባክህን የክርስቲያንን ሽሪአ የሚያስረዳውን መጽሐፍ ስጠኝ። የክርስቲያኖችን መተዳደሪያ ደንቦች ማወቅ እፈልጋለሁ" አለኝ።

እኔም፣ "የመሲሑ ደቀ መዛሙርት መተዳደሪያ ደንባቸው መንፈስ ቅዱስ ነው። የዚህ ደንብ ማዕከል ደግሞ ለጠላቶቻችን እንኳ ሳይቀር ራሳችንን ለሌሎች አሳልፈን የምንሰጥበት የፍቅር አገልግሎት ነው። የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ለመንፈስ ቅዱስ በመታዘዝ መኖር ቀዳማይ ዐላማቸው መሆኑን ማቴዎስ በወንጌሉ የጻፈው የተራራው ስብከት ትልቅ አብነት ነው። ሰዎች እንዴት መኖር እንዳለባቸው ስለማንኖውም ነገር ጠንቅቀህ ልትጽፍ አትችልም፣ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ሰውን አዲስ ፍጥረት ስለሚያደርገው ከእግዚአብሔር ሐሳብ ጋር በተጣጣመ መልኩ እንዴት መኖር እንደሚገባው መንፈስ ቅዱስ ራሱ ይገልጽለታል። ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ እንደ ገና ስለመፈጠር ሲናገር ዳግም መወለድ እንደ ሆነ አመልክቶአል" አልሁት።

በሌላ አጋጣሚ ደግሞ አንድ ያልተማረና በዕድሜ የገፋ አብዱላሂ የተባለውን የመሲሑ ደቀ መዝሙር የነበረን ሰው፣ "እውነተኛውን ነገር እንዴት ታውቃለህ?" አልሁት። እርሱም፣ "ልቤ ልክ እንደ ደነዘ ቢላዋ ነው። መንፈስ ቅዱስ ደግሞ እንደ ሞረድ ነው። በምሽት መንፈስ ቅዱስን በምሰማበት ጊዜ

ልቤን ይሞርደዋል። ሁሉንም ነገር ስል እና ግልጽ ያደርግልኛል" ብሎ መለሰልኝ። ይህ መንፈስ ቅዱስ አዲስ ፍጥረት ሲያደርገን የምናገኘው ነጻ ስጦታ ነው። ጳውሎስ ጉዳዩን በዚህ መንገድ አስቀምጦታል፦—

"እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም። በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ ዐርነት አውጥቶኛልና" (ሮሜ 8+1-2)።

የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ

ዮሐንስ 16+5-16፤ ገላትያ 5+16-26

የቁርአን ምንባብ

ሱራ 2+177፤ 58+22

<u>የአስተሙሶትና የውይይት ጥያቄዎች</u>

1. በይሁዲነትና በእስልምና እምነት "ሕግ" ጥልቅ መስብ ኖሮት፣ በክርስትና ግን ይህ ዐይነቱ አካሄድ በጭራሽ የማይደገፈው ለምን ይመስልዎታል?
2. እስልምና ለመንፈስ ቅዱስ አናሳ ስፍራ (ትኩረት) የሚሰጠው ለምንድን ነው?
3. በወንጌል ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ የተመሠረተው በክርስቶስ አገልግሎትና ሕይወት ላይ ነው። መንፈስ ቅዱስን በተመለከተ በእስልምና ነገረ መለኮትና በክርስትና ነገረ መለኮት መኻል ያለውን መረዳትና የሚያስከትለውን እንድምታ ግለጽ።
4. ሱናና ሽሪአ የእስልምናን ባህልና የፖለቲካ ሥርዐት ለመመሥረት አንዱ ከሌላው ጋር ያለው መስተጋብር/ጥምረት እንዴት ይመስላል?
5. መለወጥና የአንድ የሃይማኖት ባህል አባል መሆን ልዩነቱ ምንድር ነው? መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን ይለውጣል ሽሪአ ደግሞ የሰዎችን ሃይማኖትና ባህል ይቀይራል።

ጸሎት

ሰላት—ንብረት

አብዲ የሚለው ስም በሙስሊሞች ዘንድ ተወደደ ስም ነው:: በዐረብኛ አብዲ ማለት፣ "አገልጋይ" ማለት ነው:: ታማኝ የሆኑ ሙስሊሞች ሁሉ ለእግዚአብሔር አገልግሎት የተሰጡ ናቸው:: ለዚህም ነው በቀን ዐሥራ ሰባት ጊዜ ያህል በእጆቻቸውና በግንባራቸው በመደፋት በእግዚአብሔር ፊት የሚሰግዱት:: ታማኝ ሙስሊሞች በቀን አንድ ሰዓት ያህል ግዴታዊ ለሆነው ለሥርዐተ አምልኮ ጸሎት (ሰላት) ያውላሉ::

ሙስሊሞች በእግዚአብሔር ለተገለጠው እውነተኛ ሃይማኖት (ዲን) መገዛት ይፈልጋሉ:: እውነተኛ ዲን የሆነው እስልምና በአምስት ወይም በስድስት የሃይማኖት ዐምድና በአምስት ወይም በስድስት ምግባራዊ ዐምድ ሊጠቃለል ይችላል:: አጠቃላይ መሰጠቱ የሚገለጠው እንደ እግዚአብሔር አገልጋዮች ለእውነተኛው ዲን በመገዛት ነው::

ሰላት (ስግደት) ለእግዚአብሔር መገዛታችንና መሰጠታችንን የሚገልጽ ሥርዐታዊ የጸሎት ልምምድ ነው:: ሥርዐታዊ የስግደት ጸሎቶች ሙስሊሞች ለቁርአን ለተገለጠው የእግዚአብሔር ፈቃድ በሁለንተናቸው መገዛታቸውንና መሰጠታቸውን የሚያሳይ ቋሚ ምልክት ነው:: በቀን አምስት ጊዜ የሚደረገው የጸሎት ሥርዐት፣ ሙስሊሞች ለአምላክ መሰጠታቸውን የሚያሳይ ውጫዊ ምልክት ነው:: ለእምነቱ ሕይወትን የማስገዛት መንገድ የእስልምና ልምምድና የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው:: ሰላትና የመጨረሻው ፍርድ (ዕድል ፈንታ) በአንድ የተቈራኙ ናቸው:: ሰላትና ሰላት የሚወክለውን ዐይነት መገዛት ባለቤት የመሆናችንም ሆነ ያለመሆናችን ጉዳይ፣ እግዚአብሔር የመጨረሻ ዕድል ፈንታችንን በሚወስንበት ጊዜ ወሳኝ የሆነ ድርሻ አላቸው::

በአንድ ወቅት በመስጊድ ውስጥ የተከሠተ አንድ ድርጊት ለዚህ ጥሩ ናሙና ነው:— የምሽት ጸሎቱ ከተጠናቀቀ በኋላ፣ የመስጊዱ ኢማም ለመስጊድ ማስጠንቀቂያ ገንዘብ እንዲያዋጣ ጉባኤውን አስጠነቀቁ:: "የመጨረሻው ፍርድ እየመጣ መሆኑን ልብ ልትሉ ይገባል:: ለዚህ ጉዳይ ላለመስጠት መወሰናችሁ የሚያስከትለውን ዘግናኝ ድርጊት ለጥቂት ጊዜ እንኳ አስቡ:: ከመስጊድ

እንደወጣችሁ መኪና ገጭቶ ይገድላችኋል። በመጪረሻው የፍርድ ቀን ይህ ለመስጊድ የመስጠት መልካም ሥራ መልካምና ክፉን በሚመዝነው በሚዛናችሁ ላይ አይቀመጥላችሁም ማለት ነው። ምን ያህል ዘግናኝ እንደ ሆነ ልብ በሉ። ስለዚህ ገንዘብ ሳታዋጡ ከዚህ እንዳትወጡ አሳስባችኋለሁ"።

ይህ ምዕራፍ ልዩ አምልኮተ ሥርዐት የሆነውን ሰላትን የሚመለከት እንዲሁም ሰላት ለእግዚአብሔር ፈቃድ ሙሉ በሙሉ መገዛትን በማመልከቱ ረገድ ያለውን ሰፊ ትርጉም ይመረምራል። በመጀመሪያ ሰላት የሃይማኖቱ ዐምድ እንዲሁም የምንባር ማዕከል የመሆኑን ጉዳይ እንመለከታለን። በመቀጠልም ተለምዷዊ በሆነው የዘወትር ጸሎት ውስጥ፣ ለእግዚአብሔር መገዛትን በማመልከቱ ረገድ ያለውን ቦታ እንቃኛለን። ታማኝ ለሆኑ ሙስሊሞች እያንዳንዱ ሕይወት ሰላት ነው። ይኸውም በቁርአን ለተገለጠው ለእግዚአብሔር ፈቃድ በትሕትና መገዛት ማለት ነው።

የእምነት አዕማድ

ከዚህ በፊት በነበሩት ምዕራፎች፣ የእምነት (ሶሊማን) ዐምዶችን ለመመልከት ሞክረናል። የአይሁድ የእምነት መግለጫ፣ "እስራኤል ሆይ፣ ስማ እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው፣ አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም ኀይልህ ውደድ" (ዘዳግም 6÷4-5) በሚለው በአንድ ጥቅስ እንደ ተጠቃለለ ሁሉ፣ ለሙስሊሞችም ዐቢይ የሆኑት የእምነት አናቅጽ በአንድ የቁርአን ጥቅስ ውስጥ ተጠቃለው ይገኛሉ።

ቁርአን አምስት ዐበይት የሚባሉ እምነቶችን ዐቅፎአል። ይህ ቍልፍ ጥቅስ እንዲህ ይላል:— "እናንተ የምታምኑ ሆይ! በአላህና በመልእክተኛው ላይ ባወረደው መጽሐፍ በዚያም ከበፊቱ ባወረደው መጽሐፍ እመኑ፤ በአላህና በመላእክቱም በመጽሐፎቹም፣ በመልእክተኞቹም በመጪረሻውም ቀን የካደ ሰው (ከውነት) የራቀን መሳሳት በእርግጥ ተሳሳተ" (ሱራ 4÷136)።

ይህ ጥቅስ የእስልምናን እምነት (ሊማን) በዚህ መልክ ያጠቃልለዋል:—

1. በአንድ አምላክ ማመን
2. በእግዚአብሔር ነቢያት ማመን (ማንኛውም ሕዝብ የራሱ የሆነ ነቢይ ነበረው ሆኖም ግን መሐመድ የነቢያት ሁሉ መደምደሚያ ናቸው)።
3. በተገለጡት መጽሐፍት ማመን (ይህ በምዕራፍ 6 ተጠቅሷል)።
    - ሱሑፍ (ገጾች) ለአብርሃም የተሰጠው ነገር ግን አሁን የጠፋ መጽሐፍ ነው።
    - ተውራት (ፔንታቱክ) ለነቢዩ ሙሴ የተሰጡት የአሪት መጻሕፍት።
    - ዘቡር (መዝሙር) ለነቢዩ ዳዊት የተሰጠው መጽሐፍ።
    - ኢንጅል (ወንጌል) ለመሲሑ ለኢየሱስ የተሰጠው።
    - ቁርአን ለነቢዩ መሐመድ የተሰጣቸው።
4. በመላእክት ማመን። ይህ እጅግ በጣም መሠረታዊ ጉዳይ ነው ምክንያቱም መልእክቱን ያወረዱት/ያመጡት መላእክቶች ናቸውና።
5. በመጪረሻው ቀንና በመጪረሻው ፍርድ ማመን።

ሙስሊሞች አዘውትረው ስድስተኛ የእምነት ዐምድ ይጨምራሉ፣ ይህም ቃዳር (ውሳኔ) ሊለወጥ የማይቻል የእግዚአብሔር ፈቃድና ሉዓላዊነት። "የዓለማት ጌታ አላህ ካልሻም አትሹም" (ሱራ 81÷29)።

ሐዲስ እነዚህን ስድስት እምነቶች በዚህ መልክ ይገልጻል። ገብርኤል የእግዚአብሔር መልእክተኛ እምነት ባሕርይው ምንድን ነው ብሎ ጠየቀው። መሐመድም ሲመልስ፣ "ኢማን (እምነት) ማለት በአላህ በመጪረሻው ዘመን እና በቃዳር (ቅድመ ውሳኔ) ማመን ነው"[1]።

በየትም ስፍራ ላይ እስላም ያልሆኑ ሰዎች ሙስሊሞችን፣ "በምን ታምናላችሁ?" ብለው ቢጠይቋቸው የማንኛውም እስላም መልስ አንድ ዐይነት ነው። በእግዚአብሔር፣ በነቢያት፣ በመጻሕፍቶች፣ በመላእክትና በመጪረሻው ፍርድ እናምናለን ይላሉ። ብዙዎች ቅድመ ውሳኔን ሊጨምሩ ይችላሉ። ይህ ሺአይቶችም ሆነ ሱኒዎች በመካ ወይም በናይሮቢ ወይም ቴህራን ወይም ኒውዮርክ ከተማ እውነት ነው። በቀደመው ምዕራፍ እነዚህ ስለ እምነቶች የማሰጡ አመለካከቶችን ተመልክተናል። እዚህ ስፍራ የመጪረሻው ፍርድ ከዚህ እምነት አንጻር ያለውን ሚና ትኩረት እንሰጣለን።

<u>የመጪረሻው ፍርድ</u>

የመጪረሻው ዘመን ፍርድ ፍርሓት በቁርአን ውስጥ በስፋት ተንጸባርቋል። ቀኑ ድንገት ሳይታሰብ ልክ አንደ መብረቅ ብልጭታ ይመጣል። የመጪረሻው ቀን መምጣቱን ለማወጅ መለከት ይነፋል። ሰማያት ለሁለት ይከፈላሉ፣ ምድር ተሰባብራ በመድቀቅ ወደ አቧራነት ትቀየራለች።

[1] *Tradition* by Saheeh Muslim.

በዚያ በመጨረሻ ቀን በገሃነም ከአጋንንቶች ጋር የሚጣሉትን ወይም ወደ ገነት የሚገቡትን ሰዎች እግዚአብሔር ይለያል። ገሃነም የተገለጸው አስፈሪ (አስደንጋጭ) በሆነ ሥዕል ነው። ወደ ላይ የሚወነጨፍ የእሳት ትንታግ፣ የሚሰነፍጥ ጢስ፣ ፍል ውሃ፣ ኾድ ውስጥ የሚቃጠል ጭራሮ መጨመሩ ወዘተ የመሳሰሉ መግለጫዎች አሉት። ገነት የተገለጸው ውብና የደስታ ቦታ ተደርጉ ነው። የዛፍ ፍሬዎች፣ ወንዞች፣ ዛጐላማ ዐይን ያላቸው ኮረዳ ልጃገረዶች፣ ያማረ ስጋጃ ምንጣፍ፣ ያሸበረቁ ሕንፃዎች፣ የተትረፈረፈ የወይን ጠጅ (ሱራ 88+9-16፤ 56+11-24)። ደግና ክፉ ሥራው የተጻፈበት የእያንዳንዱ ሰው የራሱ መጽሐፍ ይከፈታል። እግዚአብሔርም እምነታችንንና ሥራችንን ይመረምራል።

እግዚአብሔር እኩያ (ሽሪክ) አለው ብለው የሚያምኑ ሁሉ ይኩነናሉ። ይህም የከፋው ኀጢአት ነው፤ ምክንያቱም ከአንድ በላይ አምላክ ማምለክ ነው። መልእክተኞችን ከእግዚአብሔር የሚለዩ ወይም የተወሰኑ መልእክተኞችን ተቀብሎ ሌሎችን የማይቀበል ይፈረድበታል (ሱራ 3+84-87፤ 48+8-10)። መልካም ሥራና ክፉ ሥራ ሁለቱም ሚዛን ላይ ይቀመጣሉ። መልካሙ ሥራ ከክፉው ሥራና እምነት በልጦ ከታየ እግዚአብሔር ምሕረቱን እንደሚጨምርለት ይታመናል (ሱራ 23+101-104፤ 21+47)።

ሙስሊሞች በመጨረሻው ፍርድ ሰዓት መሐመድ እንደሚማልድ ያምናሉ። ቁርአን ከፍቃድ ውጪ አማላጅነት የለም ይላል (ሱራ 20+109)። የዐሥራ ሁለተኛው ክፍለ ዘመን የሱፊ የነገረ መለኮት ምሁር አልገዛሊ መሐመድ ለማማለድ ፈቃድ እንደሚጠይቅ ይገልጻል። በመጨረሻው ፍርድ ወደ ፊት ይወጣና በመጮኽ፣ "እግዚአብሔር ለወደደውና ለመረጠው እስከ ፈቀደ ድረስ እስካሁን ባለው እኔ ለመማለድ ትክክለኛ ሰው ነኝ" ይላል። ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ሲመልስ፣ "መሐመድ ሆይ አንተ የምትሰማ ስለሆንህ ራስህን ቀና አድርገህ ተናገር የምትፈልገውን ጠይቅ ይደረግልሃል"[2] ይለዋል።

በሚቀጥለው ምዕራፍ የክርስቲያኖችንና የሙስሊሞችን ታሪክ የሚመለከተውን ክፍል እንዳስሳለን። አሁን ትኩረት የምናደርገው በአምስቱ የእምነት አዕማድና የመጨረሻ ፍርድ ማዕከላዊና ሙስሊሞች ትልቅ ግምት በሚሰጡት የታሪክ ትርጉም ነው። እስልምና ማለት በመሠረቱ መሓሪው አላህ በመጨረሻው ፍርድ ርኅራኄ እንደሚያደርግ ተስፋ በማድረግ ለፈቃዱ መገዛት ነው።

[2] Jane Idleman Smith, ed., *The Precious Pearl: A Translation from the Arabic* (Missoula, Mont.: Scholard Press, 1979) 59-60.

የምግባር አዕማድ

የሰላት (የስግደት) መንፈስ ራሱ፣ ለሥነ ምግባር ዐምዶች መገዛትን የሚያመለክት ነው። ምዕራፍ 11 እነዚህን አዕማድ በአጭሩ በመቃኘት ለኋለኛው ዘመን የእስልምና ሕግ (ሸሪአ) ያለውን አንድምታ በጸሰላ መልክ ተመልክተናል። ዐምዶቹ የእምነት መግለጫ (ሸሃዳ) ጸሎት (ሰላት)፣ ጾም (ሶውም)፣ ምጽዋት (ዘካ) እና ሃይማኖታዊ ጉዞ (ሃጂ) ናቸው። ብዙ ሙስሊሞች ስድስተኛ ሕግ ይጨምራሉ፤ ይኸውም ቅዱስ በሆነው የሃይማኖት ጦርነት (ጂሃድ) ውስጥ ተካፋይ መሆን። እነዚህ ምግባሮች እያንዳንዳቸው፣ በእስልምና መንፈሳዊነት ላይ ጥልቅ ዕውቀት የሚለግሱ ናቸው።

በጸሎት መገዛት

የእምነት አዕማድን ለመረዳት የመጨረሻው ፍርድ ወሳኝ እንደ ሆነ ሁሉ፣ በምግባር ሕጉ ላይ እንደ ተገለጸው፣ ሥርዐታዊ ለሆነው ጸሎት (ሰላት) መገዛትም ወደ ፍጽምና ለሚያደርሰው ምግባራዊ መሰጠት መሠረት ነው። ሥርዐተ አምልኮአዊ የሆነው ጸሎት፣ የእስልምናን ትርጉምና ግራኪነት የሚፈታ ቁልፍ ነው። ሰላት በእግዚአብሔር ፊት በንስሓ (ጸጸት በተሞላበት) መንፈስ የመቅረብ ሂደት ስለሆነ፣ ሰላት የእስልምና እስትንፋስ ተደርጉ ይወሰዳል።

የሜኖናይቱ ክርስቲያን ኢቫን ቦንትራገር ሲናገር፣ በእግዚአብሔር ፊት ፊቱን ከወለሉ ጋር በማገናኘት በቀን አምስት ጊዜ ለበርካታ ጊዜያት እንደ ሰገደ ይናገራል። ይህንንም ያደረገው በእስልምና ሥርዐት ውስጥ ያለውን መንፈሳዊነት ለመመርመር ነው፦—

> ጸሎት የማደርሰው ግንባሬን ወለሉ ላይ በመድፋትና እጆቼን ወለሉ ላይ በመዘርጋት ነው። በአካሌም ሆነ በአንደበቴ ለእግዚአብሔር ፈቃድ መገዛቴን እያወጅሁ ነበር። አገልጋይ ለመሆን ራሴን ሰጥቼ ነበር። በየዕለቱ ለስግደት መቅረቤ ልግድ እየሆነ ቢመጣም እንኳ፣ የጸሎቱን ትርጉም አላደበዘዘውም ነበር። በእያንዳንዱ ሷት ንጋት ላይ፣ ከዚያ ከሰዓት ላይ፣ ከቀትር በኋላ፣ ጀንበሯ ከዘቀዘቀች በኋላ እንዲሁም ለመኝታ ወደ ዐልጋዬ ከመሄዴ በፊት እጸልይ ነበር። ድሮ ዐልፎ ዐልፎ ብቻ የነበረኝ ዐይነት ልምምድ አሁን ዘወትር እንዲኖረኝ አድርጉልኛል። ይህ የዘወትር ልምምድ ከእግዚአብሔር ጋር ያለኝን ኅብረት ዕለት በዕለት እንድጠብቅ ትልቅ ትምህርት ሰጥቶኛል። እስልምና የሚያስተምረውን ያድግሞሽ ጸሎትን ጥቅም ዐውቄያለሁ። እኔ

ብሆንም እንኳ፣ ከዚህ ዐይነቱ ጸሎት በትሕትና የመገዛትን ትርጉም አይቻለሁ። እንደ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ክብር ለመኖር ራሴን አስገዛለሁ[3]።

በገጻም ይኖሩ የነበሩ ክርስቲያኖች ለብዙ መቶ ክፍለ ዘመን ለእግዚአብሔር ሙሉ መገዛትን የሚያመለክት ሥርዐታዊ ምልክት ያለውን ጸሎት ይጸልዩ ነበር። ብዙ ሙስሊሞች የጸምንና የጸሎትን ሥነ ሥርዐት በተደጋጋሚ እንዲያከናውኑት ሁሉ፣ የክርስቲያኖችም የጸም ጸሎት ሥነ ሥርዐት ትልቅ መንፈሳዊ ዋጋ አለው። በእግዚአብሔር ፊት መደፋትና ጸም ጸሎት ማድረስ የሙስሊሞች ልምምድ ብቻ አይደለም።

ለሙስሊሞች በቀን አምስት ጊዜ መጸለይ ግዴታ ነው። ሙአዚን ማኅበረሰቡን ለጸሎት ይጠራል (ሉድሃን)። ሙስሊሞች አናሳ በሆኑበት ማኅበረሰብ በጉረቤቶቻቸው ካልታገዱ በቀር አምስቱን የጸሎት ጥሪዎችና ግብዣዎች ከጸሎት ማማው ላይ በመሆን አዛንን ያውጃሉ። አዛን ማዕከላዊና ለድርድር የማይቀርቡ የእስልምናን እምነትና ተልእኮዎችን የያዘ ጥሪ ነው። የአዛን ጥሪም እንደሚከተለው ነው፣ " ምስክርነቴን እሰጣለሁ፣ አላህ እጅግ ታላቅ ነው፣ መሐመድም የአላህ መልእክተኛ ነው፣ ኑና አምልኩ"።

በፍጥነት ጉባኤው ለጸሎት ይሰበሰባል። ጸሎቱን ለማድረስ ወደ መስገጃ ስፍራው መምጣት ያልቻሉ ባሉበት ስፍራ በግላቸው ሥርዐተ አምልኮውን ያደርሳሉ። ከእያንዳንዱ ጸሎት በፊት ሥርዐታዊ መንጻት ወይም መታጠብ የግድ ነው። እያንዳንዱ ጸሎት የተወሰነ ቁጥር የጸሎት ረካ ወይም (ኡደቶች) ይጠይቃል። ንጋት ላይ ሁለት ረካዎች (በመቆም በመጉንበስ በመንበርከክ የሚደረግ የጸሎት ኡደት) ቀትር አራት ረካዎች፣ አጋማሽ ከሰዓት በኋላ አራት ረካዎች፣ ፀሓይ ከጠለቀች በኋላ ሦስት ረካዎች፣ በመኝታ ሰዓት አራት ረካዎች። እንደ ሥርዐቱ እነዚህ በአጠቃላይ ዐሥራ ሰባት ረካዎች ልክ እንደ ሥርዐቱ መፈጸም አለባቸው። ሰላት ከዕቅድ (ኒያ) ይጀምርና ሰባት ደረጃዎችን ይይዛል፦—

1. ታክቢር (አላህ ታላቅ ነው) ሲባል ሁለት እጆች በእያንዳንዱ የፊት ክፍል ይቀመጣሉ። ይህ አምላኪው ፊቱን ወደ ካባ ሲያዞር ሰይጣንንና የዓለምን ትችት እንደሚቃወም ያመለክታል። ማህራብ (በመስጊዶች) ግድግዳ ላይ የከአባን ቂብላን (አቅጣጫን) ለጸሎት የሚያመላክት ነው

[3] Evan Bontrager, "My Participation in Ramadan," *The Mennonite* (19 November 2002): 11.

(ሙስሊሞች ለጸሎት ፊታቸውን ወደ ካዕባ አቅጣጫ መመለስ አለባቸው)።

2. ቀኝ እጅ በግራ እጅ ላይ አነባብሮ ደረት ላይ ማስቀመጥ እና እግዚአብሔርን ለማክበር የማነብነብ ጸሎት ማድረግ። መደምደሚያው ሐሳብ፣ "ከተረገመው ዲያቢሎስ ሸሽቼ በእግዚአብሔር አተገናለሁ" ይላል። ከዚያም አምላኪው በአል-ፋአታሃ የተጻፈውን ጸሎት ይደግማል (የመጀመሪያው ቁርአን ክፍል)። ይህም ፍጽምና እንደ ተሞላበት የጸሎት ናሙና ይታያል። ይህም ግለሰቡ ቆሞ የሚደግመው ጸሎት ነው። ብዙ ጊዜ ሌላ የቁርአን ምዕራፍ (ሱራ) ሊደገም ይችላል።
3. እንደቆሙ ከወገብ ዝቅ ብሎ ታክቢርን መድገም (እግዚአብሔር እጅግ ታላቅ ነው ማለት)።
4. ቀጥ ብሎ መቆም።
5. በጉልበት ወደ ምድር በማጉንበስ ወለሉ ግንባርን እስኪነካ ድረስ ወደ ምድር መውረድ፣ ሁለቱም እጆች ሁለቱም ጉልበቶች እንዲሁም የእግር አውራ ጣቶች በመሬት ላይ ይሆናሉ።
6. መቀመጥ እና ሁለት እጆችን በጉልበቶች ላይ አድርጉ ሌላ ተክቢር መድገም።
7. ታክቢርን እየደገሙ እንደ ገና ወደ ምድር መውደቅ። ከዚህ በኋላ አምላኪው ታክቢርን እየተናገረ ይነሣና የጸሎት ኡደቱ (ረካ) ይጠናቀቃል። እነዚህ ሰባት ደረጃዎች በአንድ ረካ (በጸሎት ዑደት) የታቀፉ ነው። የጸሎት ኡደቱ ሲጠናቀቅ አምላኪው ሸሃዳን ይደግማል፣ "ከአላህ በስተቀር አምላክ የለም፣ መሐመድ የአላህ ነቢይ ነው"። ወደ ቀኝና ወደ ግራ በመዞር ጠባቂ መላእክት በቅርብ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ። እርስ በእርሳቸውም ሰላምታ ይለዋወጣሉ።

ከሥርዐታዊው ጸሎት በኋላ አምላኪዎች ቢመጡና እጆቻቸውን በመክፈት መዳፎቻቸውን ወደ ላይ በማንሣት ጸሎታቸውን ለእግዚአብሔር ሊያቀርቡ ይችላሉ። ይህ የአክብሮት ጥያቄ (ዱአ) የሚቀርበው በዐረብኛ ላይሆን ይችላል። ሆኖም ማንኛውም ሥርዐታዊ ጸሎቶች (ሰላት) መደረግ ያለባቸው በዐረብኛ ነው[4]። አብዛኛውን ጊዜ የዱአ ጸሎት በሚቀርብበት ጊዜ አምላኪዎቹ ዐይኖቻቸውን ወደ ላይ ያነሣሉ፣ መዳፎቻቸውን ከፍተው ወደ ላይ

[4] Muhammad Hamidullah, *Islam in a Nutshell* (Philadelphia: Ayesha Begum Hyderabad House, Inc., 1990), 12-53.

ያነሣሉ። በተረጋጋ መንፈስ አዛኝና ሩኅሩኅ ለሆነው አምላክ ምልጃቸውን በሰላት ለአምላክ ያቀርባሉ።

ሁል ጊዜ አንድ ሰው የሚደረጉ ጸሎቶቹን ለመምራት ከፊት ይቆማል። ይህ ሰው ኢማም ሊሆን ይችላል። ሆኖም ይህ ቢያንስ በሱኒ ጉባኤዎች ግዴታ አይደለም። አትኩሮትን እንዳይቀንስ በሚል ሁል ጊዜ ሴቶች ከወንዶች እንዲለዩ ይደረጋል። ሙስሊሞች የጸሎትን ሰዓት ካሳለፉ ማካካሻ ረካዎች ያደርጋሉ። ይህንንም የሚያደርጉት ምሽት ላይ በመስጊድ ውስጥ ነው። ከጉባኤ መደበኛ ጸሎቶች በፊትና በኋላ ግለሰቦች በመስጊድ ውስጥ ለብቻ ቆመው ረካዎችን ሲደግሙ ይታያሉ። ሙስሊሞች እንደ ነገሩኝ አንዳንድ አምላኪዎች ለሠሩት መጥፎ ድርጊት ማካካሻ ተጨማሪ ረካዎችን ያደርጋሉ።

ጉባኤው

በጸሎት ጊዜ በመስጊድ መሰብሰብ ለሙስሊሞች ያመረጥ ነው። ለአምስቱም የጸሎት ጊዜ ወደ መስጊድ መሄድ ካልተቻለ ማንኛውም ሙስሊም ባለበት ቦታ ሆኖ ጸሎት ማድረስ ይችላል። ሆኖም በዕለተ ዐርብ ለእኩለ ቀኑ ጸሎት አካባቢው በሚገኝ መስጊድ እንዲገኝ ይበረታታል። ብዙ ሙስሊም ማኅበረሰቦች አንድ ትልቅ መስጊድን፣ "የዐርብ መስጊድ" ብለው ይለዩታል። በዚህ መስጊድ በአካባቢው የሚገኙ ሙስሊሞች ሁሉ በሳምንት አንድ ጊዜ ተሰብስበው ይሰግዳሉ ስብከትም ያዳምጣሉ። ነገር ግን ወንዶችና ሴቶች በማንኛውም ወቅት በመስጊድ በአንድነት አይሰበሰቡም። አንዳንድ ጊዜ ለሴቶች ለብቻ መስጊድ አላቸው፣ ብዙ ጊዜ ግን ሴቶች ከዋናው ጉባኤ በተለየ ስፍራ እንዲሰበሰቡ ይደረጋል።

ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ማድረግ

ታማኝ የሆኑ ሙስሊሞች ሁሉ ሰላት የሚጠይቀውን ግዳጅ ሁሉ ለመፈጸም ራሳቸውን የሰጡ ናቸው። በእስልምና ሕግ ላይ ጥናት ያካሄዱ የእስልምና የነገረ መለኮት ምሁራን፣ ለእግዚአብሔር ሕግ በታማኝነት ለመገዛት ይቻል ዘንድ፣ ጥቃትን ናቸው የሚባሉትን ሕግጋት ሳይቀር ለሙስሊሙ ማኅበረሰብ ሁሉ በሚሆን መልኩ ይተነትኑታል። በነገረ መለኮት እግዚአብሔርን ማወቅ እንችላለን? ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ሊኖረንስ ይችላል? ይህ ጥያቄ በሙስሊሞች መካከል የሚገኘውን የሱፊ እስልምናን አካሄድ ወለደ። ምንም እንኳ ዋነኛው የእስልምና እምነት (አርቶዶክስ እስልምና) ሰዎች ከእግዚአብሔር

ጋር በሚያደርጉት ግላዊ ግንኙነት እግዚአብሔርን ሊያውቁት አይችሉም ቢልም፣ ሱፊዎች ግን በእግዚአብሔር መገኘት ውስጥ በመታቀፍ እግዚአብሔርን ማወቅ ይፈልጋሉ። ዐልፎ ዐልፎ በኦርቶዶክስ እስልምናና በሱፊ እስልምና መካከል የነገረ መለኮት ውጥረቶች ስለሚካሄዱ ግጭቶች ይፈጠራሉ።

ለምሳሌ በአንድ ወቅት በቴምኽል ዩኒቨርስቲ በእስልምና ላይ የዶክትሬት ጥናቱን የምታካሂድ አንዲት የሶሪያዊት ሙስሊም አንድ ቀን ሙሉ በተካሄደ ዐውደ ጥናት ላይ እኔ ለማስተምራቸው ክርስቲያን ተማሪዎች ንግግር አደረገች። በሰሌዳው ላይ ከላይ "አላህ" ከሥር ደግሞ "ሰው" ብላ ከጻፈች በኋላ የእምነትና የምግባር አዕማድን ስትተነትን እግዚአብሔር ሰዎች ከእርሱ ጋር ለማድረግ ከሚፈልጉት ግላዊ ግንኙነት/መስተጋብር ሊታወቅ እንደማይችል ዐልፎ ዐልፎ ትገልጽ ነበር። "አላህ" እና "ሰው" በሚሉት ቃላት መካከል የአንድ ኢንች ያህል ውፍረት አግድም በማስመር የሱኒ እምነቷ የሚያስተምረውን ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት ያለመቻልን ነገረ መለኮት አበክራ ታስረዳ ነበር። ንግግሯን የቋጨችው እርሷ በግሏ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ለመገዛት ራሷን የሰጠች ሰው ብትሆንም፣ እግዚአብሔርን በግሏ ለማወቅ ድፍረት እንዳልሆናችት በመግለጽ ነው።

ሱፊ ተማልሶታዊነት

የሱፊ ተማልሶታውያን (mysticism) ለእግዚአብሔር በመገዛት ላይ ትኩረት ከሚያደርግ ሆኖም ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረትን ማድረግ እንደማይቻል ከሚያስተምረው ቀጥተኛ መንፈሳዊነት በተለየ መንገድ ነው እምነታቸውን የሚያራምዱት። ሱፊዎች ከእግዚአብሔር ጋር በረቀቀ መንገድ የሚያገናኛቸውን ሥልጣን ይናፍቁታል፤ ይፈልጉታልም። የሱፊዎች እግዚአብሔርን የሚፈልጉበት አትጣጫ በክርስቲያኖች ነገረ መለኮት ግዕከል እንደ ሆነው፣ "እኔና-አንተ" በሚለው ግንኙነት አይደለም። ይልቁንም ሱፊዎች በመለኮት (ፋና) ውስጥ በመሆን የራሳቸውን ማንነት መጥፋት/ማደብዘዝ ይፈልጋሉ። አርቶዶክስ ሙስሊሞች በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ምንም ግንኙነት የለም በሚለው በቁርአናዊ አስተምህሮ በታንዚል ላይ ትኩረት ያደርጋሉ። ሆኖም ሱፊዎች በቁርአን ውስጥ አንዳንድ ሰዎች የእግዚአብሔር በልጆሮች (አወልያ) እንደ ነበሩ አመልክተዋል።

አብርሃም ካሊለ አላህ (የእግዚአብሔር የቅርብ ወዳጅ) ነበሩ። ስለዚህ ሱፊዎች ለእግዚአብሔር መገዛትን ከእግዚአብሔር ጋር ወዳጅነታቸውን የሚያሳድግላቸው እንዲሁም ከመለኮት ጋር የረቀቀ ግንኙነት መኖሩን መረዳት ይፈልጋሉ (ማይዳ 5+53-54፣ ዩኑስ 10+62)።

አምላኪዎቹ ከእግዚአብሔር ጋር ጎብረት እንዴት ሊያደርጉ ይችላሉ? የሱፊ መንፈሳዊነት ትኩረት የሚሰጥባቸው ብዙ ጭብጥ መልእክቶች አሉት። በዚህ አጭር ክፍል እነዚህን መንፈሳዊ መንገዶች ለመመርመር አይቻልም። ቤተሰቦቻችን ለረዥም ዓመታት በናይሮቢ ኢስሊ በሚገኘው መስጊድ መገገድ ማዶ ኖረዋል። ስለዚህ ስለዚህ ማኅበረሰብ የምለው ነገር አለኝ። እነርሱም አራት ናቸው ይሸውም፦— መንፈሳዊ መሪ፣ ከማኅበረሰቡ አንደ አማላጅ ሆኖ የሚያገለግል ጸዲቅ የሥርዐቱ መሥራች፣ እግዚአብሔርና ጸድቃንን ማስታወስና አምላኪዎችን ምስጢራዊ በሆነ መንገድ ከመለኮት ጋር ጎብረት በሚፈጥርላቸውን የማኅበረሰቡን ምስጢር መካፈል። በሁሉም የሙስሊም ማኅበረሰብ ግለትም ኡማ የሱፊ እንትስቃሴ አለ፣ እነዚህ ሱፊ ማኅበረሰቦች ታሪቃስ (መንገዶች ወይም ሥርዐቶች) በመባል ይታወቃሉ።

ስፔንሰር ትሪሚንግሃም እንዲህ ሲል ጽፎአል፦—

> የእስልምና ሃይማኖት ሥርዐት መሠረት ከእግዚአብሔር ጋር መተሳሰርን (ጎብረት ማድረግን) የሚፈልግ አማኝ በዚህ መንገድ ልምምድ ካለውና ልዩ በሆነ በረከት (በረካ) የተባረከን ሰው ምሪትና በአማኞች እና በእግዚአብሔር መካከል የመግለድን ተግባር የሚፈጽም ሰው ያስፈልጋል። የታሪቃን መሥራች የነበሩት እንደዚህ ያገለገሉ እና መንፈሳዊ ዘሮቻቸው ይህን ባርኮት (በረካ) በመውረስ አገልግሎታቸው እስከዚህ ቀን ድረስ የቀጠሉ ናቸው[5]።

በኢስቢ የማኅበረሰብ ውስጥ የሚገኙት የሱፊ መንፈሳዊ መሪዎች፣ የማዕረጋቸውን ምልክት በቀደሪያ ሥርዐት ውስጥ ይቀበላሉ። ማኅበረሰቡም ይህንን በረከትና ሥልጣን ያገኘው ከቅዱሳን ጋር ካለው የቀረበ ግንኙነት እንዲሁም የሥርዐቱ መሥራች ከሆኑት ከአብዱል ቃዲር አል ጂላኒ በቀጥታ መንፈሳዊ ሥልጣንና ጎይል በመማር ነው። መሥራች አባላት ይህንን ብልጎት የተቀበሉት በነቢዩ መሐመድ መስመር መንፈሳዊ ሥልጣን ከነበራቸው የጎይል ሰዎች ነው። ሱፊዎች ይህንን የሥልጣንና የበረከት መስመር በቀጥታ

[5] J. Spencer Trimingham, *Islam in Ethiopia* (New York: Barnes and Noble, 1965), 232.

የመንደሩን ቅዱሳን በጎይል፣ በበረከትና በምሥጢራዊ መንገድ ከመሥራች መሪዎች ጋር የሚያገናኝ ሰንሰለት ነው።

የቃደሪያ ሼክ ተከታዮች በናይሮቢ ኢስሊ ሁል ጊዜ ሐሙስ ማታ ከመሪያቸው ጋር በመስጊድ ይገናኛሉ። በሌላ ጊዜ በሼኪው ቤት ይገናኛሉ። ይህ ግንኙነት ሁል ጊዜ መንፈስን ሙሉ በሙሉ በማስገዛት የእግዚአብሔርን ስም ደጋግሞ መጥራትን ያካተተ ነው። እርሱም እግዚአብሔርን ማስታወስ (ዲክር) ይባላል። የመሐመድንና የሥርዐቱን መሥራቾችንም ስም በመደጋገም ይጠራሉ። ይህንን የሙገሳ ንግግር የሚያደርጉት አንዳንዴ ሻይ ለመጠጣትና መነቃቃት የሚፈጥረውን ጫት ለመቃም በርጋታ ቀጭ ብለው ነው። የምልክት ጨርቆችን ያውለበልባሉ ዕጣን ያጨሳሉ። የአምልኮው ግብ የግንኙትን ስሜት ለመግደልና ወደ ሁልዐቀፍነት ለመዋጥ ነው።

የአማላጅ አስፈላጊነት

አንድ ጊዜ ከጓደኞዬ ከፋራ ዓሊ ጋር በመሆን በየዓመቱ ወደ መቃብር ስፍራ የሚሄድበትን ሃይማኖታዊ ጉዞ አብረን ተጓዝን። ሁሉም የሱማሌ ጉዟዎች የሱፊ ቅዱሳን ናቸው። በየዓመቱ ወደ መቃብር ስፍራ የሚደረገው ሃይማኖታዊ ጉዞ የጉዟዎች ጎብረት የሚታደስበት እንዲሁም የሞቱ ጻድቃንን ጎይል ምስጢራዊ በሆነ መንገድ የሚከፈሉበት መንፈሳዊ ክብረ በዓል ነው። የሃይማኖት ተጓዦቹ እየሮሁ (እያለቀሱ) እየጸለዩ እና ከመቃብሩ ላይ ዐፈር በእጆቻቸው በመውሰድ ሰውነታቸው ላይ እየበተኑ ነበር ወደ መካነ መቃብሩ የተጓዙት።

ወደ ቤት ጉዞ እንደ ጀመርን፣ ፋራ እንዲህ አለ፣ "እኛ ኀጢአተኞች ስለሆንን እግዚአብሔር ጸሎታችንን አይሰማም። ከእኛ እንደ አንዱ በመሆኑ ምክንያት ነው ወደ ሱፊ ቅዱስ መቃብር የሄድነው። እርሱ ጸሎታችንን ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሰውን መሐመድን ይግልድልናል። እናውቃለን ይህ መልካም የሚባለው እስልምና አይደለም፣ ምክንቱም በእስልምና ምንም አማላጅ የለም ሆኖም ሌላ አማራጭ መንገድ የለንም"።

እኔም በበኩሌ እንዲህ አልሁ፣ "ጭንቀታችሁ ይገባኛል። ነገር ግን እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ሁሉ የመደበው አንድ አማላጅ አለ። እርሱም መሲሑ ነው። መሲሑ አማላጃችን እንዲሆን እግዚአብሔር ሾሞታል"።

"አስገራሚ ነው፣ እስኪ ስለዚህ ነገር በደንብ ንገረኝ" አለ ፋራ::

ፋራ የሱፊ እምነቱ ሙሉ ለሙሉ ምኞት አልሰጠውም:: ለዚህ ምክንያቱ የዋነኞች የሱኒ ሙስሊሞች የሱፊን እምነት እምብዛም ስለማይቀበሉ ነው:: ሱፊዝም ለእርሱ በጣም ወሳኝ ትርጉም ያለው እምነት ቢሆንም፣ እርሱና ብዙ ሙስሊሞች ከእስልምና እምነት ጋር የሚቃረን እንደ ሆነ ይሰማቸዋል::

በሌላ ጊዜ አንድ ባልንጀራዬ በጃቫ ከተማ ወደ አንድ ሱፊ ቅዱስ መቃብር ወሰደኝ:: እናም የመቃብሩን ታምርና የመግለድ ኀይል በብዙ መቶዎችና ሺዎች የሚቈጠሩ የሃይማኖት ተጓዦች ወደዚህ መቃብር ስፍራ በመምጣት እንደሚያከብሩት አብራራልኝ::

"ይህ በእስልምና እምነት ተቀባይነት ያለው ነውን?" ብዬ ጠየቅሁ::

ባልንጀራዬም፣ "ይህንን ጥያቄ አትጠይቅ ሁላችንም ይህ ትክክለኛ ሙስሊም መከተል የሌለበት እንደ ሆነ እናውቃለን" አለኝ:: ሆኖም ስለ ሱፊዎች ከተወሰነው ተቃርኖ ባሻገር የሱፊዎች እምነት ለሱኒ ሙስሊሞች ሕይወት የሚለግስ ነው:: ሱፊዝም ከፈጣሪ ጋር ለመገናኘት ላለው ፍላጐት መልስ ነው::

በአራተኛው ክፍለ ዘመን ይኖር የነበረው ሰሜን አፍሪካዊው ክርስቲያንና የነገረ መለኮት ምሁር አውግስጢኖስ፣ ልባችን በእግዚአብሔር እስኪያርፍ ድረስ ዕረፍትን ፈላጊ መሆኑን በመገንዘቡ እንዲህ ሲል ይጸልያል:— "አምላኬ ሆይ፤ እንዴት ላይህ እችላለሁ? አንተን አምላኬን ስመለከትህ የተባረከውን የሕይወት ደስታን እመለከታለሁ:: በሕይወት እንድኖር አንተን መመልከት አለብኝ"[6] ይህ የሱፊዎች እንቅስቃሴም ደስታንና ዕረፍትን ፍለጋ ላይ መሆናቸውን የሚያስረግጥ ነው::

መሲሑና የሱፊዎች እውነት ፍለጋ

ሱፊዎች ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት የሚያደርጉት ፍለጋ በመሲሑ በኩል በሆነ አስገራሚ ስጦታ ተፈጽሟል:: መሲሑ በእግዚአብሔር የተሾመ አማላጅ ነው:: በእርሱ ሕይወትና አገልግሎት ሁላችን ቤተሰቦች፣ ጓደኞች ወንድና

[6] Saint Augustine, *Confessions*, translated by R. S. Pine-Coffin (Baltimore: Penquin, 1961), 226.

ሴቶች ልጆች ለመሆን ተጋብዘናል:: ይህ ግንኙነት ሰብአውነትን የሚደመስስ ሳይሆን፣ ከእግዚአብሔር ጋር፣ "በእኔና-አንተ" ዐይነት የቅርበት ግንኙነት ላይ የተመሠረተና ጎብረትን የሚያረጋግጥ ነው:: መንፈስ ቅዱስ አማኞችን በእግዚአብሔር መኖርና (መገኘት) እንዲሁም ጎይል ይሞላቸዋል:: የውስጥ መለወጥ እንዲያገኙና አዲስ ፍጥረት እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል:: ይህ ሁሉ የሚሆነው በእምነት በተሳሰሩ ማኅበረሰቦች ውስጥ እንጂ፣ በማይታዩ ምስጢራዊ መንፈሳዊ መሪዎች አይደለም:: ሆኖም አንድ በሚያደርገውና በሚያስተሳስረው መንፈስ ነው::

የሱፊ መንፈሳዊ መስመር የሙስሊም ማኅበረሰብ አባላት ለሚሰማቸው መንፈሳዊ ፍላጐት መልስ ሰጥቶአል:: የቤተ ክርስቲያን ምስክርነት በመሲሑና በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ይህ መንፈሳዊ ፍላጐት (ጥማት) በሰውየው ፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ነው:: ወንጌል የጠራን ከእግዚአብሔር ጋር ጎብረት እንድናደርግ እንጂ ትርጉም የለሽ መንፈሳዊ ተመስጠ ውስጥ እንድንገባ አይደለም::

አብርሃምና እምነት

ምንም እንኳን የሱፊዎች እምነት (መንገድ) ተከታዮችን ለተግባሉ ቅድስና ቢጋብዝም፣ ለሁሉም እስልምና ሰላት መገዛትንም አይቃወሙም፤ ማንኛውም ትክክለኛ የሱፊም ሆነ የኦርቶዶክስ ሺይትም ሆነ ሱኒ እስላም በሸሪአ እንደ ተደነገገው መተግበር አለበት:: በ2000 በበልግ ላይ የእንግሊዝ ሙስሊም ተማሪዎች ማኅበር ላይ እንግዳ ተናጋሪ ሆኜ በተጠራሁበት ወቅት በአየሁት እውነት ተደንቄ ነበር:: እነዚህ ሙስሊም ተማሪዎች ዓለማዊ በሆነና ጥድፊያ በነገሠበት ማኅበረሰብ ውስጥ ቢኖሩም እንኳ፣ የሰላት ሰዓታቸው በምንም መልኩ እንዲሰረቅባቸው አይፈቅዱም ነበር::

በአንድ ምሽት ከተማሪዎቹ ጋር በነበረኝ ውይይት የውይይታችን ርእሰ ጒዳይ የነበረው አብርሃም ነበር:: የመልእክቱም ፍሬ ሐሳብ፣ "አብርሃም በእግዚአብሔር አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት" (ዘፍጥረት 15÷6) የሚለው ነበር:: ለአብርሃም በእግዚአብሔር ማመን አዳጋች ነበር:: አብርሃም በአንዳንድ የእምነት ፈተናዎች ደክሞ ነበር፣ መንገድ ስቶ በጎጢአት ወድቋል:: ይህም ሆኖ በእምነት መሆንን መርጦአል:: በማመኑም እግዚአብሔር ታማኝ ጓደኛው እንደ ሆነ ተምሮአል:: የአብርሃም በእምነት መጓዝ አስደናቂ ጸጋን በሕይወቱ ከፍቶለታል:: እርሱ የተጓዘበት እምነት ቀድሞ የተገለጠ እኛ ዛሬ በመሲሑ በኢየሱስ ሕይወትና አገልግሎት የተጠራንበት ጸጋና እምነት ነው:: የጓንነው

በጸጋው ነው፤ እምነት እንኳ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው፤ ዮኀጢአታችንን ይቅርታ ያገኘነውና እግዚአብሔር የሚወደን የሰማይ አባታችን መሆኑን ያወቅነው በጸጋው ነው። በራሳችን ይህንን ሞገስ ማግኘት አንችልም። ይህ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው።

የሙስሊም ጓደኛዬ አብርሃም ዛሬ የሚገኙት ሙስሊሞች በማንባራቸው ወደ መሬት ተደፍተው እንደሚሰግዱት ይሰግድ እንደ ነበር እግዚአብሔርንም ያህዌ ብሎ ሳይሆን አላህ በማለት በእውነተኛ ስሙ ይጠራው እንደ ነበር ተናገረ። አብርሃምና ኢስማኤል በካዕባ ያሉትን ጣዖታት አስወግደው የእስልምናን እምነት መሥርተዋል። የእግዚአብሔርን ቤት በካዕባ በማደስ እግዚአብሔርን በትክክለኛ መልኩ (መንገድ) አምልከዋል። ጓደኛዬ ብቸኛ የጸሎት መንገድ የሆነውን በግምባር ወደ መሬት መደፋትን አብርሃምን እንደ ምሳሌ ይከተሉ ዘንድ ውይይቱን ያደምጡ የነበሩ ክርስቲያኖች ሁሉ እንዲያደርጉት ጥሪ አቀረበ። እግዚአብሔርንም በእውነተኛ ስሙ አላህ ብለው እንዲጠሩት ጠየቀ። አብርሃም የእምነት አባት የሆነው ፊቱን ወደ ካዕባ በመመለስ በግንባሩ በእግዚአብሔር ፊት እንደ ወደቀ በማወቅ ማንም ሰው በጸሎት ፊቱን ወደ ካዕባ፣ ወደ እግዚአብሔር በማዞር መጸለይ አለበት።

የአብርሃም የእምነት አባትነት ተልእኮው ብርቱ ውይይት የሚጠይቅ መሆኑ ግልጽ ነው። እምነት ምንድን ነው? ለእግዚአብሔር መገዛት ምንድን ነው? እውነተኛ አምልኮ ምንድን ነው? ለእግዚአብሔር የምንሠራውስ ሥራ ነው? ትክክለኛ የአምልኮ ተግባራት የእግዚአብሔርን ምሕረት ያስገኝልናል ወይ? ወይስ እግዚአብሔር ላደረገልን የምንሰጠው ክብርና በደስታ የእግዚአብሔርን ጸጋ ማክበራችን ነው?

የአምልኮ ትርጉም

በሶማሊያ እኖር በነበረበት ጊዜ በመሲሑ በሚያምኑ አማኞች ጎብረት ላይ የአምልኮን ትርጉም አስመልክቶ ተከታታይ ውይይት ተካሂዶ ነበር። የአሜሪካ ሜኖናይት ሚስዮናውያንና የሶማሊያ ክርስቲያኖች በጋራ በመሲሑ ኢየሱስ የተገለጠውን አምልኮ ላይ ጥናት አድርገዋል። አንዳንድ ጊዜ ሙስሊሞች የሚሰጡት አስተያየት ክርስቲያኖች ጎብረት ለማድረግ ሲሰበሰቡ መዝሙራቸው ግብዣ ያለባቸው ያስመሰላቸዋል በማለት ነው። ይህ አስተያየት እውነት ነው። በመሲሑ ለተሰጠን ጸጋ እግዚአብሔርን በግብዣ እያከበርነው ነው፤ ትኩረት የሰጠነው የክርስቲያን አምልኮ ዋና ፍሬ ነገርና በሶማሊያ ሙስሊሞች ዐውድ ለሙስሊሙ ማኅበረሰብና በአማኞች ጎብረት ላይ ትርጉም

ያለው ተግባበት ሊፈጥር የሚችል ተምሳሌት ላይ ነበር። ከውይይቱ የተገኙት አስተያየቶች የሚከተሉት ናቸው።

የእሑዱ አምልኮ በሱማሊያ እየተፈጠረች ላለችው ትንሽ ጉባኤ በእሑድ ከሚያመልከው የዓለም ዐቀፍ ጉባኤ ጋር የሚያገናኛት ነው። ለአምልኮ የተለየ ስፍራ መኖሩ አስፈላጊ ነው። ይህ ስፍራ የእግዚአብሔርን ቅድስና እንድናስብ ያደርገናል። ወደ ውስጥም ስንገባ ቅዱሱን ለመገናኘት እንደምንገባ በመቍጠር ጫማችንን ማውለቅ አለብን። ጉባኤውን የሚመሩት መሪዎች አለባበሳቸው እንደ ካህናት ቢሆን መልካም ነው። እንደ ኢማሞች በማኅበረሰቡ መኻል መሪነታቸውን የሚያመለክት አለባበስ ቢለብሱ ጥሩ ነው። በመደበኛ አምልኮ ጊዜ የሐዋርያትን የሃይማኖት መግለጫ እንዲሁም የጌታችንን "አባታችን ሆይ ጸሎት" ማድረስ አስፈላጊ ነው። የአባታችንን ጸሎት እንደ ምስጢራዊ ጸሎት ምልክት መድገም ቢቻል መልካም ነው። መደበኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ በስብሰባ ወቅት ሁሉ ማንበብ ያስፈልጋል።

ጥምቀት ሰውየው ወደ አዲስ የቃል ኪዳን ማኅበረሰብ መግባቱ ምስክር ነው። የጌታ ራት (ቅዱስ ቁርባን) መሲሑ የእግዚአብሔር በግ እኛን ለመቤዠት የከፈለውን መሥዋዕትነት ለማክበር በመደበኛ ሁኔታ መወሰድ (መከበር) አለበት። ሁል ጊዜ የሚደረግ ዮኀጢአት ኑዛዜ፣ በአምልኮ ጊዜ ውስጥ ማካተት ያስፈልጋል። መሱሑ የሐዋርያትን እግር የማጠቡን ምሳሌ በመከተል በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የእግር መታጠብ ሥርዐት ማበጀት ያስፈልጋል። እግር ማጠብ ክሱማሌ ባህል ተጻራሪ ነው። ሆኖም መሲሑ የመጣው ኩሩዎችን አገልጋይ ሊያደርግ መሆኑ መታወስ አለበት።

አማኞች በማንባራቸው ወደ ምድር መደፋት ሳይሆን መቆም ነው ያለባቸው። ባሮች በማንባራቸው ይደፋሉ። በመሲሑ የሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ሴቶችና ወንዶች ልጆች ሆነዋል። ስለዚህ ልጆች ከአባታቸው ጋር ቆመው ነው የሚያወሩት እንጂ በማንባራቸው ተደፍተው አይደለም። በተጨማሪም በማንባር መደፋት በእስልምና ወደ ከአባ አቅጣጫ መዞርን ይፈልጋል። ሆኖም መሲሑ ጌታችን ተነሥቶአል። በመንፈሱ በመካከላችን እንዲሁም ከእኛ ጋር ስለሆነ፣ አቅጣጫን በመወሰን በማንባር የመውድቅበት ምንም ዐይነት አቅጣጫ አይኖርም። ክርስቲያኖች ጌታቸውን ፊት ለፊት መገናኘት በመቆም መጸለይን እንደ ምልክት አድርገው መጠቀም አለባቸው። ሥርዐተ አምልኮ በሚካሄድበት ጊዜ ሁሉ ለእግዚአብሔር ዝማሬ ማኅሌት መቅረብ አለበት። የሶማሌ አጫጭር ዝማሬዎችና የአካባቢው ሙዚቃና የአነጋገር ዘይቤ ቢጻፍ አምልኮውን ያበለጽገዋል።

እውነትና መንፈስ

የዚህ ዐይነት ውይይቶች በተለያዩ ጊዚያት ይካሄዱ ነበር። ሆኖም የአምልኮን ትርጉም ለማጥናት ለብዙ ወራት በየቅዳሜው አንድ ቡድን ይሰበሰብ ነበር። ቡድኑ ኢየሱስ በሲካር በያዕቆብ ጕድጓድ አጠገብ ከሳምራዊቷ ሴት ጋር ያደረገውን ንግግር ያጠኑ ነበር (ዮሐንስ 4÷1-26)። ሴቲቱ ለአምልኮ ትክክለኛ ስፍራና መንገድ መኖሩን በማሰብ አይሁዶች በኢየሩሳሌም ሰገዱ/አመለኩ እኛ ሳምራውያን ደግሞ በተራራ አመለከን (ሰገድን) አለች። ኢየሱስ መልሶ፦—

> አንቺ ሴት እመኚኝ በዚህ ተራራ ወይም በኢየሩሳሌም ለአብ የማትሰግዱበት ጊዜ ይመጣል። እናንተስ ለማታውቁት ትሰግዳላችሁ እኛ መዳን ከአይሁድ ነውና ለምናውቀው እንሰግዳለን። ነገር ግን በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል። አብ ሊሰግዱለት እንደዚህ ያሉትን ይሻልና እግዚአብሔር መንፈስ ነው። የሚሰግዱለትም በመንፈስ እና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል። (ዮሐንስ 4÷21-24)።

ኢየሱስ ከሳምራዊቷ ሴት ጋር ባደረገው ንግግር፣ "መዳን ከአይሁድ" እንደ ሆነ አስረግጦ ተናግሯል።

በእርግጥ ወንጌልና ቤተ ክርስቲያን ከእስራኤል ታሪክና ቅዱሳት መጻሕፍት ሊነጠሉ ትርጕመቢስ ይሆናሉ። ቤተ ክርስቲያን የቆመችው በመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣናዊ ቃል ነው። ቤተ ክርስቲያን የብሉይ ኪዳኑ የቃል ኪዳኑ ሕዝብ ቀጣይ ነው። መሲሑ የቀድሞውን ሕግ ፈጸመው እንጂ አልሻረውም። ቤተ ክርስቲያን ተወልዳ ያደገችው በመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት ሲሆን፣ ቃላቱም መተርጕምና መተግበር ያለበት በቤተ ክርስቲያን ነው። መጽሐፍ ቅዱስና ቤተ ክርስቲያን ተደጋጋፊዎች ናቸው።

በዚያ በሱማሊያ ስብሰባ ወቅት፣ "በመንፈስና በእውነት" የሚለውን አምልኮ ትርጕም አጥብቄን አስበንበታል። ስፍራን በተመለከተ አምልኮተ እግዚአብሔር ለማካሄድ፣ የሰማርያ ተራራም ሆነ የአይሁዶች መቅደስ አስፈላጊ አይደለም። ኢየሱስ ፊታችሁን ወደ ካሰብም መልሱ አላለም። የመልካም አምልኮ መሠረቱ በእውነትና በመንፈስ ማምለክ ነው። የተሰወረ ኀጢአት ሊኖር አይገባም። አምልኮ የላቀ ታማኝነትን ይጠይቃል። ስለዚህ እውነተኛ አምልኮ ኮነጢአት ኑዛዜን ያካትታል። መንፈስ መገኘትንና ኀብረትን ያመለክታል። እኛ እግዚአብሔርን እናውቀዋለን፣ እግዚአብሔርንም እኛን ያውቀናል፣ በአምልኮም ከእግዚአብሔር ጋር ኀብረትን እናደርጋለን።

ሳምራዊቷ ሴት ይህ ሁሉ የሚሆነው፣ "መሲሑ ሲመጣ ሁሉን ይነግረናል" በለችው መሠረት ነው። ኢየሱስም፣ "የምናገርሽ እኔ እርሱ ነኝ" ብሎ አስደነቃት (ዮሐንስ 4÷25-26)።

ሁለት ጸሎቶች

ይህንን ክፍል የምንደመድመው በሁለቱ ጸሎቶች ነው። የእስልምና ፋትያ፣ ታማኝ ሙስሊሞች በቀን ዐሥራ ሰባት ጊዜ የሚደግሙት እንዲሁም ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ባስተማረው፣ "በአባታችን ጸሎት" ነው። እነዚህ ሁለት ጸሎቶች ጠንካራ የአምልኮ ማዕከል ናቸው (በእግዚአብሔር ፈቃድ መገዛት የሚገኝ ሰላም እንዲሁም በክርስቲያኑ ማኅበረሰብ የአምልኮ ልክ ነው--እግዚአብሔርን እንደ ሰማይ አባት በማወቅ የሚገኝ ደስታ)።

ፋትያ

> በአላህ ስም በጣም ርኅሩኅ በጣም አዛኝ በኾነው።
> ምስጋና ለአላህ ይግባው የዓለማት ጌታ ለሆነው፣
> እጅግ በጣም ርኅሩኅ በጣም አዛኝ፣
> የፍርድ ቀን ባለቤት ለኾነው።
> አንተን ብቻ እንገዛለን አንተንም ብቻ ርዳታህን እንለምናለን።
> ቀጥተኛውን መንገድ ምራን።
> የነዚያን በነርሱ ላይ በጐ የዋልክላቸውን በነሱ ላይ
> ያልተቆጣህባቸውንና ያልተሳሳቱትንም ሰዎች መንገድ
> (ምራን በሉ)። (አል-ፋቲሐህ 1÷17)

የአባቶቻችን ጸሎት

> በሰማያት የምትኖር አባታችን ሆይ ስምህ ይቀደስ መንግሥትህ ትምጣ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንደሁ በምድር ትሁን የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን። እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን። ከክፉም አድነን እንጂ ወደ ፈተናም አታግባን መንግሥት ያንተናትና ኀይልም ክብርም ለዘላለሙ አሜን።
>
> (ማቴዎስ 6÷6-13)

የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ

ማቴዎስ 6÷9-13

የቁርአን ምንባብ

ሱራ 1÷1-7

<u>የአስተውሎትና የውይይት ጥያቄዎች</u>

1. በእስልምና የሰላት ትርጉሙም ነው? በክርስቲያኑ ልምምድ የአምልኮ ትርጉም ምንድን ነው? በሥርዐታዊ አምልኮ ውስጥ ያለው ዋጋ ምንድን ነው?
2. ፋቲያን ከአባታችን ጸሎት ጋር ያነጻጽሩ። ክርስቲያኖች ፋቲያን መጸለይ ይችላሉ። ሆኖም ሙስሊሞች የአባታችንን ጸሎት መጸለይ አይችሉም። በእነዚህ ነጥቦች ላይ ሐሳብ ይስጡ።
3. በሱፊዎችና በክርስቲያኖች መካከል ስለ፣ "አማላጅ" የሚደረገውን ውይይት ልብ ይበሉ። የዕብራውያን መጽሐፍ መሲሑን እንደ ካህንና እንደ አማላጅ የሚያቀርበው (ዮሐንስዕብራውያን 7÷1-8÷6፤ ሱራ 20÷109፤ ሱራ 6÷51:70)፣ ሱፊዎች አማላጅ የመፈለግ ጉዳይ ትርጉም በሚሰጥና በእነርሱም መረዳት ነው። በዚህ ሐሳብ ላይ አስተያየትዎን ይስጡ።
4. አራት የተለያየ የአምልኮ ልምምድ ያላቸውን ውስጣዊ ትርጉም ይተቹ፡— (1) በቀን ውስጥ በሚሰገዱ ሰላቶች ውስጥ የሚካሄዱ ዐሥራ ሰባት ረካዎች (ጉንበስ ቀና ማለት)። (2) በሱፊ ስብሰባዎች ላይ የእግዚአብሔርንና የሥርዐቱ መሥራች ቅዱስ ስሞች በተደጋጋሚ መጥራት። (3) የአሁድ አምልኮ በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን። (4) የአሑድ አምልኮ ባህላዊ ፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን
5. እግዚአብሔርን በእውነትና በመንፈስ ማምለክ ማለት ምን ማለት ነው (ዮሐንስ 4÷21-25)?
6. የሱፊዎች ፍለጋ፡— በሙስሊሙ ልምምድ ወደ ሁልአቀፍነት በመዋጥ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ነው። የመሲሑ ሕይወትና አገልግሎት እንዲሁም የመንፈስ ቅዱስ ሥራና መገኘት ሰው እግዚአብሔርን እንዲያውቅ ስጦታን መስጠት ነው። እነዚህን ሁለት የተለያዩ ዐይነት መንፈሳዊነት ልብ በል። በሙስሊሞች መኻል ያለው የሱፊ እንቅስቃሴ ሙስሊሞች የክርስቲያኑን ወንጌል መረዳት እንዲችሉ ድልድይ መሆን ይችል ይሆን? በዚህ ሐሳብ ላይ አስተያየት ይስጡበት።

ምድራዊ ተልእኮ
ኡማ—ቤተ ክርስቲያን

በምድር ላይ ከሚኖረው ሕዝብ መካከል ግማሹ ሙስሊም አልያም ክርስቲያን ነው። ይህ እውነት የሁለቱም ወገን ያሉት ዓለም ዐቀፍ ማኅበረሰቦች ማለትም የሙስሊሙ ኡማና ቤተ ክርስቲያን እምነታቸውን ለማስፋፋት ያላቸውን ትልቅ ትጋት በጉልሕ የሚያሳይ ነው።

ሚስዮናዊ በሆነው እንቅስቃሴ ውስጥ፣ ኡማውና ቤተ ክርስቲያን እርስ በርስ እየተፎካከሩ ናቸው። በመቅድሙ ላይ ለማብራራት እንደ ሞከርሁት፣ ከጥቂት ዓመታት በፊት በድሩ ዲ. ቀትራጋና እኔ በተዋስኦ (በውይይት) መልክ ያዘጋጀነው መጽሐፍ፣ በድሩ የሙስሊሙን ማኅበረሰብ እኔ ደግሞ የክርስቲያኖችን እማኝነት በመወከል የቀረበ ውይይት ነበር።

በድሩ፣ ለሙስሊሙ ማኅበረሰብ ንግግር ለማድረግ በተዘዋወረባቸው ዓለም ዐቀፋዊ ጉዞዎች ላይ ሁሉ፣ ይህ እኔና እርሱ የጻፍነውን መጽሐፍ ወደ ላይ ከፍ በማድረግ፣ ለጉባኤው ታዳሚ የሚከተለውን ቁም ነገር እንደ ነገራቸው አጫውቶኛል፡—

> ዴቪድ ቬንክ በሉቲኒያ ክርስቲያን ዩኒቨርስቲ ሲያጠቃልም ነው የቀየው። እኔ ደግሞ በዩጋንዳ ሙስሊም ዩኒቨርስቲ ሳቋቁም ቀይሮለሁ። እኔ ለእስልምና እምነት ምስክር በመሆኔ በእንጻፋ ደግሞ እርሱ ለቤተ ክርስቲያን ተልእኮ የተሰጠ ሰው በመሆኑ ሁለታችንም ቱክክር ላይ እንዳለን እናውቃለን። ጻፉ ግን እኔና ዴቪድ ጥሩ ባልንጀሮች ነን። እርስ በእርስ ያለን ቀረቤታ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች ሁሉ ሊኖራቸው ስለሚገባው ግንኙነት ተምሳሌት መሆን የሚችል ነው።

ሚስዮናዊ የሆኑ ማኅበረሰቦች

የሚያሳዝነው ግን አብዛኛውን ጊዜ ሚስዮናዊ በሆኑት በእነዚህ ሁለት ማኅበረሰቦች መካከል ያለው ግንኙነት በድሩ እንዳስቀመጠው፡ የመከባበርና ወንድማማችነት የሰፈነበት አይደለም። ዛሬ በእነዚህ ማኅበረሰቦች ላይ ለተጋረጠው የግንኙነት መሰናክል እንዲሁም ዓለም ዐቀፉ ሚስዮናዊ

እንቅስቃሴ በጥንታዊው የክርስቲያንና የሙስሊም ታሪካዊ እንቅስቃሴ ላይ ዘልቆ የተመሠረተ ነው።

እስልምና እንቅስቃሴውን በጀመረበት በአንድ ክፍለ ዘመን ውስጥ፣ ግማሽ የሚሆነው የክርስቲያኑ ዓለም በእስልምና ሃይማኖት አገዛዝ ሥር ወድቋል። ሙስሊሞች፣ ቀደምት የሆነው ይህ የሙስሊሞች ድል የተቀረው የክርስቲያን ክፍል በአጠቃላይ ሙስሊም እንደሚሆን የሚያመለክት ነው የሚል አቋም አላቸው።

<u>የመስ�ፋት አቅጣጫዎች</u>

ሰዎች ሙስሊም እንዲሆኑ የማያቋርጥ ግፊት ካለባቸው አካባቢዎች በስተቀር፣ ክርስቲያኖች ወደ እስልምና የተቀየሩበት ዓለም ዐቀፍ እንቅስቃሴ የለም። ግለሰቦች ወደ እስልምና ሃይማኖት የሚለወጡበት ሁኔታ ቢኖርም እንኳ፣ ከክርስትና ወደ እስልምና የሚደረግ መጠነ ሰፊ ለውጥ እየተካሄደ ያለው፣ ሙስሊሞች የፖለቲካ የበላይነት ባገኙባቸው አካባቢዎች ብቻ ነው። አስቀድሞ እንዳስተዋልነው በእስልምና አገዛዝ ሥር ጥበቃ የሚደረግላቸው ክርስቲያኖች (ዚሚ) ቤተ ክርስቲያንን ለመጠበቅ ያለው ስምምነት ክርስቲያኖች ሙስሊም እንዲሆኑ ጫና የሚያደርግና እስልምናን እንዲቀበሉ የሚገፋፋ ነው። በእስልምና አገዛዝ ሥር ባሉ ክልሎች የምትገኝ ቤተ ክርስቲያን የአባሉጅ ቁጥር ቀስ በቀስ ይመናመናል። ለዚህ ዋናው ምክንያት፣ እነዚህ ክርስቲያኖች በተለያየ ምክንያት እስልምናን እንዲቀበሉ ጫና ስለሚደረግባቸውና እስልምናን በግድም ሆነ በውድ ስለሚቀበሉ ነው።

ይህ እንዳለ ሆኖ፣ ሁሉም የእስልምና ዕድገት በፖለቲካ ሥልጣን (ጎይል) የተመሠረተ ነው ማለት ግን አይደለም። በቅርብ ዓመታት በአሜሪካን አገር በሺዎች የሚቆጠሩ ክርስቲያናዊ መሠረት ያላቸው አፍሪካ-አሜሪካውያን ከክርስትና ወደ እስልምና ሃይማኖት ተቀይረዋል። ለዚህ እንቅስቃሴ ትልቅ አስተዋፅኦ ያደረገው፣ በአሜሪካ የታየውና እየታየ ያለው የዘረኝነት እንቅስቃሴ ነው። በእርግጥ የኡማ (የሙስሊሙ ማኅበረሰብ) ተልእኮ ለክርስቲያኑ ማኅበረሰብ ብቻ አይደለም። ሙስሊሞች ሃይማኖታቸውን የሚሰብኩት ለየትኛውም ሕዝብና በማንኛውም ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ላሉ ሰዎች ነው። ሙስሊም ነጋዴዎችና የሃይማኖቱ ሰባኪዎች እስልምናን፣ ክርስቲያን ወዳልሆነው ወደ እስያና አፍሪካ በማሠራጨት ረገድ ውጤታማ የሆኑት የፖለቲካ ጎይል በሌለበት ሁኔታ ነው።

ዕድሉን ባገኙባቸው ሁኔታዎች ሁሉ ግን፣ ሙስሊሞች የእስልምናውን ማኅበረሰብ (ኡማ) ተልእኮ ከዳር ለማድረስ የፖለቲካን ሥልጣን መሻታቸው አልቀረም። ይህም ዐልፎ ዐልፎ ወደ ጂሃዳዊ (ቅዱስ የሃይማኖት ጦርነት) ወደ ሆነ ወታደራዊ መስፋፋት (ጃር ለል-ሊስላም) ሲመሰጻቸው ታይቶአል። በዐሥራ ስምንተኛውና በዐሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን የተካሄደው የምዕራብ አፍሪካው የጂሃድ እንቅስቃሴ ወታደራዊ ጎይልና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ሰፊ በሆነው ከሰሐራ በታች በሚገኘው ምዕራብ አፍሪካ ክልል ተስፋፍቶአል[1]። በእነዚህ አካባቢዎች በቅርቡ ቤተ ክርስቲያንም ሰፊ ዕድገት አሳይታለች። ለምሳሌ በሰባተኛውና በስምንተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሙስሊሞች ሰሜን አፍሪካን ከተቆጣጠሩ በኋላ በ1975 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ በአፍሪካ የሙስሊሙና የክርስቲያኑ ቁጥር እኩል ሆኖአል። ከ25 ዓመት በኋላ ግን ከሙስሊሞች ቁጥር በላይ ሃምሳ አምስት ሚሊዮን ተጨማሪ ክርስቲያኖች ነበሩ (380 ሚሊዮን አፍሪካውያን የሆኑ ክርስቲያኖችና 325 ሚሊዮን አፍሪካዊ ሙስሊሞች)። በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን መግቢያ ላይ በአፍሪካ የሚገኘው የክርስቲያኖች ዓመታዊ ዕድገት 10.75 ሚሊዮን ሲሆን፣ የእስላሙ ማኅበረሰብ ደግሞ 8.25 ሚሊዮን ነበር[2]። የአፍሪካ ልምድ ለሙስሊሙና ለክርስቲያኑ እምነት መስፋፋት ዓለም ዐቀፍ ተምሳሌት ነው።

በዓለም ላይ የክርስቲያኖች ቁጥር የሙስሊሞችን ቁጥር በሁለት ዕጥፍ ይበልጣል። በ1900 ዓ.ም 200 ሚሊዮን ሙስሊሞች እንዲሁም 558 ሚሊዮን ክርስቲያኖች ነበሩ። በዚህን ወቅት ክርስትና ብዙ ተከታዮችን አግኝቶአል። የሙስሊሙም ኅብረተሰብ በከፍተኛ ፍጥነት አድጓል[3]። ሆኖም ለሙስሊሙ ማኅበረሰብ ዕድገት ትልቅ ምክንያት የሆነው፣ በርካቶች የእስልምናን ሃይማኖት መቀበላቸው ሳይሆን፣ ሙስሊሞች በርካታ ልጆችን መውለዳቸው ነው። አንዳንድ ሙስሊሞች ዐማፂ ቡድኖችን በማደራጀትና ወታደራዊ ጎይልን በመጠቀም የቤተ ክርስቲያንን ዕድገት ለማደናቀፍ ከፍተኛ የሆነ ሙከራ ያደርጋሉ። በደቡብ ሱዳን እንደሚደረገው ዐይነት ማለት ነው።

---

[1] John Alembillah Azumah, *The Legacy of Arab-Islam in Africa* (Oxford: Oneworld Publications, 2001), 63-69.

[2] Patrick Johnstone and Jason Mandryk, *Operation World: When we Pray God Works* (Waynesboro, Ga.: Paternoster Publishing, 2001), 18-21.

[3] David B. Barrett and Todd M. Johnson, "Annual Statistical Table on global Mision," *International Bulletin* 25:1 (January 2002), 25.

የሙስሊሞች ተልእኮ

የሙስሊሞች ተልእኮ ሁለት ገጽ ያለው ነው። ይኸውም ጸዋ እና ጸዋላ ናቸው። ጸዋ ምስክርነት እና ጉብኝት ነው። ይህ የሙስሊሞች ተልእኮ የሚገለጠው በቀን 5 ጊዜ በዓለም ላይ ያሉ በመቶ ሺዎች በሚቆጠሩ የጸሎት ግማዎች የጸሎት ጥሪ ሲደረጉ፦—

አላህ እጅግ ታላቅ ነው።
ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ እኔ ምስክርነቴን እሰጣለሁ።
መሐመድ የአላህ መልእክተኛ እንደ ሆኑ ምስክርነቴን እሰጣለሁ።
ወደ ጸሎት ኑ።
መልካም ወደ ሆነው ኑ።
ከእንቅልፍ ጸሎት የተሻለ ነገር ነው።
ወደ ተሻለ ተግባር ኑ።
አላህ እጅግ ታላቅ ነው። አላህ እጅግ ታላቅ ነው።
ከአላህ ሌላ አምላክ የለም[4]።

ይላሉ። በዚህ ተልእኮ ላይ ግዳጅ የለም። በግልጽና በትጎትና የሚደረግ ጥሪ ነው። ይህንን ምስክርነትና ጥሪ የሚሰማ በመምጣት ወይም በሩቅ ለመቀየት መወሰን አለበት።

ጸዋላ ሁለተኛው የእስላምና የተልእኮ ክፍል (ገጽታ) ነው። ይህ የኡማ (የሙስሊም ማኅበረሰብ) ፖለቲካዊ ዕገዛ ግዛታዊ ተልእኮ ነው። በምዕራፍ ዘጠኝ ይህ የእስልምና ፖለቲካዊ ተልእኮ ገጽታ ተብራርቶአል። እርሱም ዳር-አል-ኢስላምን (የእስልምና ግዛት) በአስፈላጊ ቦታና ስፍራ ለመመሥረት የሚደረግ ትጋት ነው። በሐሳብ ደረጃ ዳር አል-ኢስላም ሕዝብ ወደ እስልምና እንዲቀላቀል የሚያስገድድ አይደለም። ጻሩ ግን ፖለቲካዊ እስልምና የኡማው አንድነት መጠበቁን የሚያረጋግጥ ነው። ጸዋላ የፖለቲካ ሥልጣንን በመጠቀም ሁሉን የሕይወት ክልል በእስልምና ሥልጣን ሥር ለማስገዛት መትጋት ነው።

የጸዋላንም ሆነ የጸዋን እስላማዊ ተልእኮ ገጽታ ታሪካዊ እውነታዎች ተፈታትነውታል። ንጹሕ እስልምናን ለማራመድ የሚፈልጉ እንደ አፍጋኒስታኑ ታሊባን ያሉ እንቅስቃሴዎች በብዙ ዓለም እንዳይወደዱ አድርጓቸዋል። ቤተክርስቲያን ለማደግ ስፍራ (ክፍተት) ስታገኝ ብዙ ጊዜ ታድጋለች። እስልምና የሚገዛባቸው ሰፊ ክልሎች በድኽነትና በመሃይምነት የተወረሩ

[4] Kenneth Cragg, *The Call of Minaret* (Marvknoll. N.Y.: Orbis Books, 1985), 26.

ናቸው። (በአንዳንድ የላቲን አሜሪካና በአፍሪካ አካባቢ የሚኖሩ በብዙ መቶ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ክርስቲያኖች በድኽነት እንደሚኖሩ የሚካድ አይደለም)።

ኡማው (የእስልምና ማኅበረሰብ) ዐላማውን ውጤታማ በማድረግ ለሕዝቦች መመሰክር ተልእኮው ቢሆንም፣ የተፈለገውን ያህል ግን ውጤታማ አይደለም። ሁኔታዎችን ለማስተካከል (ለመለወጥ) መንገድ መፈለግ አለበት። በእርግጥ ለሙስሊሙ ኅብረተሰብ የተልእኮውን እንድርድሮሽ መልሶ መያዣው መንገድ በጣም ቀርቦአል። ሙስሊም መልእክተኞች ዕቅድ ተስፋ ያለው ነው። በመካከለኛው ምሥራቅ የሚገኙ ሕዝቦች በዘይት እጅግ ብዙ ትርፍ እያገኙ ነው። ዓለም ዐቀፍ የሆነውንም የእስልምና ተልእኮ ተያይዘውታል።

የእስልምና ባህል ለነበራቸው ለቀድሞ የሶቭየት ኅብረት አገሮች በአሁኑ ጊዜ ልዩ ትኩረት ሰጥተዋል። በቀድሞ ኮሚኒስት ማኅበረሰብ ፍርስራሽ ውስጥ የእስልምና መልእክተኞች በትውፊት ሙስሊም የነበረውን ሕዝብ እስልምና ለሚያቀርበው አማራጭ እንዲነሣሣ እያደረጉ ናቸው። በእነዚህ ክልሎች ሁሉ ቤተ ክርስቲያንና ኡማው ይህንኑ ክፍል በብርቱ ትጋት ወደ ራሳቸው እየሳቡ ይገኛሉ። በእነዚህ ቀድሞ የሙስሊም ማኅበረሰብ በነበሩ አካባቢዎች የእስልምና መልእክተኞች የማይናቅ አዎንታዊ ምላሽ እያገኙ ነው።

ዓለም ዐቀፍ የሆነው ኡማ በመስፋፋት ላይ ይገኛል። ሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን እንደ ጀመረ በዓለም ዙሪያ ያለው የሙስሊሞች ቁጥር በየዓመቱ በሃያ ሰባት ሚሊዮን ዕያደገ ነው[5]።

የክርስቲያኖች ተልእኮ

ኢየሱስ ሞትን ድል አድርጎ ከተነሣ ከአርባ ቀን በኋላ ደቀ መዛሙርቱን በኩረብታ ላይ አገኛቸው። እንዲህም አላቸው፦—

መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኀይልን ትቀበላላችሁ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ። (ሐዋርያት ሥራ 1+8)

እንዲሁም ታላቁን ተልእኮ ሰጣቸው። እንዲህ ሲል፦—

[5] Johnstone and Mandryk, *Operation World*, 2.

ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው። እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ (ማቴ 28÷19-20)።

እነዚህ ኢየሱስ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት ለደቀ መዛሙርቱ የሰጣቸው ትእዛዛትና መመሪያዎች ናቸው። ኢየሱስ ይህን ትእዛዝና መመሪያ ከሰጠበት ማግሥት ጀምሮ፣ ቤተ ክርስቲያን ይህን ትእዛዝና ተልእኮ ከዳር ለማድረስ በሰፊው ተንቀሳቀሳለች። ምዕራፍ አንድ ላይ ለማየት እንደ ሞከርነው፣ ከቁስጠንጢኖስ ዘመን በኋላ፣ በምዕራቡ ዓለም የምትገኘዋ ቤተ ክርስቲያንም ሆነች መንግሥት፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ወኪሎች ነን የሚለውን ጉዳይ ታሳቢ በማድረጋቸው፣ የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር ላይ እንዴት ይመሠረታል የሚለውን ጉዳይ አስመልክቶ በፖለቲካውም ሆነ በሃይማኖቱ ረገድ በርካታ ለውጦች ተካሂደዋል። ይህም "የክርስቲያን መንግሥት" (Christendom) የሚባለው አስተሳሰብ እንዲዳብር ምክንያት ሆኗል። ይህ ሙስሊሞች ዳር አል-ኢስላም (በእስልምና አገዛዝ ሥር የሆኑ ግዛቶች) ከሚሉት ጋር ተመሳሳይ ነው።

ዳሩ ግን በምዕራብ በሚገኙት ክርስቲያኖች ዘንድ የነበረው ይህ ታላቅ ተልእኮና ራእይ ቀስ በቀስ እየተዳከመ መጥቶአል። የአውሮፓ ክርስቲያኖች ይህን ራእይ በዓለም ሁሉ ከማቀጣጠል ይልቅ በእርስ በርስ ሽኩቻ ተወጥረው ይገኛሉ። የቤተ ክርስቲያንን ምድራዊ ተልእኮ ከፉኛ ከተፈታተኑት ጉዳዮች መካል ከእስልምናው ወገን የሚቀርቡት ፈተናዎች ብቻ ሳይሆኑ፣ እንደ ግርክሲዝም ያሉ ዓለማዊ ንቅናቄዎች ጭምር ናቸው። እነዚህ ተግዳሮቶች በራሱ በወንጌልም ላይ ቀጥተኛ ተቃውሞ ሰንዝረዋል። በግርክሲስት ማኅበረሰብ ውስጥ ክርስትና በከፍተኛ ታቃውሞ ውስጥ ስለወደቀ ብዙ ክርስቲያኖች ተሰደዋል፣ የሕይወት ዋጋም ከፍለዋል። ክርስቲያናዊ በሆነው ምድር የናዚ ጀርመኖች የአይሁድን ዘር ለማጥፋት ያደረጉትን የዘር ጭፍጨፋ ከቶውንም የሚዘነጋ አይደለም። ይህ ዐይነቱ እኩይ ተግባር በክርስቲያኑ ማኅበረሰብና ክርስቲያናዊ በሆነው ምዕራባዊ ሥልጣኔ ውስጥ እንዴት ሊከሠት ቻለ? ይህ ጉዳይ በምዕራብ የሚገኙትን የክርስቲያኖችን ራእይ ከፉኛ ያጨለመ የታሪክ ክሥተት ነው።

ሆኖም ይህ በምዕራብ አውሮፓ መታወክ የገጠመው የክርስቲያኖች እንቅስቃሴ፣ በብዙ የዓለም ክፍል የሚገኙትን ቤተ ክርስቲያን የሚወክል

አይደለም። በዓለም ዐቀፍ ደረጃ ሲታይ፣ ቤተ ክርስቲያን አስደናቂ የሆነ ተሐድሶና ዕድገት ተጐናጽፋለች። ይህ ዐይነቱም እምነትና ተስፋ ዛሬም አለ። ከኮሚኒዝም ውድቀት በኋላ በምሥራቅ አውሮፓና በቀድሞዋ ሶቭየት ኅብረት የተከሠተው አስደናቂ የቤተ ክርስቲያን ዕድገት፣ ከየትኛውም የታሪክ ጊዜ ጋር የሚወዳደር አይደለም። በቻይና የምትገኙትም አብያተ ክርስቲያናት ከዚህ ቀደም ታይቶም ሆነ ተሰምቶ የማይታወቅ ድል እየተቀዳጁ ነው። በክፍለ ዘመኑ መጀመሪያ ላይ በቻይና አንድ መቶ ሚሊዮን የሚደርሱ ክርስቲያኖች ነበሩ። በሃያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ ግን በየዓመቱ ሰባት ሚሊዮን አዳዲስ ክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያንን ይቀላቀላሉ[6]።

በየዓመቱ በዐሥር ሺዎች የሚቈጠሩ የወንጌል መልእክተኞች በዓለም ዙሪያ የወንጌሉን ሥራ ይሠራሉ። ባለጠጋ ናቸው ከሚባሉት ከምዕራብ አብያተ ክርስቲያናት ብቻ ሳይሆን፣ በዓለም ላይ ካሉ ከየትኛውም አገር የወንጌል መልእክተኞች በተለያየ ስፍራ ወንጌልን እንዲሰብኩ ወደ ተለያዩ አገሮች ይላካሉ። በሃያ አንደኛው ሞቶ ክፍለ ዘመን መግቢያ ላይ፣ በዓለም ዐቀፍ ደረጃ ከዘጠና ስምንት ሺህ በላይ የሚሆኑ የወንጌል መልእክተኞች ከአገራቸው ውጪ የሚያገለግሉ ሲሆን፣ ከሁለት መቶ ሺህ በላይ የሚሆኑት ደግሞ በአገራቸው ውስጥ ባህል ዘለል የወንጌል መልእክተኛ በመሆኑ ከቀዬአቸው ርቀር ያገለግላሉ። ኮርያ የወንጌል መልእክተኞችን በመላክ ግንባር ቀደሟ የዓለማችን አገር ሆናለች። ዛሬ ኮርያ ዐሥራ አንድ ሺህ የወንጌል መልእክተኞች ወደ ተለያዩ የዓለማችን አገሮች በመሄድ የምሥራቹን ወንጌል በመስበክ ላይ ናቸው[7]።

የታሪክ ግብ

ሙስሊሞችም ሆኑ ክርስቲያኖች ሰዎች እስልምናን ወይም ወንጌልን እንዲቀበሉ ጥሪ የሚያቀርቡት ለምንድን ነው? የዚህ ንቅናቄ አራማጅ የሆኑ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች፣ መልእክተኞቻቸውን ወደ ተለያዩ የዓለማችን አገሮች የሚያሠማሩት ለምንድን ነው? በተለያየ አጋጣሚ ወደ ተለያዩ ስፍራዎች የሚሄዱ ሙስሊሞችም ሆኑ ክርስቲያኖች እምነታቸውን ለሌሎች በመስበክ ሰዎች እስልምናን ወይም ወንጌልን እንዲቀበሉ ግብግ የሚያቀርቡት ለምንድን ነው? ክርስቲያንም ሆኑ ሙስሊም ስደተኞች በምጸተኝነት በሚኖሩባቸው

[6] ዝኒ ከማሁ፣ 180።

[7] ዝኒ ከማሁ፣ 747:749።

አገሮች የሚገኙትን ጉረቤቶቻቸውን የእነርሱን ጹሳ እንዲከተሉ የሚጋብዙበት ምክንያት ምንድን ነው?

በሙስሊሙ ማኅበረሰብም ሆነ በክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያን ያላቸው የዚህ ሚስዮናዊ ተልእኮና ራእይ መሠረቱ የታሪክ ዐላማና ግብ ምንድን ነው በሚለው ርእሰ ጉዳይ ላይ ያላቸውን መረዳት መሠረት ያደረገ ነው። የታሪክ ትርጉሙ ምንድን ነው? ሁለቱም ወገኖች ለዚህ ጥያቄ የሚሰጡት መልስ የተልእኮአቸውን ዐላማና ግብ ይወስነዋል። ሙስሊሞችም ሆኑ ክርስቲያኖች ለዚህ ጥያቄ የሚሰጡትን መልስ ወደ መመርመሩ እንገለት።

አስሰምናና ታሪክ

በሙስሊሞች መረዳት ታሪክ ልክ እንደ ቅንፍ ስብስብ ነው። በምዕራፍ 3 እንደ ተገለጸው ከጅምሩ አዳምና ሔዋን የተፈጠሩት በገነት እንጂ በምድር ለመኖር አልነበረም። ነገር ግን አዳም በሰይጣን በመታለሉ ምክንያት እግዚአብሔር ወደ ምድር አባረረው። እንደ ብዙ ሙስሊሞች እምነት ሰዎች በዚህች ምድር ያላቸው ቆይታ የፈተና ዘመን ነው[8]። ይህ የፈተና ዘመን የሚጠናቀቀውም ታላቅ በሆነ ፍርድ ነው። ከፍርዱም በኋላ በርካታ ሰዎች ዘላለማዊ ወደ ሆነው ገሃነመ እሳት ሲሄዱ ብዙዎች ደግሞ ወደ ገነት ይገባሉ። የገነት ምጽአትና የሰብአውያን ታሪክ መጠናቀቂያ በሆነው ዘመን መካከል ላይ ያለን ሲሆን ከቀጣዩ ዘመን ደግሞ በገነት ወይም በገሃነም የሚጠናቀቅ የመጨረሻው ፍጻሜ ነው። ስለዚህ ይህ የታሪክ ወቅት በሽግግር ላይ የምንገኝበትና በቅንፍ የሚመሰልበት ወቅት ነው። ስለዚህ ይህ ዘመን በቅንፎቹ ዘመን መካከል የሚገኝ ታሪካዊ ወቅት ነው።

እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ወደ ምድር ካባረራቸው በኋላ የመጀመሪያው የእግዚአብሔር ቤት ከሚገኝበት በካዕባ አካባቢ በአራፋት ሜዳ ላይ ይኖሩ ነበር። በምድር ላይ በሚኖሩበት ዘመን ሁሉ፣ እነርሱም ሆኑ ዘሮቻቸው እንደ እግዚአብሔር ከሊፋ (ጠባቂዎች) ሆነው የማገልገል ኀላፊነት ነበረባቸው። የሰው ልጆች ኀላፊነት የሚሰማቸው አገልጋዮች እንዲሆኑ እግዚአብሔር በምሕረቱ መመሪያን ሰጥቶአል። ይህም መመሪያ እስልምና ነው። ይህ መመሪያ በነቢያት በኩል ሲመጣ አደም የመጀመሪያው ነቢይ ነበር። ማንኛውም ሕዝብ የራሱ

[8] Badru D. Kateregga and David W. Shenk, *A Muslim and a Christian in Dialogue* (Scottdale, Pa.: Herald Press, 1997), 44.

የሆነ ነቢይ አለው ምናልባትም በሰብአውያን ታሪክ ውስጥ የታዩት አንድ መቶ ሃያ አራት ሺህ (124,000) የሚሆኑ የእግዚአብሔር ነቢያት ናቸው[9]።

ይህ የአምላክ ምሪት ባሕርይ ተለውጦ አያውቅም፣ ይኸውም እስልምና ነው። ሰዎች ይህን ምሪት ረስተው ወይም ለመለወጥ ሙከራ አድርገው ይሆናል። ነገር ግን ይህ በፍጹም ሊሆን አይችልም። ምሪቱ ከሰማይ የተላከ ምሪት ስለሆነ ከታሪክ ሂደት የላቀ ነው። ሊኩረጅም ሆነ ሊመሰል በፍጹም አይችልም፣ "በቅርጹ ከታሪካዊ ንባብ ጊዜያት ጋር ምንም ዐይነት ዝምድና የለውም። ቃል በቃል ከሰማይ የወረደና አስቀድሞ በመለኮታዊ ሰሌዳ ላይ ተጽፎ የነበረ ነው"[10]።

እንግዲህ ይህ የማይመስልና የማይኩረጅ ባሕርዩ ነው ቁርአን ከወረብኛ ቋንቋ ውጪ እንዳይተረጐም ያደረገው። ባለፉት ዘመናት ብዙ ሕዝቦች ምሪቱ ከእግዚአብሔር ስለመላኩ ቸልተኛ ሆነው ነበር። ቸል ከማለትም በላይ ረስተውት እንዲሁም ለመቀየር ፈልገው ነበር። ሆኖም የሙስሊሙ ተልእኮ የመጨረሻ መገለጥ የሆነውን ቁርአንን ከማንኛውም ፈጠራ መጠበቅ ነው። እያንዳንዱ ቃል በሰማይ ካለው ቅጅ ጋር አንድ ዐይነት የሆነ ፍጹም ግልባጭ ነው።

በዚህ ዐይነት በማያጠራጥር ሁኔታ መገልበጡን መረዳት ማለት የእስልምና መጽሐፍ ከታሪካዊ ክሥተቶች ጋር ዐቢይ ግንኙነት እንደሌላቸው ማጽናት ነው[11]። ለምሳሌ አስቀድመን ለማየት እንደ ሞከርነው፣ ቁርአን መሲሑ አልተሰቀለም ካለ፣ በምንም ዐይነት መልኩ ይህን የሚቃረን ታሪካዊ ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም። በምንም ዐይነት መልኩ ታሪካዊ ክሥተቶች የቁርአንን ሥልጣንና ተአማኒነቱን ጥያቄ ውስጥ ሊያስገቡ አይችሉም። ታሪክም ሆነ የሰብአውያን ተሞክሮ ስለመጽሐፉ ይዘት መሠረት አልሆኑምና። ራሱን ችሎ የሚቆመው ቁርአን ከሰው ልምምድ እጅግ የላቀ ነው።

ይህ መገለጥ ወደ ምድር ተልኳል የሚለው ግንዛቤ፣ ከታሪክና ከፍጥረት አንጻር በሰዎች ኀላፊነት ላይ እንዴት ተጽእኖ ሊኖረው ይችላል? በታሪክ ትርጉም ላይስ ምን ተጽእኖ ይኖረዋል? የምናደርጋቸው ነገሮች እግዚአብሔርንም ሆነ

[9] ዝኒ. ከማሁ፣ 64።

[10] Andrew Rippin, *Muslims: Their religious Beliefs and Practices* (New York: Routledge, 2001), 236.

[11] ዝኒ. ከማሁ፣ 238-245።

መገለጡን የማይነኩ ከሆኑ፣ እኛ በታሪክ ውስጥ ያለን ድርሻም ሆነ ቁም ነገር ምን ምን ሊፈይድ ይችላል። ስለዚህ በዚህ ረገድ ትልቅ ድርሻ ያለው እግዚአብሔር ከሰማይ ወደ ምድር የላከው ምሪት ብቻ ነው። ለዚህም ነው ሙስሊም በሆነው ማኅበረሰብ ውስጥ የእስልምና ሕግ ጥናት፣ ሌሎች የጥናት ዘርፎችን መተካቱ የማያስደንቀው[12]። ሙስሊሞች የእግዚአብሔር ሕግ መልካም ዜና እንደ ሆነ እርግጠኛ ናቸው።

የታሪክ ሊቁ ዊልያም ካንትዌል ስሚዝ እንዳስተዋለው :—

> ለእንዲ እና ለመጪረሻ በግልጽ ቃል የአላህ እውነትና ፍትሕ ወደ ምድር ተልኳል። መልእክቱን ያለምንም መዛነፍ ያደርስ፣ ይተረጉም፣ ይኖረው ዘንድ መልእክተኛ ተመርጧል። በጥንቃቄ እና በታማኝነት መልእክቱን የሚጠብቁ ኅብረተሰብ እስከ ምድር ጫፍ መልእክቱን እንዲያውጅና ተግባራዊ አንድምታውን ሁሉ ባካተተ መልኩ እንዲታዘዙት ተጠርተዋል[13]።

ስለዚህ የታሪክ ዐላማ እያንዳንዱ ሰው ለእግዚአብሔር ሕግ የሚሰጠውን ምላሽ መፈተን ነው። ይህ የፈተና ወቅት ከገነት የወጣንበት እና ወደ ገነት ተመልሰን በምንገባበት አልያም ፈተናውን የወደቁ ወደ ከሃነም የሚጣሉበት የሽግግር ወቅት (ቅንፍ) ነው። የቁርአን ዐቢይ መልእክት ፍርድ ነው። የፍርድ ሰዓት እየደረሰ ነው። የሰው ልጅ ጊዜያዊ የምድር መኖሪያው ሲያበቃ ገነት ወይም ገሃነም ይጠብቀዋል።

የሰው ልጅ ከዚህ የፈተና ጊዜ ማምለጥ የሚችለው፣ ወደ መሐሪው አምላክ ለሚያደርሰው የእስልምና ሃይማኖት በመገዛት ነው። የኡማ ተልእኮ ለዚህ ምሪት ምስክርነት መስጠትና በቁርአን እንደ ተገለጠው ፍጹም ለሆነው ለእግዚአብሔር ሕግና በሐዲስና በሸሪአ እንደ ተብራራው ሕዝቦች እንዲገዙ በየስፍራው ሁሉ ማብራታት ነው።

ነገር ግን ሙስሊሞች ሁሉ ለእስልምና በታማኝነት ይገዛሉን? በፍጹም በሁለት ሐሳብ የሚያነክሱ ብዙዎች ናቸው። ይህንን ማስተካከል የተሐድሶአውያኑ ሙስሊሞች ተግባር ነው። እነዚህ ግለሰቦች በጊዜያዊነት በዚህ ምድር በሚኖሩበት ወቅት ሙስሊሞች ለእስልምና ሃይማኖት ታማኝ እንዲሆኑ

[12] H. A. R. Gibb, *Mohammedanism* (New York: Oxford University Press, 1969), 9.
[13] Wilfred Cantwell Smith, *Islam in Modern History* (Princeton: Princeton University Press, 1957), 14.

ይረዷቸዋል። የሙስሊሙ ታማኝነት በብዙ መልኩ ከዛሬው ይልቅ የተድሞው የሚበልጥ ሆኖ ሳለ፣ ዛሬ ዓለም ዐቀፉ የሙስሊም ኡማ እስልምናን ወርቃማ ወደ ሆነው የቀድሞ ዘመን ለመመለስ በሚፈለጉ የተሐድሶ እንቅስቃሴዎች ተጋልጦ ይገኛል። እነዚህ ተሐድሶዎች ሦስት መልክ አላቸው[14]:—

1. **ዐማፅያንና ጅሃዳውያን:—** ይህ እንቅስቃሴ አሁን ያለንበት ውጥንቅጥና አደገኛ ወቅት ሊስተካከል የሚችለው፣ አስላማዊ ያልሆኑ ክልሎችንና እስልምናን ለመቀየር በተነሡ ግብዝ ሙስሊሞች ላይ ሁከት በመፍጠር እንዲሁም እነዚህን ግለሰቦችና ተቋማት ፊት ለፊት በጎይል በመጋፈጥ ነው የሚል እምነት አለው። የእስልምና ወርቃማ ዘመን ነው የሚባለው፣ በመዲና መሐመድ በመሠረቱት ተምሳሌት ሙስሊሞች ለማኅበረሰቡ ታማኝ ሲሆኑ ነው። በዚያን ወቅት በመዲና እስልምናን ለመመሥረት፣ ለመቀደስና ለማስፋፋት ዐመፅ ጥቅም ላይ መዋሉ ለዛሬ ምሳሌ ሲሆነን እንዲሁም በዘመናችን ሁኔታ የግድ ልንተረጉመው የሚገባን ጉዳይ ነው የሚል ንቅናቄ ነው (ለምሳሌ አልቃይዳ)።
2. **ሕግ አጥባቂ ተሐድሶዎች፣** የእስልምና ወርቃማ ዘመን የሚመጣው ኡማው በታማኝነት ሱናንና ቁርአንን ሲከተል እንዲሁም እነዚህን መመሪያዎች ታማኝ በሆነ ሸሪአዊ ልምድ ሲተገብር ነው የሚል እምነት አላቸው (ለምሳሌ የወረቡ ውሃቢያ)።
3. **ተራማጆች** ደግሞ የቁርአን መንፈስ ለዘመናዊ ሃይማኖታዊ ላልሆነ የሙስሊም ማኅበረሰብ ግንባታ መነሻ መሆን አለበት ይላሉ። ሐዲስ፣ ሱናና ሸሪአ ኡማው በዘመናዊው ዓለም ውስጥ ጥሩ ተምሳሌት ሆኖ ኑሮውን እንዳይኖር አጣብቂኝ ውስጥ አስገብተታል ባይ ናቸው።

እነዚህ የተሃድሶ እንቅስቃሴዎች ሁሉ በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ይስማማሉ:—

1. እስልምና የተጨቋኞችና የተጣሉ ሰዎች እምነት ነው። በተቃራኒው ክርስትና ግን የጨቋኞች እምነት ነው (ሙስሊሞች የምዕራቡ ክርስቲያን ጨቋኝ ነው የሚለውን አስተሳሰብ እያደረባቸው የመጣው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ነው)[15]።
2. ሙስሊሞች የእስልምናን ሥልጣን በምድር ሁሉ ላይ ለማስፈን ጠንክረው መሥራት አለባቸው።

[14] Dudley Woodberry, "Justice and Peace," *Christian History* 21:2 (August 2002), 44.
[15] ዝኒ ከማሁ፣ 45።

3. ሙስሊሞች፣ የሙስሊሙን ሕዝብ ክብርና ሥልጣን ለማስመለስ ማዕከላዊ ወደ ሆነው የእስልምና እምነትና ተግባር መመለስ አለባቸው።

ተሐድሶአውያኖቹ እያንዳንዱ ማኅበረሰብ የራሱ ዐይነተኛ መለያ ጠባዩን እንደያዘ ይኑር በሚለው ጉዳይ ላይ ትልቅ ትኩረት ያደርጋሉ። በተወሰነ ደረጃም ቢሆን፣ እስልምና ልዩነትን ይቀበል ነበር፤ እያንዳንዱ ሕዝብ የራሱ የሆነ ነቢይ እንደ ነበረው ያምን ነበርና። ሆኖም አሁን ቁርአን ተገልጧል። በመጨረሻው የፍርድ ጊዜ ገኑት ለመገለት ተሰፋ የሚያደርጉ ለእስልምና መገዛት ብቸኛው አማራጫቸው ነው። የተለያዩ የተሐድሶ ንቅናቄዎች ግን ልዩነትን በተለያየ መንገድ የማስተናገድ ዐላማ አላቸው። ነገር ግን ለእስልምና መገዛት ሙስሊሟን ምድራዊ ሕይወታቸውን እንዲሁም ወደ ፊት ገኑትን ለመውረስ ብቸኛ ጉዳይ እንደ ሆነ ያምናሉ።

ስሚዝ የሚከተለውን አስተያየት ይሰጣል፦

> በጋራም ሆነ በተናጠል ሙስሊሞች ከዚህ ዓለም ባሻገር ገኑትን ይፈልጓታል። ለገኑት የግል ዝግጅት ለማድረግ አመቺ የሆነ ማኅበረሰብ ያስፈልጋል። ይህ ምድራዊ ሕይወት ጊዜያዊውን ጽድት ዘመን ከማይሽረው የመጪው ዘመን ድነት ጋር ለማዋሐድ የሚደረግ ትግል ነው። የታሪክ ትርጉም የሚወሰነው ይህ ምን ያህል እውነት ይሆናል በሚለው ጉዳይ ላይ ነው[16]።

ይህ ማንኛውም የሕይወት አቅጣጫ ለእስልምና መገዛት አለበት የሚለውን መሠረት ያደረገ ነው። ይህ ተግባር በሱኒ እስልምና የከሊፋዎች ድርሻ እንዲሁም በሺአ እስልምና የኢማሙ ድርሻ ነበር። የክርስትና ነገረ መለኮት እንዲሁም የእስልምና ሃይማኖት ምሁሩ ኬኔት ካሬግ ሲያብራራ፦

> እስልምና የአምልኮ መንገድ ብቻ ሳይሆን፣ የአገዛዝ ዐይነትም ነው። የእግዚአብሔር ግዛት ሰዎች ላይ እንዲሰፍን ብቻ ሳይሆን፣ ሰዎች ይህን ግዛት እንዲያሰፍኑት ይጠብቃል[17]።

ነፍስን ሁሉ በእስልምና ሥር ማስገዛት የሙስሊሙ ሕዝብ የመጨረሻ ተልእኮ ነው። በታሪክ ፍጻሜ የሚከናወነው የፍርድ ቀን መምጣት ተልእኮው እስከ

[16] Smith, *Islam in Modern History*, 22.

[17] Kenneth Cragg, *Sandals at the Mosque* (New York: Oxford University Press, 1959), 124.

ምን ድረስ ነው በሚለው ርእሰ ጉዳይ ላይ የሙስሊም ምሁራን አይግባቡም። በድሩ ዲ. ቱትራጋ እንደሚናገረው የእስልምና ነገረ መለኮታውያን የሙስሊም ግዛት ከመጨረሻው ፍርድ በፊት የሚያትፈው ክልል ላይ አይስማሙም። አንዳንዶች ሙስሊሞች እንደ ጨው በየቦታው ተበትነው ይኖራሉ ሲሉ፣ አንዳንዶች ግን የሙስሊሙ ኡማ ዓለም ዐቀፋዊ ይሆናል ባይ ናቸው ሌሎቹ ደግሞ ከመጨረሻው ፍርድ በፊት ከእስልምና እምነት የማፈግፈግ ሁኔታ ይከሠታል የሚል እምነት አላቸው።

ጂ.ኢ. ግሩነባውም አስተውሎቱን በሚከተለው መንገድ ይገልጻል፦

> ሰዎች ለፖለቲካና ለመንፈሳዊ ሕይወት መታደስ ያላቸው ጉጉት ሰዎች መጻኢ ዘመናቸውን ለማሻሻል ያላቸውን ጽኑ ፍላጐት አመልካች ነው። ይህም ነገሮች መልካም ሆነው እንዲቀጥሉ በማድረጉ ረገድ ያለው ድርሻ ቀላል አይደለም። ይህ እምነት የእስልምና ትውፊት ታሪክን እያሽቆለቆለ ይሄዳል ብሉ ከሚያምነው የተለየ ነው። ትልግ ዕድገት የታየበት እስልምና በነቢዩ መሐመድ ዘመን የነበረው እስልምና ነው። ሁለተኛው ደግሞ በእርሳቸው ተተኪዎች ዘመን የነበረው እስልምና ነው። ዓለምም ሆነች እስልምና አብረው እያሽቆለቆሉ ነው[18]።

ይሁንና ይህ የታሪክ የሽግግር ወቅት ወደ ድምዳሜ ሲደርሱ፣ መሲሑ ኢየሱስ ወደ ምድር ይመጣል። ለዚህ እምነት አስተዋጽኦ ያደረገ አንድ ግልጽ ያልሆነ ጥቅስ አለ (ሱራ 43፥61)። የነገረ መለኮት ሰዎች ኢየሱስ ካልተገኘ በስተቀር ኢየሱስ የፍርድ ምልክት ሊሆን እንደማይችል ያመለክታሉ። በተጨማሪ የክርስቶስን ዳግም ምጽአት የሚያመለክተው ሐዲስ የተባለው መጽሐፍ ነው።

የተወሰኑ የሺአይት እስልምና ቡድኖች ኢየሱስ መድረሻው ካልታወቀው ከዐሥራ ሁለተኛው ኢማም ጋር ዳግም እንደሚመጣ ያምናሉ። ኢየሱስ ሲመጣ ምን ያደርጋል? እነዚህ ሺአይቶች ከዐሥራ ሁለተኛው ኢማም ጋር ኢየሱስ በኢየሩሳሌም እንደሚገለጥ የሰው ሁሉ ዐይኖች እንደሚያያቸው ያምናሉ። ኢማሙና ኢየሱስ ሙስሊሙና ክርስቲያኑ በአንድነት ሆነው በሰላም እንዲኖሩ ያዛሉ።

[18] G. E. von Grunebaum, *Islam Essays in the Nature and Growth of a Culturl Tradition* (New York: Barnes and Noble, 1961), 227.

ኢየሱስ ዐሣማዎችንና መስቀልን በመደምሰስ የክርስቲያኖችን ስሕተት እንደሚያርም ብዙ የሱኒ ሙስሊሞች ያምናሉ። እስልምናን በማደስ ዓለምን ለፍርድ ያዘጋጃል። ኢየሱስም በሥጋው ይሞትና ከሌሎች ጋር ለመጪረሻው ፍርድ ይነሣል ባቦች ናቸው።

ከዚህ ሁሉ አንጻር ሲታይ፣ የእስልምና ተልእኮ ምንድን ነው? በቅርቡ ለሁለት የእስልምና ምሁራን ይህን ጥያቄ አቀረብሁላቸው። በመጀመሪያ አሁን በጀርመን የሚኖር ኢራናዊ የቪአይት ምሁር ይህንን አስተያየት ሰጠ፣ "ጻር አል-ሰላም (የሰላም ግዛት) ሙስሊሞች በሚከበሩበት ተቀባይነትን ባገኝበት ስፈራ ይሰፍናል። እኛ ሙስሊሞች በጀርመን ሰላምን እስካገኘን ድረስ የፖለቲካ ሥልጣን አያሰፈልገንም። ተልእኮአችን የእስልምና ምስክሮች መሆን ነው። ሁሉም ሕዝብ የራሱ የሆኑ ነቢያት አሉት። ስለዚህ እግዚአብሔር የእምነት ልዩነትን ፈቅዷል። እያንዳንዱ ሰው ሙስሊም መሆን የለበትም። ይህ ቢሆን ያሰለች ነበር"።

ከሳምንት በኋላ የሱኒ ሙስሊም የሆነውን ሕንዳዊ፣ "በሰሜን አሜሪካ የሙስሊሞች ተልእኮ ምንድን ነው?" ብዬ ስጠይቀው እንዲህ መለሰልኝ፣ " ተልእኳችን በሰሜን አሜሪካ የእስልምናን እውነት መመስከር እና ሰዎች ለእስልምና እንዲገዙ ጥሪ ማቅረብ ነው። በአሁኑ ሰዓት ብዙ የፖለቲካ ሥልጣን እንዳናገኝ ማኅበረሰባችን በጣም ትንሽ ነው። ሆኖም ወደ በኋላ የፖለቲካ ሥልጣን ለማግኘት ወሳኝ የሆነ ብዛት ይኖረናል። ያኔም ጻር አል-ኢስላምን (በሙስሊም የምትተዳደር አካባቢ) በመላው ሰሜን አሜሪካ እንመሰርታለን" እነዚህ ሁለት አስተያየቶች በዓለም ዐቀፍ እስልምና ማኅበረሰብ ውስጥ ያሉትን ልዩነቶች የሚያሳዩ መስኮቶች ናቸው። ሆኖም ዋናው ሐሳብ ለታማኝ ሙስሊሞች እውነቱ ሁሌም አንድ ነው። የሙስሊም ሕዝቦች ተልእኮ ከአላህ በቀር አምላክ እንደ ሌለና መሐመድ የአላህ ነቢይ እንደ ሆነ መመስከር ነው።

ጠንቋይና ታሪክ

በመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ፣ የሰው ልጅ ታሪክ በኤድን ገነት እንደ ጀመረና በወደፊቱ የከበረች ከተማ እንደሚጠናቀቅ ይገልጻል። ከተማዋ ከሰማይ ወደ ምድር ትወርዳለች፣ የመሲሑ ሙሽራ ቤተ ክርስቲያን ነች። ይህም ታሪክ ትክክለኛው የእግዚአብሔር ሥራ መታያ ነው ለማለትና ሁሉም ታሪክ በምድርና በሰማይ ላለው የእግዚአብሔር መንግሥት ፍጻሜ ወደ ፊት እየገሠገሠ ነው። ለዚህም ነው የመጽሐፍ ቅዱስ ግልጠት ዋናው ፍሬ ነገር የእግዚአብሔር ተግባር በታሪክ ውስጥ የሆነው። ብዙው የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ

የእስራኤል የጉዞ ታሪክና ጊዜ የእግዚአብሔርን ጥሪ ለማከናወን በሚያደርጉት የወደፊት እርምጃና የሚገጥማቸውን መሰናክል ያሳያል።

ከኒውዮርክ እና በዋሽንግተን ዲ.ሲ. ጥቃት ከተፈጸመ ከብዙ ሳምንታት በኋላ፣ እኔና ባለቤቴ በካዛኪስታን የካራጋንዳን አብያተ ክርስቲያናት እየጐበኘን ነበር። በአካባቢው ሬዲዮ ጣቢያ ቃለ መጠይቅ ተደርጕልኝ ነበር። ብዙዎቹ አድማጮች ዓለማዊ ሙስሊሞች ነበሩ።

ጠያቂዬ እንዲህ አለ፡— "እኛ እንደምናምነው አገራችሁ ለድኅ ሕዝቦች ደኅንነት (መልካምነት) አትጨነትም። እንደ ክርስቲያን በአሜሪካ መራሽነት በአሸባሪዎች ላይ በሚደረገው ጦርነት ያንተ አመለካከት ምንድን ነው?"።

"መንግሥታት የራሳቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ ይተጋሉ" ስለዚህ ወደ ጦርነት ቢሄዱ ምንም የሚያስደንቀኝ ነገር የለም። ሆኖም መንግሥታት የሚከተሉት ያለው መንገድ የእግዚአብሔርን መንግሥት መሲሑ ኢየሱስ ባስተዋወቀበት በታሪክ ድራማ ድምዳሜ በሚመጣበትና በሚፈጸምበት መንገድ አይደለም። ማዕከላዊው የእግዚአብሔር መንግሥት ሥነ ምግባር ኢየሱስ እንደ ወደደ ጠላትን እንኳን መውደድ ነው። እንደ ገናም ይህ ማኅበረሰብ ሆኖ የእግዚአብሔርን መንግሥት ኢየሱስ እንዳደረገ በፍቅርና ሌሎችን በማገልገል መግለጥ የቤተ ክርስቲያን ጥሪ ነው።

ለመንግሥቴ እጸልያለሁ ለሕዝቤና ለዓለም ሕዝቦች በአጠቃላይ ፍትሕና ጽድቅ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲሆን እመሰክራለሁ። ሆኖም የመጀመሪያ ታማኝነቴ ለእግዚአብሔር መንግሥት ነው። ይህ መንግሥት ከተለያየ ጐሣ፣ ነገድና ቋንቋ የተሰበሰቡ የታረቁና ይቅር የተባሉ ሕዝቦች ስለሆነ አስደናቂ መንግሥት ነው።

አሳማ ቢን ላደንን አግኝቼ ዐቅፈው እርሱን የሚወደው የንጉሡ አምባሳደር መሆኔን ልነግረው እፈልግ ነበር። የንስሓ ይቅርታ እና የዕርቅ ጥሪ አቀርብለት ነበር።

የወንጌል ማዕከል እግዚአብሔር በመሲሑ ሆኖ በመስቀል ሞትና ትንሣኤ በተገለጠ ፍቅር እኛን ከራሱ ጋር ማስታረቁ ነው። እግዚአብሔር በሰዎች ታሪክ መጀመሪያ የቃል ኪዳን ዘር ተከለ። አዳምና ሔዋንም ከእግዚአብሔር ፈታቸውን ሲመልሱ ኀጢአተኛነትና ሞት የሰዎች ዕጣ ፈንታ ሆነ። ሆኖም እግዚአብሔር አዳምና ሔዋን ይኖሩበት ወደ ነበረው ስፍራ መጥቶ ፈለጋቸው፣ ጠራቸውም። ቀጥሮ ሥር ተደብቀው ሲያገኛቸው በጥልቅ ሐዘን ሆኖ ቃል

ኪዳን ገባላቸው። እባብ (ክፉ ኀይላት) ከሴት የሚወለደውን ወንድ ልጅ ያቄስሉታል:— እርሱ ግን ጭንቅላታቸውን ይፈጠፍጠዋል።

ይህ በገነት የተደረገው ትዕይንት መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነውን የታሪክ ትርጉምና ዐላማ ለመረዳት ዋና ነገር ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ትረካ፣ እግዚአብሔር በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ የሚያከብሩትንና ለሌሎች ሕዝቦች ብርሃን የሚሆኑትን የታደገበት ታሪክ ነው። እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን በመግባት የመጀመሪያው ሕዝብ ነው። ጥሪውም ለዓለም ሕዝብ በረከት እና ብርሃን እንዲሆኑ ነው።

በመሲሑ ሁሉም ሕዝቦች ለእግዚአብሔር ቤተሰብነት ተጠርተዋል። ክርስቲያኖች እንደሚያምኑት ቤተ ክርስቲያን ሁሉንም ጐሣ ቋንቋና ሕዝብ ያቀፈች እንዲሁም በወንጌል ሁሉንም የምትደርስ የእግዚአብሔር ቤተሰብ ነች።

እስራኤል ብቻ ሳትሆን ሕዝቦች ሁሉ የተፈጠሩት እግዚአብሔርን ለማክበርና ከእርሱ ጋርም በኅብረት ለዘላለም በመደሰት ነው። የእኛ ዐመፅና ኀጢአተኛነት አሳዛኝ በሆነ ሁኔታ ይህንን ዐላማ አቃውሶታል። ሆኖም እግዚአብሔር ለዘላለሙ አልጣለንም። ይልቁንም በየግል ተገናኝቶን በታሪካችን ውስጥ እውናዊ ተሳትፎ አደረገ፣ "የቄሰለው ፈዋሻችን"[19] ሆኖ ራሱን ገለጠ። በመሲሑ ሆኖ እግዚአብሔር ስለ እኛ ተሠቃየ፣ ለእኛ ሞቶ ተቤዠን። በእርሱ መሥዋዕታዊ ሞት እኛ ይቅር ተባልን፣ ቤተ ክርስቲያንም ይቅር የተባሉ ኀጢአተኞች ኅብረት ነች።

የሚያምኑ ሁሉ አዲስ የእግዚአብሔር መቅደስ ይሆናሉ። ምክንያቱም የእግዚአብሔር መቅደስ እርሱ የሚኖርበት ሕዝቡ ነው። ከእግዚአብሔር ሕዝብ ውጪ ሌላ የእግዚአብሔር ቤት የለም። ከእንግዲህ ሌላ ቤተ መቅደስ አያስፈልግም። የተቀደሰው ማዕከል ግለት ከሞት የተነሣው መሲሕ በመንፈሱ በሕዝቡ ውስጥና በስሙ በተሰበሰበበት ሕዝብ መኻል መገኘቱ ነው (ኤፌሶን 2፥19-22፣ ማቴዎስ 18፥20)። ይህ መንፈስ ቅዱስ የሚያድርባት ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር በሥጋ ተገልጦ በምድር መኖር ግለት ነው።

እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል ይኖራል። ኢየሱስ ለፍትሕ የሚተጋ ነበር። በየትም ስፍራ የእርሱ መንግሥት ስትመጣ ለድኾችና ለተጨቈኑ ተስፋ አለ።

[19] Henri J. M. Mouwen, *The Wounded Healer* (New York: Image Books, 1979).

ቤተ ክርስቲያን በዙሪያችንና በዓለማችን የመሲሑ የፍትሕና ለሰላም መግዛት ተምሳሌት ተብላ መጠራት አለባት። መሲሑ እየመሠረተ ያለው መንግሥት ዓለም ዐቀፍ እንዲሁም በፈቃደኝነት የሚከናወን ነው። ሁከትም የሌለበት ነው። በዚህ መንግሥት ጒልበት ስፍራ የለውም። ይህ መንግሥት ለሚቀበሉ ሁሉ የሰላም መንግሥት ነው። መስቀሉ ለእግዚአብሔር መንግሥት ግብረገባዊ መንገድ ነው፣ በተጨማም የመንግሥቱ ማኅበረሰብ የሆነች ታማኝ ቤተ ክርስቲያን ናት።

የቤተ ክርስቲያን ሃይማኖታዊ ጒዞ በኢየሱስ ስም መሰብሰብን ይጨምራል። ለአምልኮ የሚሰበሰቡት ዐልፎ ዐልፎ አብሮ ጸቦ በመቀኒረስና ጽዋውን መጠጣት ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሆኖ ለተሰቀሉት ይቅርታን እንደ ጠየቀ እንዲሁም እንደ ሰጠ መቤዠነትና ይቅርታ ቃል ኪዳን ምልክቶት (ምሳሌነት) ይጠ ቀሙበታል። የተቈረሰው ጸቦና የተጪመቀው በኢየሱስ የተመሠረተው ቃል ኪዳን ምልክት ነው። የንስሓ ቃል ኪዳንና አንዱ ለአንዱ ለጠላቱ ጨምሮ መሥዋዕታዊ ፍቅር የሚገለጽበትና ራስን በመስጠት የሚያገለግልበት ቃል ኪዳን መልክት ነው።

መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያንን ይመሠርታል። አዲስ ሕይወትንም ይሞላታል። የብሉይ ኪዳን ነቢይ የሆነው ሕዝቅኤል ከኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ከመሠዊያው እየፈሰሰ ምድረ በዳን የሚያጠጣ ወንዝ በራእይ ተመለከተ (ሕዝቅኤል 47፥1-2)። በወንዙ ዳር ላይ ቅጠሎችና ፍሬ ያለው ለመድኀኒት የሚሆን ዛፍ ይበቅላል። ከመሠዊያው ወደ ምድረ በዳ ይፈስ የነበረው፣ ሕዝቅኤል በራእይ ያየው ውሃ በዘይቤያዊ አነጋገር ከእባብ እንዲሁም ከተሰቀለውና ከተነሣው መሲሕ የሚሠርጸው መንፈስ ቅዱስ ነው።

በራእይ የታየው መድረ በዳ ደግሞ ዓለም ነው። የሕይወት ወንዝ ከመሠዊያውና ከመቅደሱ ወደ ምድረ በዳ ይፈሳል። ከመሲሑ ከኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ፈሷል። ይህ ሕይወት ሰጪ ወንዝ ነው ዛፎች በምድረ በዳ እንዲያድጉና ፍሬ እንዲያፈሩ የሚያደርገው። እንደ እኔ ግምት ፈዋሽ ቅጠል ጻድቅ ሕዝቦች ሲሆኑ የዛፍ ፍሬ ደግሞ የመሲሑ መንፈስ ፍሬ ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጐነት፣ ታማኝነት፣ ጭምትነት እና ራስን መግዛት ናቸው (ገላትያ 5፥22)።

የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ በምድር ላይ ያለው ምድረ በዳ ሁሉ በዚህ ሕይወት ወንዝ (መንፈስ ቅዱስ) እስኪነካ ድረስ ለሁሉም ማኅበረሰብ የወንዙ መተላለፊያ መሆን ነው። ይህ የደስታ ተልእኮ ነው። በየትም ስፍራ ላይ በኢየሱስ ስም

ሰዎች ሲገናኙና በእርሱ ጸጋ ሲደሰቱ ደስታ አለ። ይህ የመጸኢው ዓለም ባለተስፋ ማኅበረሰብ ነው። በሰማይ ያለው የእግዚአብሔር ፈቃድ በምድር የሚፈጸምበትን ዘመን የሚጠብቅ ነው። ቤተ ክርስቲያን በማኅበረሰብ ውስጥ የምትገኝ ማኅበረሰብ ነች። በምድር ትኖራለች፣ ነገር ግን ከምድር አይደለችም። "ጨው" እና "ብርሃንም" ተብላለች (ማቴዎስ 5÷3-16)። ይህም ተጽእኖ ማሳደርን እንጂ መቈጣጠርን የሚያመለክት አይደለም።

መሲሑ ለደቀ መዛሙርቱ መመሪያ ሲሰጥ፣ "ሂዱና አሕዛብን ሁሉ ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው" (ማቴዎስ 28÷19) ብሏል። በአዲስ ኪዳን ውስጥ መልእክቱ በፍጥነት መዳረስ እንዳለበት በአጽንኦት ተነግሮአል። ሁሉም ሕዝቦች ወንጌልን መስማት አለባቸው፤ የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ ይህንን መልካም ዜና ከሕዝብ ወደ ሕዝብ ማድረስ ነው። ታሪክ ፍጻሜ አግኝቶ የሚደመደመው ሁሉም ሕዝቦች ወንጌልን ሲሰሙ ነው። ይህንን ቀን በመጠበቅ ስለ ወደ ፊት፣ "ውሃ ባሕርን እንደሚከድን ምድር የእግዚአብሔርን ክብር በማወቅ ትሞላለች" (ዕንባቆም 2÷14)።

ኢየሱስ እንዲህ አለ፣ "ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል በዚያን ጊዜም መጨረሻው ይሆናል" (ማቴዎስ 24÷14)። ክርስቲያኖች እንደሚያምኑት ወንጌልን መቀበልና መታመን በአንድ ሕዝብ መኖርና ከአንዱም ሕዝብ ወደ ሌላው በመተላለፍ የእግዚአብሔር መንግሥት ይስፋፋል። ይህም የሚሆነው ቤተ ክርስቲያን ስትመሠረትና በእውነተኛ አማኞችና ደቀ መዛሙርት ስትሞላ ነው።

የቤተ ክርስቲያን ከሕዝብ ወደ ሕዝብ መንቀሳቀስ የእግዚአብሔር መንግሥት መስፋት ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል።

ብዙ ቤተ ክርስቲያናት እኔ አባል የሆንሁባትን የአናባፕቲስት አብያት ክርስቲያናት ጨምሮ፣ ሙስሊሞች ትኩረት ከሚሰጡት የእግዚአብሔርን አንድነት ፈቃዱን መግለጽ አለባቸው። ለሚለው የሙስሊም እምነት ተመሳሳይ አቋም አላቸው። በአዲስ ኪዳን አገላለጽ ቀውሂድ ማለት አማኙ ማኅበረሰብ የመሲሑ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት የሆኑ ማለት ነው። አማኞች በመሲሑ መንገድ ሲጓዙ በአንድነት በኅብረት ራስን በመስጠት በእግዚአብሔር ፍቅር ይኖራሉ። ከላይ እንደ ተገለጸው ቤተ ክርስቲያን ለእግዚአብሔር መንግሥት መኖር እውነተኛ ምልክት ነች። ይህ ንስሓ የገባና ይቅር የተባለ፣ ለእግዚአብሔር የሚገዛ ማኅበረሰብ ነው። በጴጋው እና በመንፈስ ቅዱስ ኀይል የሚኖር ኅብረት ነው። የሚጸልይ ሕዝብ፣ የእግዚአብሔር ፈቃድና

መንግሥት፣ "ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁም በምድር" (ማቴዎስ 6÷9-13) ባለበት ስፍራ መሆንን የሚጠማ ሕዝብ ነው።

በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር መንግሥት ፍጻሜ ሁል ጊዜ መንግሥቱን ከሚቃወሙ ኀይላትና ግለሰቦች በተቃርኖ ነው። በመጨረሻው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሚገኘው አስደናቂው ራእይ፣ ድንት ስለሆነችው ዘላለማዊ ከተማ ብቻ ሳይሆን፣ መቤዠትን እምቢ ለሚሉም የፍርድ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶአል።

ንስሓ የማይገቡና ክፉዎች ከእግዚአብሔር ከተማ ውጪ ናቸው (ራእይ 21÷27፤ 22÷11:15)። ኢየሱስ፣ "ፍየሎች" የሆኑት ለደግ፣ ለተራበ፣ ለታሰረና ለታመመ እከብካቤ የማያደርጉ ሁሉ ለዲያቢሎስ ወደ ተዘጋጀው ወደ ዘላለም እሳት እንደሚጣሉ አስጠንቅቋል (ማቴዎስ 25÷31-46)። ይህ፣ እግዚአብሔር በመጨረሻው የፍርድ ሰዓት እንኳ የጽድቅን መንግሥት በማንም ላይ አስገድዶ እንደማይጭን የሚያስረዳ ነው። የእግዚአብሔርን መንግሥት የሚቃወሙና የእርሱን የመታረቅና የመቤዠት ጽኑ ጥሪውን የሚቃወሙ ፍርድ ይጠ ብቃቸዋል።

2002 ዓ.ም በበልግ ወቅት በኢራን በሺአይቶች መስጊድ የዐሥራ ሁለተኛው ኢማም ልደት ሲያከብሩ ለብዙ መቶ ጉብኤዎች ንግግር አድርጌ ነበር። ከላይ እንደገለጽሁት እነዚህ ሺአይቶች ዐሥራ ሁለተኛው ኢማም በታሪክ ፍጻሜ ከኢየሱስ ጋር ይመጣል ብለው ያምናሉ። የአካባቢው መስጊድ ኢማም ስለመሲሑ ኢየሱስ ዳግም ምጽአት እንድናገር ጋበዘኝ።

ይህንን ነበር ያካፈልኋቸው፣ "የመሲሑ አገልግሎት ለድኽችና ለጭቁኖች ተስፋ ነበር። ወደ እርሱ የመጡትን ሁሉ ፈውሷል። ሆኖም በምድር ላይ ፍትሕንና ሰላምን ለመመሥረት ተልእኮውን አልፈጸመም። ይህ ተልእኮ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ድርሻ ስለነበር ተልእኮውን የመቀጠል ኀላፊነት አለባቸው። ከእንስሳት ጋር የሚኖረን ግንኙነት እንኳን ለእግዚአብሔር ፍጥረት እና ለእያንዳንዳችን የምንሰጠው ትኩረት አመልካች መሆን አለበት"።

እነዚህ ጥረቶች ሁሉ ከንቱ እንዳይደሉ እምነት አለን፤ መሲሑ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለዘላለም ለመፈጸም አንድ ቀን ይመጣል፤ ሕዝቦች ሁሉም ያዩታል።
"ምንድን ነው የምናየው? የስቅለቱ ምልክት የሆኑትን የቈሰሉ እጆች ተዘርግተው እናያለን። ሁላችንን ሊያቅፈንና ሊቤዠን የሚፈልገውን የቈሰለውን መሲሕ ዐይኖች ሁሉ ያዩታል። ኀጢአታችን ኢየሱስን ምን እንዳደረገው ስናይ

ሁላችንም እንጸጸታለን (ራእይ 1÷7)። በእነዚህ በቁሰሉ እጆች እግዚአብሔር ምን ያህል እንደ ወደደን እናያለን። የእግዚአብሔር መንግሥት የሚመጣው በመቤዠታዊ ፍቅር ነው። ለተሰቀለውና ለተነሣው መሲሕ ታሪክን ወደ ትክክለኛ ፍጻሜ እንዲያመጣው ሥልጣንን ሰጥቶታል። መሲሑ ወደ ምድር ሲመለስ ፍጥረትን ሁሉ ይቤዠል ምክንያቱም አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ይሆናልና። የጽድቅና የሰላም መንግሥቱን ለዘላለም ይመሠረታል። እርሱን የሚወዱ ሁሉ ከእርሱ ጋር ለዘላለም ይገዛሉ (ራእይ 5÷9-10፤ 21÷1-5፤ 22÷1-5)።

ሁሉም የሙስሊም ማኅበረሰብ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን የታሪክን ፍጻሜ በንቃት ይጠብቃሉ። በሁለቱም ማኅበረሰቦች መሲሑ ኢየሱስ ታሪክን ወደ ድምዳሜ ለማምጣት ታላቅ አስተዋጽኦ አለው።

ብዙ ጊዜ በክርስትናና በእስልምና ጉዞ ላይ ሳለን፣ ኢየሱስ ልዩ በሆነ መንገድ ለእርሱ መገኘት እንድንቀበል ጽኑ ፍላጐቱ ነው። ሆኖም በመጨረሻው ዘመን የኢየሱስ ተልእኮ የሙስሊምና የክርስቲያኖች ተስፋ ለየትል ነው። እርሱ ያዋህዳል ያለያያልም። እርሱ ሥልጣኑን ሥራ ላይ የሚያውለው ክርስቲያኑንና ሙስሊሙን በሚያስደንቅ መንገድ ነው። የእርሱን የማያጸድጥ አብሮነት ወደ ጸር የሚያደርግ አንዳችም ነገር የለም። ይህ የሚሆነው ለምንድን ነው?

የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ

ሕዝቅኤል 47÷1-12፤ ራእይ 22÷1-7

የቁርአን ምንባብ

ሱራ 50÷16-45

የአስተዉሎትና የዉይይት ጥያቄዎች

1. የአዲስ ኪዳንንና የቁርአንን አማኒ ማኅበረሰብ የተልእኮ ግንዛቤ ያወዳድሩ።
2. ታሪክን በተመለከተ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ቅዱሳት መጻሕፍቶቻቸውን መሠረት በማድረግ የሚሰጡትን ትንታኔ ያወዳድሩ።
3. የመሲሑ የደግሞ ምጽአት ተልእኮ ከእስልምናና ከአዲስ ኪዳን አስተምህሮ አንጻር ያወዳድሩ።

4. ሰዎች "ከሥልጣኔ ጋር ስለሚደረግ ጦርነት" ሰፊ ሐሳብ አላቸው። የዚህ ሐሰብ መሠረቱ ምንድን ነው? ለዚህ ጉዳይ ቤተ ክርስቲያን ያላት መልስ ምን መሆን ይኖርበታል?
5. እያንዳንዱ ክርስቲያን ማኅበረሰብ ለተልእኮው አስተዋጽኦ የሚያደርግ ልዩ የሆነ የጸጋ ስጦታ አለው። የዳግም መጥምቃውያን ስጦታ ምንድን ነው? የካቶሊኮች ስጦታስ? የእንጨቌስጤ እንቅስቃሴ ያለባቸው ቤተ ክርስቲያናትስ?
6. የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ለቤተ ክርስቲያን የሚያበረክተው ስጦታ አለ? ሙስሊሙ ማኅበረሰብ ቤተ ክርስቲያን ይበልጥ ታማኝነቷን ጠብቃ እንድትኖር የሚጫወተው ሚና አለን?
7. ስለሙስሊሙ ማኅበረሰብ እርስዎን ያስደነቅዎት ነገር ምንድን ነው? በምን መንገድ ነው የእስልምናው አማራጭ የወንጌልን ትርጉም ለማብራራት የሚረዳን?
8. ስለ ቤተ ክርስቲያን ተልእኮ ያስደነቅዎ ነገር ምንድን ነው?

ማጠቃለያ ሐሳብ

የሙስሊሙ ማኅበረሰብም ሆነ ክርስቲያኖች፣ ቃለ እግዚአብሔርን በሕይወታቸውና በኑሮአቸው ተግባራዊ ለማድረግ ጽኑ ፍለጎት ያለቸው ሕዝቦች ናቸው። ሁለቱም ክፍሎች የእግዚአብሔርን ቃል እውነት፣ ለሰው ልጆች ሁሉ ያማሳወቅ ኀላፊነት እንዳለባቸው ያምናሉ።

የሙስሊሙ ማኅበረሰብ እግዚአብሔር ራሱን በሙላት የገለጠው፣ በዐረብኛ ቋንቋ ተጽፎ ከሰማይ ወደ ምድር በወረደው በእግዚአብሔር ቃል (በቁርአን) አማካይነት ነው የሚል አቋም ሲኖረው (ሱራ 12÷2)፣ ክርስቲያኖች ደግሞ፣ "ቃልም ሥጋ ሆነ ጸጋንና እውነትንም ተሞልቶ በእኛ ዐደረ፣ አንድ ልጁም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን" (ዮሐንስ 1÷14) የሚለው አስተምህሮ የድነት ሁሉ ማዕከል ነው በሮች ናቸው።

የሙስሊሞች ቀዳማይ ዐላማ ሕዝቦች ለእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዐላማ በመገዛት ወደሚገኘው ሰላም እንዲመጡ እንዲሁም የእያንዳንዱን የሰው ልጆች የሕይወት ክፍል ለእግዚአብሔር ፈቃድ ይገዛ ዘንድ፣ ለሕዝቦች ሁሉ ታማኝ ምስክር መሆንና ሰዎች ሁሉ ለእስልምና ሃይማኖት እንዲገዙ ጥሪ ማድረግ ነው።

የክርስቲያኖች ቀዳማይ ዐላማ ደግሞ፣ እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት በሙላት መገለጡን ማወጅ ነው። ይህም ኢየሱስ ሕፃን ሆኖ በቤተ ልሔም በበረት ውስጥ መወለዱን፣ በግብፅ ስደተኛ መሆኑን፣ በናዝሬት ይኖር የነበረ አናጢ መሆኑን፣ ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወረ ማስተማሩን፣ በሁለት ሌቦች መካከል መሰቀሉን፣ ሞትን ድል አድርጎ የተነሣ መሲሕ መሆኑን እንዲሁም ፈርተው ለነበሩት ደቀ መዛሙርቱ የሰላምን እስትንፋስ እፍ አንዳለባቸው መመስከር ነው። የቤተ ክርስቲያንም ቀዳማይ ዐላማ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ለመታረቅ ምክንያት የሆናትን ይህን መሲሕ ማክበር/ማወደስ ነው።

የዓለማችን በኹከት በምትናጥበት በዚህ ታሪካዊ ወቅት፣ ክርስቲያኑ ማኅበረሰብ በእነዚህ ቦታዎች ሁሉ በመገኘት፣ የእግዚአብሔር መንግሥት በወታደራዊ ጡንቻ እንደማትመሠረት ወይም በግዴለሽነት እጅን አጣጥፎ በመቀመጥ እንደማትመጣ፣ ነገር ግን ጉልጉታ በመባል በሚታወቀው ኩረብታ ስፍራ ላይ

በተሰቀለው መሲሕ አማካይነት እውን መሆን እንደምትችል ማወጅ ይኖርባቸዋል፣ "እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን . . . የእግዚአብሔር ኀይልና የእግዚአብሔር ጥበብ የሆነው ክርስቶስ ነው" (1ቆሮንቶስ 1+23-24)።

የተሰቀለውንና ሞትን ድል አድርጎ የተነሣውን መሲሕ እግዚአብሔር እንዳከበረው፣ "ከስም ሁሉ በላይ የሆነውን ስም" (ፊልጵስዩስ 2+9) እንደ ሰጠው የሚያምኑ ማኅበረሰቦች፣ በመከራ ውስጥ የሚገለጥ ፍቅር ክፉትን ድል የመንሣት ኀይል እንዳለው ማወቅ እንዲሁም ይህ እውነት በሕይወታቸው እውን እንዲሆን መፍቀድ ይኖርባቸዋል። ይህን እውነት ማዕከል ያደረገ ምስክርነት (እማኝነት) እጅግ አስደናቂ እንዲሁም ትልቅ ውጤት እንደሚያመጣ አምናለሁ። በመሲሑ በክርስቶስ መንፈስ ለማገልገል ፍለጎት ያላቸው አማኞች፣ ሙስሊሞችን ጨምሮ በሕዝቦች ሁሉ ዘንድ ዕርቀ ሰላምን የማውረድና ፈውስን የማምጣት ታላቅ የሆነ ከእሱት እንዳላቸው አልጠራጠርም።

ሙዳየ ቃላት

ደበረብኛ ቃላት

አባሲድ:— የአባሲድ ካሊፋቶች ከስምንተኛው እስከ ዐሥራ ሦስተኛው ክፍለ ዘመን በሉት ጊዜያት ባግዳድን መናገሻ ከተማቸው በማድረግ ይመሩ ነበር። ይህ ወቅት የሙስሊሞች ወርቃማ ዘመን በመባል ይታወቃል።

አብዲ:— የእግዚአብሔር ባሪያ ወይም አገልጋይ ማለት ነው።

አዛን:— የጸሎት (የሰላት) ጥሪ ማለት ነው።

አህል አል-ኪታብ:— የቃሉ ጥሬ ትርጉም፣ "የመጽሐፉ ሰዎች" ማለት ሲሆን፣ ይህም ክርስቲያኖችንና አይሁዶችን የሚያመለክት መጠሪያ ነው።

አላህ:— በዐረብኛ እግዚአብሔር ማለት ነው (በዐረብኛ የእግዚአብሔር የተጸውዖ/የመጠሪያ ስም ነው)።

አያ/አያት:— ምልክት/ምልክቶች ማለት ሲሆን፣ ፍጥረት ለእግዚአብሔር መኖር ምልክት እንደ ሆነ ሁሉ፣ እያንዳንዱም የቁርአን ጥቅስ ለእግዚአብሔር አልሆት/መኖር ምልክት ነው።

በረካ:— ብረክት ማለት ነው።

ቢዳህ:— የተከለከለ ለውጥ ወይም አዲስ አሠራር ማለት ነው።

ቡራቅ:— መሐመድን በአንድ ምሽት ተአምራዊ በሆነ መንገድ ከመካ ወደ ኢየሩሳሌም ይዛቸው የሄደች ክንፍ ያላት ፈረስ ነች።

ዳር አል-ሐርብ:— በእስልምና አስተዳደር ሥር ያልዋለ የጦርነት ቀጣና የሚጠራብት መጠሪያ ነው።

ዳር አል-ኢስላም:— በእስልምና ቀጥተር ሥር የዋለ እስላማዊ አካባቢ የሚጠራብት ስም ነው።

ዳዕዋህ:— ሰዎች የእስልምናን ሃይማኖት እንዲቀበሉ የሚደረግ ጥሪ ነው።

ዳውላህ:— በአንድ አካባቢ የሙስሊሞች የፖለቲካ የበላይነት እንዲሰፍን ማድረግ ወይም ማረጋገጥ ማለት ነው።

ዚክር:— ትውስታ ማለት ነው። ሱፊ ሙስሊሞች በጸሎት ጊዜ የአላህን ስም ለማወደስ/ለማውሳት ዝማሬ ያቀርባሉ።

ዚሚ፡— በሙስሊም አስተዳደር ሥር የደኅንነት ከለላ የተሰጣቸው የማኅበረሰብ ክፍሎችን የሚያመለክት ስያሜ ሲሆን፣ የዚህ መብት ተጠቃሚዎች ክርስቲያኖችና አይሁዶች ናቸው።

ዲን፡— ሃይማኖት ማለት ነው።

ዱአ፡— መደበኛ በሆነው በሃይማኖታዊ ጸሎት (ሰላት) ውስጥ የማይመደብ፣ በወረብኛም ሆነ በሌሎች ቋንቋዎች መቅረብ የሚችል፣ ሙስሊሞች እግዚአብሔርን ለመማጸን በእግዚአብሔር ፊት የሚያቀርቡት የጸሎት ዐይነት ነው።

ፋናስ፡— ሱፊ ሙስሊሞች አምላክ ዘንድ ለመቅረብ ሲፈልጉ የሚያካሂዱት ጉዞ ነው።

ፋቲሐ፡— የቁርአን የመክፈቻ ጸሎት ሲሆን፣ ሙስሊሞች ሰላት ሲሰግዱ በእያንዳንዱ ስግደት ይደጋገሙታል፤ ፋቲሐ የቁርአን የመጀመሪያው ምዕራፍ መጠሪያም ነው።

ፋትዋ፡— ሕጋዊ በሆነ የሙስሊም ባለሥልጣን የሚወሰን ሕጋዊ ውሳኔ ነው።

ፊቅህ፡— የእስልምና ሕግ ሳይንስ።

ሐድ፡— በተግባር ላይ ካልዋሉ ቅጣት የሚያስከትሉ የተከለከሉ ገደቦች።

ሐዲስ፡— የነቢዩ መሐመድን ንግግሮች፣ አባባሎችና የኑሮ ዘይቤ የያዙ መጻሕፍት መጠሪያ ነው። እነዚህ መጻሕፍት ከቁርአን ቀጥሎ ለሃይማኖታዊ መመሪያነት ያገለግላሉ።

ሐጅ፡— በዓመት አንድ ጊዜ ወደ መካ የሚደረግ ሃይማኖታዊ ጉዞ ነው። የሐጅ ጉዞ ከአምስቱ የእስልምና ሃይማኖታዊ መሠረቶች ውስጥ አንዱ ነው።

ሐላል፡— የተፈቀዱ ተግባራት።

ሐኒፍ፡— ከእስልምና በፊት የአብርሃምን አምላክ ያመልኩ የነበሩ ዐረቦች መጠሪያ ነው።

ሐራም፡— የተከለከሉ ተግባራት።

ሒጅራ፡— መሐመድ በ622 ዓ.ም ከመካ ወደ መዲና ያደረጉት ጉዞ መጠሪያ ሲሆን፣ ይህም ለእስልምና የዘመን አቆጣጠር መጀመሪያ ነው።

ኢብሊስ፡— የክፋት ሁሉ ምንጭ የሆነው የሰይጣን መጠሪያ ነው።

ኢድ አል-አድሐ፡— በሐጅ ጉዞ ሥነ ሥርዐት ወቅት በመጨረሻዎቹ አራት ቀናት የሚከበር በዓል ነው። በዚህ በዓል ወቅት ሙስሊሙ አብርሃም

ልጁን እስማኤልን መሥዋዕት አድርጎ በእግዚአብሔር ፊት በማቅረብ ላይ እያለ፣ እግዚአብሔር በእስማኤል ፈንታ የመሥዋዕቱን በግ አዘጋጀ የሚለውን ታሪክ የሚዘክር ከብረ በዓል ነው።

ኢድ አል-ፈጥር፡— ሙስሊሞች በረመዳን ጾም ማብቂያ ጊዜ ለሦስት ቀናት የሚያከብሩት በዓል ሲሆን፣ ቁርአን ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጠ ስጦታ መሆኑንም ያስባሉ።

ኢህራም፡— የሐጂ ተጓዦች ራሳቸውን ለሐጂ ጉዞ መለየታቸው።

ኢጃዝ፡— ቁርአን በተአምራዊ ሁኔታ የተገለጠ መለኮታዊ ቃል ስለሆነ፣ እርሱን የሚመስል ቁርአን ማንንም መጻፍ ወይም መፍጠር አይችልም፣ የሚል አስተምህሮ ነው።

ኢጅማዕ፡— የእስልምናን ሥርዐተ አምልኮዎችና ሕጎችን በተመለከተ ስምምነት ላይ መድረስ ማለት ነው።

ኢጅቲሐድ፡— የቁርአንን ትርጉም ለማብራራትና በሕይወት ተግባራዊ ለማድረግ የግል ጥረትንና ዕውቀትን መጠቀም ማለት ነው።

ኢማም፡— የጸሎት መሪ ማለት ነው። በሺአ ሙስሊሞች ዘንድ የማኅበረሰቡም መሪ ኢማም ተብሎ ይጠራል።

ኢማን፡— እምነት።

ኢንጂል፡— ወንጌል ማለትም መልካም የምሥራች ማለት ነው። በመሲሑ በኢየሱስ በኩል የተገለጠው የወንጌል መልእክት ማለት ነው።

ኢሳ፡— በቁርአን ለኢየሱስ የተሰጠ የመጠሪያ ስም።

እስልምና፡— መሐመድ ያስተማረው ሃይማኖት መጠሪያ ሲሆን፣ የቃሉ ጥሬ ትርጉም ለእግዚአብሔር ፈቃድ መገዛት ወይም ሰላም ማለት ነው። የእስልምና እምነት ተከታዮች ደግሞ ሙስሊሞች ተብለው ይጠራሉ።

ኢስማ፡— መሐመድ ጎጢአት የለባቸውም የሚለው አስተምህሮ መጠሪያ።

ኢስናድ፡— በሐዲስ ውስጥ ከሚገኙ ሁለት ክፍሎች ውስጥ አንዱ ሲሆን፣ ነቢዩ መሐመድ የተናገሯቸው ንግግሮች በጽሑፍ እስከ ተዘጋጁበት ጊዜ ድረስ በአፈ ታሪክ መልክ ያስተላለፉትን የሰዎች ስም ዝርዝር የያዘው ክፍል ነው።

ኢስራዕ፡— መሐመድ በአንድ ምሽት ከመካ ወደ ኢየሩሳሌም ያደረጉት ተአምራዊ ጉዞ መጠሪያ ነው።

ጃሂሊያ፡— ከእስልምና ሃይማኖት መጀመር በፊት በዐረብያ የነበረውን የጨለማ ዘመን የሚያመለክት ቃል ነው።

ጅሐድ:— የአላህን ፈቃድ በመከተል የእስልምናን እምነት ከጥቃት ለመጠበቅ የሚካሄደውን ትግል/ጦርነት የሚያመለክት ቃል ነው። ትግሉ የእስልምናን ሃይማኖት ካልተቀበሉ ወይም ከሰይጣን ወይም ደግሞ ከራስ ነፍስ ጋር የሚደረግ ትግል ሊሆን ይችላል። አንዳንዴም ጅሐድ እንደ ስድስተኛ የእስልምና ሃይማኖት መሠረታዊ ሕግ ተደርጎ ይቆጠራል።

ጂኒ:— መንፈስ ማለት ሲሆን፣ ርኩሳንንም ሆነ ቅዱሳን መናፍስትን የሚያመለክት ቃል ነው።

ካዕባ:— በመካ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቤት መጠሪያ ሲሆን፣ ቅዱስ የሆነው ጥቁር ድንጋይ ያለበትን ስፍራ ሁሉ ያካትታል።

ኸሊፋ:— ሁሉም ሕዝብ በምድር ላይ የእግዚአብሔር ወኪል/ኸሊፋ ሆኖ የማገልገል ኀላፊነት አለበት። እንዲሁም ኸሊፋ ማለት ከመሐመድ ሞት በኋላ የሙስሊሙን ማኅበረሰብ የሚመራው መሪ የሚጠራበት ስም ሆኖ ያገለግላል።

ሚህራብ:— በመስጊድ ውስጥ የሰላት አቅጣጫን የሚያሳይ ቦታ ነው።

ሚዕራጅ:— መሐመድ ሙስሊሞች በቀን ምን ያህል ጊዜ መስገድ እንዳለባቸው ከእግዚአብሔር ዘንድ መመሪያን ለመቀበል ወደ ሰማይ ያደረጉት ጉዞ ነው።

ሙስሊም:— የእስልምና እምነት ተከታይ እንዲሁም በአላህ የሚያምን ሰው መጠሪያ ነው።

ነቢይ:— ከእግዚአብሔር የተላከ ማለት ነው።

ቀድር:— የእግዚአብሔር ቅድመ ውሳኔ ማለት ነው።

ቃዲ:— የሙስሊሞችን ሕግ ማለትም ሸሪአን የሚተረጉም ዳኛ ማለት ነው።

ቂብላ:— ሙስሊሞች ጸሎት የሚያደርሱበት አቅጣጫ።

ቂያስ:— ስለ እስልምና ሕጉች ውሳኔ ለማሳለፍ ይረዳ ዘንድ በቁርአን ወይም በሐዲስ ውስጥ የተገለጡትን ምሳሌዎች በመጠቀም መወሰን ማለት ነው።

ረከአ:— በስግደት (በሰላት) ሰዓት ለስግደት መቆምን፣ መጉንበስንና መንበርከክን የሚያጠቃልል ሥርዐተ ስግደት ነው።

ረሱል:— የእግዚአብሔር መልእክተኛ/ነቢይ እንዲሁም ቅዱስ ቃሉን የሚገልጥ ሰው።

ሰላት:— በቀን አምስት ጊዜ የሚሰገድ ሃይማኖታዊ ጸሎት ነው። እንዲሁም በስግደቱ ጊዜ የአማኙ ሕይወት አጠቃላይ ለአላህ መገዛቱን በአካላዊ እንቅስቃሴ ይገለጣል።

ሰውም:— በረመዳን ወር የሚጸም ጾም ነው።

ሸሀዳ:— ከአላህ በቀር አምላክ የለም፣ እንዲሁም መሐመድ የአላህ መልእክተኛ ናቸው በማለት መመስከር።

ሸሪአ:— በቁርአን፣ ከሐዲስ፣ ከኢጅማና ከቂያስ የተዘጋጀ የእስልምና እምነት መተዳደሪያ ሕግ።

ሺአ:— ከእስልምና ቡድኖች አንዱ ሲሆን፣ ሺአዎች የሙስሊሙን ማኅበረሰብ መምራት ያለባቸው የመሐመድ የአጉት ልጅ የሆነው አሊ ቢን አቡ ጣሊብና የእርሱ ዘሮች ናቸው የሚል እምነት አላቸው። በዓለም ካለው የሙስሊም ቁጥር ከመቶ አሸ ዐሥር እጅ የሚሆኑት ሺአ ሙስሊሞች ሲሆኑ በብዛት የሚገኙትም በኢራን አገር ነው።

ሽርክ:— ለእግዚአብሔር አጋር በመፈለግ ለእግዚአብሔር አቻና እኩያ አለው ማለት ሲሆን፣ ይህ ዐይነቱን ኀጢአት የፈጸመ ሰው ለኀጢአቱ ሥርየት አያገኝም።

ሹራ:— ወደ ውሳኔ የሚያደርስ ምክክር

ሲሲሳ:— የሱፊ የጸሎት ሰዎች መንፈሳዊ ምሥጢራት የሚያገኙበት የመንፈሳዊ ሥልጣን ቀለበት/ዑደት ነው።

ሱፊ:— ከእስልምና ቡድኖች መካል ከእግዚአብሔር ጋር መለኮታዊ ኅብረት ለማድረግ ፍላጎት ያላቸው ክፍሎች።

ሱና:— የነቢዩ መሐመድ መንገድ።

ሱኒ:— ከሺአ ሙስሊሞች ጋር ሲነጻጸሩ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የኦርቶዶክስ እስላም ክፍሎች ናቸው።

ሱራ:— የቁርአን ምዕራፍ።

ተከቢር:— አላህ ትልቅ ነው (አላሁ አክበር) ብሎ መናገር።

ጣሪቃ:— የሱፊ ሙስሊሞች አንድ ክፍል።

ተውራት:— ለሙሴ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጠው መልእክት (መጽሐፍ) ተውራት በመባል ይጠራል። ሙስሊሞች ተውራት ክርስቲያኖች ቶራህ የሚሏቸው አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት (ብሔረ አሪት) ናቸው። ቁርአን፣ ተውራት የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ ያረጋግጣል።

ቶውሂድ:— የእግዚአብሔር አንድነትና ፈቃድ ማለት ነው።

ኡስማ:— የእስልምና ሕግ ምሁራን።

ኡማያዶች:— የመጀመሪያዎቹ ካሊፋቶች ሲሆኑ ከ661-750 ዓ.ም የሙስሊሙን ማኅበረሰብ መርተዋል።

ኡማ:— የሙስሊም ማኅበረሰብ።

ወሐቢያ:— በ1787 ዓ.ም የሞተው የዐረብ ተሐድሶ መሪ የኢብን አብድ አል-ወሐብ ደቀ መዛሙርት መጠሪያ ነው። ይህም የተሐድሶ እንቅስቃሴ በሳውዲ መንግሥት የሚደገፍና የሚደራጅ ነው። በዚህ ዘመን ባለው በዓለም ዐቀፍ የእስልምና እንቅስቃሴ ላይ ጉልህ ስፍራ አለው።

ወሲ/ኸወሲያ:— የእግዚአብሔር ጓደኛ ወይም ባልንጀሮች ማለት ነው። ቅዱሳን ሰዎች በዚህ ስም ይጠራሉ። ይህ አመለካከት ለሱፊ ሙስሊሞች እምነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው።

ዘቡር:— ሙስሊሞች ለዳዊት የተሰጠ መልእክት ወይም መዝሙረ ዳዊት ነው ይላሉ።

ዘካት:— ምጽዋት መስጠት፣ ከእስልምና አምስቱ ሃይማኖታዊ ትእዛዛት መካከል አንዱ

ዘምዘም:— ከመካ መስጊድ አጠገብ የሚገኝ ጉድጓድ ሲሆን፣ አጋር ለተጠማው ልጅዋ ለእስማኤል ከዚህ ጉድጓድ ውሃ ቀድታ እንዳጠጣ ጣችው ይታመናል።

የክርስትና ቃላቶች

አናባኘቲስት:— ከወራሪ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ አውሮፓ ክርስቲያኖች መካከል መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናት የተጀመረ እንቅስቃሴ ነው። መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን መለየት እንዳለባቸው እንዲሁም የውትድርናን አገልግሎት መስጠት ከክርስቶስ አስተምህሮ ጋር የሚቃረኑ ተግባራት እንደ ሆኑ ያምናሉ። የሕፃናትን ጥምቀት ስለሚቃወሙ፣ ሰዎች የውሃ ጥምቀት መውሰድ ያለባቸው በክርስቶስ አምነው ሲለወጡና ለመለወጣቸው ምስክርነት ሲሰጡ ብቻ ነው የሚል አቋም አላቸው።

ሐዋርያዊ ተዋረድ:— በካቶሊክና በኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት የጳጳሳት ሥልጣን መሠረቱ ከኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት በተዋረድ በመጣው መንፈሳዊ ሥልጣን እንደ ሆነ ይታመናል። በኤፒስኮፓል ቤተ ክርስቲያንም ተመሳሳይ የእምነት አቋም አለ።

ሐዋርያት:— የመጀመሪያዎቹ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሲሆኑ አብዛኞቹ በአካል ሥጋ ከክርስቶስ ጋር የነበሩ ናቸው።

ዕርገት:— ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት ከተነሣ ከአርባ ቀን በኋላ ደቀ መዛሙርቱ እያዩት ወደ ሰማይ ዐረገ። ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት ደቀ መዛሙርቱ ወደ ዓለም ሁሉ እንዲሄዱና ወንጌል እንዲሰብኩ አዞአቸዋል።

ሥርዐት:— ለጎጢአት ይቅርታ የሚቀርብ መሥዋዕት

ጥምቀት:— አንድ ሰው ከክርስቲያኑ ማኅበረሰብ ጋር መቀላቀሉን በውሃ በመጠመቅ የሚያሳየው ምልክት። የዐዋቂዎችን ጥምቀት የሚቀበሉ አብያተ ክርስቲያናት የሚያጠምቁት አንድ ሰው ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ አምኖ ሲቀበል ብቻ ነው። ነገር ግን በሕፃናት ጥምቀት የማያምኑ አብያተ ክርስቲያናት፣ ጥምቀት የሰው ልጆች ይቅርታ የሚያገኝበትና ሕፃናትን ጨምሮ ሰዎችን ሁሉ ወደ ቤተ ክርስቲያን ኅብረት የሚጠራው የእግዚአብሔር ጸጋ ተምሳሌት እንደ ሆነ ያምናሉ።

ጳጳስ:— የቤተ ክርስቲያናት ኅላፊነት የተሰጠው የቤተ ክርስቲያን መሪ ማለት ነው።

ካቶሊክ:— የቃሉ ጥሬ ትርጉም ዓለም ዐቀፋዊ ቤተ ክርስቲያን ማለት ሲሆን፣ በዓለም ከአንድ ቢሊየን በላይ ምዕመን ያሳት የታሳቅዋ የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን መጠሪያም ነው።

ክርስቶስ:— ክርስቶስ ማለት መሲሕ ወይም የተቀባ ማለት ነው። ክርስቶስ የሚለው ቃል ግሪክ ሲሆን ከአማርኛው ስያሜ ጋር አንድ ዐይነት ነው።

የክርስቲያናዊ ግዛት:— በምዕራቡ ዓለም ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት አንድነት ፈጥረው ነበር። ይህም ዐይነቱ የቤተ ክርስቲያንና የመንግሥት ጥምረት በእስልምናው ሃይማኖት ዳር አል-ኢስላም በመባል ከሚጠራው ሐሳብ ጋር የሚመሳሰል ነው።

ቤተ ክርስቲያን:— በኢየሱስ ክርስቶስ መሲሕነትና ጌትነት ያመኑ የክርስቲያኖች ኅብረት።

የኒቂያ ጉባኤ:— በ325 ዓ.ም ስለክርስቶስ ማንነት ክርስቲያኖች ምን ዐይነት እምነት ሊኖራቸው እንደሚገባና በሌሎች ርእሰ ጉዳዮች ዙሪያ ለመምከር ኒቂያ በተባለ ስፍራ የተደረገ የቤተ ክርስቲያን ጉባኤ ነው። በስብሰባው ማጠቃለያ ላይ የእምነት አቋም በማውጣት የተጠናቀቀ ሲሆን የካቶሊክ፣ የኦርቶዶክስና የኾሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ይህን መሠረተ እምነት ከሙሉ ልባቸው ይቀበላሉ።

ቁስጠንጢኖስ:— የምዕራብ ሮማ ግዛት መሪና በ313 ዓ.ም ክርስትናን በሮም ግዛት ውስጥ ሕጋዊ ሃይማኖት እንዲሆን ያደረገ መሪ ነው። መንግሥትና ቤተ ክርስቲያንን ለማጣመር የታገለ ሰው ነው።

ቃል ኪዳን:— በሁለት ወገኖች መካከል የሚደረግ ስምምነት ነው። እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር የቃል ኪዳን ግንኙነት ለማድረግና ቃል ኪዳኑን የሚጠብቁትን ሰዎች ለመባረክ ተስፋ ይሰጣል።

ዲያቆን:— ጳጳሱን ወይም ካህኑን የሚያግዝ አገልጋይ ነው።

ደቀ መዝሙር:— ተከታይ ወይም ተማሪ ማለት ሲሆን፣ ኢየሱስን የሚከተሉና አብረውት የሚያገለግሉ ዐሥራ ሁለት ደቀ መዛሙርት ነበሩት።

ኤል/ኤሎሂም:— አብርሃም እግዚአብሔርን ይጠራበት የነበረ ስም ነው። አላህ የሚለው ዐረብኛ የእግዚአብሔር ስም፣ ከዕብራይስጡ ኤል/ኤሎሂም ከሚለው የእግዚአብሔር ስም ጋር ተመሳሳይ ነው።

ቅዱስ ቁርባን/የጌታ ራት:— ከመሲሑ ከኢየሱስ ጋር ባለን ኅብረት በኩል ስለተገለጠልን የእግዚአብሔር ጸጋ ለእግዚአብሔር ክብር የምንሰጥበት ሃይማኖታዊ ሥርዐት ነው። አብዛኞቹ የክርስቲያን ጉባኤዎች በየጊዜው የክርስቶስን ሕይወት፣ ስቅለትና ትንሣኤ መታሰቢያ ጻቦና የወይን ጭማቂ በጋራ ይወስዳሉ።

ሽማግሌ:— ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የማኅበረ ምዕመን መሪ ወይም አገልጋይ።

መልእክቶች:— የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያት ለቤተ ክርስቲያናት የጻፉዋቸው ደብዳቤዎች።

ምጽአት:— ወደ ፊት ክርስቶስ ዳግም ተመልሶ ወደዚህች ምድር ሲመጣ፣ የመጨረሻ ፍርድ የሚሰጥበትና፣ የእግዚአብሔር መንግሥት ለዘላለም የሚመሠረትበት ጊዜ ነው።

የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች:— ክርስቶስን በማመን አዲስ ፍጥረት የሆነው አማኝ በሕይወቱ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎች ይታያሉ። ለምሳሌ ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ወዘተ።

ኤድን ገነት:— አዳምና ሔዋን በኀጢአት ከመውደቃቸው በፊት ይኖሩበት የነበረ ስፍራ።

ወንጌል:— ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ሕይወት፣ አገልግሎት፣ ትምህርት፣ ሞትና ትንሣኤ የሚተርክ መልካም የምሥራች ማለት ነው።

ወንጌላት:— በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስለመሲሑ ኢየሱስ ሕይወትና አገልግሎት የሚተርኩት አራቱ ወንጌላት ማለትም ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስና ዮሐንስ ወንጌልን የሚያመለክት ቃል ነው።

ታላቁ ተልእኮ:— ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት ለደቀ መዛሙርቱ ወደ ዓለም ሁሉ እንዲሄዱና ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ እንዲሰብኩ የሰጣቸው የመጨረሻው ትእዛዝ።

መንፈስ ቅዱስ:— የእግዚአብሔር መንፈስ ሲሆን፣ የመሲሑ ኢየሱስ አገልግሎት ቀጣይነት እንዲኖረው፣ የሰዎች ልብ ለእውነት ምላሽ እንዲሰጥ በማዘጋጀት እንዲሁም የክርስቶስን አስተምህሮ መሠረታቸው አድርገው ለመኖር የሚፈልጉትን ሰዎች ጎይል በመስጠት ይሠራል።

ያስና የሚኖር:— እግዚአብሔር ለሙሴ በኮሬብ ተራራ በእሳት ነበልባል በእሾህ ቍጥቋጦ ውስጥ ሲገለጥለት ራሱን ያሳወቀበት ስም ነው። የነገረ መለኮት ምሁራን ይህ ስም የዕብራይስጡ ያህዌህ የሚለውን የእግዚአብሔር ስም ይገልጻል ይላሉ።

አማኑኤል:— እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ማለት ሲሆን፣ መልአኩ ገብርኤል ለድንግል ማርያም ስለኢየሱስ መወለድ ሲያበስርላት የኢየሱስ ስም አማኑኤል እንደሚባል ተናግሮአት ነበር።

ተስግም (ምስጢረ ሥጋዌ):— ሥጋ መልበስ ማለት ነው። በድንግል ማርያም ልጅ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እግዚአብሔር በሙላት ተገልጠአል የሚለውን መሠረተ እምነት ያመለክታል።

የኢየሩሳሌም ጉባኤ:— የቀድሞ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከአሕዛብ ወገን የሆኑ አማኞች ከአይሁድ ባህል እና ከብሉይ ኪዳን ሥርዐቶች አንጻር እንዴት መኖር እንዳለባቸው ውሳኔ ያሳለፉ ስብሰባ ነው። በስብሰባው ፍጻሜ አሕዛብ የራሳቸውን ባህል ጠብቀው መኖር እንደሚችሉ ነገር ግን ከአንዳንድ መጥፎ ከሆኑ ተግባራት እንዲታቀቡ ውሳኔ አሳልፎአል። ስለስብሰባው አጠቃላይ ገጽታ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 15 ላይ ተጠቅሶአል።

ኢየሱስ:— የመሲሑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስም ነው። ትርጕሙም፣ "እግዚአብሔር ያድናል" ማለት ነው።

ዮሴፍ:— የኢየሱስ እናት የሆነችውን ድንግል ማርያምን ያገባ ሰው ነው። ዮሴፍ አናጺ የነበረ ሲሆን፣ ኢየሱስም በመጀመሪያዎቹ ዘመናት የአናጺነት ሥራ ሳይሠራ አይቀርም።

የእግዚአብሔር መንግሥት:— የእግዚአብሔር አስተዳደር ያለበት ቦታ ሁሉ የእግዚአብሔር መንግሥት ነው። ክርስቲያኖች ክርስቶስ በሰው ታሪክ ውስጥ የእግዚአብሔር መንግሥት በሙላት ተገልጠአል ብለው ያምናሉ። የእግዚአብሔር መንግሥት አሁን ተጀምሮአል ነገር ግን የሚፈጸመው በክርስቶስ ምጽአት ነው።

የእግዚአብሔር በግ:— ከመሲሑ ከኢየሱስ ስሞች ውስጥ አንዱ ነው። ይህም ክርስቶስ በመስቀል ላይ ለሰዎች ሁሉ ኀጢአት መሥዋዕት ሆኖ መሞቱን የሚያመለክት ሲሆን፣ ኢየሱስ የእግዚአብሔር በግ ነው

ከሚለው ትርጓሜ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ሥርዐቶች በብዙ ሃይማኖቶች ውስጥ አሉ። ምክንያቱም ለአብርሃም ልጅ ምትክ እንዲሆን የመሥዋዕቱ በግ እንደ ተሰጠ ሁሉ፣ ለሰዎች ምትክ ይሆኑ ዘንድ እንስሳት መሥዋዕት ይደረጋሉ። ክርስቲያኖች ሰው ሁሉ ኀጢአተኛ ስለሆነ ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች እንደ ሆነ፣ ነገር ግን ኢየሱስ የእግዚአብሔር በግ በእኛ ፈንታ ስለታረደ ከፍርድ ነጻ ሆኖ ምሕረትን እንደሚያገኝ ያምናሉ።

መሲሕ፡— በእግዚአብሔር የተቀባ ማለት ነው። ኢየሱስ መሲሕ ነው።

የሲና ተራራ፡— እግዚአብሔር ዐሥርቱን ትእዛዛት ለእስራኤል የገለጠበትና የቃል ኪዳን ሕዝቡ እንዲሆኑ ጥሪ ያደረገበት ተራራ ነው።

ናዝሬት፡— ክርስቶስ የልጅነት ዘመኑን የኖረበት ስፍራ ነው።

አዲስ ኪዳን፡— የመጽሐፍ ቅዱስ ሁለተኛው ግማሽ ክፍልና ከመሲሑ ኢየሱስ መወለድ በኋላ የተጻፈ መጽሐፍ ነው።

ብሉይ ኪዳን፡— የመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያ ግማሽና ከመሲሑ ከኢየሱስ ልደት በፊት የተጻፈ መጽሐፍ ነው።

ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን፡— ከሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጋር በብዙ መልክ የምትመሳሰል ቤተ ክርስቲያን ስትሆን፣ ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ጋር የነበራትን ኅብረት ያቆመችው በ1054 ዓ.ም ነው። አብዛኛዎቹ የምሥራቋ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያናትና የምዕራብ አውሮፓ ፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያናት የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያናት ተብለው ይጠራሉ።

ፋሲካ፡— በፈርዖን ዘመን እግዚአብሔር በጽኑ ክንዱ እስራኤላውያንን ከግብፅ ባርነት ነጻ ያወጣበትን ታሪክ ለማሰብ አይሁዶች የሚያከብሩት በዓል ነው። ሙሴ የእስራኤልን ሕዝብ እየመራ ከግብፅ ምድር ሲወጣ እግዚአብሔር ተአምራትን እየሠራ ሕዝቡን ነጻ አውጥቶአል። እስራኤላውያን ነጻ የወጡበት ምሽት ፋሲካ ተብሎ ይጠራል። ምክንያቱም በዚያች ምሽት የሞት መልአክ የግብፃውያንን የበኩር ልጆች ሁሉ ሲገድል፣ የበግ ደም በመቃኑ ላይ የተቀባው የእስራኤላውያኖቹ ቤት ግን ከዚህ ሞት ማምለጥ ችሏል።

ጳውሎስ፡— የትንሣኤው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እስኪገናኘው ድረስ ክርስቲያኖችን የሚያሳድድ ሰው ነበር። በክርስቶስ ኢየሱስ ከአመነ በኋላ የቤተ ክርስቲያን መሪና ከአይሁድ ወገን ያልሆኑ ሰዎች የመሲሑን መንገድ እንዲከተሉ በብርቱ ይፈልግ የነበረ ሐዋርያ ነው። በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያሉት በርካታ መልእክቶች ጳውሎስ የጻፋቸው ናቸው።

ጴንጠቆስጤ፡— እህል በሚሰበሰብበት ጊዜ የሚከበር የአይሁድ በዓል ሲሆን፣ ክርስቶስ ከሙታን ከተነሣ በኋላ በዚሁ በዓል ቀን መንፈስ ቅዱስ በታላቅ ኀይል በክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ላይ ወረደ፤ ቤተ ክርስቲያንም በዚያች ቀን ተመሠረተች።

ጴጥሮስ፡— የክርስቶስ ደቀ መዝሙርና ቍልፍ ከሆኑት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ውስጥ አንዱ ነው። ቤተ ክርስቲያንን አይሁድ ወዳልሆኑት ሕዝቦች በማስፋፋቱ ሂደት ውስጥ ትልቅ ሚና ተጫውቶአል።

የእስራኤል ሕዝብ፡— በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ሕዝብ እነርሱም የአብርሃምና የይስሐቅ ዘሮች ናቸው።

ሲቀ ጳጳስ፡— የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን እንዲሁም የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን መሪ።

ነቢይ፡— የእግዚአብሔርን ቃል የሚናገርና ሕዝቡን ወደ ንስሓ የሚጠራ በእግዚአብሔር የተላከ ሰው ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን እግዚአብሔር ነቢያትን ቅዱሳት መጻሕፍትን እንዲጽፉ በማነሣሣት መገለጥን ይሰጣቸው ነበር።

ኘሮቴስታንት፡— በ16ኛው ክፍለ ዘመን ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ተለይቶ የወጣ የክርስቲያኖች ቡድን ነው። ኘሮቴስታንቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣንና ድነት በእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ በነጻ/በጸጋ የተሰጠ ስጦታ ነው በሚሉት ርእሰ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ይሰጣሉ።

መዝሙራት፡— ከብሉይ ኪዳን መጻሕፍት መካከል በግጥም የቀረበ መጽሐፍ ነው። ዳዊት እነዚህን ግጥሞች ከጻፋት ሰዎች ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል።

ነጻ መውጣት፡— አንድን ሰው ከአደጋ፣ ከጥፋት ወይም ከእስር ቤት ዋጋ ከፍሎ ማዳን ማለት ነው። ኀጢአትና ሰይጣን በእኛ ላይ ካመጡብን ጥፋት ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ድነት የሚያስፈልገውን ዋጋ ሁሉ በመክፈል አዳነን።

ንስሓ፡— አቅጣጫን መቀየር ወይም ከራስ ወዳድነትና ኩነኔአት መንገድ መሲሑን ለመከተል መወሰን ማለት ነው።

መሥዋዕት፡— ብዙ ሃይማኖቶች ኀጢአታቸው ይቅር እንዲባልላቸው እንስሳ ወይም የእህል መሥዋዕት ለአምላኮቻቸው ያቀርባሉ። በአዲስ ኪዳን ኢየሱስ ክርስቶስ የእኛን ኀጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ ሆኖ እንደ ተሰዋ ተጽፎአል።

ድነት:— የኀጢአት ይቅርታና የዘላለም ሕይወት ነው። ደነት ዕረፍትና ሰላም ነው።

ሰይጣን:— ኢብሊስ ከሚለው የዐረብኛ ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው። ሰይጣን ውሸታም ነው።

አዳኝ:—የኢየሱስ ስም ነው። አዳኙ እኛን ከኀጢአታችን የሚያድነን፣ ይቅርታን የሚያደርግልን፣ አሁን ሰላማዊ የሆነ እንዲሁም በሰማይ የዘላለምን ሕይወት የሚሰጠን ነው።

ዳግም ምጽአት:— ኢየሱስ ክርስቶስ በመጨረሻው ፍርድ ጊዜ ሙታን ሲነሡና የእግዚአብሔርን መንግሥት ለዘላለም ፍጹም ለማድረግ ዳግም እንደሚመለስ ቃል ገብቶአል። በዚያ ጊዜ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ይመሠረታሉ።

የተራራው ስብከት:— ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ በተራራ ላይ ስለ ጽድቅ ኑሮ ያስተማረው ትምህርት ነው።

የእግዚአብሔር ሰጅ:— በመሲሑ ውስጥ እግዚአብሔር በሙላት ተገልጠአል ከእግዚአብሔር ጋርም ፍጹም የሆነ ኅብረት አለው።

ቤተ መቅደስ:— ለመጀመሪያ ጊዜ በንጉሥ ሰሎሞን የተገነባው የአይሁድ የአምልኮ ስፍራ ስም ነው።

ዐሥርቱ ትእዛዛት:— እግዚአብሔር ለሙሴ በሲና ተራራ ላይ ሰዎች ትክክለኛ ሥነ ምግባር እንዲኖራቸው አስቦ የሰጠው ሕግ ነው።

ኪዳን:— ስምምነት ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ አዲስ ኪዳንንና ብሉይ ኪዳንን የያዘ መጽሐፍ ነው።

ቶራህ:— የመጀመሪያዎቹ አምስቱ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ናቸው።

ሥላሴ:— ክርስቲያኖች ፈጣሪ፣ አዳኝና መንፈስ (አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ) በሆነው አንድ አምላክ ውስጥ ባሉት ሦስት አካላት መካከል ያለውን የፍቅር ግንኙነት ለመግለጽ የሚጠቀሙበት ቃል ነው።

ድንግል ማርያም:— የኢየሱስ ክርስቶስ እናት።

ያህዌ:— እግዚአብሔር ለሙሴ በእሳት አምሳል በእሾህ ቁጥቋጦ ውስጥ "ያለና የሚኖር እኔ ነኝ" ብሎ ስሙን ለሙሴ ሲናገር የተናገረውን ሐሳብ ለመግለጥ ጥቅም ላይ የዋለው የእግዚአብሔር ስም ነው።

ዋቢ መጻሕፍት
ከአጫጭር ማብራሪያዎች ጋር

<u>የቅኝት/አስሳ መጻሕፍት</u>

Abdalati, Hammaudah. *Islam in Focus.* Indianapolis, Ind.: American Trust Publications, 1975. Reprinted. ሙስሊሞች እስላማዊውን አስተምህሮና ሕይወት ጠንቅቀው እንዲረዱ የሚያግዝ መሠረታዊ መጽሐፍ ነው።

Chittick, William C., and Sachiko Murata. *The Vision of Islam.* St. Paul: Paragon House, 1994. የእስልምናን ሃይማኖት ከሱፊዎች አስተምህሮ አንጻር የሚመረምር መጽሐፍ ነው።

Denny, Frederick Mathewson. *An Introduction to Islam.* 2nd ed. New York: Macmillan, 1994. በብዛት በኮሌጅ ደረጃ በመማሪያ መጽሐፍነት የሚያገለግል ሲሆን በርካታ ርእሰ ጉዳዮችን ይዳስሳል።

Endress, Gerhard. *An Introduction to Islam.* New York: Columbia University, 1987. ከንባረ መለኮት ይልቅ ለታሪክ ትኩረት ይሰጣል።

Esposito, John L. *Islam: The Straight Path.* 3rd ed. New York: Oxford University Press, 1998. ሙስሊም ባልሆነ ሰው የተጻፈ የቅኝት/የአሰሳ መጽሐፍ ነው።

Hamidullah, Muhammad. *Introduction to Islam.* Kuwait: International Islamic Book Center, n.d. ከላይ ከተጠቀሰው ከዛሙዳሃ መጽሐፍ ይልቅ ሰፊ ማብራሪያ ይሰጣል።

Jomier, Jacques. *How to Understand Islam.* Trans. From French by John Bowden. London: SCM Press, 1989. መጽሐፉ በመጀመሪያ በፈረንሳይኛ ቋንቋ የተጻፈ ሲሆን፣ ከክርስቲያኖች ከእስልምና ሃይማኖት ጋር እንዲተዋወቁ የሚረዳ የቅኝት መጽሐፍ ነው።

Miller, Roland E. *Muslim Friends, Their Faith and Feeling: An Introduction to Islam.* St. Louis: Concordia, 1996. እስልምናን ከክርስቲያኖች አንጻር የሚመለከት መጽሐፍ ነው።

Rahman, Fazlur. *Islam.* 2nd ed. Chicago: University of Chicago Press, 1979. ወደ ዘመናዊነት ባጋደለ ፓኪስታናዊ ምሁር የቀረበ ዘገባ ነው።

Renard, John. *Seven Doors to Islam: Spirituality and the Religious Life of Muslims.* Berkeley: University of California Press, 1996, and the companion volume *Windows on the House of Islam: Muslim Sources on Spirituality and Religious Life.* Berkeley: University of California Press, 1998.

Rappin, Andrew. *Muslims: Their Religious Beliefs and Practices.* 2nd ed. London: Routledge ለማስተዋል በሚረዳ መልክ የቀረበ ሲሆን፣ እስላማዊ የትመጣሁን (origin) በሰፋት ይመረምራል::

Robinson, Neal. *Islam: A Concise Introduction.* Washington, D.C.: Georgetown University, 1999. ክርስቲያኖች መጠየቅ ለሚገባቸው ጥያቄ ትኩረት ይሰጣል::

Schimmel, Annemarie. *Deciphering the Signs of God: A Phenomenological Approach to Islam.* Edinburgh: Edinburgh University Press, 1994

Waines, David, *An Introduction to Islam.* Cambridge: Cambridge University Press, 1995. እጅግ ጠቃሚ የሆነ ታሪካዊ ቅኝት ያቀርባል::

የመሐመድ ሕይወት

Guillaume, A. *The Life of Muhammad: A Translation of Ishaq's Sirat Rasul Allaa.* Karachi: Oxford University, 1955. (13th Printing in 1998). በመሐመድ ሕይወት ላይ የቀረበ ዐረባዊ ሥራ ነው::

Haykal, Muhammad Husayn. *The Life of Muhammad.* Trans. I. F. al-faruqi from the Arabic. London: Shorouk International, 1983. በመጀመሪያ በ1985 ዓ.ም የታተመ ሲሆን፣ ዘመናዊ በሆነ ግብፃዊ ሙስሊም የተጻፈ መጽሐፍ ነው::

Lings, Martin. *Muhammad: His Life Based on the Earliest Sources.* Cambridge: The Islamic Texts Society, 2001. ሙስሊሞች ታሪክን በሚተርኩበት መንገድ የሚተርክ ጥሩ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ነው::

Rodinson, Maxime. *Mohammed.* Trans. Anne Carter from the French. London: Penguin, 1971.

Watt, W. Montgomery. *Muhammad, Prophet and Statesman.* London: Oxford University Press, 1961.

የእንግሊዝኛና የአማርኛ ቁርአን

Ali, Abdullah Yusuf. *The Holy Qur'an.* Lahore 1937. በቆየው የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተተርጉሞ ለበርካታ ጊዜያት የታተመ እንዲሁም ሙስሊሞች በሰፋት የሚጠቀሙበት ቅጅ ነው::

Arberry, A. J. *The Koran Interpreted.* London: 1955. በቋንቋ ጥራቱ የእስልምናን ሃይማኖት በሚያጠኑ ሊቃውንት ዘንድ በእጅጉ የሚወደድ መጽሐፍ ቢሆንም፣ የቀጥሮቹ አቀማመጥ በአሁኑ ጊዜ በሰፋት ጥቅም ላይ እየዋለ ከሚገኘው ጋር አብሮ የሚሄድ አይደለም::

Dawood, N. J. *The Koran.* London: Penguin, 1956. ዘመናዊውን እንግሊዝኛ የሚጠቀም፣ ለማንበብ ቀላል የሆነ፣ በተደጋጋሚነት ለረጅም ጊዜ የታተመ እንዲሁም ሙስሊም ባልሆነ ሰው የተተረጐመ ቅጅ ነው::

Fakhry, Majid. *The Qur'an: A Modern English Version.* Reading, UK: Garnet Press, 1997. ዘመናዊ በሆነ እንግሊዝኛ የተተረጐመ ጥሩ ቅጅ ነው::

Pickthall, Mohammed Marmaduke. *The Meaning of the Holy Qur'an.* እንግሊዛዊ በሆነ ሙስሊም፣ ዘመናዊ ባልሆነ እንግሊዝኛ የተተረጐመ ቅጅ ነው::

ሸህ ሰይድ ሙሐመድ ሳዲቅና ሐጂ ሙሐመድ ሳኒ ሐቢብ፣ ቅዱስ ቁርአን በአማርኛ ትርጉም፣ ሁለተኛ ዕትም፣ አዲስ አበባ፣ ነጃሺ አሳታሚ ድርጅት፣ 1997::

ቁርአናዊ ጥናት

Cragg, Kenneth. *The Event of the Qur'an: Islam in Its Scripture.* Oxford, UK: Oneworld, 1994.

Cragg, Kenneth. *The Mind of the Qur'an.* London, 1973.

Gätje, Helmut. *The Qur'an and Its Exegesis.* Trans. By Alford T. Welch. Oxford, UK: Oneworld, 1996. የተውጣጡ ጽሑፎችን በአንድ ላይ ያካተተ የቁርአን ግብራሪያ/አንድምታ ነው::

Hawting, G. R., and Abdul-Kadar A. Shereef, eds. Approaches to the Qur'an. London and New York, Routledge, 1993.

Muslim-Christian Research Group (GRIC). *The Challenge of the Scriptures.* Maryknoll, N.Y.: Orbis, 1989. ከሙስሊሞች ጋር ለሚደረግ ውይይት ጥሩ ትምህርት ይሰጣል::

Nelson, Kristina. *The Art of Reciting the Qur'an.* University of Texas, Austin, 1985. የቁርአንን መሠረታዊ ነጥቦች የሚያስተምርና ለመካከለኛ ሙስሊሞች የሚሆን መጽሐፍ ነው።

Parrinder, Geoffrey. *Jesus in the Qur'an.* Oxford, UK: Oneworld Publications, 1995. ቁርአን ስለ ማርያም፣ ስለ ኢየሱስ፣ ስለ ክርስቲያኖችና ስለ ክርስትና የሚያስተምራቸውን ምንባባት ሁሉ የሚመረምር መጽሐፍ ነው።

Rahman, Fazlur. *Major Themes of the Qur'an.* Chicago: Bibliotheca Islamica, 1980. ቁርአናዊ አስተምህሮዎችን የሚያስተምር ጥሩ መጽሐፍ ነው።

Rippen, A., ed. *Approaches to the History of the Interpretation of the Qur'an.* Oxford, UK: Clarendon Press, 1988.

Sherif, Faruq. *A Guide to the Contents of the Qur'an.* Reading, UK: Garnet Publishing, 1995.

Sells, Michael. *Approaching the Qur'an: The Early Revelations.* Ashland. Ore.: White Cloud, 1999. ጥሩ ነገር ግን ያልተሟላ የቁርአን ግጥም መጽሐፍ ሲሆን፣ CD-ROM ያካተተ ነው።

Watt, W. Montgomery. *Introduction to the Qur'an.* Edinburgh: University of Edinburgh Press, 1970. በምሁራን ዘንድ ያሉትን ሙያዊ የሆኑ የነገረ መለኮት ርእሰ ጉዳዮችን በአሰላ መልክ የሚያቀርብ ጥሩ መጽሐፍ ነው።

ትውፊት(ሐዲስ)

Ali, Maulana Muhammad. *A Manual of Hadith.* London: Curzon Press 1977. በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተረቡት ሐዲሶች ከሃይማኖታዊው ሕግ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ናቸው።

Burton, John. *An Introduction to the Hadith.* Edinburgh: Edinburgh: Edinburgh U.P., 1994. የሐዲስን ታሪክና አስተምህሮ በአሰላ መልክ የሚያቀርብ ሙስሊም ባልሆነ ጸሐፊ የተዘጋጀ መጽሐፍ ነው።

Graham, William. *Divine Word and Prophetic Word in Early Islam.* The Hague: Mouton, 1977.

Siddiqi, M. Z. *Hadith Literature: Its Origin, Development, and Special Features.* Cambridge: Islamic Texts Society, 1993. ሙስሊም በሆነ

ጸሐፊ የተዘጋጀ ጥሩ አስላሚ ጥናት ነው። መጽሐፉ ሐዲስን በተመለከተ ለምዕራባውያን ሒስ መልስ ለመስጠት ይሞክራል።

አስላማዊ ሕግ

Al-Misri, Ahmad ibn Naqib. *Reliance of the Traveller: A Classic Manual of Islamic Sacred Law.* Rev. ed. Trans. And ed. Nuh Ha Mim Keller. Beltsville, Md.: Amana, 1994. በ10ሥራ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተጻፉ የሱኒ ምንባባትን በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተርጉሞ ያቀረበ መጽሐፍ ነው። አስላማዊ ሕጎች በታሪክ ውስጥ እንዴት ይታዩ እንደ ነበር እንዲሁም አሁንም እንኳ አብዛኛውም ሕዝብ እንዴት እንደሚረዳቸው ለማወቅ ይሆን መጽሐፍ ግንባብ ትልቅ ጠቀሜታ አለው።

An-Na'im, Abdullahi A., ed. *Islamic Family Law in a Changing World: A Global Resource Book.* London: Zed Books, 2002. የተለያዩ አገሮችን አስላማዊ ሕግ በአሰላ መልክ የሚቃኝ መጽሐፍ ነው።

Cook, Michael. *Commanding the Right and Forbidding the Wrong in Islamic Thought.* Cambridge: Cambridge U.P., 2000. በአስላማዊ ሕግ ውስጥ አንድ ሰው ለሌላው ሰው ያለበት ኀላፊነት ምን እንደሚመስል የሚተነትን እንዲሁም እጅግ በርካታ ታሪካዊ ዘገባዎች የቀረበበት መጽሐፍ ነው።

Coulson, N. J. *A History of Islamic Law.* Edinburgh: U. P., 1964.

Esposito, John L. *Women in Muslim Family Law.* Syracuse, N.Y.: Syracuse U.P., 1982.

Hallaq, Wael B. *A History of Islamic Legal Theories: An Introduction to Sunni Usûl al-Fiqh.* Cambridge: Cambridge U.P., 1997.

Kamali, M. H. *Principles of Islamic Jurisprudence.* 2nd ed. Cambridge: Islamic Texts Society, 1991.

Masud, Muhammad Khalid, Brinkley Messick, and David S. Powers. *Islamic Legal Interpretation: Muftis and Their Fatwas.* Cambridge, Mass.: Harvard University, 1996. ፋትዋን አስመልክቶ ጥሩ ግብራሪያ ይሰጣል።

Omrun, Abdel Rahim. *Family Planning in the Legacy of Islam.* London: Routledge, 1992. ርእሰ ጉዳዩ ላይ ሰፊ ግብራሪያ የሚሰጥ መጽሐፍ ነው።

Pearl, David. *A Textbook on Muslim Personal Law.* London: Croom Helm, 1987. በእንግሊዞችና በደቡብ አስያውያን ዐውድ የቀረበ መጽሐፍ ነው።

Schacht, Joseph. *An Introduction to Islamic Law.* Oxford: Oxford U. P., 1964.

Weiss, Bernard G. *The Spirit of Islamic Law.* Athens, Ga.: The University of Georgeia, 1998. እስላማዊ ሕግን በቀላል አቀራረብ የሚያብራራ መጽሐፍ ነው::

በጦርነት፣ በሰላምና በሰብአዊ መብት ዙሪያ የእስላማዊ ሕግ እይታ

Abu Sulayman, Abdul Hamid A. *Towards on Islamic Theory of International Relations.* Rev. ed. Herndon, Va.: The International Institute of Islamic Thought, 1993.

'Alwani, Taha Jabir al-. *The Ethics of Disagreement in Islam;* Herndon, Val.: The International Institute of Islamic Though, 1994.

Johnson, James Turner, and John Kelsay. *Cross, Crescent, and Sward: The Justification and Limitation of War in Western and Islamic tradition.* New York: Greenwood Press, 1990.

Kelsay, John and James Turner Johnson, ed. *Just War and Jihad: Historical and Theoretical Perspectives on War and Peace in Western and Islamic Traditions.* New York: Greenwood Press, 1991.

Kelsay, John. *Islam and War: The Gulf War and Beyond.* Louisville, Ky.: Westminster/John Knox, 1993.

Khadduri, Majid. *War and Peace in the Law of Islam.* New York: AMS, 1979.

Mawdudi, Abul A'la. *Human Rights in Islam.* Nairobi: The Islamic Foundation, 1976.

Mitri, Tarek, ed. *Religion, Law and Society.* Geneva: WCC Publications, 1995.

Peters, Rudolph. *Jihad in Classical and Modern Islam.* Princeton: Markus Wiener, 1996. መሠረታዊ ምንባባትን ተርጉሞ እንዲሁም አጫጭር የትንታኔ ጽሑፎችን እንዲሁም ጠቃሚ የዋቢ መጻሕፍት ዝርዝሮችን ያካተተ መጽሐፍ ነው::

Peters, Rudolph. *The Doctrine of Jihad in Modern History.* Gravenhage: Mouton, 1979.

Qutb, Sayed. *Islam and Universal Peace.* Riyadh: International Islamic Publishing House, 1991.

Watt, W. Montgomery. *Islamic Political Thought.* Edinburgh U.P.: 1968.

ሴቶች በእስልምና ውስጥ ያላቸው ቦታ (እንዲሁም ከላይ እስላማዊ ሕግ የሚለውን ይመለከታል)

Abu-Lughod, Lila. Veiled Sentiments: Honor and Poetry in a Bedouin Society. Berkeley: University of California Press, 1986.

Afkhami, Mahnaz. *Faith and Freedom, Women's Human Rights in the Muslim World.* London: I. B. Tauris Publishers, 1995.

Ahmed, Leila. *Women and Gender in Islam: Historical Roots of a Modern Debate.* New haven, Conn.: Yale U.P. Publications, 1975.

El Saadawi, Nawal. *The Hidden Face of Eve: Women in the Arab World.* London: Zed Books, 1980.

Glaser, Ida, and Napoleon John. *Partners or Prisoners? Christians Thinking About Women and Islam.* Cumbria, UK: Solway, 1998.

Jawad, Haifaa A. *The Rights of Women in Islam: An Authentic Approach.* London: Macmillian Press, 1998.

Khan, Maulana Wahiduddin. *Women in Islamic Shari'ah.* New Delhi: Al-Risala Books, 1995.

Macleod, Arlene, Elowe. *Accommodating Protest: Working Women, the New Veiling, and Change in Cairo.* New York: Columbia U. P., 1991.

Mernissi, Fatima. *Beyond the Veil: Male-Female Dynamics in Muslim Society.* Rev. ed. Indianapolis: Indiana U.P., 1987.

Mernissi, Fatima. *The Harem Within: Tales of a Moroccan Girlhood.* London: Doubleday, 1994.

Nazlee, Sajda. *Feminism and Muslim Women.* London: Ta-Ha, 1996. እስልምና በሴቶች ላይ ያለውን ቀደምት አስተሳሰብ ከሒስ የሚከላከል መጽሐፍ ነው::

Sachiko, Murata. *The Tao of Islam: A Sourcebook on Gender Relationships in Islamic Thought.* Albany, N.Y.: State University of New Yourk Press, 1992.

Shaltut, Mahmoud. *The Qur'an and Women*. Cairo: International Islamic Centre for Population Studies and Research, n.d.

Stowasser, Barbara Freyer. *Women in the Qur'an, Traditions, and Interpretation*. New York: Oxford U.P., 1994.

Wadud-Muhsin, Amina. *Qur'an and Woman*. Kuala Lumpur: Penerbit Fjar Bakti, 1992.

Yamani, Mai. *Feminism & Islam: Legal and Literary Perspectives*. Reading, UK: Ithaca Press, 1996.

አስላማዊ ዩሃይማኖት መግለጫ፣ ነገረ መለኮትና ፍልስፍና

Abduh, Muhammad. *The Theology of Unity*. Translated from Arabic by Ishaq Musa'ad and Kenneth Cragg. London: George Allen & Unwin, 1966. አብዱ የግብፅ ዘመናዊ አስተሳሰብን ያራምዱ የነበሩ አንጋፋ ሰው ናቸው::

Caspar, R. *A Historical Introduction to Islamic Theology: Muhammad and the Classical Period*. Rome: Pontificio Istituto di Studi Arabi eIslamici, 1998. ከፈረንሳይኛ ቋንቋ የተተረጐመ መጽሐፍ ነው::

Fakhry, Majid. *A History of Islamic Philosophy*. 2nd ed. New York: Columbia U.P., 1983.

Fakhry, Majid. *A Short Introduction to Islamic Philosophy, Theology and Mysticism*. Oxford: Oneworld, 1997. ርእሰ ጉዳዩን ለማጥናት ጥሩ የጀማሮ መጽሐፍ ነው::

Goodman, L. E. *Avicenna*. London: Routledge, 1992. በእስልምና ታሪክ ውስጥ እጅግ ሰመ ጥር የሆኑትን ፈላስፎች የሚያስተዋውቅ መጽሐፍ ነው::

Leaman, Oliver. *A Brief Introduction to Islamic Philosophy*. Cambridge: Polity, 1999.

Martin, Richard C. and Mark R. Woodward with Dwi S. Atmaja. *Defenders of Reason in Islam: Mu'tazilism from Medieval School to Modern Symbol*. Oxford: Oneworld, 1997.

Watt, W. Montgomery. *Islamic Creeds:* A Selection. Edinburgh: Edinburgh U.P., 1994.

Watt, W. Montgomery. *Islamic Philosophy and Theology. 2nd ed.* Edinburgh: Edinburgh U.P., 1985.

ሱፈይዝም አስላም

Andrae, Tor. *In the Garden of Myrtles: Studies in Early Islamic Mysticism*. Trans. Birgitta Sharpe from the Swedish. Albany, N.Y.: State University of New York Press, 1987.

Awn, Peter J. *Satan's Tragedy and Redemption: Iblîs in Sufi Psychology*. Leiden: E. J. Brill, 1983.

Baldick, Julian. *Mystical Islam: An Introduction to Sufism*. London: I. B. Tauris, 1989.

Chittick, William C. *Imaginal Worlds: Ibn 'Arabî and the Problem of Religious Diversity*. Albany, N.Y.: State University of New York Press 1994. በእስልምና ታሪክ ውስጥ እንዲሁም በርእሰ ጉዳዩ ዙሪያ ባለው ዕውቀት አንቱ በተባለ ምሁር የቀረበ ጸሰላዊ ጥናት ነው::

Haeri, Fadhlalla. *The Elements of Sufism*. Shaftesbury, Dorset, UK: Element, 1990. በሱፊ ሼኽ የቀረበ ግልጽ ጥናት የሱፊይዝም ነው::

MacCarthy, R. J., trans. *Al-Ghazali's Path to Sufism*. Louisville, KY.: Fons Vitae, 2000. አል-ጋዛሊ እንዴት ወደ ሱፊይዝም እንደ ተቀየረ የገለጸበትና ታዋቂ የሆነው ግለ ታሪኩ ተተርጉሞ የቀረበበት መጽሐፍ ነው::

Nasr, Seyyed Hossein, ed. *Islamic Spirituality: Foundations*. New York: Crossroad, 1985, and *Islamic Spirituality: Manifestations*. New York: Crossroad, 1991. and Islamic Spirituality: Manifestations. New York: Crossroad, 1991. የመጀመሪያው ቅጽ በቀርእን፣ በሐዲስ እንዲሁም በቀደምት ሱፊይዝም ወዘተ ላይ የሚያተኩር ሲሆን፣ ሁለተኛው ቅጽ ደግሞ በሱፊ አስተሳለፍ፣ ሥነ ጽሑፍ እንዲሁም ሥዕል ላይ ያጠነጥናል::

Nicholson, Reynold *A. Studies in Islamic Mysticism*. Surrey, UK: Curzon Press, 1994. እጅግ ጠቃሚ የሆኑ የሱፊ ጽሑፎች ተተርጉመው የቀረበበት መጽሐፍ ነው::

Padwick, Constance. *Muslim Devotions: A Study of Prayer-Manuals in Common Use*. Oxford: Oneworld Publications, 1996. ዋና ዋና የሚባሉ የእስልምና ጸሎተች በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተተርጉመው የቀረበበት መጽሐፍ ነው::

Schimmel, Annemarie. *And Muhammad Is His Messenger: The Veneration of the Prophet in Islamic Piety.* Chapel Hill, N.C.: The University of North Carolina Press, 1985.

Schimmel, Annemarie. *Mystical Dimensions of Islam.* Chapel Hill, N.C.: The University of North Carolina Press, 1975.

Smith Margaret. *Readings from the Mystics of Islam.* London: Luzac, 1950. በርእሰ ጉዳዩ ላይ እጅግ ጠቃሚ የሆነ ብቸኛ መጽሐፍ ነው::

Trimingham, J. Spencer. *The Sufi Order in Islam.* Oxford, Clarendon, 1971; reprint 1998.

ሻይዝም

Daftary, P. *The Isma'ilis: Their history and Doctrine. London: C.U.P., 1990.*

Halm, Heinz. Shiism. *Trans. Janet Watson from the German.* Edinburgh: Edinburgh U.P., 1991

Monmen, Moojan. *An Introduction to Shi'I Islam: The History and the Doctrines of Twelver Shi'ism.* New Haven, Conn.: Yale, 1985.

የእስልምና ታሪክ

Al-Faruqi, R. Isma'il, and Lois Lamya' al-Faruqi. *The Cultural Atlas of Islam.* New York: Macmillan, 1986. የእስልምናን አስተምህሮ ከጥቃት ለመከላከል ታስቦ የተዘጋጀ መጽሐፍ ነው::

Esposito, John, ed. *The Oxford History of Islam.* Oxford, UK: Oxford U.P., 2000.

Holt, P. M., Lambton, A. K. S., and Lewis, B., eds. *The Cambridge History of Islam.* 2 vol. Cambridge: Cambridge U.P., 1970.

Hourani, Albert H. *A History of the Arab Peoples.* London: Faber, 1991. እጅግ ጠቃሚ የሆነ በተለይ ደግሞ አሁን ላለው ነባራዊ ሁኔታ የሚጠቅም አስሳዊ ጥናት ነው::

Lapidus, Ira M. *A History of Islamic Societies.* 2nd ed. Cambridge: Cambridge U.P., 2002. ስለ እስልምናው ዓለም በአጠቃላይ ጠቃሚ መረጃ የሚሰጥ መጽሐፍ ነው::

Riley-Smith, Jonathan, ed. *The Atlas of the Crusades.* London: Times Books, 1991.

Robinson, Francis, ed. *The Cambridge Illustrated history of the Islamic World.* Cambridge: Cambridge U.P., 1999.

Robinson, F. *Atlas of the Islamic World Since 1500.* New York: Facts on File, 1982.

Smart, Ninian. *Atlas of the World's Religions.* Oxford, UK: Oxford U.P., 1999. በጎበረ ቀለማት ያሸበረቁ ካርታዎችን የያዘ ጠቃሚ መጽሐፍ ነው::

አስልምና በአሜሪካ

Haddad, Yvonne Yazbeck, and John L. Esposito. *Muslims on the Americanization Path?* Oxford UK: Oxford University, 2000.

Smith, Jane I. *Islam in America.* New York: Columbia University, 1999. ሚዛናዊ የሆነ እጅግ ጠቃሚ መጽሐፍ ነው::

አስልምና በአፍሪካ

Haynes, J. *Religion and Politics in Africa.* London: Zed Books, 1996.

Hisket, Mervin. *The Course of Islam in Africa.* Edinburgh: Edinburgh U.P., 1994.

Hisket, Mervin. *The Development of Islam in West Africa.* London: Longman, 1984.

Kritzeck, J., and W. H. Lewis, eds. *Islam in Africa.* New York: Van Nostrand, 1969.

Levzion, Nehemia, and Randall L. Pouwels, eds. *The History of Islam in Africa.* Athens, Ohio: Ohio U.P., 2000. ትንንሽ የሆኑ በርካታ ጽሑፎችን የያዘ መጽሐፍ ነው::

Rasmussen, L. *Christian-Muslim relations in Africa.* London: I. B. Tauris, 1993.

Sanneh, Lamin. *The Crown and the Turban: Muslims and West African Pluralism.* Boulder: Westview Press, 1997.

Stamer, P. Josef. *Islam in Sub-Saharan Africa.* Königstein, Germany: Aid to the Church in Need, 1995. ግልጽና እጂጭር የሆኑ ክርስቲያናዊ መልሶችን ያካተተ መጽሐፍ ነው::

እስልምና በዘመናዊው ዓለም

Abu Rabi, Ibrahim M. *Intellectual Origins of Islamic Resurgence in the Modern Arab World.* Ithaca, N.Y.: State University of New York Press, 1995.

Ahmed, Akbar S. *Postmodernism and Islam. Predicament and Promise.* London: Routledge, 1992. በዘመናዊው ዓለም ውስጥ የእስልምና ወይኑተኛ ባሕርያት ናቸው የሚባሉትን ግንኑቶች የሚያፈላልግ መጽሐፍ ነው::

Algar, Hamid. *Islam and Revolution: Writings and Declarations of Imam Khomeini.* Berkeley, Calif.: Mizan Press, 1981.

Arkoun, Mohammed. *Rethinking Islam: Common Questions, Uncommon Answers.* Trans. And ed. By Robert D. Lee from the French. Boulder, Colo.: Westview Press, 1994. ግልጽ እንጂሁም በእስልምና ሃይማኖት ላይ ለዘብተኛ አቋም ያለው መጽሐፍ ነው::

Choueiri, Youssef M. *Islamic Fundamentalism.* London: Pinter, 1997.

Cole, Juan. R. I., and Nikki R. Keddie, eds. *Shi'ism and Social Protest.* New Haven: Yale U.P., 1986.

Donohue, John J., and John L. Esposito, eds. *Islam in Transition: Muslim Perspectives.* New York: Oxford U.P., 1982. ዘመንኛ የሆኑ 50 የሙስሊም ምሁራንን ጽሑፍ ያካተተ መጽሐፍ ነው::

Eshtashtami, Anoushiravan. *After Khomeini: The Iranian Second Republic.* London: Routledge, 1995.

Esposito, John L., and Azzam Tammimi. *Islam and Secularism in the Middle East.* New York: New York U.P., 2000.

Esposito, John L., and John Voll. *Islam and Democracy.* Oxford: Oxford U.P., 1996.

Hourani, Albert. *Arabic Thought in the Liberal Age, 1798-1939.* London, 1962. Kepel, Giller. Muslim Extremism in Egypt: The Prophet and Pharaoh. Berkeley: University of California Press, 1992.

Kurzman, Charles. *Liberal Islam: A Sourcebook.* New York: Oxford U.P., 1998.

Kramer, Martin. *Arab Awakening & Islamic Revival.* New Brunswick: Transaction Publishers, 1996.

Lewis, Bernard. *The Shaping of the Modern Middle East.* New York: Oxford U.P., 1994.

Moussalli, Ahmad S., ed. *Islamic Fundamentalism: Myths and Realities.* Reading, UK: Garnet Publishing, 1998.

Moussalli, Ahmad S., *Moderate and Radical Islamic Fundamentalism: The Quest for Modernity, Legitimacy, and the Islamic State.* Jacksonville: University of Florida Press. 1999.

Mitchell, Richard P. *The Society of the Muslim Brothers.* New York: Oxford U.P., 1993. በመጀመሪያ በ1969 ዓ.ም የታተመ መጽሐፍ ሲሆን፣ በግብፅ አገር ባለው የሙስሊም ወንድማማቾች ፅድገት ዙሪያ የሚያጠ ነጥን ነው::

Voll, John O. *Islam: Continuity and Change in the Modern World.* 2nd ed. Syracuse, N.Y.: Syracuse U. P., 1994.

Zeberi, Kate. *Mahmud Shaltut and Islamic Modernism.* Oxford: Clarendon Press, 1993. መሐመድ ሳሉት በ1963 ዓ.ም የሞቱ በአል-አዛር ዩኒቨርስቲ ያስተምሩ የነበሩ ስመ ጥር ምሁር ናቸው::

Ziad, Abu-Amr. *Islamic Fundamentalism in the West Bank: Muslim Brotherhood and Islamic Jihad.* Bloomington: Indiana U.P., 1994.

የክርስቲያኖችና የሙስሊሞች ግንኙነት—ታሪክ

Daniel, Norman. *Islam and the West: The Making of an Image.* Oxford: Oneworld Publications, 1993. መጀመሪያ የታተመው በ1960 ዓ.ም ሲሆን፣ አዲሱ ዕትም በርካታ ርእሶችን ጨምሮ ቀርቦአል::

Gaudeul, Jean-Marie. *Encounters and Clashes: Islam and Christianity in History.* 2 vol. Rome: Pontificio Istituto di Studi Arabi e Islamici, 2000. የመጀመሪያው ቅጽ በታሪክ ሁለተኛው ቅጽ ደግሞ ነባረ መለኮት ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ የሚያጠነጥን ነው::

Goddard, Hugh. *A History of Christian-Muslim Relations.* Edinburgh: Edinburgh U.P., 2000. ከእስልምና በፊትም ሆነ በኋላ እንጂሁም እስከ ዛሬ ድረስ ያለውን ታሪክ የሚዘግብ ጥሩ መጽሐፍ ነው::

Southern, R. W. *Western Views of Islam in the Middle Ages.* Cambridge, Mass.: Harvard U.P., 1962; reprint, 1978.

Watt, W. Montgomery. *Muslim-Christian Encounters: Perceptions and Misperceptions.* London: Routledge, 1991.

የክርስቲያኖችና የሙስሊሞች ግንኙነት—ዘመናዊ ሰይታ

Anees, Munawar Ahmad, et al. *Christian-Muslim Relation: Yesterday, Today, Tomorrow.* London: Grey Seal, 1991. በሙስሊም አተያይ የቀረበ ጥሩ መጽሐፍ ነው::

Azumah, John Alembillah. *The Legacy of Arab-Islam in Africa: A Quest for Inter-Religious Dialogue.* Oxford: Oneworld, 2001. ክሰሐራ በታች ያሉ አገሮችን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ አስቸጋሪ በሚባሉ ጥያቄዎች ላይ የሚያጠነጥን መጽሐፍ ነው::

Borrmans, Maurice. *Guidelines for Dialogue Between Christians and Muslims.* Trans. R. Marston Speight from the French. Mahwah, N.J.: Paulist, 1990. የሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንን አስተምሀሮ መሠረት ባደረገ መልኩ፣ ከሙስሊሞች ጋር ለሚደረገው ውይይት ጠቃሚ መረጃ የሚሰጥ በጣም ጥሩ መጽሐፍ ነው::

Brown, Stuart E. *Meeting in Faith: Twenty Years of Christian-Muslim Conversations Sponsored by the World Council of Churches.* Geneva: World Council of Churches, 1989. ጠቃሚ የሆኑ እንዲሁም ሁለቱ ወገኖች በየትኞቹ ርእሰ ጉዳዮች ላይ እንደ ተወያዩ የሚገልጽ መጽሐፍ ነው::

Caspar, Robert. *Trying to Answer Questions.* Rome: Pontificio Instituto di Studi Arabi e Islamici, 1989. የሙስሊሞችን ጥያቄ ከሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን አስተምሀር አንጻር የሚመልስ መጽሐፍ ነው::

Chapman, Colin. *Islam and the West.* Carlisle, UK: Paternoster, 1998. በሙስሊሞችና በክርስቲያኖች መካከል ያለውን የግንኙነት ታሪክ በትክክል የሚያቀርብ፣ በሰብአዊ መብትና በትምህርት ረገድ ያሉትን ወቅታዊ ርእሰ ጉዳዮች የሚመለከት መጽሐፍ ነው::

Cragg, Kenneth. *The Call of the Minaret.* 3rd ed. Oxford: Oneworld, 2000. በእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ የተጻፈ እንዲሁም እስልምናን በትክክል ተረድቶ ክርስቲያናዊ መልስ የሚያቀርብ አስደናቂ መጽሐፍ ነው::

Cragg, Kenneth. *Jesus and the Muslim: An Exploration.* Oxford: Oneworld, 1999. ለሙስሊሞች የክርስቶስን ማንነት የሚተነትን መጽሐፍ ነው::

Cragg, Kenneth. *Muhammad and the Christian: A Question of Response.* Oxford: OneWorld 1999. ክርስቲያኖች መሐመድን እንዴት ባለ መልክ መመልከት እንዳለባቸው የሚገልጽ ነው::

Goddard, Hugh. *Christian and Muslims: From Double Standards to Mutual Understanding.* Surrey, UK: Curzon Press, 1995. እስልምናንና ክርስትናን ከታሪክና ከማኅበራዊ መስተጋብር አንጻር የሚያወዳድር በአሰሳ መልክ የቀረበ መጽሐፍ ነው::

Goddard, Hugh. *Muslim Perceptions of Christianity.* London: Grey Seal, 1996. በሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን በግብፅ የነበሩ ሙስሊሞች ስለ ክርስትና ያላቸውን አተያይ የሚገልጽ መጽሐፍ ነው::

Kateregga, Badru D., and David W. Shenk. *Islam and Christianity: a Muslim and Christian in Dialogue.* Scottdale, Pa.: herald Press 1997. ሙስሊም እንዲሁም ክርስቲያን በሆኑ ጸሓፍያን የቀረበ፣ እያንዳንዳቸው ባቀረቡት ዘገባ ላይ አንዱ ለሌላው የሚሰጠውን ምላሽ ያካተተ መጽሐፍ ነው::

Kirkwood, Neville A. *Pastoral Care to Muslims.* Binghamton, N.Y.: The Haworth Pastoral Press, 2001. ሙስሊሞች እንዴት መንከባከብ እንችላለን በሚለው ርእሰ ጉዳይ ላይ የሚያጠነጥንና በሆስፒታሎች አካባቢ ወንጌልን በሚሰብክ ሰባኪ የቀረበ መጽሐፍ ነው::

Nickel, Gordon. *Peaceable Witness Among Muslims.* Scottdale, P.: Herald Press, 1999. በፖለቲካ ውስጥ መሳተፍንም ሆነ ውትድርናን የማይደግፍ፣ በሚኖሩበት ምሁር የቀረበ መጽሐፍ ነው::

Tingle, Donald S. *Islam and Christianity.* Madison, Wisc.: InterVarsity Press, 1985. ክርስትናንና እስልምናን የሚያነጻጽር 32 ገጽ ያለው መለስተኛ መጽሐፍ ነው::

Zebiri, Kate. *Muslims and Christians Face to Face.* Oxford: Oneworld, 1997.

በመካከለኛው ምሥራቅ የሚገኙ ክርስቲያን ማኅበረሰቦች

Cragg, Kenneth. *The Arab Christian: A History in the Middle East.* Louisville, KY.: Westminster/John Knox Press, 1991. ነገሬ መለኮትን አስመልክቶ የቀረበው ማብራሪያ ጥሩ ቢሆንም፣ በመጀመሪያ የእስልምና ዘመናት የነበረውን የቤተ ክርስቲያን ሁኔታ በጥሩ ሁኔታ ያላመሳከረ ነው::

Horner, Norman A. *A Guide to Christian Churches in the Middle East.* Elkhart, Ind.: Mission Focus, 1989. በሰሜን አፍሪካና በመካከለኛው ምሥራቅ ያለውን መሠረታዊ ሁኔታ የሚዘግብና ጠቃሚ መረጃዎችን ያካተተ መጽሐፍ ነው::

Pacini, Andrea, ed. *Christian Communities in the Arab Middle East: The Challenge of the Future.* Oxford: Clarendon Press, 1998. በተለያዩ ምሁራን የቀረበ ዘገባ ሲሆን፣ ነባራዊውን ሁኔታ በትክክል ያመሳክረ ነው::

Partick, Theodore Hall. *Traditional Egyptian Christianity: A History of the Coptic Orthodox Church.* Greensborn, N.C.: Fisher Park Press, 1996.

Van-Doorn-Harder, Nelly, and Kari Vogt, eds. *Between Desert and City: The Coptic Orthodox Church Today.* Oslo, Intituttet for Sammenlignende Kulturforskning, 1997. የበርካታ ምሁራንን ጽሑፍ ያካተተ መጽሐፍ ሲሆን፣ ቤተ ክርስቲያን በፖለቲካ ውስጥ ሊኖራት ስለሚገባት ሚና የሚያትት ነው::

Wessels, Antonie. *Arab and Christian? Christians in the Middle East.* Kampen, The Netherlands: Kok Pharos Publishing House, 1995. ወቅታዊውን ሁኔታ ታሪክና ትንተና ያካተተ መጽሐፍ ነው::

ተስፋ ዐቃብያነ ክርስትና ማኅበር

የሚከተሉትን መጻሕፍት ገዝተው እንዲያነቡ ያበረታታል

በቅርቡ ለንባብ የሚበቁ

1. መሠረታዊ የክርስትና ትምህርት (ቅጽ 1 እና ቅጽ 2) —ከአማረ መስፍንና ከተስፋዬ ርበሌ
2. የትንሣኤው ማኅበረሰብ—ከተስፋዬ ርበሌ
3. የሙግት ጥበብ—ከተስፋዬ ርበሌ
4. የሐዳስያን ማኒፌስቶ—ከአማረ መስፍንና ከተስፋዬ ርበሌ
5. ድኅረ ዘመናዊነት—ከተስፋዬ ርበሌ
6. የፖለቲካና የሃይማኖት ፍልስፍና—ከተስፋዬ ርበሌ
7. የብሉይ ኪዳን መከፈቻ— ከአማረ መስፍንና ከተስፋዬ ርበሌ
8. የእምነት እንቅስቃሴ፣ አዲስ መገለጥ ወይስ አሮጌ ኑፋቄ —ከተስፋዬ ርበሌ
9. የሥነ ምግባር ታሪክ—ከተስፋዬ ርበሌ
10. የሐዲስ ኪዳን መከፈቻ—ከተስፋዬ ርበሌና ከአማረ መስፍን
11. የቅዱሳት መጻሕፍት የአፈታት ጥበብ—ከተስፋዬ ርበሌ
12. የመጽሐፍ ቅዱስ ጠንካራ ምንባባት —ከአማረ መስፍን ከተስፋዬ ርበሌና ከዮናስ አስፋው
13. ዐቃቤ እምነት ዘክርስትና—ከተስፋዬ ርበሌ
14. የሥነ ምግባር መርሖ (ሁለተኛ ዕትም)—ከተስፋዬ ርበሌ
15. በቅዱሳት መጻሕፍት ዘገባ በርግጥ ኢየሱስ ክርስቶስ ማነው?— ከተስፋዬ ርበሌ
16. የሥነ ምግባር ርእሰ ጉዳዮች—ከተስፋዬ ርበሌ
17. የነገረ መለኮትና የፍልስፍና መዝገበ ቃላት—ከተስፋዬ ርበሌና ከአማረ መስፍን

የአስተውሎትና የውይይት ጥያቄዎች

1. ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ኢየሱስ መሲሕ እንደ ሆነ ይስማማሉ። በሙስሊሞችና በክርስቲያኖች መካከል ስለመሲሑ ማንነት እንዲሁም ሥራ ያለውን ልዩነት ይግለጹ።
2. አንድ ሰው ሙስሊሞች ማንኛውንም ሃይማኖታዊ ተግባር እንዴት እንደሚፈጽሙ መረዳት ይችላል። ነገር ግን የክርስቲያኖችን መረዳት ያዳግተዋል። ልዩነቱ ከምን እንደ መጣ ይግለጹ። (ማቴዎስ 5÷48፣ ሱራ 33 ÷40)።
3. ሙስሊሞች ነቢዩ መሐመድ የመጨረሻ ነቢይ ናቸው ብለው ማመናቸው ምን ዐይነት ትርጉም እንዳለው ይግለጹ (ሱራ 33 ÷40)?
4. ክርስቲያኖች ኢየሱስ መሲሕ ነው ብለው ማመናቸው ምን ትርጉም ያለው ይመስሉታል (ሉቃስ 4 ÷14-40)?
5. ኢየሱስ ክርስቶስ በቁርአን ውስጥ ምስጢራዊ ሰው ነው። ኢየሱስ በሙስሊሙ ማኅበረሰብ (ኡማ) ውስጥ ያለው ስፍራ እጅግ አነስተኛ ነው። ለብዙ መቶ ዓመታት ቤተ ክርስቲያንም ኢየሱስን አስፈላጊ ወዳልሆነና ከእውነተኛ ሕይወት ተሞክሮ ውጪ በሆነ ሁኔታ ምስጢራዊ ሰው ስታደርገው ቆይታለች። ስለ ኢየሱስ እውነታ ከመሆኑ ይለቅ ምስጢር ተደርጎ የቀረበበት ምክንያት ምን እንደ ሆነ ይግለጹ።

ምዕራፍ ስድስት

ቅዱሳት መጻሕፍት
ቁርአን—መጽሐፍ ቅዱስ

ኢብራሂም መሐመድ፣ "እባክህ መጽሐፍ ቅዱስህን አውሰኝ" ሲል ጠየቀኝ። እኔም መልካሙ የምሥራች (Good News) የሚባለውንና አረንጓዴ እንዲሁም ጠንካራ ያልሆነ ጥራዝ ያለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጅ አንሥቼ ሰጠሁት። ኢብራሂምም ሰዎች የመጽሐፉን ማንነት እንዳያውቁ በሚል በቡናማ ወረቀት ለበደው። መጽሐፉን በአክብሮትና በጥንቃቄ በመያዝ ከቤታችን ሹልክ ብሎ በመውጣት ወደ ቤቱ ሄደ።

በማግሥቱ ማታ ኢብራሂም ያንኑ መጽሐፍ ይዞ ወደ ቤታችን መጣ። በኢብራሂም ገጽ ላይ ከፍተኛ የሆነ የሐዘን ድባብ በግልጽ ይነበብ ስለነበረ፣ በአያሌው እንዳዘነ ማወቅ አዳጋች አልነበረም። ቤት በመግባት ወንበር ላይ ከተቀመጠ በኋላ፣ መጽሐፉን ከቦርሳው ውስጥ በማውጣት ጠረጴዛው ላይ አነጠፈው።

"እኔ መቼም መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መስሎኝ ነበር። ነገር ግን እንደዚያ ሆኖ አላገኘሁትም። ሰዎች የክርስቲያኖችን ቅዱሳት መጻሕፍት አበላሽተዋል። እንዴት ዐይነት አሳዛኝ ጥፋት ነው! መጽሐፍ ቅዱስ የታሪክ መጽሐፍ ከሆነ እንጂ፣ የእግዚአብሔር ቃል ግን አይደለም"።

ኢብራሂም በዚህ ዐይነቱ ታላቅ ሐዘን ውስጥ እያለ፣ ቡናማ መልክ ያለውን ባዶ ቦርሳውን አንከርፍፎ በዚያ ጨለማ ወደ ቤቱ ሄደ። "ተበላሽቶአል" የተባለው የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጅ ምስቅልቅል ባለው ጠረጴዛዬ ላይ ተዘርሮአል።

ታሪክና መገለጥ

ኢብራሂም ትክክል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የታሪክ መጽሐፍ ነው። እስትንፋስ እግዚአብሔር ያለበት እገጂ እርሱም ያለ የታሪክ መጽሐፍ የለም። በእኔ ግምት ኢብራሂም ንባቡን የጀመረው ከዘፍጥረት መጽሐፍ ሲሆን፣ ንባቡን ከጀመረ ከጥቂት አንቀጾች በኋላ ቃየን ወንድሙ አቤልን የገደለበትን በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያውን የግድያ ታሪክ አንብቦአል። ከጥቂት ምዕራፎች በኋላም፣ የኖኅ ልጆች አባታቸው ሰክሮ እንዲሁም ራቁቱን ሆኖ

ስላገኙት፣ ከእርሱ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንደ ፈጸሙ፣ ያዕቆብ በረከትን ለማግኘት ዐይነ ስውር የሆነውን አባቱን ይስሐቅን፣ ኤሳው ነኝ ብሎ እንዳታለለው እንዲሁም የዮሴፍ ወንድሞች ዮሴፍን ለግብፅ ነጋዴዎች በሠላሳ ብር እንደ ሸጡት፣ በተከታታይ ምዕራፎች ውስጥ አንብቦአል። እነዚህን ታሪኮች ያነበበ አንድ ሙስሊም እነዚህ ዘገቦች የእግዚአብሔር ቃል የመሆናቸውን ጉዳይ በጭራሽ ሊቀበል አይችልም። ኢብራሂምም ከላይ የተመለከትናቸው ታሪኮች የእግዚአብሔር ቃል አይደሉም ወደሚለው ድምዳሜ እንዳደረሱት እሙን ነው።

ሙስሊሞች ቁርአንን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በማነጻጸር፣ ቁርአን ከሰው ልጆች ታሪክ በላይ እንደ ሆነ ይናገራሉ። ቁርአን የእግዚአብሔር ቃል ነው፣ ከማንኛውም ሰብአዊና ታሪካዊ ግድፈቶች የነጻ ነው እንዲሁም ከሰማይ ከአላህ ዘንድ የተላከ መገለጥ ነው የሚል ግንዛቤ አለ።

የቁርአን ሥነ ጽሑፋዊ ውቅር ከሰብአዊና ከታሪካዊ ተጽእኖዎች ነጻ እንደ ሆነ ይታሰባል። አስተምህሮው የተዋቀረበትም መንገድ፣ ከመልእክቱ መገለጥ ቅደም ተከተል ጋር አንዳችም ግንኙነት የለውም። ከመጀመሪያው ምዕራፍ በስተቀር ሁሉም የቁርአን ምዕራፎች ከረጅም ምዕራፎች ወደ አጫጭር ምዕራፎች የተደረደሩ ናቸው። ረጃጅም ምዕራፎች በመጀመሪው ክፍል ላይ ሲጻፉ አጫጭሮቹ ደግሞ ከበስተ ኋላ ተሰትረዋል። ቁርአናዊ ምንባባት ነቢዩ መሐመድ በመካ ቆይታቸው ወይም በመዲና ቆይታቸው ጊዜ የተጻፉ የመሆናቸው ጉዳይ፣ ከግምት የሚገባ አይደለም። ሙስሊሞች የአላህ መገለጥ (ቁርአን) በታሪክ ከሥተቶች ላይ አልተመረኮዘም የሚል እምነት አላቸው።

በተወሰነ ደረጃም ቢሆን፣ ቁርአን ታሪካዊ ከሥተቶችን አካቶ ይዞአል። ለምሳሌ ስለኖኅ የጥፋት ውሃ እንዲሁም እግዚአብሔር ለሙሴ በቀጥታ ውስጥ እንደ ተገለጠለት ተጽፎአል። እነዚህ ምንባባት እንደ ታሪክ ዘገባ የቃረቡ ሳይሆን፣ እውነትን ለማሳየት ከታሪክ ውስጥ እንደ ተወሰዱ ናሙናዎች ነው። እነዚህም ታሪኮች ምሉዕነት የሚጐድላቸው ሲሆን፣ በተለያየ ስፍራ ተበጣጥሰው ይገኛሉ። ሙስሊሞች መገለጥ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚወረስ መመሪያ እንደ ሆነ ያምናሉ። ታሪካዊ ከሥተቶች የመገለጡን እውነተኛነት ሊያሳዩ ይችላሉ፣ ነገር ግን መገለጡ ሲመጣ ከተፈጸሙ ከሥተቶች በስተቀር፣ ሌሉች ታሪካዊ ከሥተቶች መገለጥ ሊሆኑ አይችሉም።

ይህም ሲባል የሙስሊሙ ማኅበረሰብ (ኡማ)፣ ለታሪክ ግድ የለውም ማለት ግን አይደለም። ነቢዩ መሐመድና የጥንቱ የሙስሊም ማኅበረሰብ በቁርአን ውስጥ

አልተካተቱም። የነቢዩ መሐመድ ታሪክና አባባሎች ሐዲስ በተባለው መጽሐፍ ውስጥ ተመዝግበው ይገኛሉ። ሐዲስ ትልቅ ዋጋ እንዳለው ቢታሰብም በቁርአን ውስጥ ምንም ስፍራ የለውም። በሙስሊሞች እሳቤ መጽሐፍ ቅዱስ የተምታታ የሐዲስና የእግዚአብሔር ቃል ቅይጥ ነው።

እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ በሠራው ሥራ ራሱን ገልጦአል የሚለውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ፣ የእስልምና ነገረ መለኮት የሚቃወመው ለምንድን ነው? እስልምና እግዚአብሔር ሉዓላዊ አምላክ እንደ ሆነ ያምናል። ስለዚህም እግዚአብሔር ራሱ ባሮቹ የሆኑትን የሰው ልጆች መልክ ይዞ ተገለጠ የሚለው ትምህርት፣ እግዚአብሔርን ዝቅ እንደማድረግ ይታሰባል። እግዚአብሔር እጅግ ትልቅ አምላክ ነው። ሙስሊሞች፦— " ይህ ትልቅ አምላክ በተፈጥሮ ውስጥ ራሱን እንዴት ይገልጣል?[1] ራሱስ እንዴት ሰው ሆኖ በሰዎች መካከል ይገለጣል? ይህ በፍጹም ሊሆን አይችልም" ብለው ያስባሉ።

ይሁንና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪክ፣ እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ የሠራውን ሥራ መሠረት ያደረገ ታሪክ ነው። ክርስቲያኖችና አይሁዶች እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ የሠራቸው ሥራዎች የመጽሐፍ ቅዱሳዊው መገለጥ ዋነኛ ክፍል እንደ ሆኑ ያምናሉ። የአይሁድ የነገረ መለኮት ምሁር ኢሚል ፋከንሀይም እነዚህ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተዘገቡ የታሪክ ክሥተቶች ለዘመናት እያስደነቁን የሚኖሩ መሠረታዊ መረጃዎች ናቸው ብሉአል[2]። ለምሳሌ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከፈርዖን የባርነት ቀንበር ዐርነት አውጥቶአቸዋል። ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በሲና ተራራ ተገናኛቸው (ዘፀአት 1-14: 19-20)። መጽሐፍ ቅዱሳዊው ነገረ መለኮት የተመሠረተው፣ በእነዚህ ሁለት ክሥተቶች ላይ ነው። በእርግጥ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ ከሠራቸው ሥራዎች፣ የሚሉ የኢየሱስ ሕይወት፣ ሞትና ትንሣኤ ቀዳማይ እንደ ሆነ ያምናሉ።

ሙስሊሞች በተደጋጋሚ የሚነግሩኝ፣ በአዲስ ኪዳን ኢየሱስን በተመለከተ የቀረበው ዘገባ እንዲሁም አስተምህሮ ጳውሎስ ሆን ብሎ የፈጠረው ፈጠራ እንደ ሆነ ነው። በእርግጥ በዘመናችን ያሉ እንዳንድ የነገረ መለኮት ምሁራን ይህ ዐይነት አመለካከት አላቸው፣ ምናልባትም ሙስሊሞች ይህን አመለካከት

[1] Kenneth Cragg, *Muhammad and the Christian* (Maryknoll, N.Y.: Orbis Books, 1984), 134-135.

[2] Emil Fackenheim, *The Presence of God in History: Jewish Affirmations and Philosophical Reflections* (New York: New York University Press, 1970), 8-14.

ስላነበቡ ይሆናል ይህን መሰል አስተያየት የሚሰነዝሩት። በእርግጥ ይህ አባባል ግን ትክክለኛ ነውን? ኢየሱስ ለዘመናት አማኞችን ሁሉ እንዳስደነቀ ጳውሎስም በክርስቶስ ተደንቆአል፤ ከዚህ በተረፈ ግን ጳውሎስ ከሌሎች የተለየ ነገር አላደረገም።

ጳውሎስ ወጣት በነበረ ጊዜ ክርስቲያኖች በከፍተኛ ሁኔታ ይሰደዱ፣ እርሱም ክርስቲያኖችን ክፉኛ ያሳድድ ነበር። የትንሣኤው ጌታ በራእይ ከተገናኘው በኋላ ግን፣ ስለኢየሱስ ያለው አድናቆት መቼም ቢሆን ከልቡናው ሊጠፋ አልቻለም። የኢየሱስን ሕይወት አጥብቆ ይመረምር ነበር። የጳውሎስ ባልንጀራ የነበረውም ሉቃስ ከጳውሎስ ጋር በመሆን የኢየሱስን ሕይወት መመርመር ጀመረ። ከዚህም የተነሣ የክርስቶስን ሕይወትና አገልግሎት የሚተርከውን ወንጌሉን ለመጻፍ እንዲዘጋጅ ምክንያት ሆነ። ሉቃስ ራሱ፣ የሉቃስ ወንጌልን ለመጻፍ ያደረገውን ጥረት እንዲህ ሲል ገልጾታል፦—

> የተከበርህ ቴዎፍሎስ ሆይ፤ ከመጀመሪያው በዐይን ያዩትና የቃሉ አገልጋዮች የሆኑት እንዳስተላለፉልን፣ በእኛ ዘንድ ስለተፈጸመው ነገር ብዙዎች ታሪክን በየተራው ለማዘጋጀት ስለሞከሩ፣ እኔ ደግሞ ስለተማርኸው ቃል እርግጡን እንድታውቅ በጥንቃቄ ከመጀመሪያ ተከትዬ በየተራው ልጽፍልህ መልካም ሆኖ ታየኝ (ሉቃስ 1+1-4)።

ስለዚህ የጳውሎስ ነገረ መለኮት፣ በክርስቶስ ሕይወት ውስጥ ለተፈጸመው ታሪካዊና መለኮታዊ ከሥተት ምላሽ ነው[3]። በጳውሎስ የተጻፉ መልእክቶች በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ ተካተዋል። መልእክቶቹም በክርስቶስ ሕይወትና አገልግሎት ውስጥ የተፈጸሙ አስደናቂ ከሥተቶች ናቸው። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ባሕርይ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ እንዲሁም ሰዎች ለእርሱ የሰጡትን ምላሽ የሚተርክ መጽሐፍ ነው።

ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስ ሲጻፍ፣ የአጻጻፍ ሂደቱ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት እንደ ተካሄደ ያምናሉ። ይህን እምነት መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ሲል ያብራራዋል፦—

> ከሕፃንነትህም ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳት መጻሕፍትን ዐውቀሃል። የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ፣ ልብንም ለማትናት፣ በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል (2ጢሞ 3+15-17)

[3] N.T. Wright, *The Challenge of Jesus: Rediscovering Who Jesus Was and Is* (Downers Grove, Ill.: InterVarsity Press, 1999).

ምሪትና ጎብረት

እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ አማካይነት ከሰዎች ጋር ጎብረት ያደርጋል። በቁርአን ግን እግዚአብሔር ፈቃዱን ወደ ሰው ልጆች እንደሚልክ ይታሰባል። የሙስሊሞችና የክርስቲያኖች ጸሎትም ይህንን ልዩነት የሚያንፀባርቅ ነው። ክርስቲያኖች "የአባታችን ጸሎት" ብለው በሚጠሩት ጸሎት በአንጻሩ በቁርአን የመጀመሪያዎቹ ምዕራፎች ላይ ደግሞ፣ "በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩኅ በጣም አዛኝ በኾነው" ተብሎ ተጽፎአል። "እግዚአብሔር አባታችን" በሚለውና "በእግዚአብሔር ስም" ተብሎ በሚቀርበው ስግደትና ጸሎት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

መጽሐፍ ቅዱስ፣ እግዚአብሔር በግላችን እንደሚገናኘን ያስተምራል። እግዚአብሔር እኔን አግኝቶኛል፤ ራሱንም ገልጾልኛል። እርሱ እግዚአብሔር አባቴ ስለሆነ በሐዘኔና በደስታዬ ውስጥ እውናዊ ተሳትፎ ያደርጋል። እግዚአብሔር ትልቅ አምላክ ቢሆንም እንኳ እኛን ለመገናኘት ራሱን ዝቅ አደረገ። በሰማያት ያለው አባታችን ደስታችንን እንደሚጋራ ሁሉ በሐዘናችንም አብሮን ያዝናል[4]። ፍሥሓችንንና ሕማማችንን ይካፈላል።

ቁርአን እግዚአብሔር የቅርብ አምላክ እንደ ሆነ ያስተምራል። ሱራ 50+16 "ሰውንም ነፍሱ (በሐሳቡ) የምታሚውተውን የምናውቅ ስንሆን፣ በእርግጥ ፈጠርነው፤ እኛም ከደም ጋኑ ጅግት ይበልጥ ወደርሱ ቅርብ ነን" ይላል። እግዚአብሔር በቅርበት የሚከታተለን የእርሱን ፈቃድ መፈጸም አለመፈጸማችንን ለማረጋገጥ ነው። ፈቃዱን የምንፈጽመውም ለእግዚአብሔር በመስገድ ነው። በእስልምና "እግዚአብሔር ቅርብ ነው" የሚለው አስተሳሰብ፣ ደስታችንንና ሐዘናችንን ለመጋራት ነው የሚለውን ጉዳይ ታሳቢ ያደረገ አይደለም። ሩኅሩኅ ለሆነው አምላክ እንገዛለን፤ ነገር ግን አምላኬ በሚለው መረዳት እርሱን ማወቅ አንችልም[5]። እግዚአብሔር ጸሎታችንን ሰምቶ ይመልሳል፤ ይሁንና በእኛ ልመና ከእኛ ጋር መስተጋብር አይፈጥርም። መቼም ቢሆን እርሱ የእኛን መከራ አይጋራም።

በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በተለያዩ አጋጣሚዎች፣ በመከራ ውስጥ ባለንበት ጊዜ እንደሚገናኘን ተጽፎአል። አዳምና ሔዋን በገነት ዛፎች መካከል በተሸሸጉበት ስፍራ ተገናኛቸው። እግዚአብሔር ኖኅን እንዲሁም አብርሃምንና

[4] Cragg, *Muhammad and the Christian*, 134-135.

[5] ዝኒ ከማሁ።

ሣራን ተገናኛቸው። እምላካችን አጋርን በጭንቀትዋ ጊዜ ሲያገኛት ሙሴንም በቁጥቋጦ ውስጥ በእሳት አምሳል ተገለጠለት። በተጨማሪም እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በሲና ተራራ ተገለጠላቸው። እግዚአብሔር ለሰዎች በተገለጠባቸው በእያንዳንዱ አጋጣሚ ለተገለጠላቸው ሰዎች ሁሉ ትልቅ ቦታ እንዳለው አመላካች ሲሆን፣ ለሌሎችም በረከት የሚሆንበት ሁኔታ ነበር። እግዚአብሔር ሲገለጥልን ጥሪውን እንሰማለን፣ ለሌሎችም በረከት እንሆናለን።

የእስልምና እምነት አማኙ ግለሰብ ከእግዚአብሔር ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት እንዳያደርግ ወደ ሌላ አቅጣጫ ይመራዋል። ለምሳሌ እግዚአብሔር ለመሓመድ የእስልምናን አስተምህሮ እንዲገልጥላቸው መልአኩ ገብርኤልን ልኮአል። ነገር ግን መገለጡ በመጣባቸው አጋጣሚዎች ሁሉ፣ እግዚአብሔር መሐመድን በግል አልተገናኛቸውም። ይሁንና እግዚአብሔር ሙሴን በቀጥቋጦ ውስጥ በእሳት አምሳል በተገናኘው ጊዜ፣ ከእርሱ ጋር ቀጥተኛ መስተጋብር እንደ ነበረው አመላካች ነገሮች አሉ። አንዳንድ ሙስሊም የነገረ መለኮት ምሁራን ግን ለሙሴ በቀጥቋጦ ውስጥ የተገለጠው መልአኩ ገብርኤል እንጂ እግዚአብሔር አይደለም ይላሉ። አብዛኛው ሙስሊም ይህንን አመለካከት ይቀበላል[6]።

በቁርአን መሓሪው አምላክ ፈቃዱን ለሰዎች እንደ ገለጠ ሲጻፍ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ ፍቅር የሆነው እግዚአብሔር ሰዎችን ባሉበት ሁኔታ በግል እንደሚገናኛቸው ተገልጸአል። እነዚህ የተለያዩ አስተምህሮዎች በቁርአንና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሰፊው ተመዝግበዋል። ቀጥለን በመጀመሪያ ቁርአንን በአጭሩ ከተመለከትን በኋላ፣ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ እንሄዳለን።

ቁርአን

በደቡባዊ ሶማሊያ በጀግማ ውስጥ በምትገኝ መንደር ግብጣ ላይ እንዳለን ሶማሌያዊ የሆነው እንግዳ፣ "ይህቺ ምሽት ከዐሥር ሺህ ምሽቶች ትበልጣለች" አለ። ምሽቱ የረመዳን ጾም ፍቺ (ኢድ አልፈጥር) ቀን ነበር። ተናጋሪው አስተናጋጃችንና ሌሎች ሶማሌያውያን ከአምስቱ የእስልምና የእምነት ተግባራት ውስጥ አንዱ የሆነውን የረመዳን ጾም፣ ለአንድ ወር በታማኝነት ጾመው ጾሙን የሚያሳርጉበት ቀን ነበር።
የተዘጋጀውን ምግብ በጎብረት ከመቋደሳችን በፊት፣ ጋባዣችን ስለበዓሉ ደስታ በተሞላ አነጋገር እንዲህ አለ:— "ይህ ምሽት ከዐሥር ሺህ ምሽቶች ይበልጣል! በዚህ ምሽት ቁርአን ከሰማይ መውረድ የጀመረበትን ቀን እናስባለን።

[6] Badru D. Kateregga and David W. Shenk, *A Muslim and a Christian in Dialogue* (Scottdale, Pa.: Herald Press, 1997), 67.

የሮመዳን ጾምም የእግዚአብሔር መልእክት መገለጥን ስጦታ ወደ ፊት እንድንመለከት ያደርገናል። ዛሬ በዚህ ምሽት ቀኑን የምናከብረው መልእክቱ ከሰማይ ወደ ምድር በመምጣቱ ነው። ስጦታውም አሁን በእጃችን አለ፣ እርሱም ለሰዎች ሁሉ መመሪያ የሆነው ቁርአን ነው"። ቁርአን በሱራ 2÷185 እንዲህ በማለት ያውጃል:—

> (እንድትጾሙ የተጻፈባችሁ) ያ በርሱ ውስጥ ለሰዎች መሪ ከትን መንገድና (እውትን ከውሸት) ከሚለዩም ገላጮች እንቀጾች ሲሆን፣ ቁርአን የተወረደበት የረመዳን ወር ነው፤ ከእናንተም ወሩን ያገኘ ሰው ይጹመው፤ በሺተኛ ወይም በጉዞ ላይ የሆነም ሰው ከሌሎች ቀኖች ቁጥሮችን (በልኩ) መጾም አለበት፤ አላህ በእናንተ ገሩን (ነገር) ይሻል፤ በናንተም ችግሩን አይሻም፤ ቁጥሮችንም ልትሞሉ አላህንም ቅኑን መንገድ ስለመራችሁ ታከብሩትና ታመሰግኑት ዘንድ (ይህንን ደነገግንላችሁ)"። (በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)።

እንዲሁም በሌላ ስፍራ:—

> እኛ (ቁርአኑን) በመወሰኛዪቱ ሌሊት አወረድነው። መወሰኛዪቱም ሌሊት ምን እንደ ሆነች ምን አሳወቀህ? መወሰኛዪቱ ሌሊት ከሺሕ ወር በላጭ ናት (ሱራ 97÷1-3 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)።

የእግዚአብሔር መልእክት ከሰው ልጆች ግምት በላይ የሆነ እውነት እንደ ሆነ ቁርአን ያስተምራል። ተራሮች የቁርአን መልእክት ቢያርፍባቸው እግዚአብሔርን ከመፍራታቸው የተነሣ ይሰነጠቃሉ (ሱራ 59÷21)። እንደ እስልምና አስተምህሮ ይህ እውነት ነው አማኞችን ከማያምኑ ሰዎች የሚለያቸው እንዲሁም እውነተኛ አማኞች ቁርአን ሲነበብ ለእግዚአብሔር በፍርሓትና በመንቀጥቀጥ ይሰግዳሉ (ሱራ 84÷20-22)።

ሙስሊሞች እግዚአብሔር በተለያየ ዘመናት በመላእክት አማካይነት ለሰው ልጆች መልእክት ልኮአል የሚል እምነት አላቸው። መልአኩ ገብርኤል (ጅብሪል) የመጨረሻ መልእክት የሆነውን ቁርአን ለመሐመድ አምጥቶአል። መልአኩ ገብርኤል በተገለጠ ጊዜ መሐመድ ፈርተው ነበር። ገብርኤል በ610 ዓ.ም ለመሐመድ ሲገለጥላቸው፣ መሐመድ በሒራ ዋሻ ውስጥ ነበሩ። መልአኩም ወደ እርሳቸው ቀርቦ እንዲህ ሲል አዘዛቸው:—

> አንብብ በዚያ (ሁሉን) በፈጠረው ጌታ ስም። ሰውን ከረጋ ደም በፈጠረው (ጌታህ ስም)። አንብብ ጌታህ በጣም ቸር ሲኾን፣ ያ በብዕር ያስተማረ፣ ሰውን ያላወቀውን ሁሉ ያሳወቀ ሲሆን (ሱራ 96÷1-5 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)።

ለመጀመሪያ ጊዜ ለመሐመድ የተገለጠላቸው ቃል፣ "እንብብ" የሚል ነበር። ቁርአን የሚለውም ቃል ትርጉም "እንብብ" ማለት ነው። ሙስሊሞች፣ ቁርአን በሰማይ የመጻሕፍት ሁሉ እናት (ኡም አል-ኪታብ) ከተባለው መጽሐፍ የተወሰደ ንባብ እንደ ሆነ ያምናሉ (ሱራ 13÷39)። ለመጀመሪያ ጊዜ ከመጣው መልእክት በኋላ፣ መልአኩ ገብርኤል ወደ መሐመድ በየጊዜው እየመጣ የቀሩትን የሰማያዊውን መጽሐፍ ክፍሎች ያስተምራቸው ነበር። በቁርአን ውስጥ ያሉ መገለጦች ከመልአኩ ገብርኤል በስተቀር በሌላ እንዳልመጡ ቁርአን ያስተምራል[7]።

መሐመድ ከመልአኩ ገብርኤል የመጣላቸውን መልእክት በታማኝነት ምንም ሳይቀንሱና ሳይጨምሩ ለተከታዮቻቸው ያነቡላቸው እንደ ነበር ሙስሊሞች ያምናሉ። ተከታዮቻቸውም የመልእክቱን አብዛኛ ክፍል በአእምሮአቸው የያዙት ሲሆን፣ የተወሰነውን ክፍል ደግሞ ጽፈው አስቀምጠውታል። ይህንንም ተግባር በታማኝነት መፈጸም ትልቅ ጎላፊነት ነበር። የመሐመድ ተከታዮች እያንዳንዱ ጥቅስ (አያህ) መሓሪ ከሆነው ፈጣሪ ወደ ምድር የተላከ መልእክት እንደ ሆነ ያምናሉ። የቁርአን አጠቃላይ መልእክት ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ መሐመድ የመጣው፣ መሐመድ ለሃያ ሁለት ዓመት በምድር ላይ በነበራቸው በአገልግሎት ዘመን ጊዜ ነበር። እያንዳንዱ የቁርአን ምዕራፍ ለመጀመሪያ ጊዜ የተነበበው ደግሞ በመሐመድ ነው።

የቁርአን ምዕራፎች ተሰብስበው የተጻፉት፣ እንደ ጉርጉሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር በ653 ዓ.ም በካሊፍ ኡስማን ዘመን ነው። ይህም ነቢዩ መሐመድ ከሞቱ ከሃያ ዓመት በኋላ ማለት ነው። በዚያን ጊዜ የነበሩ ሌሎች አማራጭ የእጅ ጽሑፎች ተቃጥለዋል። ከዚህም የተነሣ ጥንታዊ አማራጭ የቁርአን እጅ ጽሑፎችን በንጽጽር ለማጥናት አልተቻለም።

ቁርአን ከ1.2 ቢሊዮን ለሚበልጡ የዓለማችን ሙስሊሞች የሕይወት መመሪያ ነው። ሙስሊሞች ለቁርአን እጅግ ትልቅ ክበሬታ አላቸው። በሚሊዮን የሚቈጠሩ ሙስሊሞች፣ የቁርአንን መልእክት ቃል በቃል በአእምሮአቸው ይይዛሉ። ሁሉም የሶማሌ ልጆች የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን ከመጀመራቸው በፊት የተወሰኑትን የቁርአን ምዕራፎች በቃላቸው ያጠናሉ።

[7] Nahl (The Bee) 16:103. Tarif Khalidi, *The Muslim Jesus* (Cambridge: Harvard University Press, 2001), 20-21. Najm (The Star) 16:19-23; Haff (The Pilgrimage) 22:52-53. George W. Baswell Jr., *Islam: Its Prophet, Peoples, Politics, and Power* (Nahville: Broadman & Holman Publishers, 1996), 45.

በሌላ ስፍራ የሚገኙ ሙስሊሞችም ተመሳሳይ ልማድ አላቸው። እያንዳንዱ የቁርአን ጥቅስ (አያህ) የተቀደሰ ነው። በዐረብኛው ቋንቋ "አያህ" ማለት ምልክት ማለት ነው። እንደ እስልምና አስተምህሮ ፍጥረት ለእግዚአብሔር አልሆት ምልክት እንደ ሆነ ሁሉ፣ ቁርአንም የእግዚአብሔር የተከበረ ምልክት ነው። ሕፃናት የቁርአንን ጥቅሶች (አያህዎች) በቃላቸው ባጠኑ መጠን፣ የአላህ የምልክቶቹ ምስጢርና ተአምራቶች በአእምሮአቸው ውስጥ ይቀረጻል የሚልም አስተሳሰብ አለ።

ቁርአን ቤት ውስጥ ካሉ ዕቃዎች በተለየ ሁኔታ ጥንቃቄ ሊደረግለት ይገባል። ማንኛውም ሰው ቁርአንን ለመያዝ ሃይማኖታዊ ዕጥበት ማካሄድ አለበት። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አንዳችም ጽሑፍ እንዲሁም ምልክት መጻፍ የተከለከለ ነው። ቁርአንን ከእናት ቋንቋው ከዐረብኛ ወደ ሌላ ቋንቋ መተርጉም የተከለከለ ሲሆን፣ ቢተረጉም እንኳ የተተረጉመው የቁርአን ቅጅ እንደ ቅዱስ ቁርአን አይታይም። የቁርአን ምዕራፎች በየቀኑ በዓለም ዙሪያ በሚደረጉ የአምልኮተ ስግደት (የሰላት) ሥርዐቶች ወቅት ይነበባሉ። ቁርአን የሙስሊሙ ማኅበረሰብ መሠረት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት መጻሕፍት ተጽፈው የተጠናቀቁት በአንድ ሺህ አምስት መቶ ዓመታት ጊዜ ውስጥ ነው። የመጻፉ ሥራ የተጀመረው በሙሴ ሲሆን፣ የተፈጸመው ደግሞ በዮሐንስ ዘመን ነው። ከአብርሃምና ከእስራኤል ታሪክ ጅማሬ እስከ ቤተ ክርስቲያን ምሥረታ ያለው ዘመን ደግሞ፣ ሁለት ሺህ ዓመት ያህል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲረዱና እግዚአብሔር በመካከላቸው ሰላደረገው ታሪክ የሚተርክ እንዲሁም የነገረ መለኮት አስተምህሮ መጽሐፍ ነው። በውስጡ ያሉ ታሪኮች እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ የሠራቸውን ሥራዎች የሚያስተዋውቁ ናቸው።

የመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያው ክፍል ታሪክ በሕዝቦች ታሪክ ላይ የሚያጠነጥን ነው (ዘፍጥረት 1-11)። ታሪኩም ዓለም ዐቀፋዊ የሆነ ታሪክ ነው። ለምሳሌ የአዳምና የሔዋን ታሪክ በዓለም ላይ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ያሉበትን ሁኔታ የሚያሳይ ታሪክ እንደ ሆነ ክርስቲያኖች ያምናሉ። ሰዎች ሁሉ በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥረናል። እኛ ሁላችንም የተገኘነው ከአዳምና ከሔዋን ነው። ስለዚህ ሁላችንም ሰብአዊ ፍጡሮች ነን። በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ የሰው ዘር ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ ዐምፆአል፣ ኀጢአትም በሰዎች ሕይወትና ኑሮ እንዲሁም በሚኖሩባት ዓለም ላይ ነግሦ።

ሁለተኛው ዐይነት ታሪክ እግዚአብሔር ሰውን ሲጠራና ተስፋ ሲሰጥ የሚያሳይ ነው (ዘፍጥረት 12-50)። በእነዚህ ምዕራፎች እግዚአብሔር አብርሃምን ከሕዝቡ ተለይቶ እንዲወጣ እንዳዘዘው፣ የአሕዛብ ሁሉ አባት እንደሚሆን እንዲሁም አሕዛብ ሁሉ በእርሱ በኩል እንደሚባረኩ የሚገልጹ ታሪኮች ተዘግበዋል። በዘፍጥረት 12-50 ያለው ክፍል ደግሞ ከአብርሃም የተገኙት ሦስት ተከታታይ ትውልዶች፣ ለእግዚአብሔር ጥሪ በመታዘዝ ያለፉበትን የሕይወት ጉዞና የሚዳስስ ነው። ይህ የሕይወት ጉዞም ለሕዝበ እስራኤል ማንነት መሠረት የጣለ ነበር።

ሦስተኛው ታሪክ እግዚአብሔር እስራኤልን መርጦ ለዓለም ሕዝብ ብርሃን በማድረግ፣ ከእስራኤል ጋር የገባውን ቃል ኪዳን፣ ከዘፀአት እስከ ዘዳግም ባሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የሚተርክ ነው። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብፅ የፈርዖን ቀንበር ዐርነት በማውጣት፣ በሲና ተራራ ላይ ተገናኝቸው። ስለዚህ የሙሴ መጻሕፍት በመባል የሚታወቁት መጻሕፍት እግዚአብሔር አብርሃምንና ቤተሰቡን እንዴት እንደ ጠራቹውና እንዴትስ እንደ መራቹው እንዲሁም እስራኤልን በምድረ በዳ በመምራት ከእርሷ ጋር ያደረገውን ቃል ኪዳን የሚተርክ መጽሐፍ ነው።

አራተኛው ታሪክ ከኢያሱ እስከ ዝኖት ዘመን ያለውን የታሪክ ጊዜ የሚያጠቃልል ሲሆን፣ እስራኤላውያን የከነዓንን ምድር እንዴት እንደ ወረሱ እንዲሁም እንደ አገር ራሳቸውን መምራት እንደ ጀመሩ የሚያሳይ ነው። ስምንት መቶ ዓመት የሚሆነው ጊዜ፣ እግዚአብሔር ራሱንና ሥራውን ይፋ ያደረገበት የታሪክ ጊዜ ነው። በእነዚህ ዘመናት እስራኤላውያን እንደ ቃል ኪዳን ሕዝብ በተለያዩ ጦርነቶችና ወረራዎች ውስጥ እንዴት እግዚአብሔርን አክብረውና አስከብረው መኖር እንዳለባቸው እግዚአብሔር አስተምሮአቸዋል። በተጨማሪም እስራኤል እንደ አገር እንዴት መመሥረት እንዳለባት፣ ስለ አስተዳደር፣ ስለሌሎች አማልክት፣ ስለምጣኔ ሀብት፣ ስለሃይማኖታዊ ሥርዐቶች፣ ስለፍትሕ፣ ስለድኽችና፣ ስለመጻተኞች የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደ ሆነ የተገለጠበት ጊዜ ነው። እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ፈቃድ የተግሩት ያለጎጢአት ሆነው አልነበረም። በዚህም ምክንያት የእግዚአብሔርን ፍርድ እንዲሁም ጸጋ እንዲቀበሉ ምክንያት ሆኖአል።

አምስተኛው ታሪክ ስለምርኮና ከምርኮ መልስ ያለውን የእስራኤላውያንን ሕይወት የሚዳስስ ነው። ይህ ወቅት ብዙ ነገረ መለኮታዊ ጉዳዮች የተነሡበት ጊዜ ነበር። ብዙ የነቢያት መጻሕፍትም የተጻፉት በዚህ የታሪክ ጊዜ ውስጥ ነው። የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ሕዝብ በሌሎች ሕዝቦች ተሸንፈው፣ ቤተ

መቅደሳቸውም ፈርሶ ወደ ግዞት አገር እንዴት ሊወሰዱ ቻሉ? ክርስቲያኖች ለወንጌል ያላቸው የመከራ ነገረ መለኮት መሠረት ያገኘው በዚህ የታሪክ ጊዜ ከተፈጸሙት ታሪኮች ነው።

እነዚህ አምስት የታሪክ ዘመናት የተጻፉት እንዲሁም ነገረ መለኮታዊ ትርጓሜ የተሰጣቸው ብሉይ ኪዳን ተብሎ በሚጠራው የመጽሐፍ ቅዱስ አጋማሽ ክፍል ነው። ከዚህ በመቀጠል ስድስተኛውን ታሪክ የምናገኘው አዲስ ኪዳን ተብሎ በሚጠራው የመጽሐፍ ቅዱስ ሁለተኛ አጋማሽ ክፍል ውስጥ ነው።

ስድስተኛው ዘመን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደትና አገልግሎት እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን ምሥረታ የተካሄደበት ዘመን ነው። በክርስቶስ ሕይወት እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እየሆኑ የነበሩት ነገሮች፣ እግዚአብሔር አብርሃምን ከጠራበት ጊዜ አንሥቶ ለነበሩት ጊዜያት ቀጣይ ክፍል ነው። ከመሲሑ ምጽአት በፊት የነበሩት ትንቢቶች፣ ስለመሲሑ መምጣት የተነገሩትን ተስፋዎች በዋነኛነት የያዙ ናቸው:— "ሠረገላውንም ከኤፍሬም ፈረሱንም ከኢየሩሳሌም አጠፋለሁ፤ የሰልፍም ቀስት ይሰባል፤ ለአሕዛብም ሰላምን ይናገራል፤ ግዛቱም ከባሕር እስከ ባሕር፣ ከወንዙም እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ይሆናል" (ዘካርያስ 9÷10)።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ ታሪኮች በርካታ ገጽታ አላቸው። ከሠላሳ ያላነሡ ሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስን የተወሰኑ ክፍሎች ጽፈዋል። የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የተጻፉት በዕብራይስጥ ቋንቋ ሲሆን፣ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ደግሞ በግሪክ ቋንቋ የተጻፉ ናቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ መጻሕፍት የተለያየ ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጽ ያላቸው ናቸው። ከእነዚህም ሥነ ጽሑፋዊ ቅርጾች መካል ታሪክ፣ ቅኔ፣ ግጥም፣ ትንቢት፣ አቡቀለምሲሳዊ፣ የግጽናናትና የግሣጼ ደብዳቤዎች ዋነኛውን ቦታ ይይዛሉ።

ብዙ ሰዎች ታሪካዊ ጽሑፎች ተአማኒ ናቸውን? በሚለው ጉዳይ ላይ፣ የተለያዩ ጥያቄዎችን ያነሣሉ። የብሉይ ኪዳን ታሪኮች የተጻፉት በዚያን ዘመን ከእስራኤል ውጪ የነበሩት ሕዝቦች ትክክለኛ ታሪክ ለመዘገብ ምንም ዐይነት ትኩረት በማይሰጡበት ጊዜ ነው። አንዳንድ የግኅበረሰብ ክፍሎች ለታሪክ ትኩረት የማይሰጡበት ዐቢይ ምክንያትም ታሪክ ትርጉመ ቢስ ድግግሞሽ ነው የሚለውን አስተሳሰብ ታሳቢ ስለሚያደርጉ ነው። የቻይና ነገሥታትን የመሰሉ ጥቂት ሰዎች፣ ስለአገራቸውና ስለሕዝባቸው ታሪክ በመጻፍ ትክክለኛውን ታሪክ ለማሳየት ሞክረዋል። ቻይናውያን የአገራቸውን ታሪክ በመጻፍ በአገሪቱ ጥሩ መሪዎች በተነሡበት ወቅት ለአገሪቱ የስኬት ዘመን

እንደ ነበር፣ በእንጻሩ ደግሞ ከፉ መሪዎች በተነሡበት የታሪክ ዘመን መከራ ወደ ሕዝቡ እንደ መጣ አሳይተዋል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ታሪኮች የተለያየ ይዘት አላቸው። ታሪኮቹም በእያንዳንዱ ትውልድ የተፈጸሙትን ከሥተቶች ይዘግባሉ። ዘገባዎቹ እውነተኛ ታሪኮች ሲሆኑ፣ የሰዎችን ሥናይና እኩይ ምግባራት የሚይዙ ናቸው። ለምሳሌ እግዚአብሔር እንደ ልቤ ብሉ የጠራው ንጉሥ ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር ዝሙት መፈጸሙን እንዲሁም የቤርሳቤህን ባል እንዳስገደለ ተጽፎአል። የሃያኛው ምዕተ ዓመት የክርሰ ምድር ጥናት ተመራማሪዎች፣ በርካታ የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ታሪኮችን እውነተኝነት በጥናታቸው ለማረጋገጥ ችለዋል። ዊሊያም አልብራይት የተሰኘው የሃያኛው ክፍለ ዘመን ዕውቅ የክርሰ ምድር ተመራማሪ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ታሪኮች፣ ስለጥንታዊው ዘመን ከሚናገሩ ታሪኮች ሁሉ ይልቅ እጅግ ተአማኒ የሆኑ ታሪኮች እንደ ሆኑ ተናግሮአል[8]።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሓፍያን፣ የታሪክ ክሥተቶችን እውነተኝነት ለመጠበቅ ከፍተኛ ትኵረት የሰጠበት ዐቢይ ምክንያት ምንድን ነው? ጸሓፍያኑ እግዚአብሔር በሰብአውያን ታሪክ ውስጥ እውናዊ ተሳትፎ እያደረገ እንዲሁም የታሪኩን ፍሰት እየተቈጣጠረ እንዳለ ፈጽመውና ጨልጠው በማመናቸው ነው። በዚህ ዐይነቱ ከፍተኛ ጥንቃቄ ውስጥ የተጻፈ መጽሐፍ ለሰው ልጆች ሁሉ ትልቅ ትርጉም ያለው መጽሐፍ ነው። የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ሕዝብ የነበሩት እስራኤላውያን ይህን እምነት በዕለት ተዕለት ኑሮአቸው ይፋ ያደርጉ ነበር። ከዚህም የተነሣ የእስራኤል ታሪክ በጥንቃቄ ተዘግቦአል።

በጥንት ዘመን የነበረው ይህ ከፍተኛ የሆነ ጥንቃቄ፣ በአሁኑ ጊዜ ያሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጆች ያለ ስሕተትና ብልሽት የጥንቱ መጽሐፍ ቅዱስ ቀጥተኛ ቅጆች መሆናቸውን የሚያረጋግጡልን ናቸው። በሌላ አንጻር ግን ቁርአን ነቢዩ መሐመድ ከሞቱ ከ20 ዓመታት በኋላ በካሊፍ ኡስማን ዘመን ዘይድ ካዘጋጀው ቁርአን በስተቀር ሌሎች ሰዎች ያዘጋጅዋቸው ቁርአኖች እንዲቃጠሉ ተደርገዋል። ነገር ግን በሺዎች የሚቈጠሩ ጥንታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፎች አሉ። ከእነዚህም ውስጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን መጻሕፍት እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን አባቶች ተአማኒነት የላቸውም ብለው ያወገዟቸውን መጻሕፍትንም የሚጨምር ነው።

[8] W. F. Albright, *From the Stone Age to Christianity* (Maryknoll, N. Y.: Orbis Books, 1984), 45.

የብሉይ ኪዳንን ተአማኒነት በተመለከተ የሙት ባህር ጥቅሎች ወይነተኛ መረጃ ይሰጣሉ። የሙት ባህርን ጥቅል ያገኙት እረኞች ሲሆኑ፣ እንደ ጉርጉሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር በ1947 ዓ.ም በሙት ባህር አካባቢ ባለ ዋሻ ውስጥ ከሁለት ሺህ ዓመት በላይ ዕድሜ ያላቸው የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ተገኝተዋል።

በተጨማሪም የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን በርካታ ጥንታዊ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍትን ከተለያዩ ቦታዎች አግኝተዋል። በአሁኑ ጊዜ ቢያንስ አምስት ሺህ የሚሆኑ እጅግ ጥንታዊ የሆኑ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ቅጆች በእጃችን አሉ። እነዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት ተቀምጠው የተገኙበት ሁኔታ እጅግ በጣም የሚያስደንቅ ነው። ለምሳሌ ሰባ አምስት የሚሆኑ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ክፍሎች የተገኙት፣ እንደ ጉርጉሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር 1897 ዓ.ም በግብፅ አገር አክሲርንቾስ በተባለው ቦታ፣ መጻሕፍቱ እንዳይበላሹ በዐዞ ቈዳ ተጠቅልለው በክብር ከተቀመጡበት ስፍራ ነው። ከእነዚህም የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ክፍሎች ውስጥ አንዱ የዮሐንስ ወንጌል ሲሆን፣ ይህም መጽሐፍ እንደ ጉርጉሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር በ135 ዓ.ም የተጻፈ እንደ ሆነ ይገመታል። እነዚህ ጥንታዊ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ትክክለኛና ተአማኒነት ያለውን የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ለንባብ እንዲያቀርቡ ረድቶአቸዋል። ኤፍ. ጄ. ኤ. ሆርት የተባሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁር በእጃችን ያሉት የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት፣ ቀደምት/አንጋፋ (አርጅናል) ከሆነው መጽሐፍ ጋር ሲነጻጸሩ፣ ከአንድ ሺህ ንጽጽሮች ውስጥ ምናልባት አንድ ልዩነት ቢገኝባቸው እንጂ፣ ከዚያ ያለፈ ልዩነት ሊገኝባቸው በፍጹም አይችልም የሚል አስተያየት ሰጥተዋል[9]።

እነዚህ ጥንታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጆች፣ ቀደምት/አንጋፋ የሚባሉት ጽሑፎች አሁን በእጃችን ካሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጆች ጋር ሲነጻጸሩ የተለየ ይዘት እንደሌላቸው የሚያረጋግጡ ናቸው። ይሁንና በተለያዩ ምክንያቶች አሁን የምንጠቀምባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጆች፣ ከጥንታዊ ጽሑፎች ጋር ልዩነት ቢፈጥሩ እንኳ ጥንታውያኑ መጻሕፍት በእጃችን እስካሉ ድረስ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን ይህን ችግር ለማስወገድ የከለሳ ሥራ ሊሠሩ ይችላሉ። ያልተዛባና ያልተዛነፈ የመጽሐፍ ቅዱስን መልእክት ከትውልድ ወደ ትውልድ ማስተላለፍ የነገረ መለኮት ምሁራን ቀዳማይ ዐላማ ነውና።

ከርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው የሚል ጽኑ እምነት አላቸው። መሲሑ ኢየሱስም የእግዚአብሔር ቃል ነው ብለው ያምናሉ። ይህ

[9] Sean Kealy, *The Changing Bible* (Nairobi: KUC, n.d.). 87.

ማለት ምን ማለት ነው? የድነት ሥራ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉት ርእሰ ጉዳዮች መካል ዋነኛው ርእስ ነው። የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት እግዚአብሔር በመሲሑ በኢየሱስ በኩል ሰዎችን እንዳዳነ ያስተምራሉ። በጽሑፍ ሰፍሮ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል (መጽሐፍ ቅዱስ) ለዘላለም ሕያው ከሆነው ከእግዚአብሔር ቃል ማለትም ከመሲሑ ከኢየሱስ ጋር ኅብረት እንድናደርግ ምሪት ይሰጠናል።

መሲሑ ኢየሱስ እንዲህ ብሎአል:—

> እናንተ በመጻሕፍት የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ይመስላችኋልና እነርሱን ትመረምራላችሁ፣ እነርሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው፣ ነገር ግን ሕይወት እንዲሆንላችሁ ወደ እኔ ልትመጡ አትወዱም (ዮሐንስ 5÷39-40)።

መሰለሞችና የቀደሙት መጻሕፍት

ሙስሊሞች ብዙ ጊዜ ስለመጽሐፍ ቅዱስ ግራ ይጋባሉ። ይሁን እንጂ ቁርአን ሙስሊሞች ሁሉ በቀደምቶቹ ቅዱሳት መጻሕፍት እንዲያምኑ ያዛል። ቁርአን ቀደምቶቹን መጻሕፍት በአራት ይከፍላቸዋል።

1. ሱሐፍ (የተወሰኑ ገጾች):— ለአብርሃም የተሰጠው መገለጥ ሲሆን፣ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ጠፍቶአል።
2. ተውራት (ቶራህ):— ለነቢዩ ሙሴ የተሰጠ መገለጥ ነው።
3. ዘቡር (መዝሙራት):— ለንጉሥ ዳዊት የተሰጠ መገለጥ ነው።
4. ኢንጂል (ወንጌል):— ለመሲሑ ኢየሱስ የተሰጠ መገለጥ ነው።

ሙስሊሞች ሁሉ በእነዚህ መጻሕፍት ውስጥ ያሉት መልእክቶች፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ ለሰው ልጆች የተሰጡ መገለጦች እንደ ሆኑ ያምናሉ። በተጨማሪም እነዚህን መጻሕፍት ማንኛውም ሰው እንብቦ ይጠቀምባቸው ዘንድ ክርስቲያኖች ለሰው ልጆች ሁሉ የማቅረብ ግዴታ እንዳለባቸው ቁርአን ያዛል[10]።

[10] በኬንያና በሶማሊያ የሚገኙ ክርስቲያኖች ቁርአን የእግዚአብሔር ቃል ናቸው የሚላቸውን መጻሕፍት ማለትም አምስቱ የሙሴ መጻሕፍትን፣ መጽሐፈ መዝሙርንና ወንጌላትን ለሙስሊሞች እያዘጋጁ ያቀርባሉ። በዚህም ጥናት ውስጥ በርካታ ሙስሊሞች መሲሑ ማን ነው? እንዲሁም ተልእኮውስ ምን ነበር? የሚሉትን መሠረታዊ ነጥቦች በውል እንዲገነዘቡ ያደረገ ሲሆን፣ ይህም ጥናት አርባ በሚበልጡ ቋንቋዎች እንዲተረጉም ተደርጎአል። በየዓመቱም በሺዎች የሚቆጠሩ ሙስሊሞች

እንደ ሙስሊሞች እምነት፣ ከእነዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት በኋላ እግዚአብሔር የመጨረሻው መልእክት የሆነውን ቁርአንን፣ በነቢዩ መሐመድ በኩል ይፋ አድርጎአል፣ እንዲሁም ቁርአን ከእርሱ በፊት ለነበሩት ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ ማጠቃለያ እንዲሁም እነዚህን መጻሕፍት የሚያብራራ መጽሐፍ ነው። ምንም እንኳ ሙስሊሞች ለአብርሃም የተሰጠው መገለጥ (ሱሐፍ) ጠፍቶአል የሚል እምነት ቢኖራቸውም፣ ክርስቲያኖችና አይሁዶች (የመጽሐፉ ሰዎች) እግዚአብሔር የሰጣቸውን ቅዱሳት መጻሕፍት ሳይጠፉ እስከ ዛሬ ድረስ ጠብቀው አቆይተዋል። ቁርአን የመጨረሻው መልእክት እንዲሁም የቀድሞዎቹን መጻሕፍት የሚያብራራ መጽሐፍ ነው የሚል እምነት ቢኖርም እንኳ፣ ለቀድሞዎቹ መጻሕፍት ትልቅ አክብሮት እንዳለው ሊሰመርበት የሚገባ ጉዳይ ነው። ቁርአን እነዚህ መጻሕፍት የክርስቲያኖችም ሆነ የአይሁዶች እምነትና ሕይወት ምን መምሰል እንዳለበት የሚያስተምሩ እንዲሁም ለሰው ዘር ሁሉ፣ "መመሪያና ብርሃን" የሚፈነጥቁ መጻሕፍት መሆናቸውን በግልጽ ያስተምራል (ሱራ 5÷44-47)።

ቁርአን ሙስሊሞችንም ሆነ ነቢዩ መሐመድን እንዲህ ሲል ያዛቸዋል:—

> ወደ አንተም ካወረድነው በመጠራጠር ውስጥ ብትሆን እነዚያን ከአንተ በፊት መጽሐፉን የሚያነቡትን ጠይቅ፣ እውነቱ ከጌታህ ዘንድ በእርግጥ መጥቶልሃል፣ ከተጠራጣሪዎቹም አትሁን (ሱራ 10÷94)።

በሌላ ስፍራም ቁርአን ለሙስሊሞች:—

> አላህ የነዚያን መጽሐፉን የተሰጡትን ቃል ኪዳን ለሰዎች በእርግጥ ታብራሩታላችሁ፣ አትደብቁትምም በማለት የያዘባቸውን (አስታውሱ) (ሱራ 3÷187 በትንፍ ያለውን ይጨምራል)።

ነገር ግን ቁርአን ለሙስሊሞችና ለመሐመድ እነዚያ የመጽሐፉ ሰዎች (ክርስቲያኖችና አይሁዶች):—

> "አላህም ወደ አንተ ካወረደው ከከፊሉ እንዳያሳስቱህ ተጠንቀቃቸው" (ሱራ 5÷49 በትንፍ ያለውን ይጨምራል)።

ትምህርቱን እንዲከታተሉ ዕድል ሰጥቶአቸዋል። ለትምህርቱም ያላቸው ፍላጎትና አቀባበል እጅግ የሚያስደንቅ ነው።

በመካከለኛው ምሥራቅ የሚገኙ ክርስቲያኖች ደግሞ፣ ይህን የሙስሊሞችን የቃል እግዚአብሔር ፍላጎት ለማርካት፣ ለሕፃናት በየቀኑ የሚጠኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን በሥዕል እያስደገፉ ማቅረብ በመቻላቸው፣ በዐሥር ሺዎች የሚቆጠሩ መጻሕፍት ታትመው በክልሉ እንዲሠራጩ ተደርጎአል።

በግለት ያስጠነቅቃል። ቁርአን ከመጽሐፉ ሰዎች (ክርስቲያኖችና አይሁዶች) ውስጥ የአንዳንዶቹን ሥራ ቢቃወምም፣ ለመጽሐፉ ሰዎች አክብሮት አለው። የመጽሐፉ ሰዎችም መጻሕፍቶቻቸውን በጥንቃቄ እንዲጠብቁ እንዲሁም ማንኛውም ሰው የመጻሕፍቱ ተጠቃሚ ይሆን ዘንድ በሮችን መክፈት እንዳለባቸው ያዛል[11]።

ተበላሽቶአልን?

ሙስሊሞች መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ መገለጥ እንደ ሆነ ቢያምኑም፣ ቁርአንንና መጽሐፍ ቅዱስን ማስታረቅ በአያሌው ይቸግራቸዋል። በዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ ኢብራሂም የተባለው ሰው በክርስትና ውስጥ ካሉ ዋና ዋና ችግሮች መካከል አንዱ፣ መጽሐፍ ቅዱስ "የመበላሸቱ" ጉዳይ እንደ ሆነ ተናግሮ ነበር። ኢብራሂም መጽሐፍ ቅዱስ ተበላሽቶአል ከሚለው አስተሳሰቡ በተጨማሪ፣ ሌሎች ጥያቄዎችም ነበሩት። ኢብራሂምን ካስጨነቁ ነገሮች መካል አንዱ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ዋንኛ ክፍል ታሪክ የመሆኑ ጉዳይ ነው። ታሪክ ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል እንዴት ሊሆን ይችላል? የሚለው ጉዳይ ደግሞ የበርካታ ሙስሊሞች ጥያቄ ነው።

የኢብራሂም ሁለተኛው ጥያቄ፣ በቁርአንና በመጽሐፍ ቅዱስ መካከል ሊታረቁ የማይችሉ እጅግ ብዙ ልዩነቶች አሉ የሚለው ነጥብ ነው። በኬንያ በሚገኘው ኬንያታ ዩኒቨርስቲ ቅጥር ግቢ ውስጥ ከሙስሊሞች ጋር ያደረግነው ውይይት ይህን ችግር የሚያስረዳ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ እኔና ጃማ ሑሴይን የዓለም ሃይማኖቶች የሚል ትምህርት በዚሁ ዩኒቨርስቲ ስናስተምር፣ እንድ ተማሪ ጃማ ሑሴይንን እንዲህ ሲል ጥያቄ ጠየቃቸው፦—

> ሁሉም ሙስሊሞች መጽሐፍ ቅዱስን ማመን አለባቸው ብለሃል። ነገር ግን በቁርአንና በመጽሐፍ ቅዱስ መካከል ልዩነቶች አሉ። ለምሳሌ አራቱ ወንጌላት የክርስቶስን ሞትና ትንሣኤ ያስተምራሉ፤ ነገር ግን ቁርአን ኢየሱስ እንደ ሞተና ሞትንም ድል አድርጎ እንደ ተነሣ ይክዳል።

ጃማ ሑሴይን ለተማሪው እንዲህ ሲል መለሱለት፦—

> በቁርአንና በመጽሐፍ ቅዱስ መካከል ልዩነት የመጣው መጽሐፍ ቅዱስ በመበላሸቱ ምክንያት ነው። ሙስሊሞች በአንጋፋው (በእርጅናሉ) መጽሐፍ ቅዱስ እናምናለን፤ ነገር ግን አሁን በተበላሸውና በክርስቲያኖችም እጅ በሚገኘው መጽሐፍ ቅዱስ አናምንም።

እኔም ለጃማ ሑሴይን የሚከተለውን ጥያቄ አቀረብሁ፣ "መጽሐፍ ቅዱስ ተበላሽቶአል ብለው የሚናገሩት ከምን መረጃ ተነሥተው ነው?"። ጃማ ሑሴንም፣ "ከቁርአን መረጃ ተነሥቼ ነው፤ ቁርአን ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን እንዳበላሹት ያስተምራል" ሲሉ መለሱልኝ። እኔም፣ "ቁርአን ይህ ዐይነቱን ነገር የሚያስተምረው በየትኛው ክፍል ነው?" ስል ጠየቅሁ። ጃማ ሑሴይንም፣ "የየትኛው የቁርአን ክፍል ይህ ዐይነቱን ትምህርት እንደሚያስተምር ከትምህርቱ ክፍለ ጊዜ በኋላ በትክክል አመላክትሃለሁ" አሉኝ።

የትምህርቱ ክፍለ ጊዜ ከተጠናቀቀ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ወደ ቢሮአቸው ወስደውኝ፣ በስፋት የሚታወቀውን የሚከተለውን የቁርአን ክፍል ለትምህርታቸው ማጠናከሪያነት አሳዩኝ፦—

> ከእነርሱም እርሱ ከመጽሐፉ ያይደለ ሲኾን፣ ከመጽሐፉ መኾኑን እንድታስቡ በመጽሐፉ ምላሶቻቸውን የሚያጣምሙ ክፍሉች አሉ። እርሱ ከአላህ ዘንድ ያልሆነ ሲኾን እርሱ ከአላህ ዘንድ ነውም ይላሉ። እነርሱ የሚያውቁ ሲኾኑም በአላህ ላይ ውሸትን ይናገራሉ (ሱራ 3+78)።

እኔም ለጃማ ሑሴይን እንዲህ ስል ጥያቄ አቀረብሁ፦— "እስካሁን ድረስ እኔም ሆንሁ እርስዎ መጽሐፍ ቅዱስን ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ በምላሳችን ጠቅሰነው አናውቅምን? ታዲያ ይህ የቁርአን ክፍል ይህ ዐይነቱ ስሕተት እንዳይፈጠር የሚያስጠነቅቅ አይደለምን? እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ ይህን ክፍል በመጥቀስ መጽሐፍ ቅዱስ ተበላሽቶአል ማለት ትክክል አይመስለኝም፤ ክፍሉ መጽሐፍ ቅዱስ ተበላሽቶአል ወደሚል ድምዳሜ የሚያደርስ ቅንጣት ታህል ፍንጭ የለውም"።

በእርግጥ ቁርአንም ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ለዘላለም ጸንቶ እንደሚኖር ይናገራሉ። ቁርአን፣ "የአላህም ንግግሮች ለዋጭ የለም" (ሱራ 6+34) ሲል፣ መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ "አቤቱ ቃልህ በሰማይ ለዘላለም ይኖራል" (መዝ 119+89) ይላል።

እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ በዓለም ዙሪያ የሚገኘው የሙስሊሙ ማኅበረሰብ በአጠቃላይ፣ አሁን ያለው መጽሐፍ ቅዱስ ተአማኒነት የጐደለው መጽሐፍ ነው

[11] ከዚህ በላይ ያለውን የግርጌ ማስታወሻ ይመለከቷል።

የሚል አመለካከት አለው። ጃግ ሑሴይን የተናገሩትም ንግግር በየመስጊዱ ከሚነገረው ንግግር ቅንጣት ታህል የተለየ አይደለም።

ክርስቲያኖችና ቁርአን—ሙስሊሞችና መጽሐፍ ቅዱስ

ሙስሊሞች በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ አመኔታ ማጣታቸውና ማንቋሸሻቸው ክርስቲያኖችን በአያሌው ያሳዝናቸዋል። በክርስቲያኖች እይታ ሙስሊሞች መጽሐፍ ቅዱስን ላለማመናቸውና ለማንቋሸሻቸው በቂ የሆነ ቁርአናዊ መረጃ የለም የሚል ጽኑ አቋም አላቸው። ይሁንና ቁርአንን የማብራራቱና የመተርጐሙ ሥራ የሙስሊሞች ኀላፊነት ነው። ክርስቲያኖች ስለቀድሞዎቹ ቅዱሳት መጻሕፍትም ሆነ ስለሌሎች ርእሰ ጒዳዮች የራሳቸውን አመለካከት በቁርአን ላይ መጫን ያለባቸው አይመስለኝም።

ይሁን እንጂ ሙስሊሞችም ሆኑ ክርስቲያኖች ቁርአን ስለቀድሞዎቹ መጻሕፍት የሚያስተምረውን ትምህርት በሚገባ ማወቅ አለባቸው። ቁርአን ስለቀድሞዎቹ መጻሕፍት ሁለት ትልልቅ ትምህርቶች አሉት።

1. የቀድሞዎቹ መጻሕፍት ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጡ መለኮታዊ መገለጦች ናቸው።
   "ከርሱ በፊት ያሉትን መጽሐፍት የሚያረጋግጥ ሲኾን መጽሐፉን (ቁርአንን) ባንተ ላይ ከፋፍሉ በእውነት አወረደ። ተውራትንና ኢንጂልንም አውርዷል" (ሱራ 3+3 በትንፍ ያለውን ይጨምራል)።

   ወደ አንተም መጽሐፉን ከበፊቱ ያለውን መጽሐፍ አረጋጋጭና በርሱ ላይ ተጠባቂ ሲኾን በእውነት አወረድን (ሱራ 5+48)።

   እላንተ የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! ተውራትንና ኢንጂልን ከጌታችሁም ወደናንተ የተወረደውን እስከምታቆሙ (እስከምትሠሩባቸው) ድረስ በምንም ላይ አይደላችሁም በላቸው (ሱራ 5+68 በትንፍ ያለውን ይጨምራል)።

   ለሙሳንና ለሃሩንም እውነትንና ውሸትን የሚለይን ብርሃንንም ለጥንቁቆችም መገሠጫን በእርግጥ ሰጠናቸው (ሱራ 21+48፣ 10+64)።

   የኢንጅልም ባለቤቶች በውስጡ አላህ ባወረደው ሕግ ይፍረዱ፣ አላህም ባወረደው የማይፈርድ ሰው፣ እነዚያ አመጠኞች እነርሱ ናቸው (ሱራ 5+47፣ 11+17፣ 21+48)።

   "የአላህ ቃላት መለወጥ የላትም" (ሱራ 10+64)።

ወንጌልን በተመለከተ ቁርአን እንዲህ ይላል:—

   በፍላጐታቸውም (በነቢያቶቹ ፊለግ) ላይ የመርየምን ልጅ ኢሳን ከተውራት በስተፊቱ ያለውን አረጋጋጭ ሲኾን አስከተልን፣ እንጂልንም በውስጡ ቀጥታና ብርሃን ያለበት በስተፊቱ ያለችውን ተውራትንም የሚያረጋግጥ ለጥንቁቆችም መሪና ገሳጭ ሲኾን ሰጠነው (ሱራ 5+46 በትንፍ ያለውን ይጨምራል)።

እንዲሁም ቁርአን ነቢዩ መሐመድን እንዲህ ሲል ይመክራል:—

   ወደ አንተም ካወረድነው በመጠራጠር ውስጥ ብትኾን እነዚያን ከአንተ በፊት መጽሐፉን የሚያነቡትን ጠይቅ (ሱራ 10+94)።

አንዳንዴ ቁርአን የእግዚአብሔርን ቃል ማንም ሊያበላሸው እንደማይችል ያስተምራል። ቀጥሎ ያለው የቁርአን ክፍል ይህንን እውነት ያረጋግጣል:—

   ከበፊትህም መልእክተኞች በእርግጥ ተስተባበሉ፣ በተስተባበሉብትም ነገርና በተሠቃዩት ላይ እርዳታችን እስከመጣላቸው ድረስ ታገሡ፣ የአላህም ንግግሮች ለዋጭ የለም፣ ከመልእክተኞቹም ወሬ (የምታረጋጋበት) በእርግጥ መጣልህ (ሱራ 6+34 በትንፍ ያለውን ይጨምራል)።

2. የመጽሐፉ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ማክበርና በጥንቃቄ መጠበቅ አለባቸው።

ቁርአን ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን እንዳያበላሹት፣ እንዳይደብቁት፣ ለጥቅም ብለው እንዳይለውጡት እንዲሁም ከወደደ ምንባቡ ውጪ እንዳያብራሩት ይመክራል:—

   አላህ የነዚያ መጽሐፉን የተሰጡትን ቃል ኪዳን ለሰዎች በእርግጥ ታብራሩታላችሁ አትደብቁትምም፣ በግለት የያዘባቸውን (አስታውሱ) (ሱራ 3+187 በትንፍ ያለውን ይጨምራል)።

እንዲሁም:—

   ከነሱም እርሱ ከመጽሐፉ ያይደለ ሲኾን ከመጽሐፉ መሆኑን እንድታስቡ በመጽሐፉ ምላሶቻቸውን የሚያጣምሙ ክፍሎች አሉ። እርሱ ከአላህ ዘንድ ያልሆነ ሲኾን እርሱ ከአላህ ዘንድ ነው ይላሉ። እነርሱ የሚያውቁ ሲሆኑም በአላህ ላይ ውሸትን ይናገራሉ (ሱራ 3+78)።

የመጽሐፉ ሰዎች ሆይ! እውነቱን በውሽት ለምን ትቀላቅላላችሁ? እውነቱንም እናንተ የምታውቁ ስትኾኑ ለምን ትደብቃላችሁ (ሱራ 3÷71)::

ለነዚያም መጽሐፉን በእጆቻቸው ለሚጽፉና ከዚያም በርሱ ጥቂትን ዋጋ ሊገዙበት ይህ ከአላህ ዘንድ ነው ለሚሉ ወዮላቸው፤ ለነርሱም ከዚያ እጆቻቸው ከጻፉት ወዮላቸው፤ ለነሱም ከዚያ ከሚያፈሩት (ጎጢአት) ወዮላቸው (ሱራ 2÷79 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)::

በእርግጥ ቁርአን ስለራሱ የመጨረሻ መልእክት እንዲሁም የቀድሞዎቹን መጻሕፍት የሚያብራራ መጽሐፍ እንደ ሆነ በግልጽ ይናገራል:: ይህ እንዳለ ሆኖ፣ ሙስሊሞች ወደ መጽሐፉ ሰዎች ሄደው ለሕይወታቸው የሚጠቅማቸውን ምክር እንዲጠይቁአቸው ያዛል::

በአንድ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ከሙስሊሞች ጋር በነበረኝ ውይይት ለሙስሊም ወዳጆቼ፣ "ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን አበላሽተዋል እያላችሁ አትክሰሱ:: ይልቁንም ከእኛ ጋር ቁጭ ብላችሁ የመጽሐፍ ቅዱሱን ትምህርት ከእኛ ልትሰሙ ይገባል:: ቁርአን የሚያስተምራችሁ ይህን እንድታደርጉ ነው" በማለት ቃለ እግዚአብሔርን በጎብረት እንድናጠና ጥሪ አደረግሁላቸው::

በተቃራኒው ሙስሊም ባልንጀራዬ እንዲህ ሲል መለሰልኝ:— "እኛ እናንተን መስማት እንዳለብን ይገባናል፤ ነገር ግን እናንተ የምትመክሩንን ምክር ሁሉ እንዳንቀበል ቁርአን ያስተምረናል:: ምክንያቱም እናንተ ሙስሊሞችን ልታሳስቱ ትችላላችሁና"::

ሙስሊም ጓደኛዬ እንደ ተናገረው ሙስሊሞች ወደ ክርስቲያኖች እንዲሄዱ እንዲሁም ክርስቲያኖች ስለመጽሐፋቸው ማብራሪያ እንዲሰጥዋቸው ታዘዋል:: እንዲሁም ሙስሊሞች በክርስቲያኖች ምክር ከእውነተኛው የእስልምና እምነት እንዳይስቱ ቁርአን ያስተምራል:: ይህ እንዳለ ሆኖ ክርስቲያኖች ከሙስሊሞች ጋር በሚያደርጉት ውይይት የታዘብነው ቁም ነገር ሙስሊሞች መጽሐፍ ቅዱስን በተመለከተ ያላቸው መረጃ ፍጹም የተዛባ መሆኑን ነው::

በጀርመን አገር ዳግም መጥምቃውያን ከሙስሊሞች ጋር በነበረን ውይይት ላይ ከሙስሊሞች በኩል የእስልምናን አመለካከት ያቀረበው ምሁር፣ "የእስልምና ነገረ መለኮት ምሁር እንዲሁም የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቅ የሆነ ሙስሊም ሰው

ታውቃለህ?" የሚል ጥያቄ ቀርቦለት ነበር:: እርሱም፣ "እንደዚህ ዐይነት ሙስሊም መኖሩን ሰምቼ አላውቅም" ሲል ነበር መልስ የሰጠው::

እስካሁን ድረስ በየትኛውም የሙስሊም ዩኒቨርስቲ የመጽሐፍ ቅዱስ ወይም የክርስትናን አስተምህሮ የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ አልተከፈተም:: በተቃራኒው ግን ብዙ የክርስቲያን ዩኒቨርስቲዎች እስልምናንና ቁርአንን የሚያጠና የጥናት ዘርፍ አላቸው:: እንዲሁም በቁርአን ትምህርት በጣም የተካኑና የተከበሩ በርካታ ክርስቲያን ሊቃውንት አሉ:: እነዚህ ክርስቲያኖች ስለእስልምና ማብራሪያ እንዲሰጡ በሙስሊሞች እንኳ ሳይቀር በርካታ ግብዣዎች ይቀርብላቸዋል::

በክርስቲያኖችና በሙስሊሞች መካከል ይህ ዐይነቱ ልዩነት እንዴት ሊፈጠር ቻለ? ለሚለው ጥያቄ መልስ የምናገኘው በሚቀጥለው ምዕራፍ ሲሆን፣ ስለ "ታንዚል" (ከሰማይ የወረደ መልእክት) እና ስለ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መገለጥ (ተሰግዎ) በሰፋት እንዳስሳለን::

ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የተለያዩ አመለካከቶች

በለንደን ከተማ ደቡባዊ ክፍል በሚገኘው መስጊድ ውስጥ፣ ለነበረው በመቶ ለሚቆጠር ሕዝብ የሙስሊሞቹ ተወካይ፣ "ዳዊት መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንዳልሆነ ገልጸአል" ሲል ተናገረ:: እኔም ጸሓፍያኑ የተከተሉት የሥነ ጽሑፍ፣ ፊሊጣዊ አነጋገሮች እንዲሁም የጸሓፍያኑ ተሞክሮ የመጽሐፍ ቅዱስ ይዘት አካል ናቸው አልሁት:: የሙስሊሞቹ ተወካይ ዳግም ስለቁርአን ሲያብራራ፣ "ቁርአን የባህል ወይም የሰዎች ልምምድ ተጽእኖ ያለበት መጽሐፍ ሳይሆን፣ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ የወረደ ንጹሕ መልእክት ነው" ሲል ተናገረ::

በዚያን ሌሊት የምንነጋገረው፣ "የቅዱሳት መጻሕፍት መገለጥ" በሚለው ርእሰ ጉዳይ ላይ ነበር:: በርእሰ ጉዳዩም ላይ ለሦስት ሰዓት ያህልም ተወያይተናል:: በመጨረሻም እግዚአብሔር ቅዱስ ቃሉን ለቅዱሳን ሰዎች ገልጦአል በሚለው ነጥብ ላይ ተስማማን:: ምንም እንኳ በዚህ ነጥብ ዙሪያ መግባባት ላይ ብንደርስም፣ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች የማይስማሙባቸው በርካታ ርእሰ ጉዳዮች አሉ:: ከእነዚህም ውስጥ:—

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ለስተምህሮ፦— ቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፉት በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ነው።
ቁርአናዊው ትምህርት፦— በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ያለው መልእክት ቀጥታ ከሰማይ የወረደ (ታንዚል) ነው።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ለስተምህሮ፦— እግዚአብሔር በሰዎች ሕይወት ውስጥ እውናዊ ተሳትፎ በማድረግ ራሱን ገልጦአል።
ቁርአናዊው ትምህርት፦— እግዚአብሔር በነቢያቱ አማካይነት ፈቃዱን ይፋ አድርጎአል።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ለስተምህሮ፦— ቅዱሳት መጻሕፍት የሰብአውያንን ታሪክ ያገናዘቡ ናቸው። ይህም ማለት የሰብአውያን አካሄድ እግዚአብሔርን ግድ የሚለው ጉዳይ ስለሆነ፣ በሰዎች የአካሄድ ዐይነት የእግዚአብሔር ምላሽ ይወሰናል።
ቁርአናዊው ትምህርት፦— ቅዱሳት መጻሕፍት የሰብአውያንን ታሪክ ያገናዘቡ አይደሉም። የሰዎችም አካሄድ የእግዚአብሔርን ምላሽ አይወስነውም።
መጽሐፍ ቅዱሳዊ ለስተምህሮ፦— የመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ መልእክት፣ እግዚአብሔር የሰዎች ልጆችን ታሪክ በመጋራት፣ ሰብአውያንን ለመታደግ የከፈለውን ዋጋና የሄደበትን መንገድ መተረክ ነው።
ቁርአናዊው ትምህርት፦— የቅዱሳት መጻሕፍት መልእክት ከታሪክ ክሥተት ውጪ ነው። በቁርአን ውስጥ የሚገኙት ታሪካዊ ዘገባዎች ተምሳሌታዊ ንግግሮች ብቻ ናቸው።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ለስተምህሮ፦— ነቢያትም ሆኑ የቅዱሳት መጻሕፍት ጸሐፍያን እግዚአብሔር የሠራው ሥራ ምን ትርጉም አለው የሚለውን ጉዳይ ማብራራት የቻሉት በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ነው። ስለዚህ መለኮታዊው መገለጥ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የተደረገ ማብራሪያም ጭምር ነው። አንዳንድ ጊዜም ጸሐፍያኑ የእግዚአብሔርን ቃል "ሰሙ" ወይም "አዩ" እንዲሁም "የእግዚአብሔር ቃል በአፋቸው ነበር" ተብሎ ተገልጸአል።
ቁርአናዊው ትምህርት፦— ቅዱሳት መጻሕፍትን የጻፉት ነቢያት በእግዚአብሔር መለኮታዊ መልእክት መገለጥ ሂደት የእግዚአብሔር አፍ ብቻ በመሆን አገልግለዋል።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ለስተምህሮ፦— ቅዱሳት መጻሕፍት የሰው ልጆችን ታሪክ ያካተቱ ናቸው። በዚህ ታሪክ ውስጥ ሰዎች ለእግዚአብሔር የሰጡትን ምላሽ

እንዲሁም ትንቢታዊ መልእክቶችን ይዘዋል። ሰዎች ለእግዚአብሔር ትእዛዝ የነበራቸው ተቃውሞ የታሪኩ ሌላኛው ገጽታ ነው።
ቁርአናዊው ትምህርት፦— ቅዱሳት መጻሕፍት ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጡ መለኮታዊ መልእክቶች ናቸው። የሰዎችን ታሪክ ወይም ሰዎች ለእግዚአብሔር የሰጡትን ምላሽ የሚዘግቡ መጻሕፍት ቅዱሳት መጻሕፍት ሊሆኑ አይችሉም። ለምሳሌ ሱና (የነቢዩ መሐመድ ታሪክ) መለኮታዊ መገለጥ አይደለም።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ለስተምህሮ፦— ቅዱሳት መጻሕፍትን ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጉም ይቻላል።
ቁርአናዊው ትምህርት፦— ቁርአን ተብሎ የሚጠራው በዐረብኛ ቋንቋ የተጻፈው ቁርአን ብቻ ነው። የቁርአንን መልእክት በተለያዩ ቋንቋዎች ማብራራት ቢቻልም፣ ቁርአን የሚለውን ስያሜ ማግኘት የሚችለው ዐረብኛው ቁርአን ብቻ ነው።
መጽሐፍ ቅዱሳዊ ለስተምህሮ፦— ቅዱሳት መጻሕፍት የሁለት ወገንን (የእግዚአብሔርንና የሰው ልጆችን) ግንኙነት ማዕከል ያደረጉ መጻሕፍት ናቸው።
ቁርአናዊው ትምህርት፦— ቅዱሳት መጻሕፍት የአንድ ወገን ንግግር ብቻ ናቸው። እግዚአብሔር የሰው ልጆች የሚመሩበትን ምሪት አወረደ፣ የሰው ልጆችም በተሰጠን ምሪት መሠረት እንድንገዝ ታዘናል።

ወንጌል፦— የቅዱሳት መጻሕፍት መሠረታዊ ትምህርት ኢየሱስ መሲሕ መሆኑን ይፋ ማድረግ ነው። እርሱም ሥጋ የሆነ አምላክ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስን ትክክለኛ ትርጉም ማወቅ የሚቻለው ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር ተያይዞ ሲብራራ ነው።
ኢስላምና፦— ቁርአን ለሰዎች ሁሉ መመሪያ እንዲሆን ከእግዚአብሔር የተሰጠ የመጨረሻው መገለጥ ነው። ቁርአን የቀድሞዎቹን ቅዱሳት መጻሕፍት የሚጠቀልል እንዲሁም የሚያብራራ ነው።

ወንጌል፦— የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት እጅግ በጣም አስደናቂ መልእክት ሲሆን፣ አንድ ሰው ይህንን የምሥራች ወንጌል በእምነት ሊቀበል የሚችለው መንፈስ ቅዱስ ሲረዳው ብቻ ነው።
ኢስላምና፦— የቁርአን መልእክት ቀጥተኛ እንዲሁም ምክንያታዊ ስለሆነ ሰዎች በሚያነቡት ጊዜ ያላንዳች ዕርዳታ ትምህርቱን ሊያስተውሉ ይችላሉ። ሰው ሁሉ ሲወለድ ሙስሊም ሆኖ ስለሚወለድ እንዲሁም የእስልምና

አስተምህሮ ከሰብአዊ ባሕርይ ጋር የሚጣጣም ስለሆነ ሰዎች የቁርአንን ትምህርት ያላንዳች ጥያቄ ሊቀበሉት ይችላሉ።

መሲሑ— ትስብእት (ሥጋ) የሆነ አምላክ እንዲሁም የአምላክ ቃል ነው።
ቁርአን— ቁርአን ተአምራዊ በሆነ መንገድ ከሰማይ ወደ ሰው የመጣ የእግዚአብሔር ምሪት ነው።

መለኮታዊ መገለጥን በተመለከተ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች በተወሰኑ ነጥቦች ላይ ተመሳሳይ እቋም አላቸው። ይሁን እንጂ እንስማማበታለን በሚሏቸውም ነጥቦች ላይ የተወሰኑ ልዩነቶች አሏቸው። ነገር ግን ይህ ልዩነት ከሙስሊሞች ጋር ላለው ግንኙነት እንቅፋት ሊሆን አይገባም። ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች ቅዱሳት መጻሕፍትን መሠረት ያደረገ ምስክርነት ሊለዋወጡ እንዲሁም ውይይት ሊያካሂዱ ይገባል።
መጽሐፍ ቅዱስ ከቁርአን በአያሌው የተለየ በመሆኑ ምክንያት በርካታ ክርስቲያኖች ከሙስሊሞች ጋር ለመወያየት በሚፈልጉበት ጊዜ ከሙስሊሞች አመንታዊ ምላሽ አያገኙም። ቁርአን ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚለየውም ታሪካዊ ዘገባዎችን በማቅረቡ እንዲሁም በመሲሑ በኢየሱስ ላይ ባሉ ነጥቦች ዙሪያ ነው። እንደ አብርሃም ታሪክ ያሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች ብዙ ሙስሊሞችን ግራ የሚያጋቡ ቢሆንም፣ አብዛኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ በርካታ ሙስሊሞችን የሚመስጥና ልቡናቸውን የሚማርክ ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ
ዘፍጥረት 3+1-20
የቁርአን ምንባብ
ሱራ 20+9-24

<u>የአስተዉሎትና የጡይይት ጥያቄዎች</u>

1. እግዚአብሔር ለሙሴ በሚቃጠለው ቁጥቋጦ ውስጥ መገለጡን የሚናገረው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዘገባ በቁርአን ውስጥ ካለው ታሪክ ጋር ተመሳሳይ ነው። ይህ ክሥተት እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተ ከሙስሊሞች ጋር ላለን ውይይት እንዴት ልንጠቀምበት እንችላለን (ዘፍጥረት 3+1-20፤ ሱራ 20+9-24)?
2. ኢብራሂምን ግራ ሊያጋባው የቻለው የመጽሐፍ ቅዱስ አብዛኛው ክፍል ታሪክ የመሆኑ ጉዳይ ነው። ቁርአን ግን እንደዚህ ዐይነት ታሪኮችን

አልዘገበም። በመጽሐፍ ቅዱስና በቁርአን መካከል ያሉ እነዚህ ልዩነቶች ስለ መለኮታዊ መገለጥና እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ስላለው ግንኙነት በሙስሊሞችና በክርስቲያኖች መካከል ያለውን የአመለካከት ልዩነት እንዴት ሊያሳዩ ይችላሉ (ዘፍጥረት 3+8-10:15፤ ሱራ 2+38)?
3. ማንኛውም ሙስሊም "አምላኬ" ብሎ ሳይሆን "በእግዚአብሔር ስም" ብሎ ነው የሚጸልየው። ክርስቲያኖች ደግሞ "አምላኬ ሆይ" ወይም "አባታችን ሆይ" ብለው ይጸልያሉ። ሙስሊሞችም ሆኑ ክርስቲያኖች እንዲህ ብለው የሚጸልዩበትን ምክንያት ይግለጹ (ሱራ 1+1-7፤ ማቴዎስ 6+9-13)።
4. "መጽሐፍ ቅዱስ ተበላሽቶአል" ለሚለው የሙስሊሞች ተቃውሞ ክርስቲያኖች ምን ዐይነት ምላሽ መስጠት እንዳለባቸው እንዲሁም ምላሻቸውን በምን ዐይነት መልክ ማቅረብ እንዳለባቸው አስተያየቶትን ይስጡ።
5. ቁርአን መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ሆነ ይናገራል (ሱራ 3+3፤ ሱራ 5+47-49)። እነዚህ ቁርአናዊ ምንባባት ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች እምነትን አስመልክቶ ለሚያካሂዱት የጋራ ውይይት ምን ዐይነት ዕገዛ ሊኖራቸው ይችላል?

ምዕራፍ ሰባት

መገለጥ

ታንዚል—ተሰግዎ

በመካከለኛው ምሥራቅ የሚኖር አንድ ክርስቲያን፣ "በእኔ አገር የሚኖሩ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ጥሩ ግንኙነት አላቸው። በንግግራችን መካል የሃይማኖት ጉዳይ ከተነሣ ግን ውይይቱን አቋርጠን እንለያያለን" ሲል ነግሮኛል። ይህ ለምን ሊሆን ቻለ? እንደኛው ሌላኛውን ማዳመጥ አስቸጋሪ ለምን ሆነበት? እኛ እምነታችንን ለሌሎች ለመናገር ምን አስፈራን? ሙስሊሞች አለን ብለው የሚናገሩት እውነት ክርስቲያኖችን ስለሚረብሽ ነውን? ወይስ የክርስትና እምነት ሙስሊሞችን ስለሚረብሻቸው ነው?

አንድ ሙስሊም ኘሮፌሰር በሙስሊሙ ኡማና በክርስቲያኖች መካከል እውነትን አስመልክቶ ያሉትን የተለያዩ መረዳቶች በሚከተለው መንገድ ገልጸአል። ኘሮፌሰሩ በመጀመሪያ እጁን ጨብጠ ቁርአንን በእጁ ላይ አኖረው። ይህንን ድርጊት ሲያብራራ "የተጨበጠው እጄ መሐመድን ያመለክታል። ለሙስሊሞች ቁርአን ከመሐመድ በላይ ነው። ቁርአን ከእግዚአብሔር ዘንድ የወረደ መልእክት ስለሆነ፣ ከማንኛውም ታሪክና ከየትኛውም ነቢይ በላይ ነው። ሁሉም እውነት በቁርአን ውስጥ ተብራርቶአል" አለ።

በመቀጠልም የተጨበጠ እጁን ከመጽሐፍ ቅዱስ በላይ በማሳረፍ፣ "የተጨበጠ እጄ የሚያመለክተው መሲሑ ኢየሱስን ነው አለ። ለክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስ ሁል ጊዜ የሚያመለክተው ወደ ክርስቶስ ነው። እርሱ እውነትና የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትንቢቶች ፍጻሜ ነው። እንዲሁም እርሱ ለሰዎች የተገለጠ እውነትና ሥጋ ለብሶ የተገለጠ አምላክ ነው። እውነት ሁሉ ፍጻሜ የሚያገኘው በመሲሑ ሲሆን፣ መጽሐፍ ቅዱስ በአጠቃላይ ስለ እርሱ ይመሰክራል" አለ።

በአንድ መስጊድ ውስጥ በነበረን የምሽት ውይይት ላይ እንዲህ ስል ተናገርሁ "ውይይታችን ያተኮረው የእውነት መሠረቱ ምንድን ነው" በሚለው ጥያቄ ዙሪያ ነው። ክርስቲያኖች መሲሑ ኢየሱስ በአካል የተገለጠ እውነት ነው ብለን እናምናለን። ሙስሊሞች ደግሞ በዚሁ ምሽት፣ ቁርአን የሰው ልጆች እውነቶችን ሁሉ እንዲመዝኑበት ከሰማይ የወረደ መልእክት ነው ብለዋል። ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች በተገናኘን ቁጥር ሁሉ እነዚህ ጥያቄዎች ዘወትር

ከእኛ ጋር ናቸው። ስለሕይወትና ስለእግዚአብሔር ያለን ምልከታ የሚወሰነው ቀጥሎ ባሉት ሁለት ጥያቄዎች በምንሰጠው ምላሽ ነው፦— መሲሑ ማን ነው? ቁርአን ምንድን ነው?

መገለጥ እንደ ታንዚል

ሙስሊሞች፣ ቁርአን ከእግዚአብሔር ዘንድ ለመጨረሻ ጊዜ የወረደ መለኮታዊ መልእክት ነው የሚል እምነት አላቸው። ታንዚል የሚለውም የዐረብኛ ቃል "ከሰማይ የወረደ" የሚል ትርጉም አለው። በሰው ልጆች ታሪክ ሁሉ እግዚአብሔር ለሰብአውያን የሚሆነውን መልእክቱን ይፋ ያደረገው በነቢያት በኩል ቃሉን በመላክ ነው። እንደ ቀድሞዎቹ መገለጦች ሁሉ ቁርአንም ከእርሱ በፊት የነበሩትን መገለጦች ለማብራራት እንዲሁም ለመጨረሻ ጊዜ ከሰማይ የወረደ (ታንዚል) መልእክት ነው። ይህ ሙስሊሞች ሁሉ የሚቀበሉት መሠረታዊ አስተምህሮ ነው።

ይህ አስተምህሮ ከሚከተለው የሙስሊሞች ትምህርት ጋር የሚዛመድ ነው። ሙስሊሞች በሰማያዊ ስፍራ በወርቃማ ጽሑፍ የተጻፈ ሰሌዳና የመጻሕፍት እናት ተብሎ የሚጠራ መዝገብ እንዳለ ያምናሉ። ይህም መጽሐፍ የእግዚአብሔር ዘላለማዊና የማይለወጥ ፈቃድ የተጻፈበት መጽሐፍ ነው። አዳም የእግዚአብሔር ምሪት ከመጣላቸው ነቢያት መካከል የመጀመሪያው ሰው ነው። ይህም ምሪት አዳም በምድር ላይ በትክክል የአላህ ወኪል ሆኖ እንዲኖር ረድቶታል። ኋላም ይህ የመጻሕፍት ሁሉ እናት የሆነው መጽሐፍ ቀሪ ክፍል በአራቱ መጻሕፍት ማለትም በተውራት፣ በዘቡር፣ በኢንጂልና በቁርአን ውስጥ ተገልጦአል።

ሙስሊሞች ቁርአን ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ መገለጥ የመሆኑ ጉዳይ ማረጋገጫ አለው የሚል አቋም ስላላቸው ትልቅ ደስታ ይሰማቸዋል። ማረጋገጫውም ቁርአንን የመሰለ መጽሐፍ ሌላ ሰው ማዘጋጀት አለመቻሉ (ኢጃዝ) ነው[1]። ይህም ማለት የቁርአንን ተአምራዊነት አመሳስሎ መድገም ማንም ያለመቻሉ ነው። ቁርአንና ሙስሊሞች ይህንን ሐሳብ ደጋግመው ያውጃሉ (ሱራ 2÷23)። የመሐመድ ተቃዋሚዎች መሐመድ የቁርአንን መልእክት ያገኘው ከጥንት አፈ ታሪክ ነው ብለው በሚቃወሙት ጊዜ፣ የመሐመድ መልስ ቁርአንን የመሰለ ትንሽ መጽሐፍ አዘጋጅታችሁ አቅርቡ የሚል እንደ ነበረና ተቃዋሚዎቹም ይህን ማድረግ እንዳልቻሉ ይታመናል። በዘመናችንም ሙስሊሞች፣ የዐረብኛው ቁርአን የቋንቋና የግጥም ሁኔታ በጣም

[1] Andrew Rippin, *Muslims: Their Religious Beliefs and Practices* (New York: Routledge, 2001), 33-34.

አስገራሚ እንዲሁም ማንም ተመሳሳዩን ሊያዘጋጅ አይችልም ብለው ይናገራሉ።

ሌሎች ሙስሊሞች ደግሞ ቁርአን ስለሳይንስ ያለውን አመለካከት ይናገራሉ። ቁርአን በዘመናችን በሳይንስ ስለተገኙት ግኝቶች ቅድመ ትንበያ ይሰጣል ይላሉ። ሙስሊሞች እነዚህን ሁሉ መረጃዎች ለማቅረብ የሚሞክሩት፣ ቁርአን ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ መለኮታዊ መገለጥ፣ እጅግ ተአምራዊ የሆነ እንዲሁም ስለ ዘመናዊው ሳይንስ አስቀድሞ ትንቢት የተናገረና ከሳይንስም ጋር ተጣጥሞ የሚሄድ መጽሐፍ መሆኑን ለማሳየት ነው።

የታንዚል (የቁርአን መገለጥ) አስተምህሮ ሙስሊሞች ቁርአንን ከብልሽት ጠብቀው እንዳቆዩ ያስተምራል። የቁርአን ብልሽት ማለት ምን ማለት ነው? ቁርአን ተበላሽቶአል ስንል ውጫዊ ሰብአዊ ተጽእኖ አለበት ማለታችን ነውን? ምንም እንኳ መሐመድ የሌሎችን ሰዎች ምክር ይጠይቁ የነበረ ቢሆንም፣ ቁርአንን የመሰለ መጽሐፍ ማዘጋጀት አይቻልም የሚለው አስተምህሮ ቁርአን ከሰብአዊ ተጽእኖ ነጻ እንደ ሆነ ይገልጻል። ቁርአን በምንም መልኩ አልተበላሸም፣ ከማንኛውም የሰዎች ተጽእኖ ነጻ ነው (ሱራ 10+37-38)። ቁርአን ለሰው ልጆች ተገለጠ እንጂ በሰው ልጆች ተጽእኖ ውስጥ የወደቀ መጽሐፍ አይደለም።

በድሩ ዲ. ቀትራጋ የተባለው በናይሮቢ የእስልምና ፕሮፌሰር እንዲህ ሲል ጽፎአል፦—

> በመለኮታዊ መጻሕፍት ውስጥ ያሉት መገለጦች ከእግዚአብሔር ዘንድ በቀጥታ የወረዱ (ታንዚል) እውነተኛ ምሪቶች ናቸው። የእግዚአብሔር ቃል የተገለጠው ለተመረጡ ነቢያት ነው። የነቢያቱ ማንነት፣ ወይም ሕይወታቸው ወይም ደግሞ ታሪካቸው ለመለኮታዊ መልእክቱ መሠረት አልሆነም[2]።

መገለጥ እንደ ተሰግዎ

በመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ተሰግዎ መገለጥ ነው። ይህም ታንዚል ከሚለው የእስልምና አስተምህሮ ጋር ልዩነት አለው። ተሰግዎ ማለት "በሥጋ መገለጥ" ማለት ነው። ይህም የሚያመለክተው መለኮታዊው ቃል ሥጋ መሆኑን ነው።

[2] Badru D. Kateregga and David W. Shenk, *A Muslim and a Christian in Dialogue* (Scottdale, Pa.: Herald Press, 1997), 150.

በምዕራፍ ስድስት ላይ እንደ ተመለከትነው፣ ሙስሊሞች መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በሰዎች ሕይወት ውስጥ ጣልቃ በመግባት የሠራውን ሥራና የሰብአውያንን ምላሽ የያዘ መጽሐፍ የመሆኑ ጉዳይ መጽሐፍ ቅዱስ ተበላሽቶአል እንዲሉ አድርጓቸዋል። ከሰው ልጆች ሕይወት ጋር ተያያዥ የመሆኑ ጉዳይ መጽሐፍ ቅዱስ ተበላሽቶአል ወደሚለው ድምዳሜ የሚያደርስ ከሆነ በርግጥ መጽሐፍ ቅዱስ ተበላሽቶአል ማለት ይቻል ይሆናል። ሁሉም የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በሰው ልጆች የታሪክ ሂደት ውስጥ የተገለጡ ናቸው። ስለዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት የሰዎችን ፈሊጣዊ ንግግሮች፣ የሰዎችን ማንነት፣ ባህል እንዲሁም የአስተሳሰብ ዘይቤዎችን በግንዛቤ ውስጥ ያስገባ መጽሐፍ ነው። በርግጥ መጽሐፍ ቅዱስ በታሪክ ውስጥ የተገለጠ መለኮታዊ መልእክት ነው።

በመጽሐፍ ቅዱሳዊው አስተምህሮ መሠረት፣ እግዚአብሔር በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ ራሱን በሙላት የገለጠው መሲሑ ክርስቶስ ኢየሱስ ሰው ሆኖ ወደዚህ ምድር በመጣ ጊዜ ነው። እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ወደዚህ ዓለም ልኮአል (ዮሐንስ 3+16)። ይህም ብቸኛው የእግዚአብሔር ልጅ አናጢ የነበረው የናዝሬቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እግዚአብሔር በመሲሑ በኩል ሰው ሆነ።

በዮሐንስ ወንጌል የእግዚአብሔር ቃል፣ ዘላለማዊ የእግዚአብሔር እውነት ተብሎ ተጠርቶአል። እግዚአብሔር ዓለምን በፈጠረበት በቃሉ በኩል ራሱን ገለጠ። የእግዚአብሔር ቃል የሆነው መሲሑ የናዝሬቱ ኢየሱስ ሥጋ ሆኖ/ለብሶ እንደ ተገለጠ የዮሐንስ ወንጌል እንዲህ ሲል ይገልጻል፡—

> በመጀመሪያው ቃል ነበረ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ። ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ።. . . ቃልም ሥጋ ሆነ፣ ጸጋንና እውነትንም ተሞልቶ በእኛ ዐደረ፣ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየን (ዮሐንስ 1+1-2:14)።

መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎች በእግዚአብሔር አምሳል እንደ ተፈጠሩ ያስተምራል። ከሰዎች ኀጢአትና ዐመፅ የተነሣም በሰዎች ላይ ያለው የእግዚአብሔር መልክ/አምሳል ተበላሽቶአል። አዳምና ሔዋን ኀጢአት በሠሩ ጊዜ የተበላሸውን በሰዎች ላይ ያለውን የእግዚአብሔር ምስል፣ እግዚአብሔር በመሲሑ በኩል አድሶታል። ወላጆቻችን የሆኑት አዳምና ሔዋን በሠሩት ኀጢአት ምክንያት በሁላችን ላይ ሞት ተፈረደብን። ይሁንና ሥጋ ለብሶ የተገለጠው እግዚአብሔር (መሲሑ) ተበላሽቶ የነበረውን በሰው ላይ ያለውን የእግዚአብሔር ምስል ሙሉ በሙሉ አድሶታል።

እኛ ሁላችን ኀጢአታችን የተነሣ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረን ኅብረት ተበላሽቶአል። ነገር ግን እግዚአብሔር በመሲሑ በኩል ወደ እኛ በመምጣት ከወደቀው ማንነታችን አነሣን። በአዳም ምክንያት ኀጢአትና ሞት ወደ ሰው ልጆች ሁሉ ደረሰ። ነገር ግን በክርስቶስ በኩል እግዚአብሔር ወደ ሰው ልጆች መጣ። ለእግዚአብሔር ጥሪ በእምነት አዎንታዊ ምላሽ የሚሰጡ ግለትም ንስሓ ለሚገቡና ራሳቸውን ለክርስቶስ አሳልፈው የሚሰጡ ሁሉ፣ በክርስቶስ ቤዛዊ ሥራ ጽድቅንና አዲስ ሕይወትን ያገኛሉ። ይህን እውነት በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡—

> በአንዱ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኀጢአተኞች እንደ ሆኑ እንዲሁ ደግሞ በአንዱ መታዘዝ ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ (ሮሜ 5+19)።

እንዲሁም፡—

> ሞት በሰው በኩል ስለመጣ ትንሣኤ ሙታን በሰው በኩል ሆኖአልና። ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉ (1ቆሮ 15+21-22)።

የውይይቱ አስቸጋሪነት

በእስልምና እምነት እግዚአብሔር ፈቃዱን በነቢያት በኩል አስታወቀን የሚል እምነት ሲኖር፣ በወንጌል ውስጥ ግን እግዚአብሔር በሉዓላዊነቱ ራሱን መግለጥ በማድረግ ፍቅሩን እንደ ገለጠልን ተጽፎአል። እነዚህ ሁለቱ አመለካከቶች በታንዚልና በተሰግዎ በተገለጠ መልእክት መካከል ላለው ልዩነት መሠረቶች ናቸው።

ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ለውይይት በሚገናኙበት ጊዜ ሁሉ ልዩነቶቹ መንፀባረቃቸው የግድ ነው። በክርስቲያኖች አመለካከት የእግዚአብሔር መለኮታዊ መገለጥ የተፈጸመው በሰዎች ታሪክ ውስጥ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን ታሪካዊ ክሥተቶችንና ባህላዊ ዐውዶች ማወቅ የመጽሐፍ ቅዱስን መልእክት በትክክል ለመረዳት ታላቅ ዕገዛ አለው። በተጨማሪም የመጽሐፍ ቅዱሱ መገለጥ በሁለት ወገኖች መካከል የሚደረገው ዐይነት መስተጋብር/ውይይት ነው። እግዚአብሔር በሰዎች ታሪክ ውስጥ ሲገለጥ፣ ከፉ ሥራችንን ሲቃወም እንዲሁም የእኛን ጥያቄ ሲመልስና በቀናው ጉዳና ሲመራን እንመለከታለን።

በኢሳይያስ 1+18 ላይ "ኑና እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር"። ስለዚህ እግዚአብሔር ፈቃዱን የሚያስታውቅ ብቻ ሳይሆን ከሰዎች ጋር የሚዋቀስ አምላክ ነው። ብዙ ሙስሊሞች ይህንን አባባል ለቁርአን አይሠራም ይላሉ፣ ምክንያቱም የቁርአን መልእክት ከሰብአውያን ጋር እንዳች ትስስር የሌለው የአምላክ መልእክት ብቻ ነው። እግዚአብሔር ሰዎችን ለውይይት አይጠራም፣

ይልቁንም ከምሕረቱና ከርኅራኄው የተነሣ ፍጹም የሆነውን ፈቃዱን ለእኛ ላከልን። ስለዚህ ሙስሊሞች ለእግዚአብሔር ፈቃድ መገዛት እንጂ፣ ከእግዚአብሔር ጋር መወያየት አንችልም ይላሉ።

ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ተገናኝተው በእግዚአብሔር መገለጥ ላይ ያላቸውን አመለካከት በሚወያዩበት ወቅት፣ የማያግባቧቸው ርእሰ ጉዳዮች ያጋጥሟቸዋል። ከእነዚህም ርእሰ ጉዳዮች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፦—

የክርስቶስ ሞት

በሙስሊሞችና በክርስቲያኖች መካከል ላለው ልዩነት ዋንኛው ርእሰ ጉዳይ ስለ ክርስቶስ በመስቀል ላይ መሞት ያላቸው አመለካከት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ እንደ ሞተ ሲያስተምር ቁርአን በተቃራኒው "አልገደሉትም፣ አልሰቀሉትምም" (ሱራ 4÷157) ይላል።

እኔ በርካታ ጊዜ ከሙስሊሞች ጋር ስለክርቶስ ሞትና ትንሣኤ ተወያይቼአለሁ። ከእኔ ጋር የተወያዩት ሙስሊሞች፣ ከተለያየ የኅብረተሰብ ክፍል የመጡና የተለያየ የትምህርት ደረጃ ያላቸው ናቸው። ነገር ግን ማናቸውም ቢሆኑ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሞቶአል የሚለውን ኑጥብ ለማስተናገድ ፈቃደኞች አይደሉም።

ብዙ መቶ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በተገኙበት ከሙስሊም ምሁራን ጋር ባደረግኋቸው ውይይቶች በተደጋጋሚ፣ "ከእያንዳንዱ ወንጌል ውስጥ አንድ ሦስተኛው እጅ ከክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ጋር የተያያዘ ነው" እንዲሁም ክርስቶስ ኢየሱስ ለመሞቱና ከሙታንም ለመነሣቱ "እጅግ በርካታ እንዲሁም ተአማኒ የሆኑ የዐይን ምስክሮች የዘገቧቸው ዘገባዎች ዛሬም ድረስ አሉ" እላለሁ። ከእነዚህ ዘገባዎች መካከል አንዳንዶቹ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ ሲሆን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ደግሞ ይህን እውነት የሚያስረግጡ በርካታ የታሪክ ድርሳናት አሉ። የወንጌል ዐቢይ ትምህርትም የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ነው። ስለዚህ ይህ ድርጊት ከተፈጸመ ከስድስት መቶ ዓመታት በኋላ፣ አንድ ሰው በጻፍዋት አንዲት ዐረፍተ ነገር ምክንያት የመጽሐፍ ቅዱስንና ተአማኒ የሆኑ የታሪክ ድርሳናትን ምስክርነት ዋጋ ማሳጣት ተገቢ ነውን?

ለዚህ ጥያቄ ከሙስሊሞች በኩል የሚሰጠኝ መልስ፦— "ቁርአን ብሉአል። አል-መሲሕ ኢሳ አልተሰቀለም፣ አልሞተምም። የመጽሐፍ ቅዱስ ዘገባዎች የተበላሹ ናቸው" የሚል ነው።

ሰብአዊ ተጽእኖ

በሙስሊሞችና በክርስቲያኖች መካከል ልዩነት ከሚፈጥሩ ነጥቦች መኻል ሌላኛው፣ የሰዎች ማንነትና የሕይወት ዘይቤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የራሱ የሆነ ቦታ ይዞ የመገኘቱ ጉዳይ ነው። ከሙስሊም ባልንጀራዬ ጋር ስንወያይ እንዲህ አልሁት፦— "በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የጸሓፊው ማንነትና ባህል ተካቶአል። ጳውሎስ ሲጽፍ ማንነቱን ሳይለቅ እንደ ጳውሎስ ሆኖ ጻፈ፣ ጴጥሮስም እንደ ጴጥሮስ ሆኖ ጻፈ"። ለዚህ ንግግሬ ይህ ጓደኛዬ እንዲህ ሲል መለሰልኝ፦— "አንተ በግልጽነት እንደ ተናገርኸው የእግዚአብሔር ቃል ከሰዎች ባህልና የኑሮ ዘይቤ ጋር ስለተደባለቀ መጽሐፍ ቅዱስ ተበላሽቶአል። ቁርአን ግን ከእንደዚህ ዐይነቱ ብልሽት የጸዳ ነው። ምስጋና ለእግዚአብሔር ይሁን"

የእግዚአብሔር ምጡቅነትና ጎደል

ሙስሊሞች ቅዱሳት መጻሕፍትን በሰዎች ባህል፣ የኑሮ ዘይቤና ታሪክ ውስጥ ተገልጠዋል ብሉ መቀበል የእግዚአብሔርን ልዕልና፣ ልዕቀትና ጎደል እንዲሁም የቃሉን ክብር ያጉድፋል ይላሉ። የእስልምና ነባረ መለኮት የእግዚአብሔር ቃል ከሰማይ መውረዱ (ታንዚል) ከእግዚአብሔር ልዕልና፣ ልዕቀትና ጎደል ጋር በእጅጉ እንደሚስማማ ያስተምራል።

ዳሩ ግን ክርስቲያኖች ሙስሊሞችን "የእግዚአብሔር ቃል ከሰማይ መውረዱ የእግዚአብሔርን ጎደልና ክብር ለመጠበቅ ፍጹም ተመራጭ መንገድ ነውን?" ሲሉ ይጠይቃሉ። ሙስሊሞችም "አዎን" ሲሉ ይመልሳሉ።

ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል በሰዎች ታሪክ ውስጥ መገለጡ እንዲሁም ክርስቶስ በመስቀል ላይ መሞቱ ደካማነት ነውን? የቤተ ክርስቲያንም ምስክርነት የሚያተኩረው እግዚአብሔር ሥጋ ለብሶ በመገለጥ መከራ መቀበሉ የእግዚአብሔርን ጎደልና ሰዎችን ሁሉ የሚለውጥ፣ የሚያድስና የሚያሳድግ የተትረፈረፈ አዲስ ሕይወት የሚሰጥ ነው በሚለው ርእስ ላይ ነው።

ኪኔት ክራግ የተባሉ ጻጻስ ብዙውን የሕይወት ዘመናቸውን በአብዛኛው ያሳለፉት ከሙስሊሞች ጋር ከላይ በተመለከትናቸው ጥያቄዎች ዙሪያ በመወያየት ነበር። የእግዚአብሔር ቃል በሰዎች ታሪክና ባህል የመገለጡን እውነት ሙስሊሞች እንዲያስተናግዱት ተማጽነዋል። ከሙስሊሞች ጋር በሚወያዩበት ጊዜ ሁሉ ቁርአንና የመሐመድ ትንቢቶች የሰውን የኑሮ ዘይቤ እንዲሁም የሰብአውያንን ታሪኮች ታሳቢ ያደረጉ ናቸው በማለት ይሞግቱ

ነበር:: እንዲህ ሲሉም ይግጸናሉ፣ "እባካችሁ አስተውሉ ቁርአን የሰዎችን ግንኑትና ታሪክ በውስጡ የያዘ መጽሐፍ እኮ ነው"[3]::

የክራግ ምኞት ይህንን እውነት በማሳየት ብዙ ሙስሊሞች የሰዎችን ባህልና ታሪክ የያዘውን መጽሐፍ ቅዱስን ይሰሙ ዘንድ ነው:: ክራግ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር በራሳችን ዐውድ በተለይም በክርስቶስ በኩል ተገለጠልን የሚለውን እውነት ለሙስሊሞች ለመግለጥ ትልቅ ፍላጐት የነበራቸው ሲሆን፣ ይህን ምኞታቸውን እውን ለማድረግ ብዙ ጥናቶችን አካሂደዋል:: ይሁን እንጂ ከጽሑፎቻቸው የምንማረው ነገር ከሙስሊሞች ጋር በነበራቸው ውይይት ተስፋ መቁረጣቸውን ነው:: ሙስሊሞች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን የሰው ልጆችን ታሪክ፣ የኑሮ ዘይቤ እንዲሁም የባህል አሻራ መቀበል በጣም ይከብዳቸዋል[4]::

ታሪክና ታንዚል

ራሳቸው ሙስሊሞች ቁርአንን በሚያጠኑበት ጊዜ፣ የቁርአንን ታሪካዊና ባህላዊ ዐውድ በተከተለ መልኩ ስለሚያጠኑ ቁርአን ከታሪክ ውጪ ነው ማለት አይቻልም የሚለውን አቋም በመያዝ የሙስሊሞችን አቋም የሚተቹ ክርስቲያኖች አሉ:: የተከበሩት የስዊዝ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የነገረ መለኮት ምሁር የሆኑት ሐንስ ኩንግ ባካሄዱት ጥናት፣ ሙስሊሞች በቁርአን ውስጥ ያሉትን ታሪኮች እንደ ታሪክ በጥልቀት ለማየት ፈቃደኞች ካልሆኑ፣ ክርስቲያኖች ከሙስሊሞች ጋር ውይይት ማድረግ አይችሉም በማለት ተናግረዋል:: ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ስለእግዚአብሔር ቃል ለመነጋገር ብቸኛው መንገድ ሙስሊሞች ታሪክን ለማጥናት ፈቃደኛ መሆናቸው ወሳይ ጉዳይ ነው በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል[5]::

ይሁንና የእግዚአብሔር ቃል ከሰማይ የወረደ መለኮታዊ መገለጥ ነው የሚለውን አስተምህሮ፣ የእግዚአብሔር ቃል በሰዎች ባህልና ታሪክ ውስጥ ተገልጠአል ከሚለው እምነት ጋር ማስማማት ይቻላልን? ሐንስ ኩንግ

[3] Kenneth Cragg, *The Event of the Qur'an: Islam in Its Scriptures* (Oxford: Oneworld Publications, 1994).

[4] ዝኒ ከማሁ፣ እንዲሁም Kenneth Cragg, *Muhammad and the Christian* (Oxford: Oneworld Publications, 1999).

[5] Hans Kung, et al., *Christianity and World Religions: Paths to Dialogue with Islam, Hinduism, and Buddhism*, translated by Peter Heinegg (New York: Doubleday, 1986), 28-36.

ከሙስሊሞች ጋር ለመወያየት በቅድመ ሁኔታነት ያስቀመጡት መስፈርት የራሳቸውን አመለካከት በሙስሊሞች ላይ እየጫኑ ነው ወደሚለው ድምዳሜ አይወስድም? ሙስሊሞች በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያላቸው ይህ ዐይነቱ አተያይ እስካልተቀየረ ድረስ ክርስቲያኖች ከሙስሊሞች ጋር መወያየት አይችሉም የምንል ከሆነ ከሙስሊሞች ጋር መወያየት የምንችለው እንዴት ነው?

የእስልምና ምሁር የሆኑት አንድሪው ሪፒን እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል:— "ታሪክ የእውነት መለኪያ እንዲሁም ከቁርአን የሚበልጥ ነው የሚለው አስተሳሰብ ሙስሊሞች በፍጹም ሊቀበሉት የማይችሉት ጉዳይ ነው:: በሰዎች ታሪክ ላይ ተመሥርቶ ያልተጻፈውን የቁርአን አስተምህሮ ወደ ሰዎች ታሪክ ዝቅ አድርጉ መቀበል ስለማይቻል እስልምና ትክክል አይደለም ወደሚለው ድምዳሜ ይወስዳል የሚለው ጉዳይ ብዙ ሙስሊሞችን ያሳስባቸዋል"[6]::

ታንዚልና መጽሐፍ ቅዱሳዊው መገለጥ ስለ እውነትና ስለ መገለጥ ያሉ ሁለት የተለያዩ መረዳቶች እንደ ሆኑ መቀበል የተሻለ ውጤት ያስገኛል:: ቁርአን ስለ እግዚአብሔር ቃል መገለጥ ለሙስሊሙ ኡማ የሚያስተምረው ትምህርት መጽሐፍ ቅዱስ ለክርስቲያኖች ከሚያስተምረው በጣም የተለየ ነው:: ስለታንዚል ያለውን አስተምህሮ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲቀበል ማስገደድ በአንጻሩ ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል በሰዎች ታሪክ ውስጥ ተገልጠአል የሚለውን ትምህርት ቁርአን እንዲቀበለው ማስገደድ ውይይታችን ስኬታማ እንዳይሆን ከማድረጉም በላይ፣ እስልምናና ወንጌል የሚያስተምሩትን ትምህርት ማበላሸት ነው:: ሁለቱም የእምነት ቡድኖች ከራሳቸው እምነት አቋም በመነሣት የየራሳቸውን ምስክርነት ይሰጣሉ::

ሁለቱ የእምነት ክፍሎች ስለእግዚአብሔር ቃል ግልጠት የሚያስተምሩት ትምህርት፣ እምነቶቹን በማስፋፋት ረገድ ባላቸው ተልእኮ ላይ በሚገባ ተንጸባርቀዋል:: ሁለቱም የእምነት ክፍሎች እግዚአብሔር የእግዚአብሔርን ቃል ለዓለም ሁሉ እንዲመሰክሩ ተልእኮ እንደ ሰጣቸው ያምናሉ:: ቅዱሳት መጻሕፍቶቻቸውም እስልምናን ወይም የምሥራቹን ወንጌል ይሰብካሉ:: ቀጥለን እስልምናና ክርስትና ለዓለም ህዝብ ያላቸውን ተልእኮ እንመለከታለን::

ታንዚል እና እስላማዊ ተልእኮ

ሙስሊሞች ከእግዚአብሔር ዘንድ የወረደው መልእክት የዐረብኛው ቁርአን እንደሆነ ያምናሉ:: ስለዚህም ቁርአንን በተለያዩ ቋንቋዎች መተርጐም

[6] Rippin, *Muslims*, 240-41.

አይቻልም። ወደ ሌላ ቋንቋ ከተተረጉመ ደግሞ ቁርአን መሆኑ ይቀራል። የቁርአንን ማብራሪያዎች በሌሎች ቋንቋዎች መጻፍ ይቻላል፣ ነገር ግን ማብራሪያዎቹ ቁርአን አይደሉም። የዐረብኛው ቁርአን ሙስሊሞች እምነታቸውን ለማስፋፋት ያላቸውን አመለካከት በምን መልኩ ይጐዳዋል? ይህ ጉዳይ ለእምነቱ መስፋፋት ዐቢይ እንድምታ አለው።

በጣም ግልጽ ከሆኑት እንድምታዎች ውስጥ አንዱ የዐረብኛ ቋንቋ በሙስሊሞች ጸሎት (ሰላት) ውስጥ ያለው ሚና ነው። ለምሳሌ በዓለም ዙሪያ በየዓመቱ በተለያየ ሁኔታ በርካታ ሰዎች የእስልምናን ሃይማኖት ይቀበላሉ። ባልቲሞር በተሰኘው ከተማ ባለ መስጊድ ውስጥ በአንድ ምሽት ብዙ ክርስቲያኖች ወደ እስልምና ሃይማኖት ተቀብለዋል። የምሽት ጸሎቱ ሲጠናቀቅ አንድ ሽማግሌ ወደ ሙስሊሞቹ መሪ በመቅረብ "ሙስሊም መሆን እፈልጋለሁ" አለው። በመስጊዱ ውስጥ የተሰበሰቡ ሙስሊሞች "አልሐምዱሊላህ" (ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን) በማለት አስተጋቡ።

የሙስሊሞቹ መሪ (ኢማም) አዲሱን አማኒ የእስልምና የእምነት አንቀጽ በዐረብኛ "ላ ኢላህ ኢለላህ ሙሐመዱን ረሱል አላህ" (ከአላህ በቀር ሌላ አምላክ የለም፣ መሐመድ የአላህ መልእክተኛ ነው) እንዲያውጅ አደረገው። ከዚያም የሙስሊሞቹ መሪ፣ "ይህ ሰው ከዚህ በኋላ ሙስሊም ነው" በማለት ካስታወቀ በኋላ ሙስሊሙ ማኅበረሰብ እንዲቀበለውም ጥሪ አቀረበ። ኢማሙ ለአዲሱ አማኝ በየምሽቱ በመስጊዱ ውስጥ የዐረብኛ ትምህርት እንደሚሰጥ ነገረው። የእስልምና መጽሐፍ የተጻፈው በዐረብኛ ቋንቋ ስለሆነ እንዲሁም ሃይማኖታዊ ጸሎት ማድረስ የሚቻለውም በዐረብኛ ቋንቋ ብቻ መሆኑን ከገለጠለት በኋላ፣ ዐረብኛ ቋንቋ መማሩ መሠረታዊ ጉዳይ እንደ ሆነ ለአዲሱ አማኒ ገለጠለት።

የዐረብኛው ቁርአን

ላሚን ሳኔህ የተባሉት የነገረ መለኮት ምሁር፣ በዐረብኛ ቋንቋና በእስላማዊ ተልእኮ መካከል ስላለው ዝምድና በስፋት ጽፈዋል። የሳኔህ ዕድገት በምዕራብ አፍሪካ በሙስሊም ቤተሰብ ውስጥ ሲሆን የክርስትናን እምነት የተቀበሉት ገና ወጣት ሳሉ ነበር። ኋላም ዬል በሚባለው ስመ ጥር የአሜሪካን ዩኒቨርስቲ ውስጥ "ሚስዮሎጂ" በሚባለው የጥናት ዘርፍ ለበርካታ ዓመታት አስተምረዋል። የዶክትሬት ዲግሪ ጥናታቸው እስልምና በምዕራብ አፍሪካ በሚል ርእስ ላይ የሚያጠነጥን ነበር።

ሳኔህ በጥናታቸው ቁርአን ከሰማይ የወረደ መገለጥ (ታንዚል) ነው የሚለው አመለካከት በእስልምና ሃይማኖት መስፋፋት ውስጥ ያለውን ድርሻ በስፋት መርምረዋል። ይህም የሙስሊሞች አመለካከት ቁርአን ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች እንዳይተረጐም ምክንያት ሆኖአል። እንደ እስልምና ትምህርት፣ ቁርአን በመባል የሚጠራው በዐረብኛ ቋንቋ የተጻፈው መጽሐፍ ብቻ ነው። በተለያዩ ቋንቋዎች የሚተረጐሙት መጻሕፍት ማብራሪያዎች እንጂ እውነተኛ ቁርአን ሊሆኑ አይችሉም። በዚህ ዐቢይ ምክንያት እስልምና በተስፋፋባቸው አካባቢዎች ሁሉ ዐረባዊነት ከእምነቱ ጋር እየተስፋፋ ሄደ። የዐረብኛ ቋንቋ ትምህርት ቤቶች ከእስላማዊ ሚስዮናዊ ተልእኮ ጋር የተቈራኘ ነው።

የሳኔህ ሒስ ቀጥተኛ የሆነ ሂስ ነው። ሳኔህ የዐረብኛው ቁርአን እስልምናን የሚቀበሉ ሰዎችን ባህል ክፉኛ እንደሚያጻክም ይገልጻሉ[7]። በትውልዳቸው ዐረብ የሆኑ ሚስዮናውያን የዐረብኛውን ቋንቋ ጠንቅቀው ስለሚያውቁ፣ የእስልምናን ሃይማኖት ተቀብሉ የዐረብኛን ቋንቋ የተማረ ግለሰብ ቁርአንን በደንብ የተማረውንና ቋንቋውን ጠንቅቆ የሚያውቀውን ዐረባዊ ሙስሊም ቁርአናዊ አስተምህሮን በተመለከተ ሂስ እንዴት ማቅረብ ይችላል? በአንጻሩም የዐረብ ሙስሊም ሚስዮናውያን የሚያሳድሩት የባህል ተጽእኖም በቀላሉ የሚገመት አይደለም።

በአንጻሩ ደግሞ እስልምና በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት እያገኘ ነው። ዐረብኛው ቋንቋ አዲሱ አማኝ በዓለም ዙሪያ ካሉ ሙስሊሞች ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖረው ያደርጋል። አዲስ የሆነ ማንኛውም ሙስሊም ሰላት ሲሰግድ በመቶ ሚሊዮኖች ከሚቈጠሩ ከዓለም ሙስሊሞች ጋር በመሆን አላህ ለገለጠው ፈቃድ እየተገዛ እንደ ሆነ ያምናል። በዐረብኛ ቋንቋ የሚፈጸመውን ጸሎት (ሰላት) ማወቅ፣ ዓለም ዐቀፋዊ ለሆነው ለአላህ ፈቃድ የመገዛት ምልክት እንደ ሆነ ይታመናል።

የፖለቲካ ሥርዐት

የዐረብኛውን ቁርአን ማክበር በፖለቲካ ሥርዐት ውስጥ የራሱ የሆነ ተጽእኖ አለው። የሕንድ ሙስሊም ምሁር የሆነው ራፊቅ ዘካሪያ፣ በእስልምና ውስጥ ያለውን የፖለቲካ ገጽታ በሦስት ዋና ዋና ርእሶች በመክፈል ጽፎአል። ይኸውም፦—

[7] Lamin Sanneh, *Translating the Message: The Missionary Impact on Culture* (Maryknoll, N.Y.: Orbis Books, 1989), 211-14.

1. በፖለቲካው ሥርዐት ያለው ሚና:— "በእስልምና እምነት ግዢው፣ መንግሥት ወይም አስተዳደር የእስልምናውን ርዕዮተ ዓለም በጥንቃቄ መከተል አለበት:: ነቢዩ መሐመድ የፖለቲካውን ሥርዐት በመጠቀም የእስልምናን እምነት ለማሳደግና ለማስፋፋት ተጠቅመውበታል"[8]::
2. ከፖለቲካ ሥርዐት በላይ የሆነው ሥልጣን:— እንደ ሙስሊማኑ ትውፊት፣ በአንድ ወቅት ነቢዩ መሐመድ ሲናገሩ፣ "ዐረቦች በሌሎች ሕዝቦች ላይ አንዳችም የበላይነት እንደ ሌላቸው ሁሉ ሌሎች ሕዝቦችም በዐረቦች ላይ የበላይ አይደሉም"[9] ብለዋል:: የሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን የፓኪስታን የተሐድሶ መሪ ማሁዱዲ ይህንን የነቢዩን መሐመድ ንግግር አዘውትሮ በመጥቀስ፣ ዐረብ ያልሆነውን የሙስሊም ማኅበረሰብ ከዐረብ ተጽእኖ ለማላቀቅ ከፍተኛ ትግል አድርጎአል:: ይሁን እንጂ ራፊቅ ዘካሪያ ደግሞ፣ የሙስሊሙ ማኅበረሰብ በአጠቃላይ የዐረብኛ ቋንቋ ለሚያውቁ እንዲሁም ለዐረቦች ከፍተኛ አክብሮት እንዳለው ገልጸአል[10]::
በቀደምትነት እስልምናን የተቀበለው የዐረቡ ማኅበረሰብ በዙሪያው ከሚገኙት ማኅበረሰቦች በሥልጣኔ ወደ ኋላ የቀረ ነበር:: የዐረብኛው ቁርአን በሥልጣኔ ወደ ኋላ ለቀረው ለዐረብ ሕዝብ ትልቅ ጎደል ሰጥቶአል:: ነገር ግን እየቆየ ሲሄድ በዐረብኛ ቋንቋ የተገለጠው መልእክት ዐረብ ያልሆነውን የሙስሊም ማኅበረሰብ ማግለያ መሣሪያ መሆን ጀመረ:: እስልምና ወደ ተለያዩ አካባቢዎች እየተስፋፋ ሲመጣ፣ የዐረብኛ ተናጋሪ ከሆኑት በተጨማሪ የነቢዩ መሐመድ ዘመዶች (ቁሬይሾች) የሙስሊሙ ማኅበረሰብ የበላይ ሆኑ፣ የዐረብ ዝርያ የሌለው ሙስሊም በእነርሱ ቀጥተር ሥር ወደቀ[11]:: ለብዙ ዓመታት መሐመድ የዐረቦችን የበላይነት ለማስቀረት የተናገሩት ንግግር በፍጹም በተግባር ሊተረጉም አልቻለም[12]::
3. የፖለቲካ ሥርዐት መቀየር:— የፖለቲካ ሥርዐትን ስለመቀየር ራፊቅ ዘካሪያ እንዲህ ይላል:— "የሙስሊሙ ኅብረተሰብ መሪ መቼና እንዴት ይቀየር? የሚለው ጥያቄ በመጀመሪያዎቹ የእስልምና ዘመናት ላይ የነበሩትን የሸሪአ ሕግ ምሁራንን ግራ አጋብቶ ነበረ:: መሪዎች ሰነፍ ሲሆኑ፣ ዓለማዊነት ሲያጠቃቸው፣ ታማኝነት ሲጐድላቸው፣ አምባገነን

[8] Rafiq Zakaria, *The Struggle within Islam: The Conflict Between Religion and Politics* (New York: Penguin, 1989), 284.
[9] ዝኒ ከማሁ፣ 285::
[10] ዝኒ ከማሁ::
[11] ዝኒ ከማሁ::
[12] ዝኒ ከማሁ::

ሲሆኑ ወይም ደግሞ ዐላማቸውን ሲስቱ ሙስሊም የነገረ መለኮትና የሕግ ምሁራን መሪዎች ከሥልጣናቸው እንዲነሡ የሚጠይቅ አንዳችም አስተያየት አልሰጡም:: እነዚህ ምሁራን በተቃራኒው ነቢዩ መሐመድ "ለባለሥልጣናት ተገዙ" ያሉትን ንግግር በመጥቀስ ሕዝቡ ለእነዚህ መሪዎች እንዲታዘዝ አስተምረዋል"[13]::

እነዚህ ሦስት ነጥቦች ዲሞክራሲያዊ ሥርዐት የተመሠረተባቸውን መሠረታዊ ፋይዳዎች የሚያንፀባርቁ አይደሉም:: ነገር ግን በዚህ ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ፣ በኡላማዎች (በእስልምና ሕግ ምሁራን) መካከል ምክክሮች (ሹራ) ይካሄዳሉ:: ሹራ በኡላማዎች መካከል የሚካሄደውን ዲሞክራሲያዊ ውይይት አመልካች ቢሆንም፣ ኡላማዎች የሚያስተላልፉት ውሳኔ የእስልምናን ሕግ (የሸሪአን ሕግ) መሠረት ባደረገ መልኩ ብቻ ነው:: ይህ አሠራር ሌሎች ማኅበረሰቦች ከሚከተሉት አስተዳደር ፍጹም የተለየ ነው:: በእስልምና ማኅበረሰብ ውስጥ ያሉ የዲሞክራሲያዊ ሥርዐት አራማጆች፣ የዲሞክራሲን መሠረታዊ ፋይዳዎች በትክክል ለመረዳት ከእስልምና ውጪ መመልከት የግድ ይሆንባቸዋል[14]::

በቴምፕል ዩኒቨርስቲ ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ዲሞክራሲያዊ አስተዳደርን ያበረታታል ብዬ ስናገር በዚሁ ዩኒቨርስቲ የሚማር ሙስሊም ተማሪ "እስልምና ዲሞክራሲ አይደለም" ሲል ተናገረ::
ከሰማይ የወረደው መልእክት (ቁርአን) የሙስሊሙ ማኅበረሰብ በሌሎች "ሰዎች ላይ መስካሪዎች" እንዲሆን ነው (ሱራ 2+143) የሚለው ቁርአናዊ ትምህርት አንዳንዴ ሙስሊሞች በሌሎች ሕዝቦች ላይ ወታደራዊና ፖለቲካዊ ዘመቻ እንዲያደርጉ የሚያበረታታ ነው:: አፍሪካዊው የታሪክ ምሁር ጆን አለምቢላህ አዙማህ የአፍሪካውን ተሞክሮ በመጥቀስ ይህ የሙስሊማኑ አስተሳሰብ ሙስሊሞች በአፍሪካውያን ላይ ጦርነት ለመክፈት እንዴት እንዳነሣሣቸው ጽፎአል:: አዙማህ በምዕራብ አፍሪካ አገሮች እስልምና የተስፋፋው በጂሐድ ጦርነት አማካይነት እንደ ሆነም በስፋት አብራርቶአል[15]:: በሱዳን ለሩብ ምዕተ ዓመት የነበረውን የእርስ በርስ ጦርነት ያባባሰው፣ ሙስሊም ሱዳናውያን ለጂሐድ ጦርነት የነበራቸው አመለካከት ነው:: ይህ ሁኔታ በሙስሊሞችና በክርስቲያኖች መካከል መተማመን እንዳይፈጠር ትልቅ የሆነ እክል

[13] ዝኒ ከማሁ፣ 290::
[14] ዝኒ ከማሁ፣ 288-89::
[15] John Alembillah Azumah, *The Legacy of Arab-Islam in Africa* (Oxford: Oneworld Publications, 2001), 63-108.

ፈጥሮአል። በጦርነት መሻል ዕርቀ ሰላም ማውረድ ከፍተኛ ዋጋ የሚያስከፍል አስቸጋሪ ጉዳይ ነው።

በሌላ አንጻር ደግሞ እስልምናን ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለማስፋፋት የሚፈልጉ ሙስሊም ሚስዮናውያን ተልእኮዋቸው መሠረት ያደረገው፣ ስለሰላም በቁርአን ውስጥ የተገለጹትን ምንባባት ነው። በምሥራቅ አፍሪካና በኢንዶኔዥያ እስልምና የተስፋፋው በጦርነት ሳይሆን በንግድና በስደት ሲሆን፣ የእስልምናን ሃይማኖት ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለማስፋፋት ራሳቸውን በሰጡ ሰዎች በተለይም በሱፊ ሙስሊሞች አማካይነት ነው። በጂሐድ ጦርነትም ሆነ በሰላማዊ መንገድ እልምናን ያስፋፉ ሙስሊሞች፣ "አላህ ለሰው ልጆች መለኮታዊ መልእክት ልኮአል፣ ሰዎች ሁሉ ለዚህ መልእክት ሊገዙ ይገባል" የሚል ተመሳሳይ ዐላማ ያንገቡ ናቸው።

ሂሰዊ አስተሳሰብ

ሰዎች ታንዚልን መሠረት ስላደረገው መገለጥ ያላቸው ምልከታ፣ እውነትን ለማወቅ ያላቸውን አመለካከት በምን መልኩ ይወስነዋል? በምዕራፍ ሦስት ላይ አዳም "ለእንስሳት ስም እንዲያወጣ ታዘዘ" በሚለው ርእስ ሥር ለዚህ ጥያቄ መልስ ሰጥተን ነበር። የእግዚአብሔር ቃል ከሰማይ ወረደ (ታንዚል) የሚለው አስተሳሰብ፣ እግዚአብሔር ለአዳም የእንስሳትን ስም ሁሉ አስተማረው ከሚለው ቁርአናዊ ትምህርት ጋር ይስማማል። አንድ ሰው ከሰማይ ተገለጠ ስለተባለው እውነትና ነጻ በሆነ መንገድ አእምሮውን በመጠቀም ከሚደርስበት እውነት ጋር እንዴት ይዛመዳል የሚለው ጥያቄ መሠረታዊ ጥያቄ ነው። ይህ ጥያቄ ሙስሊሞችም ሆነ ክርስቲያኖች ሊመልሱት የሚገባ ወቢይ ጥያቄ ነው። ነገር ግን ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ስለ መለኮታዊ መገለጥ ያላቸው አመለካከት የተለያየ መሆኑ ይህንን ጥያቄ በተለያየ መንገድ እንዲመልሱ ያደርጋቸዋልን?

ሻቢር አህታር የተባለው ዘመናዊ ሙስሊም ፈላስፋ በግሌዥያ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ለሚማሩ ተማሪዎቹ እውነትን በተመለከተ የተለያዩ ጥያቄዎችን መጠየቅና በጥያቄውም ላይ በግልጽነት መወያየት እንደሚያስፈልግ አስተያየቱን ሰጥቶአል። የአህታር ባልንጀሮች ግን፣ "ሙስሊሞች...ሊማሩት የሚችሉት አንዳችም አዲስ ነገር የለም። የምዕራባውያን ነጻ ምርመራ ዐላማ ቢስ ነው። እግዚአብሔር እውነትን ሁሉ ስለገለጠልን ነጻ በሆነ መንገድ አእምሮአችንን

በመጠቀም ነገሮችን እንመርምር የሚለው ጥያቄ አስፈላጊ አይደለም" ሲሉ ይከራከራሉ[16]።

አህታር አብረውት ያሉትን የዩኒቨርስቲ ማኅበረሰብ፣ "እውነትን መፈለግና እውነትን መመዘን ያስችለናል በሚል ዘመናዊ ዩኒቨርስቲ አቋቁመን እውነት ሁሉ ተገልጠልኛል በሚል ጭፍን አመለካከት ውስጥ እንኖራለን...በማለት ይሞግታል"[17] አህታር ሙስሊሞች እውነትን በተመለከተ ማናቸውንም ዐይነት ጥያቄዎች እየጠየቁ እንዲወያዩ ያበረታታል። አንዳንዴ ይህ ዐይነቱን አቋም ይዞ መነሣት ብቸኛ ሊያደርግ ይችላል። እውነትን ሁሉ እግዚአብሔር ገልጠልናል በአንጻሩ ደግሞ እውነትን በተመለከተ የተለያዩ ጥያቄዎችን እያነሣን በመወያየት እውነትን ማፈላለግ አለብን የሚሉት አመለካከቶች እርስ በርሳቸው ይስማሙ ይሆን?

ተሰግዎና የክርስቲያኖች ተልእኮ

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እውን የሆነው የክርስቲያኖች ተልእኮ ምን እንደሚመስል በአጭሩ እንመለከታለን። በጴንጤቆስጤ (በበዓለ ኀምሳ) ቀን በኢየሩሳሌም የነበሩ ሰዎች ሁሉ፣ ሐዋርያት ወንጌልን በእነርሱ ቋንቋ በመስበካቸው ምክንያት ተደንቀው ነበር። ይህ ሕዝብ፣ "የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ በልሳኖቻችን ሲናገሩ እንሰማቸዋለን" ሲሉ ተናግረዋል (ሐዋርያት ሥራ 2+11)። ሐዋርያት በልሳን የተናገሩት ከዐሥራ ሁለት በሚበልጡ ቋንቋዎች ነው። ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሰዎች ሁሉ በራሳቸው ቋንቋና ባህል ውስጥ የእግዚአብሔርን መልእክት መቀበል እንደሚችሉ ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች መተርጐም

ከጴንጤቆስጤ (ከበዓለ ኀምሳ) ቀን ጀምሮ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች በመተርጐም፣ ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል በራሳቸው ቋንቋ እንዲያነቡ/እንዲሰሙ ታላቅ ጥረት አድርጋለች። ቤተ ክርስቲያን ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንዲደርሳቸው ያደረገችበት ወቢይ ምክንያት ምንድን ነው? ለዚህ መሠረታዊ

[16] Rippin, Muslims, 288.
[17] ዝኒ ከማሁ።

ምክንያቱ የእግዚአብሔር ቃል በሰዎች ባህልና ቋንቋ ውስጥ መገለጡ ነው። የወንጌልም መሠረታዊ ትምህርት አምላክ በመሲሑ በክርስቶስ አማካይነት ከእኛ ጋር ሆነ (አማኑኤል) የሚል ነው። እግዚአብሔር በአካል በመሲሑ በኩል በእስራኤል ባህል፣ ቋንቋ እንዲሁም ማኅበረሰብ ውስጥ ተገለጠ። በእርግጥ ከላይ እንደ ተመለከትነው ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል በሰዎች ባህልና ቋንቋ ውስጥ ተገልጦአል። እግዚአብሔር ቃሉን በሰዎች ቋንቋ አማካይነት ገለጠ። እርሱ እኛ ባለንበት ነባራዊ ሁኔታ ውስጥ ወደ እኛ በመምጣት በሙላት፣ በታላቅ ክብር እንዲሁም በማያሻማ ሁኔታ በክርስቶስ በኩል ተገናኘን።

ይህም ወንጌል በሰዎች ባህልና ቋንቋ ውስጥ ስለተገለጠ፣ ማንኛውም ዐይነት ባህልና ቋንቋ ሳይገድበው ይሠራል የሚለውን እንድምታ ታሳቢ ያደረገ ነው። ለምሳሌ አዲስ ኪዳን የተጻፈው በግሪክ ቋንቋ ቢሆንም፣ ወደ ግብፃውያን ቋንቋ ሲተረጉም እግዚአብሔር ለግሪኮች በግሪክ ቋንቋ የተናገረውን መልእክት ለግብፃውያን በግብፅ ቋንቋ ያንኑ መልእክት እንዲያውቁት አድርጓል። የግሪክ ክርስቲያኖችም በግብፅ ክርስቲያኖች ላይ አንዳችም ተጽእኖ ማድረግ በፍጹም አይችሉም። (የሚያሳዝነው ግን አንዳንዴ ቤተ ክርስቲያናት በሌሎች አገሮች ባሉ ቤተ ክርስቲያናት ተጽእኖ ሲደረግባቸው ይስተዋላል። ይህ ዐይነቱ ድርጊት የወንጌልን መልእክት ክፉኛ የሚጻረር ነው)።

ለብዙ ዓመታት በአውሮፓ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ከወንጌሉ ባሕርይና ትምህርት ጋር የሚጻረሩ ተግባራትን ሲፈጽሙ ቆይተዋል። በመካከለኛው ዘመን የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ሌሎች ሕዝቦችን ትጨቁን የነበረው በላቲን ቋንቋ የተጻፈውን መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ በመጠቀም ነበር። በግብርና የሚተዳደረው የኅብረተሰብ ክፍል በላቲን የተጻፈውን መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብም ሆነ መረዳት አይችልም ነበር[18]።

በዐሥራ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የማተሚያ መሣሪያ መፈልሰፉ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ተለያየ የአውሮፓውያን ቋንቋዎች እንዲተረጉም እንዲሁም የነጻነት እንቅስቃሴዎች በመላው አውሮፓ እንዲስፋፉ አስተዋጽኦ

[18] ይህ ዐይነቱ ችግር በኢትዮጵያ በምትገኘውም፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሰፋት የሚስተዋል ዘመን የፈጀ ችግር ነው። ሥርዐተ አምልኮ በሚፈጸምበትም ጊዜ ሆነ፣ ስብከተ ወንጌልና ትምህርተ ወንጌል በሚቀርብበት ጊዜ ሁሉ ቤተ ክርስቲያኒቱ የግእዝን ቋንቋ መጠቀሟን፣ በርካታ ምዕመናን የወንጌልን ትምህርት በትክክል እንዳይረዱ አክል ፈተሮባቸው ይገኛል። የቤተ ክርስቲያኒቱ ምሁራንና መሪዎች በጉዳዩ ላይ ሊመክሩ ለችግሩም ሁነኛ መፍትሔ ሊያፈላልጉ እንደሚገባ እናምናለን።

አድርጉአል። ከእነዚህ እንቅስቃሴዎች በኋላ በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖች ተቋቋሙ። በአውሮፓ በአጠቃላይ አዲስ በተፈጠሩ የክርስቲያን ኅብረቶች ውስጥ የወንጌል መልእክት ሥር እየሰደደ መጣ። የኅሮቴስታንት ተሐድሶና የዳግም መጥምቃውያን (የአናባፕቲስት) እንቅስቃሴ በዐሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ኅብረት ውጤቶች ናቸው።

በአሁኑ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች ተተርጉሞአል። የመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰኑ ክፍሎች ሦስት ሺህ በሚሆኑ ቋንቋዎች የተተረጉሙ ሲሆን፣ ዘጠና አምስት ከመቶ ለሚሆነው የዓለማችን ነዋሪ በራሱ ቋንቋ መጽሐፍ ቅዱስ (ቢያንስ የመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰነ ክፍል) ተተርጉሞ ቀርቦለታል።

<u>መጽሐፍ ቅዱስን በተለያዩ ቋንቋዎች የመተርጉም ጥቅም</u>

መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች መተርጉም፣ ሰዎች የቃለ እግዚአብሔርን ትምህርት እፍ በፈቱበት ቋንቋ አንብበው እንዲረዱ፣ መሲሑን እንዲቀበሉና የወንጌልን ትምህርት በራሳቸው ዐውድ ውስጥ እንዲያጣጥሙ ታላቅ ዕገዛ ያደርግላቸዋል። ያልተግሩ ሰዎች እንኳ አምልኮተ እግዚአብሔር በሚካሄድበት ወቅት የሚነበበውን የቃለ እግዚአብሔር ትምህርት በትክክል እንዲረዱ እንዲሁም ጸሎታቸውን በራሳቸው ቋንቋ ወደ አምላካቸው እንዲያደርሱ ይረዳቸዋል። ወንጌል በራሳቸው ባህልና ቋንቋ ውስጥ ተጣጥሞ መገለጡ፣ ለእምነታቸው ጥንካሬ ይሰጣል። ይህ ዐይነት ሥራ፣ የኅብረተሰቡን ባህልና ቋንቋ ማዕከል ያደረገ ወንጌል የሚሰበክበት ስለሆነ ጠንካራ የሆነች ዐውዳዊ ቤተ ክርስቲያን ትመሠረታለች።
ላሚን ሳኔህ መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች መተርጉሙ ሁለት ዐይነት ችግሮችን ያስወግዳል ብለዋል። አንደኛው፣ አዲስ የተመሠረተችው ቤተ ክርስቲያን ከሚስዮናውያን የባህል ተጽእኖ ነጻ እንድትወጣ ያደርጋታል። ሁለተኛው ደግሞ፣ ቤተ ክርስቲያኒቱ በተመሠረተችበት አካባቢ ባለው ባህል ውስጥ ያለውን ክፉ ልምምድ አጥርታ እንድታይ ዕገዛ ያደርግላታል። በየትኛውም መንገድ መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች መተርጉም፣ ወንጌል በኅብረተሰቡ ውስጥ ዘልቆ እንዲገባ የሚያደርግ ሲሆን፣ ቤተ ክርስቲያንም ለማኅበረሰቡ ጨውና ብርሃን በመሆን እኩይ የሆነውን ባህል የመለወጥ ዐቅም ታገኛለች[19]።

[19] Sanneh, *Translating the Message*, 157-209.

ተሰግሞና ባህል

መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች መተርጉም ስለዚያ ማኅበረሰብና ባህል ጥናት እንዲደረግ የሰዎችን ፍላጐት ከመቀስቀሱም ባሻገር የማኅበረሰቡ ባህል ተጠብቆ እንዲኖር ታላቅ ዕገዛ ያደርጋል። በዓለማችን በመቶዎች ለሚቈጠሩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ለመጀመሪያ ጊዜ በቋንቋቸው የተጻፈው መጽሐፍ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስን ለማንበብ በሚያደርጉትም ጥረት ውስጥ ከትምህርት ጋር እንዲተዋወቁ ትምህርት ቤቶችንም እንዲቈረቍሩ ምክንያት የሆነባቸው በርካታ ሁኔታዎች አሉ። ሰዎች በቋንቋቸውና በባህላቸው መኩራት ሲጀምሩ ባህላቸውና ቋንቋቸው ይታደሳል። እነርሱም "እግዚአብሔር በራሳችን ቋንቋ ውስጥ እየተናገረን ነው፣ ይህም አስደሳች ጉዳይ ነው" ይላሉ።

ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን የወንጌል ተልእኮ መጽሐፍ ቅዱስን በጎበረተሰቡ ቋንቋ ማቅረብ ብቻ አይደለም። ለምሳሌ በአሁኑ ዘመን በአፍሪካ አህጉር የቤተ ክርስቲያን የወንጌል ተልእኮ የአፍሪካውያንን ባህል በመለወጥ በማቆየትና ሰዎች ለባህል ጥናት ፍላጐት እንዲኖራቸው በማድረግ በኩል ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጐአል። የቀለም ትምህርት፣ የኅብረተሰብ ልማት፣ ሳይንሳዊ አብዮት፣ የሕክምና አገልግሎት እንዲሁም የማኅበረሰብ ጤና አጠባበቅ ትምህርት በአፍሪካ አህጉር ከቤተ ክርስቲያን የወንጌል አገልግሎት ጋር ተያይዘው የተከሠቱ ነገሮች ናቸው። በተጨማሪም ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥሮአል፤ እግዚአብሔር እያንዳንዱን ሰው ይወዳል፤ ያከብራል፤ እግዚአብሔር የሰዎችን ነጻነት ያከብራል፤ ክፉ መሪዎች በእግዚአብሔር የፍርድ ወንበር ፊት ስለሚቀርቡ እኩይ የሆነውን አስተዳደራዊ አካሄዳቸውን መቀየር አለባቸው የሚሉት መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎች፣ ዲሞክራሲያዊ ተቋማትንና መንግሥታትን ለመመሥረት እጅግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል[20]።

በ1834 ዓ.ም የሞተውና የፕሮቴስታንት ሚስዮናዊ ሆኖ ከእንግሊዝ ወደ ሕንድ የሄደው ዊሊያም ኬሪ "የሕንድ ቋንቋዎች አባት" የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል። ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? ዊሊያም ኬሪና የእርሱ ሚስዮናዊ ቡድን የሕንድ ቋንቋዎችን ለማስተማር በሕንድ የቋንቋ ትምህርት ቤቶችን ከፍተው ስለነበር ነው። እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስን ጨምሮ የተለያዩ መጻሕፍትን ለምሳሌ ስለባዮሎጂ፣ ስለሥነ እፅ፣ ስለግብርና፣ ስለታሪክ የሚያስተምሩ እንዲሁም

[20] Kwame Bediako, *Christianity in Africa: The Renewal of Non-Western Religion* (Maryknoll, N.Y.: Orbis Books, 1995), 39-58, 172-188.

የሂንዱ ሃይማኖት መጻሕፍትን በአገሬው ቋንቋ አሳትመው ማቅረባቸው ነው ይህን ከብር እንዲጐናጸፉ ያደረጋቸው[21]።

ሕንዳውያን፣ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ወደ ህንድ አገር ከመጣታቸው በፊት ትምህርት ለመማር የሚመቸው ብቸኛው ቋንቋ የሂንዱ ሃይማኖት መጻሕፍት የተጻፉበት የሳንስክሪት ቋንቋ፣ ቁርአን የተጻፈበት የዐረብኛ ቋንቋ፣ የእንግሊዞቹ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ነው የሚል እምነት ነበራቸው። በወቅቱ የነበሩት የቤተ ክርስቲያን ሚስዮናውያን ስለቋንቋ የነበራቸው እምነት ከዚህ ዐይነቱ አስተሳሰብ ፍጹም የተለየ ነበር። ዊሊያም ኬሪና የእርሱ ሚስዮናዊ ቡድን "ሴራምፖር ክርስቲያን ኮሌጅ" የተባለ፣ በእስያ የመጀመሪያው የሊበራል አርት ዩኒቨርስቲ ከፈቱ። የኮሌጁ ቀዳማይ ዐላማ ከሆኑት መካል አንዱ በሕንድ በሚገኙ አካባቢዎች በሙሉ፣ በአገሪ ሰብ ቋንቋ ትምህርት ቤቶችን የሚጀምሩ መምህራንን ማሠልጠን ነበር። እያንዳንዱ ቋንቋ ክቡር ነው! እያንዳንዱ ሰው በአፍ መፍቻ ቋንቋው የማንበብ ዕድል ሊያገኝ ይገባዋል[22]።

ስጥቃት መጋለጥ

በተሰገዎ የተገለጠው ወንጌል ዘወትር ለጥቃት የተጋለጠ ነው። በማናቸውም ምክንያት ሰዎችን የማስገደድ ባሕርይ የለውም። ወንጌል እርስ በርስ የመከባበርን፣ የፍቅርንና የነጻነትን ዘር ይዘራል እንዲሁም ፍትሓዊ ያልሆኑና ሰዎችን የሚያዋርዱ ተግባሮችን አጥብቆ ይቃወማል። ለአምላክዋ ታማኝ የሆነች ቤተ ክርስቲያን የጌታ ጸጋና ተሰገዎን ያማከለ አገልግሎት የሚታይባት ቤተ ክርስቲያን ነች። ይህ የመሲሑ አገልግሎት በተመሳሳይ መንገድ በክርስቶስ ሕይወት ጸጋና በአገልግሎት ለእኛ ተገለጠልን። የመሲሑ የፍቅር አገልግሎትና ምስክርነት እንዲሁም ይህ ዐይነቱ እውነት ዘወትር ለጥቃት የተጋለጠ ነው። መሲሑ ኢየሱስ የሞተበትም ዐቢይ ምክንያት ይኸው ነው። ከእርሱም ሞት የምንማረው ይህንኑ እውነት ነው።

እውነት ምንድን ነው? ሰዎች እውነትን ሊቈጣጠሩ እንዲሁም እውነትን ባሻቸው መንገድ ሊጠመዝዙ ይችላሉን? ምንም እንኳ ከላይ እንደ ተመለከትነው የፕሮፌሰር ሻቢር አህታር ተማሪ በዚህ ጉዳይ መረበሹን ቢናገርም ብሩሕ አመለካከት ላለው ምሁር ወንጌል ለዚህ ዐይነቱ ጉዳይ የሚሰጠው መልስ ምንድን ነው? የሚለውን በአንክሮ ሊመለከተው የሚገባው

[21] J. T. K. Daniel and R. E. Hedlund, *Carey's Obligation and India's Renaissance* (Serampore: Council of Serampore College, 1993), 153-298.

[22] ዝኒ ከማሁ 153-175።

ጥያቄ ነው። ይህ እንዲያውም እንደዘበት አናንቀነው የምናልፈው ጥያቄ አይደለም። ሙስሊሞችም ሆኑ ክርስቲያኖች የተገለጠውን መልእክት በመቀበልና ሌላ እውነት አለ ብሉ እውነታውን ለማወቅና እውነታውን ለመቀበል በሚደረገው ጥረት መካከል ያለውን ልዩነት ለማስታረቅ ይቸገራሉ። እውነት ለጥቃት የተጋለጠች በአንጻሩ ደግሞ ድል ነሺ ናት ወይስ እውነትን ሊያበላሹ ከሚነሡ ሰዎች መጠበቅ አለባት?

ዊሊያም ኬሪ መንጌል ነጻ ያደርጋል፤ ጎይልም ይሰጣል። ስለ እውነት መመስከር እንጂ ስለ እውነት ጠበቃ መሆን አያስፈልግም ብሉ ስለሚያምን ሴራምፖር በሚገኘው የሊበራል አርት ኮሌጅ ተማሪዎች የተለያዩ ዐይነት ትምህርቶችን እንዲያጠኑ ይበረታቱ ነበር። ሳንስክሪትና የሂንዱ ሃይማኖት እንኳ የኮሌጁ ዋና የትምህርት ዘርፎች ነበሩ። የወንጌልም ትምህርት አብሮ ይሰጥ ነበር። ተማሪዎች በጥልቀት እንዲያስቡ፣ እንዲመራመሩ እንዲሁም በወንጌል ውስጥ ስላለው እውነት በነጻነት የራሳቸው ውሳኔ እንዲወስኑ ተደርገዋል።

ዊሊያም ኬሪ ይህን መንገድ መከተሉ ትክክል ነውን? ሙስሊሞችም ሆኑ ክርስቲያኖች የትኛውን መንገድ እንከተል በሚሉት ጉዳዮች ይቸገራሉ። አንድ ሰው ለተገለጠው እውነት ታማኝ እየሆነ በአንጻሩ ደግሞ ስለ እውነት ግልጽና ጥልቅ የሆኑ ጥያቄዎችን እየጠየቀና ለጥያቄዎቹም መልስ እያፈላለገ መኖር እንዴት ይችላል? የሙስሊሞችና የክርስቲያኖች የእምነት ጉዞ የሚመራው ስለመለኮታዊ መገለጥ ባላቸው የተለያየ መረዳት ነው። ሙስሊሞች በታንዚል ክርስቲያኖች ደግሞ በተሰገው። እነዚህ የተለያዩ ምልከታዎች የሚያመጡት ልዩነት ምንድን ነው?

የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ

ዮሐንስ 1+1-5:14

የቁርአን ምንባብ

ሱራ 96+1-5

<u>የአስተውሎትና የውይይት ጥያቄዎች</u>

1. ሰዎች እምነታቸውን እውነትን ሊያጠፉ በሚችል መንገድ ሲጠ ቀሙበት ያዩባቸው አጋጣሚዎች ካሉ በምሳሌነት ያቅርቧቸው።
2. የሙስሊሙ ኡማና ቤተ ክርስቲያን ለተገለጠላቸው እውነት ታማኞች ናቸው። የተገለጠውን እውነት አስመልክቶ በሙስሊሞችና

በክርስቲያኖች መካከል የሚደረጉ ውይይቶችን አስቸጋሪ የሚያደርጉ ምክንያቶች ምን ምን እንደ ሆኑ ይግለጹ።

3. ሙስሊሞች ስለታንዚል ያላቸው መረዳት ስለተለያዩ ባህሎች ያላቸውን አመለካከት በምን መልኩ ወስኖታል? ክርስቲያኖች ስለእግዚአብሔር ቃል መገለጥ ያላቸው እምነት ስለሌሎች ባህሎች ባላቸው አመለካከት ላይ ምን ዐይነት ተጽእኖ አስከትሎአል (ሐዋርያት ሥራ 2+5-12፣ ሱራ 12+2)?
4. ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን እንዲሁም የመጽሐፍ ቅዱስን የተለያዩ ክፍሎች በሺዎች በሚቆጠሩ ቋንቋዎች ተርጉማለች። የሙስሊሙ ኡማ ግን ዐረብኛውን ቁርአን ይጠቀማል። በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ የራስዎትን አስተያየት ይስጡ (ማቴዎስ 1+23፤ ሱራ 16+103፤ 85+21-22)።
5. ጥልቅ ምርምርና ግልጽ የሆነ ጥናት የምዕራባውያን ዩኒቨርስቲዎች ቀዳማይ ተግባር ነው። እነዚህ ዩኒቨርስቲዎች ለቁርአንና ለመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶች ታማኝ ሆኖ ለሚኖረው የማኅበረሰብ ክፍል ያላቸው ተግዳሮት ምንድን ነው?

ምዕራፍ ስምንት

ጎይል
ሒጅራ—መስቀል

ከሥራ ባልደረቦቼ ጋር በመሆን፣ "የእግዚአብሔር ሕዝብ" የሚል የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በማዘጋጀት ላይ ሳለን፣ አንድ ባልንጀራዬ፣ "ሙስሊም ጓደኞቻችን ይህንን መጽሐፍ አይቀበሉትም" አለኝ። በዚያን ጊዜ ስለኖኅና ስለጥፋት ውሃ ታሪክ የመጀመሪያውን ዙር ጽሑፌን አጠናቅቄ ነበር። እኔ ግን ቁርአን ስለ ኖኅ ታሪክ ስለሚናገር ሙስሊሞች ስለ ኖኅ ለመማር ደስተኛ እንደሚሆኑ እርግጠኛ ነበርሁ።

ግማሽ ደርዘን የሚሆኑና ከእስልምና ወደ ጌታ የመጡትን አማኞች በአባልነት የያዘው የሥነ ጽሑፍ አማካሪዎች ቡድን አንዱ የሆነው ሰው የሰጠው አስተያየት፣ ስለ መጽሐፉ ይዘት ራሴን እንድጠይቅ አደረገኝ። እኔም፣ "ይህ መጽሐፍ ሙስሊሞችን ሊያበሳጭ የሚችለው በምን ምክንያት ነው?" ስል ጠየቅሁ። የሥነ ጽሑፍ አማካሪዎች ቡድኑ ዘፍጥረት 6፥6 ላይ፣ "እግዚአብሔር ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ ተፀፀተ በልቡም አዘነ" የሚለውን ክፍል ጠቀሱልኝ። እኔም በአግራሞት፣ "ይህ ክፍል ሙስሊሞችን እንዴት ያበሳጫል?" ስል ጠየቅሁ። በእኔ ግንዛቤ ማነስ ግራ በመጋባት፣ "አሁንም አልገባህም እንዴ?" በማለት የሥነ ጽሑፍ አማካሪዎች ቡድኑ ጠየቀኝ። እነርሱም "በእስልምና እምነት እግዚአብሔር ሰዎች በሚሠሩት ነገር አይታወከም። እርሱ ልዑልና ሁሉን ቻይ ነው። እግዚአብሔር እኛ በምንሠራው ሥራ መቼም ቢሆን አዝናለሁ አይልም" አሉኝ።

በእስልምናና በወንጌል መካከል ትልቅ ልዩነት እንዳለ እንመለከታለን። እስልምናና ወንጌል ስለ እግዚአብሔር ጎያልነት ያስተምራሉ። እስልምና ሁሉን ቻይ የሆነው አምላክ ለሰዎች ሲል መከራን አይቀበልም ይላል። ነገር ግን ወንጌል፣ ሁሉን ቻዩ እግዚአብሔር ለእኛ ሲል መከራን መቀበል እንደ መረጠ ያስተምረናል።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በእስልምናና በወንጌል መካከል ያለውን ይህን ልዩነት በሰፊው ለመመልከት እንሞክራለን። በዚህ ጥናታችን በተቃራኒ አቅጣጫ ያሉትን ሁለት የተለያዩ ጉዞዎች ማለትም ሒጅራንና መስቀልን

እንመለከታለን። ሒጅራ ማለት መሐመድ ከመካ ወደ መዲና ያደረጉት ጉዞ ነው። መስቀል ግን ኢየሱስ ከገሊላ ወደ ኢየሩሳሌም ከተጓዘ በኋላ በመስቀል ላይ በመሞት ጉዞውን ያጠናቀቀበት ስፍራ ነው። የሒጅራና የመስቀል ጉዞዎች ስለ እግዚአብሔር ያለንን መረዳት በተመለከተ መሠረታዊ ልዩነት የሚፈጥሩ ናቸው። እነዚህ ትምህርቶች ስለ እስልምናና ሆነ ስለ ወንጌል መልእክት ከፍተኛ ትርጉም አላቸው። እግዚአብሔር ለእኛ ሲል ከእኛ ጋር በመሆን መከራን ይቀበላልን? ይህን ጥያቄ በተመለከተ ከእስልምናና ከወንጌል አንጻር የሚሰጡ ትምህርቶች ለሙስሊሙ ማኅበረሰብና ለቤተ ክርስቲያን መሠረቶች ናቸው።

በመጀመሪያ ክርስቶስ ወደ ኢየሩሳሌምና ወደ መስቀል ያደረገውን ጉዞ በእሰሳ መልክ የምንቃኝ ሲሆን፣ ከዚያ በኋላ መሐመድ ከመካ ወደ መዲና ያደጉትን ጉዞ (ሒጅራ) እንመለከታለን። እነዚህ ጉዞዎች እኛ ስለ እግዚአብሔር ባሕርያትና ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ያለንን መረዳት እምነት ምን ዐይነት መረጃዎች ይሰጣሉ?

ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ተጓዘ

ኢየሱስ ገሊላ ተብሎ በሚጠራው በሰሜናዊ ኢየሩሳሌም ይኖር ነበረ። ኢየሱስ በጣም ደስተኛ ነበር። ሐዋርያው ጴጥሮስ እርሱና ሌሎች ሐዋርያት በኢየሱስ ላይ ያላቸው እምነት ምን እንደሚመስል እንዲህ ሲል ምስክርነቱን ሰጠ፦— "አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ"።

ኢየሱስ በጴጥሮስ ንግግር በመደሰት፦— "የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ። እኔም እልሃለሁ አንተ ጴጥሮስ ነህ በዚችም ዐለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ ፡ግህነም ደጆችም አይችሉአትም" (ማቴዎስ 16+17-18) ሲል ተናገረ።

ኢየሱስ መሲሕ እንደ ሆነ የመሰከሩት ደቀ መዛሙርቱ ብቻ ሳይሆኑ፣ መሲሕነቱ ከእርሱ ጋር በገሊላ በሚኖሩ ሰዎች መካከልም የታወቀ ጉዳይ ነበር። በተለይም ሴቶችና ሕፃናትን ጨምሮ አምስት ሺህ ወንዶችን ከመገበ በኋላ፣ የክርስቶስ ዝና በገሊላ ምድር ሁሉ ተሰማ። ኢየሱስ ይህንን ሕዝብ የመገበው አምስት እንጀራና ሁለት ዓሣ በመባረክ ነበር። በዚያ የነበሩ ሰዎች በሥራው በመደነቅ ንጉሥነው እንዲሆን ጠየቁት።

በዚያን ጊዜ የተወሰኑ የገሊላ ሰዎች የሮማ መንግሥትን አዝዝ በመቃወም በስውር ይዋጉ ነበር። እነዚህ ቡድኖች፣ "ቀናተኞች" ("ቀናይያን") በሚል ስያሜ ይታወቁ ነበር። ኢየሱስን ንጉሥነው ቢያደርጉ ተአምራዊ በሆነ መንገድ ጥቂቱን ምግብ በመባረክ ወታደሮቻችንን ይቀልብልናል የሚል ስሜት አድሮባቸው ነበር። የገሊላ ሰዎች በጎይልም እንኳ ቢሆን፣ ኢየሱስን ንጉሥነው ለማድረግ ተዘጋጅተው ነበር (ዮሐንስ 6+15)።

ኢየሱስ ንጉሥ እንዲሆን የቀረበለትን ጥሪ በመቃወም፣ ከሕዝቡ ተለይቶ ወደ ተራራ በመውጣት ሌሊቱን ሙሉ ሲጸልይ ወደረ። ከዚያ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ፊቱን አቀና (ሉቃስ 9+51)። የሚያስደንቀው ጉዳይ ግን ኢየሱስ በኢየሩሳሌም የመስቀል ሞት እንደሚጠብቀው ያውቅ ነበር። ለደቀ መዛሙርቱ በኢየሩሳሌም ሰዎች የሰው ልጅን "ለአሕዛብ አሳልፈው ይሰጡታልና ይዘብቱበትማል ያንገላቱትማል ይተፉበትማል ከገረፉትም በኋላ ይገድሉታል በሦስተኛውም ቀን ይነሣል" (ሉቃስ 18+32-33) ብሎ ይናገራቸው ነበር። ይህ ዐይነቱ ጉዳይ ባለበት ሁኔታ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ተጓዘ።

የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት እርሱ መሲሕ እንደ ሆነ ያምኑ ነበር፣ ሆኖም ግን ተሰቅሎ እንደሚሞት በጭራሽ አላወቁም። እንዲያውም ይህን ሁኔታ ባወቁ ጊዜ እንኳ ጉዳዩን ለመቀበል በብዙ ተቸግረው ነበር። መሲሑ ይሰቀላል ብሎ ማሰብ በጭራሽ ተቀባይነት የሌለው ጉዳይ ነበር። በአንድ አጋጣሚ ኢየሱስ ስለ ስቅለቱ ሲናገር ጴጥሮስ ወደ እርሱ ወስዶ ኢየሱስን ይገስፀው ጀመር። ነገር ግን ኢየሱስ ጴጥሮስን፣ "ወደ ኋላዬ ሂድ አንተ ሰይጣን የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብምና እንቅፋት ሆነህብኛል አለው" (ማቴዎስ 16+23)።

በኢየሩሳሌም ኢየሱስ ተይዞ ከታሰረ በኋላ፣ የመስቀል ላይ ሞት ፍርድ ተፈረደበት። በዚያም ሰዓት እርሱ ከዐሥራ ሁለት ጭፍሮች የሚበዙ መላእክትን መጥራት እንደሚችል ተናገረ (ማቴዎስ 26+53)። ይህ ማለት ሰባ ሁለት ሺህ የሚሆን የመላእክት ሰራዊት ማለት ነው። ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ ከመስቀል ሞት ሊያድነው የሚያስችል የሰውም ሆነ የመላእክት ድጋፍ አልፈለገም።

ኢየሱስን የያዙ ሰዎች ለፍርድ ወደ ጲላጦስ ወሰዱት። በዚያን ጊዜ ጲላጦስ የሮም አስተዳዳሪ ነበር። ኢየሱስም በጲላጦስ የንጉሥ ችሎት ፊት እንዲህ ሲል ተናገረ፣ "መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም መንግሥቴስ ከዚህ ዓለም ብትሆን ወደ አይሁድ እንዳልሰጥ ሎሌዎቼ ይዋጉልኝ ነበር፤ አሁን ግን መንግሥቴ ከዚህ አይደለችም አለው" (ዮሐንስ 18+36)።

ኢየሱስ ከመሰቀሉ በፊት ገረፉት፤ አፈዘብትም፤ ምራቃቸውንም ፊቱ ላይ ተፉ። እንዲሁም የእሾህ ጉንጉን ሠርተው በጭንቅላቱ ላይ አኖሩ። ጫፉ ከብረት በተሠራ ጅራፍም ገረፉት። ዐይኑንም አስረው ተሳለቁበት። ከዚህ በኋላ እጁንና እግሩን በምስማር ቸንክረው በሁለት ወንበዴዎች መካከል በመስቀል ላይ ሰቅለው ገደሉት። በሞት መካከል እያጣጣረ ሳለም በእርሱ ላይ መሣለቃቸውን አላቆሙም ነበር። ሞቱ ሲቃረብ በታላቅ ድምፅ "አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው አለ" (ሉቃስ 23÷34)። ከዚያም "ተፈጸመ" ብሎ ነፍሱን ሰጠ (ዮሐንስ 19÷30)። ክርስቶስ በሞተበት ቅጽበት፣ "እነሆም የቤተ መቅደሱ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ከሁለት ተቀደደ፤ ምድርም ተናወጠች፤ ዐለቶችም ተሰነጠቁ፤ መቃብሮችም ተከፈቱ፤ ተኝተው ከነበሩትም ከቅዱሳን ብዙ ሥጋዎች ተነሡ" (ማቴዎስ 27÷51-52)።

ኢየሱስ ሙሉ ለሙሉ መሞቱን ለማረጋገጥ ከሮማ ወታደሮች አንዱ ጐኑን በጦር ወጋው። ደምና ውሃ ከተወጋው ስፍራ ወጣ። የኢየሱስ ወዳጆች አስከሬኑን መስደው ቅርብ በነበረ መቃብር ቀበሩት። የክርስቶስን አስከሬን ደቀ መዛሙርቱ እንዳይሰርቁት በሚል የሮማ መንግሥት የመቃብሩ በር በትልቅ ድንጋይ እንዲዘጋ ካደረገ በኋላ፣ ጠባቂ ወታደሮችን አስቀመጠ። ነገር ግን እግዚአብሔር ድንጋዩን ያንከባልሉ ዘንድ መላእክቶቹን ላከ። ይህም የሆነው ከሳምንቱ በመጀመሪያ ቀን ወይም ክርስቶስ ከተቀበረ በሦስተኛው ቀን ነው። ብዙ ሴቶች መቃብሩን ለማየት ሲመጡ መቃብሩ ባዶ ሆኖ አገኙ። እግዚአብሔር ኢየሱስን ከሙታን አስነሥቶታልና!

ከዚያ በኋላ ባሉት አርባ ቀናት ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ በተደጋጋሚ ሲታያቸው እንደቆየ ወንጌላት ያስተምራሉ። ቢያንስ ዐሥራ አንድ ጊዜ ያህል የታያቸው ሲሆን፣ በአንዱ አጋጣሚ ደግሞ አምስት መቶ ለሚሆኑ ሰዎች በአንድ ጊዜ ታይቶአል። ኢየሱስ፣ ከሙታን መነሣቱን ይጠራጠር ለነበረው ሐዋርያ (ቶማስ) በምስማር የተቸነከሩትን እጆቹንና እግሮቹን አሳይቶታል።

ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ከታየባቸው አጋጣሚዎች አንዱ እንዲህ ተጽፎአል:—

> ያም ቀን እርሱም ከሳምንቱ ፊተኛው በመሸ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ተሰብስበው በነበሩበት አይሁድን ስለፈሩ ደጆቹ ተዘግተው ሳሉ ኢየሱስ መጣ፤ በመካከላቸውም ቆሞ:— ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው። ይህንም ብሎ እጆቹንም ጐኑንም አሳያቸው። ደቀ መዛሙርቱም ጌታን ባዩ ጊዜ ደስ አላቸው። ኢየሱስም ዳግመኛ:— ሰላም ለእናንተ ይሁን፣ አብ እንደላከኝ እኔ

ደግሞ እልካችኋለሁ አላቸው። ይህንም ብሎ እፍ አለባቸውና:— መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ (ዮሐንስ 20÷19-22)።

የመሐመድ ወደ መዲና መሰደድ

ከክርስቶስ ልደት ከስድስት ምዕተ ዓመት በኋላ፣ መሐመድ የሳውዲት ዐረቢያ ምድር በሆነችው በመካ ከተማ የእስልምናን ሃይማኖት መስበክ ጀመሩ። የስብከታቸውን መልእክት የተቀበሉት ከእግዚአብሔር ዘንድ በመልአኩ ገብርኤል አማካይነት እንደ ሆነ ይናገሩ ነበር። ለዐሥራ ሁለት ዓመታት የተገለጠላቸውን የቁርአንን የተወሰኑ ክፍሎች እንደ ሰበኩ ይታመናል። የዐረቢያ ነዋሪዎች ከጣዖት አምልኮ እንዲመለሱ፣ ክፉ ተግባራትን እንዳይፈጽሙና ማኅበራዊ ፍትሕን እንዲያስጠብቁ ማስጠንቀቂያ ይሰጡ ነበር።

መሐመድ ከሕዝቡ ዘንድ የቀረበላቸው ምላሽ መዘባበቻ መሆን ነበር። ሕይወታቸውም አደጋ ውስጥ ነበር። ቢያንስ አንድ ጊዜ በድንጋይ ተወግረዋል፤ ሰዎች ቆሻሻ ጥለውባቸዋል። እስልምናን ከተቀበሉ ሰዎችም መካል አንዳንዶቹ ተደብድበዋል፤ አንዳንዶች ደግሞ ተገድለዋል። የተቀሩት ወደ ኢትዮጵያ ተሰደዋል[1]። በወቅቱ ባመኑና ባላመኑ ሰዎች መካከል የነበረው ትግል ቀላል አልነበረም።

እግዚአብሔር ጎያል አምላክ ከሆነ ሙስሊም አማኞች ለምን ይሠቃያሉ? እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ከሆነ የመሐመድ ሕይወት አደጋ ላይ የወደቀው ለምንድን ነው? የእስልምና እምነት የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ ለምን የሙስሊም ኡማ መመሥረት አልተቻለም? እነዚህና ሌሎች ጥያቄዎች በመካ የነበሩትን ሙስሊሞች ግራ ያጋቡና ጥርጣሬ ውስጥ የጣሉ ነበሩ። እነዚህ ጥያቄዎች ስለእግዚአብሔር ባሕርይና ከሰው ጋር ስላለው ግንኙነት ምርምር ውስጥ የሚከቱን ናቸው።

ምንም እንኳ ሙስሊሞች በመካ የነበራቸው ሕይወት በብዙ ችግሮችና ነገረ መለኮታዊ ግራ መጋባቶች የተሞላ ቢሆንም፣ የመሐመድ ሁለቱ ጉዞዎች (ሚዕራጅና ሒጅራ) ሙስሊሞችና መሐመድ እንዲበረታቱ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደረገ ነው።

---

[1] Badru D. Kateregga and David W. Shenk, *A Muslim and a Christian in Dialogue* (Scottdale, Pa.: Herald Press, 1997), 71-72.

ሚዕራጅ መሐመድ በአንድ ምሽት ከመካ ወደ ኢየሩሳሌም ያደረጉት ምሥጢራዊ ጉዞ ነው። ጉዞው ሁለት ደረጃዎች አሉት። አንደኛው ኢስራዕ የሚባለው ሲሆን፣ መሐመድ አል ባራቅ በምትባል ክንፍ ባላትና ፈረስ በምትመስል እንስሳ ከመካ ወደ ኢየሩሳሌም ያደረጉት ጉዞ ነው። ሁለተኛው ገጽታ ደግሞ መሐመድ ከኢየሩሳሌም ቤተ መቅደሱ ከፈረሰበት ስፍራ ወደ ሰባተኛው ሰማይ ያደረጉት ጉዞ ነው። ይህም ሚዕራጅ ተብሎ ይጠራል[2]።

የሚዕራጅ ጉዞ ኢየሳሌምና ቤተ መቅደሱ የፈረሰበት ስፍራ በእስልምና እምነት ከፍተኛ ትኩረት እንዲያገኙ አድርጓቸዋል። የፈረሰው ቤተ መቅደስ በሙስሊሞች አል-አቅሳ ተብሎ የሚጠራው ሲሆን፣ መሐመድ ከመካ ወደ ኢየሩሳሌም ባደረጉት ጉዞ ያረፉበት ቦታ ነው። ምንም እንኳ ቁርአን ስለሚዕራጅ ጉዞ ግልጽ አድርጉ ባያስተምርም የሙስሊሞቹ የትውፊት መጽሐፍ ይህ ጉዞ ለመሐመድ ትልቅ ብርታት የሰጣቸው ተአምራዊ ጉዞ እንደ ነበር ዘግቦአል (ሱራ 17+1)።

ሒጅራ የተሰኘው ሌላኛው ጉዞ በመሐመድ ሕይወትና አገልግሎት ውስጥ ከፍተኛ ተግባራዊ ገጽታ አለው። መሐመድ በመካ በብዙ መከራ ውስጥ በነበሩበት ጊዜ መልካም የምሥራች ከያትሪብ (መዲና) መጣላቸው። የመዲና ከተማ ከመካ በስተሰሜን 250 ማይል ርቀት ላይ ይገኛል። በዚያን ጊዜ በመዲና ከተማ ይኖሩ የነበሩ ሽማግሌዎች መሐመድንና ተከታዮቻቸውን ወደ መዲና እንዲመጡ ጋበዝዋቸው። በመዲና የጐሣ ክፍፍልና ጦርነት ስለነበር መሐመድ ከተማዪቱን እንዲያስተዳድሩና ሰላምን እንዲያሰፍኑ ሥልጣን ሰጧቸው።

መሐመድና በመቶዎች የሚቆጠሩት የመካ ሙስሊሞች የመዲናውያንን የስደት ጥሪ በምሥጢር ተቀብለዋል። እንደ ጐርጐሮሳውያኑ የዘመን አቆጣጠር በ622 ዓ.ም ማለትም መሐመድ በመካ መስበክ ከጀመሩበት ከ10ሥራ ሁለት ዓመት በኋላ፣ ሙስሊሞች ወደ መዲና ተሰደዱ። ስደቱ በምሥጢር ለብዙ ወራት ቀጥሎ ነበር። በዚሁ ዓመት በመስከረም 24 ቀን መሐመድ ወደ መዲና ሲደርሱ፣ በዚያ የነበሩ ሰዎች በታላቅ ደስታ ተቀበሏቸው። የመዲና ከተማ ሁከት የነገሣባት ከተማ ስለነበረች የመዲና ነዋሪዎች መሐመድ ለከተማዪቱ ሰላም ያወርዳሉ የሚል ተስፋ ነበራቸው።

[2] Abdullah Yusuf Ali, *The Holy Qur'an: Text, Translation, and Commentary* (Beirut: Dar Al Arabia, 1968), 691-93.

መሐመድ በመዲና ከነቢይነት በተጨማሪ የአገር አስተዳዳሪና የጦር መሪ ሆኑ[3]። ይህንን የፖለቲካ የበላይነት በመጠቀም መሐመድና ተከታዮቻቸው የሙስሊሙን ማኅበረሰብ መሠረቱ። ወደ ዓለም ሁሉ የተሠራጨው የሙስሊም ማኅበረሰብ መሠረቱን የጣለው በመዲና ነው።

መሐመድና ሙስሊሞች ከመካ ወደ መዲና ያደረጉት የስደት ጉዞ ሒጅራ ተብሎ ይጠራል። ይህ ክሥተት በእስልምና አዲስ ምዕራፍ ከፍቶአል። የእስልምና ዘመን የተጀመረው በመሐመድ ልደት እንደ ጐርጐሮሳውያኑ የዘመን አቆጣጠር 570 ዓ.ም ወይም ለመሐመድ የመጀመሪያው መገለጥ በሒራ ዋሻ ውስጥ እንደ ጐርጐሮሳውያኑ የዘመን አቆጣጠር በ610 ዓ.ም በመጣላቸው ጊዜ አይደለም። የእስልምና ዘመን የጀመረው በመካ፣ በችግርና በመከራ ውስጥ የነበሩት መሐመድ ወደ መዲና በመሰደድ ባለሥልጣን እንዲሁም ባለብዙ ኀይል መሆን ሲጀምሩ ነው።

ሙስሊሞች ይህ ክሥተት መሐመድ የእግዚአብሔር ነቢይ መሆናቸውን እንደሚያረጋግጥ ከሙሉ ልባቸው ይቀበላሉ። መሐመድና ሙስሊሞች በተፈጠረላቸው የፖለቲካና የጦር የበላይነት ስኬታማ መሆን ችለዋል። ሙስሊሞች ይህ ስኬት የመሐመድን ነቢይነትና የእስልምናን እውነት የሚያረጋግጥና ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ሆነ የሚያሳይ ነው የሚል አቋም አላቸው። ቁርአን ይህንን ሐሳብ ሲያብራራ፦—

> እነዚህ የካዱት ሊያስሩህ ወይም ሊገድሉህ ወይም (ከመካ) ሊያወጡህ ባንተ ላይ በመከሩብህ ጊዜ (አስታውስ)፤ ይመክራሉም አላህም ተንኮላቸውን ይመልስባቸዋል፤ አላህም ከመካሪዎቹ ሁሉ በላይ ነው (ሱራ 8+30 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)።

ይህ የቁርአን አንቀጽ አላህ ከቱዎችን ለመቅጣት መከራን እንደሚያመጣ የሚገልጽ ነው። በመዲና የነበረው ሁኔታ በመካ የነበረውን ችግርና ስደት ያካካሰ ነበር። አሁንም ሙስሊሞች ማሸነፍ አለባቸው፤ እግዚአብሔርን የሚገዙ ሰዎች አሸናፊዎች ናቸውና የሚል አስተሳሰብ አለ።

እርስ በርስ የሚቃረኑ ጉዞዎች

መሲሑ ኢየሱስና የእስልምናው ነቢይ መሐመድ በተቃራኒ አቅጣጫዎች ተጉዘዋል። ኢየሱስ ከብዙ ሰራዊት ጋር ንጉሥ እንዲሆን ሲጠየቅ ጥሪውን ወደ

[3] W. Montgomery Watt, *Muhammad: Prophet and Statesman* (New York: Oxford University Press, 1961), 82-228.

ጌን በመተው በመስቀል ላይ ለመሞት ፊቱን ወደ ኢየሩሳሌም አቀና። ነገር ግን መሐመድ ከመዲና መሪ እንዲሆኑ ለመጣላቸው ጥሪ አዎንታዊ ምላሽ በመስጠት በመካ የነበረውን አገልግሎት በመተው ወደ መዲና ተጓዙ። እነዚህ የኢየሱስና የመሐመድ የተለያዩ የሕይወት ጉዞዎች ለሙስሊሙ ማኅበረሰብና ለቤተ ክርስቲያን ሥነ ምግባራዊ ሕይወት መሠረቶች ናቸው። የክርስቲያን ሥነ ምግባር የመስቀሉን መንገድ መከተል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቲያኖች ክርስቶስ በመስቀል ላይ በመሞት ያሳየውን የሕይወት ጉዞ እንዲከተሉ ጥሪ ያደርጋል፦—

> የተጠራችሁ ለዚህ ነውና ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ስለ እናንተ መከራን ተቀብሎአልና። እርሱም ኀጢአት አላደረገም ነገር ግን በጽድት ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ (1ጴጥሮስ 2÷21-23)።

የሒጅራ ጉዞና እንዲሁም ከዚያ በኋላ የነበረው የመዲና ሁኔታ፣ ሙስሊሞች ስለ ሥነ ምግባር ያላቸውን አመለካከት በእጅጉ ቀርጾታል። ቁርአን ሙስሊሞች አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ሁሉ ጠላቶቻቸውን እንዲበቀሉ ያስተምራል፦—

> እነዚያንም የሚጋደሉዋችሁን (ከሐዲዎች) በአላህ መንገድ ተጋደሉ፣ ወሰንንም አትለፉ፣ አላህ ወሰን አላፊዎችን አይወድምና። ባገኛችኋቸውም ስፍራ ሁሉ ግደሉዋቸው፣ ከአወጧችሁም ስፍራ አውጧቸው፣ መከራም ከመግደል ይበልጥ የበረታች ናት...ቢጋደሉዋችሁም ግደሉዋቸው፣ የከሐዲዎች ቅጣት እንደዚህ ነው...እውከት እስከማይገኝና ሃይማኖት ለአላህ ብቻ እስከሚኾን ድረስ ተጋደሉዋቸው፣ ቢከለከሉም ወሰንን ግለፍ በበዳዮች ላይ እንጂ የለም (ወሰን አትለፉባቸው) (ሱራ 2÷190-193 በቅንፍ ያለውን ይጨምራል)።

የእግዚአብሔር ልዕልናና ጎይል በእነዚህ ሁለት ጉዞዎች ውስጥ ትልቅ ስፍራ አላቸው። በወንጌላት መሲሑ የመከራንና የድካምን መንገድ እንደ መረጠ እናነባለን። እርሱ አምላክ ነው፣ ነገር ግን ወደ ምድር መምጣትን መረጠ። የሰውንም ሥጋ ለበሰ፣ ራሱን አዋረደ። የባሪያን መልክ ያዘ። እርሱ በመስቀል ላይ እንኳ ለመሞት የታዘዘ ሆነ። "በዚህ ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው፣ ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው፣ ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው" (ፊልጵስዩስ 2÷9-11)።

በእስልምና እምነት መሐመድ በሒጅራ ጉዞ ያገኙት ስኬት፣ በምድር ላይ የእግዚአብሔር አስተዳደር ባለበት ሁሉ ድል አለ ለሚለው የሙስሊም ኡማ አስተሳሰብ መሠረት ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ በምድር ሁሉ ላይ እንዲሰፍን የፖለቲካና የጎንይል የበላይነት አስፈላጊ ነው። ስደትና መከራ ለእግዚአብሔር ፈቃድ ለሚገዙ የተገባ አይደለም። ከዚህም የተነሣ ሙስሊሞች የመስቀልን ታሪክ ይቃወማሉ፣ መሲሑ በመስቀል ላይ ሊሞት ከቶ አይችልም ይላሉ።

ስለ መሲሑ የሙስሊሞች ሙግት

በመዲና የነበሩ አይሁዶች መሲሑ በመስቀል ላይ እንደሚሞት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደ ተጻፈ ይናገሩ ነበር። ከዚህም የተነሣ ነብር ኢየሱስ መሲሕ ነው የሚለውን እውነታ የተቃወሙት። አይሁዶች መሲሑ በመስቀል ሊሞት አይችልም የሚለውን አቋም መሠረት ስለሚያደርጉ፣ ኢየሱስ መሲሕ ነው የሚለውን የሙስሊሞችን እምነት ይቃወሙ ነበር። አይሁዶች ኢየሱስ በፍጹም መሲሕ ሊሆን አይችልም ሲሉ ተከራክረዋል፣ ምክንያቱም ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሞቶአልና።

ከዚህ ምሰራፍ በፊት ሙስሊሞች ስለክርስቶስ ሞት ያላቸውን ተቃውሞ ተናግረን ነበር (ሱራ 4÷157)። ይህ የቁርአን ዐውድ በነቢዩ መሐመድ የተነገረው፣ በመዲና የሚኖሩ አይሁዶች ከሙስሊሞች ጋር ግጭት ውስጥ በነበሩበት ወቅት ነው። መሐመድ ኢየሱስ መሲሕ ነው ነገር ግን በመስቀል ላይ ተሰቅሎ አልሞተም ሲሉ አይሁዶችን ተቃወሙ።

እግዚአብሔር ሉዓላዊ እንዲሁም ሁሉን ቻይ አምላክ ነው። ይህ በሆነበት ሁኔታ እግዚአብሔር መሲሑን ለመከራ አሳልፎ ሊሰጠው በጭራሽ አይችልም። እግዚአብሔር መሐመድን በመካ ከነበረው መከራ እንዳስመለጣቸው ሁሉ ኢየሱስንም በመስቀል ላይ ሊደርስበት ከነበረው መከራ አስመልጠታል። እግዚአብሔር ግራ መጋባትን በአይሁዶች ላይ ላከ፣ በኢየሱስም ፈንታ ሌላ ሰው ተሰቀለ፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ኢየሱስን ተአምራዊ በሆነ መንገድ ከሞት አስመልጠታል። ኢየሱስ ወደ ፊት ሰዎችን ለመጨረሻው ፍርድ ለማዘጋጀት ዳግም ወደዚህ ምድር ተመልሶ ይመጣል። እግዚአብሔር መሲሑ በመስቀል ተሰቅሎ እንዳይሞት ትድግናውን አሳይቶአል።

የሙስሊሙ ኡማ ኢየሱስ መሲሕ እንደ ሆነ ለማስረገጥ የክርስቶስን ሞት አጥብቆ ተቃውሞአል። ይሁን እንጂ ኡማው ኢየሱስ መሲሕ መሆኑን ለማስረገጥ የተሄደበት መንገድ እግዚአብሔር በወንጌሉ ያስቀመጠውን እውነት

ያገናዘበ አለመሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ የወንጌሉን እውነትና የተገለጠውን ተአምር ጸብ ልበስ እንዲል አድርጎታል። አሳዛኙ እውነት ኢየሱስ በመስቀል ላይ አልሞተም የሚለው ይህ አስተሳሰብ በሙስሊሞች ዘንድ ሁሉ ተቀባይነት ማግኘቱ ነው።

የመስቀሉ መሰናክልነት

አንድ ቀን የሙስሊም ነገረ መለኮት ምሁር ለሆነ ሰው እንዲህ ስል ተናገርሁ፦— "በእኔ ግንዛቤ፣ ስለ ኢየሱስ ስቅለት፣ ሞትና ትንሣኤ የሚያስተምሩ የቁርአን ጥቅሶች ግልጽነት የሚጐድላቸው እንዲያውም እርስ በርሳቸው የሚጣረሱ ይመስለኛል። ሁኔኛ የሆነ ምርመራና ጥናት ሙስሊሞች የክርስቶስን ስቅለት ከግምት ውስጥ እንዲያስገቡ በሮችን ሊከፍትላቸው አይችልምን?" እርሱም ሲመልስልኝ፦— "ጥሩ ዐይነት ዕይታ ነው ያለህ። የቁርአንን ጥቅሶች በተመለከተ አንተ ያልኸው እውነት ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ስለክርስቶስ ሞት የእኛ የሙስሊሞች ተቃውሞ በአንድ ወይም በሁለት ጥቅሶች ላይ የተመሰነ ብቻ ሳይሆን፣ ከእስልምና ነገረ መለኮት ጋር የተያያዘ ነው። እግዚአብሔር መከራን ሊቀበል አይችልም"።

ክርስቲያኖች ከሙስሊሞች ጋር ሲወያዩ ሙስሊሞች ስለ ክርስቶስ ስቅለትና ሞት በተደጋጋሚ ሲቃወሙ ይስተዋላል። ታሪፍ ኻሊድ የተባለው ሰው "የሙስሊሞቹ ኢየሱስ" በሚለው መጽሐፉ ስለዚህ ጉዳይ ሲጽፍ፦— "ወንጌላት ስለ ክርስቶስ ሞት ትኩረት ሲሰጡ ቁርአን ግን ስለ ኢየሱስ መከራና ሞት ከማስተማር ይልቅ ተአምራዊ በሆነው ልደቱ ላይ ትኩረት ይሰጣል" ብሎአል[4]።

በዓለማችን ምሥራቅና ምዕራብ ጫፍ ባሉ ሁለት አገሮች ላይ የተደረጉ ውይይቶች ይህንን ርእሰ ጉዳይ በበለጠ የሚያብራሩ ናቸው። የመጀመሪያው ውይይት የተደረገው እንደ ጉርጉሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር በ1980ዎቹ አጋማሽ ላይ በኒው ዮርክ ከተማ "የእግዚአብሔር ሞቱን" ተብሎ በሚጠራውና የሞቱን ቅርጽ ባለው ብሔራዊ የአብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ፣ በሙስሊሞች የነገረ መለኮት ሰዎችና በክርስትና የነገረ መለኮት ምሁራን ዘንድ በተካሄደው ውይይት ተካፋይ ነበርሁ። የውይይቱ እንግዶች የሳሙኤል ዝዊመር ኢንስቲትዩት ዳይሬክተር ቄስ ዶን ማክኩሪ እና

[4] Tarif Khalidi, *The Muslim Jesus* (Cambridge, Mass.: Harvard University Press, 2001), 14.

በዋሽንግተን ዲሲ የሚገኘው የእስልምና ማዕከል ዳይሬክተር የነበሩት ዶክተር አብድል ራውፍ ናቸው።

በውይይታችን ማጠቃለያ ላይ ዶክተር አብድል ራውፍ "በእውነቱ እናንተ መሲሑ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሞተ ብላችሁ ታምናላችሁን?" ሲሉ ታዳሚውን ጠየቁ። እኛም "እንዴታ! በመሲሑ መስቀል እግዚአብሔር ለእኛ ሲል መከራን መቀበሉን እንዲሁም ለሰው ልጆች ራሱን አሳልፎ የሰጠበትን ፍቅር ለማየት ችለናል" አልናቸው። ዶክተር አብድል ራውፍ ቀጣ በተቀላቀለበት መንፈስ፣ "ይህ እንዴት ይሆናል? መሲሑ በመስቀል ላይ ሞተ ማለት እግዚአብሔር ደካማ ነው ማለት ነው። ይህ በፍጹም ሊሆን አይችልም" አሉ።

ሁለተኛውን ውይይት ያካሄድሁት፣ በኒው ዮርክ የተደረገው ውይይት ከተካሄደ ከስድስት ወር በኋላ፣ ራቅ ወዳለው የባንግላዲሽ የገጠር መንደር በሄድሁበት ወቅት ነበር። በአንድ ምሽት ፊደል ካልቈጠሩ ዝቡራዎች ጋር ቁጭ ብለን በምንወያይበት ወቅት እንዲህ የሚል ጥያቄ ጠየቅኋቸው፦— "እኔ ክርስቲያን እንግዳችሁ እንደ መሆኔ መጠን ልትጠይቁኝ የምትፈልጉት ጥያቄ አላችሁን?" እነርሱም፣ "አዎን" አሉኝ። "ክርስቲያኖች መሲሑ በመስቀል ላይ ተሰቅሎአል ብለው እንደሚያምኑ ሰምተናል። ምን ዐይነት እንግዳ ትምህርት ነው! አንተም እንደነርሱ ታምናለህን?" አሉኝ።

እኔም "አዎን እኔም እንደ እነርሱ አምናለሁ" አልኋቸው። ዝቡራዎቹም "ይህ በፍጹም ሊሆን አይገባውም" ሲሉ መለሱልኝ። በመቀጠልም፣ "እግዚአብሔር ልዑል አምላክ ስለሆነ መሲሑ በእንዲህ ዐይነት አሳፋሪ ሁኔታ መከራን አይቀበልም" አሉ።

እነዚህ ሁለት ውይይቶች ተቃራኒ በሆኑ የዓለማችን ክፍሎች የተካሄዱ ውይይቶች ናቸው። አንደኛው ውይይት በነገረ መለኮት ሊቃውንት እንዲሁም በዶክተሮች መካከል የተደረገ ውይይት ሲሆን ሁለተኛው ባልተማሩ ዝቡራዎችና በእኔ መካከል የተደረገ ነው። ነገር ግን በሁለቱም ውይይቶች ውስጥ የምንገነዘበው ጉዳይ መስቀሉ የማሰናከያ ዐለት መሆኑን ነው።

ሰላምን መሻት

ምንም እንኳ የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ክርስቶስ በመስቀል ላይ አልሞተም የሚል አቋም ቢያራምድም፣ እንዳንድ ሙስሊሞች ግን ስለ ክርስቶስ መስቀል ለማወቅ ከፍተኛ ፍላጐት አድሮባቸዋል። መሐመድ ካሚል ሑሴይን የተባሉ ጸሓፊ፣

"የስሕተት ክተማ" በሚል ርእስ በጻፉት መጽሐፍ፣ ኢየሱስ እንዲታሰርና መከራ እንዲቀበል ምክንያት የሆነው፣ መንፈሳዊ መሪዎችና የፖለቲካ መሪዎች ስለ እርሱ በነበራቸው ጥላቻ እንደ ሆነ አብራርተዋል። ይሁን እንጂ በመጽሐፋቸው መጨረሻ ላይ፣ ኢየሱስ በተያዘ ጊዜ በነበረው ግርግርና ሰዎች በጨለማው ምክንያት ግራ እየተጋቡ ሳሉ እግዚአብሔር ኢየሱስን ከሞት አስመልጠታል ብለዋል[5]።

በጀርመን አገር ለአራት ቀናት የሺአይት ሙስሊም ከሆነች ሴት ጋር በነበረኝ ውይይት፣ ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሞቶአል የሚለውን አስተምህሮ በጥልቀት ለማወቅ ፍላጐት እንዳደረባት ነገረችኝ። ነገር ግን በመስቀል ላይ የሞተው ሰው ኢየሱስ ክርስቶስ አይደለም የሚል የጸና አቋም እንዳላት ገልጻልኛለች።

አንዳንድ የእስልምና ቡድኖች ለእምነት ሲባል መከራን መቀበል የታማኝነት ምልክት ነው ይላሉ። በምዕራብ አፍሪካ ካሉ የእስልምና እንቅስቃሴዎች ውስጥ አንዳንዶቹ ጠረኛ እንቅስቃሴን ይቃወማሉ[6]። ብዙዎቹ የሱፊ እስልምና ቡድኖች ለእምነት መከራን መቀበልንም ሆነ ሰማዕት መሆንን ይደግፋሉ። አንዳንድ የሺአ ሙስሊሞች እንደዚህ ዐይነት አመለካከት አላቸው። በሙስሊም ኡማ እምነትና ሕይወት ውስጥ መልካምነት፣ ትጎትናና የአክብሮት መንፈስ በተለያዩ አጋጣሚዎች እንደሚንፀባረቅ መዘንጋት የለብንም።

ይሁንና ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች በአዲስ ኪዳን ላለው የመስቀል ትርጓሜ የሚሰጡት ምላሽ ስለክርስቶስ ባላቸው አመለካከት ላይ ትልቅ ተጽእኖ አለው። በሶማሊያ በመምህርነት በሠራሁባቸው ጊዜያት አንዳንዴ ከሙስሊም ተማሪዎች ጋር በአቅራቢያችን በሚገኘው ሻይ ቤት አብረን ሻይ እንጠጣ ነበር። አንድ ምሽት ሰላምን መፍጠር እንዴት ይቻላል በሚለው ርእሰ ጉዳይ ላይ ተነጋገርን።

በውይይታችን መካከል አንድ ሙስሊም ተማሪ፣ "እስልምና የዓለምን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ ሃይማኖት ነው" አለኝ። በመቀጠልም "አንተ አንድ ጉንጭህን ብትመታኝ፣ ሁለተኛ እንዳትመታኝ ያንተን ጉንጭ አንተ ከመታኸኝ ምት በተሻለ ሁኔታ መምታት አለብኝ በእስልምና አስተምህሮ ሰላም የሚመጣው

[5] Muhammad Kamil Husain, *City of Wrong*, translated by Kenneth Cragg (Oxford: Oneworld Publications, 1995).

[6] Lamin Sanneh, *Piety and Power: Muslims and Christians in West Africa* (Maryknoll, N.Y.: Orbis Books, 1996), 73, 123-24.

በዚህ መንገድ ነው። ነገር ግን የመሲሑ የኢየሱስ አስተምህሮ ነባራዊውን ሁኔታን ያላገናዘበ ስለሆነ ተግባራዊ ሊሆን አይችልም። እርሱ ጠላቶቻችሁን ውደዱ ብሎ አስተምሮአል። እንዲያውም አንድ ጉንጭህን ለሚመታህ ሌላውን አዙርለት ብሎአል። ሰላምን በዚህ መልኩ ማስፈን በፍጹም አይቻልም"።

እኔም እንዲህ ስል መለስሁለት፡— "አንተ በእኔ ላይ ስላደረግኸው ክፉ ነገር አጸፋውን ብመልስ፣ አንተ ደግሞ በተመሳሳይ መንገድ በሌላ ጊዜ ጠብቀህ ትበቀለኛለህ። ስለዚህ አንዱ በቀል ሌላ በቀል እየወለደ ይቀጥላል እንጂ ሰላም አይመጣም። ኢየሱስ በመስቀል ላይ በተሰቀለ ጊዜ የበደሉትን ሰዎች ከልብ በመነጨ ፍቅር ይቅር አላቸው። እንዲህ ዐይነት አስደናቂ ይቅርታ በቀል እንዳይቀጥል ያደርጋል"።

በዚያች ምሽት ከእኔ ጋር ሻይ ሲጠጡ የነበሩ ተማሪዎች እኔ የነገርኋቸው ሰላምን የመከተል መንገድ ብዙም አልተዋጠላቸውም። ከእስልምና በፊት በዐረብያ ባህላዊ እምነት ይከተሉ የነበሩ ዐረቦች፣ "ጠላቶቹን የማይበቀል ሰው ሌሎች ሰዎች ያጠቁታል"[7] ሲሉ የተናገሩትን ንግግር በሙስሊሞቹ አስተምህሮ ውስጥ አይቼዋለሁ። በዚህ አባባልና ሙስሊሞች ሰላምን ለማምጣት በሚጠቀሙበት ዘዴ መካከል አንዳችም ልዩነት የለም።

ሶማሊያንና የሶማሊያን ሕዝብ እያጠፋ ያለውን ፍጅት ባሰብሁ ጊዜ ሁሉ፣ ከተማሪዎቹ ጋር ያደረግሁት ይህ ውይይት እፊቴ ላይ ድቅን ይላል። በሶማሊያ ጐሣዎች መካከል እየተካሄደ ያለው የእርስ በርስ በቀል ለረጅም ዓመታት ሳይቋረጥ መካሄዱ፣ አገሪቱን ባድማ ከማድረጉ ማሻገር ሕዝቡን ለስደትና ለረሀብ ዳርጎታል።

የሒጅራ ነገረ መለኮት አንዳችም ዐይነት ሽንፈትን ወይም ለጥቃት የመጋለጥን መንገድ አይከፍትም። መሐመድ ከመካ ወደ መዲና እንደ ተሰደዱት፣ በሃይማኖት ምክንያት የሚመጣ ጊዜያዊ ስደት ወይም መከራ ተገቢ እንደ ሆነ እስልምና ያስተምራል። ነገር ግን ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ማሸነፍ የግድ ይኖርበታል። መሐመድ ከመዲና ወደ መካ በድል እንደ ተመለሱ ሁሉ፣ ሙስሊሞች ሁሉ ድል ማድረግ አለባቸው። መሐመድና ተከታዮቻቸው የማታ ማታ በተቃወሙዋቸው የመካ ነዋሪዎች ላይ ድል እንደነሡ፣ በመጨረሻ የሙስሊሙ ማኅበረሰብ በጠላቶቹ ላይ ድልን ይጐናጸፋል።

[7] C. J. Lyall, *Translations of Ancient Arabian Poetry* (London: 1930), 5, in Kenneth Cragg, *Muhammed and the Christian* (Maryknoll, N. Y.: Orbis Books, 1984), 39.

በሙስሊሙ ማኅበረሰብ ውስጥ ጦርነትን የሚቃወሙና ችግሮችን በውይይት መፍታት ተገቢ እንደ ሆነ የሚያምኑ ሰዎች እንዳሉ ቀደም ብለን ተመልክተናል። ንስሓ ለሚገቡና ከሙስሊሞች ጋር የሚደረገውን ጦርነት ለማቆም ለወሰኑ ሰዎች ምሕረት ማድረግ እንደሚገባ ቁርአን ያስተምራል። ይሁን እንጂ ዋና ዋና በሚባሉት የእስልምና ሃይማኖት ክፍሎች ውስጥ፣ ከምሕረት ይልቅ ኀጢአትን የሠራ ወይም ደግሞ የሙስሊሙን ማኅበረሰብ ያጠቃ ሰው፣ ለሠራው ጥፋት ቢያንስ ተመጣጣኝ ቅጣት ሊሰጠው እንደሚገባ በአጽንዖት ተገልጸአል[8]። የሚያሳዝነው ቅጣቱ ለሌላ በቀል እንደሚያነሣሣ ያለመገንዘቡ ነው።

በመካከለኛው ምሥራቅ በእስራኤልና በፍልስጥኤም መካከል በሚደረገው የሰላም ድርድር የፍልስጥኤም ነጻ አውጪ ድርጅት (ፒ. ኤል. ኦ) በሰላም ውይይቱ ውስጥ መሳተፉ አስደናቂ ጉዳይ አይደለም። ምክንያቱም ፒ. ኤል. ኦ እስላማዊ ድርጅት ሳይሆን የተለያየ እምነትና አመለካከት ያላቸው ሰዎችን ያቀፈ እንዲሁም ሃይማኖታዊ ያልሆነ ድርጅት ነው። በውስጡ የዐረብ ክርስቲያኖች መኖራቸው እስላማዊ ድርጅት እንዳይሆን አድርጉታል። እንደ ሐማስ ያሉ እስላማዊ ድርጅቶች ግን ጠላታችን ከሚሉት ከእስራኤል መንግሥትና ክርስቲያኖችን ካቀፈው ከፒ. ኤል. ኦ ጋር ለሰላም ድርድር በክብ ጠረጴዛ ዙሪያ መቀመጥን በጭራሽ አይፈልጉም።

እንደ ጉርጉሮሳውያኑ የዘመን አቈጣጠር በ2002 ዓ.ም በአንድ ክርስቲያናዊ ኮሌጅ የተሰባሰቡ ተማሪዎች ለአንድ ሴሚስተር በእስራኤልና በዌስት ባንክ በመቆየት። ስለ እስራኤልና ፍልስጥኤም ሰላም ሦስት ስብሰባዎችን አድርገዋል። የመጀመሪያውን ስብሰባ ያደረጉት ከሐማስ መሪ ጋር ነው። የሐማሱ መሪ የጅሐድ ጦርነት በእስልምና ነገረ መለኮት ውስጥ ያለውን እንድምታ አብራርቶላቸዋል። በመቀጠልም አሁን ባለው ሁኔታ ከእስራኤል ጋር የጅሐድ ጦርነት ማድረግ አማራጭ የሌለው ጉዳይ እንደ ሆነ ተናግሮአል።

ሁለተኛ ስብሰባ ያደረጉት ከእስራኤል ሰፋሪዎች ጋር ነው። የሰፋሪዎቹ መሪ ለተማሪዎቹ፣ "እስራኤላውያን የሰፈሩት ድሮ የራሳችን በነበረው መሬት ላይ ነው። ፍልስጥኤማውያን በእስራኤል ሰፋሪዎች ላይ የሚያደርሱትን ጥቃት

[8] Kenneth Cragg, *Muhammad and the Christian* (Maryknoll, N. Y.: Orbis Books, 1984), 39-42.

መከላከል ያለብን መልሶ በማጥቃት እንጂ ሌላ ምንም አማራጭ የለውም" ሲል የሰፋሪዎቹን አቋም ገልጸአል።

የተማሪዎቹ ቡድን በሦስተኛነት ያነጋገረው በቤቶቻቸው ፍርስራሽ ላይ ተቀምጠው የነበሩትን የፍልስጥኤም ክርስቲያን ቤተሰቦችን ነው። ይህ ቤተሰብ እስራኤል አካባቢውን ባጠቃችበት ወቅት አለን የሚሉት ንብረት ሁሉ ወድሞባቸዋል። እነዚህ ክርስቲያኖች በዚህ ዐይነቱ ሁኔታ ውስጥ ሆነው፣ የኢየሱስን ሕይወት በናሙናነት በመጥቀስ፣ እርሱ ጠላቶቹን ይቅር ብሎአል፣ እኛም ቤታችንን ባፈረሱ ሰዎች ላይ ቂም አንይዝም። የክርስቶስን ፍቅር ለዐመፅ ለሚነሣሡ ሰዎች ሁሉ ለመንገር ተዘጋጅተናል ብለዋል።

ምንም እንኳ የሙስሊም ነገረ መለኮት የመስቀሉን ሥራ ቢክድም የመሲሑ ጉዞ ወደ መስቀል ነበር። በዚህም መስቀሉ እንቈቅልሽ መሆኑ ቀጥሎአል። በፊላደልፊያ በሚገኝ መስጊድ ውስጥ በአንድ ምሽት በነበረን ውይይት፣ ቡቴምፐል ዩኒቨርስቲ የዶክትሬት ዲግሪዋን የምትሠራ አንዲት ወጣት እንዲህ ስትል ጥያቄ ጠየቀችን:— "በሶማሊያ ውስጥ ያለው የእርስ በርስ ግጭት ለምን አይቆምም? ሶማሊያ ሙስሊም አገር ሆና ሳለ እንደ ዳግም መጥምቃውያን (ሜኖናይት) ያሉ ክርስቲያኖች በዚህች አገር ሰላም በማምጣቱ ሂደት ውስጥ ብዙ የሚደክሙት በምን ምክንያት ነው?" ወጣቷ ጥያቄውን የጠየቀችን እኔ ሶማሊያ ውስጥ መቆየቴን ስለምታውቅ ነው።

እኔም፣ "ለእርስ በርስ ግጭቱ መቀጠል የተለያዩ ምክንያቶች አሉ። ነገር ግን ክርስቲያኖች በሰላም ሂደቱ ውስጥ የሚጫወቱት ሚና መሲሑ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የሰቀሉትን ጠላቶቹን ይቅር እንዳለ እኛም ይቅር ማለት አለብን በሚለው እምነት ላይ የተመሠረተ ነው። በጣም የሚያሳዝነው ነገር ላለፉት በርካታ ምዕተ ዓመታት የሶማሊያ ሕዝብ ክርስቶስ በመስቀል ላይ እንደ ሞተና ጠላቶቹን ይቅር እንዳለ የሚሰብኩትን ክርስቲያኖች በሶማሊያ ኅብረተሰብ ውስጥ እንዳይኖሩ አግልሎአል። ክርስቶስ ለሰዎች የሰጠው የይቅርታ መንገድ ከዚህ ማኅበረሰብ ዐይን ተሰውሯል" አልኋት።

በዚያ ምሽት ከመስጊድ ውስጥ የሰማሁት ምላሽ፣ "ዋ! ብትጠነቀቁ ይሻላል። መሲሑ ኢየሱስ አልተሰቀለም" የሚል ነበር።

"በዚህ ምሽት በድጋሚ የክህደትን ንግግር እየሰማን ነው" አልሁ። በመቀጠልም "ሕዝብንም ሆነ እኛን በግላችን ሊፈውስ የሚችል ይቅርታ የሚያደርግ ፍቅር

በክርስቶስ መስቀል ተገልጠአል። እኛ ይህንን ፍቅር ስንቃወም እውነተኛ የሆነውን ዕርቅና ፈውስ እየተቃወምን እንደ ሆነ ልብ ልናደርግ ይገባል"።

በአንድ አጋጣሚ ኢየሱስ በመስቀል ላይ በመሞት ስለገለጠው አስደናቂ የማስታረቅ አገልግሎት ከተናገርሁ በኋላ አንዲት ሙስሊም የነገረ መለኮት ምሁር እንዲህ ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጡ፦ "እስከ ዛሬ ድረስ እኔ ቤተ ክርስቲያን የማስታረቅን አገልግሎት ስትፈጽም አላየሁም። ኢየሱስ ጠላቶቹን ከመበቀል ይልቅ ከጠላቶቹ ፊት መሸሽን መረጠ የሚለውን አነጋገርህን ስሰማ የመጀመሪያዬ ነው። እኛ ሙስሊሞች ቤተ ክርስቲያንን የምናውቃት ሁኔታዎች ፈታኝ ሲሆኑባት ወደ በቀልና ጦርነት እንደምትዞር ነው"።

እኔም በተራዬ፣ "በወንጌል ውስጥ የተገለጸውን ኢየሱስን ሳይሆን፣ በቀለኛውን ኢየሱስን የምትሰብክ ቤተ ክርስቲያን ካለች እግዚአብሔር ይቅር ይበላት። እናንተም ብትሆኑ በእግዚአብሔር ጸጋ እኛን ይቅር ማለት አለባችሁ። የእርስዎ አስተያየት እኛ ክርስቲያኖች የተቀበልነውን እምነት ያጐደፉትን ክርስቲያኖች ለንስሓ የሚጠራ ነው" ስል አስተያየቴን ሰጠሁ።

በመጨረሻም ወይዘሮዋ እኔን ካመሰገኑ በኋላ፣ በጥልቅ ስሜት ውስጥ ሆነው፣ "ስለቤተ ክርስቲያን ጎጢአት አንድ ክርስቲያን ከሙስሊሙ ይቅርታን ሲጠይቅ የሰማሁት ለመጀመሪያ ጊዜ ነው። በአንተ ንስሓ ውስጥ እኔ ከዚህ ቀደም ያላወቅሁትን የመሲሑን መልክ አይቻለሁ" አሉኝ።

እውነተኛው ጎይል

መስቀል ጎይላችን ነው። ከላይ የተመለከትናቸው ውይይቶች የሚያሳዩን የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ነን የሚሉ ክርስቲያኖች ስለጎይል ያላቸው አመለካከት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ከመሆን ይልቅ እስላማዊ መሆኑን ነው። ከተለያዩ ጓደኞቼ ጋር በመኖሪያ ቤቴ ውስጥ ያደረግናቸው ውይይቶች እውነተኛ ጎይል እንዴት ይገኛል የሚለውን መሠረታዊ ነጥብ የሚያንጸባርቁ ናቸው።

ከሰማሊያ የመጡ ሦስት ሙስሊም ጓደኞቼ ለተወሰኑ ቀናት እቤታችን ዐርፈው ነበር። እሑድ ማለዳ ቁርስ እየበላን ሳለ፣ ከሁሉም በዕድሜ ገፋ ያለው ሰው፣ "በሰማሊያ የሰላም ሂደት ውስጥ የቤተ ክርስቲያን ድርሻ ምንድን ነው?" ሲል ጠየቀኝ። በመቀጠልም፣ "አገራችን እየፈራረሰች ነው። የእናንተ የሚኖናይት

ቤተ ክርስቲያን ሰዎች የሰላም ሂደቱ በእግሩ እንዲቆም በርካታ ድጋፍ አድርጋችኋል ለዚህ ያነሣሣችሁ ምክንያት ምንድን ነው?"።

እኔም እንዲህ ስል መለስሁለት፦ "የእኛ ሰላምን የማምጣት አገልግሎት የክርስቶስ ሕይወትና አገልግሎት ነፀብራቅ ነው። ኢየሱስ ታልፎ ከመሰጠቱና ከመከራው በፊት አሳልፎ የሚሰጠውን የአስቆሮቱ ይሁዳን እግር አጠበ። በዚህም አገልግሎቱ ክፉ ሊያደርግበት ለተዘጋጀው ሰው ርኅራኄ እንዲሁም እርሱን ለማገልገል ዝግጁ መሆኑን አሳየ"።

"በተጨማሪም በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሳለ፣ ለሰቀሉት ሰዎች ይቅርታ አደረገላቸው። እንዲህ ዐይነት ፍቅር ደካማነት አይደለም። መሥዋዕት የሚያስከፍለው የእግዚአብሔር ፍቅር ከጠላቶቹ ጋር ዕርቅንና ይቅርታን የሚመሠርት ፍቅር ነው አልኋቸው"።

ይህንን እየተናገርሁ ሳለ ሙስሊሞኑ ባልንጀሮቼ፣ "ይህ በፍጹም ሊሆን አይችልም። እግዚአብሔር መሲሑን በጎይል ቀብቶታል። ጎያሉ መሰሕ ደግሞ መከራ ሊቀበል አይገባውም። ደግሞም እግዚአብሔር ሰዎችን ይህን ያህል በፍጹም ሊወድ አይችልም" አሉ። እኔም፣ "ወንድሞቼ እባካችሁ፣ የእግዚአብሔርን ማንነቱን እኛ ልንወስንለት መከራ አናድርግ" ስል ምክሬን አጋራኋቸው።

በዚህ ውይይታችን ምክንያት በዚያ ማለዳ የነበረውን የመጀመሪያውን የእሑድ የአምልኮ ፕሮግራም ሳንካፈል ቀረን። ምክንያቱም በቤታችን ውስጥ ይደረግ የነበረው ውይይት ዐቢይ ጠቀሜታ ስለነበረው ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ

ዮሐንስ 6÷1-15፤ ማቴዎስ 16÷21

የቁርአን ምንባብ

ሱራ 9÷30፤ 58÷20-22

<u>የአስተውሎትና የሙያይት ጥያቄዎች</u>

1. መሐመድና ኢየሱስ በተቃራኒ የሕይወት ጉዞዎች ውስጥ አልፈዋል ለሚለው ዐረፍተ ነገር ያልዎትን አስተያየት ይስጡ።

2. ኢየሱስ የፖለቲካም ሆነ የጦር ኀይልን መጠቀም አልፈለገም፣ ነገር ግን መሐመድ የፖለቲካም ሆነ የጦር ኀይልን መጠቀምን ወደደ (ዮሐንስ 18+36፤ ሱራ 2+190-193) የሚሉትን ዐረፍተ ነገሮች ያበራሩ።

3. የመሐመድ የሕይወት ጉዞ ሙስሊሞች ለጠላቶቻቸው ባላቸው አመለካከት ላይ ተጽእኖ የሚያደርገው እንዴት ነው? ክርስቶስ ወደ መስቀል ያደረገው ጉዞ ክርስቲያኖች ለጠላቶቻቸው ያላቸውን አመለካከት ሊቀርጽ የሚችለው እንዴት ነው?

4. ሒጅራ በእስልምና አዲስ ምዕራፍ የተጀመረበት ነው። ይህ ክሥተት ሙስሊሞች ስለራሳቸው ባላቸው አመለካከት እንዲሁም በእስልምና ነገረ መለኮት ላይ ትልቅ ለውጥ ያመጣበትን ምክንያት ይግለጹ።

5. በእግዚአብሔር ወይም በእግዚአብሔር ኀይል የተቀባ ሰው መከራ ይገጥመዋልን? በሒጅራ ጊዜ የተፈጠረው ሁኔታ ስለዚህ ጥያቄ ምን ምላሽ ይሰጣል? ለዚህ ጥያቄ ምን የእርስዎ መልስ ምንድን ነው? (ሱራ 8+30፤ ሉቃስ 23+34)።

6. ለራስዎትም ሆነ ለሌሎች ጥሩ ነው ብለው የሚያምኑትን ነገር የሚወስኑት እንዴት ነው? ይህን ለመፈጸም የሒጅራን ጉዞ ወይስ የመስቀሉን ጉዞ ይመርጣሉ?

7. ስለመስቀልና ስለ ሒጅራ ያለው ነገረ መለኮት ስለፍትሓዊ ጦርነት ምን ምላሽ ይሰጣል?

ምዕራፍ ዘጠኝ

ቅድስቲቱ ከተማ መዲና—ኢየሩሳሌም

መዲና በዐረብያ ምድር የእስልምና ኡማ የተጀመረባት ከተማ ናት። በፍልስጥኤም—እስራኤል ውስጥ የምትገኘው ኢየሩሳሌም ደግሞ ቤተ ክርስቲያን መጀመሪያ የተቈረቈረባት ከተማ ናች። በእነዚህ ሁለት የታሪክ ወቅቶች ቤተ ክርስቲያንና የሙስሊሙ ኡማ አብረው ነበሩ። በዚህ ምዕራፍ የሙስሊሙ ኡማ በመዲና የመፈጠሩን ሁኔታና ቤተ ክርስቲያን በኢየሩሳሌም የመጀመሯን ጉዳይ እንመለከታለን።

ቤተ ክርስቲያን—የሙስሊሙ ኡማ

የሙስሊማኑና የክርስቲያኑ እንቅስቃሴዎች ከእመሁ አልቦ የተጀመሩ (ከባዶ ነገር ውስጥ የበቀሉ) አይደሉም። ከቤተ ክርስቲያንና ከሙስሊም ኡማ ብዙ መቶ ዓመታት አስቀድሞ፣ እግዚአብሔር እስራኤል ለሕዝብ ሁሉ ብርሃን እንድትሆን እንደ መረጣት ክርስቲያኖችም ሆኑ ሙስሊሞች ያምናሉ። እግዚአብሔር እስራኤል የቃል ኪዳን ሕዝብና በአሕዛብ መካከል ምስክር እንድትሆን መረጣት። ቤተ ክርስቲያንም ሆነች የሙስሊሙ ኡማ ከጅማሬያቸው እግዚአብሔር ለእስራኤል ያደረገው ጥሪ ፍጻሜና የእስራኤልን ተልእኮ የማስፋፋት ሥራ እንደሚሠሩ ያምኑ ነበር። (ምዕራፍ አራትን ይመልከቱ)።

የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት የተጻፉት ቤተ ክርስቲያን እንደ ተመሠረተች ነበር። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉት አማኞች ኢየሱስ መሲሕ፣ ጌታና አዳኝ እንደ ሆነ ይመሰክሩ ነበር። ከአይሁድ ወገን ያልሆኑት አሕዛብ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይቀላቀሉ ነበር። ይህም ቤተ ክርስቲያን የተለያየ ዐይነት ሕዝብ ያለባት የጎበረተሰብ ክፍል እንድትሆን አስቻላት። ይህ ጉዳይ እግዚአብሔር ለአብርሃም፣ "አሕዛብ ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ" ያለው የተስፋ ቃል ፍጻሜ እንደ ሆነ ቤተ ክርስቲያን ታምናለች።

ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አለ፦—

ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኀይልን ትቀበላላችሁ፣ በኢየሩሳሌም፣ በይሁዳና በሰማርያ ሁሉ፣ እስከ ምድር ጻርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ (ሐዋርያት ሥራ 1÷8)።

ቁርአን የተጻፈው የመጀመሪያው የሙስሊም ኡማ ሲቋቋም ነበር። ሙስሊሞች የሙስሊሙ ኡማ ከእስራኤልና ከቤተ ክርስቲያን የሚልቅ እንዲሁም ዓለም ዐቀፋዊ እንደ ሆነ ያምናሉ። የእስራኤል አገልግሎት ለተወሰነ ጊዜ የሚቆይ፣ የሙስሊሙ ኡማ ግን ይህንን አገልግሎት ወደ ዓለም ሁሉ የሚያደርስ እንደ ሆነ ይታመናል። ቤተ ክርስቲያን በተለያዩ አስተምህሮአዊ ጥያቄዎች ስለተከፋፈለች የሙስሊሙ ኡማ ተልእኮ ለእነዚህ ጥያቄዎች መፍትሔን መስጠት እንደ ሆነ ሙስሊሞች ያምናሉ።

ቁርአን በሱራ 14÷1 ላይ፣ "አ.ለ.ረ (አሊፍ ላም ራ፣ ይህ ቁርአን)፣ ሰዎችን በጌታቸው ፈቃድ ከጨለማዎች ወደ ብርሃን አሸናፊ ምስጉን ወደ ኾነው ጌታ መንገድ ታወጣ ዘንድ ወዳንተ ያወረድነው መጽሐፍ ነው" ይላል።

ቤተ ክርስቲያንም ሆነች የሙስሊሙ ኡማ አብርሃም የእምነት አባታቸው እንደ ሆነ ያስተምራሉ። እነዚህ የእምነት ክፍሎች እግዚአብሔር ለአብርሃም፣ "አሕዛብ ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ" ካለው ቃል ጋር አብሮ የሚሄድ ተልእኮ እንዳላቸው ያምናሉ። የቤተ ክርስቲያን ተልእኮ፣ እግዚአብሔር ለእስራኤል፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወደ ዓለሙ ሁሉ ታስፋፊያለሽ ሲል የሰጣትን የተሰፋ ቃል ፍጻሜ ላይ ማድረስ ነው። የሙስሊም ኡማ ደግሞ ከእስራኤልና ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የተሻለ አገልግሎት እንዳለው ያምናል። ስለዚህ በእነዚህ ሁለት የእምነት ቡድኖች መካከል ለዘመናት የቆየ ውጥረት መኖሩ አያስደንቅም።

ይህ ምዕራፍ በኢየሩሳሌም፣ ስለ ተካሄደው የቤተ ክርስቲያን ምሥረታ እንዲሁም በመዲና ደግሞ የሙስሊም ኡማ እንዴት እንደ ተጀመረ ማብራሪያ ይሰጣል። የቤተ ክርስቲያን ምሥረታ ከሙስሊም ኡማ ስለሚቀድም፣ በቀዳሚነት ስለቤተ ክርስቲያን አጀማመር ከተመለከትን በኋላ፣ ስለኡማ ደግሞ በቀጣይነት እንመለከታለን።

ቤተ ክርስቲያን በኢየሩሳሌም ተመሠረተች

ኢየሱስ ከሦስት ዓመት አገልግሎቱ በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም አቀና። በዚያን ጊዜ ከተማዋ በከፍተኛ ቀውስ ውስጥ ነበረች። ኢየሱስ ከኢየሩሳሌም በስተ ምሥራቅ ከሚገኘው የደብረ ዘይት ተራራ ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ የገባው በአማረ አጀብና እልልታ እንዲሁም በታላቅ ሆታና ፍሥሓ ነበር።

ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ገባ

ኢየሱስ በአህያ ውርንጫ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ፣ ዙሪያውን ከበውት የነበሩ ሰዎች፦—

> ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ፣
> በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው፣
> ሆሣዕና በአርያም እያሉ ይጮኹ ነበር (ማቴዎስ 21÷9)።

የአይሁድ ባለሥልጣናት በዚህ ዐይነቱ ሁኔታ ክፉኛ ተቆጡ። ኢየሱስ ውርንጫ በሆነች አህያ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም በመግባቱ፣ እነርሱ አጥብቀው የሚቃወሙትን ነገር ስለ ራሱ እያወጀ መሆኑን ተረድተዋል። ኢየሱስ በአህያ ላይ ተቀምጦ እንደሚመጣ ስለመሲሑ በነቢዩ በዘካሪያስ የተነገረ ትንቢት ነው። ይህ ድርጊት ከመከሠቱ ከአምስት መቶ ዓመት በፊት፣ ነቢዩ ዘካርያስ ስለመሲሑ እንዲህ ሲል ጽፎአል፦—

> አንቺ የጽዮን ልጅ ሆይ፣ እጅግ ደስ ይበልሽ፣ አንቺ የኢየሩሳሌም ልጅ ሆይ እልል በዪ፣ እነሆ ንጉሥሽ ጻድቅና አዳኝ ነው፣ ትሑትም ሆኖ በአህያም፣ በአህያዪቱ ግልገል በውርንጫዪቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል። ሠረገላውንም ከኤፍሬም ፈረሱንም ከኢየሩሳሌም አጠፋለሁ፣ የሰልፉንም ቀስት ይሰብራል፣ ለአሕዛብም ሰላምን ይናገራል፣ ግዛቱም ከባሀር እስከ ባህር፣ ከወንዙም እስከ ምድር ጻርቻ ድረስ ይሆናል (ዘካርያስ 9÷9-10)።

ኢየሱስ በአህያ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም በመግባት፣ መሲሕ እንደ ሆነ እንዲሁም ለዓለም ሁሉ የሚሆን የሰላም መንግሥት ጅማሬ መሆኑን አብሥሮአል። ይሁንና የአይሁድ መሪዎች በኢየሱስ ድርጊት ክፉኛ ተብሳጩ። ለዚህ ዐቢይ ምክንያት ኢየሱስ እነርሱ የጠበቁት ዐይነት ንጉሥና መሲሕ ስላልነበረ ነው።

እነርሱ የሚጠብቁት ንጉሥ ወደ ኢየሩሳሌም የሚገባው በኑጭ ፈረስ ላይ ተቀምጦ፣ ጋሻና ጦር በታጠቁ በብዙ መቶ የሚቈጠሩ ሰዎች ታጅቦ ነው። ይህ ንጉሥ ጣዖት አምላኪ የሆነውን የሮማን መንግሥት ገልብጦ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት በከተማዪቱ፣ ከተማዪቱ በምትገኝባቸው አካባቢዎች እንዲያውም በዓለም ሁሉ እንደሚመሠርት ይታመን ነበር።

በሕዝቡ ጩኸት ታጅቦ በውርንጫ አህያ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም የገባው ኢየሱስ፣ በከተማዪቱ ላይ ንጉሥ መሆን አልቻለም። ፈሪሳውያን የሚጮኸውን ሕዝብ ኢየሱስ እንዲገሥጻቸው ቢጠይቁትም ኢየሱስ ሕዝቡን

አልገሠጸም። እንዲያውም በተቃራኒው፣ "እነርሱ ዝም ቢሉ፣ ድንጋዮች ይጮኻሉ አላቸው" (ሉቃስ 19+40)።

የእንግሊዝ የነገረ መለኮት ምሁር ኤን. ቲ. ራይት ኢየሱስ በአህያ ላይ ተቀምጦ መምጣቱ እርሱ ከምሥራት በኩል ወደ ኢየሩሳሌም የሚገባ የእግዚአብሔር ክብር እንደ ሆነ መግለጽ ነው ሲል ያስተምራል[1]። ይህ ዐይነት መረዳት በትንቢተ ሕዝቅኤል ውስጥ ከሰፈረው ትንቢት ጋር የሚጣጣም ነው። ነቢዩ ሕዝቅኤል በአህያ ላይ ስለሚቀመጠው ንጉሥ ሲጽፍ የእግዚአብሔር ክብር ወደ እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ከምሥራቅ በኩል እየመጣ እንደ ሆነ ጽፎአል፦—

> እነሆም የእስራኤል አምላክ ክብር ከምሥራቅ መንገድ መጣ፤ ድምፁም እንደ ብዙ ውሆች ይተምም ነበር፣ ከክብሩም የተነሣ ምድር ታብራ ነበር... የእግዚአብሔርም ክብር ወደ ምሥራቅ በሚመለከት በር ወደ ቤተ መቅደሱ ገባ...በመቅደሱም ሆኖ የሚነግረኝን ሰማሁ በአጠገቤም ሰው ቆሞ ነበር። እንዲህም አለኝ፦— የሰው ልጅ ሆይ በእስራኤል ልጆች መካከል ለዘላለም የምቀመጥበት የዙፋኔ ስፍራና የእግሬ ጫማ መረገጫ ይህ ነው። ዳግመኛም የእስራኤል ቤትና ነገሥታቶቻቸው በግልሙትናቸው በከፍታቸው ባለው በነገሥታቶቻቸው ሬሳ ቅዱስ ስሜን አያረክሱም (ሕዝቅኤል 43+2:4:6-7)

ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም በአህያ ላይ ተቀምጦ ሲገባ፣ የእርሱ ወደ ኢየሩሳሌም መግባት የነቢዩ ዘካሪያስ ትንቢት ብቻ ሳይሆን የነቢዩ ሕዝቅኤል ትንቢትም ፍጻሜ እንደ ሆነ ማወጁ ነበር። መሲሑ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም በአህያ ላይ ተቀምጦ መግባቱ፣ በእርሱ ማንነት አማካይነት የእግዚአብሔር የክብሩ ነጸብራቅ ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱንና ለዓለም ሁሉ የሚደርስ የጽድቅ፣ የፍትሕና የሰላም መንግሥት መጀመሩን ያመለክታል።

ኢየሱስ ቤተ መቅደሱን አነጻ

ነቢዩ ሕዝቅኤል እንደ ተነበየው፣ የእግዚአብሔር ክብር በሙላት የተገለጠበት ኢየሱስ ወደ ቤተ መቅደሱ ገባ። ነገር ግን ቤተ መቅደሱ በነጋዴዎች ተጨናንቆ ነበር። ነጋዴዎቹም መሥዋዕት ለሚያቀርቡ ሰዎች እንስሳትና ምግብ በመሸጥ ላይ ነበሩ። ኢየሱስ ይህን ባየ ጊዜ የገንዘብ ለዋጮችን ጠረጴዛዎች ገለበጠባቸው፣ ለሽያጭ የቀረቡትንም እንስሳት ከቤተ መቅደሱ አስወጣቸው። እርሱም የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ለሕዝብ ሁሉ የጸሎት

[1] N. T. Wright, *The Challenge of Jesus: Redisscovering Who Jesus Was and Is* (Downers Grove, Ill.: InterVarsity, 1999), 123.

ቤት ይሆናል እንጂ፣ የዘራፊዎች ዋሻ አይሆንም አለ (ማቴዎስ 21+13)። የቤተ መቅደሱ ባለሥልጣናት ኢየሱስን በምን ሥልጣን ነው ይህን ሁሉ የምታደርገው ሲሉ ጠየቁት። ኢየሱስም፣ "ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት፣ እኔም በሦስት ቀን መልሼ አነሣዋለሁ" ብሎ መለሰላቸው (ዮሐንስ 2+19)።

ኢየሱስ ይህን የተናገረው ከሞተ ከሦስት ቀን በኋላ ከመቃብር እንደሚነሣ ማመልከቱ ነበር። ይህ እንዳለ ሆኖ ይህ ከሥተት ሌላ ተጨማሪም መልእክት የያዘ ነው። ኢየሱስ ይህን ሲል በድንጋይ የተሠራው ቤተ መቅደስ ከዚህ በኋላ አስፈላጊ አይደለም ማለቱ ነው። የእግዚአብሔር ክብርና የመለኮት ሁሉ ሙላት በመሲሑ በኢየሱስ በኩል ተገልጠአልና ነው[2]። የቤተ መቅደስ ባለሥልጣናት ኢየሱስ በድፍረት እኔ በአካል ስለመጣሁ በድንጋይና በእንጨት የተሠራው ቤተ መቅደስ አያስፈልግም ማለቱ እንደ ሆነ ተረድተዋል።

ኢየሱስ የተናገረው የቤተ መቅደሱን አላስፈላጊነት ብቻ ሳይሆን፣ የኢየሩሳሌምን መፍረስም ጭምር ነው። ኢየሱስ በአህያ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ፣ ስለ ኢየሩሳሌም አለቀሰ። ምክንያቱም ኢየሩሳሌም የታነጸችው የሰላም ከተማ እንድትሆን ቢሆንም፣ ኢየሱስ ኢየሩሳሌም ለሰላሟ የሚሆናትን ንጉሥ ባለ መቀበልዋ እንዲሁም ወደ ፊት በእርስዋ ላይ ስለሚደርሰው ከፍተኛ መከራና ጥፋት ከሩት ተመልክቶ አለቀሰ። እውነታው አሐዱ ተብሎ በኢየሱስ የተጀመረው የእግዚአብሔር መንግሥት፣ ቤተ መቅደስም ሆነ ኢየሩሳሌም አያስፈልገውም።

ኢየሱስ ተሰቀለ

የቤተ መቅደስ መሪዎች ቀኑን በፍጹም በቀላሉ ሊበርድ አልቻለም። ባለፈው ምዕራፍ ላይ እንደ ተመለከትነው፣ ኢየሱስን ይዘው አሰሩት፣ ከዚያም በኋላ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ እንዲሞት ፈረዱበት። ቅጣቱን ለማክበድ በኢየሱስ ላይ የተለያዩ ዐይነት ከሶችን አቀረቡ፣ በዋነኛ የቅጣት ማክበጃነት የቀረበው ነጥብ ስለቤተ መቅደስ የተናገረው ንግግር ነበር። ሌላኛው ክስ ደግሞ እኔ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ የሚለው አነጋገሩ ነው።
ከዚህ በፊት በነበረው ምዕራፍ እንደ ተመለከትነው ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሲሰቀል፣ ደቀ መዛሙርቱ ከፍተኛ ሐዘንና ፍርሐት ስለወደቀባቸው በተለያየ አቅጣጫ ተበታተኑ። ሆኖም ከሦስት ቀን በኋላ፣ ከሳምንቱ በመጀመሪያ ቀን ወደ መቃብሩ የሄዱ ሴቶች መቃብሩ ባዶ እንደ ሆነ አዩ። ይህም ኢየሱስ ከሞት የመነሣቱ እውነታ ነበር። ደቀ መዛሙርቱም በዚህ ድርጊት እጅግ

[2] ዝኒ ከማሁ፣ 110።

በጣም ተገረሙ። ከዚያ በኋላ ባሉት አርባ ቀናት ውስጥ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ከዐሥራ አንድ ጊዜ በላይ ታይቶአቸዋል።

ኢየሱስ ትእዛዝ ሰጠ

ኢየሱስ ለመጀመሪያ ጊዜ ለደቀ መዛሙርቱ የታያቸው የተቸነከሩትን እጆቹን እግሮቹንና ጐኑን እያሳየ ነበር። ከዚያም በኋላ ባርከአቸው። "ሰላም ለእናንተ ይሁን፤ አብ እኔን እንደ ላከኝ፣ እኔም እናንተን እልካችኋለሁ" አላቸው። (ዮሐንስ 20÷21)።

ደቀ መዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስን እስኪቀበሉ ድረስ በኢየሩሳሌም እንዲቆዩ አዘዛቸው። ከዚያ በኋላ መቶ ሃያ የሚሆኑ ደቀ መዛሙርት ለዐሥር ቀን በጸምና በጸሎት ሆነው የመንፈስ ቅዱስን ምጽአት ይጠብቁ ነበር። በዚህ ዐይነቱ ሁኔታ ላይ እያሉ፣ በበዓለ ኀምሳ (በጴንጠቈስጤ) ቀን መንፈስ ቅዱስ በእያንዳንዳቸው ላይ ወረደባቸው።

ቤተ ክርስቲያን ተመሠረተች

በአይሁድ ሥርዐት የጴንጠቈስጤ በዓል የአዝመራውን የበኵር ምርት በሚሰበስቡበት ጊዜ የሚከበር በዓል ነው። በዚያች ቀን በኢየሩሳሌም ይህ በዓል ልዩ ትርጉም ነበረው። ምክንያቱም የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የሆነችው የመጀመሪያዪቱ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችበት ቀን ነው። መንፈስ ቅዱስ እንደሚነጥት ኀይለኛ ዐውሎ ነፋስ በደቀ መዛሙርቱ ላይ ወረደ። በእያንዳንዱም ላይ የተከፋፈሉ የእሳት ልሳኖች ዐረፈባቸው። በተለያዩ ልሳኖችም እግዚአብሔርን አመሰገኑ።

በዚያ ቀን ከመካከለኛው ምሥራቅና ከሰሜን አፍሪካ የመጡ በኢየሩሳሌም የነበሩ ሰዎች እየሆነ ያለውን ነገር ለማየት ደቀ መዛሙርቱ ወዳሉበት ቦታ ተሰበሰቡ። የወንጌልን እውነትና ቤተ ክርስቲያን በተአምራዊ መንገድ መቈርቈሯን እንዲሁም ወንጌልን በራሳቸው ቋንቋ በመስማታቸው እጅግ በጣም ተገረሙ።

ጴጥሮስም በጉባኤው መካከል ቆሞ የመጀመሪያውን ስብከተ ወንጌል ለተሰበሰቡት ሰዎች አበሠረ። የወንጌልን እውነት በተመለከተ ጴጥሮስ የሰበከው ስብከት በሐዋርያት ሥራ 2÷22-24:36 ላይ ይገኛል፦—

> የእስራኤል ሰዎች ሆይ ይህን ቃል ስሙ፤ ራሳችሁ እንደምታውቁ የናዝሬቱ ኢየሱስ እግዚአብሔር በመካከላችሁ በእርሱ በኩል ባደረገው ተአምራትና

> በድንቆች በምልክቶችም ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእናንተ የተገለጠ ሰው ነበረ። እርሱንም በእግዚአብሔር በተወሰነው አሳቡና በቀደመው ዕውቀቱ ተሰጥቶ በዐመፀኞች እጅ ሰቅላችሁ ገደላችሁት። እግዚአብሔር ግን የሞትን ጣር አጥፍቶ አስነሣው ሞት ይይዘው ዘንድ አልቻለምና...እንግዲህ ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን እግዚአብሔር ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገው የእስራኤል ወገን ሁሉ በእርግጥ ይወቅ።

ይህን በሰሙ ጊዜ በዚያ የነበሩ ሰዎች "እንግዲህ ምን እናድርግ?" አሉ። ጴጥሮስም "ንስሓ ግቡ፦— ኀጢአታችሁም ይሠረይ ዘንድ፣ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፣ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ" (ሐዋርያት ሥራ 2÷37-38) አላቸው። በሺህ የሚቈጠሩት እነዚህ ሰዎች የወንጌልን መልእክት በሰሙ ጊዜ፣ መንፈስ ቅዱስ ስለ ኀጢአትና ስለ እውነት ወቀሳቸው። ሦስት ሺህ የሚሆኑ ሰዎች ስለ ኀጢአታቸው ንስሓ ገቡ፣ መሲሑ ኢየሱስ ጌታና አዳኝ እንደ ሆነም አመኑ። ሐዋርያትም ያመኑትን ሁሉ አጠመቁ። ያመኑትም በታላቅ ደስታና ፍሥሓ ተሞሉ። ሁሉም፣ ያላቸውን ነገር ሁሉ ለሌለው ያካፍሉ ነበር እንጂ፣ በመካከላቸው ድኻ አልነበረም። "በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ በቤታቸው እንጀራ እየቈረሱ በደስታና በጥሩ ልብ ምግባቸውን ይመገቡ ነበር፤ እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ በሕዝብ ሁሉ ፊት ሞገስ ነበራቸው። ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር" (ሐዋርያት ሥራ 2÷46-47)።

ቤተ ክርስቲያን ተሰደደች

በሐዋርያት እጅ ተአምራቶች ቢፈጸሙና ብዙ ሰዎች ቢያምኑም እንኳ ወዲያውኑ በቤተ ክርስቲያን ላይ ስደት ተነሣ። ክርስቶስ መከራን እንደ ተቀበለው ሁሉ፤ ቤተ ክርስቲያንም እንዲሁ ተሰደደች። ቤተ ክርስቲያን በተመሠረተች በሳምንታቶች በሚቈጠር ጊዜ ውስጥ ንጉሥ ሔሮድስ ሐዋርያው ያዕቆብ ዐንገቱ ተቀልቶ እንዲሞት አስደረገ። ቀጥሎም ዲያቆን የነበረው እስጢፋኖስ በድንጋይ ተወግሮ ሞተ። ሐዋርያው ዮሐንስና ጴጥሮስ ተይዘው ከተደበደቡ በኋላ፣ ወኅኒ ተወረወሩ። ይህ ሁሉ የሆነው ቤተ ክርስቲያን በኢየሩሳሌም ማደግ በጀመረችበት ጊዜ ነው። በማደግ ላይ የነበረችው ቤተ ክርስቲያን የፖለቲካ ወይም የጦር ኀይል አልነበራትም፤ ይልቁንም በባለሥልጣናት ክፉኛ ትሰደድ ነበር።

በኢየሩሳሌም የተቀሰቀሰው ስደት ከርስቲያኖች ወደ ተለያዩ ቦታዎች እንዲበተኑ አደረጋቸው። አማኞች ወደ ተለያዩ ቦታዎች ቢበተኑም በተበተኑባቸው ስፍራዎች ሁሉ የምሥራቹን ወንጌል ይዘው ሄዱ። አማኞች

በሄዱባቸው ቦታዎች ሁሉ አዳዲስ የሆኑ ቤተ ክርስቲያናት ተቈረቈሩ። ቤተ ክርስቲያን ይህ ሁሉ የሆነው መንፈስ ቅዱስ ከሚሠራው ሥራ የተነሣ እንደ ሆነ ከሙሉ ልብ ትተበባለች።

ቤተ ክርስቲያን የአግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ናት

የቤተ ክርስቲያን ግዕከል ኢየሩሳሌም ነው የሚለው አስተሳሰብ ቀስ በቀስ እየደበዘዘ መጣ። ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተች ከአንድ ትውልድ በኋላ ግለትም በሰባ ዓመተ ምሕረት የሮም ባለ ሥልጣናት በኢየሩሳሌም የነበረውን ቤተ መቅደስ አፈረሱ። ኢየሩሳሌምም በሮም ቀጥተር ሥር ወደቀች፣ ሌሎች ከተሞችም ፈራረሱ። በመሠረቱ ኢየሩሳሌምም ሆነች ቤተ መቅደሱ፣ የክርስትና ግዕከል አልነበሩም። ግንኛውም ክርስቲያኖች በመሲሑ በክርስቶስ ስም የሚሰበሰቡበት ቦታ ሁሉ የክርስትና ግዕከል ነው። ክርስቲያኖችም በታላቅ መደነቅና በከፍተኛ ሐሴት፣ "እኛ የሕያው እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነንና ይላሉ" (2ቆሮንቶስ 6÷16)።

ቤተ ክርስቲያን ተበተነች ተስፋፋችም

ክርስቲያኖች ከኢየሩሳሌም ከተማ ወደ ተለያዩ ቦታዎች ቢበተኑም፣ መከራን ግን ግምለጥ አልቻሉም። በመጀመሪያዎቹ ሦስት ምዕተ ዓመታት ቤተ ክርስቲያን አንዳችም ዐቅም ስላልነበራት በእጅጉ ትሰደድ ነበር። ይሁንና ቤተ ክርስቲያን ከተጀመረች በኋላ ባሉት ሁለት መቶ ዓመታት ውስጥ፣ በግብፅ ይኖር የነበረው አርጌንስ (Origen) እንዲህ ሲል ጽፎአል:— "ክርስቶስ ወደዚህ ምድር በመምጣቱ ምክንያት የእንግሊዝ ሕዝብ በአንድ አምላክ አምኖአል። በአፍሪካ የሚገኙት የሙር ሕዝቦችም የወንጌልን እውነት ተቀብለዋል። ወንጌል ወደ ዓለም ሁሉ ደርሶአል። ቤተ ክርስቲያናት አሁን በዓለም ዋና ዋና በሚባሉ ስፍራዎች ሁሉ ተተክለዋል፤ ምድር ሁሉ በደስታ እልል ትበል"[3]።
ምንም እንኳ ቤተ ክርስቲያን የፖለቲካ ኀይል ባይኖራትም፣ ትንሽ እርሾ ብዙውን ሊጥ እንደሚያቦካው፣ ወንጌል የባለሥልጣናት ቤት እንኳ ሳይቀር ገባ። ለምሳሌ ጳውሎስ በሮም እስር ቤት ሆኖ፣ ወንጌል በቄሳር ቤተሰቦች ዘንድ እንኳ እንደ ተሰበከና እንደ ታመነ ጽፎአል። ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ?

በሁለተኛው ክፍለ ዘመን ቤተ ክርስቲያንን ተቃውሞ ይጽፍ የነበረውና አረማዊ የሆነን እምነት ይከተል የነበረው ሴልሱስ፣ ስለዚህ ነገርም ጽፎአል። ሴልሱስ

[3] John Foster, *Church Histroy: the First Advance, A.D. 29-500* (London: Society for Promoting Christian Knowledge, 1972), 35.

በወቅቱ እየሆነ በነበረው ነገር እጅግ ተሰፋ ቈርጦ ነበር፤ ምክንያቱም ወንጌል የባለ ሥልጣኖችን ሰፈር ሁሉ እያጸረሰ ስለነበረ ነው። ሴልሱስ የክርስቲያኖቹን እንቅስቃሴ ሊገታ ባለመቻሉም መሪር የሆነ ሐዘን ነበረነት። ክርስቲያን የሆኑ የቤት አገልጋዮች/ሠራተኞች እንኳ የጌቶቻቸውን ልጆች በሚያሳድጉበት ጊዜ ለልጆቹ ስለ ወንጌል ይናገሩ ነበር። ልጆቹም ለወላጆቻቸው ወንጌልን ይናገሩ ስለነበር ብዙም ሳይቆይ ባልተማሩና የገጠር ሰዎች በሆኑ የቤት ሠራተኞች አማካይነት፣ የብዙ ቤተ ሰብ አባላት ኢየሱስን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው ተቀበሉ[4]።

ክርስቲያኖች የክርስቲያኑን ማኅበረሰብ፣ "አዲስ ትውልድ"[5] አድርገው ይቈጥሩታል :—

> እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጐነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ፣ የንጉሥ ካህናት፣ ቅዱስ ሕዝብ፣ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ። እናንተ ቀድሞ ወገን አልነበራችሁም፤ አሁን ግን የእግዚአብሔር ወገን ናችሁ። እናንተ ምሕረት ያገኛችሁ አልነበራችሁም፤ አሁን ግን ምሕረትን አግኝታችኋል (1ጴጥሮስ 2÷9-10)።

አማኞች እግዚአብሔር ከዓለም ሕዝቦች፣ ከተለያዩ ቋንቋዎችና ጐሣዎች መካከል የጠራቸው የተለዩ እንዲሁም አዲስ ማኅበረሰቦች እንደ ሆኑ የቀድሞዱቱ ቤተ ክርስቲያን ታምናለች። ኢየሱስ ከመስቀሉ በፊት ሲጸልይ እንዲህ ብሎአል :— "እኔ ከዓለም እንዳይደለሁ ከዓለም አይደሉም. . .ወደ ዓለም እንደላክኸኝ እንዲሁ እኔ ወደ ዓለም ላክኋቸው" (ዮሐንስ 17÷16:18)።

ቤተ ክርስቲያን መጀመሪያ ወደ ኢየሩሳሌም ከዚያም ወደ ሌሎች ቦታዎች እንድትስፋፋ ጠንካራ አስተዳደርና ጥሩ አደረጃጀት መዘርጋቱ የግድ ነበር። ለማመን በሚያስቸግር ሁኔታ፣ ቤተ ክርስቲያን በጅማሬዋ ወቅት እንኳ ጠንካራ የሆነ አስተዳደራዊ መዋቅር ትጠቀም ነበር። ከክርስቶስ ጋር አብረው የነበሩት ዐሥራ ሁለቱ ሐዋርያት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ነበሩ። ከዐሥራ ሁለቱ እንዱ የነበረው ይሁዳ፣ ኢየሱስን አሳልፎ ከሰጠ በኋላ ራሱን ስለገደለ፣ ሐዋርያት በእርሱ ፋንታ ማቲያስን መረጡ። ቤተ ክርስቲያን በተተከለችባቸው አካባቢዎች ሁሉ፣ ጉባኤውን ሊመሩ የሚችሉ በሳልና መንፈሳዊ መሪዎች

[4] William G. Yong, *Handbook of Source Materials for Students of Church History up to 650 A.D* (Madras: The Diocesan Press, 1969), section 63.

[5] Foster, *Church Histroy*, 35

በሕዝቡ ይመረጡ ነበር። የድኾችን የገንዘብና የቍሳቍስ ችግሮች የሚፈ
ዲያቆናትም በተመሳሳይ መንገድ በሕዝቡ ተመረጡ።

ስለዚህ በአስተዳደራዊ ጒዳዮች ላይ በጥምረት የሚሠሩ ሦስት ክፍሎች ነበሩ።
እነሱም ዲያቆናት፣ ሽማግሌዎችና ሐዋርያት ናቸው። በተለያዩ ዘመናት ቤተ
ክርስቲያን የተለያዩ የአስተዳደር ዘዴዎችን ተጠቅማለች። ነገር ግን የተለያዩ
ዘዴዎች ቢኖሩም የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን የተጠቀመችባቸው የአስተዳደር
አካሄዶች እስከ ዛሬ ድረስ በሁሉም ቤተ ክርስቲያናት ውስጥ ይሠራሉ።
የመሪነት ዘርፎች ዲያቆናት፣ ሽማግሌዎች (መጋቢዎች ወይም ካህናት) እና
እረኞች (ጳጳሳት) ናቸው። መሪዎች ደግሞ የሕዝቡ አገልጋዮች እንጂ ገዥዎች
አይደሉም (ዮሐንስ 13÷2-17)።

የለውጥ ሐዋርያ የሆነች ቤተ ክርስቲያንና አዲስ የበቀለው ኡማ

በአራተኛው ክፍለ ዘመን የሮም መሪ የነበረው ቈስጠንጢኖስ፣ በቤተ
ክርስቲያንና በመንግሥት መካከል የነበረውን ግንኙነት አዲስ አቅጣጫ
እንዲይዝ አድርጒታል። ቈንስጠንጢኖስ ቤተ ክርስቲያንን የሮማን ገዛት ወደ
አንድነት ለማምጣትና ለማስፋፋት ተጠቅሞባታል። ይህም የምዕራብ አገሮችን
ጨምሮ የቤተ ክርስቲያንን የአስተዳደር ዘዴ እንዲሁም የቤተ ክርስቲያንን
ሚና መሠረታዊ በሆነ ሁኔታ ለውጦታል። ጳጳሳት በጎብረተሰብ ጒዳዮች ላይ
ወሳኝ ሰዎች ሆኑ፣ የቤተ ክርስቲያን የአስተዳደር አካሄድ የሮም መንግሥትን
የአስተዳደር ዘይቤ መከተል ጀመረ። ይህ የሆነበት ምክንያት ከቈንስጠንጢኖስ
ዘመን ጀምሮ የምዕራቢ ቤተ ክርስቲያን የመንግሥትን ሥልጣን ተጠቃሚ
በመሆንዋ ነው። ይሁንና በአሁኑ ዘመን ያለው ዓለማዊ የሆነው ባህል በምዕራቡ
መንግሥታት ቤተ ክርስቲያን በፖለቲካው ውስጥ ያላትን ሚና እየሸረሸረው
ይገኛል።

በዚህ መጽሐፍ መግቢያ ላይ እንደ ተመለከተው፣ በአብዛኛው መቶ ክፍለ
ዘመን የሙስሊም ኡማ ሲጀመር በቈንስጠንጢኖስ ዘመን በጠንካራ መሠረት
ላይ የታነጸው የመንግሥትና የቤተ ክርስቲያን ጎብረት በጥሩ ሁኔታ ላይ
ነበር። የምዕራቢ ቤተ ክርስቲያንና አንዳንድ የመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች፣
ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት መዋሐድ አለባቸው ብለው ያምኑ ነበር። ነገር
ግን በፐርሺያ፣ በሕንድና በአረብያ የነበሩት ቤተ ክርስቲያናት ግን
በጎብረተሰቡ ውስጥ ጒልሕ የሆነ የበላይነት አልነበራቸውም።

በመዲና የነበሩ ሙስሊሞች የሙስሊሙን ማኅበረሰብ አንድ ለማድረግ
የተጠቀሙበት ዘዴና ፖለቲካዊ አስተዳደር የሶሪያና የምዕራቢ ቤተ ክርስቲያን
ከተከተሉት የአስተዳደር አካሄድ ጋር በእጅጉ ተመሳሳይ ነው። የሙስሊሙን
ኡማ አደረጃጀት የሚነትፉ ክርስቲያኖች፣ የሙስሊም ኡማ ከመጀመሩ ከብዙ
ዓመታት በፊት፣ የምዕራቢ ቤተ ክርስቲያን የኡማ አደረጃጀትን ዐይነት መርሕ
መከተልዋን ሊያስተውሉ ይገባቸዋል። ቀጥለን በሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን
የሙስሊሙ ኡማ በመዲና እንዴት እንደ ተጀመረና እንደሰፋ እንመልከት።

ኡማ በመዲና ተጀመረ

መሐመድ የዘጠኝ ቀን ጒዞ አድርገው ከመካ ወደ መዲና ሲገቡ፣ በመዲና
ታላቅ ፈንጠዝያ ነበር። በምዕራፍ እንደ ተገለጸው ይህ ጒዞ ለእስልምና አዲስ
ምዕራፍ የተከፈተበት የሒጅራ ጒዞ ተብሎ ይጠራል።

ሙስሊሞች ኡማን መሠረቱ

መዲና ከሚገኙ ሙስሊሞች በተጨማሪ፣ በመቶዎች የሚቈጠሩ ከመካ ወደ
መዲና የተሰደዱ ሙስሊሞች በመካ ይኖሩ ነበር። እነዚህም ሙሐጂሩን
ተብለው ይጠራሉ። የመዲና ሙስሊሞች ደግሞ አንሳር በመባል ይጠራሉ።
መሐመድ እነዚህ ሁለቱ ክፍሎች ተዋሕደው የሙስሊሙን ኡማ እንዲፈጥሩ
ሥልጣን ሰጧቸው። በመዲና የነበሩት ሙስሊሞች ከመካ የመጡትን ስደተኞች
ለማቋቋም ያላቸውን ሁሉ አካፍለዋል።

የሙስሊሙ ኡማ ከተቋቋመ በኋላ፣ መሐመድ በመዲና መስጊድ ለመሥራት
ዕቅድ አወጡ። ይህ መስጊድ ለሙስሊሙ ማኅበረሰብ የመጀመሪያው መስጊድ
መሆኑ ነው። በዚህ መስጊድ ውስጥ የተጀመረው አምልኮና የአምልኮ ሥርዐት
በዓለም ሁሉና በየትኛውም ዘመን ለሚኖሩ ሙስሊሞች እንደ አብነት
የሚጠቀስ ነው።
በመስጊዱ ውስጥ ሚህራብ የሚባል ቦታ አለ። ይህም ሙስሊሞች በጸሎት
ሰዓት ወዴት አቅጣጫ መስገድ እንዳለባቸው የሚጠቁም ነው። በእስልምና
የመጀመሪያዎቹ ዘመናት፣ ሙስሊሞች ፊታቸውን ወደ ኢየሩሳሌም አድርገው
ይሰግዱ ነበር። ወደ ኢየሩሳሌም መስገዳቸው ለአይሁድ ሕዝብና ነቢያት
ከበሬታ ለመስጠት እንዲሁም እስልምና ከአይሁድ እምነት የቀጠለ መሆኑን
ለማሳየት ሳይሆን አይቀርም። እስልምና ከአይሁድ እምነት የቀጠለ ነው
የሚለው አስተሳሰብ፣ በመጀመሪያዎቹ ሙስሊሞች ዘንድ ዉቢና ጒልሕ ቦታ
ነበረው። ነገር ግን በመዲና ይኖሩ የነበሩት ሙስሊሞች የጸሎት አቅጣጫውን
ከኢየሩሳሌም፣ መካ ወደሚገኘው ካዕባ ቀየሩት።

በመዲና ለአላህ የሚቀርበው አምልኮ ወደ መካ የሄዱትን ስደተኞች እንዲሁም የመዲናን ድኾች በእንድ ያጣመረ ነበር። ይሁንና መፍትሔ የሚሹ ፖለቲካዊና ባህላዊ ጉዳዮች ነበሩ። ስለዚህ መሐመድ የአምልኮ ስፍራና የአምልኮ ሥርዐቱን ከመሠረቱ በኋላ፣ ሙስሊማዊ ለሆነ ፖለቲካዊ ሥርዐት መሠረት ጣሉ። ለመዲና ነዋሪዎችም የመተዳደሪያ ደንቦችን አዘጋጁ።

ሙስሊሞች መተዳደሪያ ደንብ አዘጋጁ

ሙስሊሞች ያዘጋጁት መተዳደሪያ ደንብ ስለ ወንድማማችነት፣ ስለ ፍትሕ እንዲሁም በእንድ ጉዳይ ላይ ስለመስማማት መመሪያን የሚሰጥ ነበር። የመተዳደሪያ ደንቡ ዋና ዐላማ የሙስሊሙን ኡማ አንድነት መጠበቅ ነው። የግለሰቦች መብት ለኡማው መብት መገዛት አለበት። በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ ያሉት ሕጐች በዘመናችን ያለውን ዐይነት የዲሞክራሲ አካሄድ የሚከተሉ አይደሉም[6]። ሙስሊሞች በሊበራል ዲሞክራሲ ውስጥ ያለውን የግለሰቦችን መብት ጉዳይ ሲሰሙ ከፍተኛ የሆነ ድንጋጤ ይሰማቸዋል።

እንዲያውም በቅርብ ዓመታት ውስጥ ለተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብቶች ጥያቄ ምላሽ ይሆን ዘንድ፣ የሙስሊም አገሮች መግለጫ እስላማዊ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌ አውጥቶአል። ከ፴ሥራ ሦስት ምዕተ ዓመት በፊት በመዲና እንደ ነበረው ሕግ፣ የግንበረሰቡ መብት ከግለሰብ መብት በላይ እንደ ሆነ ዛሬም ሙስሊሞች ያምናሉ[7]።

መሐመድ የሙስሊሞችን አገዛዝ በመዲና አካባቢ በሚኖሩ ግዛቶች ሁሉ አስፋፉ፤ ሕጉም ተግባራዊ የሚሆነው እስልምናን በተቀበሉ ሰዎች ላይ ብቻ አልነበረም። ሙስሊም ያልሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች በሙስሊሙን አስተዳደርና በእስልምና ሕግ ሥር ሆነው መኖር ነበረባቸው። በመዲና ሙስሊም ያልሆኑትን ክፍሎች በተለይም የአይሁዶች፣ የክርስቲያኖችንና የዞራአስተሪያንን መብቶች በተወሰነ መልኩም ቢሆን መጠበቅ ተችሎአል። ይሁን እንጂ ግንኙውም ግለሰብም ሆነ ቡድን የእስልምናውን የግዛት አንድነት በአደጋ ላይ መጣል አይፈቀድለትም። ለምሳሌ በአይሁድ ማኅበረሰብ ውስጥ የነበሩ ሰዎች፣

[6] George W. Braswell Jr. *Islam: Its Prophet, Peoples, Politics and Power* (Nashville: Broadman & Holman Publishers, 1996), 127.

[7] Javid Iqbal, "Democracy and the Modern Islamic State," in *Voices of Resurgent Islam*, edited by John Esposito (New York: Oxford University Press, 1983), 252-60.

በእስልምና ላይ እያሤሩ እንደ ሆነ መሐመድም ሆኑ ሙስሊሞች ባረጋገጡ ጊዜ በሤራው የተጠረጠሩ ሰዎች ሁሉ እንዲገደሉ ተደርጉአል።

የዐረብ ማኅበረሰብ በተለያዩ ጉዛዎች የተከፋፈለ እንዲሁም አንዱ ጉሣ ከሌላው ጉሣ ጋር በጠላትነት የሚተያይ ነበር። መሐመድ በመዲና ቆይታቸው በከተማው የነበሩትን ተጻራሪ ጉሣዎች ወደ አንድነት በማምጣት፣ የሙስሊሙን ኡማ መሠረቱ። ይህም ኡማ የሙስሊም ግዛት ተብሎ ይጠራል። እንዲህ ዐይነቱ ሥራ ንቁ የፖለቲካ ብቃትን ይጠይቃል። በተወሰኑ ዓመታት ውስጥ እርስ በርሳቸው ይዋጉ የነበሩትን የመዲና ጉሣዎች ዕርቀ ሰላም እንዲያወርዱ የማድረጉ ጥረት በዐረብያ ያሉ ጉሣዎች ሁሉ ወደ አንድነት እንዲመጡ ምክንያት ሆኖአል።

የእስልምናው እንቅስቃሴ ከመዲና ዐልፎ ወደ ሌሎች ቦታዎች ሲዛመት፣ ዐረብ ክርስቲያኖች ለዚህ ዐይነቱ ሙስሊማዊ አካሄድ ትልቅ ፈተና ነበሩ። ሙስሊሞች፣ ዐረብኛው ቁርአን የመጨረሻው የአምላክ መገለጥ ስለሆነ፣ የዐረብ ዝርያ ያላቸው ሰዎች ሁሉ ወደ እስልምና መቀየር አለባቸው የሚል እምነት ነበራቸው። በቀጣዮቹም ሁለት ምዕተ ዓመታት ውስጥ ዐረቦች ሁሉ ወደ እስልምና ተቀየሩ። ይሁን እንጂ አንዳንድ ዐረብ ክርስቲያኖች ወደ እስልምና የተለወጡት ሙስሊሞች ያካሂዱባቸው ከነበረው ከፍተኛ ጫና እንዲያውም ከፍተኛ የሆነ ማስፈራራት የተነሣ ነበር። ሙስሊሞች በክርስቲያኖች ላይ ያደርሱ ስለነበረው ጫና በናሙናነት ከሚያሳዩን ማስረጃዎች መካል አንዱ፣ ካሊፍ ዋሊድ የተባለው ሰው፣ ታግሀሊብ ለተባለው የክርስቲያኖች መሪ በተግሣጽ መልክ ያስተላለፈውን መልእክት እንመልከት፦— "አንተ የዐረብ መሪ ስትሆን እንዴት መስቀልን ታመልካለህ? ይህ የአንተ ድርጊት ዐረቦችን የሚያሳፍር ድርጊት ነው[8]"።

የዳር አል-ኢስላም (የሰላም/የሙስሊሞች ክልል) መጀመር

በመዲና አማኙ ኅብረተሰብና የፖለቲካው ሥርዐት ተቀላቅለው ነበር። መሐመድ ነቢይም የአገር ገዢም ነበሩ። በመሐመድ አስተዳደር ሥር የነበረው አካባቢ ዳር ሰላማዊ እንደ ነበር ይታመናል። ይህ የሰላም ቀጣና በመዲና አካባቢ ዳር አል-አህድ (የስምምነት ቤት) ወይም ዳር አል-ኢስላም (የሙስሊሞች ቤት) በመባል ይጠራል። ከሦስት ምዕተ ዓመታት በኋላ ዳር

[8] Jacqueline Hoover, "Pre-Islamic Arabia." Lecture from excerpts of Robert G. Hoyland, *Arabia and the Arabs* (New York: Routledge, 2001), 229-47.

አል-ሳላም (የሰላም ቀጣና) የሚለው አስተሳሰብ ሙስሊሞች ዓለምን ሁሉ መምራት አለባቸው የሚለውን አስተሳሰብ ወለደ::

ዳር አል-ኢስላም ማለት በሙስሊሞች አስተዳደር ሥር ያለ የሰላም ቀጣና ማለት ነው:: ሙስሊሞችንና ሙስሊም ያልሆኑትን በተመለከተ ዳር አል-ኢስላማ የሚለው የአስተሳሰብ ዘር የተዘራው የእስልምናው ኡማ በመዲና በተጀመረ ጊዜ ነው:: ቁርአን ራሱ ይህንን ዘር በጎብረተሰቡ ውስጥ ዘርቶአል:: ቁርአን ዳር አል-ኢስላምን ውብ በሆነ ቋንቋ እንዲህ ሲል ገልጸታል:—

> አላህም ወደ ሰላም አገር ይጠራል፤ የሚሻውንም ሰው ወደ ቀጥተኛው መንገድ ይመራል:: ለነዚያ መልካም ለሠሩት መልካም ነገርና ጭማሪም አላቸው፤ ፊቶቻቸውንም ጥቁረትና ውርደት አይሸፍናቸውም፤ እነዚያ የገነት ሰዎች ናቸው፤ እነርሱ በውስጧ ዘውታሪዎች ናቸው (ሱራ 10+25-26)::
>
> ለነርሱ በጌታቸው ዘንድ የሰላም አገር አላቸው፤ እርሱም ጌታህ ይሠሩት በነበሩት ምክንያት ረዳታቸው ነው (ሱራ 6+127)::

የሙስሊም ኡማ በመዲና የፖለቲካ የበላይነት ስለነበረው፤ ፈጣን ዕድገት አሳየ:: በመዲና የነበረው የሙስሊሞች ስኬት በመካ ሥልጣንና የፖለቲካ የበላይነት ያልነበራቸው ሙስሊሞች ከደረሰባቸው መከራ ፍጹም ተቃራኒ ነበር::
ሙስሊሞች በመካና በመዲና የነበራቸው ተሞክሮ እስልምናን ለማስፋፋት የፖለቲካውንና የሥልጣንን የበላይነት መያዝ አንገብጋቢ ጉዳይ ነው እንዲሉ አድርጓቸዋል:: ሙስሊሞች የፖለቲካ የበላይነት በሌላቸው ጊዜ የሙስሊም ተልእኮና ስኬት መሰናክሎች እንደሚገጥሙት በአንጻሩ ደግሞ የሙስሊሞች የፖለቲካ የበላይነት መረጋገጥ እውነት እንዲያሸንፍና የሙስሊሙን ማኅበረሰብ መብቶች ለማስከበር ይረዳል የሚል እምነት አላቸው::

ሙስሊሞችና መንግሥት

ኬኔት ክራግ፤ "የእስልምናን ታሪክ እንዲሁም የእስልምናን ነገረ መለኮት ማጥናት ማለት፤ ከየትኛውም እምነት ይልቅ ሀልውናውንና ትምክታቸውን ለማረጋገጥ የፖለቲካን ሥልጣን መሠረት የሚያደርግ ከፍተኛ የሆነ ቀጥተኝነት ያለውን የሃይማኖት ክፍል ማጥናት ማለት ነው"[9] ይላሉ::

[9] Kenneth Cragg, *Muhammad and the Christian* (Maryknoll, N.Y.: Orbis Books, 1984), 32.

በጎሪንስተን ዩኒቨርስቲ የእስልምና ሃይማኖት ምሁር የሆኑት በርናርድ ልዊስ ስለዚሁ ጉዳይ እንዲህ የሚል አስተያየት ሰጥተዋል:—

> ሙስሊም የሆነ ማንኛውም መንግሥት ቀዳማይ ዐላማው፤ እያንዳንዱ ሙስሊም መልካም የሆነ ሙስሊማዊ ሕይወት እንዲኖር ማስቻል ነው:: ይህ የመልካም ሙስሊማዊ መንግሥት ዐላማ የመጨረሻው መመዘኛ ሲሆን እግዚአብሔር መንግሥትን የመሠረተበት እንዲሁም ባለሥልጣናትን የሚሾምበት ዋነኛ ዐላማም ይኸው ነው የሚል እምነት አላቸው:: የመንግሥት ብቃት፤ የባለሥልጣናት መልካምነትና ክፋት የሚመዘንበት መስፈርትም ይኸው ነው[10]::

ሙስሊም ያልሆነ አንድ መንግሥት ይህ ዐይነቱን ሙስሊማዊ ጥቅም ማስከበር ይችላልን? ላይፈጽም ይችላል:: ይህ ርእሰ ጉዳይ በዐሥራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን በነበሩ ኡላማዎች (የእስልምና ሕግ ምሁራን) መካከል ይደረግ የነበረ ክርክር ነው:: ክርክሩ ሙስሊሞች የሙስሊም ግዛት ወዳልሆኑት የምዕራባውያን አገሮች እንዳይሄዱ እንዲሁም ኑሮአቸውን በዚያ እንዳያደርጉ ወደ መከልከሉ ያዘነበለ ነው[11]:: ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ ያለው ከፍተኛ ፍልሰት በዚህ ረገድ ያለው ሕግ እውን እንዳይሆን አድርጎአል:: እንዲያውም በአሁን ጊዜ የተወሰኑ ሙስሊሞች ለሃይማኖት ጉዳይ ለዘብተኛ የሆነው የምዕራባውያኑ ባህል ለሙስሊሙ ኡማና ለእያንዳንዱ ሙስሊም ከፍተኛ የሆነ ከለላ ሊሰጥ እንደሚችል ተረድተዋል::

የእስልምና ሃይማኖት ፕሮፌሰር እንዲሁም የኢራን ሺአ እስልምና ተከታይ የሆኑት ሐሚዳህ ሞሐንጊ የሚባሉት ወይዘሮ በጀርመን አገር ከሁለት ዐሥርት ዓመታት በላይ የኖሩ ሲሆን፤ በጀርመን አገር ለተሰበሰቡት አናባፕቲስቶች ከላይ ያለውን ሐሳብ በመደገፍ እንዲህ ሲሉ ንግግር አድርገዋል:—

> ሙስሊሞች በሰላም የሚኖሩበት ሥፍራ ሁሉ የእስልምና ቤት ነው:: ያም ዳር አል-ኢስላም ነው:: ጀርመን ሙስሊሞች በሰላም የሚኖሩባት አገር እስከ ሆነች ድረስ ጀርመን ዳር አል-ኢስላም ናት[12]::

[10] Bernard Lewis, *The Political Language of Islam* (Chicago: Chicago University Press, 1969), 29

[11] Bernard Lewis, *What Went Wrong? Western Impact and Middle Eastern Response* (New York: Oxford University Press, 2002), 36-37.

[12] Hamideh Mohagheghi, "The House of Islam." Lecture at the *Theologische Studientage der* AMG, Heiligenstadt, October 6-10, 2002

ዛሬም መዲና ሞዴል ናት

ሙስሊሞች የጥንቷን መዲና የፍጽምና ተምሳሌት አድርገው ስለሚመለከቱ፣ አብዛኛው ሙስሊም ጻር አል-ኢስላምን መመሥረት ቀዳማይ ግቡ ነው። ፕሮፌሰር ሐሚዳህ ይህንን ዐሳማ አስመልክተው በ2002 ዓ.ም ላይ በጀርመን አናባኘቲስት መማክርት ላይ በመገኘት እንዲህ የሚል አስተያየት ሰጥተዋል:—

> የእስልምና አስተዳደር በመዲና ከተማ ከተመሠረተ በኋላ እንሰላት እንኳ በሰላም መኖር ጀምረው ነበር። በነቢዩ አስተዳደር መዲናና አካባቢው ፍጹም የሆነ ሰላም ሰፍኖበት ነበር[13]።

ይህ የመዲና ተሞክሮ የሙስሊሞች ኡማ ይረጋገጥ ዘንድ የፖለቲካ የበላይነት ማግኘት ዋነኛ ነገር እንደ ሆነ፣ ይህም የፖለቲካ የበላይነት ሰላምን እንደሚያሰፍን ትምህርት እንደ ሆናቸው ይናገራሉ። በእስልምና ቀኖተር ሥር ያልዋለ አካባቢ (ጻር አል-ኢስላም) የጦርነት ምድር (ጻር አል-ሐርብ) ተብሎ ይጠራል። ሙስሊሞች ዓለማችንን በሁለት ዐቢይ ወገን ከፍለው ይመለከቷታል። ይኸውም በእስልምና ቀኖተር ሥር የዋለው አካባቢ የሰላም ምድርና ተብሎ ሲጠራ፣ በእስልምና ቀኖተር ሥር ያልዋለው አካባቢ ደግሞ የጦርነት ምድር ይባላል።

ድል ሰድረጊ ሙስሊሞች

መሐመድ ከሒጅራ ጉዞ በኋላ ለዐሥር ዓመት በሕይወት ኖረዋል። በእነዚህ ዐሥር ዓመታት የነበረው የመሐመድ ወታደራዊና ፖለቲካዊ መስፋፋት (ጻር አል-ኢስላም) እጅግ አስገራሚ ነበር። ሙስሊሞች፣ ስኬታማ የሆነው የሙስሊሙ ማኅበረሰብ እስላማዊውን አስተዳደር በምድረ ዐረቢያ ሁሉ ማስፋፋት ሲጀምር (ጻር አል-ኢስላም)፣ የጦር ምድር (ጻር አል-ዐረብ) የሚባለው ክልል መሸሸና ማፈግፈግ ግድ ሆኖበታል ይላሉ።

በሰላም ምድርና በጦርነት ምድር መኻል የተካሄደው በጦር ጎይል የታገዘ ነው። የእስልምና ጎይሎች በመሐመድ መሪነት ከእስልምና ጠላቶች ጋር ባደረጉዋቸው ውጊያዎች ሁሉ አመርቂ ድሎችን አግኝተዋል። የጠላት ጦር ቁጥር በበዛባቸው ዐውደ ግንባሮች ሳይቀር ሙስሊሞች ጠላቶቻቸውን ድል ነሥተዋል። የሙስሊሞች ድል የመሐመድን ነቢይነትና የእስልምናን እውነት የሚያረጋግጥ እንደ ሆነ በሱራ 8÷5-19 ላይ ተገልጸአል። ሙስሊሞች ይህን ይበሉ እንጂ፣ ቢያንስ በአንድ የጦር ውሎ መሐመድና ተከታዮቻቸው ድል እንደ ተመቱ ይታወቃል። በኡሑድ ዐውደ ግንባር የመካ ጦር በመሐመድ የሚመራውን የሙስሊም ጦር ያሸነፈ ሲሆን፣ መሐመድ በጦርነቱ ክፉኛ ቈስለው ሁለት ጥርሶቻቸውን ያጡ ሲሆን፣ ሰባ ሙስሊሞችም በዐውደ ግምባሩ ተገድለዋል።

ቁርአን በሱራ 3÷134-200 ይህ ሽንፈት ለምን ሊከሠት እንደ ቻለ ሰፊ የሆነ ነገረ መለኮታዊ ማብራሪያ ይሰጣል። ይኸውም እስልምናን ለመከላከል የሚሞቱ ሰዎች ሰማዕት ሲሆኑ፣ መንግሥተ ሰማይም በቀጥታ የመግባት ዕድል ያገኛሉ። እግዚአብሔር እያንዳንዱ ሰው የሚሞትበትን ቀን ስለወሰነ፣ አንድ ሰው ጦር ሜዳ ቢሄድ ወይም ደግሞ በሰላም ቤቱ ቢቀመጥ ቀኑ ከደረሰ ከሞት ማምለጥ አይችልም። በመሞቻው ቀን ላይ አንዳችም ለውጥ ሊያመጣ አይችልም። ጣዖት አምላኪዎች በእስልምና ላይ ምን ጊዜም የበላይነት ሊኖራቸው እንደማይገባ እንዲሁም ሙስሊሞች ለነቢዩ መሐመድ እስከ ታዘዙ ድረስ ድል በደጃቸው እንደ ሆነች የኡሑዱም ጦርነት ሙስሊሞች እምነታቸው የሚፈተንበት ዐውደ ግንባር እንደ ሆነ ነው። በርቱ የማታ ማታ ድሉ የእኛ ነው። እግዚአብሔር ይቅር ባይና መሓሪ ነው[14]።

ሙስሊሞች ከኡሑድ ጦርነት ሽንፈት በማገገም፣ ከሒጅራ ጉዞ ዐሥር ዓመት በኋላ መላው ዐረብያን በእስልምና አስተዳደር ሥር እንዲገባ አደረጉ። ከሒጅራ ጉዞ ስምንት ዓመት በኋላ፣ መሐመድ የሙስሊምን ጦር በመምራት መካን ያዙ። የመሐመድ ጦር ተከታታይ መሆኑ ጥቃት በማካሄዱ የመካ ነዋሪዎች ወታደራዊ ጉልበት ተፈታ። መሐመድ ዐሥር ሺህ የሚሆን ጦር እየመሩ ወደ መካ የገቡት፣ "እውነት መጣ፣ ውሸትም ተወገደ፣ እነሆ ውሸት ተወጋጅ ነውና" (ሱራ 17÷81) የሚለውን በማወጅ ነበር።

እውነትና የፖለቲካው ሥርዐት

መሐመድ በመዲና ቆይታቸው የሙስሊሙን ማኅበረሰብ እምነትና የፖለቲካው ሥርዐት እንዲጋባ አድርገዋል። በዚህ ስኬት መሐመድ ዓለም ዐቀፋዊ ራእይ እንዲኖራቸው እንዲሁም ይህ ራእይ በዓለም ሙስሊሞች ዘንድ ቀጣይነት እንዲኖረው አድርገዋል። ጻር አል-ኢስላም የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ከፖለቲካው ሥርዐት ጋር በቀጥኝት እንዲሠራ የሚያደርግ ምልክታ ነው።

ሙስሊሞች ኢየሱስ የፖለቲካውን ሥርዐት ለመቈጣጠር አንዳችም ፍላጎት እንዳልነበረው ይረዳሉ። በእርግጥም ሥልጣን ሊያሰጡት የሚችሉትን

[13] ዝኒ ከማሁ።

[14] Alfred Guillaume, *Islam* (New York: Penguin, 1979), 46.

አጋጣሚዎች አልተጠቀመባቸውም—አይፈልገውምና። በሙስሊሞች ዕይታ ግን ይህ ዐይነቱ የኢየሱስ አካሄድ፣ ተግባራዊነት የጐደለውና ምሉዕ ያልሆነ ነው። እንደ ሙስሊማኑ ትምህርት፣ ተግባራዊ እምነት በፖለቲካ ውስጥ መሳተፍንና የበላይነት መያዝን ይጠይቃል። አብዛኛውን ጊዜ ሙስሊሞች፣ "እናንተ ኢየሱስ ባስተማረው የፍቅር ሕግ አገርን እንዴት መምራት ትችላላችሁ?" ሲሉ ይጠይቃሉ። ይህ የፍቅር ሕግ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ላስገዙ መነኰሳት እንጂ፣ ይህንን ክፉ ዓለም ለማስተዳደር አይሠራምና። ስለዚህ የክርስቶስ አገልግሎት በተወሰኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ላይ ብቻ የተወሰነ ነው። ሙስሊሞች የፖለቲካ ሥርዐቱም ሆነ የመንግሥት ሹማምንት ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊመጡ የሚችሉት በኢየሱስ ሳይሆን በመሐመድ አገልግሎት እንደ ሆነ ይናገራሉ።

የመሐመድ የፖለቲካ አካሄድ ከኢየሱስ ጋር ተመሳሳይ እንዳይደለ ሙስሊሞች መረዳታቸው/መናገራቸው ትክክል ነው። ኢየሱስ በኢየሩሳሌም በፖለቲካና በጦር ኀይል የታገዘውን መንግሥት አልቀበልም በማለት ለቀረበለት ጥሪ ጀርባውን ሰጠ። ይሁን እንጂ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ በዓለም ላይ "ጨው"፣ "ብርሃን" እንዲሁም "እርሾ" በመሆን ዓለምን እንደሚያጣፍጡና እንደሚያደምቁ አስተምሮአል። ይህ የጽድቅን መንገድ የሚከተሉ ሰዎች በእያንዳንዱ የኅብረተሰብ ክፍልና በፖለቲካው ውስጥ መልካምን ነገር ለማምጣት ኀያልና ለውጥ ሊያመጣ የሚችል ተጽእኖ ማድረግ እንደሚችሉ የሚያሳይ ነው። ነገር ግን ኢየሱስ ተከታዮቹ ፖለቲካውን የመቈጣጠር አጀንዳ እንዲኖራቸው የማነሣሣት ዕቅድም ሆነ ትምህርት አልነበረውም። ነገር ግን ማናቸውም ዐይነት የፖለቲካ ሥርዐት የእግዚአብሔርን መንግሥት ምስክርነት ማዳመጥ እንዲሁም ለፍትሕና ለጽድቅ አምንታዊ ምላሽ መስጠት አለበት—ይጠበቅበትማል። ነገር ግን ኢየሱስ በሕይወቱም ሆነ በትምህርቱ ግልጽ ያደረገው ቀሥም ነገር የትኛውም የፖለቲካ ሥርዐት የእግዚአብሔር መንግሥት ያለመሆኑን ነው።

እንደዚህ ሲባል ግን በመንግሥትና በቤተ ክርስቲያን መካከል መደጋገፍ አይኑር ወይም ለጌታ ታማኝ የሆነች ቤተ ክርስቲያን ሁል ጊዜ መሰደድ አለባት ወይም ቤተ ክርስቲያን ለመንግሥት የምታስተምረው ነገር የለም ማለት በፍጹም አይደለም። ሆኖም የተለያዩ የክርስቲያን ማኅበረሰብ ክፍሎች የቤተ ክርስቲያንና የመንግሥት ግንኙነት ምን መምሰል አለበት በሚለው ጒዳይ ላይ የተለያየ ዐይነት አመለካከት አላቸው። ከዚህም ምልከታ የተነሣ፣ በመንግሥትና በቤተ ክርስቲያን መካከል በአንዳንድ አካባቢዎች የቀረቡ ግንኙነት ሲኖር፣ በአንዳንድ አካባቢዎች ደግሞ ምንም ዐይነት ግንኙነት

አይታይም። ለምሳሌ በሶቭየት ሶሻሊስት ሥርዐት ዘመን የሶሻሊስቱን ርዕዮተ ዓለም የሚከተሉ አገሮች፣ የቤተ ክርስቲያን ጠላቶች ሆነው ነበር።

በዐሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሣው የጸጋም መጥምቃውያን (የአናባፕቲስት) እንቅስቃሴ፣ ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት የተለያዩ ተቋማት ናቸው የሚል አስተምህሮ ነበረው። እስካሁን ድረስ የአናባፕቲስት አመለካከት ያላቸው ክርስቲያኖች የቤተ ክርስቲያን መልክ የሚበላሸው ቤተ ክርስቲያን ተልእኮዋን ለማስፈጸም ስትል ከመንግሥት ጋር መተባበር ስትጀምር ወይም መንግሥት አገራዊ አጀንዳውን ለማስፈጸም ከቤተ ክርስቲያን ጋር ሲሠራ ነው ይላሉ። ኢየሱስ ለኢየሩሳሌም ሰላም ሠርቶአል፣ ጸልዮላታልም። ነገር ግን የእርሱ መንግሥት ኢየሩሳሌምን የፖለቲካ ሥርዐት ማዕከል ያደረገ አልነበረም። አናባፕቲስት ክርስቲያኖች፣ የመጀመሪያዪቱ የሆነችው የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያንና በወቅቱ የነበረው መንግሥት የተለያዩ ተቋማት ሆነው የመኖራቸው እውነት በየትኛውም ዘመን ለሚኖሩ ክርስቲያኖች ምሳሌ ነው ብለው ያምናሉ። እነዚህ ክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያን በቤተ ክርስቲያንነቷ፣ መንግሥትም መንግሥትነቱ ይቀጥል፣ አንዱ ከሌላው ጋር ሊጋባ አይገባውም ይላሉ።

በኢየሩሳሌም የነበረችው የመጀመሪያዪቱ ቤተ ክርስቲያን እንዲሁም በመጀመሪያ በመዲና የነበረው የሙስሊሙ ኡማ አሁን ላለችው ቤተ ክርስቲያን እንዲሁም ለሙስሊሙ ኡማ መሠረትን ጥለዋል። በሙስሊም ኡማ የኡማውና የፖለቲካ ሥርዐቱ መዋሐዳቸው እጅግ በጣም አስፈላጊ እንዲሁም የሙስሊሙ ኅብረተሰብ መሠረት ነው። የሙስሊሙ ማኅበረሰብ የፖለቲካውንና የጦር ኀይሉን የበላይነት እስካልተቈጣጠረ ድረስ፣ እስልምና ወደ ፍጽምና ደረጃ እንደ ተሸጋገረ አይቈጠርም። እንደ ሙስሊማኑ ትምህርት የፖለቲካው ኀይል ለእውነት (ለእስልምና) ጥበቃ ያደርጋል፣ እውነት ደግሞ በፖለቲካ ኀይል ሲደገፍ ያሸንፋል።

እውነትና ኀይል

የእምነትና የፖለቲካ ሥርዐት ይለያዩ ወይስ ይጣመሩ የሚለው ጒዳይ፣ እውነት የፖለቲካን ኀይል ድጋፍ ትፈልጋለችን? የሚል ጥያቄ ያስነሣል። በጦር ኀይል ተገዶ አንድን እምነት የሚቀበል ሰው ሕይወት/ነፍስ ዕጣ ፈንታዋ ምንድን ነው? የሃይማኖት ትምህርት ይህ ዐይነቱን የአስገድዶ ማሳመን አካሄድ እንዴት ይመለከተዋል?

እነዚህ ርእሰ ጉዳዮች የእስልምናን ሃይማኖት ስለሚያሳስቡት ቁርአን፣ "በሃይማኖት ማስገደድ የለም" (ሱራ 2+256) ሲል የተግሣጽ ምክር ይመክራል። ሙስሊሞች ለዚህ ቁርአናዊ ምክር ምን ያህል ታማኞች ሆነዋል? ቤተ ክርስቲያንስ ብትሆን ሰዎች የማመን ወይም ያለማመን መብታቸውን እንዲጠቀሙ ምን ያህል ነጻነት ትሰጣለች?

ኢየሱስ እውነትን በመግለጥ፣ ሰላምን ሰበከ እንጂ፣ እውነቱን ተቀበሉ በሚል ማንንም አላስገደደም። ይሁዳ ለሞት አሳልፎ እንደሚሰጠው እያወቀ እንኳ፣ አቋሙን እንዲለውጥ ግዳጅ ሲያደርግበት አንመለከትም። ሰዎች አንድን እምነትን ለመከተልም ሆነ ለመቃወም ሙሉ ነጻነት አላቸው።

ይህ ሰዎች በነጻነት በሙሉ ፈቃደኝነታቸው እምነታቸውን ይወስኑ የሚለው አስተሳሰብ፣ በዐሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተነሡት ዳግም መጥምቃውያን የሕፃናትን ጥምቀት እንዲቃወሙ እንዲሁም ለማመንና ክርስቶስን ለመከተል የወሰኑ ዐዋቂዎች ብቻ የውሃ ጥምቀት እንዲወስዱ ካደረጓቸው ምክንያቶች ውስጥ ይህ አንዱ ነው። ወላጆች እንኳ ለልጆቻቸው እምነትን መምረጥ አይችሉም። በርግጥ በሕፃናት ጥምቀት የሚያምኑ ቤተ ክርስቲያናት እንኳ፣ ሕፃኑ ካደገ በኋላ የእምነት ማጽኛ ትምህርት በመከታተል እምነቱን በጉባኤ ፊት እንዲያሳውቅ ያደርጋሉ። ሰዎች የማመንም ሆነ ያለማመን መብታቸውን በነጻነት እንዲያደርጉት ቤተ ክርስቲያን ብታደፋፍርም አንዳንድ ጊዜ ግን ይህ የነጻነት ውሳኔ ጉዳይ በጉልሕ ሲከወን አይታይም።

ቤተ ክርስቲያን በኢየሩሳሌም ስትመሠረት የነበረው ሁኔታ ምን ይመስል ነበር? የሙስሊም ኡማ በመዲና በሚጀመርበት ወቅትስ? እነዚህ ከሥተቶች በቤተ ክርስቲያንና በሙስሊም ኡማ መካከል ስላለው እውነትና የፖለቲካ ኀይል ምን ያስተምሩናል? ከተወሰኑ ዓመታት በፊት ቨርጂኒያ በሚገኘው በብሔራዊ የሕዝብ ሬዲዮ ጣቢያ ፕሮግራም ቃለ መጠይቅ ተደርጉልኝ ነበር። በቃለ ምልልሱ ወቅት አስተያየት የሰጠሁት መሐመድና ኢየሱስ ከፖለቲካ ኀይልና ከእውነት ጋር ያላቸው ግንኙነት ምን ይመስላል የሚለውን ጉዳይ የሚመለከት ነበር።

ቃለ መጠይቁን ያደረገልኝ ሰው፣ "በኢየሩሳሌም በኢየሱስ ዘመን የነበሩ ክርስቲያኖችና ሰባኪዎች ምናልባት በኢየሩሳሌም ከኢየሱስ ጋር ከመሆን ይልቅ በመዲና ከመሐመድ ጋር መሆንን የሚመርጡ ይመስለኛል" ሲል ተናገረ። እኔም፣ "ምናልባት ይህ አንተ የምትለው ነገር እውነት ሊሆን እንደሚችል

እኔም ግምት አለኝ" አልሁት። ይህ ጉዳይ ከሙስሊሞች ጋር በምንወያይባቸው ጊዜዎች ሁሉ ወደሚነሣው መሠረታዊ ጥያቄ የሚወስደን ነው።

መሲሑ ኢየሱስ በአህያይቱ ውርጫ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ የተገለጠው እውነት ምንም ዐይነት የኀይል ተገን አያስፈልገውም። ኢየሱስ በመስቀል ላይ የተቸነከሩትንና የቁሰሉትን እጆቹን በመዘርጋት በመስቀል ላይ ለሰቀሉት ሰዎች የይቅርታ እንባ በማንባቱ የተገለጠ እውነት ነው። በተጨማሪም ከትንሣኤው በኋላ ለደቀ መዛሙርት በሰጣቸው ሰላምና በላከላቸው መንፈስ ቅዱስ የኢየሱስ እውነት ተረጋግጦአል። በአንጻሩ ግን መሐመድ ወደ መካ ሲገቡ የሰበኩት እውነት የጦር ድጋፍ የጠየቀ ነበር። እንግዲያው እውነት ምን ዐይነት ባሕርይ አለው? የእውነተኛ ሰላም ባሕርይስ ምንድን ነው?

ወንጌልና እስልምና በልባችን እንዲሁም በታሪክ ለተጻፉት እውነታዎች የተለያየ ምላሽ አላቸው። እነዚህም የተለያዩ ምላሾች የተገለጡት ወደ ሁለት ከተሞች በተደረጉ የተለያዩ ጉዞዎች ውስጥ ነው። የናዝሬቱ ኢየሱስ በሕፃናት መዝሙር ታጅቦ ለመስቀል ሞት ፈቃደኝነቱን ያረጋገጠበት ጉዞ አንዱ ሲሆን፣ የቁሬይሹ መሐመድ ደግሞ የፖለቲካውንና የወታደራዊውን ኀይል ለመቆጣጠር ወደ መዲና የተሰደዱበት ጉዞ ደግሞ ሌላው ነው።

ሙስሊሞች ስለእስልምናው ሰላም ምስክርነታቸውን ይሰጣሉ። ቤተ ክርስቲያን የተጠራችው ግን የመሲሑን ሰላም ለማወጅ ነው። በዚህ የቤተ ክርስቲያን ጥሪ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን ጥቃት ሊያደርስበት ለሚችለው ለዚህ የወንጌል እውነት ሕያው ምስክር የመሆን ታላቅ ኀላፊነት አለባት። ይህንን የእውነት ስጦታም ሰዎች በሙሉ ነጻነትና ፈቃድ ሲቀበሉትም ሆነ ሊቃወሙት ሙሉ መብት አላቸው። እንዲህ ዐይነቱም እውነት ታማኝነትና ድፍረት የተሞላበትን ምስክርነት ይፈልጋል። ይህን እውነት ለማወጅ አንዳችም የፖለቲካም ሆነ የጦር ኀይል ተገን አያስፈልገውምና።

የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ

ሉቃስ 10+28-48

የቀደሰን ምንባብ

ሱራ 8+5-19

የአስተውሎትና የውይይት ጥያቄዎች

1. ኢየሱስ በአህያ ውርንጫ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም በገባ ጊዜ ያሳየው የእግዚአብሔር መንግሥት ምን ዐይነት ባሕርይ አለው (ዘካርያስ 9÷9-10፤ ሉቃስ 19÷28-44)?
2. መሐመድ በመዲና የመሠረቱት መንግሥት ባሕርዩ ምንድን ነው (ሱራ 8÷37-41)?
3. የቤተ ክርስቲያን በተጀመረችበት ቀን የነበረውን ሁኔታ ይግለጹ (ሐዋርያት ሥራ 2÷1-47)። በቤተ ክርስቲያንን ለመመሥረት የመንፈስ ቅዱስ ሚና ምን እንደ ነበር ያብራሩ።
4. በመዲና የሙስሊም ኡማ እንዴት እንደ ተጀመረ ይግለጹ። ለኡማው መመሥረት የመሐመድ ሚና ምን እንደ ነበር ይዘርዝሩ (ሱራ 8÷20-21)።
5. እውነት የሚያሸንፈው እንዴት ነው? በበዓለ ኀምሳ ቀን ቤተ ክርስቲያን በተጀመረችበት መልኩ ነው ወይስ የሙስሊም ኡማ በመዲና በተመሠረተበት መንገድ ነው?
6. "ወንጌልን የተቀበሉ ሰዎች እውነትን ከጥቃት ለመከላከል አንዳችም ጎይል ወይም ዐመጽ አይጠቀሙም" በሚለው ዐረፍተ ነገር ላይ የራስዎን አስተያየት ይስጡ።
7. አሁን ቤተ ክርስቲያን ከኢየሱስ ጋር ኢየሩሳሌም ጉዞ የምታደርገው እንዴት ነው?

ምዕራፍ ዐሥር

አሐዱ አምላክ
ቶውሂድ—ሥላሴ

በፍጥነት ይጓዝ በነበረው ማርቸዲስ አውቶቡስ ውስጥ እንደ እኔው በጉዞ ላይ የነበረ አንድ ሰው፣ በአውቶቡሱ ውስጥ ከሚሰማው ከፍተኛ የሆነ የሙዚቃ ድምፅ በላይ ድምፁን ከፍ አድርጎ፣ "ሙስሊም ነህ እንዴ?" ሲል ጠየቀኝ።

"የለም እኔ ክርስቲያን ነኝ" ብዬ መለስሁለት። ሰው ሁሉ ይሰማው ዘንድ ይበልጥ ድምፁን ከፍ አድርጎ፣ "እንግዲያው የመድበለ አማልክት አምላኪ ነኻ! ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ታምናለህ። ለእግዚአብሔር ልጅ የወለደችለት ሴት የእግዚአብሔር ሚስት ነበረች ማለትህ ነው?" ሲል ጠየቀኝ።

በሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ግንኙነት ውስጥ፣ "ኢየሱስን በተመለከተ የክርስቲያኖች እምነት ምንድን ነው?" የሚለው ጥያቄ ሙስሊሞች ሊያውቁት የሚፈልጉት ጥያቄ ነው። ይህ ዐይነቱም ጥያቄ በአውቶቡሱ ውስጥ እንደ ነበረው ዐይነት፣ ሰዎች ተጨናንቀው በሚገኙባቸው ቦታዎችም ሆነ ረጭ ባሉ ስፍራዎች ዘወትር የሚጠየቅ ጥያቄ ነው።

ይህ የአውቶቡስ ክሥተት ከተካሄደ ከብዙ ዓመት በኋላ በኒውዮርክ የተባበሩት መንግሥታት ቢሮ በሚገኝበት አካባቢ፣ በርካታ ክርስቲያኖች ከሙስሊም የነገረ መለኮት ምሁራን ጋር የአንድ ቀን ውይይት አካሂደን ነበር። በስፍራው የሚካሄደው ውይይት፣ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች በጎበረት የሚሳተፉበት የማኅበራዊ ዕድገትና የሰላም አፈላላጊ ጥምረት መመሥረት በሚቻልበት ሁኔታ ላይ የሚመክር ነበር። ከሙስሊሙ ወገን የተገኙት ሰዎች ከፍተኛ ትምህርት ያላቸው ባለ ሙያዎች ሲሆኑ፣ ሙስሊም ወርልድ ሊግ በተባለው አስላማዊ ድርጅት ውስጥ የመሪነት ድርሻ የነበራቸውም ሰዎች የጉባኤው ታዳሚ ነበሩ።

ርእሰ ጉዳዩ ዙሪያ በመወያየት ላይ እያለን፣ የሊጉ መሪ ከምንወያይበት ርእስ ጋር በፍጹም ባልተዛመደ መልኩ ድንገት እመር ብለው፣ "የክርስቲያኖችንና የሙስሊሞችን ልዩነት በተመለከተ ማወቅ ያለብን መሠረታዊ ቁም ነገር አለ፣

ይሽውም ክርስቲያኖች በሦስት አማልክት ሲያምኑ እኛ ሙስሊሞች ግን በአንድ አምላክ ብቻ ነው የምናምነው" በማለት ተናገሩ::

በሥላሴ ላይ የሚነሡ ተቃውሞዎች

ሁሉም ሙስሊሞች በእግዚአብሔር አሐድነት/አንድነት (ቶውሂድ) ያምናሉ:: በተጨማሪም እግዚአብሔርን ሦስት አካል እንዳለው ማሰብ አንድነቱን (ቶውሂድነቱን) እንደ መጣስ አድርገው ይመለከቱታል:: ይህ አስተምህሮ በሙስሊም ትምህርት ውስጥ ትልቅ ቦታ አለው፣ ምክንያቱም ይህ ጉዳይ በቁርአን ውስጥ ሰፊ ትኩረት ስላገኘ ነው:: ርእሰ ጉዳዩን በቀጥታ እንዲሁም በማያወላዳ መንገድ መልስ ካልሰጠነው፣ በክርስቲያኖችና በሙስሊሞች መካከል እውነተኛ የሆነ መተማመንም ሆነ ፍሬያማ ውይይት ማካሄድ አይቻልም[1]::

አሕመድ እኛ በምንኖርበት ናይሮቢ በኢስትሌይ በሚገኘው ቤታችን አቅራቢያ የሚኖር ሱማሌያዊ መድረሳ (የእስልምና ትምህርት ተማሪ) ነው:: ከመስጊድ ወደ እኛ ቤት በመምጣት ላይ በነበረበት ወቅት፣ ስለ እግዚአብሔር አሐድነት (ቶውሂድነት) እያሰበ ነበር:: "ሆዲ" ብሎ ተጣራ:: ኬንያውያን ከደጅ ወደ ቤት መግባት ሲፈልጉ በቤት ያለው ሰው በር እንዲከፍትላቸው የሚጠሩት "ሆዲ" በማለት ነው:: እንዲገባ የበራችንን በር ስከፍትለት፣ "ለመሆኑ ሦስት አማልክት አሉ ብላችሁ ለማስተማር እንዴት ደፈራችሁ?" ሲል በቁጣ ጠየቀኝ::

"ግባ ግባ" ስል ጋበዝሁት፣ "ያሳሰበህን ነገር ሻያችንን ቶት እያልን ብንወያይበት ምን ይመስልሃል?" አልሁት:: አሕመድ ወደ ሳሎኑ እየገባ፣ "አይሆንም ዛሬ ከአንተ ጋር ለመቀመጥም ሆነ ሻይ ለመጠጣት በፍጹም ፈቃደኛ አይደለሁም:: በማኅበረሰባችን ውስጥ የምትዘሩት ሐሰትና ማታለል መቆም አለበት:: እግዚአብሔር አንድ (ቶውሂድ) እንጂ ሦስት አይደለም" አለ:: እኔም፣ "እኔ ራሴ የማምነው በአንድ አምላክ ብቻ ነው" ስል ከእርሱ ጋር ተፋጠጥሁ:: "ሥላሴ!" አለ በጩኸት፣ "ሥላሴ እያልህ በአንድ አምላክ አምናለሁ ማለት

[1] በትምህርተ ሥላሴ ላይ ሰፊ ማብራሪያ ከፈለጉ፣ ተስፋዬ ሮበሌ፣ *የሕሰተምህርተ ሥላሴ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት* በሚል ርእስ ያዘጋጀውን እንዲሁም አማረ መስፍንና ተስፋዬ ሮበሌ፣ *ቅድስት ሥላሴ የሕሰተምህርተ ሥላሴ መጽሐፍ ቅዱሳዊ፣ ታሪካዊና ነገረ መለኮታዊ ትንታኔ* በሚል ርእስ የጻፉትን መጽሐፍ ይመለከቷል:: የመጀመሪያው መጽሐፍ የትምህርተ ሥላሴን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ለጀማሪ አንባብያን የሚያስተዋውቅ ሲሆን፣ ሁለተኛው መጽሐፍ ደግሞ አስተምህሮውን ከመጽሐፍ ቅዱስ፣ ከታሪክና ከሥነ አመክንዮ አንጻር ይተነትናል::

አትችልም፣ የሥላሴ እምነት የመድበለ አማልክት እምነት ነው:: ይህ ደግሞ ከእግዚአብሔር አንድነት (ቶውሂድ) ጋር በቀጥታ የሚጋጭ ነው:: ይህ አምላኖና እኩያ ለሌለው እግዚአብሔር፣ አምላኖና እኩያ (ሽርክ) ማበጀት ነው:: ይህ ዐይነቱ ኀጢአት የሰው ልጆች ሊሠሩ ከሚችሉት ኀጢአት ሁሉ እጅግ የከፋው ኀጢአት ነው:: ለበደሉም ይቅርታ የለውም"::

የሥላሴ ትርጉም

"ሥላሴ ማለት የእኔና የአንተ መዋደድና መከባበር ማለት ነው" አልሁ:: አሕመድም እጅግ በመደነቅ፣ "ምን እያልህ ነው?" ሲል ጠየቀኝ:: :

"ሥላሴ ማለት የእኔና የአንተ መዋደድ ማለት ነው" በመቀጠልም "በርግጥ ሥላሴ የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አይገኝም:: በነገረ መለኮት ትምህርት ውስጥ ክርስቲያኖች ቃሉን መጠቀም የጀመሩት ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ከወረገ ከሁለት መቶ ዓመት በኋላ ነው:: ተርቱሊያን የተባለ የሰሜን አፍሪካ የነገረ መለኮት ምሁር፣ ክርስቲያኖች ስለ እግዚአብሔር ያላቸውን መረዳት ሊወክል ከቻለ በሚል፣ 'ሥላሴ' የሚለውን ቃል ጥቅም ላይ አውሉአል:: እግዚአብሔርን ከዚህ በተሻለ መንገድ የሚገልጽ ቃል ካለ፣ ያንን ቃል ልንጠቀምበት እንችላለን" አልሁት::

በእምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በሰሜን አፍሪካ ይኖር የነገረው የነገረ መለኮት ምሁር ቅዱስ አውግስጢኖስ፣ በዚሁ ርእሰ ጉዳይ ላይ ያለውን ነገር በመዋስ ገለጻዬን እንደሚከተለው አቀረብሁ፣ "እኛ ክርስቲያኖች ሥላሴ የሚለውን ቃል የምንጠቀመው የእግዚአብሔርን ፍቅር ደካማ በሆነው በሰዎች ቋንቋ ለመግለጽ በምናደርገው ሙከራ ነው:: ሥላሴ ማለት በራሱ በእግዚአብሔር ውስጥ ያለውን መስተጋብር፣ ኅብረት፣ የፍቅር ግንኙነት እንዲሁም አንድነት ለመግለጽ የምንጠቀምበት ቃል ነው:: ሥላሴ ማለት እግዚአብሔር ፍቅር ነው ማለት ነው:: ከእኛም ጋር ኅብረትን ያፈጠረው በራሱ አማካይነት የፍቅር አገልግሎት በመስጠት ለዚያም ደግሞ እኛን በመጋበዝ ነው::

እግዚአብሔር ራሱን እንዲሁም ፍቅሩን የገለጠልን፣ በመሲሑ በኢየሱስ ሕይወትና አገልግሎት ውስጥ ነው:: እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ኅብረት እንዲኖረን የጋበዘን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን በሰጠበት ፍቅርና ኅብረት ነው:: በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አማካይነትም ኢየሱስ እኛን በወደደበት ፍቅር እርስ በርሳችን እንድንዋደድ ኀይል ተሰጥቶናል::

በአጠቃላይ ሥላሴ ማለት፣ በእግዚአብሔር ውስጥ ያለ የፍቅር ግንኙነት ማለት ነው። እግዚአብሔር እርሱ ያለው ዐይነት ፍቅር እኛም እንዲኖረን ግብዣ፣ ዐቅርቦልናል።

አሕመድ በተመስጠ ያደምጠኝ ነበር፣ ነገሩም እጅግ ሳያስደንቀው የቀረ አይመስልም። ጥቂት ካሰበ በኋላ፣ "የእግዚአብሔር በሆነው ፍቅር እኛም እርስ በርስ መዋደዳችን ጥሩ ነው" የሚል አስተያየት ሰጠ።

ከዚያ በኋላ ግን አሕመድ የቅርብ ወዳጄ እንዲሁም በኢሰሊ በሚገኘው ሙስሊም ማኅበረሰብ ስለእኔ የሚሟገት ሰው ሆነ። ይህ ውይይት ሙስሊሞች ከክርስቲያኖች ጋር የሚያወዛግባቸው ርእሰ ጉዳይ ምን እንደሚመስል በተወሰነ ደረጃም ቢሆን አመላካች ነው።

ተዘውትረው የሚሰሙ ስሑት/የተሳሳቱ አስተሳሰቦች

ስለ ሥላሴና የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነው ስለ ኢየሱስ ሙስሊሞች ያላቸው ግራ መጋባት ወይም ተቃውሞ ትክክለኛ የሆነ የነገረ መለኮት መሠረት ያለው ነው። እነዚህ የነገረ መለኮት ተቃውሞዎች በአክብሮት፣ በውይይትና በምስክርነት መልስ ማግኘት አለባቸው።

ሁሉም ዐይነት ተቃውሞዎች የነገረ መለኮት መሠረት አላቸው ማለት እንዳልሆነ ግን ልብ ሊባል ይገባዋል። አብዛኛው ሙስሊም በክርስቲያኖች መሠረተ እምነት ላይ ያለው ተቃውሞ፣ ክርስቲያኖች ከሚያምኑት እምነት ጋር የተቃረነ እንዲሁም በተዛባ መረጃ ላይ የተመሠረተ ነው። ሙስሊሞች መጽሐፍ ቅዱስ በርእሰ ጉዳዩ ላይ የሚያስተምረውን ትምህርት በጠለለ ሁኔታ ይረዱ ዘንድ፣ አሁን ያለውን ግራ መጋባት በለስነ ሁኔታ ማረም ያስፈልጋል። በክርስትና መሠረተ እምነት ላይ ያላቸው መረዳት የተሳሳተ እስከ ሆነ ድረስ፣ በተለያዩ ርእሰ ጉዳዮች ላይ ከሙስሊሞች ጋር የነገረ መለኮት ውይይት ማድረግ አዳጋች ነው።

እነዚህ የተምታቱ መረዳቶች የበቀሉት የእስልምና እንቅስቃሴ ከተነሣበት ዐረባዊ ዐውድ (ሁኔታ) ነው። በምዕራፍ 2 ላይ እንደ ተመለከተው፣ መሐመድ ስብከታቸውን የጀመሩት የዐረብ አማልክቶች እርስ በርስ ተጋብተው ልጅ እንደሚወልዱ በሚታመንበት ማኅበረሰብ ውስጥ ነው። ስለዚህም በሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩ የዐረብ ክርስቲያኖች፣ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው የሚለው አነጋገራቸው መሐመድን ክፉኛ አወካቸው። ይህ ሐሳብ

አማልክት እርስ በርሳቸው ተጋብተው ልጅ ይወልዳሉ፣ ከሚለው የመድብለ አማልክት አምላክያን ሐሳብ ጋር ተመሳስለባቸው።

አስደናቂው ቁም ነገር፣ በሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ይኖሩ የነበሩ እነዚህ የዐረብ ክርስቲያኖች ሥላሴ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ መሆኑን ያለመረዳታቸው ነው። ስለዚህም ማርያም የእግዚአብሔር እናት ስለሆነች የሥላሴ አካል ነች ይሉ ነበር። ስለዚህ ሥላሴ ማለት አብ፣ ማርያምና ኢየሱስ ሲሆኑ፣ እነርሱም ሦስት አማልክት ናቸው የሚል የተሳሳተ አስተሳሰብ ነበራቸው። በወቅቱ የነበሩት አብዛኞቹ ክርስቲያኖች አሁን ባለው መልኩ መጽሐፍ ቅዱስ እንደ ልብ በእጃቸው ያለመኖሩ፣ ለዚህ ችግር ዋነኛ ምክንያት ተደርጎ ይወሰዳል። ቁርአን የሥላሴን አስተምህሮ የሚቃወመው ከዚህ ዐይነቱ የመድብለ አማልክት አስተሳሰብ አንጻር ቆሞ ነው። ቁርአን የሥላሴ አስተምህሮ እጅግ ጸያፍና ውጉዝ ነው ሲል፣ እግዚአብሔር ሚስት አግብቶ በወሲባዊ ግንኙነት ልጅ አይወልድም የሚለውን የአረማውያንን አስተሳሰብ ታሳቢ ባደረገ መልኩ ነው (ሱራ 5፡75፣ 6፡100-101)። በየዘመናቱ ያለው የሙስሊም ኡማ ስለ ሥላሴ ያለው ግንዛቤ፣ ይህ ዐይነት አመለካከት ባለው የቁርአን አስተምህሮ የተቃኘ ስለሆነ፣ በየዘመናቱ ያሉ ሙስሊሞች ሥላሴን ከአረማውያን የመድብለ አማልክት አስተሳሰብ ጋር በማነጻጸር አስተምህሮውን እንዲቃወሙ አድርጎአቸዋል።

ቁርአን ክርስቲያኖች ስለ ሥላሴ ያላቸውን የአብ፣ የወልድንና የመንፈስ ቅዱስን ትምህርት በተመለከተ የሚናገረው አንዳችም ነገር የለም። የኢየሱስን ከእግዚአብሔር ጋር መስተካከል የተቃወመው የቁርአን ጥቅስ፣ ኢየሱስ መሲሕ እንዲሁም የእግዚአብሔር መንፈስ እንደ ሆነ ይናገራል (ሱራ 4፡171)። እነዚህ የተሳሳቱ ሐሳቦች ሙስሊሞች ስለ ሥላሴ ያላቸውን ግንዛቤ በትክክለኛው ትምህርት ለማረቅ/ለማስተካከል የሚደረገውን ጥረት አስቸጋሪ ቢያደርጉትም፣ የልብ ስፋቱ እስካለ ድረስ፣ ለውይይት ያለው ተስፋ ተሟጦአል ማለት አይደለም።

የሆነ ሆኖ እስላማዊ ነገረ መለኮት የጸበረው፣ የክርስቲያኖችን ቅዱሳት መጻሕፍት ባላገናዘበ ሁኔታ ነው። ከዚህም የተነሣ ሙስሊሞች ቁርአንን ሲተረጉሙ ቁርአንንና ሐዲስን መሠረት በማድረግ ብቻ እንጂ፣ ስለ መንፈስ ቅዱስ ወይም ስለ መሲሑ የእግዚአብሔር ቃልነት መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን ትምህርት ባገናዘበ መልኩ አይደለም።

ስለዚህ ሙስሊሞች፣ "የእግዚአብሔር መንፈስ መልእኩ ገብርኤል ነው" እንዲሁም "ኢየሱስ ተአምራዊ በሆነ ሁኔታ በእግዚአብሔር ቃል የተፈጠረ ፍጥረት እንጂ፣ እርሱ ራሱ የእግዚአብሔር ቃል አይደለም" ባይ ናቸው::

ለሙስሊሞች የማሰናከያ ዐለት የሚሆንባቸው የእግዚአብሔር ሥላሴነት፣ ወይም ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ የመሆኑ ጉዳይ ብቻ አይደለም:: የተሳሳቱ ሌሎች ግንዛቤዎችም አሉ:: ለምሳሌ ክርስቲያኖች መሲሕ የሚሉት እግዚአብሔር አብን እንደ ሆነ ቁርአን ያስተምራል:: ይህን ጉዳይ በተመለከተ ቁርአን እንዲህ ሲል ያስጠነቅቃል፣ "እነዚያ አላህ እርሱ የመርየም ልጅ አልመሲሕ ነው ያሉ በእርግጥ ካዱ" (ሱራ 5+17)::

ክርስቲያናዊው ነገረ መለኮት መሲሑ እግዚአብሔር አብ ነው የሚል አንዳችም ትምህርት የለውም:: ይህ ማለት ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረ ጊዜ የጽንፈ ዓለሙ ሁሉ አምላክ ኢየሱስ ነበር እንደ ማለት ነው:: ይህ ትክክል አይደለም:: ኢየሱስ አዘውትሮ አፍቃሪው ወደ ሆነው ሰማያዊ አባት ይጸይል የነበረ መሲሕ ነው:: በእግዚአብሔርም ላይ ይደገፍ ነበር:: ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሚያስተምሩት ኢየሱስ በእግዚአብሔር ላይ የማይደገፍ አልነበረም:: መሲሑ ኢየሱስ እግዚአብሔር አብን የሚታዘዝና ከእርሱም ጋር ጠንካራ የሆነ ኅብረት ነበረው:: ከኢየሱስ ጋር ኅብረት ማድረግ ማለት ከአብ ጋር መተዋወቅ ማለት ነው (ዮሐንስ 14+6-11):: የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት መሲሑ ኢየሱስ አምላክ እንደ ሆነ ቢያስተምሩም፣ ኢየሱስ እግዚአብሔር አብ ነው የሚል ትምህርት ግን የላቸውም:: አብና ወልድ የተለያዩ አካላት ናቸውና[2]::

ቁርአን ውስጥ በተደጋጋሚነት የሚስተዋለው ሌላው ችግር፣ ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ጋር አቻ/እኩያ (አጋሮች) ነን ይላሉ የሚለው ትምህርቱ ነው:: እግዚአብሔር አቻና እኩያ የለውም፣ እግዚአብሔር እግዚአብሔር ነው:: ቁርአንም ቢሆን ከዚህ እውነት ጋር ይስማማል (ሱራ 6+22-23: 136-37: 163):: አንድ የቁርአን ምንባብ፣ በሁለት አግልክት የሚያምኑ ሰዎችን ይኮንናል (ሱራ 16+51):: ከእነዚህ የቁርአን ምንባባት ውስጥ አንዳንዶቹ የአረማውያንን መድብለ አግልክት እምነት የሚቃወሙ ናቸው:: ይሁን እንጂ አንዳንዶቹ ምንባባት በግልጥም ሆነ በስውር (በውስጠ ወይራ) ክርስቲያኖችን የሚመለከቱ ናቸው::

[2] በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ ሰፊ ማብራሪያ ከፈለጉ፣ ተስፋዬ ሮበሌ፣ *ሰባልዮሳውያን "የሐዋርያት ቤተ ክርስቲያን" የሥላሴ አስተምህሮ በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን* በሚል ርእስ ያዘጋጀውን መጽሐፍ ይመለከቷል::

በተሳሳተ ግንዛቤ ላይ የተመሠረተው ስሑት/ስሕተት የሆነው ይህ የቁርአን አተያይ፣ በየትኛውም አካባቢ በሚገኙ ሙስሊሞች ዘንድ በግልጽ ይስተዋላል:: ለምሳሌ ከክርስቲያን ባልንጀሮቹ ጋር በመሆን፣ በአራት የተለያዩ ከተሞች ውስጥ በሚገኙ መስጊዶች ያካሄድኋቸው ጉብኝቶች ይህንኑ ጉዳይ የሚያጸኑ ናቸው:: በአራቱም መስጊዶች የሚገኙት ኢማሞች በተመሳሳይ መንገድ እንዲህ አሉ፣ "እግዚአብሔር ልጅ ይወልዳል ማለት ለእግዚአብሔር አቻና እኩያ አለው እንደ ማለት ስለሆነ፣ በእግዚአብሔር ሬት የሸርክ ኀጢአት መፈጸም ነው:: ይህ ደግሞ ኮነጢአቶች ሁሉ የከፋው ኀጢአት ነው:: የሸርክ ኀጢአት ንስሓ የለውም:: እግዚአብሔር ልጅ ይወልዳል የሚል ማንኛውም ሰው ወደ ሲኦል ይሄዳል"::

እነዚህ ኢማሞች ይህን ነገር ደጋግመው የነገሩን ለእኛ ግድ ስላላቸው ነው:: ይህን መሰሉን የማስጠንቀቂያ መልእክት በቀጥታ የሚነግሩንም ለዚሁ ነው:: በእነዚህ አጋጣሚዎች ሁሉ ኢማሞቹ ምናልባት በተግሣጻችን አስተይመናቸው ይሆናል ብለው ስለፈሩ፣ ከተግሣጻቸው በኋላ ይቅርታ ይጠይቁን ነበር:: ይሁን እንጂ ልናስቀይማቸው እንችላለን በሚል ይህን ጉዳይ ከመናገር ቸል አላሉም::

እርግጥ ነው ክርስቲያኖች እግዚአብሔር አቻና እኩያ አለው ሲሉ አይገባም:: በአዲስ ኪዳን እግዚአብሔር ራሱን በመሲሑ በኩል በሙላት ገለጠ የሚለው ነገረ መለኮት፣ እግዚአብሔር ሁለት ወይም ሦስት ነው ወይም ደግሞ እግዚአብሔር አቻና እኩያ አለው ማለት በፍጹም አይደለም:: ይህ ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ከሆነው እምነት እጅግ የራቀና ፍጹም የተዛባ ስለሆነ፣ ቤተ ክርስቲያን ከሙስሊሙ ማኅበረሰብ (ኡማ) ጋር ውይይት በምታደርግበት በማናቸውም ጊዜና በየትኛውም ቦታ፣ ይህን የተውገረገረና የተምታታ ሐሳብ የማስተካከል ትልቅ ኀላፊነት አለባት::

ትክክለኛ የሆነ መረጃን መሠረት ያላደረገው ይህ የተዛባ አስተሳሰብ፣ ሁኔኛ ማስተካከያ እስካልተበጀለት ድረስ፣ ቤተ ክርስቲያን ራሱን በመሲሑ በኢየሱስ አማካይነት እንደ አዳኝና እንደ ቤዛ የገለጠውን አምላክ ለሙስሊሞች መግለጥ አትችልም:: ይህ የተምታታ መረጃ፣ እግዚአብሔር በመሲሑ ሆኖ እኛን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበር የሚለውን የወንጌል ትምህርት እንዳይቀበሉ መሰናክል ይሆንባቸዋል (2ቆሮ 5+18)::

ስለ እግዚአብሔር ልጅ ማብራራት

ከላይ እንደ ተገለጸው፣ ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ልጅነት ላይ የተፈጠረውን ይህ ዐይነቱን ግራ መጋባት ለማስተካከል፣ በክርስቲያኖችና

በሙስሊሞች ባልንጀርነት ውስጥ ጠንካራ የመተማመን ግንኙነት እስኪፈጠር ድረስ መቆየት ያስፈልጋል ማለት የለባትም። ርእሰ ጉዳዩ የሙስሊሞችን አእምሮ ክፉኛ የሚረብሽ ጉዳይ ቢሆንም፣ ቤተ ክርስቲያን በቄራዋነት ልትናገረው የሚገባ እውነት ነው። በዚህ ረገድ የሐዋርያው የጴጥሮስ ምክር ግለፈያ ነው፦—

> ማንፈራራታቸውንም አትፍሩ አትናወጡም፣ ጻሩ ግን ጌታን እርሱም ክርስቶስ በልባችሁ ቀድሱት። በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያት ለሚጠይቀአችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ፣ ነገር ግን በየዋህነትና በፍርሓት ይሁን። በክርስቶስ ያለውን መልካሙን ኑሮአችሁን የሚሳደቡ ሰዎች ክፉን እንደምታደርጉ በሚያሙበት ነገር እንዲያፍሩ፣ በጉ ኅሊና ይኑራችሁ። የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲህ ቢሆን ክፉ ስለማድረግ ሳይሆን በጉ ስለማድረግ መከራን ብትቀበሉ ይሻላችኋል (1ጴጥ 3÷15-17)።

አንድ ምሽት የቀዶ ጥገና ሐኪም የሆኑት ዶክተር ዓሊና እኔ፣ በአንድ የፊላደልፊያ ጉዳና ላይ በሚገኝ መስጊድ ውስጥ ውይይቶችን እንመራ ነበር። በስብሰባው ሃምሳ የሚሆኑ ሰዎች የሚገኙ ሲሆን፣ የሙስሊሞቹና የክርስቲያኖቹ ቍጥር እኩል ነበር።

ዶክተር ዓሊ፣ "እኛ መሲሑ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው የሚለውን ሐሳብ ሙሉ በሙሉ አጥብቀን እንቃወማለን፣ ለእግዚአብሔር አጅና እኩያ ማበጀት እግዚአብሔርን መሳደብ ነው" አሉ በለጽንኦት።

"ለዚህ ንግግርዎ መልስ እንድሰጥዎ ይፈቅዱልኛል?" ሰል ፈቃድ ጠየቅሁ። ጥሩ ወዳጄ የሆኑት ዶክተር ዓሊም፣ "እንዴታ! ትችላለህ" አሉኝ።

ትልቅ አክብሮት በተሞላበት ሁኔታ ለአምስት ደቂቃ ያህል ስለ ክርስትና እምነት ለማብራራት ሙከራ አደረግሁ፦— "ክርስቲያኖች ሁሉ እግዚአብሔር ወሲባዊ ግንኙነት አድርጉ/ሚስት አግብቶ የልጅ አባት ሆነ የሚል አንዳችም እምነት የላቸውም። ይህ በጭራሽ ተቀባይነት የሌለው ነገር ስለሆነ ልናስወግደው ይገባል! ለእግዚአብሔር አጅና እኩያ ማበጀትም በመጽሐፍ ቅዱስ የተወገዘ ጉዳይ ነው። እኛም በሁለት ወይም በሦስት አግልክት በጭራሽ አናምንም"።

ነገር ግን እግዚአብሔር ራሱ መሲሑን "ልጄ" ሲል ጠርቶታል። በመሲሑ በኢየሱስ አገልግሎት ውስጥ እግዚአብሔር ሁለት ጊዜ ከሰማይ "የምወደው ልጄ ይህ ነው" ሲል ተደምጦአል። እግዚአብሔር መሲሑን የምወደው ልጄ

እርሱ ነው ሲል ምን ማለት ፈልጎ ነው የሚለውን ጉዳይ መመርመር ያለብን እኛ ነን። በራሱ በቁርአን እንኳ እግዚአብሔር መሲሑን "የምወደው ልጄ" ያለበት ሁኔታ አለ። እንዲሁም መሲሑ ካሊማቱኢላሂ (የእግዚአብሔር ቃል) ተብሎአል (ሱራ 4÷171)።

ዶክተር ዓሊም ለዚህ ንግግሬ እንዲህ ሲሉ ተቃውሞአቸውን አቀረቡ። "በእርግጥ መሲሑ የእግዚአብሔር ቃል ነው። ይህ ማለት ግን የእግዚአብሔር ልጅ ነው ማለት አይደለም። በእግዚአብሔር ኪነ ጥበባዊ አሠራር እግዚአብሔር ቃል በሚናገርበት ጊዜ መሲሑ በእናቱ ማሕፀን ውስጥ ተፀነሰ። የእግዚአብሔር ቃል አዳምን እንደ ፈጠረው፣ በተመሳሳይ መንገድ የእግዚአብሔር ቃል መሲሑን በድንግል ማሕፀን ውስጥ እንዲፀነስ አደረገ"።

እኔም በመቀጠል፣ "'ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው' ለሚለው ቁርአናዊ ሐረግ ለተሰጠኝ ሙስሊማዊ ትንተና አመሰግናለሁ። ኢንጂልም (ወንጌልም) መሲሑ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ይናገራል። መጽሐፍ ቅዱስ መሲሑን 'የእግዚአብሔር ቃል' ሲለው፣ ምን ማለት ፈልጎ ነው የሚለውን ጉዳይ በዚህ ምሽት ሳብራራ በጥሙና እንድታዳምጡኝ እፈልጋለሁ" አልሁ።

"ሙስሊማን እንደ መሆናችሁ መጠን፣ በሰግያት ስለሚገኘው የመጻሕፍት ሁሉ እናት ዐልፎ ዐልፎ ትናገራላችሁ (ሱራ 3÷7፣ 13÷39፣ 43÷4)። ይህ መጽሐፍ የማይለወጥና ያልተፈጠረ እንዲሁም በወርቅ ጽላት ላይ የተጻፈ መጽሐፍ ነው የሚል እምነት አላችሁ። በእርግጥ የወርቅ ጽላት የሚለው ገለጻ ተምሳሌታዊ ዘይቤ መሆኑ ግልጽ ነው። እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ራሱን የሚገልጽ አምላክ ስለሆነ፣ ቃሉ ሕያው ነው። በእግዚአብሔር ዘንድ ደግሞ ውሸት ስለሌለ ቃሉ ዘወትር ስለ እግዚአብሔር ማንነት ትክክለኛ የሆነ መረጃ ይሰጣል። በእግዚአብሔር ቃልና በእግዚአብሔር መካከል አንዳችም ልዩነት የለም"።

"የክርስቲያን ቅዱሳት መጻሕፍት እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን ምስክርነት እንደሚያሰረዳው፣ መሲሑ ሰው ሆኖ የተገለጠ የእግዚአብሔር ቃል ነው። ሕያው የሆነው፣ ፈጣሪ ዐቅም ያለው እንዲሁም የሚቤዥው የእግዚአብሔር ቃል፣ በጽላት ላይ ብቻ ሊወሰን በፍጹም አይችልም። ይልቁንም ሕይወት ሰጪ የሆነው የእግዚአብሔር ቃል ሰው በመሆን በመካከላችን ተመላለሰ። እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል ለማወቅ ከፈለግን፣ ከመሲሑ ጋር መገናኘት ግድ ይሆናል። እግዚአብሔር ራሱን በመካከላችን በሙላት የገለጠው በመሲሑ አማካይነት ነው። ስለዚህም በቃሉና በእግዚአብሔር መካከል አንዳችም ልዩነት የለም።

"የእግዚአብሔር ልጅ ማለት በሰው አምሳል የተገለጠ የእግዚአብሔር ቃል ማለት ነው። የእግዚአብሔር ልጅ የሚለውም ስያሜ ግንኙነትን አመላካች ቃል መሆኑ ብቻ ሳይሆን መሲሑ ከእግዚአብሔር ጋር ፍጹም የሆነ የፍቅር ግንኙነት እንዳለው የሚያሳይ ነው። ለዚህም ነው መሲሑ ኢየሱስ 'እኔና አብ አንድ ነን። እኔንም ያየ አብን አይቶአል' (ዮሐንስ 14÷8-10) ሲል የተናገረው"።

"በመሲሑ አገልግሎት እኛም እግዚአብሔር ሰማያዊ አባታችን መሆኑን እንድናውቅ ተጋብዘናል። መሲሑ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው። ከሰማይ አባቱ ጋር የነበረውም ግንኙነት ፍጹም ነበር። እኛም በመሲሑ በኩል የእግዚአብሔር ቤተ ሰቦች እንዲሁም ወንድና ሴት ልጆች ለመሆን ተጠርተናል/ተጋብዘናል (ኤፌሶን 1÷5)"።

ከረዥም ዝምታ በኋላ ዶክተር ዓሊ፣ "ነገሩ እንዲህ ከሆነ ግመን እችላለሁ" አሉ።

በርካታ ወንጌላት

ይህ ዐይነቱ ውይይት ሙስሊሞች በክርስቲያኖች ላይ ላላቸው ተቃውሞ ሁሉ መፍትሔ እንደግይሰጥ እሙን ነው። ሙስሊሞች አዲስ ኪዳንን በተለይም ወንጌልን ሲያነቡ፣ ከዚህ የተለዩ በርካታ የሆኑ መሰናክሎች ይጋረጡባቸዋል። የናይሮቢን መስጊድ ከበርካታ ሰዎች ጋር ሆነን በመጐብኘት ላይ ሳለን፣ አንድ የእስልምና ሃይማኖት ምሁር እንዲህ ሲሉ ጥያቄ ጠየቁ፣ "የመሲሑ የኢየሱስ ወንጌል የት ነው ያለው? አዲስ ኪዳን የአራት ሰዎችን ወንጌል ይዟል እንጂ የመሲሑን ወንጌል አልያዘም። ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲያርግ ወንጌሉን ይዞ መሄዱ ግልጽ ነው"።

ይህ ዐይነቱ ግራ የተጋባ ጥያቄ ከሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ጋር የተወሰነ ትውውቅ ባላቸው በበርካታ የሙስሊም ሃይማኖት ምሁራን ዘንድ በስፋት የተሠራጨ ትምህርት ነው። ሙስሊሞች ቁርአን አንድ ነው ነገር ግን ወንጌል በአራት የተለያዩ ሰዎች የተጻፈ እንዲሁም የመሲሑን ወንጌል ያላካተተ መጽሐፍ እንደ ሆነ ያስባሉ። ከአራቱ ወንጌላት መኻል የመሲሑ ወንጌል የለም የሚለው አስተሳሰብ፣ ሙስሊሞችን ወደ ተሳሳተ ድምዳሜ መስጂቸዋል።

በዚያን ወቅት በናይሮቢው መስጊድ ውስጥ አብረውን ከነበሩ ሰዎች መኻል አንዱ፣ "በዐረብኛው ቁርአን መሲሑ ኢየሱስ 'ኢንጅል' (መልካሙ ዜና/የምሥራች) ተብሎ ተጠርቶአል (ሱራ 3÷45)። ኢንጅል ማለት መልካም

የምሥራች ወይም ወንጌል ማለት ነው። መሲሑ ኢንጅል የተባለበት ምክንያት እርሱ ራሱ ወንጌል ስለሆነ ነው። ክርስቲያኖችም ኢየሱስ ወንጌልን ከሰማይ ይዞ መጥቶአል ብለው ሳይሆን፣ እርሱ ራሱ ከሰማይ የመጣ ወንጌል ነው የሚል እምነት ነው ያላቸው። እርሱ ሰው ሆኖ የተገለጠ የእግዚአብሔር ቃል ነው። ስለዚህ ወንጌል መጽሐፍ ሳይሆን ሰው ነው፣ ይኸውም ሰው ሆኖ የተገለጠው የእግዚአብሔር ቃል መሲሑ ኢየሱስ ነው"።

"ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስና ዮሐንስ ወንጌል ስለሆነው ስለ ኢየሱስ የራሳቸውን ምስክርነት ሰጥተዋል። እነዚህ አራት ሰዎች ስለኢየሱስ ሕይወትና ትምህርት አንድ ዐይነት ምስክርነት ባይሰጡን እንዲሁም ስለ ኢየሱስ ሕይወትና ትምህርት የዘገበልን አንድ ሰው ብቻ ቢሆን ኖሮ፣ ግለሰቡ የዘገበውን ዘገባ ተአማኒነት ማረጋገጥ አይቻልም ነበር። ነገር ግን እነዚህ አራት ምስክሮች በተለያየ መንገድ አንድ ዐይነት ምስክርነት መስጠታቸው የዘገባቸውን ትክክለኛነት የሚያስረግጥ ነው። በሕግ ችሎት ላይ የአራት ሰዎች ምስክርነት ከፍተኛ የሆነ ተቀባይነት አለው"።

"ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስና ዮሐንስ ስለ መሲሑ የራሳቸውን ምስክርነት በሚያቀርቡበት ጊዜ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ መርቶአቸዋል። ስለዚህም ስለ ኢየሱስ ሕይወት፣ ትምህርትና አገልግሎት የሰጡት ምስክርነት እውነት እንደ ሆነ እናምናለን"።

ይህ በዓለም ዙሪያ በሚገኙ ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች፣ እውነተኛ ለሆነ ውይይትና መደማመጥ ራሳቸውን በአዘጋጁበት ስፋራ ሁሉ ሊገኝ የሚችል ተምሳሌታዊ ውይይት ነው። ሙስሊሞች መሲሑ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው የሚለውን ጉዳይ ለመቀበል የሚቸገሩበትን ምክንያት ክርስቲያኖች በውል ማወቅ ይፈልጋሉ። በተለይ ሙስሊሞች ስለ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ስለ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅነት፣ ስለ ትምህርተ ሥላሴ ወዘተ ያላቸው አሉታዊ አመለካከት ከየት የመጣ እንደ ሆነ እንዲሁም እነዚህን ትምህርቶች ላለመቀበል ምክንያት የሆናቸውን የነገረ መለኮት መሠረት ማወቅ ይፈልጋሉ። የተዛባው ምልከታ በትክክል ከተመለሰ በኋላ ነው የነገረ መለኮት ውይይቱ መካሄድ የሚኖርበት። ሙስሊሞች አዲስ ኪዳን ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ሲል ምን ማለቱ ነው፣ የሚለውን ጉዳይ በትክክል መረዳት አለባቸው። ክርስቲያኖች ትልቅ ዋጋ የሚሰጡትን እውነት ማለትም እግዚአብሔር በመሲሑ በኩል እኛን የማስታረቁን እውነት ሙስሊሞች ሊገነዘቡ የሚችሉት፣ በቤተ ክርስቲያንና በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት አማካይነት ብቻ ነው።

ወንጌልና ቁርአን

መሲሑ ኢየሱስን ከመሐመድ ጋር በማነጻጸር ማቅረብ፣ መሲሑ በክርስትና መሠረተ እምነት ውስጥ ያለውን ሁነኛ ስፍራ እንዲሁም መሐመድ በእስልምና ሃይማኖት ውስጥ ያላቸውን ዐቢይ ቦታ ክፉኛ የሚያበላሽ ነው:: ለዚህም አንዱ ምክንያት ሙስሊሞች ቁርአን በመሐመድ በኩል መጣ ብለው ሲያምኑ ክርስቲያኖች ኢየሱስ ወንጌል አምጪ ሳይሆን፣ እርሱ ራሱ ወንጌል ነው የሚለው እምነታቸው ነው::

"ሙስሊሞች እንደ መሆናችሁ መጠን፣ እግዚአብሔር ቁርአንን የገለጠው በመሐመድ በኩል ነው የሚል እምነት አላችሁ፣ አይደለም እንዴ?" ስል በፈላደልፊያ መስጊድ ለተሰበሰቡት ሙስሊሞች ጥያቄ አቀረብሁ:: የመስጊዱም ኢማም፣ "አዎን ትክክል ነው" አሉኝ::

በመቀጠልም የሚከተለውን ነጥብ ተናገርሁ፣ "ሙስሊሞችም ሆኑ ክርስቲያኖች መሲሑ ኢየሱስ ከድንግል ማርያም የመወለዱን እውነት ይቀበላሉ:: ራሱ ወንጌል የሆነው መሲሕ ወደ ዓለም የመጣው በድንግል በኩል ነው:: ሙስሊሞች ቁርአን በነቢዩ መሐመድ በኩል መምጣቱን ይቀበላሉ:: ድንግሊቱ መሲሑ ወደ ምድር የመጣባት ሰብአዊ መሣሪያ (ምክንያት) ስትሆን፣ መሐመድ ደግሞ ቁርአን የተገለጠባቸው ሰብአዊ መሣሪያ ናቸው"::

እውነታው ምንድን ነው?

መሲሑም ሆነ ቁርአን በየራሳቸው ለቤተ ክርስቲያንና ለሙስሊሙ ማኅበረሰብ (ኡማ) የእውነት ማዕከል ናቸው:: ሁለቱም ወገኖች፣ ኢየሱስም ሆነ ቁርአን መሠረታዊ የሆኑ እውነታዎችን እንደ ገለጹ ያምናሉ:: ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፣ "እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፣ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም" (ዮሐንስ 14÷6):: በሌላ ስፍራ፣ "እናንተ በመጻሕፍት የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ይመስላችኋልና እነርሱን ተመረምራላችሁ፣ እነርሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው:: ነገር ግን ሕይወት እንዲሆንላችሁ ወደ እኔ ልትመጡ አትወዱም" (ዮሐንስ 5÷39):: ኢየሱስ በማመንና ባለማመን መካከል ልዩነት እንዳለም ተናግሮአል (ዮሐንስ 12÷35-50)::

በቁርአንም "ያም ከመጽሐፍ ወዳንተ ያወረድንልህ ከበፊቱ ላለው አረጋጋጭ ሲኾን እርሱ እውነት ነው" (ሱራ 35÷31):: ቁርአን የእውነት ሁሉ መለኪያ

እንደ ሆነ ይታመናል:: ይህም ጉዳይ እውነተኛ አማኞችንና እውነተኛ አማኞች ያልሆኑትን ሰዎች የሚለይ ጉዳይ እንደ ሆነ ይታሰባል (ሱራ 84÷20-25)::

በመሐመድ የተነገረው ቁርአንና ከድንግል ማርያም የተወለደው መሲሑ ኢየሱስ፣ የፍጹማዊ እውነት መስፈርትን በተመለከተ የሚያስተላልፉት መልእክት እርስ በርሱ ሊወዳደር/ሊነጻጸር የሚችል ነው:: መሲሑ በሰው አምሳል የተገለጠ የእግዚአብሔር ቃል ሲሆን፣ ቁርአን ደግሞ በመጽሐፍ መልክ የተገለጠ የእግዚአብሔር ቃል ነው:: የእውነት ማዕከል የሆነው ቁርአን ነው ወይስ መሲሑ የሚለው ጥያቄ ምን ለውጥ ሊያስከትል ይችላል? አንዳንድ የነገረ መለኮት ሰዎች ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች፣ ኢየሱስንም ሆነ ቁርአንን በመያዝ የሚፈጥሩትን ክርክር ዕርግፍ አድርገው በመተው፣ ውይይታቸውን በእግዚአብሔር ላይ ብቻ ያድርጉ ሲሉ ይመክራሉ:: ምክንያቱም እርስ በርስ የሚያግባባቸውን መሠረት የሚያገኙት በእግዚአብሔር ላይ ብቻ ነው የሚል ግምት ስላላቸው ነው::

ነገር ግን ያግባባል የተባለው እግዚአብሔር ራሱ ማነው? በርግጥ እርሱ አምባገነን ነውን? በርግጥ እርሱ ሰዎችን ያፈቅራል ወይስ ይጠላል? እርሱ ለሰው ልጆች የገለጠው ፈቃዱን ብቻ ነው ወይስ ራሱን/ማንነቱን ጨምሮ ነው? የሕይወት ትርጉሙና የሰው ልጆች የመጨረሻ ዕጣ ፈንታ ምንድን ነው? እነዚህንና እነዚህን መሰል ጥያቄዎች የምንመልሰው ከእግዚአብሔር ዘንድ ተገልጠዋልናል ከምንለው መገለጥ አንጻር እስከ ሆነ ድረስ የትኛውን መገለጥ ተከትለን እንሂድ የሚለው ጉዳይ እጅግ መሠረታዊ ነጥብ ይሆናል::

በእርግጥ በመጽሐፍ ቅዱስና በቁርአን መሠረታዊ አስተምህሮ ላይ ስምምነቶች አሉ:: ይሁን እንጂ፣ ጳጳስ ኬኔት ክራግ ጥሩ አድርገው እንደ ገለጹት በእያንዳንዱ ስምምነት ላይ ልዩነት አለ:: ለዚህም ምክንያቱ መሲሓዊ የሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችና የሙስሊሞኑ ቁርአን ወደ ተለያየ አቅጣጫ ስለሚወስዱን ነው::
መጽሐፍ ቅዱሳዊው መሠረተ እምነት፣ እግዚአብሔር በመሲሑ አማካይነት እርሱ ራሱ በኀጢአት በተበላሸው ሕይወታችን ውስጥ ጣልቃ በመግባት፣ ከኀጢአታችንና ኀጢአታችን ካስከተለው ሞት ዐርነት እንዲወጣን ያስተምራል:: እግዚአብሔር በመሲሑ አማካይነት ከራሱ ጋር እንዲሁም እርስ በርሳችን እንዲሁም ደግሞ ከፍጥረት ጋር እንድንታረቅ እርሱ ራሱ በፍቅር ጠራን:: ቁርአን ደግሞ በአንጻሩ ርኅሩኅና አዛኝ የሆነው አምላክ ፈቃዱን ከሰማይ ወደ ምድር እንደ ላከልን እንዲሁም ለፈቃዱ በመገዛት መልካምን ነገር

እንደምናገኝ ያስረዳል። ኢየሱስ የመቤዠትን ሥራ ሲሠራ ቁርአን ግን ምሬትን ይሰጣል።

<u>ሰንድነት-ተሰሰኮ-ሰዋነት</u>

እግዚአብሔር አንድ (ቶውሂድ) ነው። እግዚአብሔር አብ፣ እግዚአብሔር ወልድ፣ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ (ሥላሴ) አንድ አምላክ ነው። ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች ስለ እግዚአብሔር ያላቸው ይህ ምልከታ የመነጨው መጻሕፍቶቻቸውን፣ ምስክርነታቸውንና ተልእኮአቸውን በታማኝነት ለመግለጽ ካላቸው ብርቱ ፍላጐት ነው።

ይህ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች ስለ እግዚአብሔርና ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ ያላቸው የተለያየ መረዳት ሊመጣ የቻለው፣ ረጅም በሆነ የእምነት ጉዞ ነው። ይህ ዐይነቱ እምነት በምንኖርባት ምድር ስለ አንድነትና በአንድነት ላይ መሠረት ስላደረገ ልዩነት ትልቅ የሆነ ተሞክሮአዊ እንድምታ ያስከትላል። እነዚህ የተለያዩ መረዳቶች የሙስሊሙ ማኅበረሰብና ቤተ ክርስቲያን ስለ ሚስዮናዊነት ባላቸው ግንዛቤ ላይ ጉልሕ ሚና አላቸው።

የሙስሊሙ ማኅበረሰብ (ኡማ) እግዚአብሔር አንድ ነው (ቶውሂድ) የሚለውን ያህል ክርስቲያኖችም እግዚአብሔር አንድ ነው የሚለውን ጉዳይ ከሙሉ ልብ ይቀበላሉ።

አንድ ክርስቲያን ሥርዐተ ጥምቀትን በሚወስድበት ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ሥርዐቱን የምትፈጽመው በእግዚአብሔር አብ፣ በእግዚአብሔር ወልድና በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ስም ነው። በአጠቃላይ ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን በተለይም ሥርዐተ አምልኮ፣ አንቀጸ ሃይማኖትና የሃይማኖት መግለጫዎች ሁሉ መሠረት ያደረጉት አብን እንደ ፈጣሪ፣ ወልድን እንደ አዳኝ/መሲሕ እንዲሁም መንፈስ ቅዱስን በክርስቲያኖች ውስጥ እንደሚኖረው የእግዚአብሔር መንፈስ፣ ራሱን በአንድነትም ሆነ በሦስትነት ለገለጠልን አምላክ በምንሰጠው የእምነት ምላሽ ላይ ነው። ይህ እንግዲህ በእግዚአብሔር ውስጥ ያለ አንድነትና ብዙኃነት ነው።

እግዚአብሔር እንደ ሥላሴ ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ በማድረሱ ሂደት ውስጥ ትልቅ ድርሻ አለው። እግዚአብሔር አብ አንድያ ልጁን ላክ! እግዚአብሔር አብ መንፈስ ቅዱስን ላክ! ይህ ፍቅር የሆነው እግዚአብሔር በድነት ሥራ ውስጥ

ቀጥተኛ ተሳትፎ እንዳለው አመላካች ነው። እግዚአብሔር እንደ ሥላሴ ፈቃዱን ብቻ ሳይሆን፣ ራሱንም ጭምር ነው ይፋ ያደረገው። ኀጢአተኞችን በመውደዱ ኀጢአተኞችን ሊያድን ፈቀደ። ይህ ዛሬ ቤተ ክርስቲያን ለዓለም ያላት ትልቅ የምሥራች እንዲሁም ጥሪ ነው። እግዚአብሔር ልጁን ወደ ዓለም እንደ ላከ፣ ቤተ ክርስቲያንንም ወደ ዓለም ልኳታል። ለምን? መሲሑ ኀጢአተኞችን ሁሉ ወዶ በፍቅር ሊያገለግላቸውና ሊያድናቸው በጐ ፈቃዱ እንደ ሆነ ሁሉ፣ ቤተ ክርስቲያንም የጠፉትን ልትፈልግ፣ ልትወድና ልታገለግል ኀላፊነት ስላለባት ነው።

በእግዚአብሔር ራስን የመስጠት ፍቅር ውስጥ አንድነት እንዲሁም አንድነትን መሠረት ያደረገ ልዩነት አለ የሚለው የእምነት አንቀጽ፣ ዐበይት በሆኑ አስተምህሮዎች ላይ መሠረት ላደረገው የቤተ ክርስቲያን አንድነት እንዲሁም ንዑሳን/ደቂቃን ለሆኑ ትምህርታዊ ልዩነቶች መሠረት ጥሎአል። የቤተ ክርስቲያን አንድነት የተመሠረተው በፍቅር ራስን በመስጠት መሠረት ላይ ነው፤ ይኸውም እግዚአብሔር ለእኛ ራሱን አሳልፎ የሰጠበት ፍቅር እንዲሁም እኛ ለእግዚአብሔር ራሳችንን አሳልፈን የሰጠንበት ፍቅር በተጨማሪም አንዳችን ለሌላችን ራሳችንን የሰጠንበት ፍቅርና ለኀጢአተኞች ራሳችንን የምንሰጥበት ፍቅር ነው። ይህን ጉዳይ በተመለከተ ቤተ ክርስቲያን እንዲህ የሚል አቋም አላት፦—

> በመጠራታችሁ በአንድ ተስፋ እንደ ተጠራችሁ፣ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፤ አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት፣ ከሁሉ በላይ የሚሆን ከሁሉ በላይ የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉ አባት አለ (ኤፌሶን 4፡4-6)።

ይህ በአንድነት ውስጥ ያለውን ልዩነት የሚያቅፍ ነው። የሥላሴ አስተምህሮ ራስን በመስጠት ላይ በተመሠረተው ፍቅርና ኅብረት ላይ የተመሠረተ ነገረ መለኮት ነው። ይህም ዓለም ዐቀፏን ቤተ ክርስቲያን በሁለት መንገድ ያሳድጋታል፤ ይኸውም በልዩነትና በአንድነት።

ሙስሊሞች ብዙ ጊዜ፣ "ቤተ ክርስቲያን ትልቅና አስገራሚ ልዩነት አላት። በዓለም ላይ ያለው የሙስሊም ማኅበረሰብ ግን በተመሳሳይ ሰዓትና በአንድ ዐይነት መልክ ይጸልያል። የአምልኮ ቋንቋው እንኳ ሳይቀር አንድ ነው። እኛ በዓለም ዐቀፍ ደረጃም ቢሆን ጠንካራ አንድነት አለን" ሲሉ ሐሳብ ይሰጣሉ።

ይህ በተመሳሳይ መንገድ ጸሎት የማድረሱ ሂደት የእግዚአብሔርን አንድነት ከሚገልጸው የሙስሊም ነገረ መለኮት (ቶውሂድ) ጋር የሚጣጣም ነው።

ሙስሊሞች በእግዚአብሔር መካከል ልዩነት እንደ ሌለ ሁሉ፣ በፈቃዱም ውስጥ ልዩነት የለም፣ ይህ አንድነት መንጸባረቅ ያለበት ደግሞ በአምልኮ ውስጥ ነው የሚል አቋም አላቸው። ለምሳሌ ከላይ ለማየት እንደ ሞከርነው የእግዚአብሔር ፈቃድ በዐረብኛው ቁርአን ውስጥ ተገልጸአል። ይህ እግዚአብሔር ፈቃዱን የገለጠበት የዐረብኛ ቁርአን፣ በተለያዩ ቋንቋዎች መተርጉሙ፣ በሙስሊሙ ማኅበረሰብና በእግዚአብሔር መገለጥ ላይ ልዩነት ስለሚያስከትል የዐረብኛው ቁርአን በተለያዩ ቋንቋዎች በፍጹም መተርጉም የለበትም።

የእስልምና ተሐድሶ እንቅስቃሴ አራማጆች የእግዚአብሔርን ፈቃድ በምድር ላይ እንመሠርታለን ለሚለው ጥረታቸው መነሻ ሐሳብ የሚያደርጉት፣ የእግዚአብሔርን አንድነትና የእግዚአብሔርን አንድያ ፈቃድ ነው። በዚህ ማዕቀፍ ውስጥ ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዴት ይገለጽ በሚለው ርእሰ ጉዳይ ላይ የተለያዩ አተረጓጎሞች አሉ። በዚህ ማዕቀፍ ውስጥ አራት ዐይነት የትንታኔ አቅጣጫ የሚከተሉ የእስላማዊ የሕግ ትምህርት ቤቶች አሉ (ምዕራፍ ዐሥራ ሁለት ስለ እስላማዊ ሕግ በስፋት ይተነትናል)። ይህ ቢሆንም ግን ሁሉም እስላማዊ የተሐድሶ እንቅስቃሴዎች፣ የእግዚአብሔርን ብቸኛ ፈቃድ በምድር ላይ መመሥረት ቀዳማይ ዐላማቸው ነው።

ኢራናዊው የኅብረተሰብ ጥናት ምሁር ዓሊ ሻሪአቲ፣ የኢራንን እስላማዊ አብዮት ለማብራራት በሞከሩበት ወቅት፣ የዚህን አመለካከት ነገረ መለኮታዊ መሠረት ለመተንተን ሙከራ አድርገዋል። የዚህ አብዮት ዋነኛ ዐላማ የእንዱን እግዚአብሔር አሐዳዊ ፈቃድ፣ በምድር ላይ በሚኖሩ ሕዝቦች ላይ በእንድ ጊዜ እንዲሰፍን ማድረግ ነው። ሻሪአቲ፣ አንድ ከሆነው ከዚህ የእግዚአብሔር ፈቃድ ማፈንገጥ ለእግዚአብሔር አምና እኩያ (ሽርክ) ማበጀት ነው ባይ ናቸው። ሁሉም የሕይወት ክልል መንፈሳዊ ይዘት አለው (የተቀደሰ ነው)፣ ፖለቲካው፣ ምጣኔ ሀብቱ፣ ባህሉ፣ የአደባባይና የማጀት ሕይወት ሁሉ፣ አሐዳዊውን የእግዚአብሔር ፈቃድ ማንጸባረቅ አለባቸው[3]።

ሻሪአቲ በሚተነትኑት በዚህ አሐዳዊ ማዕቀፍ ውስጥ አንዳችም አንድነትን መሠረት ያደረገ ጎብረ ልዩነት የለም። ስለዚህ አሐዳዊ የሆነው ይህ እስላማዊ እንቅስቃሴ በግድም/በጎይልም እንኳ ቢሆን፣ ተግባራዊ ይሆን ዘንድ ግድ ነው። አሐዳዊው የእግዚአብሔር ሕግ በሕዝቡ ላይ በጎይልም እንኳ ቢሆን

[3] Ali Shari'ati, On *the Sociology of Islam,* translated by Hamid Algar (Berkeley, Calif.: Mizan Press, 1979).

እንዳይጫን የሚከለክል ማንኛውንም ነገር ማስተናገድ፣ ልንታገሣቸው የማንችላቸው ልዩነቶች እንደ አሸን እንዲፈሉ በር ይከፍታል። ይህም የቶውሂድን መሠረታዊ አስተምህሮ የሚቃረን ነው። ይህ ዐይነቱን አመለካከት በሠለጠነው ዓለም ላይ ልጫን ብሎ መነሣት ደግሞ ቀላል የሆነ ትግል የሚጠይቅ አይደለም። ይህም የኢራናውያን አብዮት ፍትጊያ የበዛበት እንዲሆን ማድረጉ የግድ ነው።

ሙስሊሞች ለቤተ ክርስቲያን የሚያቀርቧቸው ጥያቄዎች

ሙስሊሞች ቤተ ክርስቲያንን የሚመለከቱት፣ አሐዳዊውን የእግዚአብሔር ፈቃድ (ቶውሂድ) በምድር ላይ ለማስፈን ችላ እንደለ አካል አድርገው ነው። ይህ ወቀሳ ጣምራ ገጽ አለው። ይኸውም ግራ መጋባትን አመላካች ነው። ይህ ትችት በሚከተሉት ሁለት ጥያቄዎች ሊገለጽ ይችላል።

በክርስትና እምነት ይህን ያህል ልዩነት ስምን ሲከሠት ቻለ?

በመጀመሪያ ሙስሊሞች፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይህን ያህል ሰፊ የጣለ እንዲሁም የአሠራር ልዩነት የመኖሩ ጉዳይ ያስገርማቸዋል። የሃይማኖት ሥርዐት ወይም ክህነታዊ ተቋማት የሌላቸው ክዌከሮች (Quakers)፣ ክህነታዊ ሥርዐት ካላቸው እንዲሁም በአምልኮተ ሥርዐት ወቅት ዕጣን ከሚታጠንባት የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን ጋር በአንድነት፣ ክርስቲያኖች እንዲሁም በአንድ መሠረተ እምነት ውስጥ ያሉ የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ሊባሉ እንዴት ይችላሉ? ክርስቲያኖች በክርስትና እንቅስቃሴ ውስጥ ያለውን ልዩነት በጎብረ ቀለማት ባሸበረቀ በጎ-ልዩነትና ጎይል ቢመለከቱትም፣ ሙስሊሞች ግን ይህን በይዘት አንድ ሆኖ በቅርጽ የሚለያየውን ልዩነት መልካም ነው የሚል እምነት የላቸውም።

ክርስቲያኖች ኢየሱስን የማይከተሉት ስምንድን ነው?

ከሙስሊሞች ወገን የሚሰነዘረው ሁለተኛው ሒስ፣ አብዛኛውን ጊዜ ክርስቲያኖች ምድራዊውን ሕይወት መንፈሳዊና ዓለማዊ በማለት በሁለት ወገን የመወገን አባዜ ተጠናውቶአቸዋል የሚለው ጉዳይ ነው። ለምሳሌ 1979-1981 ዓ.ም ተከሥቶ በነበረው የኢራን የዕገታ ቀውስ ወቅት ቻርልስ ኪምባል የተባለው የቅርብ ባልንጀራዬ፣ የአሜሪካ ቤተ ክርስቲያን ወኪል ሆነው ከተጓዙት የልዑካን ቡድን አባላት ጋር ወደ ኢራን በመጓዝ፣ የኢራን እስልምና አብዮት መንፈሳዊ መሪ ከሆኑት ከአያቶላ ኾሚኒ ጋር ተገናኝቶ ነበር።

ወቅቱ የአሜሪካና የኢራቅ ግንኙነት አጣብቂኝ ውስጥ የወደቀበት ጊዜ ነበር። ሆኖም አያቶላው ለአሜሪካውያኑ የልዑካን ቡድን የሰጡት ምክር፣ "ለአሜሪካ ቤተ ክርስቲያን መልእክት አለን፣ ይኸውም እናንተ አሜሪካውያን ኢየሱስን ተከተሉ፣ በአሜሪካ የሚገኙ ክርስቲያኖች መሲሑ ኢየሱስን ቢከተሉ ኖሮ፣ በኢራንና በአሜሪካ መካከል ያለው ይህ ችግር በፍጥነት ይፈታ ነበር" የሚል ነበር።

እኔ እንደምገምተው እኚህ መንፈሳዊ መሪ፣ የአሜሪካ ክርስቲያኖች በዓለም ዐቀፍ ፖሊሲ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ የሚል የተጋነነ ግምት ያደረባቸው ይመስለኛል። አያቶላው የአሜሪካኑን የኢራን መልእክተኛ ልዑካን እንደ መከሩት ብዙ ሙስሊሞች፣ "ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ ካመናችሁ፣ ከዚህ እምነት ጋር በተጣጣመ መንገድ ሕይወታችሁን ምሩ" ብለው ይነግሩኛል።

ብዙውን ጊዜ ሙስሊሞች፣ "እንደ እስልምናው ትምህርት የኢየሱስ አስተምህሮ ዘወትር በምድራዊ ሕይወት ተግባራዊ መሆን የሚችል አይደለም። ቁርአን ግን በዕለት ተዕለት ኑሮ ውስጥ ዘወትር ተግባራዊ መሆን የሚችል እንደ ሆነ እናምናለን። ለምሳሌ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ጦር እንዳይሰብቁ ወይም ፍቺ እንዳይፈጽሙ አስተምሮአል። እኛ ሙስሊሞች ይህ አሳብ በፍጹም ተግባራዊ መሆን እንደማይችል ጠንቅቀን እናውቃለን። ከዚህ ተቃራኒ በሆነው መልኩ ደግሞ፣ ቁርአንም ሆነ እስላማዊው ሕግ ከጠላቶቻችን ጋር እንዴት መዋጋት እንዳለብን፣ ለጠላታችን ምን ዐይነት አመለካከት ሊኖረን እንደሚገባ፣ ሥርዐቱን በጠበቀ መንገድ እንዴት ፍቺ መፈጸም እንዳለብን ይነግሩናል። እስልምና ተግባራዊ ሊሆን የሚችል ትምህርት ስላለው፣ ዓለም ዐቀፋዊ ለሆነው እስላማዊ ሕግ መገዛት ይቻላል"።

በክርስትና ያለው ትልቁ ተቃርኖ፣ "እናንተ ክርስቲያኖች በአንደበታችሁ ኢየሱስ ጌታ ነው ብትሉም እንኳ፣ የኢየሱስን መርሕ በሕይወታችሁ ተግባራዊ ለማድረግ አስቸጋሪ እንደ ሆነባችሁ ሕይወታችሁ ራሱ ይመሰክርባችኋል። በዕለት ተዕለት ሕይወታችሁ የእስልምናን አስተምህሮ ተግባራዊ በማድረግ፣ የኢየሱስን አስተምህሮ ተግባራዊ ለማድረግ አስቸጋሪ ጉዳይ መሆኑን ማሳየታችሁ አልቀረም። ስለዚህም ሕይወታችሁን በተለያየ መደብ በመከፋፈል ሲመቻችሁ ለኢየሱስ በመታዘዝ፣ ሳይመቻችሁ ደግሞ ኢየሱስን በመቃረን በተቃርኖ የተሞላ ሕይወት መኖር ግድ ሆኖባችኋል። የተቃረነ ሕይወት በመኖር የክርስትናን አንድነት (ቶውሂድ) ጥሳችኋል።

ይህ ከአሕመድ ጋር ከረጅም ዓመታት በፊት በናይሮቢ ስለ ሥላሴ በተነጋገርንበት ወቅት አሕመድን ካሳሰበው ጉዳይ ጋር ይመሳሰላል። በአሁኑ ጊዜ አሕመድ በአሜሪካን አገር፣ በዋሽንግተን ዲሲ የታክሲ ሹፌር ሲሆን፣ የኢትዮጵያውያኑ እንጀራና ወጥ ወደሚገኝበት ምግብ ቤት በመውሰድ እንጀራ በወጥ እየጋበዘኝ፣ "ክርስቲያኖች ኢየሱስ ጌታ ነው ይላሉ። ሆኖም የኢየሱስን አስተምህሮ የሚከተል አንድም ክርስቲያን አላገኘሁም። መሲሑ ኢየሱስን የሚታዘዙት ሲመቻቸው ብቻ ነው። ሆኖም በአብዛኛው ክርስቲያኖች ኢየሱስን ቢከተሉት ኖሮ ይህቺ አገር በአስደናቂ መንገድ ትለወጥ ነበር። ዐልፎ ተርፎ የአሜሪካን ቤተ ክርስቲያን በሁሉም ስፍራ ለሚኖሩ ማኅበረሰቦች ታላቅ በረከት ትሆን ነበር" አለ።

እዚህ አሜሪካ ከመገናኘታችን ከረጅም ዓመታት በፊት አሕመድ በናይሮቢ ኢስትሌይ ወደሚገኘው ቤቴ ለመግባት የውጪውን በር አንኳክቶ ሲገባ፣ ያሳሰበውና ያስጨነቀው የነበረው የቶውሂድ አስተምህሮ ነበር። ይኸውም የቶውሂድ አስተምህሮ ከሥላሴ አስተምህሮ ጋር በቀጥታ የሚጣረስ ስለመሰለው ነበር። ዛሬ ግን አሕመድ እኛ ክርስቲያኖች ኢየሱስን ለመከተል ቀላጠኛና ጽኑ ውሳኔ ማድረግ እንደሚገባን አበክሮ እየጠየቀኝ ነው፣ "የመሲሑ ሕግ ፍቅር ከሆነ በዚያ መንገድ ኑሩ! መሲሑ ሰዎችን ሁሉ እንደሚያፈቅር ሰዎችን ሁሉ የሚወድ ክርስቲያን በእርግጥ ዓለምን ማሸነፍ እንዲሁም የዓለምን ሕዝቦች ሁሉ መማረክ ይችላል"።

የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ

ማቴዎስ 28÷18-20፤

የቁርአን ምንባብ

ሱራ 30÷30-32፤ 42÷13-15

የአስተውሎትና የሙያዊት ጥያቄዎች

1. የሙስሊሙ ማኅበረሰብ በትምህርተ ሥላሴ እንዲሁም ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው በሚለው አስተምህሮ ላይ ያለው የተሳሳተ ግንዛቤ የመጣው፣ የክርስትናን መሠረተ እምነት በተሳሳተ መንገድ መረዳት እንዲሁም በክርስትና አስተምህሮ ላይ በተፈጠረ የተዛባ ምልከታ ምክንያት ነው በሚለው ጉዳይ ላይ የራስዎን አስተያየት ይስጡ (ሱራ 5÷75 ፤ 6÷100-101)።

2. ክርስቲያኖች መሲሑ የእግዚአብሔር ልጅ ነው የሚለውን ጉዳይ ለሙስሊም ጓደኞቻቸው እንዴት ማስረዳት ይችላሉ (ዮሐንስ 1+1:14፣ ሱራ 4+171)?
3. ቶውሂድ (የእግዚአብሔር አሐድነት) የኢራንን አብዮት በመሳሰሉ የሙስሊም የተሐድሶ እንቅስቃሴዎች ላይ ትጽእኖ ማሳደር የቻለው በምን ዐይነት መንገዶች ነው?
4. አብዛኛውን ጊዜ የሙስሊሙ ማኅበረሰብ፣ "የኢየሱስ ሕይወትና ትምህርት በምንናርባት በዚህች ዓለም ውስጥ በፍጹም ተግባራዊ ሊሆን አይችልም በሚለው ሐሳብ ላይ፣ ክርስቲያኖች ራሳቸው ከሙስሊሞች አስተሳሰብ ጋር ይስማማሉ" የሚል አስተያየት ይሰጣል። በዚህ ጉዳይ ላይ የራስዎን አስተያየት ይስጡ።
5. ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ፈቃድ በሰማይ እንደ ሆነ ሁሉ በምድርም እንዲሆን ይጸልያሉ። ሆኖም ቤተ ክርስቲያን በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ የተለያየ አስተያየት አላት። በእንጻሩ በሙስሊሙ ማኅበረሰብ ዘንድ ግን ይህ ዐይነቱ ልዩነት አይስተዋልም። ለምሳሌ የሙስሊሞች ጸሎት ሁሉ አንድ ዐይነት ነው። ይህን ጉዳይ ያብራሩ።
6. "እግዚአብሔር በሥላሴነቱ ሚስዮናዊ አምላክ ነው" በሚለው ሐሳብ ላይ አስተያየት ይስጡ።

ሃይማኖታዊ ጉዞ

ሃጅ—የጌታ ራት

ዩሱፍ የግልፍተኛነት ጠባይ አለበት። በሚኖርበት ከተማ የሠራተኞች ጉዳይ ባለሥልጣን ነው። እኔ ዳይሬክተር በነበርሁበት ትምህርት ቤት፣ ከሚገኙ የሥራ ባልደረቦቼ ጋር በመሆን ወደ እርሱ ቢሮ መሄድ ባሰብን ቀጥር ሁሉ፣ ጭንቀት ይሰማናል። ምክንያቱም የዩሱፍ ምላስ እንደ አለብላቢት ይፋጃል።

በከተማው ወሬ አቀባዮች አማካይነት ዩሱፍ ለሃይማኖታዊ ጉዞ ወደ መካ የመሄድ ዕቅድ እንዳለው የሚገልጽ መልካም ዜና፣ በከተማው በአንዴ ተናፈሰ።

የሙያተኞች ተቋጣጣሪ/አለቃ የሆነው ፋራህ እንደ ነገረኝ፣ "ዩሱፍ ከሃይማኖታዊው ጉዞ ሲመለስ አዲስ ስም ይኖረዋል—ሃጂ ዩሱፍ ይባላል። አዲስ ጠባይ ይኖረዋል። ዩሱፍ የተለወጠ ጠባይና አዲስ ስም ስለሚኖረው የከተማዋ ሕዝብ በሙሉ በትልቅ ደስታ ውስጥ ነው ያለው"።

ዩሱፍ ከሃይማኖታዊ ጉዞ የተመለሰው፣ አዲሱን የሃጂነት ማዕረግ ከተገቢው ክብር ጋር ተጉናጽፎ ነው። ግልፍተኝነቱን አስመልክቶ ቅጽበታዊ ለውጥ ማምጣቱ ባይረጋገጥም፣ በሂደትም እንኳ ቢሆን የጠባይ ለውጥ እንደሚያመጣ የከተማዋ ነዋሪዎች ትልቅ ተስፋ አላቸው።

የእምነትና የምግባር አዕማድ

ዩሱፍ ያደረገው ሃይማኖታዊ ጉዞ (ሐጅ) በእስልምና ሃይማኖት ውስጥ ከሚገኙት አምስት የእምነትና የምግባር አዕማድ ውስጥ አንዱ ነው። እነዚህ አምስት የእስልምና ሃይማኖት አዕማድ የሚከተሉት ናቸው:— (1) የእምነት ማረጋገጫ (*ሻሃዳ*)—" ይሽውም ከአላህ በስተቀር አምላክ የለም፣ መሐመድም የአላህ መልእክተኛ ነው"። (2) በአምልኮና በሃይማኖታዊ ጸሎት (*ሰላት*) ለእግዚአብሔር መገዛት (3) ለድኾች መመጽወት (*ዘካት*) (4) በረመዳን ወር መጸም (*ሳውም*) (5) ወደ መካ ሃይማኖታዊ ጉዞ ማድረግ (*ሃጂ*) ናቸው።

አንዳንድ የሙስሊም ማኅበረሰብ እንዲሁም አንዳንድ የሙስሊም ነገረ መለኮት ሰዎች፣ ሃይማኖቱን ከጥቃት ለመከላከል በሃይማኖት ጦርነት ውስጥ መሳተፍን (ጂሃድን) የሃይማኖቱ ስድስተኛ ዐምድ ያደርጉታል[1]። እነዚህ የሃይማኖቱ አዕማድ በቁርአን ውስጥ ተጠቅሰው ይገኛሉ። እነዚህ ምግባራት በቁርአን ውስጥ ተጠቅሰው ይገኛሉ ሲባል ግን፣ በእያንዳንዱ ርእስ ጒዳይ ላይ ቁርአን ትምህርት አለው ማለት ሳይሆን፣ መሐመድ ለእነዚህ ተግባራት ምሳሌ ሆነው ስላለፉ እርሳቸው ያደረጉትን ነገር ማድረግ በሃይማኖቱ ትልቅ ስፍራ እስከ ተሰጠው ድረስ፣ እነዚህ ጒዳዮች ቁርአናዊ መሠረት አላቸው ማለት ይቻላል። እነዚህ የሃይማኖቱ ምግባራትና ኀላፊነቶች፣ በሙስሊሞኑ የሃይማኖት እንቅስቃሴ የመጀመሪያዎቹ ዘመናት የራሳቸው የሆነ ዕድገት አሳይተዋል[2]። ይህ ምዕራፍ አምስተኛውን ዐምድ ማለትም ሃይማኖታዊውን ጒዞ (ሃጂን) በስፋት ለመመልከት ይሞክራል።

ወደ መካ የሚደረግ ሃይማኖታዊ ጒዞ

በየዓመቱ መካ ወደሚገኘው ወደ ካዕባ በዓለም ዙሪያ የሚገኙ ሙስሊሞች ሃይማኖታዊ ጒዞ ያደርጋሉ። ይህን ጒዞ ያደረጉ ሰዎችም የአዲስ ስም ባለቤት ይሆናሉ። በምሥራቅ አፍሪካ ይህ አዲስ ስም ለወንዶች ሃጂ ሲሆን ለሴቶች ደግሞ ሃጂያ ነው። በ1930ዎቹ በየዓመቱ አንድ መቶ ሺህ የሚጠጉ የእስልምና የሃይማኖት ተጓዦች ወደ መካ ይሄዱ ነበር። ዛሬ ግን ከአምስት እስከ ዘጠኝ ቀን ለሚፈጀው ለዚህ ሃይማኖታዊ ጒዞ፣ ሦስት ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዎች ወደ መካ ሃይማኖታዊ ጒዞ ያደርጋሉ። በደሁ-አል-ሂጃህ ወር፣ በዘጠነኛው ቀን የሚጀምረው ሃይማኖታዊ ጒዞ፣ በተለያየ ምክንያት በምድር ላይ ከሚደረጉ ስብሰባዎች በላይ እጅግ ብዙ ሕዝብ የሚሰበሰብበት ክብረ በዓል ሆኖአል።

አዳዲሶቹ ሃጂዎችና ሃጂያዎች (የሃይማኖት ተጓዦቹ) ወደ ቀዬአቸው ሲመለሱ፣ በሚናገሩባቸው በብዙ መቶዎች በሚቈጠሩ ቋንቋዎቻቸው፣ በመካ ያዩትንና ያጋጠማቸውን ነገር ሁሉ ይተርካሉ። የሃጂዎቹንና ሃጂያዎቹን ትረካ በንቃት ሲከተተሉ የነበሩ ትናንሽ ወንዶችና ሴቶች ልጆች፣ አንድ ቀን እኔም ሃይማኖታዊውን ጒዞ አደርጋለሁ የሚል ትልቅ ፍላጎት ያድርባቸዋል።

[1] Andrew Rippin, *Muslims: Their Religious Beliefs and Practices* (New York: Routledge, 2001), 97-98.

[2] H. A. R. Gibb, *Mohammedanism* (New York: Oxford University Press, 1969), 66-67.

ሃይማኖታዊውን ጒዞ እንዲያካሂዱ የሚጠበቅባቸው ወጪያቸውን መሸፈን የሚችሉ ሰዎች ብቻ ናቸው። ይሁን እንጂ የእስልምና ሃይማኖት የነገረ መለኮት ምሁር የሆኑት ሙሐመድ ሃሚዱላህ እንዲህ ይላሉ፦—

> ሆኖም የትኛው ሙስሊም ነው የሃይማኖቱ መሠረት የሆነውን የእግዚአብሔርን ቤት ለረጅም ጊዜ እንኳ ቢሆን ገንዘብ አጠራቅሞ እንድ ቀን ካሰባን እጉበኛለሁ የማይል? ቁርአን (ሱራ 3÷96) ይህን ስፍራ፣ የሰው ልጆች ለእግዚአብሔር ያበረከቱት ጥንታዊ የአምላክ ቤት እንዲሁም አሐዳዊው አምልኮ የሚካሄድበት ስፍራ ማለቱ አንዳችም ግንት የለበትም። እስላማዊውን ትውፊት ተከትለን አብርሃምን ብቻ እንኳ ብናስብ፣ አብርሃም አዳም በመጀመሪያ ያቆመውን ሕንፃ መልሶ ያደሰና የጠነ ሰው መሆኑን እንረዳለን። ይህም ሕንፃ ሰሎሞን በኢየሩሳሌም ከገነባው ቤተ መቅደስ እንኳ ይልቅ ቀዳሚ ነው[3]።

ዘጠኝ ቀን በሚፈጀው በዚህ ሃይማኖታዊ ጒዞ ላይ ለአፍታም እንኳ ቢሆን፣ ትኵረት እናድርግ። ይህ ጒዞ የእስልምናን መሠረተ እምነት ፍንትው አድርጎ ያሳያልና።

መካ መድረስ

ወንድ የሆኑ የሃይማኖት ተጓዦች ሁሉ፣ ኢህራም (ሁለት ክፍል ያለው ነጭ የሥርዐተ አምልኮ ልብስ) ይለብሳሉ። ሁሉም ሙስሊም ይህን ልብስ በወጥነት መልበሱ፣ ሙስሊሞች ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት እኩል መሆናቸውን ያመላክት ዘንድ ነው። ኢህራም ሙሉ ለሙሉ ለእግዚአብሔር ተሰጥቻለሁ የሚለውንም ሐሳብ ይወክላል። የሃይማኖት ተጓዦቹ መካ ከመድረሳቸው በፊት፣ በኢህራም መንፈስ ውስጥ ገብቶ መገኘት ይጠበቅባቸዋል። እነዚህ የሃይማኖት ተጓዦች በሚሄዱባቸው መንገዶች ላይ፣ ሙስሊም ያልሆነ ሰው በእነዚህ መንገዶች ዐልፎ ወደ መካ እንዳይቀርብ የሚከለክሉ ምልክቶች በየመንገድ ዳሩ ተለጥፈዋል። ይህም የሙስሊሙ ኡማ በምድር ላይ ከሚገኙ የማኅበረሰብ ክፍሎች ሁሉ ይልቅ፣ እጅግ የተለየ መሆኑን አመላካች እንደ ሆነ ይታመናል።

የሃይማኖት ተጓዦቹ ሁሉ፣ ጂዳ ላይ ከተሰበሰቡ በኋላ፣ ከጂዳ በ45 ማይል ርቀት ላይ ወደምትገኘው ወደ መካ ጒዞ ይጀምራሉ። ወደ መካም እየተጓዙ ሳለ፣ ታልቢያ በመባል የሚታወቀውን ጸሎት ደጋግመው ይጸልያሉ፦—

[3] Muhammad Hamidullah, *Introduction to Islam* (Paris: Centre Culturel Islamique, 1969), 64.

አምላኬ አንተ እንዳዘዝኸው እዚህ ተገኝቻለሁ፣ እነሆ በፊትህ ነኝ፣
አንተ አቻና እኩያ የለህም፣
አንተ ጸጋና ምስጋና ግዛትም ይገባሃል፣
አንተ አቻና እኩያ የለህም፣
እነሆኝ በፊትህ ነኝ![4]

ካዕባ (የመጀመሪያው የአግዚአብሔር ቤት)

የሃይማኖት ተጓዧች ሁሉ መካ ሲደርሱ ወደ መስጂድ-አል-ሃራም ይገባሉ። ይህ መስጊድ አምስት መቶ ሺህ ሰዎችን የማስተናገድ ዐቅም አለው። ካዕባም በተቀደሰው በዚህ መስጊድ መኻል ቆሞአል። ሙስሊሞች እንደሚያምኑት ስፍራው አዳም በመጀመሪያ ለአግዚአብሔር አምልኮ ያቀረበበት ስፍራ ነው። ካዕባ የአግዚአብሔር ቤት ይሆን ዘንድ በመጀመሪያ አዳም ያነጸው ቤት ሲሆን፣ ኋላም አብርሃምና እስማኤል ደጋግመው ያደሱት ቤት ነው። መሐመድ ነቢያዊ ስብከታቸውን ሲጀምሩ 360 አማልክትን ደምስሰው ካዕባን ከጣዖታት አጽድተዋል። መሐመድ የጣዖት አምላኪዎችን ጣዖት ብቻ አይደለም ያወደሙት፣ ነገር ግን ከእነዚህ አምልኮተ ጣዖታት ጋር ተያይዞ ይካሄዱ የነበሩ ሥርዐተ አምልኮዎችን፣ ለምሳሌ የሴት ሕፃናት ግድያ ኢፍትሐዊ መሆኑን ተቃውመው ሰብከዋል[5]።

በካዕባ ግድግዳ ውስጥ የተቀደሰ ጥቁር ድንጋይ አለ። ይህ ድንጋይ አዳምና ሔዋን ከገነት ወደ ምድር ሲወርዱ፣ ከሰማይ የወረደ እንደ ሆነ በሙስሊሞች ይታመናል። በአንድ ወቅት ጠፍቶና ተዘንግቶ የነበረው ይህ ድንጋይ፣ አብርሃምና እስማኤል በተአምር አግኝተውት፣ የአግዚአብሔርን ቤት ሲያድሱ በካዕባ ግድግዳ ላይ እንዳስቀመጡት ይታመናል።

መሐመድ ከመሞታቸው በፊት ባካሄዱትና ስንብታዊ በሆነው ሃይማኖታዊ ጉዞአቸው፣ ይህንን ድንጋይ እንደ ሳሙ ይነገራል። የሃይማኖት ተጓዦች ሁሉ የእርሳቸውን ፈለግ በመከተል፣ ካዕባን የሚዞሩት ይህን ድንጋይ በመሳለም ወይም እርሱን በመመልከት ነው። ካዕባን የሚዞሩት ሰዓት በሚዞርበት ተቃራኒ አቅጣጫ ስለሆነ፣ ድንጋዩና ካዕባ በዚሪዎቹ በስተግራ በኩል ይሆናል። ሥርዐተ

[4] Mohamed Amin, *Pilgrimage to Mecca* (Nairobi, Kenya: Camerapix, 1978), 20.

[5] Badru D. Kateregga and David W. Shenk, *A Muslim and a Christian in Dialogue* (Scottdale, Pa.: Hearald Press, 1997), 69.

ሃይማኖቱና አምልኮው ቅንጣት ታህል ዝንፍ የማይሉና በዝርዝር የተቀመጡ ናቸው። የሃይማኖት ተጓዧቹ ካዕባን የሚዞሩት ሰባት ጊዜ ነው።

ሙሐመድ ሃሚዱላህ በእስልምና የጥቁሩን ድንጋይና የካዕባን አገልግሎት እንዲህ ሲሉ ይገልጻሉ፦—

> በሐዲስ (በትውፊት) ነቢዩ ጥቁሩን ድንጋይ፣ "የእግዚአብሔር ቀኝ እጅ" (ያሚን አላህ) ብለው ሰይመውታል፣ ይህም ምክንያት አለው። አንድ ሰው ጉዞውን ማጠናቀቁን እንዲሁም በታማኝነትና በትሕትና መገዛቱን ለማሳየት እጁን በድንጋዩ ላይ ያኖራል፣ በዚህ መንገድ እግዚአብሔር የእኛን መገዛትና ለእርሱ ያለንን ታማኝነት ይቀበላል። በቁርአን አገላለጽ እግዚአብሔር ንጉሥ ነው፣ በእርሱ ግዛትም ውስጥ ትልት ከተማ (አማል ቁራ) አለ፣ በዚህም አማል ቁራ ቤተ መንግሥት አለ፣ በዚህም ቤተ መንግሥት ውስጥ እግዚአብሔር ይኖራል (ቤት-አላህ)። ታማኝነቱ እንዲመሰከርለት የተፈለገ ሰው ወደ ንጉሡ መኖሪያ ቀርቦ ታማኝነቱንና መገዛቱን መግለጽ አለበት። በዚህም ጊዜ የማይታየው የእግዚአብሔር ቀኝ እጅ ተምሳሌታዊ በሆነ መንገድ ይታያል። ይህም (አል ሃጀር አል-አስዋድ) በካዕባ ላይ ያለው ጥቁር ድንጋይ ነው[6]።

በእስልምና ይህ ሃይማኖታዊ ጉዞ እጅግ ወደ ተቀደሰ ስፍራ የሚደረግ ጉዞ ነው። ሙስሊሞች እንደሚያምኑት የመጀመሪያዎቹ፣ መካከለኞቹና የመጨረሻዎቹ የእስላም ነቢያት አዳም፣ አብርሃምና መሐመድ በካዕባ ልዩ በሆነ መንገድ የእግዚአብሔርን መገለጥ አግኝተዋል። ለሙስሊሞች ወደዚህ ወደ ተቀደሰ ስፍራ ሃይማኖታዊ ጉዞ ማድረግ ለእግዚአብሔር ፈቃድ የመታዘዝ ሙሉ ምልክት ነው። ካዕባ ጥቁር ድንጋይ ያለበት ሕንፃ ብቻ አይደለም። የመጀመሪያዎቹ የሰው ዘሮች ለአላህ በመገዛት የሰገዱበትና አላህን ያመለኩበት የመጀመሪያው የእግዚአብሔር ቤት እንዲሁም የምድር ዕምብርት ነው።

የሰጋር፣ ኡስማኤልና የአብርሃም ፋና

ሙስሊሞች የሃጂን ጉዞ የአብርሃምን ጉዞ እንደ መድገም ይቆጥሩታል። ሃይማኖታዊ ተጓዦቹ በአብርሃም ክልል ውስጥ ጸሎት ያደርሳሉ። ከዚያም ወደ ዘምዘም ምንጭ ይጓዛሉ። ይህ መልኡኩ ገብርኤል ለአጋርና ለእስማኤል ተአምራዊ በሆነ መንገድ ውሃን ያቀረበበት ስፍራ ነው። ይህም ውሃ በምድር ላይ ካሉት ውሆች ሁሉ ይልቅ ንጹሕ እንደ ሆነ ይታመናል። የሃይማኖት

[6] Hamidullah, *Introduction to Islam*, 66.

ተጓዦቹ ጥማቸውን ለመቀሥረጥ ብቻ ሳይሆን፣ ሃይማኖታዊ መንጻት ይሆናቸው ዘንድ ይታጠቡበታል።

ከምንጩ በቅርብ ርቀት ላይ ወደሚገኙት መንትያ ዳገቶች ወደ አል-ሳፋና አል-መረዋ ይጓዛሉ። በእነዚህ ዳገቶች መካከል አጋር በውሃ ጥም ወደ ሞት ለተቃረበው ልጇ እየጸለየች የተጓዘችበትን መከራዋን በማሰብ በአካባቢው ይዘዋወራሉ።

የመሐመድ የመጨረሻው ሃይማኖታዊ ጉዞ

የሃይማኖት ተጓዦች ከመካ ዐሥር ማይል ርቆ ወደሚገኘው ወደ አረፋት ሜዳ ይጓዛሉ። በሚጸው መኻል መሐመድ ለመጨረሻ ጊዜ ለአንድ መቶ ሺህ አማኞች የሰበኩበት የምሕረት ተራራ አለ። በዚህ መልእክትም የሃይማኖታዊ ጉዞን ሕግ ደነገጉ።

ሙስሊሞች በተራራው ላይ ሲሰባሰቡ መሐመድ በመጨረሻ የሃይማኖት ጉዞቸው ወቅት የሰበኩትን ዐይነት ስብከት ይሰማሉ። ይህ ተራራ አጸያም ከእግዚአብሔር ምሕረትንና ምሪትን የጠየቀበት ስፍራ ነው።

ይህ ከዓለም ዙሪያ ከሁለት እስከ ሦስት ሚሊዮን ሕዝብ የተሰበሰበበት ስፍራ፣ ለሃይማኖታዊ ጉዞው እጅግ የከበረው ስፍራ ነው። አንድ ወቅት ላይ አጸያምና መሐመድ ቆመውበት በነበረው በምሕረት ተራራ ሰባኪው ይቆማል። ሕዝቡ በአንድነት እንደ አንድ ሕዝብ እጅብ ብሎ በመቆም የእግዚአብሔር ቃል ሲታወጅ ያጸያጣል፣ ይህም ዐዋጅ:— "እግዚአብሔር አቻና እኩያ የሌለው ብቸኛ አምላክ ነው፤ አንዱ ሙስሊም ከሌላው ሙስሊም ጋር እኩል ነው" የሚል ነው።

የአስማኤል መታሰቢያ

የሃይማኖት ተጓዦቹ ጥቂት ዕረፍት ወስደው ከእኩለ ሌሊት በኋላ ሚና ወደ ተባሉ አጋንንትን የሚወክሉ ሦስት የድንጋይ አዕማድ ወደ ቆሙበት ስፍራ ይጓዛሉ። እነዚህ የድንጋይ አዕማድ የቆሙት ሰይጣን፣ አብርሃም ልጁ አስማኤልን እንጸይዠዋ ለማሳመን የሞከረውን ሙከራ ለማሰብ ነው። የሃይማኖት ተጓዦቹ በሰይጣንና በሽንገላ ዘዴው ላይ ያላቸውን ተቃውሞ ለመግለጽ በሚና በሚገኙት ሃውልቶች ላይ ጠጠር ይወረውራሉ።

በሚና ከሚደረገው የጠጠር ውርወራ በኋላ የሃይማኖት ተጓዦቹ የኢህራም ልብሳቸውን አውልቀው እንደ ባህላቸው ያሻቸውን ልብስ ይለብሳሉ። ከዚህ በኋላ የክብረ በዓል ጊዜ ይሆናል። ሌሊት ለመሥዋዕትና ለድግስ የሚሆኑ በጎችና ግመሎች እንዲሁም ሌሎች እንስሳት ይገዛሉ። እነዚህ እንስሳት የመሠዋታቸው ዐቢይ ዐላማ፣ እግዚአብሔር በምትኩ በግን አዘጋጅቶ የእስማኤልን ሕይወት ከመሥዋዕትነት ማትረፉን ለማሰብ ነው።

በዓለም ዙሪያ ያሉ ሙስሊሞች በዚህች ምሽት በሚካሄደው በመሥዋዕቱና በድግሱ ክብረ በዓል ላይ ይሳተፋሉ። በሙስሊሙ ግዛት የታቀፉ ሕዝቦች በዚህ መሥዋዕት የማቅረብ ክብረ በዓል ላይ (ኢድ አል-አድሃ) ይሳተፋሉ። ይህ አራት ቀን የሚፈጀው ክብረ በዓል በሐጂ መሄጃ ወር (ዙህል-ሂጻ) በዐሥረኛው ቀን ላይ ይጀምራል። ሁሉም ሙስሊሞች አብርሃምንና እስማኤልን፣ በችግሮች ሁሉ ውስጥ ጸንተው እምነታቸውን ለመሐመድና ለሙስሊሙ ማኅበረሰብ በማስተላለፍ እንዲሁም እምነትና ምግባርን መመሥረት ያስቻሉ ነቢያት እንደ ሆኑ በመቀኒጠር በአክብሮት ያስቡአቸዋል። ምትክ ሆኖ በቀረበው መሥዋዕት የእስማኤል ሕይወት ብቻ አይደለም የተረፈው ነገር ግን የእስልምና እምነት መሠረትም ተጠብቋል፤ ለሚቀጥለው ትውልድም ተላልፏል። ስጦታዎች ይሰጣሉ፣ ለድኾችም ምግብ ይዘጋጃል።

የሃይማኖት ተጓዦቹ የጉዞ ፍጻሜ ወደ መካ ተመልሶ ካዕባን ለመጨረሻ ጊዜ መጐብኘት ነው። ብዙ ተጓዦች ቆይታቸውን በማራዘም መዲናን ይጐበኛሉ። ይህ ተጨማሪ ጉዞ ለእምነት መታነጽ የሚረዳ ቢሆንም፣ ሃይማኖታዊ ተጓዥ ማሟላት ያለበት ግዴታ አይደለም።

የሃይማኖታዊው ጉዞ ነገረ መለኮት

ትልልቅ የሆኑ የነገረ መለኮት ሐሳቦች በሃይማኖታዊ ጉዞው ላይ ተሳስረዋል። ሃይማኖታዊ የሥነ ሰብ ጥናት ተመራማሪዎች በብዙ እምነቶች፣ "የምድርን እንብርት" የሚወክል ስፍራ አለ የሚል እምነት እንዳላቸው ያስረዳሉ። ይህ የምድር ማዕከል/እንብርት መለኮትንና ሰውን እንዲሁም ሰማይንና ምድርን የሚያገናኝ ስፍራ እንደ ሆነ ይታመናል። በእስልምና ይህ ስፍራ ካዕባ ነው።

በካዕባ የሚገኘው ጥቁር ድንጋይ ለአጸያምና ለሰው ልጆች ሁሉ ከእግዚአብሔር የተሰጠ ስጦታ ነው። በሰማይና በምድር፣ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ግንኙነትንና የሰዎችን አንድነት የሚወክል ነው። እግዚአብሔር እስልምናን ለሁሉም ሕዝቦች ምሕረት አድርጉ እንደ ላከው የሚያሳይ ተምሳሌትም ነው።

ድንጋጹ ነቢያትን፣ አጻምን፣ አብርሃምንና መሐመድን እንዲሁም ይሆን ድንጋይ በትልቅ አክብሮት የሚያዩት ሰዎች ሁሉ አንድ መሆናቸውን የሚያመለክት ነው።

ድንጋጹ ተአምራዊ መገለጥን የሚያመላክትና ለአጻም የተላከለት ድንጋይም ነው። ይህ ድንጋይ በአሸዋ ውስጥ ተቀብሮ ጠፍቶ ነበር። ተአምራዊ በሆነ መንገድ አብርሃምና እስማኤል ድንጋጹን እንጻገኙትና ለዘላለም በእግዚአብሔር ቀደምት ቤት በካዕባ እንደ ተቀመጠ ሙስሊሞች ሁሉ ያምናሉ።

የአብርሃም፣ የአጋርና የእስማኤል ታሪክ በሃይማኖት ጉዞው ውስጥ ሁሉን የሚያስርና ለሁሉ ትርጽ የሚሰጥ ርእሰ ጉዳይ ነው። መሐመድ ለመጨረሻ ጊዜ ያካሂዱት ሃይማኖታዊ ጉዞና ለመጨረሻ ጊዜ በአረፋት ሜዳ፣ በምሕረት ተራራ የሰበኩትም ስብከት በዚህ መልክ የሚታሰብ ነው። የአጻምም ድርሻ በዚህ ሥዕል ውስጥ ትልቅ ሚና አለው። ሃይማኖታዊው ጉዞ ሙስሊሞች ከሁሉም የእግዚአብሔር ነቢያትና ሕዝቦች ጋር በዘመናት መካከል ያለውን አንድነት በግልጽ ቋንቋ የሚያመለክት ነው። በተጨማሪም ሙስሊሞች ለእስልምና ሃይማኖት ከማይገዙ ከሌሎች ሕዝቦች ጋር ያላቸውን ልዩነት አመልካች ነው።

የመሥዋዕቱ ክብረ በዓል ትልቅ ትኩረት የሚፈልግ ነው። ሃይማኖታዊው ጉዞ በሙስሊሙ ሕዝብ ሕይወት ውስጥ፣ እግዚአብሔር ለእስማኤልና ለሙስሊሙ ማኅበረሰብ ምትክ ይሆን ዘንድ የበግ መሥዋዕት አቅርቦ የታደገበት የደስታ መታሰቢያ በዓል ነው። ይህ በሙስሊም ልቦና የተሰወረ ምሥጢር ነው። በአብርሃም ልጅ ምትክ የተሠዋው በግ ምን ትርጉም የሚወክል ነው?

ለአብርሃም ልጅ ትኪ ሆኖ የቀረበው በግ ምን ትርጉም ይመከሰል?

ከኢየሩሳሌም ቅጥር ውጪ ጉልጉታ በተባለው ኩረብታ የተሠዋውን ሌላውን መሥዋዕት፣ ሙስሊሞች እንዲያስተውሉት ክርስቲያኖች ጥሪ ያቀርባሉ። ክርስቲያኖች ይህ ስፍራ ኢየሱስ ተሠውቶበት የነበረው ስፋራ ነው የሚል እምነት አላቸው። የእግዚአብሔር በግ ተብሎ የሚጠራው መሲሑ፣ አብርሃም በልጁ ምትክ የሠዋው በግ ምስጢራዊ ፍጻሜ አይደለምን?

በረመዳን የጾም ወር ወቅት በፊላደልፊያ መስጊድ ውስጥ ከክርስቲያኖች ጋር ይወያዩ ለነበሩ ሙስሊሞች ይህ ጥያቄ ቀርቦላቸው ነበር። ጸሎቱ ለሁለት ሰዓት ተካሂዶ ስለነበር ለውይይት የተሰበሰብነው ከምሽቱ አራት ሰዓት ገደማ ላይ ነበር።

ኢማሙ፣ "በዛሬ ምሽት ተጨማሪ ጸሎት እንጸሳረግን (እንጸቀረብን) አስተውላችኋልን? በረመዳን የጾም ወር በየምሽቱ ሁለት ተጨማሪ ሰዓት እንጸልያለን። እነዚህ ተጨማሪ የጸሎት ሰዓቶች ለኀጢአታችን ማካካሻ ሊሆኑን እንደሚችሉ ተስፋ እናደርጋለን" አለ። አንዱ ክርስቲያን እንዲህ ብሎ ጠየቀ፣ "ኀጢአታችሁን ሙሉ ለሙሉ ሊያካክስ የሚችል በቂ ጸሎት አለያችሁን?"

"ስለዚያ የምናውቀው አንጻች ነገር የለም" ሲል ኢማሙ መልስ ሰጠ። እኛም እንዲህ አልን፣ "በሙሴ መጽሐፍ የእግዚአብሔር ሕዝብ ለኀጢአት መሥዋዕት የእንስሳት መሥዋዕት እንዲያቀርቡ ታዞአል። እነዚህ መሥዋዕቶች ምንድን ናቸው? ለአብርሃም ልጅ ትኪ ሆኖ የተሠዋው በግ በስተጀርባ ያለው ምሳሌ ትርጉሙ ምንድን ነው? ከመሲሑ ኢየሱስ ስሞች መካከል አንዱ የእግዚአብሔር በግ ነው። ይህ ማለት ደግሞ መሲሑ በእኛ ምትክ በመስቀል ላይ የመሥዋዕትነት ሞት ሞቶአል። በሙሴ ሕግ ይደረግ የነበረው መሥዋዕት በመጨረሻ ወደ መሲሑ መሥዋዕታዊ ሞት አመልካች እንደ ሆነ አዲስ ኪዳን ይገልጻል። እርሱ የእኛን መከራ ወሰደ። እኛም ምሕረትን (ይቅርታን) አገኘን"።

"ይህ ሊሆን አይችልም። እያንዳንዱ ሰው የራሱን ኦኀጢአት ውጤት መሸከም አለበት። ፈራጁ ፍርድን ሲያሰማ በደለኛ ሰው የኀጢአቱን ዋጋ መክፈል አለበት" በማለት ተቃወመ።

እኛም "እውነት ነው" ብለን ተስማማን። "ሆኖም ፈራጁ ራሱ ከፍርድ ዙፋኑ ላይ ወርዶ በእንተ ስፍራ እኔ እሆናለሁ፣ አንተ ነጻ ነህ ብሎ ቢልስ። ኢየሱስ ቤዛ ሆነን ማለት ይህ ነው። እግዚአብሔር መሲሑን ልኮ ችሎት በመሰየም የእኛን ስፍራ በመውሰድ ተቤዥን"። ውድ ስለሆነው የይቅርታ ስጦታና እግዚአብሔር በመሲሑ የሰጠውን መቤዠት በማሰብ በዚያች ምሽት በመስጊድ ውስጥ ለአጭር ደቂቃ የአክብሮት ዝምታ ሰፈነ።

እግዚአብሔር መሓሪው አማላጅ

መቤዠት (መዋጀት) የወንጌል ዋናው ክፍል ሲሆን፣ ለሙስሊም ነገረ መለኮት ግን መቤዠት ማዕከላዊ አስተምህሮ አይደለም። ይሁንና በእስልምናም ቢሆን እግዚአብሔር የሚዋጅ አምላክ መሆኑን የሚጠቁሙ ፍንጮች አሉ። የሚያስገርመው ነገር እግዚአብሔር ለአብርሃም ልጅ ምትክ ይሆን ዘንድ ያዘጋጀው በግን ነው። እግዚአብሔር ራሱ አማላጅ እንደ ሆነ በቁርአን ውስጥ ማረጋገጫ እናገኛለን :—

> "አላህ ያ ሰግያትንና ምድርን በመከከላቸው ያለውን በስድስት ቀኖች ውስጥ የፈጠረ በዚያም በዐርሹ ላይ (ሥልጣኑ) የተደላደለ ነው፤ ከእርሱ ሌላ በእናንተ ረዳትም አማላጅም ምንም የላችሁም አትገሠጹምን?" (ሱራ 32÷4)

በሌላ ስፍራ ደግሞ:—

> "እነዚያም በተአምራታችን የሚያምኑት በመጡብህ ጊዜ ሰላም በእናንተ ላይ ይሁን፤ ጌታችሁ በነፍሱ ላይ እዝነትን ጻፈ፤ እነሆ ከእናንተ ውስጥ በስሕተት ክፉን ሥራ የሠራ ሰው ከዚያም ከእርሱ በኋላ የተጸጸተና ሥራውን ያሳመረ እርሱ (አላህ) መሓሪ አዛኝ ነው በላቸው" (ሱራ 6÷54)።

ይህ የመጨረሻው የቁርአን ክፍል በእጅጉ ከወንጌል ጋር ይመሳሰላል። በቁርአን ውስጥ የምሕረትን ሕግ እግዚአብሔር በራሱ ላይ ደንግጓል። በእነዚህ ክፍሎች ውስጥ እግዚአብሔር ጓደኞችንና መሓሪ አማላጃችን እንደ ሆነ ተገልጸአል። በእስልምና እግዚአብሔር ወደ እርሱ በንስሓ ለሚቀርቡ ምሕረትን ያደርጋል። ንስሓ ለሚገቡና ለእስልምና ለሚገዙ ጎጢአተኞች ምሕረት አለ፤ እግዚአብሔር በራሱ ምሕረትን ደንግጓል።

እንደነዚህ ያሉት የቁርአን ማስረጃዎች ከወንጌል ጋር ተመሳሳይነት ስላላቸው ጠቀሜታቸው ታላቅ ነው። ሆኖም በወንጌል ውስጥ መሲሑ ጎጢአተኞችን ሲፈልግና አብሯቸው ሲበላ እናያለን። ሕይወቱንም ለጎጢአተኞች ሰጥቶአል። የሃይማኖት መሪዎች ደቀ መዝሙሮቹን፣ "መምህራችሁ ከቀራጮችና ከጎጢአተኞች ጋር አብሮ ስለ ምን ይበላል? አሉአቸው" (ማቴዎስ 9÷11)። ኢየሱስም ሰምቶ፣ "ሕመምተኞች እንጂ ባለ ጤናዎች ባለ መድኀኒት አያስፈልጋቸውም" ብሎ መለሰላቸው (ማቴዎስ 9÷11)።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ስለ አንድ አባትና ስለ ሁለት ልጆቹ ታሪክ የሚናገር ክፍል አለ። በምሳሌው ውስጥ አባትየው ዐመፀኛውንና የጠፋውን ልጅ በሩቅ

ሲያየው ከብሩን ጥሎ ልጁን ለማቀፍ ሮጠ። ለጠፋው ልጅ ግብዣን አዘጋጀ። ይህ አባት ከእርሱ ጋር አብሮ ይኖር የነበረው ልጅ ስለጠፋው ነገር ግን አሁን ስለተገኘው ወንድሙ ፍሥሓ እንዲያደርግ ይለምነዋል (ሉቃስ 15÷11-32)። ይህ ምሳሌ እግዚአብሔር በብዙ መንገድ የሚገለጸውን ራሱን አሳልፎ የሰጠበትን ፍቅር ይበልጡኑ ግን በመሲሑ ራሱን የሠዋበትን ፍቅር ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ነው (ሉቃስ 15÷1-7)። እግዚአብሔር በመሲሑ ጎጢአተኞችን ይፈልጋል፤ ወደ እርሱ እንዲመጡም ይጠራል። ከጎጢአተኞችም ጋር ይበላል። መሲሑ ጎጢአተኞችን ለመቤዠት ሕይወቱን ሰጥቶአል። ይህም የመሥዋዕት ግብዣ ወደሚባለው የሙስሊሞች ሐሳብ የሚወስደን ነው።

የዚህ ምሥጢር ትርጉም ምንድን ነው? እግዚአብሔር በመሲሑ በኩል የገለጠው መሥዋዕታዊና ራስን የመስጠት ፍቅር የተፈጸመበት ምልክት ይሆንን? እግዚአብሔር ለአብርሃም ልጅ ምትክ የሚሆን በግ በማዘጋጀት በጉ ለልጁ ሞት ምትክ ሆኖአል። ወንጌል እንደሚያስተምረን መሲሑ በመስቀል ላይ የፈጸመው መሥዋዕታዊ ሞት ለእኛ ምትክ ሆኖአል።

ሃይማኖታዊ ጉዞ ከመሲሑ ጋር

ሙስሊሞች *በዱሉ ለል ሂጃ* እንደሚያደርጉት ክርስቲያኖች አብርሃማዊ የሆነ የሃይማኖት ጉዞን ለመታሰቢያነት በማድረግ ቅዱስ ወደሚባሉ ስፍራዎች አይጓዙም። ሆኖም እግዚአብሔር ሁሉም የእምነት ክፍሎች እርሱን እንዲከተሉት ጥሪ አቅርቦአል። ይህም ጥሪ ልክ እንደ አብርሃም የምኞት ስፍራችንንና ቤተሰባችንን ጥለን እግዚአብሔርን በእምነት እንድንከተለው ነው። ምንም እንኳ እግዚአብሔር አንዳንድ ሰዎችን ሽንጣቸውን ጠቅልለው እርሱን እንዲከተሉት ወይም እርሱ ወደሚመራቸው ስፍራ እንዳሄዱ ጥሪ ቢያቀርብም፣ የሃይማኖታዊ ጉዞ ቀዳማይ ዐላማው እርሱን በፍጹም ልብ መከተል ነው። ይህም የእግዚአብሔር ጥሪ ፍጹም ታማኝነትን የሚጠይቅ ከሌሎች መሰጠቶች ሁሉ የሚልቅ ሃይማኖታዊ ጉዞ ነው።

የክርስቲያኖች ዘመን አቈጣጠር ከሙስሊሙ ሃይማኖታዊ ጉዞ ጋር የሚመሳሰሉም ሆነ የሚለያዩ መታሰቢያዎች አሉት:— ክርስቲያኖች ከፋሲካ በፊት ያለውን እሑድ፣ የስቅለትን ቀንና የፋሲካን በዓል በትልቅ ተመስጦ ያስቡታል፤ ነገር ግን ቱም ነገሩን ለማሰብ፣ ሙስሊሞች ወደ መካ እንደሚያደርጉት ዐይነት ጉዞ መጓዝ አስፈላጊ ነው የሚል እምነት የላቸውም።

ቤተ መቅደስ (የእግዚአብሔር ቤት)

መሲሑ ኢየሱስ አዘውትሮ ወደ ቤተ መቅደስ ይሄድ ነበር። ዐሥራ ሁለት ዓመት በነበረበት ጊዜ ቤተሰቦቹ በቤተ መቅደስ ባገኙት ጊዜ የተናገረው ቃል፣ በቤተ መቅደስ በመገኘት የተናገረው የመጀመሪያው ቃሉ ነው፣ "እርሱም ስለምን ፈለጋችሁኝ? በአባቴ ቤት እሆን ዘንድ እንዲገባኝ አላወቃችሁምን?" አላቸው" (ሉቃስ 2÷49)። ኢየሱስ የአይሁድን ሃይማኖት፣ የቤተ መቅደስን ባህል እንዲሁም ልምምድ በማክበር የሚኖር ሰው ነበር[7]።

ይሁን እንጂ ኢየሱስ በቤተ መቅደስ ውስጥ የነበረውን የፍትሕ መጓደልን፣ ግብዝነትንና ሰውን ማዋረድ ከፉኛ ተቃውሞአል። በተጨማሪም የእርሱ መምጣት ቤተ መቅደሱ የሚወክለው እምነት ፍጻሜ ማግኘቱን በተግባር እንደሚያሳይ አስተምሮአል። ይህም እምነቱ ከቤተ መቅደስ ባለሥልጣናት ጋር አጋጭቶታል። ምዕራፍ 8 ከፋሲካ በፊት ስላለው እሑድና ቤተ መቅደሱን ስለ ማጽዳት ግብራሪያ ይሰጣል። ምዕራፍ 9 ደግሞ በኢየሱስና በመቅደስ ልማድ መካከል የፈጠረው ልዩነት ያስከተለውን ጠንካራ ግጭት ይተርካል።

በአይሁዶች ነገረ መለኮት መሠረት ቤተ መቅደሱ እንደ እግዚአብሔር መኖሪያ ተደርጉ ይቆጠር ነበር። ንጉሥ ሰሎሞን የመጀመሪያውን ቤተ መቅደስ ሠርቶ ከጨረሰ በኋላ የእግዚአብሔር ክብር ቤቱን ሞላው (2ዜና 6÷17:10)። ይህ ቤተ መቅደስ 586 ዓ.ቅ.ክ በባቢሎናውያን ወራሪዎች ተደምስሶአል። ዳግመኛም ቤተ መቅደሱ በዘሩባቤል መሪነት በ515 ዓ.ቅ.ክ ታንጾ ተመርቋል። ከመሲሑ በፊትና በመሲሑ ጊዜ ቤተ መቅደሱ ዋና የሚባል ዕድሳት ተደርጉለታል። በየክፍለ ዘመናቱም አስራኤላውያን የአይሁድ በዓላትን ለመዘከር መደበኛ የሆነ የሃይማኖት ጉዞ ያደርጉ ነበር። በኢየሱስ ዘመን ቤተ መቅደስን አለቅጥ ትልቅ ዋጋ የመስጠትና የማምለክ አባዜ ተስፋፍቶ ነበር። ለብዙ አስራኤላውያን የእግዚአብሔር ቤት ጉዳይ ወጥመድ እንዲሁም ከፍ ያለ ዋጋ በማስከፈል ወደ ስሕተት የሚመራ ጉዳይ ነበር[8]። ኢየሱስም ወደ መቅደሱ ገብቶ ብልሹ የሆኑ ነጋዲዎችን እንዲህ ሲል ገሥጸአቸዋል፦ "ይህን ከዚህ ውሰዱ የአባቴን ቤት የንግድ ቤት አታድርጉት"

[7] E. P. Sanders, *The Historical Figure of Jesus* (London: The Penguin Press, 1995), 33-48.

[8] Donald B. Kraybill, *The Upside-Down Kingdom* (Scottdale, Pa.: Herald Press, 1978), 65-94.

(ዮሐንስ 2÷16)። ከሰድስት ምዕተ ዓመት በኋላ፣ መሐመድ በመካ የሚገኘውን የካዕባውን የእግዚአብሔር ቤት ከጣዖት አምልኮ አጸዱ። ይህ በኢየሱስና በመሐመድ የተካሄደው ቤተ መቅደስን የማጽዳት ሥራ በዚህ ረገድ ኢየሱስና መሐመድ ተመሳሳይ የሆነ ሥራ እንደ ነበራቸው የሚያሳይ ነው። ነገር ግን የኢየሱስ ተልእኮ የተበላሸውን መቅደስ በማጽዳት ብቻ ያበቃ አልነበረም። እውነተኛ አምልኮን ለእግዚአብሔር በማቅረብ ረገድ ቤተ መቅደሱ የማይጠቅም መሆኑን በመግለጽ፣ ባለሥልጣናቱን ከፉኛ አስደንግጦአል (ምዕራፍ 9 ይመለከቷል)።

መሲሑ ራሱ ቤተ መቅደስ ነው

ቤተ መቅደሱን ሲያጸዳ በተፈጠረው ጩኸት መካከል፣ "ይህንን ቤተ መቅደስ አፍርሱት፣ በሦስተኛው ቀንም አስነሣዋለሁ" (ዮሐንስ 2÷19) ብሎ በመናገር የቤተ መቅደስ ባለሥልጣናትን የበለጠ አስቈጣቸው። በሌላ ጊዜ ደግሞ ለደቀ መዛሙርቱ ስለቤተ መቅደሱ መፍረስ ትንቢት በሚናገርበት ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ በሁኔታው ተደናግጠዋል፦—"ይህ የምታዩት ሁሉ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ በዚህ የማይቀርበት ዘመን ይመጣል አለ" (ሉቃስ 21÷6)።

መሐመድ የእግዚአብሔርን ቤት ወይም ካዕባን የሚተኩ መሆናቸውን አልገለጹም፣ በዚህ መልክም ራሳቸውን አላቀረቡም። እንዲያውም በየዓመቱ ወደ ካዕባ የሚደረገው ሃይማኖታዊ ጉዞ፣ ለሙስሊሞች ሁሉ የእግዚአብሔር ቤት አስፈላጊ ጉዳይ መሆኑን የሚያስተምር ነው[9]።

ኢየሱስ ግን በሰው እጅ የተሠራ ቤተ መቅደስ አስፈላጊ እንዳልሆነ አስተምሮአል። እንዲያውም ኢየሱስ እርሱ ራሱ የቤተ መቅደስ ምትክ እንደ ሆነ ይፋ አድርጎአል። ስለዚህ እርሱ አሁን ወደ ምድር መጥቶአል። ከዚህ የተነሣ ቤተ መቅደስ ከዚህ በኋላ አያስፈልግም። እርሱ ራሱ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነውና[10]። ኢየሱስ ሕግን ተላላፊ ተደርጉ እንዲቆጠር እንዲሁም እንዲሰቀል የሃይማኖት ባለሥልጣናት የጠየቁት በዚሁ ምክንያት ነበር።

[9] ካዕባ ለሙስሊሙ ማኅበረሰብ መልክዐ ምድራዊ ማዕከል ነው። ክርስቲያኖችም ሆኑ ቤተ ክርስቲያን ግን ይህ ዐይነቱ መልክዐ ምድራዊ ማዕከል የላቸውም።

[10] N. T. Wright, *The Challenge of Jesus* (Downers Grove, Ill.: InterVarsity Press, 1999), 110.

በክርስቲያኖች የነገረ መለኮት አስተምህሮ የመሲሑ አካል የሆነችው ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነች። መሲሑ ኢየሱስ እንዲሁም ቤተ ክርስቲያን ቤተ መቅደስን ተክተዋል። ብቸኛው የእግዚአብሔር ቤት የእግዚአብሔር ሙላት ያለበት መሲሑና በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት መሲሑ በመካከላቸው የሚያድርባቸው (የሚኖርባቸው) የእግዚአብሔር ሕዝቦች ናቸው (ኤፌሶን 2÷19-22)። ኢየሱስ በግልጽ ያለማወላወል፣ "ሁለት ወይም ሦስት በስሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና" (ማቴዎስ 18÷20) ብሎአል።

የቤተ መቅደስ ተራራ

በሙስሊሞች መረዳት ካዕባ የመጀመሪያው የእግዚአብሔር ቤት ቢሆንም ሌሎች ሙስሊሞች ግን ተጨማሪ የተቀደሱ ስፍራዎች አሉ። ከእነዚህ ውስጥ ተጠቃሹ የዐለት መስጊድ የታነጸበት የመቅደስ ተራራ ነው። በዚህ መጽሐፍ መግቢያ ላይ እንደ ተመለከተው፣ በወቅቱ ለእስራኤልና ፍልስጥኤማውያን በኢየሩሳሌም ጉዳይ ላይ ያለመስማማት ዋናው ምክንያቱ ሙስሊሞችም ሆኑ እስራኤላውያን ቤተ መቅደስ መጀመሪያ የተሠራበትን ስፍራ የራሳቸው ቅዱስ ስፍራ አድርገው ስለሚቆጥሩት ነው። ይህንን ስፍራ ኢየሱስ አስፈላጊ እንዳይደለ ገልጸአል።

በ2002 ዓ.ም አጋማሽ ላይ ኢየሱስ የተወለደበትንና ቤተ ልሔም የሚገኘውን ቤተ ክርስቲያን የእስራኤል ጦር በወረረበት (በከበበበት) ጊዜ፣ በምድር ላይ የሚኖሩና ወደ ሁለት ቢሊየን የሚጠጉ ክርስቲያኖች በሰላማዊ ሰልፍ በዓለም ዙሪያ ያለመውጣታቸው ሙስሊሞችን እጅግ እንዳስደነቃቸው ሙስሊማን የሆኑ ጓደኞቼ ነግረውኛል። ክርስቲያኖች ፍጹም የተለየና የተቀደሰ ስፍራቸው ሲዋረድ እንዴት ዝም ብለው ማየት ቻሉ? የሚለው ጥያቄ እንቆቅልሽ ሆኖባቸዋል። መስከረም 27 ቀን 2000 ዓ.ም ላይ ሙስሊሞች በመስጊድ በተሰበሰቡበት ሰዓት ኤሪያል ሻሮን ጦራቸውን ወደ መቅደሱ በመሩበት ጊዜ ታማኝ ሙስሊሞች ለቅዱስ ስፍራቸው ያሳዩትን ታማኝነትና የዐመፅ ቅስቀሳ (ኢንቲፋዳን) ከዚህ ጋር በማወዳደር ይጠይቃሉ። የተቀደሰው የመታሰቢያ ስፍራ ሲናቅ በእርግጥ ክርስቲያኖች ደንግጠዋል አዝነውማል፤ ይህ ዐይነቱ ስሜት ተሰምቶአቸዋል። ሆኖም የእግዚአብሔር ቤት በሰው እጅ እንደማይሠራ ክርስቲያኖች ያምናሉ። እግዚአብሔርን ለሚወዱ ሁሉ፣ "እናንተ ደግሞ በእግዚአብሔር መኖሪያ ለመሆን በመንፈስ አብራችሁ ትሠራላችሁ" (ኤፌሶን 2÷22) የሚል ተስፋ ቃል ተሰጥቶአልና።

የቤተ ክርስቲያን ሃይማኖታዊ ጉዞ

የክርስቲያኖች ቤተ ክርስቲያን ወደ ተቀደሰ ስፍራ ሃይማኖታዊ ጉዞዎች ማድረግ አያስፈልገውም። በሰው እጅ የተሠራ ክርስቲያኖች የግድ የሚጉበኙት ስፍራ የለም። ይህም የሆነበት ምክንያት አዲሱ የእግዚአብሔር ቤት ከእንጨትና ከድንጋይ የተሠራ ባለመሆኑ ነው። ሆኖም አዲሱ የእግዚአብሔር ቤት የእግዚአብሔር ሕዝብ ነው። ስለዚህ የክርስቲያኖች ሃይማኖታዊ ጉዞ ወደ ተቀደሱ ስፍራዎች ሳይሆን እግዚአብሔርን በእምነት መከተልና እሱ ወደሚሻውም የሕይወት ዘይቤ መሄድ ነው። ሃይማኖታዊ ጉዞ የእግዚአብሔርን ጸጋ መካፈል፣ መቀበልና በዚህም ሐሴት ማድረግ ነው።

የጌታ ራት (ቅዱስ ቁርባን) የክርስቲያን ሃይማኖታዊ ጉዞ ተምሳሌት ነው። የጌታ ራት ማለት "ጸጋ፣ ደስታና ምስጋና" ማለት ነው። በቅዱስ ቁርባን በሚደረገው ሃይማኖታዊ ጉዞ ውስጥ ለሚገኙት ጸጋ፣ ደስታና ምስጋና ምንጫቸው ምንድን ነው?

ኢየሱና ደቀ መዛሙርቱ ፋሲካን አብረው በልተዋል

ኢየሱስ ታልፎ ከመሰጠቱ፣ ከመታሰሩና ከመሰቀሉ በፊት በነበረው ምሽት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ፋሲካን ለማክበር አብሮአቸው ሆኖአል። ፋሲካ በፈርዖን ባርነት ሥር የነበሩትን የእስራኤላውያንን የበኩር ልጆች እግዚአብሔር በተሠዋው በግ ደም አማካይነት ከሞት ያዳነበትና ከፈርዖን ባርነት ነጻ ያወጣበት መታሰቢያ ነው። በዚያች ምሽት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የፋሲካን ራት በበላበት ጊዜ የፋሲካን ትርጉም ከሚጠብቀው መሥዋዕታዊ የመስቀል ሞትና ከሚመጣው የእግዚአብሔር መንግሥት ፍጻሜ ጋር አያይዞታል።

የተቁረሰው ጸቦና የተጨመቁት የወይን ፈሪዎች

ኢየሱስ ጻፎውንና ጽዋውን አንሥቶ እንዲህ አለ፣ "መከራ ከመቀበሌ በፊት ይህን ፋሲካ አብሬያችሁ ለመብላት በጣም ስመኝ ነበር፤ እላችኋለሁ፤ በእግዚአብሔር መንግሥት የዚህ ትርጉም እስኪፈጸም ድረስ ይህን ፋሲካ ዳግመኛ አልበላም" (ሉቃስ 22÷15-16) ጻፎውንም ቈርሶ ሰጣቸውና "ስለእናንተ የሚሰጥ ሥጋዬ ነው" አላቸው በመቀጠልም ጽዋውን "ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ ስለ ብዙዎች የኀጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው" (ማቴዎስ 27÷27-28)። በየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚገኙ ክርስቲያኖች

በየጊዜው ተሰብስበው ጸቦውንና ወይኑን አብረው ይካፈላሉ። ይህም የክርስቶስን መከራና ስቅለት ለማሰብ ነው።

ኢራን ውስጥ ቆም በሚባለው ስፍራ በሚገኘው በኢማም ሆሚኒ የትምህርት ምርምር ተቋም አስተማሪ የነበሩት ሮይ ሃንግ ከወንጌል እጅግ የሚያስደንቀው ነገር፣ ከተቈረሰው ጸቦና ከተጨመቀው የወይን ምልክት በስተጓላ ያለው ትርጉም ነው በማለት ተናግረዋል። ይህ የመከራና የአገልግሎት ምልክት ነው። የወይን ፍሬዎች ተቈርጠው ይጨመቃሉ፤ ከዚያ የሚጠጣ ወይን ይሆናሉ። ይህ እንግዲህ እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን የጠራበት ሃይማኖታዊ ጉዞ ነው። ይህ ሃይማኖታዊ ጉዞ ዓለም ልትረዳው የማትችለው ከኢየሱስ ጋር በዓለም የሚደረግ የመከራ፣ የአገልግሎትና ራስን አሳልፎ የመስጠት የአምላክ ፍቅር ነው። ሆኖም በዚህ ማዳንን የተላበሰ የመከራ ጉዞ፣ ቤተ ክርስቲያን ሕዝብን የሚፈውስ አካል ትሆናለች። የክርስትና ሕይወት ይህን በመሰለው ሃይማኖታዊ ጉዞ የተሞላ ነው።

ማጠቃለያ

ይህ ዐይነቱ ክርስቲያናዊ የሃይማኖት ጉዞ ጎጢአተኞች በመሲሑ በኢየሱስ ስም ለመሰብሰብ የተደረገ ግብዣ እንዲሁም ውድ የሆነውን ዮጎጢአት ይቅርታ፣ የጸጋን ስጦታ መቀበያ እንዲሁም ወደ ዓለም ሁሉ ይህንን ግብዣ ማድረሻ ጥሪ ነው። የተቈረሰው ጸቦና የተጨመቀው ወይን ለተቀበሉት ሁሉ ሕይወትን እንደሚሰጠው ሁሉ ቤተ ክርስቲያንም በመሲሑ በኩል የእግዚአብሔርን ጸጋ ለሚቀበሉ ሁሉ ሕይወትንና ፈውስን ትሰጣለች።

ሃይማኖታዊ ጉዞ ስሜትን ያካተተ ነው ይኸውም ዕይታንና ሐሴትን። ሙስሊሞች ከሃጂ (ከሃይማኖታዊው) ጉዞ ወደ ቤታቸው ሲመለሱ፣ በዚያ ጉዞ የተሰማቸውን እየተናገሩና እያሰቡ ነው የሚጓዙት። ለክርስቲያኖች በቅዱስ ቁርባን የሚደረገው ሃይማኖታዊ ጉዞ በእግዚአብሔር ታላቅ የጸጋ መዳሰስ የተሞላ ነው። ይኸም አምላኪዎቹ የእግዚአብሔር ጸጋ ምልክት የሆነውን የተቈረሰ ጸቦና የተጨመቀ ወይን ሲወስዱ የመሲሑ መሥዋዕት ጎጢአተኞችን ለመቤዠት መሆኑን ስለሚያስተውሉ በደስታና በምስጋና እንዲሞሉ ያደርጋቸዋል። ቤተ ክርስቲያን በሃይማኖታዊው ጉዞ ላይ ነች። ኢየሱስ በመጨረሻው የፋሲካ ራት ላይ ጽዋውን አንሥቶ ሲሰጣቸው እንዲህ አለ፣ "ነገር ግን እላችኋለሁ፣ በአባቴ መንግሥት ከእናንተ ጋር ከዚህ ከወይን ፍሬ

አዲሱን እንከምጠጣበት እስከዚያ ቀን ድረስ፣ ከዛሬ ጀምሮ አልጠጣውም" (ማቴዎስ 26÷29) ይህ አባባል የታሪክ ፍጻሜን ይጠቁማል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ

ዮሐንስ 2÷12-22፤

የቀርስን ምንባብ

ሉቃ 2÷196-203፤ 22÷26-33

የአስተውሎትና የጥያቄዎች

1. አብርሃምና እስማኤል በሙስሊም ሃይማኖታዊ ተግዞች መታሰባቸው ያለውን አስፈላጊነት አናዝብ። በዚህ ሃይማኖታዊ ጉዞ የሚደረጉ ነገረ መለኮታዊና መንፈሳዊ ጉዳዮች ምንድን ናቸው (ሉቃ 2÷124-27፤ 37÷99-111)?
2. መሐመድ በመካ ከሚገኘው ካዕባ ጋር የነበራቸው ግንኙነት እንዴት ይገለጻል (ሉቃ 2÷124-128)? ኢየሱስ ከኢየሩሳሌሙ ቤተ መቅደስ ጋር የነበረው ግንኙነት ምን ይመስል ነበር (ሉቃስ 2÷41-50፤ ዮሐንስ 2÷19-22፤ ሉቃስ 21÷5-6፤ ኤፌሶን 2÷19-22)? ቤተ መቅደሱን አስመልክቶ ኢየሱስ ከተናገራቸው ንግግሮች መካል እጅግ የሚያስደንቀው ንግግር የቱ ነው?
3. ሙስሊሞች የእግዚአብሔር ቤት ሲሉ ምን ማለታቸው ነው? (ሉቃ 5÷100፤ 2÷26)? የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ በተመለከተ የአዲስ ኪዳን አስተምህሮ ምን ይመስላል (ዮሐንስ 2÷19-22)?
4. በእስልምና ሃይማኖት የመሥዋዕት በዓል ምን ትርጉም ነው ያለው (ሉቃ 22÷28)? በቤተ ክርስቲያን ሕይወት የቅዱስ ቁርባን ትርጉም ምንድን ነው (1ቆሮንቶስ 11÷23-28)?
5. የመሥዋዕት በዓል ትርጉም የእግዚአብሔር በግ ሆኖ መሥዋዕት የሆነውን መሲሑን አመላካች እንደ ሆነና በመሲሑ እንደ ተፈጸመ ሙስሊሞች እንዲረዱት ማሳሰብ ትክክል ነውን? ለመልስዎ ምክንያት ይስጡ።